መስከረም

HOOVER
STANFORD LIBRARIES
- 5 1985
INSTITUTION

- የኢትዮጵያ አብዮት የእድገት ደረጃ
- የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም አቀፍ አብዮታዊ ትግል አንፃር
- ተስፋፊነትና ጠባብነት ፡ የሶማሊያ የገዥ መደብ ዓይነተኛ ገፅታ
- ባሕልና ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤው
- የፊውዳሊዝም ገጽታዎች በኢትዮጵያ

DT
371
M469
1974

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 2 ቁጥር 7
ታኅሣሥ 1974

Digitized by Google

Digitized by Google

ET2583pp
9
Meskerem no. 7

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 7
ታኅሣሥ 1974

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገጽ - - - - - - - - - - 3
- የኢትዮጵያ አብዮት የእድገት ደረጃ - - - - - - 6
  ርቤርቶ ቺጋና
- የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም አቀፍ አብዮታዊ ትግል አንፃር - - - 31
  አብዱልሀፌዝ ዮሱፍ ፤
- ተስፋፊነትና ጠባብነት ፤ የሶማሊያ የገዥ መደብ ዓይነተኛ ገፅታ - - 50
  ሰሎሞን ዲባባ ፤
- ባሕልና ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤው - - - - - - - 64
  መሐመድ ሳላህ ፤
- የፊውዳሊዝም ገጽታዎች በኢትዮጵያ - - - - - - 85
  ተሾመ ከበደ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተ ዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ።

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ያለ አብዮታዊ ንድፈ ሃሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም !

Digitized by Google

ቁጥጥርና ሶሻሊዝም

ቁጥጥር ሰፋ ያለ ፅንስ ሀሳብን ያዘለነው ። ስለ ቁጥጥር ሲነሳ በመጀመሪያ ግልፅ ሊሆን የሚገባው ሁለት ገፅታ ያለው ለመሆኑ ነው ። ይኸውም የቁጥጥር ሶሲዩ-ኢኮኖሚያዊ ገፅታና ቴክኒካዊ ገፅታ ነው ። በሶሲዩ ኢኮኖሚያዊ ገፅታው ቁጥጥር የአንድን ማኅበራዊ ሲስተም ሕልው ና ለመንከባከብና ለመጠበቅ የሚረዳ ፤ ማኅበራዊ ሲስተሙ የሚመራበትን መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ተፈፃሚነት ወይም ተግባራዊነት የሚከታተል ፣ የአንድን ስርዓትና በውስጡ ያሉትን ማኅበራዊ ግንኙነቶች ከቁጥጥር አድራጊው ፍላጐት አንፃር ለማዋቀርም ሆነ ለማቆየት የሚረዳ በአጠቃላይ የአንድን ኅብረተሰብ ስልተ ምርት የሚያንፀባርቅና በርሱም የሚወሰን ነው ።

በዚህ ገፅታው የቁጥጥር የመጨረሻ ግብ፣የአንድን ስርዓት ክንዋኔ የሚቻለውን ያህል ከፍተኛ ያረጃ ላይ ለማድረስና በአነስተኛ ጥረትም ሆነ ወጭ የተቻለውን ያህል ከፍተኛ ውጠት ለማስገኘት በሆንም ፣ የዚህ ግብ መሳካት ስርዓቱ ከታሪካዊ የእድገት ሂደት ጋር በመጣጣሙ አኳያ ይወሰናል ።

የቁጥጥር ተግባር እንደየስርዓተ ማኅበሩ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ፤ በስርዓተ ማኅበሩ ሰ ስተሞዋ አደረጃጀት ውስጥ በቁጥጥር አድራጊውና ቁጥጥር በሚደረግበት ክፍል ዓይነት ፣ በቁጥጥሩ ስፋት ፣ አደረጃጀትና በሚጠቀምበት ስልት የተለያየ ቢሆንም ፤ የኅብረተሰብ ሕልውናና የዕድገት መሠረት የሆነው የምርት ተግባር ማኅበራዊ እስከሆነ ድረስ ፣ ቁጥጥር የማንኛውም ኅብረተሰብ ፤ የማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት ወ ስጠዊ ባሕሪና ሁለንተናዊ ተግባር ይሆናል ማለት ነው ።

ቁጥጥር በቴክኒካዊ ገፅታው በሂሳብና በመዝገብ አያያዝ ስልት የሚጠቀም ፤ ፋይናንስና ንብረት ነክ የሆኑ እስታትስቲካዊ መረጃዎችን የሚያጠናቅር፤ እንደ የምርት ግንኙነቱ ዓይነት የመላውን ኢኮኖሚም ሆነ የእያንዳንዱን የምርት ተቋም ውጤትና ውጤቱንም ለማስገኘት የወጣውን ወጭ በገንዘብ መልክ በመተመን ወጭው በገቢው መሸፈኑንና ትርፍ መገኘቱን (ካልተገኘም ያልተገኘበትን) ምክንያት ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘደ ነው ።

በአጠቃላይ ግን እንደማናቸውም ማኅበራዊ ክስተት የቁጥጥር ስርዓት የእያንዳንዱን ኅብረተሰብ ስልተ ምርት የሚያንፀባርቅና በርሱም የሚወሰን ነው ። የምርት ኃይሎች ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ባሉበት ስርዓተ ማኅበር (የጋርዮሽ ፤ የባሪያ ፤ የፊውዳል ስርዓቶች) የሚኖረው የቁጥጥር ስርዓት ቀላል ከመሆኑም በላይ ካለው ያልተወሳሰበ የማኅበራዊ ግንኙነት ጋር የሚጣጣም ነው ።

የምርት ኃይሎች በጣም ከፍተኛ የሆነ የእድገት ደረጃ ላይ በደረሱበት በካፒታለዝምም ሆነ በሶሽያሊስት ስርዓት ያለው ማኅበራዊ ግንኙነትና የሥራ ክፍፍል የበዛና የተወሳሰበ እንደመሆኑ መጠን የቁጥጥሩም ስርዓት የዛኑ ያህል የተወሳሰበ ይሆናል ።

ቁጥጥር በሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ ገፅታው ለአንድ ወይንም ለማናቸውም ማኅበራዊ ሲስተም ሕልውናና እድገት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለማሟላት የታለመ እንደመሆኑ ፤ ቁጥጥር በየትኛውም ስርዓተ ማኅበር ውስጥ የበላይነት ላለው መደብ ጥቅም ማስከበሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። ማኅበራዊ ቁጥጥር እንደየስርዓተ ማኅበሩና በየስርዓተ ማኅበሩ ውስጥ እንዳለው ፖለቲካዊ ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አደረጃጀት የሚወሰን ከመሆኑም በላይ ፤ የተለያዩ ዘርፎችን የሚያጠቃልል፤ ሲስተማዊ አደረጃጀት ያለው ነው ።

የሶሽያሊስት ቁጥጥር በአወቃቀሩም ሆነ በአሠራሩ የልዩ ልዩ ስልቶች ቅንብር እንደመሆኑ መጠን ፤ የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ቁጥጥር መዋቅሮች ፤ የሶሲዮ ኢኮኖ

Digitized by Google

ሚያዊና የቴክኒካዊ ቁጥጥር ስልቶች የተቀናጁበት ሲስተም ነው ። የሶሻያሊስት ቁጥጥር የምርት ማጠናወኛዎችን ማኅበራዊ ባለቤትነት ተመርኮዞ የሚከሰት እንደመሆኑ ፣ የሶሻያሊስት የምርት ግንኙነት ዓይነተኛ የፖለቲካ መግለጫ ነው ።

በሶሻያሊስት ስርዓት የሚዘረጋው የቁጥጥር ሥርዓት የስርዓቱን ማኅበራዊ እንቅስቃሴ የተቀላጠፈ ለማድረግ የሚያስችል ፣ ከዕድገት ነባራዊ ሕጎች ጋር የተጣጣመ ፣ የሶሺያሊስት ይዞታን መሠረት በማድረግ የተዋቀረ ፣ የስርዓቱን መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው ። በሶሻያሊስት ስርዓት የሚዘረጋው የቁጥጥር ስርዓት በሶሺያሊዝም ነባራዊ ሕጎች በመጠቀም ወደ ኮሚዩኒዝም በሚደረገው ሽግግር የኅብረተሰቡን ማቴሪያላዊ ፣ የፋይናንስና የሰው ሀብት የማደራጀትና የማንቀሳቀስ ተግባር የሚያቀላጥፍ ነው ። በመሆኑም በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች የሠራተኛውን መደብ የበላይ ገዥነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ፍቱን የሆነ መደባዊ መሳሪያ ነው ።

የሶሻያሊስታዊ ቁጥጥር ዓላማ የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነት እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ማድረግ በመሆኑ ፣ ኢኮኖሚውንም ሆነ ማኅበራዊ ሕይወትን በእቅድ ለመምራት ከሚደረገው ጥረት ጋር በቀርብ የተቀራኘ ነው ። የሶሻያሊስት ቁጥጥር ሳይንሳዊነት የሚወነወው የቀመለት ዓላማ ከነባራዊ የእድገት ሕጎጋት ጋር የሚጣጣምና በሶሻያሊዝም የኢኮኖሚ ሕጎች ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው ።

የሶሻያሊስት ቁጥጥር (ሕዝባዊ ቁጥጥር) በመሠረቱ ዲሞክራሲያዊ ነው ። ሊሆን የቻለበትም ምክንያት በምርት ማጠናወኛዎች የጋራ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑና በፖለቲካ ገፅታው የመዝአደሩ የበላይ ገዥነት በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥቂት በዝባዦች የበላይነት ተገርስሶ የብዙሀን ሠራተኞች የበላይነት የሠፈነበትና ፣ ቁጥጥሩም በብዙሀን ሠራተኞች ተሳትፎ ተግባራዊ ከንዋኔ የሚያገኝ በመሆኑ ነው ።

የሕዝባዊ ቁጥጥር ስርዓት የሶሻያሊዝምን ዲሞክራሲያዊነት በጉልህ የሚያሳይና ሠራተኛው ሕዝብ በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ነው ።

የሠራተኛው ሕዝብ የንቃተ ኅሊናም ሆነ የባሕል እድገት ደረጃ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ፣ የሶሻያሊስት ይዞታ በሰፈነበት በዳበረ የሶሻያሊዝም የዕድገት ደረጃ ቁጥጥር ለሲስተሙ ሕልውና አስፈላጊ ነው ። የሶሻያሊስቱ የምርት ግንኙነት ባልተጠናከረበት ፣ የሰፊው ሕዝብ የባሕል እድገት ደረጃ ኋላ ቀር በሆነበት የግል ሀብት የአስተሳሰብ ቀሪት ብቻ ሳይሆን የግል የኢኮኖሚ ይዞታ በተንሠራፋበት በሽግግር ወቀት ደግሞ ፣ ለሶሻያሊስቱ ይዞታ በአሸናፊነት መውጣት የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ለመገመት አያስቸግርም ።

በሽግግሩ ወቀት የሶሻያሊስቱ ይዞታና የግል የኢኮኖሚው ይዞታው እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ጎን ለጎን የሚኖሩ በመሆናቸው በነዚህ ተፃራሪ በሆኑ የኢኮኖሚ ይዞታዎች መካከል ውስብስብ የሆነ ትግል ይካሄዳል ።

በሽግግሩ ወቀት በተለይም በመጀመሪያው ጊዜ ተስፋፍቶ የሚገኘው የግል የኢኮኖሚ ይዞታ ለብዙ ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው የግለኝነት የአስተሳሰብ ቀሪት ጋር ተዳብሎ ለምዝበራና ብኩንነት መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ። በመሆኑም የግል የኢኮኖሚ ይዞታውን ለማዳከምና የሶሻያሊስት ይዞታውን ለማጠናከር የሶሻያሊስት ይዞታውን በሶሻያሊስት የቁጥጥር ስርዓት መደገፍ ያስፈልጋል ።

በሽግግሩ ወቀት በሶሻያሊስቱና በግል የኢኮኖሚ ይዞታው መካከል የሚካሄደው ትግል በሶሻያሊስቱ ይዞታ አሸናፊነት እንዲፈፀም ፣ በሶሻያሊስት ይዞታው ውስጥ የሥራ ቀልጥፍና እንዲዳብርና የሥራ ምርታማነት እንዲጨምር ፣ ለግንባታ አስፈላጊ የሆነው ክምችት እንዳይባክን አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ግደታ ነው ። ለሶሻያሊስት

Digitized by Google

ስርዓት ግንባታ የሚደረገው ትግል ለግንባታው ዋስትና ከሚሰጠው የሕዝባዊ ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ተገንጥሎ ሊታይ አይችልም ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሕዝባዊ ቁጥጥር ዓላማ የሶሽያሊስቱን የምርት ግንኙነት ለማዳበርና ለማጠናከር ሲሆን ፤ በዚህም ሂደት ውስጥ የመደብ ትግሉን በማፋፋም የሠራተኛውን ሕዝብ የበላይነት ለማስፈን ነው ።

በኢትዮጵያም ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም በአሁኑ ወቅት ፀረ አብዮት ኃይሎች የሶሽያሊስቱ የምርት ግንኙነት እንዳይጠናከር ምዝበራንና ብኩንነትን ማስፋፋት ዓይነተኛ የትግል መሣሪያቸው አድርገው ይዘውታል ። የግል የኢኮኖሚ ይዞታው መናርና የግለኝነት የአስተሳሰብ ቀሪት ከቀድሞው ስርዓት ጋር አብር ያለመደምሰሱም ለዚህ ለፀረ አብዮት ድርጊታቸው መስፋፋት አመቺ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ መሠረት አስገኝተላቸዋል ። ይሁንና በቅርቡ ሊዘረጋ የተወጠነው የሠራተኞች ቁጥጥር ምዝበራን ብኩንነትን ጉቦን ወዘተ --- የመሳሰሉትን ድርጊቶች በተናጠል ለመውሰድ የሚዋጋ ብቻ ሳይሆን ለነ ዚህ አድሀሪ ድርጊቶች ኢኮኖሚያዊ መሠረት የሆነውን የግል ይዞታና ከዚህም የሚ መነጨውን የግለኝነት አመለካከትንም ጭምር የሚዋጋ ለመሆኑ ፤ ሶሽያሊዝምን ለመገን ባት በምናደርገው ትግል ዓይነተኛ የፖለቲካ መሳሪያችን ነው ። በአንፃሩም በግንባታ ጥረታችን ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለማስወገድ የሚቻለው ሊዘረጋ ለታቀደው የቁጥጥር ስርዓት ኢሠፓአኮ ጠንካራ ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አመራር ለመስጠት ሲችል ብቻ ነው ።

የሠራተኞች ቁጥጥር ሠራተኛው ሕዝብ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በማኅበራዊ ጉዳይ ፤ በመንግሥት አስተዳደር ወዘተ --- ውስጥ በመሳተፍ እራስን በራስ የማስተዳደር ልምድ የሚቀስምበት መድረክ ነው ። የሠራተኛውን ቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋት ለወጣው አዋጅ ተግባራዊነት የሚደረገው ትግል ፤ የአብዮታችንን በአሸናፊነት ከግቡ መድረስ የሚወሰን ነው ። ለተግባራዊነቱ የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ ማሳደግ ፤ አንድ ወጥ የሚሳብና የመዝገብ አያያዝ ስልትን በመቀየስ መንግሥታዊ ቁጥጥርን በይበልጥ ማጠናከርና ማቀላጠፍ ፤ ለመንግሥታዊና ሕዝባዊ የቁጥጥር አካሎች ኢሠፓአኮ የሚሰጠውን ርዕዮተ ዓለማዊና ድርጅታዊ አመራር ማጠናከር ያስፈልጋል ። በመሆኑም የኢሠፓአኮ አባላት ለቁጥጥሩ ተግባር መሳካት በያሉበት ሁሉ የግንባር ቀደም ሚና መጫወት አማራጭ የማይገኝለት ግደታ ነው ። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ የሠራተኛ መደብና ሠርቶ አደር ሕዝቦች በሙላ በቅርቡ አብዮታዊ መንግሥት የሠራተኛውን የቁጥጥር ስርዓትን ለመዘ ርጋት ያወጣውን አዋጅ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ እስከመጨረሻው ድረስ መታገል ይና ርባቸዋል ።

የኢትዮጵያ አብዮት የዕድገት ደረጃ

ሮቤርቶ ቺጋና

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና ዓለምአቀፍ ባህሪው ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ

Digitized by Google

አጠቃላይ የዕድገት መመዘኛዎች

የዕድገት ፅንሰ ሀሳብ

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ዕድገት ከቀላልና ዝቅተኛ ወደ ውስብስብና ከፍተኛ ደረጃ የሚሄድ ፤ የማንኛውም ክስተት እንቅስቃሴ እንደሆነ ያስተምራል ። ሕይወት ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው የተፈጥሮ ክፍሎች እንዲሁም ኅብረተሰብና የማወቅ ተግባር በዚሁ የእንቅስቃሴ ወይም የዕድገት ሕግ የሚገዙ ክስተቶች ናቸው ። ዕድገት አጠቃላይ በሆኑ ዲያሌክቲካዊ ሕጎች የሚገዛ ሲሆን እያንዳንዱ የተለየ ክስተት ደግሞ የተለየ የራሱ ተጨማሪ የዕድገት ሕግ ይኖረዋል ።

የአንድ ክስተት የዕድገት መንስዔ በዚሁ ክስተት ውስጥ ያለው ቅራኔ ነው ። ቅራኔ የምንለው ደግሞ በተባለው ክስተት ውስጥ ባሉት አሮጌና አዲስ አድሃሪና ተራማጅ ኃይሎችና አዝማሚያዎች መሃል ያለው ትግል ነው ። በሁለቱ መሃል ማለትም በሟቹ ወይም በአሮጌው በአንድ በኩል በታዳጊውና በአዲሱ ኃይሎችና አዝማሚያዎች በሌላ በኩል የሚኖረው ትግል የአንድ ክስተት ሕልውናና የዕድገት መንስዔ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በነዚህ ሁለት ወገኖች መሃል የሚኖረው የትግል ሁኔታ የክስተቱን የዕድገት ደረጃም ያመለክታል ።

የኅብረተሰብን ወይም የሰውን ልጅ ታሪክ ስንመለከት ፤ እንደተቀረው እንደማንኛውም ክስተት ሁሉ ፤ ከቀላሉ ወደ ውስብስብ ፤ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ደረጃ እንቅስቃሴ ወይም ዕድገት እንዳለው እንገነዘባለን ። የዚህም ዕድገት መንስዔ ወይም አንቀሳቃሽ ኃይል በተለያዩት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅራኔ ነው ። በአንድ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶቹ መካከል ያለው ቅራኔ የሚገልጸው ደግሞ በመደብ ትግል መልክ ይሆናል ። ስለዚህም ነው እስካሁን ድረስ የሰው ልጅ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው የሚባለው ።

ማርክሳዊ የታሪክ ፍልስፍናና የዕድገት ፅንሰ ሃሳብ መነሻ በኅብረተሰብ ታሪክ የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች በባሪያ አሳዳሪ ፤ በፊውዳል . . . ወዘተ ሹም ሽር ሲሆን ፤ ይህም ሂደት በራሱ የቅራኔ ሕግጋት እንደሚፈጽምና እያንዳንዱም ደረጃ (ሥርዓት) ከሌላው ወይም ከበፊቱ የበለጠ ውስብስብና ከፍተኛ መሆኑን ይገልጻል ። በመሆኑም በአጠቃላይ ይኸ የሥርዓተ ማኅበሮች ሹም ሽር የኅብረተሰብን የዕድገት ደረጃ የሚጠቁም መለኪያ ተደርጐ ይወሰዳል ። በዚህም መሠረት ካፒታሊዝም ከፊውዳሊዝም ፤ ሶሻሊዝም ከካፒታሊዝም የተሻለና ከፍተኛ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ይሁንና ይህን የመሰለው የኅብረተሰብ ታሪክ አመለካከትና የዕድገት መለኪያ በቡርዧውና በወዛደሩ ምሁራን መሃል ያለ ትልቅ የውዝግብ ነጥብ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ። በኢትዮጵያችንም ቢሆን ነባሩን ሰለሞናዊ ጥበብ የሚሸር ነው ። ዛሬ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ «ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም» የሚለውን «የጠቢብ» አነጋገር ተራና ከአድሃሪ አመለካከት ያልተላቀቀ አባባል እንደሆነ ይገነዘባህ ። አዲስ ነገር ፤ ለውጥና ዕድገት እን ለ ከተረዳ ሰንብቷልና ። ይሁንና ረቂቅ የሆነው አድሃሪ የቡርዧ አቀራረብ ለዕድገት የሚሰጠው ፍቺና መለኪያ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። የኅብረተሰብን የዕድገት ሂደት በሚመለከት ያሉትን ሁለት ዓይነት አመለካከቶችና እነዚህም አመለካከቶች በትግላችን ሂደት ውስጥ የሚኖራቸውን ቀጥተኛ ግንዛቤ በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ ወደፊት እንመለከታቸዋለን ። በመጀመሪያ ግን የማርክሳዊ የታሪክ ፍልስፍና ይህን ሁኔታ አስመልክቶ ምን እንደሚል እንመለከታለን ።

የኅብረተሰብ ዕድገት መለኪያ

አጠቃላይ የኅብረተሰብ ታሪክ ዕድገት ማሳየቱ ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የተደረገ እንቅስቃሴ መሆኑ ይሄም በሥርዓተ ማኅበሮች መቀያየር እንደሚንፀባረቅ ቀደም ሲል ተጠቅሷል ። ይሁንና አንድ

Digitized by Google

ኅብረተሰብ ወይም ሥርዓተ ማኅበር ከሌላው ይሻላል ወይም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ነው ስንል መለኪያችን ምንድነው ?።

ሌኒን የኅብረተሰብ ዕድገት «ከፍተኛው መለኪያ የምርት ኃይሎች ዕድገት» [1] እንደሆነ ያስገነዝባል ። ይህም ማለት በመሠረቱ አንድ ኅብረተሰብ ከሌላው የላቀ መሆኑ የሚረጋገጠው በምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ነው ። አንድ ሥርዓተ ማኅበር ቀደም ሲል ከነበረው የተሻለ መሆኑ ፤ ለምሳሌ ካፒታሊዝም ከፊውዳሊዝም የተሻለ ሥርዓተ ማኅበር ነው የምንልበት መሠረታዊ ምክንያት ከፊውዳሊዝም ጋር ሲነጻጸር በካፒታሊዝም የምርት ኃይሎች ዕድገት እጅግ ከፍተኛና የተፋጠነ በመሆኑ ነው ። በሌላ በኩል አንዳንድ የቡርዧ ምሁራን ለምሳሌ እንደ ዊሊያም ሮስቶ የመሰሉት የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ብቸኛ መለኪያው የምርት ኃይሎች በተለይም ቴክኖሎጂ እንደሆነ በማቅረብ የተለያዩ ሕዝቦችንና አገሮችን በእነዚህ ዕድገት ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ ። በዚህም መሠረት የአሜሪካን ኅብረተሰብ (ዩ. ኤስ. ኤ) የዓለም ሕዝቦች የሥልጣኔ ቁንጮ አድርገው ይወስዳሉ ።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ጉዳይ ሌኒን የምርት ኃይሎች ከፍተኛው የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ መለኪያ ነው ሲል የምርት ኃይሎች ከምርት ግንኙነቶች ዕድገት ጋር ያላቸውን ወሳኝ ሚናና እንዲሁም ዝምድና በመገንዘብ ነው እንጂ የምርት ኃይሎችን ለብቻቸው በመውሰድ አይደለም ። ባጭሩ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በማጤን ነው ። አለበለዚያማ ቡርዧው ከሚያቀርበው መለኪያ ብዙም የተለየ አይሆንም ነበር ።

የምርት ኃይሎችን የዕድገት ደረጃ አብሮ ካለው የምርት ግንኙነት ውጭ በአጠቃላይም ከሥርዓተ ማኅበሩ ውጭ በመመልከት እንደ ኅብረተሰብ ዕድገት ብቸኛ መለኪያ አድርገን ከወሰድን በእርግጥም የአሜሪካን ካፒታሊዝም (ኅብረተሰብ) በአሁኑ ጊዜ የሥልጣኔ ቁንጮ ወይም ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ላይ ሊሆን ይችላል ። እንደሚታወቀው ሁሉ የብዙ ሶሻሊስት አገሮች የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ከአሜሪካና ከአንዳንድ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ያነሰ ነው ። ይህ መሆኑ ግን የሶሻሊስት አገሮች ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ባነሰ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው አያሰኝም ።

ባንድ ታሪካዊ ወቅት አንድ አዲስ ሥርዓተ ማኅበር ለምሳሌ ካፒታሊዝም ፤ አሮጌውን ሥርዓተ ማኅበር ፊውዳሊዝምን በሚተካበት ማግስት የተሻለ የምርት ኃይሎች ዕድገት ሊይኖረው ይችላል ። እንዲያውም ይህን የመሰለ የሥርዓተ ማኅበር ለውጥ በሚከናወንበት በአብዮት ወቅት አዲሱ ሥርዓት ምንም እንኳ የተሻለ የምርት ግንኙነቶችን ይዞ የመጣ ቢሆንም ለተወሰነ ጊዜ አብዮቱ በሚያስከትለው የርስ በርስና ብሔራዊ ጦርነት የተነሳ የምርት ኃይሎች ድቀትም ሊደርስ ይችላል ። ይህ በተደጋጋሚ በታሪክ የተረጋገጠ ነው ።

በዕድገት ጐዳና ጊዜያዊ ችግሮች

አብዮታቸውን ባካሄዱ ማግሥት ወይም ለጥቂት ዓመታት በኋላ በእንግሊዝ ፤ በፈረንሳይና በሩሲያ የታየውን አንዳንድ ሁኔታ እንመልከት ። «በእንግሊዝ አገር የ1648 አዝመራ በጣም ቀነሰ ። የእህል ዋጋ ናረ ፤ በነበረውም የፖለቲካ ሁኔታ ያገሪቱ ንግድ ፍጹም ወደቀ ። በፈረንሣይ አገር እ. ኤ. አ. በሚያዝያ 13 ቀን 1793 በኋላ «ማለትም ንጉሠ ነገሥቱ ሉዊ 16 ኛው ከተገደለ በኋላ» ያገሪቷ ገንዘብ ዋጋ 30 በመቶ ድረስ ቀነሰ ። በዚህም ገንዘብ ዋጋ መውረድ ምክንያት ዕምነትየ በመጥፋቱ ብዙ ካፒታል ወደ ውጭ አገር ጐረፈ ። ፍርሐት ሰፈነ ፤ የዋጋ መናርም ተከተለ [2] ። በሩሲያም ታላቁ የኦክቶበር ሶሻሊስት አብዮት ከተካሄደ በኋላ የነበረው የኢኮኖሚ ሁኔታ አስከፊ እንደነበር ይታወቃል ።

ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጀምሮ የርስ በርስ ጦርነቱ እስካበቃበት እስከ 1920 በነበረው ጊዜ ውስጥ በሩሲያ ሕዝብና ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ። ታሪክ ይህንን ሳይመዘግበው አላለፈም ። «አገሪቱ ጠቅላላ ውድቀት ላይ ትገኝ ነበር ። በጦርነቶቹ የሞተው ሰው ቁጥር ከሃያ ሚሊዮን ይበልጥ ነበር ። በዚሁ ጊዜ ማብቂያ ላይ በ1920 በሩሲያ የከባድ ኢንዱስትሪ ምርት መጠን በአገሪቱ በ1913 ይመረት ከነበረው አንድ ሰባተኛውን ያህል ነበር ። የጥጥ ጨርቃ ጨርቅ ምርት

Digitized by Google

ደግሞ በ1850 አካባቢ የነበረውን የግ.
ያህል ሲሆን የብረታ ብረት ምርት
ደግሞ አገሪቱ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት
በምታመርተው መጠን ወደቀ ። ጠቅላላ
መገናኛም ወድሞ ነበር ። የእርሻ ምርት
ደግሞ ቀድሞ ከነበረው ማለትም በ1913
ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ከነበረው
ግማሽ ያህል ነበር»[3] ።

የተሻለ ሥርዓተ ማኅበር ለማምጣት
በማደረገው ጥረት በአብዮቱ ማግሥት
ይህን የመሰለ የከፋ ሁኔታ መከተሉ የታ
ሪክ ሐቅ ነው ፤ ይነስ ይብዛ ደረጃው ይለያይ
እንጂ እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ያለ ነገር
ነው ።

በጊዜው ለሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት
ቀና አመለካከት የነበረው ስመጥሩው የእ
ንግሊዝ ታሪክ ፀሐፊ ኤች. ጂ. ዌልስ
በ1920 በሩሲያ ተገኝቶ ችግሩን ከተ
መለከተ በኋላ ለዚህ ጥፋት ማን ተጠ
ያቂ እንደሆነ ምስክርነቱን ሰጥቷል ። ይኸ
ውም ፤ «ለዚህ ሁሉ ከፍተኛ ጥፋት ተጠያ
ቂው ማነው ሊባል ነው ? የቦልሸቪኮች
አስተዳደር ! አይመስለኝም ። ለዚህ ሁሉ
ስቃይ መንስዔ ሆነ ለመስፋፋቱ በሩሲያ
የቦልሸቪክ መንግሥት ተጠያቂ አይደለም።
ተጠያቂው የአውሮፓ ኢምፔሪያሊዝም
ነው»[4] በማለት ጽፋል ።

እነዚህ ታሪካዊ ሁኔታዎች በተባሉት
አገሮች በአብዮት አማካኝነት የሥርዓተ
ማኅበር ለውጥ በሚከናወንበት ጊዜ ለጥ
ቂት ጊዜም ቢሆን የሚከተለውን የኤኮኖሚ
መዛባትና የምርት ኃይሎች አንጻራዊ ድቀት
የሚገልጹ የቅርብ ጊዜ የታሪክ መረጃዎች
ናቸው ። ነገር ግን ይበልጥ ወደኋላ መለስ
ብለን በአውሮፓ የፊውዳሊዝምን አመጣጥ
ብንመለከት ተመሳሳይ ሁኔታ እንደነበር
ይታያል ። ምንም እንኳ በመሠረቱ የፊው
ዳል ኅብረተሰብ ከባሪያ አሳዳሪው የተሻለ
መሆኑ ቢታወቅም በ5ኛው ክፍለ ዘመን
ፊውዳሊዝም በአውሮፓ ሲመጣ ለጥቂት
ዓመታት በምርት ኃይሎች ዕድገት ረገድ
የታየው ድቀት አስከፊ ነበር ። የሮም ግዛት
(Empire St te) በወራሪ የሰሜን
ጀርመን ጐሣዎች መያዝ በአውሮፓ ታሪክ
ከባሪያ አሳዳሪ ኅብረተሰብ ወደ ፊውዳሊዝም
የተደረገውን ሽግግር ያመለክታል ። የሮም
የመጨረሻው ንጉሠ ነገሥት እ. ኤ. አ.
በ476 ከወረደ በኋላ ለብዙ ጊዜ የቆየ ችግ
ርና የምርት ኃይሎች ድቀት ታይቷል ።
«በሮም ግዛት ውድቀት መጀመሪያ ላይ
ከፍተኛ የባህል መዳከም ታይቷል ። የዘ
መኑ ኪነትና ሳይንስ ከፍተኛ ግኝቶች በአ
ብዛኛው ወደሙ»[5] ። በሌላም በኩል በሮም
ግዛት ዶብረው የነበሩት «ዕደ ጥበብና ንግድ
አሽቆለቆሉ ፤ በከተሞች መሃል የነበሩ ግን
ኙነቶችም ተቋረጡ ።»[6]

ታዲያ ይህን የመሰለው የፊውዳሊዝም
አጀማመርና ችግር ፊውዳሊዝም ከሻረው
ሥርዓት ማለትም ከባሪያ አሳዳሪው ኅብረተ
ሰብ አንጻር ሲታይ የበላይነቱን አያሳጣ
ውም ። ቁም ነገሩ ጊዜያዊ ችግሩ ሳይሆን
የምርት ኃይሎች የተሻለና የተፋጠነ ዕድ
ገት ለማስገኘት የፊውዳል ሥርዓት የተ
ሻለ እንደሆነ ታሪክን መመርመር ነው ።

እንግዲህ ወደዋናው ነጥባችን ለመመ
ለስ፣የኅብረተሰብ ዕድገት መለኪያው የም
ርት ኃይል እድገት ደረጃ ሲሆን ፤ ይህን
ሁኔታ ካለው የምርት ግንኙነትና አጠቃላይ
ሥርዓተ ማኅበር ጋር አያይዘን መመልከት
ይኖርብናል ። ስለሆነም በሥርዓተ ማኅበር
ሹም ሽር ማግሥት የምርት ኃይሎች የተ
ለየ ዕድገት አይኖራቸውምና አዲሱ የምርት
ግንኙነት ከበፊቱ አይሻልም ወይም የኅብ
ረተሰብን ዕድገት አያመለክትም ለማለት
አይቻልም ። አዲሱን ሥርዓተ ማኅበርና
የምርት ግንኙነቱን እንደ ዕድገት ጠቋሚ
አድርገን የምንወስዳቸው ከዘላቂው አንጻር
ሲታይ ከቀድሞው የምርት ግንኙነት የተ
ሻለና ለፈጣን የምርት ኃይሎች ዕድገት ዋስ
ትና በመሆናቸው ነው ። ስለዚህም ነው ዛሬ
አንዳንድ የሶሻሊስት አገሮች ምንም እንኳ
ለጊዜው ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ያነሰ
የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ያላቸው
ቢሆንም ፤ በኅብረተሰብ ዕድገት አኳያ
ከፍተኛውንና የላቀውን የዕድገት ደረጃ
ይወክላሉ የምንለው ። አመለካከታችን
ዲያሌክቲካዊ በመሆኑ ወይም ነገሮችን
እንዳሉና በእንቅስቃሴያቸውም የምናይ በ
መሆናችን የሶሻሊስት ሥርዓትና የምርት
ግንኙነት በዘላቂው ሲታይ ካፒታሊዝም
ከሚኖረው የምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ
የተሻለ ዕድገት እንደሚያስገኝ እስካሁን
የታየው የኤኮኖሚ (የምርት ኃይሎች) ዕድ

ገት ራሱ የሚያስረዳ ነው ። ይህንንም በይ
በልጥ ወደፊት የሶቪዬት ኅብረትን ልምድ
በጥቂቱ ስንመለከት የምንረዳው ይሆናል ።

በሥርዓተ ማኅበርና የምርት ግንኙ ነቶች መቀየር የሚከተለው የምርት ኃይሎች ዕድገት

ከሁሉ በፊት ማርክሲዝም ሌኒኒዝም
ስለማኅበራዊ አብዮትና ውጤቱ የሚያስተ
ምረንን ማስታወስ ይበጃል ። ከአንድ ሥር
ዓተ ማኅበር ወደ ሌላው የሚደረገው የኅብ
ረተሰብ እንቅስቃሴ በተወሰኑ ሕግጋት
የሚገዛ ነው ። ይህን የመሰለው ለውጥና
የሥርዓተ ማኅበር ሹም ሽር አብዮት ይባ
ላል ። አንድ አብዮት «ያረጀውን ሥርዓት
ከሥረ መሠረቱ የሚቀይር ለውጥ»[7] «መሆ
ኑንና ለዘመናት ቀስ በቀስ ሲከማቹ የቆዩት
ቅራኔዎች ሁሉ የሚፈቱበት»[8] የኅብረተሰብ
የዕድገት ደረጃ እንደ ሆነ ሌኒን ያስተም
ራል ።

ለአንድ አብዮት መምጣት ምክንያት
ከሚሆኑት ቅራኔዎች ሁሉ ባሮጌው የም
ርት ግንኙነቱና በታዳጊው የምርት ኃይል
መሃል ያለው ቅራኔ ከፍተኛውን ደረጃ ይይ
ዛል ። እንደሚታወቀው ሁሉ በመደብ በተ
ከፋፈለ ኅብረተሰብ ይኸው መልክ ይከሰ
ታል ። የተወሰኑ መደቦች ያረጀውን ሥር
ዓተ ማኅበርና መሠረቱን ፤ ማለትም የም
ርት ግንኙነቱን ለማቆየት ሲታገሉ አብዮ
ታዊ መደቦች ደግሞ ይህንኑ ለመሻር ይነ
ሳሉ ። የዚህም ፍልሚያ ማከተሚያ በነ
ዚህ መደቦች መሀል የሚኖረው የፖለቲካ
ትግልና የርስ በርስ ጦርነት ይሆናል ።
የአንድ ማኅበራዊ አብዮትም የመጀመሪያ
ደረጃ ፖለቲካዊ ባህርይ አብዮታዊ መደ
ቦች የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝና ለማ
ቆዬት የሚያደርጉት ጥረት የአድሃሪ መደ
ቦችን የኢኮኖሚ ኃይል ከማንኰታኰቱ
ተግባር መቅደም ነው ።

የመንግሥት ሥልጣንም ከአንዱ መደብ
ወደ ሌላው እጅ ከገባ በኋላ የሚከተለው
ቀጥተኛ ለውጥ ወይም ውጤት የንብረት
ይዞታውንና የምርት ግንኙነቱን መቀየር
ነው ። ከሥልጣን የተወገደውም መደብ
(አድሃሪው) ሕልውና የሚሻረው የምርት
ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ሲቀየር በመ
ሆኑ በአብዮቱ ማግሥት የሚደረገው የን
ብረት ይዞታና የምርት ግንኙነት ለውጥ
ሕልውናውን ያሳጣልዋ ።

እንግዲህ በመሠረቱ የሥርዓተ ማኅበር
ለውጥ ወይም ማኅበራዊ አብዮት የሚመ
ጣው አሮጌው የምርት ግንኙነት የምርት
ኃይሎችን ዕድገት እንዳይገታ ሲሆን የዚ
ህም ያረጀ የምርት ግንኙነት በአዲስ መለ
ወጥ የምርት ኃይሎችን ዕድገት እንደሚያስ
ገኝ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ። የታሪክ ድጋፍ
የሚያስፈልገውም ይኸው ነው ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በእን
ግሊዝ ፤ በፈረንሳይና በሩሲያ አብዮቶች
ወይም የሥርዓተ ማኅበር ለውጥ ከተካሄደ
በኋላ ለጥቂት ጊዜ የነበረው የምርት ኃይ
ሎች ሁኔታ የከፋ ነበር ። ይሁንና ከዘለቄ
ታው አንፃር ሲታይ የሥርዓተ ማኅበርና
የምርት ግንኙነት ለውጥ የምርት ኃይሎችን
ዕድገት ማስገኘቱን ከብዙ በጥቂቱ በነዚሁ
አገሮች ታሪክ መረዳት ይቻላል ።

ከእንግሊዝና ፈረንሣይ የቡርዧ አብዮቶች በኋላ የታየው የምርት ኃይሎች ዕድገት

እ. ኤ. አ. 1640ዎች ውስጥ የእንግሊዝ
ቡርዧ «ገናና አብዮቱን» ካካሄደ በኋላ
በአገሪቱ የታየው ለውጥና ዕድገት ከፍተኛ
ነው ። እንግሊዝ በ15ኛው ክፍለ ዘመን
ከ$3\frac{1}{2}$ — 4 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያልነበ
ራት ትንሽ አገር የአውሮፓ ኃያል መንግ
ሥት ሆነች ። ስኮትላንድንም ሆነ አየርላን
ድን በቅጡ ይዛ ያልነበረችውን ያህል አሁን
ጠቅላላ የእንግሊዝ ደሴቶችን ፤ ሰሜን አሜ
ሪካንና መላ ህንድን ማስተዳደር ጀመረች»።[9]

እንግሊዝ ይህን ያህል ግዛት በቅኝ ገዥ
ነት ለመያዝ ያበቃት ወታደራዊ ኃይል ማቴ
ሪያላዊ መሠረቱ በጊዜው የታየው የምርት
ኃይሎች ዕድገት ነው ። «የእንግሊዝ የቡ
ርዧ አብዮት ካስከተላቸው ነገሮች አንዱ
ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት ነው። በሱፍና ፤
በጥጥ ምርት ፤ በድንጋይ ከሰል በማዕድን
እንዲሁም በብረት ማቅለጥ ተግባር ፈጣን
ዕድገት ታየ»[10] ። ባዚህ ረገድ የታየው ከፍ
ተኛ ዕድገት ጥበብ ወይም ከእጅ ሥራ ወደ
ማሽን ሥራ የተደረገውን ከፍተኛ የቴክኖ
ሎጂ ዕድገትና የኢንዱስትሪ አብዮትን አስ

Digitized by Google

ከተለ ። የጨርቃ ጨርቅ ሥራ በሙሉ በማሽን መሥራት ጀመረ ። የዚህ አጠቃላይ የምርት ኃይሎች ዕድገት ነው እንግሊዝን በተቀናቃኞቿ አገሮች ፣ በሆላንድ ፣ በስፓኝና በፈረንሳይ ላይ በየጊዜው ድል ሊያስገኛት የበቃው ።

በሌላ በኩል የፈረንሳይ የቡርዧ አብዮት በ1789 ከተካሄደ በኋላ ለጥቂት ጊዜ የነበረው ችግር አብቅቶ የታየው የምርት ኃይሎች ዕድገት እንዲሁ ከፍተኛ ነበር ። የፈረንሳይ ቡርዧ በአገሬው ፊውዳልና በተቀሩት የአውሮፓ ፊውዳል መደቦች ላይ ያሳየው የበላይነት በናፖሊዮን ገናናነት ሊታይ ይችላል ። የፈረንሳይ ቡርዧ በናፖሊዮን መሪነት በተከታታይ አያሌ ድሎችን በመቀዳጀት ጉረቤት የአውሮፓ አገሮችን ሳይቀር ይዟል ። አሁንም ይህ የፈረንሳይ ቡርዧ በየጦር ሜዳው ያገኘው ድል በፈረንሳይ በወቅቱ የነበረው የምርት ኃይሎች ዕድገት ውጤት እንደሆነ የማይዘነጋ ነው ።

የፈረንሳይ ቡርዧ የፊውዳሉን ሥርዓተ ማኅበር ለማፈራረስ በወሰደው የተለያዩ የንብረት ይዞታ ለውጦችና አጠቃላይ የኤኮኖሚ ፖሊሲ የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት ሊገኝ ችሏል ። የፈረንሳይ ገበሬ የመሬቱ ባለቤት በመሆኑና በመላው አገሪቱ ንግድ ከመቼውም የበለጠ በመቀላጠፉ የምርት ዝውውር ከፍተኛ ዕድገት አሳየ ። ይህም ማለት የገበያ ዋስትና ያገኘው ቡርዧ በምርት ዘርፍ የሚያወለውን ካፒታል ሳይፈራ ሳይቸገር በመጨመር ተፈላጊውን የምርት ኃይሎች ዕድገት ሊያስገኝ ችሏል ። በጦርነትም የሚያዙት አገሮች አንድ ተጨማሪ የሚያጓጓ ገበያ ሲከፍት በሌላ በኩል ደግሞ የሚከናወነው ገደብ የለሽ የጥሬ ዕቃዎችና ጠቅላላ ሃብት ዘረፋ ለካፒታል ክምችት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ የተወሰነ ታሪካዊ ልምድ ሌላ ቡርዧውና ካፒታሊዝም ለኅብረተሰብ ዕድገት ማለትም ለምርት ኃይሎች ዕድገት ያደረጉትን አስተዋፅኦ ማርክስ ባለው ለማጠቃለል ይቻላል ። ማርክስ የካፒታሊዝምንና የቡርዧውን አስተዋጽኦ ሲገልጽ እንዲህ ሲል ጽፏል ። «የቡርዧው መደብ በየወቅቱ መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት ታላቅ ተጋድሎ አድርጐ እንደነበር ከታሪክ ለመገንዘብ ይቻላል ። የሰው ልጅ ታታሪነት ምን ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ይህ መደብ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አሳወቀ ። ከግብጻዊያን ፒራሚዶች ፣ ከሮማውያን ሰው ሰራሽ የውሃ ማከፋፈያዎችና ከጥንት የጀርመን ቤተክርስቲያኖች በበለጠ እንደተአምር የሚቆጠሩ ተአምሮችን አከናወነ ። . . . በተፋጠነ አኳኋን በተሻሻሉ የምርት መሣሪያዎች በጣም ዘመናዊና ቀልጣፋ በሆነው የመገናኛ ዘዴ አማካኝነት ፣ የቡርዧው መደብ ኅብረተሰቦችን ሁሉ ፣ በጣም ኋላቀር የሆኑትን ጭምር ጉትቶ ወደ ሥልጣኔ አስገብቷቸዋል ።»[11]

ከሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት በኋላ የታየው ዕድገት

ቀደም ሲል የሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት ከተካሄደ በኋላ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን የነበረውን አስከፊ የኤኮኖሚ ሁኔታ አንጻራዊ የሆነ የምርት ኃይሎች ድቀት መኖሩ በመሠረቱ በሩሲያ ኅብረተሰብ ዕድገት አለመኖሩን እንደማያመለክትና የተለወጠውም የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ራሱ ዕድገት መሆኑ ለዘለቄታው በሚገኘው የምርት ኃይሎች ዕድገት እንደሚያረጋግጥ ተነግሯል ። አሁንም ይህ በእርግጥ ስለመሆኑ የሶቪዬት ኅብረትን የሶሻሊስት ግንባታ ልምድ ባጭሩም ቢሆን መመልከት አስፈላጊ ነው ።

ከካፒታሊዝምና ከኮሚኒዝም ወይም ከዚሁ ሥርዓተ ማኅበር የመጀመሪያ ደረጃ ከሶሻሊዝም የትኛው ከፍተኛ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃን እንደሚወክል የሚደረገው ክርክር አንዱ መልክ በሁለቱ ሥርዓቶች ግንባር ቀደም አገሮች የሆኑትን የአሜሪካንና (ዩ.ኤስ.ኤ.) የሶቭዬት ኅብረትን የምርት ኃይሎች ዕድገት በማወዳደር የሚደረግ ነው ። ኢምፔሪያሊዝምና ቅጥረኞቹ እንዲሁም ከሃዲዎች በተደጋጋሚ ሊያሳምኑን የሚፈልጉት አሜሪካ የላቀ የምርት ኃይሎች ያለበት ኅብረተሰብ በመሆኗ ካፒታሊዝም ከሶሻሊዝም የተሻለና ከፍተኛውን የሰው ልጅ ዕድገት ደረጃ እንደሚወክል ነው ።

ይሁንና ይህ ክርክር ባዶ መሆኑን ለማሳየት አያስቸግርም ። ከሁሉ በፊት የሶሻሊስት መንግሥትና ኅብረተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተባት ሩሲያ ምን ዕድገት ደረጃ ላይ ትገኝ እንደነበር ማጤን ያስፈልጋል ።

Digitized by Google

በኋላም የሶሻሊዝምንና የካፒታሊዝምን ዕድሜና በዚህ ጊዜ በሁለቱም ሥርዓቶች የታየውን የምርት ኃይሎች የዕድገት ፍጥነት በማገናዘብ የትኛው የተሻለ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል ።

በሰው ልጅ ታሪክ የካፒታሊዝምን መስፈን ከመጀመሪያው የሆላንድ የቡርዧ አብዮት አንስተን መቁጠር ብንጀምር እነሆ አራት መቶ ዓመቱን ይዟል ። ሶሻሊዝም ደግሞ ገና ስድሳ አራት ዓመቱ ነው ። ይህም ሆኖ ኃያልነቱን በብዙ ዘርፍ እያረጋገጠ ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም ሳቢያ ጉልቶ የሚወጣው ያልተመጣጠነ የኅብረተሰብ ዕድገትና የሩሲያ ኅብረተሰብ ተጨባጭ ሁኔታ የመጀመሪያው ሶሻሊስት አብዮት በሩሲያ እንዲመጣ አድርጓል ። ይህ መሆኑም የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ የምርት ኃይሎቻቸው በዳበረበት የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት አገሮች መሆኑ ቀርቶ ሩሲያን በመሰለ ኋላቀር አገር መጀመሩ የግንባታውን ተግባር ምንኛ ከባድ እንደሚያደርገው መገመት ይቻላል ። እንዲያውም በምዕራብ አውሮፓ የነበሩ ሶሻል ዲሞክራቶችና የሩሲያ ሜንሼቪኮች የሶሻሊስት አብዮቱን ከተቃወሙበት አንዱ ምክንያት በጊዜው በሩሲያ የነበረው የምርት ኃይሎች ኋላቀርነት ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚያበቃ አይደለም በማለት ነበር ።

ይሁንና የሩሲያ የምርት ኃይሎች ዝቅተኛነት ከቦልሼቪኮች የተሰወረ አልነበረም። ሌኒን ራሱ ይህንን ሁኔታ በተለያዩ ጽሑፎች የተገለጸው ሲሆን እ. ኤ. አ. 1897 በተወሰደው የሕዝብ ቆጠራ ላይ በመመርኩዝ በተደረገው ስሌት ከመላው ኅብረተሰብ (የሩሲያ) አምስት ስድስተኛው ወይም 80% ያህሉ በእርሻ የተሰማራና አንድ ስድስተኛው ብቻ ወይም 20% አካባቢ በተቀረው ክፍል ኤኮኖሚ ማለትም በኢንዱስትሪ፣ ንግድና ትራንስፖርት የተሰማራ እንደ ነበር ለማረጋገጥ ተችሏል።[12] በዚህም ጊዜ በመላ ሩሲያ የነበረው ወዛደር 2.792.000 ሲሆን[13] ፣ ይህም ከኅብረተሰቡ 14% ያህል ነበር ። ይሁንና ዛሬ ደግሞ ከመላው የሶቪዬት ሕዝብ 80% በከተማ የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ የተሠማራ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኛ ሲሆን ፣ 20% ደግሞ በእርሻና በእርሻ ኢንዱስትሪ የተሰማራ ነው ። የምርት ኃይሎች አንዱና ወሳኙ ክፍል ሠራተኛው ሕዝብ በመሆኑ በሶቪዬት ኅብረት የታየው የከተሞች ብዛትና የሠራተኛው መደብ ቁጥር ማደግ በሶሻሊዝም የሚታየውን ፈጣን የምርት ኃይሎች ዕድገት ያመለክታል ።

በሌላ በኩል የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ የተፋጠነ ዕድገት ማስገኘቱን ለማየት በአሜሪካና በሶቪዬት ኅብረት የኤኮኖሚ ዕድገት በተወሰነ ጊዜ ያሳዩትን የዕድገት ፍጥነት ማገናዘብ ያሻል።

እ. ኤ. አ. ከ1928 እስከ 1972 ባለው ጊ.ዜ የሶቪዬት ኅብረት ኤኮኖሚ አማካኝ ዕድገት 5.1% ሲሆን የአሜሪካ ግን (በዚሁ ጊዜ) 3.2% ብቻ ነበር ። እንደገና ከ1950 እስከ 1972 ባለው ገ.ዜ የሶቪዬት ኅብረት አማካኝ የኤኮኖ[illegible] ዕድ[illegible]ት ሲሆን የአሜሪካ ከዚሁ ግማሽ በሆነ 2.1% ነበር ።[14] የተሻለ ሥርዓተ ማኅበርና የምርት ግንኙነት የሚያስገኙት የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት ማለት ይህ ነው ።

አሁንም የሶቪዬት ኅብረትን ልምድ በመውሰድ በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መሃከል የሚታየውን የምርት ኃይሎች ደረጃ በምናወዳድርበት ጊዜ ልንዘነጋው የማይገባ አንድ ትልቅ ነገር አለ ። ዛሬ የቡርዧው አፈቀላጤዎች በአሜሪካን የምርት ኃይሎችን ዕድገት በማስመልከት ሲለፍፉ የሚረሱት (?) ባንድ በኩል በሶቪዬት ኅብረት የሶሻሊስት ግንባታ ላይ በኢምፔሪያሊዝም ያደረሰውን የምርት ኃይሎች ውድቀትና በሌላ በኩል ደግሞ እንደ አሜሪካ ያሉት ቀንደኞቹ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በጦርነቶች ሳቢያ ያጋበሱትን ከፍቱኛ ትርፍ ነው ።

እንደሚታወቀው ሁሉ አሜሪካ ሁለቱንም የዓለም ጦርነቶች በሰው አገር የተዋጋች በመሆኗ የደረሰባት ኤኮኖሚያዊ ጉዳት መጠነኛ ሲሆን (በአንጻራዊ አነጋገር) የጦር መሳሪያዎችና ሌሎች ሸቀጦችን በመሸጥ ያገኘችው ትርፍና ጥቅም ግን በጣም ከፍተኛ ነው ።

ነገር ግን በሶቪዬት ኅብረት የሶሻሊዝም ግንባታ በአንደኛው የዓለም ጦርነትና በኋ

Digitized by Google

ላም በርስ በርስ ጦርነቱ የደረሰውን ጉዳት የተመለከትነው ሲሆን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የደረሰውን የምርት ኃይሎች ድቀት ሳያነሱ ማለፍ ተገቢ አይሆንም ። የሁለቱ አገሮች ውድድር በሁለቱ ሥርዓተ ማኅበሮች መካከል የሚደረግ ውድድር በመሆኑ ዛሬ የሚታየውን የምርት ኃይሎቻቸውን ዕድገት ለማገናዘብ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሶቪዬት ኅብረት ላይ ያደረሰውን ጉዳት ማገናዘብ ያስፈልጋል ።

ይህንን ጉዳት የሚያመለክቱ አንዳንድ አሃዞችን እንመልከት ። «በሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የናዚ ጀርመን ወረራ ወቅት ሶቪዬት ኅብረት ከሃያ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ አጥታለች ። 1,710 ከተማዎች ወድመዋል ፤ 70,000 መንደሮች በእሳት ጋይተዋል ። 32,000 ያህል የማምረቻ ድርጅቶች ወድመዋል ። በእርሻውም ዘርፍ ቢሆን የደረሰው ጉዳት ከባድ ነው ። 1,876 የመንግሥት እርሻዎች ፤ 2,890 የማሽንና የትራክተር ጣቢያዎች ፤ 98,000 የኅብረት እርሻዎች እንዳልነበሩ ሲሆኑ 71 ሚሊዮን የቀንድ ከብቶች አልቀዋል ። ጦርነቱ የአገሪቱን ዕድገት ቢያንስ በአሥር ዓመት ወደ ኋላ መልሶታል ።»[15] ከዚህ የበለጠ የምርት ኃይሎች ድቀት ቀደም ሲል በታሪክ ተመዝግቦ አያውቅም ። ከዚህ ሁሉ ጥፋት በኋላ ነው አሁንም ሶሻሊዝም የበላይነን ለመያዝ የተፋፋመ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኘው ።

አሁንም የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት ዋስትና ስለመሆኑ አንድ የመጨረሻ ማስረጃ እንውሰድ ። ይኸውም የሶሻሊስት አገሮች የጋራ ኢኮኖሚ ትብብር አባላትን ፤ የአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮችን የአሜሪካና እንዲሁም የጃፓንን (የኢምፔሪያሊስቱን ካምፕ) እና የታዳጊ አገሮችን የኢንዱስትሪ ምርት የዕድገት መጠን እንመልከት ።

የኢንዱስትሪ ዕድገት መጠን መነሻ እ. ኤ. አ. 1970 — 100[16]

	1974	1975	1976	1977
C.M.E.A.	140	152	163	174
E.E.C + U.S.A. + Japan	120	112	121	126
Developing Countries	136	137.	148	156

በአራቱ ዓመታት ማለትም ከ1974-77 የሶሻሊስት አገሮች የኢንዱስትሪ ዕድገት 34% ሲሆን በዓመት ሲሰላ 8 ½ % ነው ። የካፒታሊስት አገሮች ጠቅላላ ዕድገት 6% ሲሆን በዓመት 1 ½ % ይሆናል ። የታዳጊ አገሮች ዕድገት ደግሞ በአራት ዓመት 20% ሲሆን በአንድ ዓመት 5% መሆኑ ነው ። በእነዚህ አሃዞች ስሌት የሶሻሊስት አገሮች የዕድገት መጠን ከሁሉም የላቀ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ፊውዳል ኢትዮጵያን ከዛሬይቱ አብዮታዊት ኢትዮጵያ በማወዳደር የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዕድገት እያሳየ ነው ስንል መለኪያችንም ግልጽ ሊሆን ይገባል ። አብዮታችንም ያሳየውን ዕድገት ስንገመግም እስካሁን ከተነሱት ጉዳዮች ጋር በማገናዘብ ነው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም ኅብረተሰብ ከቀድሞ የተሻለ ዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛል በምንልበት ጊዜ በአሁኑ ወቅት አብዮቱ የምርት ኃይሎቹን በማሳደግ ተአምር አሳይቷል ማለታችን ሳይሆን ፤ በመጀመሪያ ደረጃ አብዮቱ በሂደቱ እየቀየረው የመጣው የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ በራሱ የዕድገት ምልክት እንደሆነና ለዕድገትም አመች ሁኔታ እንደፈጠረ በመገንዘብ ነው ። ምክንያቱም በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ይኸው አዲሱን ሥርዓት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የተለወጠው የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ከፍተኛና የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት ሊያስገኝ መቻሉ ደግሞ አሌ የማይባል ነው።

Digitized by Google

ሶሻሊዝም ከካፒታሊዝም ይልቅ ከፍተኛና የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት የሚያስገኝ ሥርዓት በመሆኑ ከፍተኛውን የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ የሚወክል መሆኑን ለማሳየት ተሞክሯል ። አብዮታችንም ይህንኑ ለማድረግ የተነሳ በመሆኑ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዕድገቱ ዋስትና ያገኘ መሆኑ አያጠራጥርም ። ስለሆነም ቀጠል በማድረግ አብዮታችን በሂደቱ ያስመዘገባቸውን ድሎች እንቃኛለን ።

የኢትዮጵያ አብዮት የደረሰበት የዕድገት ደረጃ

በኢትዮጵያ አዲስ ሥርዓተ ማኅበር ለመገንባት የተጀመረው ጉዞ

አንድ ማኅበራዊ አብዮት ከሌላው የሚለየው በባሕርዩና በሚያንቀሳቅሱት ኃይሎች ነው ። እንዲሁም የአንድ አብዮት ባሕርይ የሚገለጸው ወይም የሚታወቀው በሚፈታቸው የኅብረተሰብ ቅራኔዎች ዓይነትና አዲስ በሚቋቋመው ሥርዓተ ማኅበር ዓይነት ነው ። በዚህ መሠረት የአንድ አብዮት ባሕርይ እንደ ሁኔታው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ ወይም የወዛደሩ ሶሻሊስት አብዮት ሊሆን ይችላል ። የፊውዳሊዝምን ፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ አቋምና ያረጀ የምርት ግንኙነት ለማፈራረስ ብቻ የሚካሄድ አብዮት የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሲሆን የግል ካፒታሊስት ንብረትንና የምንዳ ባርነትን ለማስወገድ የሚደረገው አብዮት ደግሞ የወዛደሩ ሶሻሊስት አብዮት ነው ።

የአንድ አብዮት አንቀሳቃሽ ኃይልናቸው የምንላቸው ደግሞ አብዮቱን የሚያካሂዱትንና የሚያራምዱትን እንዲሁም የአድሃሪውን መደብ ተቃውሞ የሚደመስሱትን መደቦች ነው ። እነዚህ ኃይሎች በአብዮቱ ባሕርይ ብቻ የሚወሰኑ ሳይሆን እንደየአገሩ ታሪካዊ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያዩ ይችላሉ ። በአጠቃላይ ባሕርያቸው የሚዛመዱ ሁለት አብዮቶች እንደ እያንዳንዱ አገር ተጨባጭና የተለየ ታሪካዊ ሁኔታ የአብዮቶች አንቀሳቃሽ ኃይሎች ሊለያዩ ይችላሉ ። ለዚህ ነው በሩሲያ እ. ኤ. አ. በ1905 — 1907 ድረስ የተካሄደው የቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከፈረንሳይ ወይም ከእንግሊዝ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች የሚለየው ።

የሌኒን አንዱ ትልቅ አስተዋጽኦ መጪው የሩሲያ አብዮት ባሕርይ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ መሆኑን ቢገነዘብም በኢምፔሪያሊዝም መምጣትና በአገሪቱ የተለየ ታሪካዊ ሁኔታ የተነሳ የዚህ አብዮት አንቀሳቃሽ ኃይሎች የተለዩ ስለሚሆኑ ለአብዮቱ ልዩ ወይም አዲስ ባሕርይ እንደሚሰጡት ማስገንዘቡ ነው ። የመጀመሪያው የሩሲያዊ ቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በ1905 — 1907 እንደፈነዳ በጻፈው «በዲሞክራሲያዊ አብዮት የሶሻል ዲሞክራቶች ሁለት ታክቲኮች» በሚለው ጽሑፉ ፤ ወዛደሩ የቡርዧውን አብዮት መምራት እንደሚችልና ታሪካዊ ግዴታውም እንደሆነ ፤ ይህም መሆኑ ለአብዮቱ አዲስ ወይም ልዩ ባሕርይ እንደሚሰጠው ገልጿል ። የሩሲያ አብዮቶችም ይኸው ትክክል መሆኑን ከማረጋገጣቸውም በላይ በኋላም በሕዝባዊ ዲሞክራሲዎች መከሰትና በብሔራዊ አርነት አብዮቶች መጠናከር የሌኒን ግንዛቤ በይበልጥ ትክክለኛነቱን አረጋግጧል ።

ሌኒን ስለ ቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት የነበረው ሌላው ግምገማ ይኸው አብዮት ባሉት የተለዩ አንቀሳቃሽ ኃይሎች የተነሳ ከወዛደሩ የሶሻሊስት አብዮት ጋር የሚኖረውን ዝምድና የሚመለከት ነው። የሩሲያ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶች በታላቁ የጥቅምት አብዮት እንደታየው በቀጥታ ከሶሻሊስት አብዮት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው አሁንም አዲስ ባህርይ እንደነበራቸው እንገነዘባለን ።

የሶቪዬት ኅብረት ኮሙኒስት ፓርቲም የራሱን ታሪክ በጻፈበት ጊዜ ልምዱን ሲገመግም ፤ የሌኒን አስተዋጽዖ አዲስ እንደመሆኑ የማርክሲዝምን ቲዎሪ ይበልጥ እንዳዳበረው ጽፏል ። በቡርዧው ዲሞክራሲያዊ አብዮት የወዛደሩ ግንባር ቀደምነትና ከዲሞክራሲያዊ አብዮት በቀጥታ ወደሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር የቦልሸቪክ ፓርቲ የቀየሰው አዲስ መስመርና የሌኒን የቲዎሪ አስተዋጽዖ ነው ።

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮት ከሞላ ጐደል በዚህ ሌኒኒስት ቲዎሪ ላይ የተመሠረተ መሆኑ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራማችን በማያሻማ ሁኔታ ይገልጸዋል ። ሚያዝያ 12 ፣ 1968 በወጣው በዚህ መሠረታዊ ሰነድ ውስጥ የአብዮታችን ሌኒኒስት መርሆዎች እንደሚከተለው ሰፍረዋል ። «ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፀረ ፊውዳል በመሆኑ በጊዜው ያሉትን ፀረ-ፊውዳል ኃይሎች አስተባብሮ ለተጨቆኑት የኅብረተሰብ መደቦችና ክፍሎች ሁሉ ዲሞክራሲን ያጐናጽፋል ። ፀረ·ኢምፔሪያሊስት በመሆኑ ደግሞ ያሉትን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ሁሉ አስተባብሮ ነፃ ብሔራዊ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል አቋም ያዳብራል ። በዚህም ባሕሪው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ተብሎ ይጠራል ። እንግዲህ በብሔራዊው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሰፊውን ሕዝብ መምራቱ»[18] ማለትም «በወዝ አደሩ መሪነት ፤ በገበሬው ተባባሪነት» ወደ[19] «ኅብረተሰብአዊነት (ሶሻሊዝም) ለሚደረገው ጉዞ ያለው ብቸኛ መንገድ ነው ።» (ስርዝ የተጨመረ) ።[20]

እንግዲህ የኢትዮጵያ አብዮት ባሕርይና አቅጣጫ በፕሮግራሙ እንደሰፈረው ሲሆን ባለፉት ሰባት ዓመታት ምን ዓይነት ዕድገት እንዳስገኘ እድገቱስ በምን ሊለካ እንደሚችል ቀጠል አድርገን እንመለከታለን ።

የአብዮታችን ዕድገት መለኪያዎች

የኢትዮጵያ አብዮት በሌኒኒስት መርሆች የሚመራ ሁለንተናዊና ልዩ ባሕርይ ያለው ሲሆን ዓላማውም በፕሮግራሙ የሰፈረ በመሆኑ ዕድገቱ ነባራዊ መለኪያዎች አሉት። ሁለንተናዊ ባሕርይ ያለው በመሆኑ መሰል ባሕርይ ያላቸው አብዮቶች ያለፉበትን ሂደት የሚገዛው ሕግ በኢትዮጵያም አብዮት ተፈጻሚ ነው ። በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ አብዮት ከሌሎች በዚሁ ዓይነት የአብዮት መንገድ ከተጓዙ አብዮቶች ጋር ሲነፃፀር የብሔራዊ ቅርፅ ልዩነት ይኑረው እንጂ የግዴታ ዓለምአቀፋዊ የይዘት አንድነት እንዳለው ይታወቃል ። ስለሆነም በይዘት አንድነቱ መሠረት መሰል አብዮቶች የፈጸሟቸውን በመመልከት አብዮታችን ከምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ በነባራዊ መለኪያዎች ለመጠቀም እንችላለን ።

አሁንም ሌኒን በተለያዩ ጽሑፎች ያሰፈረውን ከተመለከትን የአንድን አብዮት ዕድገትና የፓርቲውንም ተግባር በሶስት ደረጃዎች ከፍሎ ለማየት ይቻላል ።

በዚህ መሠረት የመጀመሪያው ደረጃ ሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ የሚያደርገውን ትግልና ፤ የዚህም ትግል ተግባራዊነት የወዛደሩ ፓርቲ ሰፊውን ሕዝብ በፕሮግራሙ ጀርባ አሰልፎ የመንግሥት ሥልጣን በሚይዝበት ጊዜ የሚገለጽ መሆኑ ነው ። ሁለተኛ የአብዮቱ የዕድገት ደረጃ የወዛደሩ ፓርቲና ሰፊው ሕዝብ የተጐናጸፉትን ድሎች (የመንግሥት ሥልጣን ወዘተ . . .) ለማቆየት አድኅሮትን በቁጥጥር ሥር የማዋሉ ተግባር ነው ። ሦስተኛውና ከፍተኛው የአብዮት ደረጃ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ሌኒን አበክሮ ያስተምራል ። በወቅቱ የሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱን ሌኒን ሲናገር «ሦስተኛው ደረጃ እየጀመረ ነው ። እስካሁን ያገኘናቸውን ድሎች ማሰባሰብና ማጠናከር አለብን ። እኛው ራሳችን ያወጅነውን ፤ በሕግ የደነገግነውን፤ የተወያየነውን ፤ ያቀድነውን ሁሉ ወደቋሚ የሥራ ዲስፕሊን መቀየር መቻል አለብን ። ይህ ተግባር በእርግጥ አድካሚ ነው ። ነገር ግን ውጤቱ የሚክሰን ይሆናል ። ምክንያቱም የዚህ ተግባር መሳካት ብቻ ነው የሶሻሊስት ሥርዓትን የሚያስገኘው»[21] ብሎ ነበር ።

የአብዮታችንን ዕድገት ለመገምገም ከፕሮግራሙ መጀመር ይቻላል ። ይህም ማለት አብዮታችን እስካሁን በፕሮግራሙ ካሰፈራቸው ጉዳዮች ምን ያህሉ ተግባራዊ እንደሆነ በማየት የዕድገት ደረጃውን መገምገም ይቻላል ። በዚህ መንገድ የሚደረገውን ግምገማ በመጀመሪያው ሁለንተናዊ መለኪያ መሠረት በሚደረገው ግምገማ ለዕውነቱ የቀረበ ወይም ይበልጥ ትክክለኛ ይሆናል ። ምክንያቱም ፕሮግራሙ ፤ የአብዮቱን ሁለንተናዊና ልዩ ባህርያቱን ፤ ዓለም አቀፋዊውንና ብሔራዊውን በማገናዘብ ወይም በመመርኮዝ የተነደፈ በመሆኑ ነው ።

በዚህ አቀራረብ ከተስማማን የኢትዮጵያን አብዮት ከፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር ወደ ሶሻሊዝም በሚያደርገው ጉዞ የት እንደደረሰ ወይም ከምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመገመት ብዙም የሚያስቸግር አይ

ሆንም ። ባለፉት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ አብዮት በየዘርፉ የወሰዳቸውን እርምጃዎች በመገምገም ምን ያህል የዱሮውን ሥርዓተ ማኅበርና የምርት ግንኙነት እንዲሁም የንብረት ይዞታ እንደቀየረ መገንዘብ ይቻላል ።

ይሁንና የአብዮቱን የዕድገት ደረጃና ድሎች በይበልጥ ለመገንዘብ ጉዟችን የጀመረበትን ሁኔታ ማስታወስ ጠቃሚ ነው ። ስለሆነም በመጀመሪያ የቅድመ አብዮት ፊውዳል ኢትዮጵያን ዋና ገጽታዎች እንመልከት ።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሁኔታ ባጭሩ

ሰፊው ሕዝብ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በመለኮታዊ የፊውዳል መንግሥት ይገዛ እንደነበር ብዙም አስታዋሽ የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም ። በዚህም የፖለቲካ ተቋም ንጉሠ ነገሥቱ ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ እንዲሁም የተቀሩት የፊውዳል ገዥ መደብ አባላት በኢምፔሪያሊዝም ጋሻ ጃግሬነት የሰፊውን ሕዝብ መብት ረግጠው ሲገዙ ቆይተዋል ።

በዚህም ተግባራቸው የብሔረሰቦችን የሃይማኖቶችንና የጾታዎችን የዕኩልነት መብት ነፍገው ቆይተዋል ። እርግጥ ይህ ተግባራቸው ከርዕዮተዓለማቸውና ከተግባራዊ አፈጻጸሙ ፣ ማለትም ከፖለቲካ አስተዳደር ሥልታቸው የሚመነጭ ነው ። በሌላ አነጋገር የፊውዳሉ መንግሥት መሠረት እንዳይናጋ ሰፊው ሕዝብ በብሔረሰብ ፣ በአካባቢ በሃይማኖትና በጾታ ተከፋፍሎ መቆየቱ ከትብብሩ የሚያገኘውን ኃያልነት ያሳጣዋል ። የጠላትና የአድህሮት ሥልት «ከፋፍለህ ግዛው» ነው ሲባል ሰፊውን ሕዝብ የመደብ አንድነትና አጋርነቱን ማሳጣት ማለት ነው ። ለዚህም ነው ኮሚኒስቶች ከሁሉም ዓይነት የኅብረተሰብ የአንድነት መሠረት የመደብ ጥቅም የበለጠ የፀና ነው የሚሉት ።

በሌላ በኩል በፊውዳሉ ሥርዓት የነበረው የምርት ግንኙነት እንዲሁ እስከፊ ነበር ። እስከ 90% የሚሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብርና የተሰማራ ሲሆን የፊውዳሉ ገዥ መደብ የገበሬውን ምርት እስከ 75% ሊወስድ እንደሚችል ሕጉ ይፈቅድ ነበር[22] ። ከዚህ ሌላ ገበሬው ለፊውዳል ጌታው የጉልበት አገልግሎትና የተለያዩ ክፍያዎች ይሰጥ ስለነበር ምዝበራው የበለጠ የከፋ ነበር ። በከተማም በማደግ ላይ የነበረው የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት በባዕድ ካፒታልና በመጠኑም ቢሆን በአገሬው ካፒታሊስቶች የተያዘ ነበር ። ይሁንና ይኸው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚም ቢሆን ብዙ የዳበረ አልነበረም ። የኢንዱስትሪ ምርት አሁንም ቢሆን ለአጠቃላይ ብሔራዊ ምርት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ወይም ድርሻ ከ10% በላይ አለመሆኑ ምን ያህል ዝቅተኛ እንደነበር[23] የሚጠቁም ነው ። የሠራተኛውንም ሁኔታ ብንመለከት ከሚደርስበት አጠቃላይ ጭቆና ሌላ የሥራ ዋስትና ፣ ጡረታ ፣ ኢንሹራንስና የፈቃድ ዓይነቶች ዝቅተኝነት በምን ዓይነት አስከፊ ሁኔታ ይገኝ እንደነበር ያሳያል ። በአንድ አገር ብሔራዊ ኤኮኖሚ ወሳኙን ሥፍራ የሚይዙት ከባድ እንዱስትሪዎች በኢትዮጵያ ነበሩ ለማለት አይቻልም ።

በመሠረቱ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከፊውዳሊዝም የወረሰቻቸው ዝቅተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል ወይም 93% ማይምነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ፣ ዝቅተኛ መሠረተ ልማትና የማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው ። የዚህም ማኅበራዊ መልክ ድንቁርና ፣ ረሃብና በሽታ ሥራ አጥነትና ዝሙት አዳሪነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ነበር ። አሁንም ከዚሁ ኋላቀርነት ለመውጣት በመታገል ላይ ስንሆን እነዚህን ጠንቆች ፈጽሞ ለማስወገድ ረዥምና ውስብስብ ትግል የሚጠይቅ መሆኑ አያጠራጥርም ።

እንግዲህ አብዮታችን ይህንን የቅድመ አብዮት አስከፊ ሁኔታ ለመሻር የመጣ በመሆኑ እስካሁን በተለያዩ መስኮች ያደረገው ነገር ሁሉ የዕድገት ደረጃውን የሚያመለክት ወይም የፕሮግራሙን በተግባር መተርጐም የሚያሳይ ይሆናል ።

የአብዮታችን ድሎች ግምገማ

የኢትዮጵያ አብዮት ከጀመረበት ከየካቲት 1966 ጀምሮ ድል በድል እየተጐናጸፈ መምጣቱ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ቁም ነገሩ ስለነዚህ ድሎች በቂ

Digitized by Google

ትንተና ከማድረጉ ላይ ነው ። በተለያዩት ዘርፎች ፤ ማለትም በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው በማኅበራዊ እንቅስቃሴያችን የተገኙት ድሎች በቅጡ መገምገምና የደረስንበት ደረጃ በግልጽ መታየት አለባቸው ።

ቀደም ሲል በሥርዓተ ማኅበር ሹምሽር ማግስት ወይም አብዮት ከተካሄደ በኋላ ለጥቂት ጊዜ የምርት ኃይሎች ድቀት ወይም መቆርቆዝ ሊኖር እንደሚችል ተመልክቷል ። ዕድገት መኖሩን የሚያመለክተው አዲስ የወጣው የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ደግሞ የተጻራሪ መደቦችን ግንኙነት ሲገልጽ የህልውናቸውም መሠረት እንደሆነ ተብራርቷል ።

በአንድ ማኅበራዊ አብዮት የሚመጣ የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ለውጥ የግዴታ የመደቦችን ሹምሽር ያመለክታል። ይህ መሠረታዊ የአብዮት ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ባህርይ ነው ። አዲስ የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ መምጣቱ አዲስ የኅብረተሰብ መሠረት በመጣሉ አንፃር ኤኮኖማያዊ ገጽታውን ሲያመለክት ፤ በዚሁ ተግባር የመደብ ሹምሽር መኖሩ ደግሞ ፖለቲካዊ ገጽታውን ያመለክታል ።

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መስከረም 2 ፣ 1967 የመንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የቀድሞውን ሥርዓት ለመቀየር የወሰዳቸው በርካታ እርምጃዎች እንዳሉ ይታወቃል ። ይሁንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በእርግጥም አዲስ ኅብረተሰብ በመገንባት ላይ እንደሆነና በዘለቄታው አንፃር ሲታይ ፤ ከፍተኛና የተፋጠነ የምርት ኃይሎች ዕድገት እንደሚኖረው መገንዘብ የሚቻለው አዲስ በተፈጠሩት የምርት ግንኙነቶችና የንብረት ይዞታዎች ነው ። እነዚህም ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተካሄደውንም የመደብ ሹምሽር ያመለክታል ።

በአብዮታችን አዲስ የተፈጠረው የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ

የሚከተሉትን ሁለት መሠረታዊ አዋጆች ለናሙና ወስደን ብንመለከት ገና ከመጠሪያቸው እንደሚታየው ፤ የቀድሞውን የንብረት ይዞታ በመሻር በአዲስ የተኩት ሲሆን አዲስ የምርት ግንኙነት ለመፍጠርም መሠረት መጣላቸውን እንረዳለን ።

የሃብት ማፍሪያ መሣሪያዎችን ወደ መንግሥት ለማዛወርና በቁጥጥር ሥር ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1967 ፤

ምንም እንኳ ከዚህ አዋጅ መውጣት በፊት በታኅሣሥ 23 እና ጥር 26 የተለያዩ ተቋሞችን ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛውን ድርሻ ወደመንግሥት ባለቤትነት ያዛወረ እርምጃ ቢኖርም ፤ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ እንደተገለጸው «በዚህ አዋጅ እንደተወሰዱ ተቆጥረዋልና» ሁሉንም ያቀፈ በመሆኑ ለአቀራረባችን ቀና ይሆናል ።

በዚህና በሌሎች ተመሳሳይ አዋጆች እንደሚታየው የቀድሞውን ካፒታሊስትና ፊውዳላዊ የግል ንብረት ይዞታ ለመሻር የወጡት አዋጆች ያላቸውን ባህርይና ይዘት ስንመለከት ፊውዳሊዝምን ሙሉ በሙሉ የሻሩት ሲሆን የካፒታሊስት ይዞታውን ግን በሁለት ደረጃና የሥራ ዘርፎች ብቻ እንደ ወሰኑት እናያለን ።

የዚህ አዋጅ (26/67) ተከታታይ አንቀጾች እንደሚገልጹት ሶስት የንብረት ይዞታዎች ጎን ለጎን እንደሥራ ዘርፋቸው እንደሚኖሩ እናያለን ። እነዚህም የመንግሥት ወይም የሕዝብ መንግሥታዊ ካፒታሊዝምና የግል ካፒታሊስት ይዞታዎች ናቸው ።

አንቀጽ 2 ፤ በመንግሥት ባለቤትነት ብቻ ያሉ ተቋሞችንና ሥራዎችን ገልጾ ሲያበቃ በነዚህ ሥራዎች «የተሰማሩ የግል ተቋሞችም ሆኑ ማኅበሮች ሁሉ ከነሃብታቸው ወደ መንግሥት ባለቤትነት» በመቀየር የቀድሞውን ካፒታሊስታዊ ይዞታ እንደሚያጠፋ ይናገራል ።

በአንቀጽ 3 ፤ እንደተገለጸው ደግሞ መንግሥት ከውጪ ካፒታል ጋር ተካፋይ በመሆን መካሄድ የሚችሉትን ወይም መንግሥታዊ ካፒታሊስት ይዞታ የሚኖርበትን የሥራ ዘርፍና ድርጅቶች ይገልጻል ። ይኸም «በተዘረዘሩት ሥራዎች በተሰማሩ የግል ተቋሞችም ሆኑ ማኅበሮች ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ድርሻ ከ51 በመቶ እንዳያንስ» አድርጐ በሚይዘው ድርሻ እንደሆነ ይገልጻል ። በአንቀጽ 4 እና «በዚሁ አዋጅ ያልተጠቀሱ ሥራዎች »ደግሞ ለግል ካፒታ

Digitized by Google

ሊስቶች የግል ይዞታ እንደተተው እናያ
ለን ፡፡ ወደ ሁለተኛው መሠረታዊ አዋጅ
ስንሄድ የሚከተለውን እናገኛለን ፡፡

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሃብት ለማድረግ
የወጣ አዋጅ ቁጥር 31/1967 ከመ
ግቢያው አንስቶ እስከ ዝርዝር አንቀጾች
ድረስ ያለውን ስንመለከት በገጠር የፊው
ዳሊዝምን የምርት ግንኙነትና የንብረት
ይዞታ ሙሉ በሙሉ እንደሚሽር በምትኩም
የመንግሥት ፤ የኅብረትና የግል ይዞታዎችን
እንደሚያሰፍን ይታያል ፡፡ ቀደም ሲል
በአንደኛ ተራ ቁጥር ካየነው አዋጅ 26/67
በብዙ ነጥቦች ይለያል ፡፡

ትልቁ የመለያ ነጥብ ይህ አዋጅ (31/67)
የፊውዳሊዝምን የምርት ግንኙነት ማለትም
በጭሰኛውና በመሬት ከበርቴው መሃል የነ
በረውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ የሚሽር
ከመሆኑም ሌላ ቀደም ሲል በገጠር የነበ
ረውን ማንኛውንም የካፒታሊስት ይዞታ
የግልም ቢሆን መንግሥታዊ የሚሽር ነው ፡፡
ይህም በአያሌ ሥፍራዎች ተገልጿል፡፡ በዚህ
አዋጅ መሠረት «የገጠር መሬት የኢትዮጵያ
ሕዝብ ሃብት ከመሆኑም በላይ ማንኛውም
ሰው ወይም የንግድ ማኅበር ወይም ሌላ
ድርጅት መሬትን በግል ባለሃብትነት ሊይዝ»
እንደማይችል በአንቀጽ 3 የተገለጸ ጉዳይ
ነው ፡፡ ስለሆነም አዋጁ የሚሰጠው መሬ
ትን በግል የመጠቀም መብት እንጅ ቀደም
ሲል እንደተፈቀዱት የግል ባለሃብት ይዞ
ታዎች ሁሉ ለመሸጥ ለመለወጥ ለማውረ
ስና ለማስያዝ እንደማይቻል አንቀጽ 3 ላይ
ተመልክቷል ፡፡

ትርፍ ምርትን ወይም ያልተከፈለበት
የሥራ ሰዓትን በማግኘት ላይ የተመሠረተን
ፊውዳላዊና ካፒታሊስታዊ ምዝበራን ያጠ
ፋል ፡፡ በግል ሠርቶ ለራስ መጠቀም እንጂ
ሌላ ሰው ቀጥሮ ማሠራት (ከተወሰኑ ልዩ
ሁኔታዎች ውጭ) በአንቀጽ 4 የተከለከለ
በመሆኑ አሁንም ካፒታሊስታዊ ምዝበራን
የሚያጠፋ ነው ፡፡ ይሁንና አዋጁ ብቻውን
ለካፒታሊዝም ግንኙነት መጥፋት ወይም
አለማንሰራራት ዋስትና ሊሆን አይችልም ፡፡
ዛሬ በኢትዮጵያ የእርሻ ክፍለ ኤኮኖሚ
ውስጥ በአዋጅ መሠረት ምንም ዓይነት
የሰው በሰው ምዝበራ የለም ለማለት ይቻ
ላል ፡፡

የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው
አዋጅ «መሬት ላራሹ» ብሎ የታገለው
ሕዝብ የትግል ፍሬ ሲሆን ይህ አዲስ የንብ
ረት ይዞታና የምርት ግንኙነትን ፈጥሮ
አል ፡፡

እስካሁን ከተመለከትነው ሁሉ የቀድ
ሞን የንብረት ይዞታና የምርት ግንኙነት
በመሻር አዲስ የመጡት የንብረት ይዞታ
ዎች በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ በሽግግር
ላይ የሚታዩ የንብረት ይዞታዎች ናቸው ፡፡
እነሱም ፤ የመንግሥት ይዞታ ፤ የኅብረት
ይዞታ መንግሥታዊ ካፒታሊስት ይዞታ·
የግል ካፒታሊስት ይዞታና የአነስተኛ ሸቀጥ
አምራቾች ይዞታ ናቸው ፡፡

ከነዚህ የተለያዩ ይዞታዎች የመጨረ
ሻው ፤ የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች ይዞታ ፤
ተጨማሪ ማብራሪያን ይፈልጋል ፡፡ ይኸ
ውም እንደ ተለያዩ አገሮች የተለያየ የዕድ
ገት ደረጃ የአነስተኛ ሸቀጥ አምራቾች
ብዛትና አንዳንድ ባህርያት ሊለያዩ የሚ
ችሉ መሆናቸው ነው ፡፡ ዛሬ በአገራችን
በዚህ ይዞታ ላይ የገበሬውንና የዕደ ጥበብ
ባለሙያዎችን እናገኛለን ፡፡ እነዚህም ፤ የአ
ገሬውን ሕዝብ ምን ያህል (ከመቶ) እንደ
ሚሆኑና ለአጠቃላይ ብሔራዊ ምርት የሚ
ያደርጉትን አስተዋጽኦ ስንመለከት በጣም
ብዙ ነው ፡፡ በተጨማሪም የግል ሃብትን
በሚመለከት ፤ ገበሬው ከማምረቻ መሣሪ
ያዎች ውስጥ የመሬቱ ባለቤት አይደለም ፡፡
የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ግን ፤ የማምረቻ
መሣሪያዎቻቸው ከሞላ ጐደል ፤ በሙሉ
የራሳቸው ናቸው ፡፡ ይህ በአገራችን ያለው
ያነስተኛ አምራቾች ከፍተኛ ሚናና የንብ
ረት ይዞታ መልክ በሌሎቹ እንዳለ የሚገኝ
ነገር አይደለም ፡፡

በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ እንደተገለ
ጸው የተከናወኑትን የንብረት ይዞታ ወይም
የባለቤትነት ሽረቶች በአዋጆች የተደረጉ
በመሆናቸው ሁለቱን አዋጆች በመውሰድ
የተከተለውን የንብረት ይዞታና የምርት
ግንኙነት ለውጥ ለማየት ተሞክሯል ፡፡ ይሁ
ንና ከዚህ ጋር በማያያዝ ይህን የንብረት
ይዞታ ለውጥ ማኅበራዊ ወይም ፖለቲካዊ
ጉኑን ማለትም የመደብ ገጽታውንም አብሮ
ማየት አስፈላጊ ይሆናል ፡፡

ዛሬ በአገራችን ሰፍነው ያሉት የንብረት

Digitized by Google

ይዞታዎች በኅብረተሰቡ ካሉት መደቦች ጋር የተሳሰሩ ናቸው ። የግል ካፒታሊስት ይዞታ የአገሬውና ዓለም አቀፍ ቡርዧው ዋልታ ናቸው ። ገበሬውና የተቀረው ንዑስ ቡርዧ ደግሞ የአነስተኛ ሸቀጥ ምርትን ሲወክል ለወደፊቱ ደግሞ በህብረት ይዞታ ሥር የሚጠቃለሉት የሶሻሊስት ንብረት ላይ ያለው የኅብረት ይዞታን ዓይነት የሚወክሉ ይሆናሉ ። የመንግሥት ይዞታ ደግሞ በሠራተኛው መደብና በዚህም ይዞታ ሥር ባለው የማህበራዊ ክፍል የሚወከል ሲሆን ሌላው የሶሻሊስት ንብረት ይዞታ መሠረት ነው ።

እነዚህ መደቦች የንብረት ይዞታው ለውጥ ወይም የዚህ ሕጋዊ መግለጫ በሆኑት አዋጆች የተጠቀሙ ወይም ሙሉ በሙሉ ያልተነኩ መደቦች ናቸው ። የመንግሥትና የኅብረት ይዞታዎች ታዳጊዎቹና የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መሠረት ናቸው ። ይኸም በመደብ አሰላለፍ አኳያ ስናየው በወዛደሩ በገበሬው በተቀረው ሠርቶ አደር አንድነት ላይ የተመሠረተ ነው ። በቅርብ የወጡት የዕደ ጥበብና የገበሬዎች የአምራቾች ኅብረት ሥራ መመሪያዎች መውጣት የነዚህን መደቦች አንድነት ይበልጥ የሚያጠናክር ለሶሻሊስት የንብረት ይዞታና የምርት ግንኙነት መሠረት እየሰፋ መሄድ በቂ ምስክር ናቸው ።

በአብዮታችን የድርጅት ግንባታ

ለአዲስ ሥርዓት አዲስ መሠረት በመጣል ላይ እንደሆንን ከላይ እንደተመለከትነው የተቀየረው የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ያስረዳሉ ። ይህም የመደብን ሹም ሽር የሚያመለክት ነው ። የኢትዮጵያ ገበሬ የፊውዳሎች የኢኮኖሚ ሃይል በማናጋት የመሬቱ ባለቤት ሲሆን የኢትዮጵያም ሕዝብ በአጠቃላይ ከግል ካፒታሊስቶች የግል ሃብትነት የማምረቻ መሣሪያዎቹን ባለቤትነት ያረጋገጠ መሆኑ ለመደብ ሹም ሽርነቱ በቂ ምስክር ነው ።

ይሁንና ይኸው አዲስ ሥርዓት የመገንባት ተግባር ድርጅታዊ መልክ ያለው እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ። ማርክስና ሌኒን ድርጅት በመደብ ትግል ያለውን ከፍተኛ አገልግሎት በመደጋገም ተናግረዋል ። ሰፊው ሕዝብ ከመደብ ጠላቶቹ ጋር በሚያደርገው ትግሉ ድርጅት ትልቁ መሣሪያ ነው ። ይህም በመሆኑ አንዳንድ የንብረት ይዞታንና የምርት ግንኙነትን የሚቀይሩ አዋጆች የሰፊውንም ሕዝብ መደራጀት አብረው ይደነገጋሉ ። በዚህም መሠረት ሰፊውን ሕዝብ በመደብ ጥቅሙና በማኅበራዊ ፍላጐቱ መሠረት በየዘርፉ ማደራጀት የአብዮታችን አንዱ ተግባር ሁኖ ቆይቷል ።

ሕባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በወዝአደሩ ግንባር ቀደምነት በገበሬው አጋርነት ፤ በተቀረው የኅብረተሰብ ክፍል ተባባሪነት ለመመሥረት የሚደረገው ትግል ዛሬ ከመቼውም በበለጠ ተፋፍሟል ። ይህም ትግል ኢሠፓአኮ ታኅሣሥ 8 ቀን 1972 ከተቋቋመ በኋላ አንድ ከፍተኛ ማዕከላዊ አመራር በማግኘት ወደከፍተኛ ደረጃ ተሸጋግሯል ።

የኢሠፓአኮ መቋቋም ታሪካዊ ትርጉም

ኢሠፓአኮ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ስለዚሁ አካል መቋቋም ብዙ ማብራሪያ የተሰጠበት በመሆኑ እዚህ ላይ ብዙ ማውሳቱ ከመደጋገም የሚመጣ ማሰልቸት በስተቀር የሚጨምረው ነገር አይኖርም ። ይሁንና በኢትዮጵያ አብዮት የኮሚኒስቶችንና የጊ/ወ/አ/ደርግን ግንኙነት በሚመለከት የኢሠፓአኮ መቋቋም ልዩና ታሪካዊ ሥፍራ የሚሰጠው ይሆናል ።

ጊ/ወ/አ/ ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ እስከ ኢሠፓአኮ መቋቋም ድረስ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ብንመለከት የሚከተለውን ርዕዮተዓለምና የፖለቲካ መስመር ለመገምገም ብዙም የሚያስቸግር አይደለም ። ከነዚህ ሁሉ የተወሰኑ የፖለቲካ ዓላማ መግለጫ የሆኑ ሰነዶችን ብቻ ብንመለከት ይኸው ጉዳይ ግልጽ ይሆናል ። የታኅሣሥ 11/1967 የኅብረተሰባዊነት መመሪያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መለስተኛ ፕሮግራምና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 91/1968 ዋነኞቹ ናቸው ።

በነዚህ ሁሉ ሰነዶች እንደሰፈረው ጊ/ወ/አ/ደርግ ከተቀሩት ተራማጅ ኃይሎችና

Digitized by Google

ኮሚኒስቶች ጋር ለመተባበር ያለውን ሙሉ
ፈቃደኛነትና መንግሥትም በመሆኑ ማን
ኛውንም ዓይነት ድጋፍ ለማቅረብ ፍላጐት
ያለው መሆኑን አስመስክሯል ። ይሁንና
አሳዛኝና አስቂኝ በሆኑ ምክንያቶች ከደርግ
ውጭ የነበሩት ተራማጅ ኃይሎች ብስለትና
ሐቀኝነት የጐደላቸው በመሆናቸው አስተ
ማማኝ የሆነ አንድ የፖለቲካ ድርጅትና
ማዕከል ሳይፈጠር እስከ ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ መቋቋም
ድረስ ቆይተናል ።

ጊ./ወ/አ/ ደርግ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ
ጊዜያዊ ጽ/ቤትን ባቋቋመበት ጊዜ ሳይን
ሳዊ ሶሻሊዝምን የማስተማር ኃላፊነት የወ
ሰደ ድርጅትና አካል መፍጠሩ ይታወቃል ።
ይሁንና በዚህ ደረጃ የኢትዮጵያ ታጋዮች
ከደርግ ጋር የሚያስተሳስራቸው አንዳችም
ድርጅታዊ መዋቅራዊ ግንኙነት አልነበረም
የሕዝብ ድርጅት ከደርግ ጋር የነበረው
ግንኙነት ተዘዋዋሪ ነበር ። የሕዝብ ድርጅ
ትን በበላይነት የሚመራው አካል ከፍተኛ
የሕዝብ ማደራጃ ኮሚቴ የሚባል ሲሆን
ይህም አካል ደርግንና የሕዝብ ድርጅትን
የሚያገናኝ አካል ነበር ። እንዲያውም በጊ
ዜው ተራማጁ ክፍል በመንግሥት ላይ
የነበረውን ስጋት የሕዝብ ድርጅትን ለማ
ቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 91/1968
አንቀጽ 10 ያሳያል ። በዚሁ አንቀጽ
እንደሰፈረው የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜ
ያዊ ጽ/ቤት ከማንኛውም የመንግሥት
መሥሪያ ቤት ፤ ከማንኛውም ድርጅት
ወይም ቡድን ቁጥጥርና ተጽዕኖ ነፃ ነው»
ይላል ።

ይሁንና የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ መምጣት አንዱና
ትልቁ ታሪካዊ ትርጉም የደርጉንና ከደርግ
ውጭ የነበሩ ኮሚዩኒስቶች በአንድ ማዕከ
ልና መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሰብሰብ
የተፈጠረውም ድርጅት በቀጥታ ከደርግ
ጋር ያለው ግንኙነት ሕጋዊና ይፋ መሆኑ
ነው ። ይኸውም ፣ ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮን ለማቋቋም
የወጣው አዋጅ አንቀጽ 10/1—20/ በሚ
ገባ ይገልጻል ። በዚህ መሠረት የጊዜያዊ
ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር
የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ ሊቀመንበር መሆናቸውን ሲደ
ነግግ ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮም ከጊዜያዊ ወታደራዊ
አስተዳደር ደርግ ጋር ሊኖረው የሚገባውን
ግንኙነትና ትብብር በሊቀመንበሩ እንደ
ሚወሰን አብሮ ተገልጿል።[24] ይህ መሆኑ
ለኢትዮጵያ ኮሙዩኒስቶች ከፍተኛ ድል
ሲሆን ኮሙዩኒስቶችም ከሰፊው ሕዝብ
በተለይም ከሠርቶ አደሩ የተለየ ጥቅም
ስለሌላቸው ለሰፊው ሕዝብ ከፍተኛ ድል
ነው እንላለን ። እንደሚታወቀው ሁሉ
ይህን የመሰለ ሕጋዊና መዋቅራዊ ግንኙ
ነት ያለው የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮና የደርግ አሠራር
መሠረታዊ በሆነው ሌኒኒስት የፓርቲና
የመንግሥት አሠራር ግንኙነት መርህ ላይ
የተመሠረተ ነው ። በመሆኑም የሠርቶ
አደሩን ፓርቲ በመመሥረት የወዛደሩን አመ
ራር ዕውን ለማድረግና ሕዝባዊት ዲሞክራ
ሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር በሚደረገው
ትግል የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንደ
ደረስን ይቆጠራል ።

በአሁኑ ጊዜ ያሉት አጠቃላይ ሁኔታ
ዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ በፖለቲካው
ትግል ዘርፍ አሁን ያለንበት ደረጃ ከኢ.ሠ.
ፓ.አ.ኮ ወደ ፓርቲ ምስረታ ከአብዮታዊት
ኢትዮጵያ ወደ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ በሚ
ደረገው ሽግግር መሃል ሌላ ደረጃ ባለመ
ኖሩ ፣ ዛሬ በፕሮግራማችን ከሰፈሩት ዓላማ
ዎች አንዱ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢት
ዮጵያን ለመፍጠር ባለው ጥረት ከፍተኛ የት
ግል ደረጃ ላይ ወይም በዋዜማው ላይ እንገኛ
ለን ። በመሆኑም አብዮታችን ፕሮግራሙን
ተግባራዊ ለማድረግ ባደረገው እርምጃ ሁሉ
እድገቱ የሚለካ ስለሆነ በእርግጥ እድ
ገት እንዳሳየ እንገነዘባለን ።

የሕዝባዊ ድርጅቶች ግንባታና መጠናከር

የወዛደሩን መሪነት የገበሬውን አጋር
ነት የተቀበሉትንም የንዑስ ከበርቴ መደብ
አባላትና የኅብረተሰብ ክፍሎች ተባባሪነት
ለመፍጠርና ለማጠናከር ሕዝባዊ ድርጅ
ቶች ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። በመሠረቱ
የኢትዮጵያ ኮሚዩኒስቶች ከሰፊው ሕዝብ
ጋር የሚገናኙባቸው መድረኮች በማበብ
ላይ ያሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች ሲሆኑ ይህም
ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ ለነዚህ ድርጅቶች በሚሰጠው
የፖለቲካ አመራር ይገለጻል ።

ዛሬ አብዮታችን በደረሰበት ደረጃ ሰፊ
ውን ሕዝብ በየፈርጁ በሕዝባዊ ድርጅቶች
በማደራጀት እየጐለበተ ነው ። ሁላ

Digitized by Google

እንደምናውቀው በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ የአንድ ሕዝባዊ ድርጅት አባል ያልሆነ ኢትዮጵያዊ በጣም ጥቂት ነው ። የኮሚዩኒስቶች የማደራጃ መርህ በሥራ ቦታና በመኖሪያ ክልል ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከፍተኛ ማኅበራዊ ኃይል ለማሰባሰብ ያስችላል ። በሥራው ቦታ መደራጀት ያልቻለ በመኖሪያ ክልሉ መደራጀቱ አይቀርም ። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ አብዮት በተቻለው ሁሉ የሚናቸውም ዜጋ አስተዋጽኦ ላለማጣት በየፈርጁ ባደራጀው ሕዝብ ብዛትና የማኅበራት ብዛት መገንዘብ ይቻላል ።

የአምስቱ ዋና ሕዝባዊ ድርጅቶች ቁጥርና የአባላት ብዛት[25] ባሁኑ ወቅት የሚከተለውን ይመስላል ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች	የመሠረታዊ ወይም መደብ ማኅበራት ብዛት	የጠቅላላ የአባላት ብዛት
መኢሠማ	1 532	242 166
መኢገማ	20 256	6 559 523
አኢወማ	17 423	3 033 165
አኢሴማ	17 325	4 217 074 *
ከነማ	11 52 * *	3 433 645

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ከሰፈሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች ውጭ አብዮታችን በተለያዩ የሙያ ማኅበራት የተደራጁትን ኢትዮጵያውያን ትብብር በአገልግሎት ላይ ከማዋል አልተቆጠበም ። በዚህም መሠረት የመምህራን ማኅበር ፣ የጤና ባለሙያዎች ማኅበር ፣ የጋዜጠኞች ማኅበር ፣ የኪነት ባለሙያዎች የአርበኞች ማኅበር ወዘተ የመሰሉትን ማኅበራት አብዮታዊ አመራር በመስጠትና የነርሱንም የፖለቲካ ድጋፍና ትብብር በማግኘት አብዮታችን እየተጠናከረ ነው ። ሰፊው ሕዝብ በመደብ ጥቅሙና ማኅበራዊ ፍላጐቱ መሠረት የሚኖረው አንድነት ድርጅት በመሆኑ በዚህ ረገድ ከላይ እንደሰፈረው የሕዝባዊ ድርጅቶች ብዛትና ያቀፏቸውም አባላት ብዛት አብዮታችን ለቆመለት ዓላማ ምንኛ ጽኑ መሠረት እንዳገኘ ያረጋግጣል ።

የኢትዮጵያ አብዮት ግብ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ መገንባት እንደሆነ በኢሠፓአኮ ሁለት መሠረታዊ ሰነዶች ሰፍሯል ። ለዚህም ዓላማ መሳካት ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ እንደተነገረው የሶሻሊስት ሥርዓት መሠረት የሚሆን የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ መፍጠር ግንባር ቀደም የአብዮቱ ተግባር በመሆኑ በዚህ ረገድ እስካሁን የተከናወነውን በመገምገም የአብዮታችንን ዕድገት ለማየት ይቻላል ።

የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታን ከሚወክሉት ሁለቱ ይዞታዎችአን ደኛው የኅብረት ይዞታ ነው ። በተለይም ከኋላቀር የዕድገት ደረጃ ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ሽግግር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወሳኙን ሚና ይጫወታሉ ። በሀገራችንም አብዛኛውን የሕዝብ አባል የያዙትን ገበሬዎችና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን ወይም አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾችንወደ ሶሻሊስት ሥርዓት ለማሸጋገር ያለው ብቸኛ አማራጭ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ናቸው ። የአነስተኛ የሸቀጥ ምርት ለአጠቃላይ ብሔራዊ ምርት ወይም ኢኮኖሚ ከፍተኛውን ድርሻ በመያዙ አሁንም የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ ወሳኙን ሚና ይይዛል ።

ባጭሩ ፣ በተያያዝነው የኢኮኖሚ ግንባታ ሶሻሊዝምን በገጠር ለማስፈን ፣ በማዕከላዊ ፕላን የሚመራውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ለማዳበር ፣ የእርሻ ምርት መጠን ፣ ዓይነ

* ይህ ቁጥር በየካቲት 1973 የተወሰደ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በአኢሴማ ውስጥ የጠቅላላ አባላት ብዛት 5,182,385 ደርሷል ።

** የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት የሦስተኛው ዙር ምርጫ የአፈጻጸም መመሪያ ፤ ሚያዝያ 1973

Digitized by Google

ትና ዋጋ ለመቆጣጠር እንዲሁም ለጥሪት ክምችት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ ።

ይህም በመሆኑ አብዮታችን የኅብረት ሥራ ማኅበራትን እንቅስቃሴ ለማጠናከር እየጣረ ሲሆን የሚያኩራራም ባይሆን የሚያበረታታ ውጤት እያገኘ ነው ። ዛሬ 47 ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውና 722 ጥንስሶች በአጠቃላይም 506 የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተቋቁመዋል ። እነዚህም ማኅበራት በጠቅላላው 85,780 ሄክታር መሬት ያርሳሉ ። የገበሬዎች የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራትም እንዲሁ በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ ። በሀገሪቱ 3 508 የሚሆኑ የገበሬዎች የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙ ሲሆን 376 የሚሆኑት ደግሞ ሕጋዊ ሰውነት አግኝተዋል ። እነዚህም ማኅበራት 41.5 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያላቸውና ለ4.8 ሚሊዮን ገበሬዎች የገበያ ፣ የወፍጮ የመጋዘን ፣ የሱቅ ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት በማቅረብ ተገቢውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ናቸው ። የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች የአምራቾችና የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትም እድገት እንዲሁ የሚያበረታታ ነው ። [26]

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊ/ወ/አ/ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሰኔ 9 ቀን 1972 የኢሠፓአኮን 1ኛ ታሪካዊ ጉባዔ ሲከፍቱ ባቀረቡት ሪፖርት የሶሻሊስት የኅብረት ይዞታ ታዳጊ በመሆኑ መጠናከር ያለበት መሆኑን ሲያስገነዝቡ እንዲህ ብለው ነበር ።

«ዛሬ በምንገኝበት የሽግግር ወቅት የምንከተለው መስመርና የሥራ አፈጻጸም ጊዜያዊና ውዳቂ በሆኑ ላይ መመካት ሳይሆን አዳጊውን ማዳበር ነው ። ስለዚህ ትኩረታችን የሶሻሊዝም ይዘት ባላቸው ጉዳዮች ላይ መሆን አለበት ።...ባለንበት የሽግግር ደረጃ ላይ የግል ይዞታ ሥፍራ እንዳለው በግልጽ የታወቀ ቢሆንም ታዳጊ የሆነው ማኅበራዊ ይዞታ በተጨባጭ መመራት እንዳለበት መገንዘብ ያሻል ። ያለዚህ መረጋገጥ የተለየ ሥልተ ምርቶችን በአንድ ጊዜ ብማስተናገድ ተወስና ሶሻሊዝምን አገነ

ባለሁ ማለት ሃሰት ነው ። በተዥጎረጎረ የኢኮኖሚ ቅንጅት መርካትም ወገናዊነት ከሌለው አመለካከት የሚመነጭ ነው።» [27]

እንግዲህ ይህ የጓድ ሊቀመንበራችን አነጋገር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይዞታ ለተያያዝነው የሶሻሊዝም ግንባታ ያላቸውን ወሳኝነት አበክሮ የሚያስተምረን ነው ። እስካሁን ድረስ በተለያዩ ዘርፎች የተመለከትናቸው ሁሉ አብዮታችን በተተለመለት አቅጣጫ እየገፋና እያደገ መሄዱን የሚያስረዱ ናቸው ። ይህም የአብዮታችንን ብሩህና ጠንካራ ጐን ሲያስመለክተን ችግሮቻችን ወይም ደካማ ጐኖቻችንንም ማስታወሱ ይጠቅማል ።

የአብዮታችን ችግሮች

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ከፉኛ የሚፈታተኑት ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ከፊቱ ተደቅነዋል ። ተገንጣይ ብሔረተኛ እንቅስቃሴዎች ፣ የሶማሊያ አድሃሪ መንግሥት ፣ የኢምፔሪያሊዝም ትንኮሳና በመሃል አገርም የፀረ አብዮት አድሃሪና ብሔረተኛ ቅስቀሳ በርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካ መስክ የሚታይ ችግሮች ናቸው ። እነዚህም በአንድነት ገጽታዎች በቡርዧው ብሔረተኛነት ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ ።

በመሠረቱ እነዚህ ችግሮች አብዮቱ ዛሬ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ መኖራቸው ብዙም የሚገርመን አይደለም ። ዛሬ አብዮታችን በሚገኝበት ሁኔታ በተለያየ መልክ የሚካሄደው ከፍተኛ ወይም ዋነኛው ፖለቲካዊ ትግል በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም ፣ በቡርዧዎችና በኮሚዩኒስቶች ፣ ለወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና በብሔረተኛነት በማሌና በአይዲሊያዝም መሃል ያለው እንደሆነ በሚገባ ልንረዳው ያስፈልጋል ። እርግጥ አብዮታችን የሚጓዝበትን መስመር ከቀየሰ የሰነበተ ቢሆንም ይህ በመሆኑ ብቻ የጠላት ሰፈር እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል አንልም ። የውስጥ አድህሮትና ኢምፔሪያሊዝም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአብዮቱን ሠፈር ለማተራመስና ለማጥቃት ወደ ኋላ እንደማይሉ የታወቀ ነው ።

አሁንም እንደምናየው በወታደራዊና ፖለ
ቲካዊ ዘርፍ የተፋፋመ የሞት ሽረት ትግል
እያካሄዱብን ነው ። በፖለቲካው ዘርፍ
አንዱና ዋንኛው የቅስቀሳቸው ይዘትና
የትግል መስመር አርገው የወሰዱት የኢት
ዮጵያን አብዮት ዓለም አቀፍ አጋርና ድጋፍ
ለማሳጣት የሚያካሂዱት ፀረ—ሶቪዬት ፕሮ
ፓጋንዳ ነው ። ዛሬ በኢትዮጵያችን የብሔ
ረተኝነት ዋነኛ መልክና የትግል መሣሪያ
ፀረ—ሶቪዬት ፕሮፓጋንዳ ነው ብንል ከዕ
ውነቱ ብዙ የራቅን አንሆንም ። ይሄን
የጠላት የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም የትግል
ዘዴ በአጭሩ ለመቅጨት የሰፊውን ሕዝብ
የርዕዮተ ዓለም ትጥቅ ማጠናከር ያስፈ
ልጋል ። በዚህ አንፃር ለሰፊው ሕዝብ
ዕውነቱን ከማሳ ወቅም ባሻገር የፀረ ሶቪ
ዬት ፕሮፓጋንዳቸውን እንደ መደብ ትግል
መሳሪያቸው አርገው በመጠቀም በኢትዮ
ጵያ ለሶሻሊዝም ልዕልና የሚደረገውን
ትግል ለማኮላሸት የተነሱትን ፀረ-አብዮት
ኃይሎች በፅኑ ሊዋጋቸው እንደሚገባ ማስ
ገንዘብ ያስፈልጋል ።

በሌላ በኩል የጠላት ሠፈር ፕሮፓጋ
ንዳ ዛሬ አብዮታችን በሚገኝበት ደረጃ
የሚታዩትን ችግሮች አጋኖ በማቅረብ አብ
ዮቱና ሶሻሊዝም ለሰፊው ሕዝብ እንደማይ
በጁ አድርጐ ለማቅረብ የሚደረገው የተለ
ያየ ረቂቅ ቅስቀሳ ነው ።

በመሠረቱ ኮሙኒስቶች ከሰፊው ሕዝብ
የሚደብቁት ችግር የለም ፡ እንደውም በተቃ
ራኒው የችግሮችን መንስዔና ውጤት ለሰ
ፊው ሕዝብ በሚገባ በማስረዳትና የራሱ
ችግር መሆኑን በማስገንዘብ ተገቢውን
እርምጃ መውሰድ ዋነኛ የትግል ዘዴያቸው
ነው ። «ትግሉ መራራ ነው ። ግባችንም
ሩቅ ነው» ሲባል የችግሩን ደረጃ አስቀድሞ
ለመግለጽና ሰፊውን ሕዝብ ለትግል ለማዘ
ጋጀት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ።

ስለሆነም ዛሬ በኢትዮጵያችን ሥራ
አጥነት ፥ ዝሙት አዳሪነት ፥ የኑሮ መወደድ
አድላዊነት ፥ ጉቦኝነትና በአጠቃላይ
ምዝበራና ብኩንነት ያሉ ስለመሆናቸው
ኮሙዩኒስቶች ከማንም ሳይሸሽጉ የሚና
ገሩት ሲሆን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ
የነዚህን ችግሮች ጠንቅ ለሕዝብ ከማስረ
ዳት ተቆጥበው አያውቁም ። አድሃሪና
ጠላት ግን የነዚህ ችግሮች ሁሉ መንስዔ
አብዮቱና ሶሻሊዝም እንደሆነ ለማሳመን
የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል ።

እዚህ ላይ የተጠቀሱትን ችግሮች አብ
ዮቱ እንዴት እንደሚያያቸው በጥቂቱም
ቢሆን ማንሳቱ ይጠቅማል ። የችግሮቻች
ንን መንስዔ ከሁለት አቅጣጫዎች ማየት
ይቻላል ። የመጀመሪያው መዋቅራዊ ሲሆን
ሁለተኛው ደግሞ ከመንግሥት ባህሪይና
ሚና መቀየር ጋር የተያያዘ ነው ።

መዋቅራዊ ችግሮች

ዛሬ በአብዮታችን ሂደት የተከሰቱት
ችግሮች መዋቅራዊ መንስዔ አላቸው የም
ንለው በኤኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ የሚታ
ዩትን ችግሮች በሚመለከት ነው ። ከሁሉ
በፊት መታወቅ ያለበት ሥራ አጥነትና
ዝሙት አዳሪነት የኢትዮጵያ አብዮት ያመ
ጣቸው ሳይሆን ከቀድሞው ሥርዓት የወረ
ሳቸው ማኅበራዊ ጠንቆች ናቸው ። ይሁንና
ይህ ማለት አብዮቱ እነዚህን ችግሮች
ማስወገድ አይገባውም ማለት አይደለም ።
ነገር ግን የነዚህ ማኅበራዊ ችግሮች ዋነኛው
መፍትሔ የሥራ ዕድል መስጠት በመሆኑና
ይህም በተራው የምርት ኃይሎችን ዕድገት
የሚጠይቅ በመሆኑ ከመቅፅበት የሚፈታ
ችግር አይሆንም ። ከቀድሞ የወረስናቸ
ውና በዘላቂው የምርት ኃይሎች ዕድገት
የሚፈቱ በመሆናቸው መዋቅራዊ ናቸው
እንላለን ። ከአሁን በፊት እንዳየነው
በአብዮቱ ማግሥት ወይም ወዲያውኑ
የሚታየው ከፍተኛ የምርት ኃይሎች
ዕድገት ሳይሆን እንዲያውም አን
ጻራዊ የሆነ ድቀትና የኢኮኖሚ ችግር
ሊሆን ስለሚችል ይህም በአብዮታችን
ማግሥት መኖሩ ብዙም ሊያስገርመን አይ
ገባም ። የሩሲያ አብዮት ከስድሳ ዓመት
በላይ ዕድሜ ያለው ሲሆን በሶቪዬት ኅብ
ረት ሥራ አጥነት ከተወገደ ግን ሃምሳ
ዓመት ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው ።

በሌላ በኩል የኑሮ ውድነትን ወይም
የሸቀጦች ዋጋ መጨመር ስንመለከት አ
ሁንም መንስዔያቸው መዋቅራዊ ነው እንላ
ለን።የእህልና የዕቃዎች መወደድ የተያያዙ
ጉዳዮች ናቸው።በአንድ በኩል የኢትዮጵያ
ኢኮኖሚ ገና በዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊ
ስት ገበያና የሥራ ክፍፍል ውስጥ ያለ
በመሆኑ በዚህ ገበያ ውስጥ የሚኖረው
የዋጋ መዋዥቅና የኢኮኖሚ ቀውስ በሀገራ
ችን ላይ በቀጥታ ያንጸባርቃል ። በዚህ
መሠረት ባለፉት ዓመታት በተፈጠረው

Digitized by Google

ከፍተኛ የንዳጅ ዋጋ መናርና ወደውጭ የምንልካቸው ዕቃዎች ዋጋ እየቀነሰ መም ጣት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሳሳቢ ገጽታ እያሳየ ነው ። ባጭሩ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ገበያ ወይም ከዓለም አቀፍ «ነፃ» ገበያ የምንገዛው ዕቃ መወደድና የንዳጅ ዋጋ መጨመር በአንድ በኩል እኛ ለዚሁ ገበያ የምናቀርበው ዕቃ ዋጋ መቀነስ ከሌላ በኩል ተደምረው የሚያመጡት ውጤት በአገር ቤት የፋብሪካ ምርቶች ሆነ ከውጭ የሚመጡት ዕቃዎች ዋጋ መጨመርን ሲሆን ይኸውም የኑሮ ውድነትን ያስከት ላል።[28] ታዲያ አሁንም ይህን የመሰለው ችግር በቅፅበት የማይፈታና መዋቅራዊም ነው የምንለው ገና በአብዮቱ ዕድገት ቀስ በቀስ የሚፈታ በመሆኑ ነው ።

አሁንም የእህልና የአንዳንድ ሌላ ዕቃ ዎች ዋጋ መወደድ መንስዔ መዋቅራዊ የሚሆነው በዘላቂው የሚፈታ ውስብስብ ችግር በመሆኑ ነው ። በአንድ በኩል ገበሬው የምርቱ ባለቤት በመሆኑ ቀድሞ ከጉ ሮሮው ተነጥቆ ወደገበያ ይደርስ የነበረው የእህል መጠን ቀንሷል ። ማለትም ገበሬው በሚያመርተው መጠን ለፍጆታ የሚያው ለው በመጨመሩ ለገበያ የሚቀርበው የእ ህል መጠን ሊቀንስ ችሏል ። በዚህም ሳቢያ የእህል ዋጋ ጨምሯል ። ይህን የመሰለው ችግር የሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት ከተካሄደ በኋላ እ.ኤ.አ. እስከ 1928 ተስፋፍቶ ነበር ፤ በዚህ ጊዜ ለገበያ የሚቀርበው የእህል መጠን 50% በመቀነሱ የሶቪዬት መንግ ሥት ራሺን አወጀ ነበር ።

በገበሬው በኩል ያለው መዋቅራዊ ችግር ይህ ብቻ አይደለም ። ገበሬው የምርት ባለቤት በመሆኑ የመግዛት ችሎታው በጣም ከፍ ብሏል ። ይህ መሆኑ ለኢንዱስትሪ ምርት ዕድገት ትልቅ ፀጋ ነበር ። ምክንያ ቱም የሕዝብ የመግዛት ችሎታ ማደግ የገበያ መስፋት ዋስትና ስለሆነ ለኢንዱ ስትሪ ምርት ማደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ። ይሁንና በአንድ ብሔራዊ ኢኮኖሚ የሕዝብ የመግዛት ችሎታና የዚ ህም መግለጫ በሆነው የፍላጐት መጨመር በተመጣጣኝ የዕቃዎች መጠን ካልተደገፈ የዋጋ መናር ይከተላል ። መሬት ለአራሹ በመሆኑ የመግዛት ችሎታው ያደገው ገበሬ ተመጣጣኝ በሆነ የዕቃዎች መጠን ገበያ ላይ ስላልተገናኘ የሚከተለው ነገር የግዴታ የዋጋ መናር ይሆናል ። ይህም ሁኔታ አም ራችን ከሸማች ከሚያገናኘው ነጋዴ የተ ሰወረ ባለመሆኑ አጋጣሚውን በመጠቀም የሸቀጦችን ዋጋ በጣም ከፍ በማድረግ የዕ ቃዎች እጥረትና መጥፋት እንዳለ በማስ መሰል ሁኔታውን ያባብሰዋል ።

አሁንም ይህን የመሰለው በገጠርና በከተማ መሃል ያለውን የተፋለሰ ሁኔታ ለማስተካከል ዘላቂ መፍትሔ የሸማቾችን የኅብረት ሥራ ማኅበራት በገጠርና በከተማ ማስፋፋትና ማጠናከር እንዲሁም መንግ ሥት በማከፋፈልና በስርጭት ተግባር ያለ ውን ድርሻ ከፍ በማድረግ ገበያን መቆጣ ጠር ሲችል ነው ። በሌላ አነጋገር ይህ ችግር መዋቅራዊ የሆነው ዘላቂ መፍትሔ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትና የንብረት ይዞታ ሲሰፍን ነው ማለት ነው ። ይሁንና አብዮቱ እስከዛውም ድረስ ቢሆን ይሽንኑ ችግር ለመቋቋም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆነ በዚሁ በማስፋፋትና በምርት ስርጭት ዘርፍ የተሰማሩት መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እያደጉ መሄዳቸውን ያሳያል ። ዛሬ የአገር ውስጥ ማስፋ ፊያ ድርጅት ፣ የእህል ሰብል ገበያ ድር ጅት ፣ በአገር ውስጥ ንግድ የጅምላና የች ርቻሮ ኮርፖሬሽን እንዲሁም የገበሬውና የከነማ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበ ራት እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ በመሆናቸው ይህንኑ የዕቃዎች ርስጭትና የማከፋፈል ችግር በመጠኑም ቢሆን ለማቃለል እንደ ቻሉ እናያለን ። ይሁንና በዚህ ረገድ የሚ ገኘው ውጤት የተሟላ እንዲሆን ትዕ ግሥትና ከፍተኛ ታታሪነት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ። እንግዲህ እስካሁን ያየነው በችግሮቻችን መዋቅራዊ መንስዔ በኩል ያለውን ሲሆን ሁለተኛውን እንዲሁ ባጭሩ እንመለከተዋለን ።

ከመንግሥት ባህርይና ተግባር የሚፈልቁ ችግሮች

ሁለተኛው የወቅቱ ችግሮቻችን መን ስዔ ከመንግሥት ባህርይና ሚና መቀየር የሚመነጭ ነው ። ከታሪክ ከታዩ የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ሌላ ለምሳሌ በህንድና በቻ ይና ፣ ከሶሻሊስት መንግሥት በስተቀር የተቀሩት መንግሥታት ሁሉ ያላቸው ዋነኛ

Digitized by Google

ባህርይና ተቀዳሚ ዓላማ ፖለቲካዊ ነው ።
ዛሬም ቢሆን ፣ በምዕራብ አውሮፓ ካፒታ
ሊስት አገሮች ያለው መንግሥታዊ ሞና
ፖል ካፒታሊዝም በአማካይ ከጠቅላላ ብሔ
ራዊ ምርት ከ20% በላይ አያበረክትም ።
ከዚህም በላይ ያለው የቡርዧው መንግሥት
ከኤኮኖሚ አመራሩ ተካፋይ የሚሆነው
ያሉት ሞኖፖሊስቶች በተባለው የኢኮኖሚ
ዘርፍ ተካፋይ ለመሆን ፈቃደኛ ባለመሆና
ቸው የተነሳ ሲሆን መንግሥቱም እንዳይተ
ወው የራሱን (የቡርዧውን) ህልውና ሊያ
ጠፋ የሚችል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ
ችግር ስለሚያስከትልበት ነው ። ስለሆነም
የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም መን
ግሥት እንኳ ያለው ተግባር በመሠረቱ
ፖለቲካዊ እንደሆነ ግልጽ ነው ።

የሶሻሊስት መንግሥት ግን ከተቀሩት
ሁሉ የሚለይበት ባህርይ የተወሰነ የአገር
ብሔራዊ ኢኮኖሚ ባለቤትና መሪም መሆኑ
ሲሆን ይህም ከሽግግሩ ወቅት የመጀመሪያ
ጊዜ አንስቶ እያደገ የሚሄድ ጉዳይ ነው ።
እንዲያውም በሥልጣን ላይ ያለው የሶሻ
ሊስት መንግሥት በኢኮኖሚው አመራር
ላይ ያለው ሚና እየጨመረ መሄድ የዚህኑ
መንግሥት መጠናከር ይገልጻል ። በዚህ
መሠረት አንድ የሶሻሊስት መንግሥትና
ወደዚሁም ደረጃ ለመድረስ በሽግግር ላይ
ያለ መንግሥት አምራች ፣ አከፋፋይና
ከፍተኛ የፍጆታውን ክፍል የያዘ እንደሆነ
ሊታወቅ ይገባል ። የሶሻሊስት መንግሥ
ትም በቡርዧው ሥርዓት የሚታየውን የም
ርት ሥርዓት አልበኝነት ለመዋጋትና ጨ
ርሶም ለማስወገድ የሚወስደው የመጀመ
ሪያ እርምጃ የግል ካፒታሊስቶችን ይዞታ
በመውረስ የመንግሥት ወይም የመላው
ሕዝብ ንብረት ማድረግ ነው ። በሰው ኃብት
አያያዙና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በማዕከላዊ
ዕቅድ ለመምራት የሚደረገው ጥረት የሚ
ጀምረው የመንግሥት ንብረትን በመፍጠር
ይሆናል ማለት ነው ።

ታዲያ ይህን ክቡር ዓላማ ዕውን
ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ብዙ የማይ
ፈለጉ ነገሮችና ችግሮች ይነሳሉ ። አድሎ ፣
የሥራ ግድየለሽነት ፣ የንብረት ማባከንና
ዘረፋ ገነው ይወጣሉ ። እንደሚታወቀው
ሁሉ ከነዚህ ችግሮች ውስጥ ከአድልዎ
በስተቀር የተቀሩት ችግሮች በግል የካፒ
ታሊስት ይዞታ ተግባራዊ ለማድረግ አስ
ቸጋሪ ናቸው ፣ እርግጥ በቡርዧው የግል
ይዞታ ወይም ድርጅት ቡርዧው ታማኝ
አገልጋዩን ከቤተ ዘመድ ቢያገኝ የሚመርጥ
በመሆኑ ችግሩ መኖሩ አይቀርም ።

ይሁንና በሌላ በኩል የካፒታሊስት
ኢኮኖሚ የፍልስፍና መሠረቱን ከተመለከ
ትንና በተግባርም እንደሚታየው በአንድ
የግል ድርጅት ውስጥ የሥራ ግድየለሽነት ፣
ብኩንነትንና ዘረፋ እንዲህ በቀላሉ ሊኖሩ
የሚችሉ አይደሉም ። ምክንያቱም የድር
ጅቱ ህልውና ወይም ማትረፍና መክሰሩ
በቀጥታ ከባለቤቱ ህልውና ጋር የተሳሰሩ
ናቸው ። የግለሰብ ቡርዧው ደህንነት ፣
ብልጽግናና ዕድገት በቀጥታ ከድርጅቱ
ዕድገትና ህልውና ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣
ቡርዧው (ባለቤቱ) የድርጅቱን ደህንነት
ከምንምን ነገር በላይ የሚመለከተው ጉዳይ
ነው ። ይህም በመሆኑ ነው በተወሰነ የኅብ
ረተሰብ ታሪክ የቡርዧው አመለካከትና
ፍልስፍና ግለሰበኝነትን ታላቅ ዕውነት
እንደሆነ የሚያስተምረው ። በአንድ የግል
ድርጅት ዘግይቶ መምጣት ወይም ከሥራ
መቅረት ፣ በሥራ ላይ የሚታይ ግድየሽነት ፣
በንብረት አያያዝ የሚታይ ብኩንነት ሠራ
ተኛውን ሆነ ተቀጣሪ አሠሪውን ከሥራ
የሚያባርራቸው ጉዳይ ነው ። በካፒታሊስቱ
የሥራ ሕግ የሥራ ዋስትና የለምና የመስ
ናበት ጉዳይ ለቡርዧው አፍታ የሚፈጅበት
አይደለም ። ሌላው ቀርቶ የድርጅቱ አስተ
ዳደር አስፈላጊውን ትርፍ ካላስገኘ የሚባ
ረር ሲሆን የወዛደሩም የሥራ ዋስትና የድ
ርጅቱ ማትረፍ ብቻ ነው ። አንዳንዴም
የወዛደሩ የሥራ ዋስትና ማጣት ካፒታሊ
ዝም መሆኑን ባለመረዳት ወዛደሩ ሥራ
ከመጀመሩ በፊት ለድርጅቱ ማትረፍ (ለባ
ለቤቱ) ፀሎት የሚያደርስበት ቦታ ሁሉ
አለ ።

ይሁንና የሰፊው ሕዝብ ወይም የሠርቶ
አደሩ መንግሥት በሚመጣበት የመጀመ
ሪያ ጊዜ አካባቢ ብዙ ችግር መኖሩ ይታወ
ቃል ። በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥት ራሱ
በኢኮኖሚው አመራር ወይም በባለቤትነት
መሥራት ሲጀምር ባለማወቅ ወይም ለሥ
ራው እንግዳ በመሆኑ ብቻ አያሌ ችግሮች
ይነሳሉ ። ይህ መቼም ሊታለፍ የማይችል
ጉዳይ ነው ። ከዚህም የሰለጠነ የአስተዳደር
ባለሙያ እጥረት በመኖሩም ችግሩን ያባብ
ሰዋል ።

Digitized by Google

በሌላ በኩል መንግሥት በቁጥጥሩ ሥር ያዋላቸውን ድርጅቶች በማዕከላዊነት ሂሳብ ለመያዝና ለመቆጣጠር ከፍተኛ መሰናዶ ይጠይቃል ። አሁንም ከልምድ አለመኖርና ከባለሙያ ዕጥረት በዚህ ረገድ ከፍተኛ ችግር መኖሩ አይቀርም ። የግል ካፒታሊስቱን ቀደም ሲል የድርጅቱን ደህንነት ለመቆጣጠር በሚያስችለው መንገድ የዕለት ሂሳቡን አስልቶ በመያዝ የሚወስደውን እርምጃ ትክክለኛነት በአዲሱ የመንግሥት ይዞታ ለማምጣት ብዙ ችግርና ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ ነው ።

መንግሥት ኢኮኖሚውን መምራት በጀመረበት ማግሥት ያለውን ስንመለከት ከፍተኛ የአሠሪና ሠራተኛ ችግር እንዳለ እናያለን ። አሠሪው ወገን በአንድ በኩል ሲታይ ከድርጅቱ ህልውና ጋር ያለው ዝምድና ቀጥተኛ ባለመሆኑ ፣ በተለወጠው ሁኔታና ባለው የፖለቲካ ሁኔታ እምነት ስለማይሰማው ፣ ለአብዮቱ ያለው ወገናዊነት ዝቅተኛ በመሆኑ በሥራው የሚያሳየው ለዘብተኛነት የድርጅቱን ህልውና ክፉኛ ይጐዳዋል ። ድርጅቱ ቢከስር ወይም ገቢው ቢቀንስ የማይደርስብኝ «ግፋ ቢል መባረር» ነው በማለት ያስባል ። ምናልባትም አሠሪው የድርጅቱን መዳከምና የአብዮቱን ጉዳት የሚሻ ከሆነ ተልዕኮውን የሚፈጽምበት መንገድ አገኘ ማለት ነው ።

ችግሩን በሠራተኛውም ወገን መመልከቱ ተገቢ ነው ። የሠራተኛው ንቃተ ሕሊና ዝቅተኛ በሆነበት አካባቢ ወይም በቀድሞው የቡርዧ ይዞታ ከፍተኛ የሥራ ዲሲፕሊን ባልነበረበት አካባቢ ሁሉ ራሱን ተቆጣጥሮ ለሕዝብ ጥቅም አስቦ መስራት በቶሎ ስለማይለመድ ይኸ ሁኔታ የመንግሥት ይዞታን ያዳክማል ። በተለይም የተዘበራረቀ የፖለቲካ አሠራርና በብዙ ማዕከል አመራር ያገኝ የነበረው የሠራተኛው መደብ በተለያዩ ምክንያቶች ከአሠሪው ወገን በመጋጨት ለምርት መዳከም አስተዋጽኦ አድርጓል ። የፀረ አብዮትም ቅስቀሳ መሣሪያና መሳለቂያ ሁኗል ። በዚህ ሁኔታ ላይ የአሠሪው ለዘብተኛነት ተጨምሮበት ከሥራ መቅረትና ግድየለሽነት አንዳንድ ቦታ በሠራተኛው መሃል እንደነውር መቆጠሩ ቀርቶ የንቁነት መግለጫ ጭምር ተደርጐ ሲታይ እንደነበር ሁላችንም የምናስታውሰው ጉዳይ ነው ።

ከሠርቶ አደሩ ፓርቲ አለመኖር ጋር የተያያዙ ችግሮች

በመጨረሻም እስካሁን በየደረጃው ላየናቸው ችግሮች ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ምክንያት እንዳለ ማስታወስ ተገቢ ነው። ይኸውም መሠረታዊ ምክንያት የምንለው የኢትዮጵያ አብዮት ገና የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አመራር ያልተቀዳጀ መሆኑ ነው። ይህ የአብዮታችን ትልቁ ደካማ ጐን ነው ለማለት ይቻላል ። እርግጥ አብዮታችን በየጊዜው ያስመዘገባቸው ድሎች ያለ ሠርቶ አደሩ ፓርቲ አመራር መሆኑ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብና ኮሚዩኒስቶች ከፍተኛ ተጋድሎ ይመሰክራል ።

ይሁንና አብዮታችን በጀመረበት ጊዜ ሆነ ከዚያም በኋላ ከነበረው ወቅት አሁን በደረሰበት ደረጃ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ አለመኖር ለብዙ ችግሮች ምክንያት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል ። በዚህ ረገድ ብዙ ነገሮች ማተት የሚቻል ቢሆንም ከሁሉም በላይ ጐልቶ የሚታየውን በካድሬ እጥረትና ጥራት በኩል ያለውን ችግር መውሰዱ ይበቃል ።

እንደሚታወቀው ሁሉ በማርክሲዝም ሌኒንዝም የአብዮት ቲዎሪ በየጊዜው የኀይል ወይም የመደብ አሰላለፍና ሽግሽግ ግምገማ ይደረጋል። ይህም ተግባር፣ ነባራዊ፣ ታሪካዊና ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ይከናወናል። በዚህ መሠረት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለው ቅራኔ በቅጡ ከተገመገመ በኋላ ባለው ሥርዓት የትኞቹ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች በሚካሄደው የመደብ ትግልና አብዮት ባንድነት ወይም በተፃራሪነት እንደቆሙ አሰላለፋቸውን አስቀድሞ ለማየት ይቻላል ። በተለመደው አጭር አቀራረብ ወዳጅና ጠላትን መለየት ማለት ነው ። ይሁንና ይህ ተግባር መደቦችንና የተለያዩ ኅብረተሰብ ክፍሎችን በአጠቃላይ በመውሰድ የሚደረግ ግምገማ እንጂ ዝርዝር የግለሰቦች ፍላጐትና ባህርይ ጥናት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት ።

በሌላ አነጋገር አጠቃላይ በሆነው በመደብ ደረጃ አብዮተኛና ፀረ-አብዮተኛ ወይም ወዳጅና ጠላት ብሎ የማስቀመጡ ተግባር

Digitized by Google

በቀላሉ ሊደረግ ይችላል ። ነገር ግን አንድ
ወይም ጥቂት ግለሰቦችን አብዮተኛና ፀረ-
አብዮተኛ ብሎ በቂና አስተማማኝ ፍርድ
ለመስጠት ትዕግሥት የተሞላበት በቂ
ጥናትን ይጠይቃል ። የሠርቶ አደሩ
ፓርቲ በሌለበት ጊዜና ቦታ ደግሞ ይህ
ተግባር ምንኛ አስቸጋሪ እንደሚሆን ከአብ
ዮታችን ታሪክ በላይ ምስክር አናገኝም ።

መለስ ብለን ጊ.ወ.አ. ደርግ ስልጣን
ለመያዝ ከተነሳበት ጊዜ አንስቶ ከዚያም
በኋላ የነበረውን ሁኔታ ብንመለከት አንዱ
ትልቁ ችግር ስለግለሰቦች በቂ ዕውቀት
ወይም ጥናት አለመኖር ሲሆን ይኸውም
በቀጥታ ከሠርቶ አደሩ ፓርቲ አለመኖር
የሚመነጭ ነው ። በዚህም የተነሳ ጊ.ወ.
አ. ደርግ በየጊዜው የሚወስደውን እርምጃ
ተግባራዊ ለማድረግ አስፈጻሚ ኃይል ወይም
ድርጅት አለመኖሩ ከፍተኛ ችግር ሁኖ
በት ቆይቷል ። እንደሚታወሰው ከሥልጣን
የተወገዱትን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥ
ልጣኖች ለመተካት እንኳ ራሱን የቻለ
ችግር ነበር ። በመደብ ደረጃ ጊ.ወ.አ.
ደርግ ወዳጁን ከጠላት ለመለየት ችግር
ገጥሞት አልነበረም ። ነገር ግን በግለሰብ
ደረጃ አብዮተኛን ከፀረ አብዮተኛ ወይም
ተራማጁን ከአድሀሪው ለመለየት መነሻ
የሚሆን ነገር ለማግኘት በጊዜው ማስቸገሩ
ግልጽ ነው ። በፈላጭ ቆራጭ ፊውዳል
ሥርዓት በነበረው በዝቅተኛ የፖለቲካ
ባህል እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅት አለመ
ኖር ለጊ.ወ.አ. ደርግ ሥልጣን መያዝ
አንዱ ምክንያት ቢሆንም ይሄው ሁኔታ ራሱ
ጊ.ወ.አ.ደርግ የሚያቀርባቸውን ግለሰቦች
በቅጡ ለማወቅ ዕድል ሳይሰጠው ቀርቷል።

ስለሆነም በጊዜው ጊ.ወ.አ.ደርግ ከወ
ሰዳቸው ጥቂት የፖለቲካ ውሳኔዎች አንዱ
በአገር ቤትና በስደት ለሚገኙ ተራማጆች
ጥሪ በማድረግ ለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ
ነበር ። እንደገና ስለግለሰቦችና በጊዜው
ሊኖር የሚችል አንድ ነባራዊ መለኪያ
የፊውዳሉን ሥርዓት መቃወም ስለነበር
በዚሁ ፀረ ፊውዳልና ዲሞክራሲያዊ አቋም
መሠረት ግለሰቦችን ለመገምገም ሙከራ
ተደርጐ እንደነበር ሁላችንም የምናስታ
ውሰው ጉዳይ ነው ። በዚህም መሠረት
በኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ተጨቁነው የታሠሩ
የተጋዙ ጡረታ የወጡ ወዘተ . . . ግለሰቦችን
በማስጠጋት አንዳንዶም ከፍተኛ ኃላፊነት
ሳይቀር የተሰጣቸው ግለሰቦች እንደነ
በሩ ይታወሳል ። የኃይለ ሥላሴን አገ
ዛዝ ይታገሉ ከነበሩት ዲሞክራሲያዊ
ንቅናቄዎች አንዱና በጊዜው ጐልቶ የሚ
ታየው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ስለነበር
ጊ.ወ.አ.ደርግ ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ
ነት ከሾማቸው መሃል የዚሁ የተማሪዎች
እንቅስቃሴ መሪዎች እንደነበሩ ይታወቃል።
በኋላም ቢሆን የአብዮታችንን የፖለቲካ
አመራር ለማቃናት በቡድንና በግለሰብ
ደረጃ በከፍተኛ አመራር እንዲቀመጡ ያደ
ረጋቸው ግለሰቦች እንዲሁ በአገር ውስጥና
በውጭ አገር የነበሩ የተማሪ ማኅበራት
መሪዎች ነበሩ ። በየጊዜው የከዱና የኮበ
ለሉ ሚኒስትሮች ቋሚ ተጠሪዎች አውራጃ
አስተዳዳሪዎች ወዘተ... ሁሉ በአንድ ወቅት፥
ተራማጅ ተብለው በኃላፊነት የተቀመጡ
እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ
ነው ። እነዚህም ግለሰቦች በጊዜው ተጠ
ቁመው በኃላፊነት ከተቀመጡ በኋላ አንዳ
ንዶቹ በተለያዩ ምክንያቶች በመንሸራተትና
በማፈግፈግ ከአብዮቱ ሰፈር ተባረዋል ።

ታዲያ ይህን ሁሉ ጠቅለል አድርገን
ስንመለከተው በየጊዜው የቢሮክራሲ አሻ
ጥር ፣ ብኩንነትና ምዝበራ እንዲሁም የአ
ድልዎ አሠራር መኖራቸው ብዙ ሊገርመን
አይችልም ። ምክንያቱም ቀደም ሲል በነ
በረው ሁኔታና በኋላም በተፋፋመው የመ
ደብ ትግል ተፈትነው የመጡ የሠርቶ አደሩ
ፓርቲ አባላት ቢኖሩ ኖሮ ከላይ የተመለከት
ናቸው ችግሮች እምብዛም ሊፈጠሩ ባልቻሉ
ነበር ።

አሁንም ቢሆን በየቦታው ለሚታዩ
ችግሮች አንዱና አስተማማኝ መፍትሄው
የሠርቶ አደሩ ፓርቲ ህልውና ማግኘት እን
ደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልጋል ። ገነው የሚ
ታዩት የፖለቲካ አሻጥር ብኩንነት ምዝ
በራ እንዲሁም አድልዎ በዘላቂው
ሲታይ መፍትሄው የኃላፊዎች መቀያየርና
ተገቢ ቅጣት መስጠት ብቻ ሳይሆን የሠ
ርቶ አደሩ ፓርቲ በየደረጃው አባላቱን
በማስቀመጥ ሁኔታውን በመቆጣጠር አመ
ራር መስጠት መቻል እንደሆነ ልንገነዘብ
ያሻል ። እርግጥ የተባሉትን ችግሮች ለመ
ቋቋም ጊዜያዊና ገቺ እርምጃዎች ከአሁኑ
ሊወሰዱ አይገባም ማለት አይደለም ። በየ
ጊዜው እነዚህን ችግሮች ለመቋቋም
በማሰብ አዲስ ኃላፊዎች የተሾሙ

Digitized by Google

ሲሆን እንደሁኔታውም ተገቢ እርምጃ የተወሰደባቸው እንዳሉ ከማናችንም የተወሰረ አይደለም ። ይሁንና ዘላቂው ድርጅታዊ መፍትሄ አብዮታችን የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አመራር እንዲቀዳጅ ማድረግ በመሆኑ የኢሠፓአኮን ተልዕኮ ማሳካት አንገብጋቢ የወቅቱ ጥያቄ እንደሆነ በሚገባ መታወቅ አለበት ። ከዚሁ ጋር አብሮ ሊታይ የሚገባው ሌላ ጉዳይ እስካሁን ያሉትን የአብዮታችንን ችግሮችና ነባራዊ መንስዔዎች በቅጡ ከተረዳን ሰፊው ሕዝብ በየደረጃው የሚያደርገውን ተሳትፎ ከፍ ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ እንገነዘባለን ። በመሆኑም ዛሬ ሰፊው ሕዝብ ሃብትና ንብረቱን የሚቀጣ ጠርበትን የመዝባሪዎችና የአባካኞችን ጥፋት የሚገታበት የሕዝባዊ ቁጥጥር መዋቅር መዘርጋት አማራጭ የማይገኝለት አብዮታዊ ተግባር እንደሆነ በሚገባ ተረጋግጧል ። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሠራተኛውን ቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋት ቅድመ ዝግጅቱ የተከናወነ መሆኑ ለአብዮቱ እድገትና ጥንካሬ ቋሚ ምስክር ነው ።

የት ደርሰናል?-አጭር ማጠቃለያ

እስካሁን በዚህ ጽሑፍ የተለያዩ ክፍሎች እንደታየው ወደማጠቃለያ ሃሳብ የሚያመሩ ወይም ዛሬ አብዮታችን የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ሊጠቁሙ የሚችሉ የጽንስ ሃሳብና የተጨባጭ ሁኔታ መለኪያዎች ተገምግመዋል ። ምናልባትም አንባቢ እነዚህን የጽንስ ሃሳብ መነሻዎች መሠረት በማድረግ በዚህ ማጠቃለያ ሊቀርቡ ከሚችሉ አጫጭር ግምቶች የተሻለና ሰፊ ግምገማ ለራሱ ሊወስድ ይችላል ። ለማንኛውም ዋነኞቹን ነጥቦች ባጭሩ እናጠቃልላቸዋለን ።

ቀደም ሲል እንዳየነው የአብዮታችን ›ድገት ነባራዊ መለኪያዎች ሁለት እንደሆኑ ተመልክቷል ። አንደኛው አብዮታችን ባለው ሁለንተናዊ ዓለም አቀፍ ባህርይ መሠረት ሌኒን የሚያቀርባቸው ሶስት ደረጃዎች ወይም መለኪያዎች ናቸው ። ሁለተኛው መለኪያ ደግሞ አ ብዮታችን ከጀመረበት ተጨባጭ ሁኔታና ብሔራዊ ልዩነት መሠረት የተነደፈው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ነው ። እነዚህም ሁለት መለኪያዎች ነባራዊና ታሪካዊ ሲሆኑ ዞር ዞር ለኛ የሚናራቸው አገልግሎት የአብዮታችንን ዕድገት ለመገምገም በመሆኑ በአንድነት ሊታዩ ይችላሉ ።

ከሌኒን ሶስት ደረጃዎች ወይም መለኪያዎች በመነሳት ዛሬ አብዮታችን የት እንደ ደረሰ ለማገናዘብ ስንሞክር የግዴታ የአብዮቱን ልዩና ተጨባጭ ሁኔታ ከመረዳት መጀመር አስፈላጊ ይሆናል ። ይሄውም በተደጋጋሚ እንደሚነገረውና በዚህም ጽሑፍ እንደተጠቀመው የኢትዮጵያ አብዮት እስካሁን ድረስ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አመራር አልተቀዳጀም ፣ ይህም ለአብዮቱ ልዩ ባህርይ የሚሰጠው ሲሆን ደካማ ጐኑም እንደሆነ ተነግሯል። እንግዲህ የሌኒንን ደረጃዎች ወይም መለኪያዎች በአብዮታችን ሂደት በቀጥታ ብናውለው ትንሽ ሊያደናግረን ይችላል ። በመጀመሪያ ደረጃ ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በሠርቶ አደሩ ፓርቲ አማካኝነት የመንግሥት ሥልጣን አልያዘም ። አሁንም በአብዮቱ ጠላቶች ላይ ሙሉ በሙሉ ድል ያልተቀዳጀ እንደሆነ ይታወቃል ። እንግዲህ የኢትዮጵያ አብዮት በሌኒን መለኪያዎች መሠረትገና ሁለቱን የመጀመሪያ ደረጃዎች በሙሉ እንዳላጠናቀቀ ይታያል ።

ይሁንና ይህንኑ ጉዳይ ይበልጥ ስንመረምረው የኢትዮጵያ አብዮት ልዩና ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚመልሰው ለመገንዘብ ይቻላል ። ከሁሉም በላይ ይህንን ጉዳይ ግልጽ የሚያደርገው የጊ.ወ.አ.ደርግን ባህርይ በሚገባ ከተረዳን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳ እስከ ዛሬ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አመራር ባይቀዳጅም አብዮቱ እስካሁን ሲመራው የቆየው መንግሥት ማለት ጊ.ወ.አ. ደርግ ያከናወናቸውን ተግባራት ሁሉ ስንመለከት የፓርቲ ምትክ ሆኖ ሲሠራ እንደቆየ ለመገመት ይቻላል ። ስለሆነም የሰፊውን ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄን በሚመለከት ረገድ እስካሁን በጊ.ወ.አ.ደርግ አብዮታዊ አመራር ሙክልና እንዳለውና በዚህም የተነሳ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሲያስከብር ቆይቷል ። ይህም በመሆኑ ከአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወደ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚደረገው ሽግግር በመሠረቱ አሁን ባለው መንግሥት የመደብ ባህርይ ላይ ለውጥ (Class character of the sate) የሚያመለክት ሳይሆን የመንግሥት መዋ

ቅራዊ አሠራር ለውጥ ነው ። ዛሬ ሰፊው
ሕዝብ በአብዮታዊ መንግሥት ወይም ጊ.
ወ. አ. ደርግ ያለው የሥልጣን ውክልና ነገ
በሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ የሠ
ርቶ አደሩ ፓርቲና የሕዝባዊ ሸንጎዎች
ይኖሩታል ማለት ነው ። እንግዲህ በዚህ
አቀራረባችን መሠረት ምንም እንኳ ዛሬ
የኢትዮጵያ አብዮት የሠርቶ አደሩን ፓርቲ
አመራር ባይቀዳጅም የሰፊውን ሕዝብ ጥ
ቅም የሚያስከብር መንግሥት ስላለ በአንድ
መልኩ ሰፊው ሕዝብ ባለው አሠራር የመን
ግሥት ሥልጣን ተካፋይ ወይም አብዮታዊ
ውክልና (Revolutionary Representation)
እንዳለው ሐቅ ነው ። በመሆኑም በሌኒን
የመጀመሪያ መለኪያ መሠረት የኢትዮጵያ
አብዮት በአንድ መልኩ ይህንኑ ደረጃ
ያሟላ እንደሆነ ለማየት ይቻላል ። ቀደም
ሲል እንደተጠቆመው ከኢሠፓአኮ ወደ ፓር
ቲ ምስረታ በሚደረገው ሽግግር መሃል ሌላ
ምንም ነገር የሌለ በመሆኑ የኢትዮጵያ
አብዮት ይህንኑ የሌኒን የመጀመሪያ ደረጃ
ለማጠናቀቅ ዛሬ በዋዜማው ላይ እንደሚ
ገኝ እንገነዘባለን ።

በሌላ በኩል አብዮታችን በጠላት ላይ
የተጎናጸፋቸው ድሎች እንዲሁ በሌኒን
ሁለተኛ ደረጃ ማገባደድ ረገድ ምን ያህል
እንደተራመድን ለማየት ያስችለናል ። በመ
ሃል አገር ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በተ
ለያየ መልክ በየጊዜው የተከሰቱት ፀረ አብ
ዮት ኃይሎች በሚገባ በቁጥጥር ሥር ውለ
ዋል ። ጨርሶ ጠፍተዋል ባይባልም ዛሬ
የኢህአፓ የመኢሶን የኢድህ ወዘተ... ፀረ
አብዮት እንቅስቃሴ አብዮታችንን በስጋት
ላይ የሚጥለው አይደለም ። ስለሆነም አብ
ዮታችንና ሰፊው ሕዝብ የሥልጣን ተቀና
ቃኞቹን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ያደረገው
ጥረት ደህና ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማየት
ይቻላል ። ይሁንና ፀረ አብዮተኛ ተገንጣይ
እንቅስቃሴዎች አሁንም ቢሆን ሙሉ
በሙሉ በቁጥጥር ሥር አለመዋላቸው አብ
ዮታችን ይህንኑ የሌኒን ሁለተኛ የዕድገት
ደረጃ ለማጠናቀቅ የሚቀረውን መጠን
ይጠቁምልናል ።

በሌላ በኩል አብዮታችን በነበረው
የርስ በርስና ብሔራዊ ጦርነት የተጎዳውን
ኢኮኖሚ ለማንሰራራት ጥረቱን በመጀመሩ
ሶስተኛውን የዕድገት ደረጃ የሚወክለውን
ተግባር እንደተያያዘው እንመለከታለን ።
በዚህ ረገድ የደቀቀው ኢኮኖሚያችን እንዲ
ያንሰራራ አብዮታዊ ዘመቻ እየተካሄደ መሆ
ኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው ። የወረስናቸውን
የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች
በሚገባ ለማንቀሳቀስ ፣ መሬት ላራሹ የሆ
ነለትን ገበሬ ምርት ለማሳደግ ከፍተኛ
የኢኮኖሚ ዘመቻ በማካሄድ ላይ እንገኛ
ለን ። የተገኘውም ውጤት የሚያበረታ
ሲሆን የምርት ኃይሎችን የተፋጠነ ዕድገት
ለማስገኘት አዲስ የንብረት ይዞታና የም
ርት ግንኙነት በእርግጥ ዋስትና እንደሆኑ
ለማየት ተችሏል ። ዛሬ የገበሬው የመግዛት
ችሎታ ከፍ ማለቱ ለኢንዱስትሪ ምርት
ከፍተኛ ገበያ ሲሆን ለጥሪት ክምችትም
ትልቅ ምንጭ ከፍቷል ።

ዛሬ የተያያዝነው የኢኮኖሚ ግንባታ
በሌኒን የሶስተኛው ደረጃ አገላለጽ «እኛው
ራሳችን ያሳለፍናቸውን ውሳኔዎች ፣ በሕግ
የደነገግናቸውን ፣ የተወያየንባቸውን ሁሉ
ተግባራዊ ለማድረግ ከባድና ውስብስብ
ተግባር በማከናወን ላይ እንገኛለን» ።

እንግዲህ እስካሁን ባየነው በነዚህ ሁለ
ንተናዊ የሌኒን ደረጃዎች ወይም መለኪያዎ
ች መሠረት የኢትዮጵያ አብዮት ባለው ልዩ
ባህርይ የተነሳ በሶስቱም ደረጃዎች የሚመለ
ከቱትን ተግባራዊ ሁኔታዎች እየፈጸመ ሲሆ
ን በሶስቱም ዘርፍ ያደረገው እንደቅደም ተ
ከተላቸው ይለያያል። ቀደም ሲል እንደተመ
ለከተው ዛሬ አብዮታችን የመጀመሪያውን
ደረጃ ለማገባደድ በዋዜማው ላይ የሚገኝ
ሲሆን ሁለተኛውን ለማገባደድ ግን ገና
የሚቀረን እንዳለ ግልጽ ነው ። ማለትም
ተገንጣይ ኃይሎችንና የቀሩትን ጥቂት የመ
ሃል አገር አድሃሪዎችን በቁጥጥር ሥር የማ
ዋሉ ተግባር ከመጀመሪያው ደረጃ መገባ
ደድ የሚያያዝና ብዙም ሥራ የሚጠይቅ
ጉዳይ ነው ። በሌላ በኩል ሶስተኛውን ደረጃ
የማገባደዱን ጉዳይ መገመት እንደሚ
ቻለው ብዙ ውጣ ውረድ ያለበትና የዚህም
ተግባር መገባደድ ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ
ማሸነፉን የሚያረጋግጥ ነው ። የኢትዮ
ጵያ አብዮት በዚህ ረገድ ገና ብዙ እንደሚ
ቀረው ጠንቅቀን ልንረዳ ይገባል ። ይህን
ጉዳይ ጠቅለል አድርገን ብንወስደው አብ
ዮታችን የመጀመሪያውን የሌኒን መለኪያ
ለማገባደድ የተቃረበ ሲሆን ሁለተኛው
ግን ከመጀመሪያው የበለጠ ጊዜ የሚወስድ
በት ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ ገና ለብዙ

Digitized by Google

ጊዜ የሚያቆየው እንደሆነ ገልጾ ነው ። በነዚህም ሶስት ዘርፎች የሚደረገው ትግል የአብዮታችንን ስር መሰደድና ድል ማድረግ የሚያረጋግጡ በመሆናቸው ዛሬ የአብዮታችን መሠረታዊ ተግባራት ጠንካራ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ መመሥረት፣ በጠንካራ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ላይ የተመሠረተ የማይ በገር የመከላከያ ኃይል መገንባት እንደሆነ በመደጋገም ተገልጿል ። በመሠረቱ የነዚህ ሶስት ተግባራት መሳካት አብዮታችን የቀረበለትን የዕድገት መለኪያ ሙሉ በሙሉ ለማገባደድ ያስችሉታል ማለት ነው ።

አብዮታችን እስካሁን ያስገኛቸውን ድሎች በመውሰድ ሁለንተናዊ በሆነው የሌኒን መለኪያዎች አንጻር ዕድገቱን ለመገምገም ያደረግነው ጥረት በፕሮግራሙም አፈጻጸም ረገድ ምን ያህል እንደተራመደ ያመለከታል ። ለዚህ ነው ከአሁን በፊት እንደተባለው የሁለቱም መለኪያዎች አገልገሎት ዙር ዙር አንድ የሚሆነው ። ስለሆነም የአብዮቱን ዕድገት በፕሮግራሙ አፈጻጸም ረገድ ለመገምገም የምናደርገው ሙከራ የግዴታ ከላይ በሌኒን መለኪያዎች መሠረት ካደረግነው ግምገማ የማይለይ በመሆኑ እንደገና ማንሳቱ አስፈላጊ አይሆንም ። አብዮታችን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ የፊውዳሊዝምን ፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ ሥርዓትና የኢኮኖሚ ምዝበራ ጨርሶ አስወግዶታል ። ዛሬ ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቱን በየደረጃው እየተጎናጸ ሲሆን ይህንንም ተግባር ከፍጻሜ ለማድረስና ቋሚ ዋስትና ለመስጠት ወደ ሕዝባዊ ዲሞክራሲ እየተቃረበ መሄዱን ተመልክተናል ። ባጭሩ አብዮታችን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት በተቃረበ መጠን ፕሮግራሙን ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረገ መገምገም ይቻላል ማለታችን ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. V.I. Lenin, coll. works, vol. 13, progress pub. Moscow p. 243.
2. K.Zaradov, *The Political Economy of Revolution*, Progress pub. Moscow 1981, p. 76-77.
3. *Short History of the World*, vol. 2, Progress pub., Moscow 1974, p.54.
4. Ibid. p.54.
5. Ibid (vol. 1) p.131.
6. Ibid (vol. 1) p.131.
7. V.I. Lenin, coll. works, vol. 33, progress pub. Moscow p.110.
8. Ibid, vol. 13, Progress pub.,Moscow, p.37
9. Short History of the world (vol. 2) Ibid p. 288.
10. Ibid p. 313.
11. Marx and Engels, selected works, vol.I, progress pub. Moscow, p. 111-112.
12. History of the C.P.S.U (Bolshevik) Moscow, 1937, p.4
13. Ibid, p. 4.
14. Paul C. Gregory & Robert stuart, *Soviet Economic performance and structure*, p. 379.
15. *History of the world*, Ibid p. 282.
16. Monthly statistical bulletin, Nov. 1981, p. 16.
17. *History of the C.P.S.U* (Bolshevik) Moscow, 1937, p. 67.
18. National Democratic Revolution's Programme, p. 7.
19. Ibid, p. 10.
20. Ibid, p. 7.
21. V.I. Lenin, *On Socialist Economic Organization*, progress pub., Moscow p. 131.
22. Civil code of Ethiopia Act.
23. *The Social and Economic Conditions of Ethiopia*, Addis-Abeba, 1989 (Unpublished).
24. Report of the Organization Department to the Second Plenary Session of the C.C. of COPWE.
25. Report of Cooperatives Dept. to the Second Plenary Session of C.C. of COPWE.
26. ከኢሠፓአኮ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መምሪያ የተገኘ ።
27. የኢሠፓአኮ 1ኛ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ማእከላዊ ሪፖርት፣ ሰኔ 1972
28. Economic Report to the 2nd Plenary Session of the C.C. of COPWE.

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም አቀፍ አብዮታዊ ትግል አንጻር

አብዱልሀፊዝ የሱፍ

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና ዓለምአቀፍ
ባህሪው ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ

በሁለንተናዊውና በገላጪው መሀል
ዲያሌክቲካዊ መተሳሰርና መስተጋ
ብር እንዳለው ሁሉ በታሪክ ዕድገት ሂደትም
በዓለም አቀፋዊውና በብሔራዊው መሀል
ተመሳሳይግንኙነትይታያል።በማኅበራዊ ዕድ
ገት ሂደት ውስጥ ይህን የመሰለ መስተጋ
ብር ለመኖሩ ከአብዮቶች ታሪክና ከወ
ቅቱ ዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎች መገንዘብ
ይቻላል ።

ስለሆነም የኢትዮጵያ አብዮት በራሱ
ብሔራዊ ክልል ብቻ በሚወሰኑ መንስኤ
ዎች ሳቢያ የተቀጣጠለ አለመሆኑን ያሀል
በዕድገቱና በውጤቱም ከዓለም አቀፋዊ
ሁኔታዎች ጋር ይያያዛል ። በአንድ በኩል
ኢምፔሪያሊዝም አንድ ምሽጉን እንዲ
ያጣ በማድረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ-
ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ተጨማሪ ድጋ
ፍና እርዳታ የሚያገኙበት አጋር የፈጠረ
በመሆኑ በዓለም አቀፍ አብዮታዊ እንቅስ
ቃሴ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ ያበረከታል ።

በዚህም ጽሑፍ የኢትዮጵያ አብዮት
በተጠቀሰው መልክ የሚያንፀባርቀውን ባሕ
ርይና ፥ ለዚህም መነሻ የሚሆኑትን መሠረ
ታዊ ጉዳዮች ጠቅለል ባለ መልኩ ለማቅ
ረብ ተሞክሯል ። የአብዮቱን ብሔራዊ ቅር
ጾች ሁለንተናዊ መሠረት በማሳየት የዓ
ለም አቀፋዊ አብዮት እኩልነቱን ለማስረ
ዳት ሙከራ ይደረጋል ። በዚህ በኩል ሊነሱ
የሚችሉት ነጥቦች አያሌና በራሳቸው እን
ኳን ሰፊ በመሆናቸው ወደ ዝርዝር ነጥቦች
ከመግባት ይልቅ ከጽሑፉ ዓላማ አንፃር
ዋና ዋናዎቹ ብቻ በአጠቃላይ መልካቸው
ቀርበዋል ።

የኅብረተሰብ ዕድገት የተወሰነ አቅ
ጣጫን በመከተል እንደሚጓዝ በተለያዩ
ዘመናትና ወቅቶች በታሪክ የተመዘገቡ
ለውጦችን በመመልከት ብቻ መረዳት ይቻ
ላል ። እነዚህ ታሪካዊ ዕውነታዎች የተከ
ሰቱት በተወሰኑ አካባቢዎች መሆኑ የተ
ለያዩ አገሮች የዕድገት ሂደት ልዩ ነው
አያሰኝም ። በመሠረቱ ስለ ኅብረተሰብ ቢነ
ገር ከሁለንተናዊ ባሕርዩ አንጻር እንጂ
አንዱን ወይም ሌላውን አገር በማሰብ
አይደለም ። ማርክስ እንዳለውም ኅብረተሰ
ብ የተለያዩ መልኮች ሊኖሩት የሚችል የሰ
ዎች የጋራና የተደጋጋፌ ድርጊት ውጤት
ቢሆንም ሰዎች ሊኖሩበት የሚፈልጉትን

Digitized by Google

ኅብረተሰብ ሊመርጡ አይችሉም ። ምክንያቱም የኅብረተሰቡ ኅልውናና የሰዎች ታሪክ መሠረት የሆነውን የምርት ኃይል ሊመርጡ ስለማይችሉ ነው ። በማንኛውም ወቅት የምርት ኃይሎች ካለፈው ትውልድ የሚወረሱ ሆነው የሚዳብሩና የሚሻሻሉ በመሆናቸው አሮጌውንና አዲሱን ፣ ያሁኑንና የወደፊቱን በማያያዝ የታሪክንም ተከታታይነት የሚያስገኙ ናቸው ።

የምርት ኃይሎች ደረጃ ተመርጦ ሊገኝ የማይቻል መሆኑ ደግሞ ሰዎች በማምረት ተግባር ውስጥ የሚኖራቸው ክንዋኔ የሚዋቀረው ከምርት ኃይሎቹ ጋር በሚጣጣም መልክ መሆኑን ግዴታ ያደርጋል ። ስለዚህም ነው የምርት ኃይሎች ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ መድረስ የነዚህን ግንኙነቶች መለወጥ በመጠየቅ በሁለቱ መሀል የሚፈጠረው ቅራኔ የማኅበራዊ አብዮት ኢኮኖሚያዊ ይዘት ነው የሚባለው ። በማንኛውም ማቴሪያላዊ ሕላዌ እንደ ሚታየው ሁሉ የኅብረተሰብም ዕድገት ዕውን የሚሆነው በውስጡ በያዛቸው ተቃራኒ ገጽታዎች መሀል በሚደረገው ትግል ቅራኔው ሲፈታ ብቻ ነው ። የቅራኔው አነሳስ ማደግና መዳበር ወይም መክረር ነባራዊ መሠረት ያለው በመሆኑ በማኅበራዊ ክስተቶች ውስጥ የሰው ልጅ ክንዋኔ የሚጫወተው ጉልህ ሚና ቢኖረውም የዕድገቱን አቅጣጫ የማሳት ችሎታ ግን የለውም ። ይልቁንም በኅብረተሰብ ዕድገት ፣ በማኅበራዊ ለውጥ ሂደት ውስጥ የማይናቅ ድርሻ ያለው የሰው ልጅ ንቁ ተሳትፎ ባህርይና ስፋት በመሠረቱ የሚገዛው በነባራዊ ሕግጋት ነው ።

የሰው ልጅ ፍላጐት የታሪክን ሂደት በነባራዊ ሕግጋት በተተለመው መሠረት እንዳይራመድ ለመግታት ቀርቶ አቅጣጫውን ለማሳየት እንኳን እንዳልቻለ መረዳቱ አስቸጋሪ አይሆንም ። የኅብረተሰብን ታሪክ መለስ ብለን የተመለከትን እንደሆነ የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ሰው የታሪክን ዕድገት ነባራዊ ኃይሎች ለመቋቋም አለመቻሉ እንጂ የዕኩልነት ኑሮን በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀል በሚኖር ግንኙነት የመለወጥ ፍላጐት ስለነበረው አይደለም የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የተተካው ። በተለያዩ ደረጃዎች በኅብረተሰብ ውስጥ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የበላይነት የነበራቸው መደቦች በአዲስ ኃይሎች የተተኩት የበላይነታቸውን ላልደረሰው ለማድረስ ፈልገው ወይም የበላይነታቸው የሚያስገኝላቸውን ጥቅም ጠግበው አልነበረም ። ሊመክቱትና ሊቋቋሙት በማይችሉት ኃይል ግፊት ተገደው እንጂ ። ስለዚህም ብዝበዛ የሌለበት ኅብረተሰብ በተቃራኒው መተካቱ ከሰዎች ፍላጐትና ቁጥጥር ውጪ በሆነ የታሪክ ዕድገት አስገዳጅነት የመሆኑን ያህል በታሪክ የታዩት የተለያዩ በዝባዥሥርዓተ ማኅበሮች መፈራረቅና በመጨረሻም የሰው በሰው መበዝበዝ ለአንዴና ለሁል ጊዜ ያከተመበት የአዲስ ኅብረተሰብ መግንባት የታሪክ ግዴታ ለመሆኑ አያጠያይቅም ።

በዓለማችን 1/3 ክፍል የሶሻሊዝም መመሥረትና ዛሬም ዕድገታቸውን በዚህ አቅጣጫ ለማድረግ የመረጡ ሕዝቦች እየጨመሩና እየተጠናከሩ መሄዳቸው በታሪክ አስገዳጅነት መሆኑ ነው እንጂ በብሔራዊ ክልሎችም ሆነ በዓለም አቀፍ አድኅሮት ኃይላት ፍላጐትማ ቢሆን ይህ ዕውነት ሕልም ሆኖ በቀረ ነበር ። በየመስኩ ከሚፈጽሙ ስውር ደባና አሻጥር እስከ ወታደራዊ ጥቃት የሚደርሱ ድርጊቶችን በመፈጸም ኢምፔሪያሊዝምና አጫፋሪዎቹ ከ1917ቱ የታላቁ የጥቅምት አብዮት ድል አንስቶ እስከዛሬም ቢሆን የሶሻሊዝምን ምሥረታና ግንባታ ለማሰናከል መሞከራቸውን አላቋረጡም ። ዳሩ ግን የታሪክን ግስጋሴ ወደ ኋላ ሊጐትት የሚችል አንዳችም ኃይል ባለመኖሩ ሶሻሊዝም ይበልጥ እየተጠናከረና እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

የታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል አድራጊነት ከአንድ ሕዝብ አርነት መውጣትና ለአዲስ ሥርዓት ግንባታ መብቃት ላይ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። በዓለም ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ መክፈቱንና የወዛደራዊ አብዮት ዘመን መጀመሩን ከማብሰሩም በላይ ለሕዝቦች ነፃነት ፣ እኩልነትና ብልጽግና ብሩህ ተስፋ ማረጋገጫም ነበር ።

የሩሲያ አብዮት ከተካሄደበት ክልል ውጪ በመንጸባረቁ ያገኘው ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ የሚመነጨው በአጋጣሚ ወይም በሕሊናዊ ኃይሎቹ ክንዋኔና ተጽዕኖ

Digitized by Google

ሳይሆን በታሪክ ሎጂክ ነው ። በመሠረቱ ታሪክ የሰፋ መግለጫ ቢኖረውም በአብዛኛው የተነጣጠሉ ገጽታዎችንና የተለያዩ ትውልዶችን ተከታታይነት የሚያሳይ ይመስላል። ማኅበራዊ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን በዚህመልክ በመመልከት የሩሲያ አብዮት ሲገመገም ባስገኘው ለውጥ ጠቀሜታውና ተጽዕኖው በተካሄደበት ብሔራዊ ክልል ውስጥ ብቻ መወሰን የሚገባው መስሎ ቢታይም ሁኔታዎችን ጠለቅ ብለን የመረመርን እንደሆነ ታሪካዊ ጠቀሜታቸው ሰፊ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ምንም እንኳ አገሮች በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው የተራራቁና በዕድገት ደረጃቸውም የተለያዩ ቢሆንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በልዩ ልዩ መስኮች ግንኙነት ይኖራቸዋል ። ስለዚህም በአንድ አካባቢ የሚደርስ ለውጥ በሌላውም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም ። ይህን የመሰለ ውጤት ላላቸው ሁኔታዎች የሚሰጠው ግምት በብሔራዊ ክልል ውስጥ ብቻ ተውጠው ከሚቀሩት የተለየ ሊሆን እንደሚገባው ሲያሳይ ማርክስ እንዲህ ብሎ ነበር ፤

እርስ በርስ ተፅዕኖ የሚደራረጉ አካባቢዎች ሑኔታ በእድገት ሂደት ውስጥ ይበልጥ እየሰፋ በሄደ መጠን ቀድሞ የነበረው የተለያዩ አገሮች ብቸኝነትም በዳበረው ስልተ ምርትና ግንኙነት ይበልጥ እየጠፋ ይሄዳል ፤ በተለያዩ አገሮች መካከል ያለው የሥራ ክፍፍልም በነዚሁ አማካይነት የግድ መምጣቱ ስለማይቀር በዚሁ ታሪክም የበለጠ ዓለምአቀፋዊ ይሆናል ።[1]

ከዚህ በመነሳት ማርክስ የሰጠው መደምደሚያ በዚህ መልክ በተሳሰሩ ኅብረተሰቦች በአንደኛው የሚደርስና በሌላኛው ላይ የሚሰማ ማንኛውም ዓይነት ሁኔታ የዓለም ታሪክነትን ያህል (world historical) ክብደት እንዳለው ነው ። ስለዚህም በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኅብረተሰቦች ከምንጊዜውም ይበልጥ በብዙ አቅጣጫዎች በተሳሰሩበት በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በአንድ ብሔራዊ ክልል ለመሠረታዊ ለውጥ የሚደረግ አብዮት በእንቅስቃሴ በውጤቱ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ከክልሉም ባሻገር ስለሚሰማ የዓለም ታሪካዊ ሂደት ዕውነታ ይሆናል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የመደብ ኅብረተሰብ የተከሰተው በታሪክ አስገዳጅነት እንደነበረው ሁሉ የመደብ አልባ ሥርዓተ ማኅበርም መመሥረት ጊዜ አይቀረጥለት እንጂ የማይቀር የታሪክ ግዴታ ነው ። በመጨረሻው የበዝባዥ ሥርዓት በሆነው በካፒታሊዝምና በመደብ አልባው ኮሚዩኒስት ሥርዓት መሀል በሚኖረው የሽግግር ጊዜ የሚገነባው ሶሻሊዝምም በታሪክ ዕድገት ሂደት ውስጥ ሁሉም ሀገሮች የሚያልፉበት ደረጃ ነው ።

ያለንበት ዘመን ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር የሚደረግበት ዘመን እንደሆነ ቢነገርም ከዓለም ሕዝብ አብዛኛው ክፍል አሁንም በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛል ። ይህ ሁኔታ ግን የሽግግሩን ሂደት መሠረታዊ ባህርይ አይለውጠውም ። ምክንያቱም የብዙ ሕዝቦች በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ውስጥ መገኘት «በራሳቸው » ተወስደው ሲታዩ እንጂ እንደዕውነቱ ከሆነ በዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው ። ሆኖም ግን በነዚህ አገሮች ሶሻሊዝምን ዕውን የማድረግ ተግባር ካፒታሊዝም ከሞላ ጐደል በተስፋፋበት አገር ሊከናወኑ ከሚገባቸው የተለየ መሆን አለበት ። ስለዚህም በሁለቱ መሀል በአቅጣጫና በደረጃ ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሶሻሊዝም በሁለቱም ውስጥ መገንባቱ የማይቀር ነው ። ሌኒን ይህን አስመልክቶ ሲናገር ፤

ሁሉም ሀገሮች ወደ ሶሻሊዝም ይደርሳሉ ። ይህ የማይቀር ሀቅ ነው ። ሁሉም ግን ወደ ዚህ ግባቸው የሚደርሱት በአንድ መንገድ በመጓዝ አይደለም ። እያንዳንዱ ከራሱ አንጻር ለተወሰነ ዓይነት ዲሞክራሲ ለተወሰነ ዓይነት የወዛደሩ የበላይ ገዥነት የተለያየ የዕድገት መጠን ላለው የሶሻሊስት ሥርዓት ሕልውና አስተዋፅኦ ያደርጋል ።[2]

በሌላ አነጋገር ይህ የሌኒን አባባል የሚያሳየን የሶሻሊስት አብዮት ከሚነሳለት ግብና በአሸናፊነት ሲወጣ በሚመሠረተው ኅብረተሰብ ባሕርይ አንፃር ሁለንተናዊ ቢሆንም ፣ እንደሚካሄድበት ሀገር የዕድገት ደረጃ ብሔራዊ መለያዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ ነው ።

Digitized by Google

ማርክስና ኤንግልስ በኋላም ሌኒን እንዳስረዱት ሶሻሊዝም ሁልጊዜ የግድ ካፒታሊዝምን ተከትሎ መምጣት አለበት ማለት አይቻልም ። ይህም ማለት ገና ካፒታሊዝም ካልዳበረበት የዕድገት ደረጃ ወደ ሶሻሊዝም መጓዝ የማይቻልበት ምክንያት የለም ማለት ነው ። በዚህን መሠረት አንድም ከዳበረ ካፒታሊዝም ወይም ደግሞ ካፒታሊዝምን በመዝለል ሶሻሊዝም መገንባት የሚቻልባቸው መንገዶች እንዳሉ መረዳት ይቻላል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ አገሮች ካፒታሊዝምን በመዝለል ሶሻሊዝምን ለመመሥረት የተቻለበት ሁኔታ ለየቅል ነው ። ለምሳሌ በሩሲያ የጠረፍ ግዛቶች ካፒታሊዝምን በመዝለል ሶሻሊዝም የተገነባው በወዛደሩ የበላይ ገዥነት ሥር ሲሆን ፣ በሞንጎሊያ ፣ በኮሪያና በቪዬትናም በሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን በመመራት ነበር ። እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍሪካና በእስያ በዚህ አቅጣጫ የሚደረገው ትግል በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እየተመራ ነው ።

ከቅድመ ካፒታሊስት ሥልተ ምርቶች በመነሳት ካፒታሊዝምን አልፎ ሶሻሊዝምን የመገንባቱ ጉዳይ በዚህ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኅብረተሰቦች ካሉት ሁለት አማራጮች አንደኛው መሆኑ በታሪክ ዕድገት ሎጂክ ውስጥ ነባራዊ መሠረት አለው ። ስለዚህም ጥያቄው የዕድገት ጐዳናን የመምረጥ ብቻ ባለመሆኑ ፣ ሶሻሊዝምን በቀጥታ የመገንባቱ ጉዳይ ምርጫ ውስጥ ሊገባ አይችልም ። ምክንያቱም የቅድመ ካፒታሊስት ሥልተምርት በሰፈነባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ ሶሻሊዝም ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ስለማይገኙ እነዚህን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ለመፍጠር በየመስኩ ልዩ ልዩ ተግባሮች የሚከናወኑበት የሽግግር ወቅት መኖር አለበትና ነው ።

ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጐዳና አንዱ አማራጭ ሊሆን የቻለው በቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰቦች ውስጥ ባለው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀት አኳያ ሁኔታው ለሶሻሊዝም ግንባታ የማያበቃ በመሆኑ ብቻ አይደለም ። ይልቁንም የዚህ ዓይነቱ የዕድገት ጐዳና አስፈላጊ መሆን ዓለም አቀፋዊ መንስኤ አለው ። የካፒታሊዝም ያልተስተካከለና ያልተመጣጠነ ዕድገት በዓለም ውስጥ ለቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰቦች እስከዛሬም መገኘትና ለነዚህ ኅብረተሰቦች ኋላቀርነት የኢምፔሪያሊዝም ተጽዕኖ ዋንኛው ምክንያት ነው ። ከውጪያዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ ለመላቀቅ ለሚመረጠው የዕድገት ጐዳና መሳካት ደግሞ ሊሟሉ የሚገባቸው ውጪያዊ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ ። እነሱም በፖለቲካ በርዕዮተ ዓለምና በኢኮኖሚ መስክ ከዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት ጋር መኖር ባለበት መተሳሰር ዙሪያ የሚገኙ ናቸው ። በአንድ በኩል የሶሻሊዝም ድል በኋላቀር አገር ሕዝቦች ዘንድ ምሳሌነቱና ማራኪነቱ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሶሻሊስት ሀገሮች በፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋማቸው ለነዚህ ሕዝቦች የሚሰጡት የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ አንፃር ይህ ግንኙነት ወሳኝ ይሆናል ።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የሶሻሊዝም መስፋፋት የአያሌ ሕዝቦች ከቅኝ አገዛዝ መላቀቅና የፀረ-ኢምፔሪያሊስትና የፀረ-ኮሎኒያል ትግሎች ይበልጥ እየተጠናከሩ መሄድ በዓለም ላይ ያለውን የኃይል ሚዛን ለውጦታል ። ለኃይል ሚዛኑ ወደ ሶሻሊዝም ማጋደል የፀረ-ኮሎኒያል ትግሎችና ብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች ከነበራቸው ድርሻ አንፃር ሲታይ ከፍ ወዳለ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር አዲስ ይዘት እንዳገኘ መገንዘብ ይቻላል ። ንቅናቄዎቹ ለብሔራዊ አርነት ብቻ ሳይሆን ለማኅበራዊ አርነትም የሚታገሉ በመሆናቸው የመደብ ባሕርያቸው ግልጽ እየሆነ መጥቷል። በዚህም የፖለቲካ ነፃነት በመጐናጸፍ ላይ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ነፃነትን ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ትግል እየተጠናከረ መምጣቱ በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መሀል ባለው ቅራኔ የዓለም ሶሻሊስት አብዮት አካልነታቸውን አስመስክረዋል ።

ለብሔራዊ አርነትና ለማኅበራዊ ነፃነት የሚደረጉት ትግሎች እርስ በርስ የሚያያዙና የሚደጋገፉ ናቸው ። የዚህም መሠረታዊ ምክንያት በሁለቱም አቅጣጫዎች የሕዝቦችን ልዕልና ለማረጋገጥ ዓላማው የኢምፔሪያሊዝም ሽንፈት መሆን ስላለበት ነው ። የዚህም ዓላማ መሳካት ከሶሻሊስቱ ካምፕ ጋር ኅብረትን ይጠይቃል ። ጥያቄው ዓለም አቀፋዊ በመሆኑ የተናጠል ትግል ፍሬ ሊሰጥ አይችልም ።

Digitized by Google

ከ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ በዓለም ዙሪያ ሲያስተጋባ የነበረው የትግል ጥሪ (የሁሉም አገር ወዝአደሮች ተባበሩ)! በዘመናችን ከተከሰተው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አንፃር መስተካከል የነበረበትም ለዚህ ነው ። ይህንኑ ለውጥ አስመልክቶ በተደረገው ውይይት በ1961 ሞስኮ ላይ የተካሄደው የኮሚዩኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ጉባኤ የሚከተለውን ወቅታዊነት ያለው ጥሪ አድርጓል ፤

የሶሻሊስት አገሮች ሕዝቦች ፤ የካፒታሊስት አገሮች ዲሞክራሲያዊ ኃይሉች ፤ አዲስ ነፃ የወጣችሁና የተጨቆናችሁ ሕዝቦች ለሰላም ፤ ለብሔራዊ አርነት ፤ ለማኅበራዊ ለውጥ ፤ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም በኢምፔሪያሊዝም ላይ በሚደረገው የጋራ ትግል ተባበሩ!![3]

እንግዲህ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጉዳናን በመረጡ ሀገሮች ማኅበራዊ መዋቅር በመወሰንና ለመለወጡ በሚደረገው ትግል አኳያም የውጪያዊ ሁኔታዎችን ድርሻ ከተመለከትን የኢትዮጵያም አብዮት በአጠቃላይ ባሕርዩ ከላይ ከተጠቀሰው ፈርጅ ውስጥ የሚወድቅ በመሆኑ ፣ የዓለምዓቀፍ አብዮት አካል መሆኑ አያጠያይቅም ። እስከ አሁን የተነሱትም ነጥቦች የኢትዮጵያን አብዮት በዚህ አቅጣጫ ለመተንተን ለሚደረገው ሙከራ በቂ መንደርደሪያ ያስገኙ ይመስለናል ።

የዓለም አቀፋዊ ሁኔታና የኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ

የኢትዮጵያን አብዮት ከዓለም አብዮታዊ ሂደት አኳያ ስንገመግም አንዱን ከሌላው ነጥሎ በማነፃፀር ሳይሆን በመሀከላቸው ካለው ውህድነት ተነስተን መሆን ይኖርበታል ። የኢትዮጵያ አብዮት በዚህ ውስጥ የሚኖረውን ሥፍራ ከመሠረቱና በትክክል ለመረዳት ደግሞ ዛሬ የሚያሳየውን ስዕልና የሚያደርገውን አስተዋጽኦ በመመልከት ብቻ መወሰን ግምገማውን በስፋቱም ሆነ በጥልቀቱ ቁንጽል ያደርገዋል ። ስለዚህም ደረጃ በደረጃ የአብዮቱን እርምጃ ከዓለም አቀፋዊ ሁኔታና ከዓለም አብዮታዊ ሂደት ዕድገት ጋር እያስተያየን ለመመርመር አነሳሱንም በዚሁ መልክ መመልከት ይጠቅማል ።

በዓለም ውስጥ በየትኛውም አካባቢ በልዩ ልዩ መስኮችና ደረጃዎች የሚካሄደው የመደብ ትግል በሁለቱ የዓለም ሥርዓቶች መሀል የሚደረገው ትግል ነጸብራቅ እንደሆነ ተደጋግሞ የሚነገር ሀቅ ነው ። በአንጻሩም የዓለም ኮሚዩኒስትና ሠራተኛ ንቅናቄ ኃይሉች በፀረ-ኢምፔሪያሊስቱ መስመር ለሚደረጉ ትግሎች በተወሰኑ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ሥር ብቻ ድጋፍ የሚሰጡ ሳይሆኑ ባጠቃላይ ለነፃነት ፣ ለፍትሕ ፣ ለሰላምና ለማኅበራዊ ዕድገት ለሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ «ተፈጥሮአዊ አጋሮች» ናቸው። የሶሻሊዝም መስፋፋትና ግንባታው በተጀመረባቸው አገሮችም ሕልውናው ጥስትና እንዲኖረው የኢምፔሪያሊዝም መዳከምና መደምሰስ ግዴታ ነው ። ስለዚህም ፀረ-ኢምፔሪያሊስት እንቅስቃሴዎችን ማገዝ ሕዝቦች ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኋላቀርነት ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል መርዳት ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ጠብ አጫሪነቱና በጦረኝነቱ እየባሰበት በመሄድ ላይ ካለው ኢምፔሪያሊዝም ሶሻሊዝምን ለመጠበቅም ጭምር ነው ። ስለዚህም ነው ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎች የሶሻሊስት አብዮት አካሎች ናቸው የሚባለው ። የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሶሻሊስት አብዮት አካል መሆኑ ከዚሁ ይመነጫል ።

የኢትዮጵያ አብዮት ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ባሕርይ በልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቋሞችና እርምጃዎች በማያሻማ ሁኔታ ሲንጸባረቅ የቆየውና በመንጸባረቅም ላይ ያለ መሆኑ የአብዮቱን ሕሊናዊ ኃይሎች በተለይም የአመራሩን ግንዛቤ ከግ መልከቱም ሌላ በነባራዊ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የተከሰተ ባሕርይ ነው። የየካቲቱን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አነሳስ መለስ ብለን ብናስተውል ይህን አባባል ግልጽ ያደርገዋል ።

የአብዮቱ ፍንዳታ

የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ከውስጣዊ ባህርዩ ከሚመነጭ ቀውስ

Digitized by Google

ተላቆ የማያውቅ ቢሆንም በ1970ዎቹ መጀ
መሪያ አካባቢ የታየው ቀውስ ከ2ኛው
ዓለም ጦርነት ወዲህ በካፒታሊስቱ ሥር
ዓት ተከስተው ከነበሩት ሁሉ በጣም ከፍ
ተኛውና በ1930ዎቹ ደርሶ ከነበረው ቀውስ
ጋር ሊወዳደር የሚችል ነው ። ስለቀ
ውሱ አመጣጥና ገጽታዎች በሰፊው ሊታ
ተትበት ቢቻልም እዚህ ላይ ግን በአጭሩና
በጥቅሉ ብቻ በማንሳት እናልፈዋለን ።
በተጠቀሰው ጊዜ የደረሰው ቀውስ እንደ
ድንገት የመጣ ሳይሆን በተለይ ከሁለተኛው
ዓለም ጦርነት በኋላ በዓለም ካፒታሊስታዊ
ሥርዓት ውስጥ በኢንዱስትሪ በበለጸጉና
በኋላቀር ሀገሮች መሀል የነበረው ያልተ
መጣጠነ የሥራ ክፍፍልና የተዛባ የገበያ
ግንኙነት የተጠራቀቀመ ችግር ውጤት
ነው ። በ1950ና 60ዎቹ (እ. ኤ. አ.) ዓመ
ታት በፀረ-ኮሎኒያል ትግሎች ድል አድራጊ
ነት ከተመሠረቱት አዳዲስ ነፃ መንግሥ
ታት መሀል ብዙዎቹ የተፈጥሮ ሀብቶቻቸ
ውን በራሳቸው ቁጥጥር ሥር ሲያውሉ በበ
ለጸጉ ካፒታሊስት ሀገሮች የጥሬ እቃዎቻ
ቸውንና የኃይል ምንጫቸውን የፖለቲካ
መሣሪያ ሲያደርጉት በዚህ በኩል የተፈጠ
ረው ችግር የተባባሰ ሆኗል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዘመነ ኮሎኒ
ያሊዝም የነበረው ዓለም አቀፋዊ የሥራ
ክፍፍል በተለወጠው የዓለም ሁኔታ አኳያ
ዘላቂ ሊሆን አለመቻሉን በመረዳት ፣ በተ
ፈጠረው አዲስ ስልት የተከሰቱት ፣ ዓለም
አቀፍ ኩባንያዎችና የካፒታሊስቱ መን
ግሥት ኢኮኖሚያዊ ሚና ማደግ በሞኖፖ
ሊስቶቹ መሀል ለጥሬ ዕቃዎችና ለገበያ ፣
የሚደረገውን ፉክክር ክፉኛ አሳድጐታል ።
በዚህም ሳቢያ በበለጸጉ የካፒታሊስት
ሀገሮች ውስጥ በሀይል ምንጭ በገንዘብ
አቅም ፣ በጥሬ እቃዎችና በመሳሳሉት
ረገድ የደረሰው ቀውስ የብዙ ፋብሪካዎች
መዘጋትን ፣ የዋጋ ንረትንና የተያያዙ ችግ
ሮችን አስከትሏል ። ችግሮቹ በካፒታሊስት
ሀገሮች ክልል የተወሰኑ ሳይሆኑ በዓለም
ካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ
በነበሩት ሀገሮች ሁሉ ያደረሱት ተጽእኖ
በጉልህ ታይቷል ። ይልቁንም ይህ ቀውስ
ባስከተለው ችግር ይበልጥ የተጐዱት ኋላ
ቀር አገሮች እንደነበሩም ግልጽ ነው ።

ኢትዮጵያም ኋላቀር ከሚባሉት ሀገሮች
አንዷ ከመሆኗም ሌላ በቅድመ አብዮት
በዓለም ካፒታሊስት ሥርዓት ምኅዋር
(orbit) ውስጥ ስለነበረች የደረሰው ቀውስ
ላስከተለው ችግር የተጋለጠች መሆኗ አል
ቀረም ። የኢትዮጵያ አብዮት በየካቲት
1966 ሲፈነዳ የነበሩትን ሁኔታዎች ብናስ
ታውስ በመሠረቱ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ
ሆኖ መቆየት የሚያስከትላቸው ችግሮች ለሕ
ዝባዊ ቁጣ ይፋ መውጣት ምክንያቶች እንደ
ነበሩ ማየት ይቻላል ። በአንድ በኩል በ
ዓለም አቀፍ ደረጃ በደረሰው የኢኮኖሚ
ቀውስ ሳቢያ ፣ በነዳጅ ዋጋ መናር ኢትዮ
ጵያ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መድረክ ከነበ
ረችበት የተዛባና ተመጣጣኝ ያልሆነ የገ
በያ ግንኙነትና የሥራ ክፍፍል የመነጨ
ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊ
ዝም ጥገኛና ተቀጥላ በመሆን የቆየችው
ለማኅበራዊ ዕድገት እንቅፋት የሆኑት ቅ
ድመ ካፒታሊስት ስልተምርቶች እንዳይ
ወገዱ የኢምፔሪያሊዝም ተጽዕኖ ስለነበረ
ነው ። ስለዚህም ለአብዮቱ ፍንዳታ አመቺ
ሁኔታ የተፈጠረው በቀጥታም ሆነ በተዘ
ዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ የዓለም ካፒታ
ሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ቤተሰብ ከመ
ሆኗ የተነሳ ነበር ማለት ይቻላል ።
ለኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳት ነባራዊ
ሁኔታው ተሟልቶ ነበር ቢባል አንድ አቢይ
ነጥብ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። አሮጌውን የም
ርት ግንኙነት በአዲስ ለመለወጥ የሚያስ
ችል ተጨባጭ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር ማለት
እንዳልሆነ ግን መዘንጋት የለበትም ።
የምርት ግንኙነት የተወሰነ የዕድገት ደረጃ
ላይ የሚገኙት የምርት ኃይሎች ማኅበራዊ
ቅርጽ እንደመሆኑ መጠን ፣ የአዲሱን የም
ርት ግንኙነት መዋቅር የሚወስነው የም
ርት ሀይሎች እድገትና ከአሮጌው የምርት
ግንኙነት ጋር ሊጣጣሙ የማይችሉበት
ደረጃ ላይ መድረስ ነው ። በዚህ አንጻር
የኢትዮጵያን ሁኔታ ብንመለከት እንደማንኛ
ውም ኋላቀርኅ ብረተሰብ ፣ የምርት ኃይሎች
ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ ፣ የምርት
ግንኙነቱ ዕድገታቸውን አፍኖአል ማለት
ያስቸግራል ። ስለዚህም የተጨባጭ ሁኔታ
ዎቹ ማሟላት መታየት የሚኖርበት አድሀ
ሪውን የገዥ መደብ በማስወገድ ፣ የፖለቲካ
ሥልጣን ጨብጦ ለአዲስ የምርት ግንኙ
ነት ዕውን መሆን አስፈላጊ የሆኑ ነባራዊና
ህሊናዊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያበቁ
ሶሺዮ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተሟልተው
እንደነበረ ነው ። የነባራዊው ሁኔታ በዚህ
መልኩ ሊታይ የሚገባው የኢትዮጵያን

Digitized by Google

ውስጣዊ ሁኔታ በሚመለከት ረገድ እንጂ
ሶሻሊዝም ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት
ጐዳናን በመከተል ለመገንባት ለሚደረ
ገው ትግል መጀመር ሁኔታው በዓለም አቀፍ
ደረጃ ከተሟላ ቆይቷል ።

የአብዮት ኀሊናዊ ኃይሎች ሁኔታ

ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው
የኅብረተሰቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አ
ደረጃጀት ከመሠረቱ ለመለወጥ ከምርት
ኃይሎቹ በሚመጣ ግፊት ሳይሆን ከላዕላይ
መዋቅሩ በሚደረግ ተጽዕኖ ነው ። ይህም
በወቅቱ የነበረውን የኅሊናዊ ኃይሎች ዝግ
ጅትን የሚመለከት ጥያቄ ያስከትላል። በተ
ለምዶ ተደጋግሞ እንደተነገረው በየካቲ
ት 1966 ኅሌናዊ ሁኔታዎች በደፈናው
ያልተሟሉ እንደነበር አድርጐ ማቅረቡ
ስህተት ነው ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ለሶሻ
ሊዝም ምሥረታ የሚያስፈልገው ኅሊናዊ
ሁኔታ አይሁን እንጂ የሥርዓቱን አስከፊነት
በመረዳትና እንዲወገድም ለመታገል ያስ
ነሳ በቂ ኅሊናዊ ሁኔታ ነበር ። አብዮቱ
ሊኖረው ከሚገባው የዘለቄታ ግብ አንፃር
ግን ኅሊናዊ ኃይሎች ያልዳበሩ ለመሆናቸው
ክርክር አያስፈልግም ። ስለዚህም የኅሊናዊ
ኃይሎች ዝግጅትና ጥንካሬ ደረጃ የሚለ
ካበትን የፖለቲካዊ ንቃተ ኅሊናንና የድር
ጅትን ጉዳይ ብቻ መመልከቱ ይበቃል ።

በፊውዳሉ መንግሥት ፀረ-ዲሞክራቲ
ክነት የሰፊው ሕዝብ ወገኖች መደባዊ
ለሆነ ዓላማ እንዳይሰባሰቡ ያፈነ ከመሆ
ኑም በላይ ተራማጅ አስተሳሰቦችም እንዳ
ይሠራጩ ከፍተኛ ክትትል ያደርግ እንደ
ነበር ዕውቅ ነው ። ሕዝባዊ ድርጅትን በተ
መለከተ ረገድ የሠራተኛ ማኅበሮች መቋ
ቋም የረጅም ጊዜ ትግል ውጤት ሆኖ ሳለ
የኃይለሥላሴ መንግሥት ለማኅበራቱ ሕ
ጋዊ ሰውነት መስጠቱ እንቅስቃሴአቸውን
ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ያደረገው እ
ንጂ የሠራተኛውን የመደራጀት መብት
ተቀብሎ አልነበረም ። ሠራተኛውም ቢ
ሆን ገና በመደብነት በመፈጠር ላይ የነ
በረና ፣ ከገጠሩ ጋር ከነበረው ግንኙነቱ
ጨርሶ ካለመላቀቁ የተነሳም በመደብነት
የተውገረገረም ስለነበር ፣ በሥርዓቱ ላይ
መሠረታዊ ተቋውሞ ነበረው ማለት ያዳ
ግታል ። ከዚህም በላይ የነበረውም አነ
ስተኛ ቁጥር የተበታተነ ስለነበር የተጠ
ናከረ ኃይል ለመፍጠር አልተቻለም ።

በአርሶ አደሩ አካባቢ የነበረው ሁኔታ
ከዚህ የባሰ ነበር ። ምንም እንኳን አልፎ
አልፎ በአንዳንድ ሥፍራዎች አርሶ አደሩ
በሥርዓቱ ላይ የነበረውን ተቃውሞ የገ
ለጸባቸው ዓመፆች የታዩ ቢሆንም ፣

እነዚህ በተለያዩ ጊዜያዊና መሠረታዊ ምክ
ንያቶች የተነሱና ተመሳሳይ ስፋትና ጥንካሬ
ያልነበራቸው የገበሬ አመጾች ለገዥው መ
ደብ ጊዜያዊ መደናገጥና መሸበር ከመፍ
ጠር ባሻገር በመሠረቱ ዘላቂና ጠቃሚነት
ያለው ውጤት ለላመጡም ፣ የአመጾቹ
የተበታተኑና ያልተቀናጁ መሆን ፣ የአድ
ሃሪው መንግሥት የኃይል ጥፍጠፋም ከሚ
ችሉት በላይ መሆን በተወሰነ ክፍሎች (ክል
ሎች) ለመግታታቸውና በአጭርም ለመቀ
ጠታቸው ዋነኛው ምክንያት ነበር ።[4]

በዚህ በኩል የነበረው ድክመትና ችግር
የአጋጣሚ ክስተት ሳይሆን ገበሬው እራሱን
ችሎና እንደመደብ ተደራጅቶ መታገል
ከሚያግደው ባኅርዩ የሚመነጭ የዚህ መ
ደብ መሠረታዊ ድክመት ነው ።

ስለ ኅሊናዊ ኃይሎች ሲወሳ ሊታለፍ
የማይገባውና በዚህ ረገድ የተሻለ ሁኔታ
በማሳየቱ የተለየ ግምት የሚሰጠው የተማሪ
ዎች ንቅናቄ ነው ። ከ1953 የመፈንቅለ
መንግሥት ሙከራ ወዲህ ፖለቲካዊ ይዘቱ
ይበልጥ እየጐላ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች
አካባቢ የተጀመረውና እያደርም በሀገሪቷ
በመላ ወደሚገኙት የሁለተኛ ደረጃ ት/
ቤቶች የተስፋፋው እንቅስቃሴ ከተቀሩት
ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ርዕዮተ ዓለማዊ
ዝንባሌ ነበረው ።

የዩኒቨርሲቲው ተራማጅ ተማሪዎች ከ
ውጪያዊው ዓለም ተራማጅና ፀረ-ኢምፔሪ
ያሊስት ትግሎች ጋር እንዲተዋወቁ በረ
ዳቸው አጋጣሚ በመጠቀም በኢትዮጵያም
ለተሻለና ለበለጸገ ኅብረተሰብ ግንባታ ድም
ጻቸውን ማሰማት የጀመሩት ከ1950 መ
ጀመሪያ አካባቢ ቢሆንም አመለካከታቸ
ው ውል ያለው ሆኖ ለመሠረታዊ ለውጥና
ለትግል ተነሱ ማለት የሚቻለው ከ1953
በኋላ ነበር ። ይህ ወቅት በተማሪዎች
ንቅናቄ በተለይና በኢትዮጵያ ተራማጅ
ኃይሎች ዕድገት ታሪክ ባጠቃላይ አዲስ

Digitized by Google

ምዕራፍ መክፈቱን ያበሰረው «የመሬት ላራሹ» መፈክር ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳ በት ነው ። ፖለቲካዊ ይዘቱ እየጐላና እየሰፋ የመጣው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋና እየ ተጠናከረ ሊሄድ የቻለው ስለሁኔታዎች በነበረው የተሻለ ግንዛቤ የሥርዓቱን አስ ከፊ ገጽታ በማጋለጥና ለሥር ነቀል ለውጥ ሕዝቡን በመቀስቀስ የሕዝብ ወገንነቱን ለማረጋገጥ በመቻሉ ነበር ። ንቅናቄው ስለኢትዮጵያ የነበረውን ግንዛቤ ከሌላ የተለየ የሚያደርገው በመጀመሪያ በግንባር ቀደም ተሳታፊዎቹ ፣ ኋላም ቁጥሩ በየጊ ዜው በጣም እየጨመረ በመጣው ተማሪ የማርክሲዝም ሌኒንዝም መመሪያ ተቀባይ ነት እያገኘ መሔዱ ነው ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ባለ ፈባቸው ደረጃዎች ውስጥ የነበሩትን ዝርዝር ሁኔታዎች እዚህ ላይ ወደጐን በመተው በአጠቃላይ በፀረ-ፊውዳልና በፀረ-ኢምፔ ሪያሊስት መስመር የተሰለፈ ሰፊ እንቅስ ቃሴ እንደነበረ ያለ ጥርጥር መናገር ይቻ ላል ። በሌላ በኩል ግን ካቀፏቸው አባላት የአመለካከት ልዩነት የተነሳ እንቅስቃሴው አንድ ወጥ አመራር ያልነበረው መሆኑ አያጠያይቅም ። በንቅናቄው ትጉህ አባላት አካባቢ በነበሩት ተማሪዎች ዘንድ ሲታዩ የነበሩት የሚጋጩና የሚገፉ አዝማሚያ ዎች የንቅናቄውን ባሕርይ በሚመለከቱ ጥያቄዎች በሚሰጡት መልሶች ላይ የሚ መሠረቱ ናቸው ። በተጨማሪ ግን ከትግል ልምድ ማነስ ጋር በሚያያዙ የግንዛቤ ችግር ችም የተለያዩ አዝማሚያዎች ሊዳብሩ ችለ ዋል ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ድም ጹን ሊያሰማ በቻለበት አካባቢ የፊውዳ ሉን ሥርዓት በይፋ በማጋለጥና ሰፊውን ሕዝብ ለረጅሙ ትግል እንዲዘጋጅ በመቀስ ቀስ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው አስተዋጽኦ እንደነበረው አይካድም ። ከዚህም ጋር የተ ማሪው ክፍል ለሕዝቡ ያለውን ወገናዊነት እንዲያጠናክር በማገዙ አብዮቱ ሲፈነዳ ተማሪዎችን የሕዝባዊ እንቅስቃሴው ግን ባር ቀደም ተሰላፊዎች አድርጓቸው እንደ ነበረም አይዘነጋም ። ከአብዮቱ እርምጃ ጋር ሰፊውን ሕዝብ የማንቃቱና የማደራ ጀቱ ተግባር ሕጋዊ መድረክ ባገኘበት ጊ ዜም ለዚህ ኃላፊነት የተደረገውን ጥሪ በመ ጀመሪያ ከተቀበሉት መሀል የተማሪው ንቅ ናቄ ያዘጋጃቸው ታጋዮች ቁጥር በጣም በርካታ ነበር ።

ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ በተጠቀሰውና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ ፣ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ በተለይም በአመራሩ አካ ባቢ መታየት የጀመሩትና ቀስ በቀስም እየሰፉ የሄዱት አዝማሚያዎች ከአብዮቱ ፍን ዳታ በኋላ በተማሪው ተሳትፎ ላይ በነበ ራቸው ተጽዕኖ የተወሰነው ክፍል አብዮቱ ን እንዲቃወምና እንዲወጋ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከአብዮቱ ፍ ንዳታ በኋላ በህቡዕ ይካሄድ በነበረው ትግል አሰላለፉ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የነበረው ድክመት ባብዛኛው የሚያንፀባርቅ ሆኖ ታይቷል ። በንቅናቄው ውስጥ የነበረው ችግር ይነስም ይብዛ በአብዮቱ ዕድገት ላይ ተጽዕኖ ነበረው የምንለው ለዚህ ነው ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የፊውዳሉን ሥር ዓት ከሥሩ ለመለወጥ ከዚያም በመ ለስ መጠነኛ የጥገና ጊዜያዊና መሠረ ታዊ ያልሆኑ መሻሻሎችን ለማስገኘት ም ቢሆን አስፈላጊ የሚሆኑትን የህ ሌናዊ ኃይሎች ዝግጅት በአጭሩ ለ መቃኘት ሞክረናል ። ለኅሊናዊ ኃይሎ ቹ አለመዳበር ቀደም ሲልየተጠቀሰው የመንግሥት ፀረ-ዲሞክራቲክነት አንደኛ ው ቢሆንም ፣ በመሠረቱ ግን ኅሊናዊ ሁኔታዎችበ ነባራዊ ሁኔታዎች ብስለት ላይ የሚመረኮዙ በመሆናቸው ለመሠረ ታዊ ለውጥ የሚያዘጋጅ ኃይል ተጧልቶ አለመገኘቱ እራሱ ነባራዊ ነው ። በሌላ አነጋገር የኅሊናዊ ኃይሎቹ ዝግጅት የሚ ታይበት ላዕላይ መዋቅር በወቅቱ በነበረው ኢኮኖሚያዊ መሠረት ላይ ሊገነባ አይ ችልም ነበር ።

በተማሪውና በምሁሩ አካባቢ ከአጠ ቃላዩ የኅሊናዊ ኃይሎች ዝግጅት አንፃር የተሻለ ሁኔታ ለመታየቱ ውጪያዊ ሁኔታዎች የነበራቸውን አስተዋጽኦ ለማየት የሚቻለውም ከዚህ ላይ ነው ።

የኅሊኒዊ ኃይሎች ወሳኝ ሚና ውጪያዊ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ከተሰነዘሩት አስተያየቶች በመነሳት በኋላቀር ሀገሮች ለማኅበራዊ

Digitized by Google

ዕድገት ኅሊናዊ ኃይሎች ዝግጅትና ጥንካሬ ከዓለም አብዮታዊ ሂደት ጋር የሚፈጠረው ግንኙነት ከፍተኛና በአንድ መልኩ ወሳኝ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ማየት አያዳግትም ።

ከኀላቀርነት ለመላቀቅ ያለው ፍላጐት ማቴሪያላዊ ዕድገትን በማስገኘት ብቻ ከተወሰነ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የሆነ ካፒታሊዝምን በማስፋፋት የኋላቀርነት መገለጫ ናቸው ከሚባሉት ምልክቶች መሀል ብዙዎቹን ማጥፋት ይቻል ይሆናል ። ሆኖም ግን በዚህ አቅጣጫ የሚደርስበት ዕድገት በሰፊው ሕዝብ ጉስቁልና የብሔራዊ ክበርቴውን ብልጽግና የሚያስገኝ ብቻ ስለሚሆን ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ሊጠቀም የሚችለው ዕድገቱ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ ጉዳናን የተከተለ እንደሆነ ብቻ ነው ። ስለዚህም ምንም እንኳ የአብዮቱ ባህርይ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ነው ቢባልም በመሠረቱ ካፒታሊስት ይዘትም ስላለው ትግሉ የሚያተኩረው የኢምፔሪያሊዝምን ብዝበዛ በማስወገድና ፊውዳሊዝምን በመደምሰስ ላይ ብቻ አይደለም ። ስፋትና ጥንካሬው በየደረጃው የተለያየ ይሁን እንጂ የካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት እንዳይስፋፋና ሥር እንዳይሰድም በመካላከል ፣ ያለውንም በማዳከም የማጥፋት ዓላማ አለው ። የትግሉ ዓላማ ይኸ መሆኑ የተመረጠውን የዕድገት ፈለግ በማሳየት ለዚህም ተግባራዊነት ከኅሊናዊ ኃይሎችን የሚጠበቀውን ድርሻ አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ለካፒታሊዝም ማደግ የተመቸ ነባራዊ ሁኔታ መኖሩም መዘንጋት እንደሌለበት ያመለክታል ። ስለዚህም ካፒታሊዝምን በመዝለል ሶሻሊዝምን እንገነባለን ሲባል አዲሱን የምርት ግንኙነት ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ ለተፋላጊዎች ገቦች ሁኔታ እንፈጥራለን ማለት ነውና ለዚህ ዕውን መሆን ላዕላይ መዋቅሩ የሚኖረውን የወሳኝነት ሚና መገንዘብ ይቻላል ። ይህ ባይሆንማ ኖሮ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጉዳና ተከትለን ሶሻሊዝምን እንገነባለን ማለት ባልቻልንም ነበር።

አሁን የምንገኝበት የሽግግር ወቅት ፣ በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በባኅላዊ መስኮች በሚከናወኑ አብዮታዊና አፋጣኝ ተግባሮች የሶሻሊዝም ቅድመ ሁኔታ የሚፈጠርበት ወቅት ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ መከናወን ያለባቸው ተግባሮች የሰመረ ውጤት ማግኘት የሚወሰነው በኅብረተሰቡ የላዕላይ መዋቅር ይዘት ሲሆን ፣ ወቅቱ ፖለቲካው ከኢኮኖሚው ቀዳሚ ሆኖ በጉልህ የሚታይበት ወቅት ነው ። ስለዚህም ነው በዚህ የሽግግር ጊዜ የአብዮቱ ኅሊናዊ ኃይሎች ሚና ወሳኝነት የሚኖረው ። የኅሊናዊ ኃይሎች በዚህ ረገድ ብቁ መሆን ግለትም የርዕዮተ ዓለማዊ መመሪያቸው ሳይንሳዊነትና ድርጅታዊ አንድነታቸውና ጥንካሬያቸው የሚገልጽባቸው የሶሻሊዝም የላዕላይ መዋቅር አካሎች ናቸው ።

የኅብረተሰቡ ማቴሪያላዊ የዕድገት ደረጃ እነዚህን በራሱ ሊያዳብር ስለማይችል ከዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ጋር ሊኖር የሚገባውን የተቀራረበ ግንኙነት አስፈላጊ መሆን ማየት ይቻላል ። «ይህም ግንኙነት የሶሻሊስት ላዕላይ መዋቅር አካሎችን ፣ በተለይም የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለምና በማርክሳዊ ሌኒናዊ መርሆች ላይ የተገነባ የፖለቲካ ፓርቲን ዕድገት በሚመለከት ረገድ የተለየ ጠቀሜታ አለው ።»

የኢትዮጵያ አብዮት ለተጐናጸፋቸው ድሎች መገኘት ፣ በተደረገው ትግል ከሶሻሊስት ሀገሮች ልምድ የቀሰምነው ትምህርት ፣ የማሌ ርዕዮተዓለም፡ በሰፊው መሠራጨትና ካድሬዎችን በማሰልጠን ረገድ እነኙሁ አገሮች የሰጡት ድጋፍ ፣ ለግንኙነቱ አስፈላጊነትና ወሳኝነት በቂ ማስረጃ ነው ።

የአብዮቱ ብሔራዊ ቅርጾችና ሁለንተናዊ ይዘት

ባለፉት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ አብዮት ካለፈባቸው ደረጃዎችና በኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ መስኮች ካስከተላቸው ለውጦች አንፃር ብሔራዊ ቅርጾቹንና ሁለንተናዊ ይዘቱን ለመመርመር ከመሞከራችን በፊት ቀደም ሲል የተጠቀሰው አብዮቱ የተነሳበትን ሶስዮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እዚህ ላይ በድጋሚ መመልከቱ ይጠቅማል ።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ምኅዋር (Orbit) ውስጥ መገኘት ፣ ለማኅበራዊ ዕድገት እን

Digitized by Google

ቅፋት ለነበረው ለጥምር ሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ
ቅንብር መኖር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል ።
በአንድ በኩል የፊውዳሉ የምርት ግንኙነት
በሰፊው የሰፈነ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በ
ጣም አነስተኛ በሆነ ገምት በማቆጥቆጥ ላይ
የነበረው የካፒታሊስታዊ ግንኙነት ለብሔ
ራዊ ኢኮኖሚና በጠቅላላውም ለማኅበራዊ
ዕድገት ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ ሳያ
ደርግ የውጪ ካፒታሊስቶችን የሚጠቅም
ክፍል ነበር ። ይህን ከመሰለ ማቴሪያላዊ
ግንኙነትና ከተቀጥላዎቹ የሚነሱት ቅራኔ
ዎች እየከረሩ መጥተው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ
በአንድ ወገን ፣ በፊውዳሊዝም ፣ በኢምፔ
ሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም
በሌላ ሆነው ለመደብ ፍልሚያው በከፍተኛ
ደረጃ መካሄድና ሁኔታው ሲሟላ የተጀ
መረው ትግል በሰፊው ሕዝብ አሸናፊነት
ወደፊት መራመድ የግድ መፈጸም የነበ
ረባቸው ተግባሮች ነበሩ ። በነዚህም ተግ
ባሮች ምንነት ነው የአብዮቱ ባሕርይ
የሚገለጸው ። የአብዮቱም ባሕርይ የሚመ
ነጨው ደግሞ ከዚህ አብዮት ከተነሳበትና
ከሚካሄድበት ሁኔታ ነው ።

ለሰፊው ሕዝብ መበዝበዝና መጨቆን ፣
ለኅብረተሰቡም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ
ኋላቀርነት ምክንያት የሆኑትን ፊውዳሊዝ
ምና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ መነ
ሳት የአብዮቱ ዓይነተኛ መለያ ነው ። የሀገ
ሪቷን ኢኮኖሚ ከኢምፔሪያሊዝም ተጽዕኖ
ነጻ ለማድረግና ፣ የፊውዳሉን ገዥ መደብ
ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የበላይነት በማስ
ወገድ ፣ ሰፊው ሕዝብ እራሱን በራሱ የሚ
መራበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ የብሔራዊ
ዲሞክራሲያዊ አብዮት መካሄዱ ግዴታ
ነው ።

ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ካፒ
ታሊዝም ባልተስፋፋባቸውና ባልዳበረባ
ቸው አገሮች የሚካሄድ አብዮት ሲሆን
ዓላማው በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በባሕላዊ
መስኮች ውስጥ ለሶሻሊዝም ግንባታ አመቺ
ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ ቅድመ ሁኔታዎችን
የመፍጠር ነው ። ቀደም ሲል እንደገለጽ
ነውም ከብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች ዕድ
ገት አኳያ ይህ አብዮትም በይዘቱ ለ
ውጥ አሳይቷል ። በ1969 ሞስኮ ላይ
በተሰየመው የኮሚዩኒስትና የሠራተኛ ፓር
ቲዎች ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በትክክል
እንደተገለጸው «ካለፉት አሥር ዓመታት
ወዲህ የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች ፀረ-ኢም
ሪያሊስት እንቅስቃሴ ጊና ከማደጉም በላይ
በአንዳንድ ሀገሮች ይህ እንቅስቃሴ ፀረ
ካፒታሊስታዊ ይዘት እያገኘ መጥቷል ።»

የኢትዮጵያ አብዮት ከተነሳበት ነባራ
ዊና ሕሊናዊ ሁኔታ ፣ በሂደቱ ውስጥ
ከነበረውና ካለው የመደቦች አሰላለፍና
ከዓላማው አንፃር ሲተነተን ከዚህ በላይ
ከተገለጸው ውጪ አይሆንም ። ስለዚህም
በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃዎች ባሉ ኅብረተ
ሰቦች ውስጥ ለሶሻሊዝም መሠረት መጣል
መከናወን ያለባቸውን ተግባሮች መፈጸም
ይኖርበታል ማለት ነው ። ሆኖም ግን ፣
እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባውን አንድ
ነጥብ ማንሳት ያስፈልጋል ።

ማርክስና ኤንግልስ እንዳስረዱትና
ኋላም ሌኒን እንዳብራራው ቅድመ ካፒታሊ
ስት ኅብረተሰቦች ካፒታሊዝምን በመዝ
ለል ሶሻሊዝምን መገንባት መቻላቸው ግል
ጽና ትክክለኛ ጽንሰ ሀሳባዊ መሠረት አለ
ው። ለዚህም ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገ
ት ጐዳናን በመከተል ዛሬ ሶሻሊዝምን በመ
ገንባት ላይ ያሉ ሀገሮች መኖራቸው በቂ
ማስረጃ ነው ። ነገር ግን ተግባራዊነቱ
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታየ አዲስ የታሪክ ክስ
ተት በመሆኑ በዚህ የዕድገት አዝማሚያ
ውስጥ ይኖራሉ ተብለው የሚገመቱ አጠ
ቃላይ ባህርያትን ማመልከት ቀላል አይደ
ለም ። የካፒታሊዝምን ወይም የሶሻሊዝምን
ዕድገት የሚገዙ ሕጐችን ለይቶ በማውጣት
ተፈጻሚነታቸውን በየትኛውም ሥፍራ
መጠየቅ የሚቻለውን ያህል ካፒታሊስታዊ
ያልሆነ የዕድገት ጐዳናን የሚገዙ ሕጐች
አሉ ብሎ መናገር ያስቸግራል ። ምክንያ
ቱም በተመሳሳይ የቅድመ ካፒታሊስት
ዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኅብረተሰቦች
የተለያየ የዕድገት አቅጣጫ የሚከተሉ መ
ሆናቸው ስለሚታይ ነው ።

በዚህ በኩል ጥናትና ምርምሩ መቀ
ጠል ያለበት ቢሆንም ብሔራዊ ዲሞክራሲ
ያዊ አብዮት ባካሄዱና በማካሄድ ላይ ባሉ
አገሮች መሀል መሠረታዊ አንድነት ያላ
ቸው ገጽታዎች መታየታቸው ግን አይካ
ድም ። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ
አብዮት ብሔራዊ ቅርጸችና ሁለንተናዊ

Digitized by Google

ይዘት በአበዮት ጉዳዮች ላይ በመወሰን ለማሳየት እንሞክራለን ።

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ሶሻሊስታዊ የዕድገት ጉዳናን ከመረጡ ከሌሎች ኅብረተሰቦች ጋር የሚለያባቸው ገጽታዎች ቢኖሩትም በሽግግር ወቅት ውስጥ መከናወን ያለባቸውን መሠረታዊ ተግባሮች ባሕርይ የሚለውጡ ሳይሆን ተግባሮቹ በሚገለጹባቸው ሁኔታዎች ወይም ተቋሞች ልዩ መሆን የሚከሰቱ ናቸው ።

የኢትዮጵያ አብዮት ከመሰሎቹ ጋር በትግሉ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀር-ፊውዳል ባሕርይው አንድ ሆኖ በዚህ አገላለጽና አፈጻጸም ግን ልዩነት ሊያሳይ ይችላል ። የአንድነቱ መግለጫ ባሕርይ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጉዳና ውስጣዊ ይዘት ሲሆን ልዩነቱ ግን ከኅብረተሰቦቹ የመደብ መዋቅር ፣ የኃይል ሚዛን ፣ የተለያዩ ስልተምርቶች ጐን ለጐን የመገኘት ሁኔታና የዓለም አቀፍና የሪጅናል ኃይል አሰላለፍ ሁኔታ የተለያዩ ከመሆን የሚመጣ ነው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ አብዮት በኤኮኖሚ ፣ በፖለቲካና ፣ በባሕል ዘርፎች ያደረጋቸው ለውጦችና ወደፊትም በዚህ አቅጣጫ የነደፈው ትልም መሠረታዊና አጠቃላይ በሆነ መልኩ ሲታይ ሁለንተናዊ ይዘት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን ። ይህም ማለት በተጠቀሱት መስኮች የተከናወኑትና የሚከናወኑት ተግባሮች ለኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ ሲባል የተነደፉና የተፈጸሙ ሳይሆኑ በየትም ቦታ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ይዘት ያለው ትግል የሚጠይቃቸው ናቸው ። ይህ መሠረታዊ አንድነት በመኖሩም ነው ከሌሎች አብዮቶች ታሪክ መማር የሚቻለው ። ይህ ሁለንተናዊ ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በአገላለጹና በአፈጻጸሙ የራሱ የሆኑ መልኮች እንዳሉት በተለያዩ መስኮች ከተወሰዱት ሥርነቀል እርምጃዎች በግልጽ ማየት ይቻላል ። የኢትዮጵያ አብዮት ልዩ ባህሪያት የሚባሉትም የሚመነጩት ከዚሁ ሁኔታ ነው ።

በኢኮኖሚው ረገድ

ማንኛውም ዲሞክራቲክ አብዮት ቀደምት ኢኮኖሚያዊ እርምጃ የፊውዳሉን የምርት ግንኙነት በማንኮታኮ ት «መሬት ላራሹ» የሚለውን መፈክር ተግባራዊ ማድረግእን ደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ አብዮት አፋጣኝ መልስ አግኝቶ ሥርነቀል የሆነ የመሬት ሥሪት ለውጥ ተደርጓል ። በብዙ ሀገሮች ይህ ተግባር የተከናወነው ቀስበቀስና በየደረጃው ሲሆን በኢትዮጵያ ግን በአንድ ወቅት በሁሉም አካባቢ ተፈጻሚነት እንዲኖረው መደረጉ ፣ ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ነጥብ ነው ። የባላባትና የጢሰኛ ግንኙነት ሳይወገድ የአርሶ አደሩን በአብዮቱ መሳተፍ በተፈለገው ስፋት ማግኘት አይቻልም ለየካቲት 25/67 የገጠርን መሬት የሕዝብ ንብረት ለማድረግ ለወጣው አዋጅ ሰፊው ሕዝብ የሰጠው ወደር የሌለው ድጋፍ የመሬት ጥያቄ መመለስ የቱን ያህል አንገብጋቢ እንደነበር የሚያስረዳ ነው ።

ከዚህ ተቀዳሚ ፀረ-ፊውዳል እርምጃ ጋር የሚያያዘው ልዩነት አፈጻጸሙን በሚመለከት የነበረው ሁኔታ ነው ። የፊውዳሉ ቢሮክራሲ በነበረው የመሬት ሥሪት አንደኛው ተጠቃሚ የነበረ በመሆኑ ፣ አርሶ አደሩን የምርቱ ባለቤት የሚያደርገውን አዋጅ ሊያስፈጽም እንደማይችል፣ በነበረው ትክክለኛ አስተያየት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ 60 ሺህ ወጣት ተማሪዎች ፣ መምህራንና መለዮ ለባሾች በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ማዝመቱ ነበር ። የሌሎች አገሮችን ልምድ ያየን እንደሆነ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ወይም የብሔራዊ አርነት ግንባሮች ፣ ሥልጣን ከመጨበጣቸው በፊትም ወይም በኋላ ለመሬት ላራሹ መሆን አባሎቻቸውና ካድሬዎቻቸው ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸው መሆኑን እንረዳለን ።

ሌኒን እንዳለው የመሬት ላራሹ መሆን ነጻነት ላራሹ ከመሆን ጋር አብሮ መሄድ ስላለበት የመሬቱና የምርቱ ባለቤት የሆነው አርሶ አደር አብዮቱ ያስገኘለትን ድል በመጠበቅና የራሱን ጉዳይ እራሱ እንዲፈጽም በጠላቱ ፊት የተጠናከረ ሆኖ በመገኘት አብዮቱን ከጥቃት መከላከል እንዲችል ፣ ከዚህም በላይ ደግሞ ወደፊት በሚመሠረተው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለሚኖረው ድርሻ ልምድ እንዲያገኝና እንዲዘጋጅ የሚያስችለውን ዲሞክራሲያዊ መብቱን የተቀዳጀበትን የገበሬ ማኅበራት ከቀበሌ እስከ አገር አቀፍ ለመመሥረት ተችሏል ። የኢትዮጵያ አርሶ አደር በቅድመ አብ

Digitized by Google

ዮት ጊዜ ክባድ በደልና ሥቃይ ይደርስበት
የነበረውን ያህል በአብዮቱ የመጀመሪያው
ተጠቃሚ ሆኗል ። የዚያኑ ያህል ደግሞ የሽ
ፍቱ ፊውዳሎች ፣ ተገንጣይ ወንበዴዎች ፣
የሱማሊያ ወራሪዎች በአብዮቱና ፣ በእናት
ሀገሩ ሕልውና ላይ በቃጡት ጥቃት ከፍተኛ
ጉዳት ደርሶበታል ። ከዚህም በላይ የኢት
ዮጵያን አብዮትና አንድነት ለመጠበቅ
በየጦር ግንባሩ በመዝመት ከፍተኛ መስ
ዋዕትነት ከፍሏል ።

በኢኮኖሚው መስክ የተወሰደውም ሌ
ላው እርምጃ ከአብዮቱ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት
ይዘት የሚመነጭ በመሆኑ በአጠቃላይ
መልኩ ከሌሎቹ አብዮቶች ጋር ቢመሳሰ
ልም ወደ ዝርዝር ሁኔታዎችና የአፈጻ
ጸም ሂደቶች ብንገባ ልዩነት መታየቱ አይ
ቀርም ። እንደማንኛውም ብሔራዊ ዲሞክራ
ሲያዊ አብዮት ፣ የኢትዮጵያም አብዮት ፣
በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ፣ የታ
ላላቅ ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶችን ፣
የገንዘብና የኢንሹራንስ ተቋሞችን በመን
ግሥት ቁጥጥር ሥር አድርጓል ። ይህ
እርምጃ ከኢምፔሪያሊዝም ነጻ ለሆነ የብሔ
ራዊ ኢኮኖሚ ግንባታና በሕዝብ ኑሮ መቆ
ርቆዝ የሚዳብረውን የብሔራዊ ካፒታሊ
ዝም ዕድገት በአጭሩ ለመቅጨት የሚያ
ስችልና ለሶሻሊዝም መሠረት መጣል ፣
በልዩ ልዩ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች መሠራት
ላለባቸው ሥራዎች ፍሬያማ መሆን ወሳኝ
ነበር ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የመንግ
ሥት እንደነበሩ የሚነገርላቸው ፣ ነገር ግን
የግለሰብ ፊውዳሎችና የንጉሣዊ ቤተሰብ
አባሎች መጠቀሚያ የነበሩ ፋብሪካዎች
ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት
ድርሻቸው ከ20-25 በመቶ ብቻ ነበር ።
በጥር ወር 1967 ዓ. ም. በወጣው አዋጅና
ከዚያም በኋላ በተከታታይ በተወሰዱት
እርምጃዎች ዛሬ ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ
ምርት የመንግሥት ድርሻ ወደ 80 በመቶ
ተጠግቷል ። [7]

የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት ለኢትዮጵያ
አብዮት ያለው በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊ
ነት መርህ ላይ የተመሠረተ ድጋፍ፡ የተገለ
ፀባቸው መስኮች በኢኮኖሚ ግንባታው
ያደረገው ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ ዕርዳታ
አንዱ ነው ። በሶቪዬት ኅብረትና በሌሎቹ
ሶሻሊስት ሀገሮች የሚሰጠው ዕርዳታ በኢ
ትዮጵያና በነዚህ ሀገሮች መሀል ካለው የተ
ናጠል ግንኙነት የሚመነጭ ሳይሆን የኢት
ዮጵያ አብዮት ከዓለም አቀፍ አብዮት
አካልነቱ ያገኘው ነው። የኢትዮጵያ አብዮት
ድል ማድረግ የዓለም ፀረ-ኢምፔሪያሊስት
ትግልን አሸናፊነት የሚያበስር በመሆኑ
የሶሻሊስቱን ሥርዓት የሚያጠናክረው ነው።
ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጉዳና በመ
ከተል የሶሻሊዝምን ምሥረታ ዕውን ከሚያ
ደርጉት ሁኔታዎች መሀል ታላቅ ግምት የሚ
ሰጠው ድል ካደረገው ሶሻሊዝም የሚያ
ገኘው ድጋፍና እርዳታ አንዱ በመሆኑ
በኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪ ዕድገትና ለዘመ
ናዊ እርሻ ሥራ መስፋፋት ከፍተኛ አስተ
ዋጽኦ አለው ።

በመሠረቱ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት
ውስጥ በኢኮኖሚው መስክ የሚታየው
ሁኔታ የሽግግር ወቅት ተግባሮች በአጠ
ቃላይ የሚከናወኑ መሆናቸውን ያመለክ
ታል ። የተቀየሰው የልማት ስትራቴጂም
በእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚው በተለይም በገበ
ሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት
መስፋፋት ላይ ማተኮሩ የኢትዮጵያን ተጨ
ባጭ ሁኔታ በትክክል ከማመልከቱም በላይ
በመሠረቱ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ
የሚገኙ ሀገሮች ሊቀይሱት የሚገባው ዓይ
ነት በመሆኑ ሁለንተናዊነት ያለው ነው ።
በኢምፔሪያሊዝም ተጽዕኖ ምክንያት ኢን
ዱስትሪ ባለመስፋፋቱ ፣ ለሶሻሊዝም ግን
ባታ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ይህ ክፍለ
ኢኮኖሚ ከሞላ ጉደል በአዲስ መጀመር
አለበት ። ይሁን እንጂ ለዚህ የሚያስፈል
ገው ክምችት አብዛኛው ክፍል ሊገኝ
የሚችለው ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በ
መሆኑ ለዚህ ማደግ የሚሰጠው ቅድ
ሚያ ወሳኝ ነው ። ጓድ ሊቀ መንበር መን
ግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከ
ላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት
ሪፖርት ላይ «ለእርሻው ዘርፍ ዕድገት
ቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንዳለብን»
አጠያያቂ እንደማይሆን ከገለጹ በኋላ እን
ዳሉት ፣

---እርሻችን ዛሬ በሚገኝበት የተበታተ
ነና ኋላቀር ሁኔታ ዕድገቱን ለማፋጠንና
የኢንዱስትሪ ግንባታ የሚጠይቀውን የጥ
ሬት ክምችት ለማፍራት እንደማንችል ግልጽ
ነው ።

Digitized by Google

በተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀምና ቴክኖሎጂን በገጠር በማስፋፋት የገብርናውን ክፍል ኢኮኖሚ የምርት ውጤት ለማሳደግ በመጀመሪያ የገበሬው ይዞታ ለከፍተኛ ምርት ከንዋኔ በሚያመች መልክ መደራጀት አለበት ። ይህንንም ለማድረግ የምርት ግንኙነቱ መለወጥ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው ።

ሰፊ የሆነውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ወደ ከፍተኛ የምርት ደረጃ ለማሸጋገርና በገጠርም ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚቻለው የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማስፋፋት ብቻ ነው ።

በዚህም መልክ በተቀየሰው የልማት ስትራተጂ መሠረትም በገጠርና በከተማ የገበሬዎችና የዕድጥበብ ባለሙያዎችን በማደራጀት የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት የሚያበረታቱ ውጤቶች ተገኝተዋል ።

የኢትዮጵያ አብዮት ዛሬ በሚገኝበት ደረጃ የሽግግር ወቅት ኢኮኖሚያዊ ተግባሮችን በአጠቃላይ በማንጸባረቅ በየዘርፉ ለሶሻያሊስታዊ የምርት ግንኙነቶች መብቀል አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር በተቀየሰው ትክክለኛ የልማት ስትራተጂ በሥራ መዋል በየአቅጣጫው ጥረቱ እጥፍ ድርብ መሆን ያለበት ወሳኝ ጊዜ ላይ ተደርሷል ።

በፖለቲካው መስክ

በጋራ ባለንብረትነት ላይ የተመሠረተ ሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ ቅንብር ከበዝባዥ ሥርዓት ሊወለድ እንደማይችል ዕውቅ ነው ። የንብረት ግንኙነቱን ብዙሀኑ ሠራተኛ ሕዝብ በሚጠቀምበት መልክ ለመለወጥ ከሁሉ በፊት በዝባዥ መደቦች ለጥቅማቸው የቆመዉን የምርት ግንኙነት ጸንቶ እንዲቆይ የሚጠቀሙበትን መሣሪያ መንጠቅ ያስፈልጋል። ስለሆነም ዛሬ ከቀድሞዎቹ ሥርዓተ ማኅበሮች የሽግግር ሂደት በተለየ ሁኔታ የላዕላይ መዋቅሩ መለወጥ የታህታይ መዋቅሩን መለወጥ ይቀድማል ። በሌላ አነጋገር ፖለቲካው ኢኮኖሚን ይቀድማል ማለት ነው ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በፖለቲካዊ መስኮችም የሶሻያሊዝምን መሠረት መጣል ያለበት በመሆኑ በዚህም በኩል የኢትዮጵያን አብዮት ብሔራዊ ቅርጽና ሁለንተናዊ ይዘት ለመዳሰስ እንሞክራለን ።

ለሶሻያሊዝም መመሥረት ጥርጊያውን በማዘጋጀት ረገድ ውጤቱ የሚወሰነው በፖለቲካው መስክ በሚኖረው እንቅስቃሴ ይሆናል ። በዚህ መስክ የሚከናወኑት ተግባሮች ከተለያዩ አቅጣጫዎችና (ከመንግሥት ፣ ከፓርቲና ፣ ከብዙሀን ድርጅቶች) በተለያዩ አካሎች የሚፈጸሙ ናቸው ። የየሀገሩን ፖለቲካዊ ሥርዓት አካሎች በሁሉም አቅጣጫ ተመሳሳይ ሆነው ማግኘት ባይቻልም ከተወሰኑ መመዘኛዎች አንጻር ሲታዩ በሁሉም የሚንጸባረቁ አጠቃላይ ባህርይዎች እንዳሉ መረዳት ይቻላል ። እነዚህ መመዘኛዎች የፖለቲካዊ ሥርዓቱ ማኅበራዊ አገልግሎትና መደባዊ ባህርይ ናቸው ። ፖለቲካዊ መዋቅሩን የሚወስነው መሠረታዊ ጉዳይ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጉዳናን በሚከተሉ ሀገሮች የሚገኘው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዋቅር በመሆኑ የተመሳሳይነት ምንጩም ይኸው ነው ።

መንግሥት

በኢትዮጵያ አብዮት ፖለቲካዊ ገጽታው ሲመረመር በመሠረቱ የሽግግር ወቅት ባህርያት የሚታዩበት ቢሆንም ከሌላው ፍጹም ልዩ የሚያደርጉት ሁኔታዎችም እንዳሉት ግልጽ ነው። ከፖለቲካዊ ሥርዓቱ አንደኛው አካል ማለትም ከመንግሥት (s t a t e) ብንጀምር በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት እንደማንኛውም መንግሥት መደባዊ ባሕርይና ማኅበራዊ አገልግሎት ያለው ነው ። ይህ መንግሥት የሚገኘው በተወሰነ የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃ (ካፒታሊዝምን በመዝለል ሶሽያሊዝምን ለመገንባት መሠረት በመጣል ላይ ያለበት) ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ራሱን የሚገልጹት ባህርያት ይኖሩታል ።

በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ከማህበራዊ ባህሪይው ሲገመገም በኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ መደቦች ላይ ያለውን አቋምና ወገናዊነት የሚንጸባረቁት ፖሊሲዎች ፣ መሠረታዊ ማኅበራዊ ችግሮችን ለማስወገድ በሚጠቀምባቸው የአቀራረብ ስል

ቶች ፡ በየመስኩ ባለው ክንዋኔ በሚታይበት ዝንባሌና በሚከተለው አቅጣጫ ፡ ለሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ የቆመ ለመሆኑ በየደረጃው በወሰዳቸው አብዮታዊ እርምጃዎችና ወደፊትም እንደሚከተላቸው ባወጣቸው ዕቅዶችና ግቦች ያለጥርጥር ለማረጋገጥ ቻላል ።

ይህም ማኅበራዊ ባህሪይው በተመሳሳይ ደረጃ ከሚገኙና አንድ የዕድገት ጐዳናን ከሚከተሉ መንግሥታት ጋር በይዘት አንድ ያደርገዋል ። ይሁን እንጂ በማኅበራዊ ባህሪውና አገልግሎቱ የሕዝብ ወገንነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥቱ ቅርጽና በአወቃቀሩ ልዩነት ይታይበታል ። ይህም የአብዮቱ ብሔራዊ ቅርጽ ከሚከሰትባቸው ሁኔታዎች መሀል አንዱ ሲሆን የመንግሥቱ የወታደራዊ አስተዳደርን ቅርጽ መያዝ ከኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የመደብ ኃይል አሰላለፍና የፖለቲካ ባህል ዕድገት ልዩ ገጽታዎች አስገዳጅነት የተከሰተ የታሪክ አጋጣሚ ውጤት ነው ። የኢትዮጵያን አብዮት ለማጥላላት ከሚጥሩ ኃይሎች አካባቢ እንደሚነዛው ውዥንብር ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፡ እንደሌሎች ወታደራዊ አገዛዞች በመፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ የመጣ አይደለም ። የኢትዮጵያን አብዮት ፍንዳታና የመጀመሪያ ሰሞን ሁኔታዎችን ለተከታተለ ሁሉ በግልጽ እንደታየው መለዮ ለባሹ የሕዝቡን ጥያቄ አብሮ በማንሳት አፈሙዙን በገዥው መደብ ላይ በማዞር በሕዝባዊ እንቅስቃሴው ውስጥ የተሳተፈ ነበር። ከዚህም በላይ የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመው ከየክፍሉ ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ በተመረጡ አባሎች በመሆኑ በጥቂት መኮንኖች ዱለታና ሚሥጥራዊ ሴራ ከሚካሄድ የመፈንቅለ መንግሥት ክስተት ጋር ሊመሳሰል እንደማይችል ጉልህ ማስረጃዎች ናቸው ። የወታደራዊ መንግሥትም ጊዜያዊ መሆን ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ያለውን ፍላጐት የሚያሳይ ከመሆኑም ሌላ ባለፉት ሰባት ዓመታት በዚህ መንግሥት የተወሰዱት እርምጃዎች የቱን ያህል ለዚህ ግብ መቃረብ እንደረዱ መመልከቱ አስቸጋሪ አይሆንም ።

መንግሥት በተለመደ ፍቺው የአንድን መደብ ወይም የአጋር መደቦችን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሣሪያ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ነው ። የተወሰኑ መደቦችን ጥቅም ለማስጠበቅ የሌሎች መደቦችን ጥቅም የሚነፍግ ስለሆነና በዚህ ተግባርም ባብዛኛው የማስገደድ ገጽታው ጉልቶ ስለሚታይበት የመንግሥትን ተግባር በዚህ መልኩ ብቻ መወሰኑ ስህተት ይሆናል ። መንግሥት አንድ መደብ በሌላው ላይ ያለውን የበላይነት የሚያረጋግጥበት መሆኑ በፖለቲካ ተግባሩ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚውና በርዕዮተዓለሙ መስክ በሚጫወተውም ሚና ጭምር ነው ።

በኢትዮጵያ የፊውዳሉ መንግሥት ከተደመሰሰ በኋላ የተተካው መንግሥት ከዚህ የተለየ ባለመሆኑ በኢኮኖሚያዊና በርዕዮተዓለማዊ ተግባሩም ሊተነተን ይችላል ። በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሚና በሚመለከት ረገድ የአብዮቱን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ፡ እንዲሁም ፀረ-ካፒታሊስት አቋም በተግባር ለመግለጽና የሶሻሊዝም ኢኮኖሚያዊ ቅድመ ሁኔታን ለማሟላት ሲባል በእርሻ በኢንዱስትሪ ፡ በንግድ ፡ ከፍላተ ኢኮኖሚዎች የመንግሥት ድርሻ ከቀድሞው በጣም የጨመረ ከመሆኑም ሌላ ወደፊትም ይበልጥ እንዲያድግ ጥረት በመደረግ ላይ ነው ። መንግሥት በብሔራዊ ኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ተሳትፎ የባለቤትነት ድርሻውን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን ፡ በግል ይዞታ ሥር ባሉት ክፍሎች ውስጥም ያለው ግንኙነት ለሠራተኛው መደብ በሚጠቅም መልክ እንዲሆን መመሪያና ደንቦችን በማውጣት ቁጥጥር ያደርጋል ።

በሽግግር ወቅት ኢኮኖሚ የመንግሥት ድርሻ ባጠቃላይ ይህን ሲመስል ፡ በተጠቀሱት አቅጣጫዎች በሚታየው የአፈጻጸም ስልትና የጊዜ ሁኔታ የተለያየ ነው ። የኢትዮጵያን አብዮት በሥርነቀልነቱና በእርምጃ አወሳሰዱ ቁርጠኝነትና ፈጣንነት ከተመሳሳይ አብዮቶች እጅግ ልዩ የሚያደርገው የታላላቅ ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶችና የገንዘብና የኢንሹራንስ ተቋሞችን በአንዴ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረጉና ለሠርቶ አደሩ በሚጠቅም መልክ ማደራጀቱ ነው ። ይህ ተግባር በእርግጥ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ባካሄዱ አገሮች የተወሰደ ቢሆንም በሌሎች አገሮች የተለያዩ ሁኔታዎች ታይተዋል ። ለምሳሌ

Digitized by Google

በአንዳንድ ሀገሮች የተወረሱት ኢንዱስትሪዎች ውጪ ካፒታሊስቶች ንብረት የሆኑና ተወሰነ አገር የመጣ ከሆነ ብቻ የተወረሰበት አገርም አለ) እነሱም ቢሆኑ የተጠቃለሉት ደረጃ በደረጃ ነበር ። የኢትዮጵያ አብዮት ግን በሌሎች አገሮች በረጅም ጊዜ የተጠናቀቀውን ሂደት በአንዴ በመፈጸም የመንግሥት ድርሻን በማሳደግ ፣ ለሕዝቡ መስጠት ባለበት አገልግሎትና የአብዮቱንና የሀገሪቱን ኀልውና ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን የመንግሥት ይዞታ በመፍጠሩ ረገድ የተወሰደው እርምጃ ፈጣንና ሰፊ አስተዋጽኦ ያለው ነው ።

በርዕዮተዓለሙ መስክ መንግሥት ያለው ድርሻም እንደዚሁ ለሶሻሊዝም ቅድመ ሁኔታ ከማመቻቸት ጋር የተያያዘ ነው ። ማርክሲዝም ሌኒንዝም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ እንዲሠራጭ ለማድረግ ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መውጣት ጋር የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ለአብዮቱ ግሥጋሴ ለሚሰጡት ግፊት የተሻለ ዝግጅትና ብቃት እንዲኖራቸው አብዮታዊው መንግሥት ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም የካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤትን ከመክፈት አንስቶ የመደበኛ ት/ቤቶችን ሥርዓተ ትምህርት እስከማሻሻል ፣ የሕዝብ ዜና ማሠራጫ ዘዴዎችን በስፋት በመጠቀም ፣ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ፣ መጽሐፍት በብዛት እንዲገቡ በማድረግ ፣ እንዲተረጐሙም በማበረታታትና በሌሎችም መንገዶች ለሠራተኛው መደብ ርዕዮተዓለም መስፋፋትና ለቡርዧው ርዕዮተዓለምና ለኋላ ቀር አስተሳሰቦች መዳከም ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል ።

ከላይ በአጭሩ በሰፈሩት ፣ ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ጉዞ መከናወን ያለባቸው ፖለቲካዊ ተግባሮችና በተለይም የመንግሥትን ሚና ስንመለከት በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ በመሠረቱ ተመሳሳይ እንደሆነ አይተናል ። ይህ እንዳለ ሆኖ በዚህ በኩል የአብዮቱን ብሔራዊ ቅርጽ በማንፀባረቅ የሚታዩት ክስተቶች የኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ መለያዎች ናቸው ። በኢትዮጵያ የሶሻሊስት ሥርዓት ምሥረታ በተያዘበት መንገድ መረጋገጥ ሌኒን እንዳለው ፣ ለተወሰነ ዓይነት ዲሞክራሲ ፣ የወዛደሩ የበላይ ገዥነትና ሶሻያሊስታዊ ዕድገት መከሰት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መገመት ይቻላል ።

በአሁኑ ጊዜ ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የዕድገት ጐዳናን በመከተል በተለያዩ ደረጃዎች የሶሻሊዝምን ቅድመ ሁኔታዎች በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ ከሚባሉ ሀያ ከሚሆኑ አገሮች በወታደራዊ መንግሥት የሚመራ ከኢትዮጵያ በስተቀር አንድም የለም ። በበርማ እስከ 1974 ድረስ ወታደራዊ አመራር የነበረ ቢሆንም እሱም ቢሆን በኢትዮጵያ ካለው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጋር ተመሳሳይ አልነበረም ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መቋቋም በፊውዳሉ ሥርዓት ላይ ዳር እስከዳር ተነስቶ ለነበረው የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥያቄ ምላሽ አስገኝቷል። የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ባብዛኛው ከሰፊው ሕዝብ የወጣና በአኗኗሩ ብዙ ያልተለየ በመሆኑ በሰፊው ሕዝብ ብሶትና ችግር መቀስቀሱ የግድ ነበር ። የፊውዳሉ መንግሥት ደግሞ ሠራዊቱን በመከፋፈልና እርስበርስ እንዳይተማመን በማድረግ የጥበቃ አገልግሎቱን አስተማማኝና ዘላቂ ለማድረግ ሲጥር የቆየ ቢሆንም የየካቲቱ ሕዝባዊ ቁጣ ሲገነፍል መለዮ ለባሹን ከሕዝቡ በመነጠል እንደለመደው መሣሪያው ሊያደርገው አልቻለም ። ይህ ብቻም ሳይሆን የተደራጀና የታጠቀው የመለዮ ለባሹ ኃይል ከሕዝቡ ጐን መሰለፍ ለእንቅስቃሴው ወደፊት መራመድ አስተማማኝ ጉልበት ስለሰጠው በአንጻሩም ደግሞ የገዥ መደቡን መሣሪያ አልባ አድርጐታል ።

መለዮ ለባሹ የሕዝቡን ጥሪ በመቀበል አፈሙዙን ወደ ፊውዳሉ መንግሥት ያዞረው አብዛኛው ክፍል ከሕዝቡ የተገኘ በመሆኑና ብሶቱን በመካፈሉ ብቻ አልነበረም ። ለዚህ አብዮታዊ ተሳትፎ ዝግጅት የተራማጅ አስተሳሰቦች በውስጡ መስፋፋት የማይናቅ አስተዋጽኦ እንደነበረውም መገመት አያዳግትም ። እንኳንስ በጦሩ ውስጥ በሌላውም አካባቢ ተራማጅ አስተሳሰቦች እንዳይስፋፉ የነበረው አፈና ለተወሰነ ጊዜ የሠራ በመሆኑ የፊውዳሉ መንግሥት ሠራዊቱን በፀረ ሕዝብ ተግባሮቹ ሲጠቀምበት ቢቆይም ይህ ሁኔታ ሊቀጥል አልቻለም ። ምክንያቱም «የተራማጅና የአብዮታዊ ኃይ

Digitized by Google

ሉች ሚናና ግፊት ከፍ እያለ መሄድና በው
ራዊቱ መሀልም መረጋገጥ የታሪክ ነባራዊ
አቅጣጫ ነውና»[9] አስተባባሪ ኮሚቴው
ከመቋቋሙ በፊትና ከዚያም በኋላ ሕዝባዊ
እንቅስቃሴውን በሚመለከት በኅብረተሰቡ
ውስጥ የነበረው የአቋም ግጭት በመለዮ
ለባሹ ውስጥም ሲንጸባረቅ ቆይቷል ።
በመጨረሻ ግን የትክክለኛ መስመር አሸ
ናፊ ሆኖ መውጣት በዚህ ውስጥ አብዮታዊ
ኃይሎች የነበራቸውን ጥንካሬ የሚያመለ
ክት ነው ። የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግ
ሥት ከተቋቋመም ወዲህ የመደብ ትግሉ
ይበልጥ እየተፋፋመና እየሰፋ በመሄዱ
በየደረጃው ባስከተለው ሽግሽግ በደርጉ
ውስጥ በተደጋጋሚ በታዩት ክስተቶች
በውስጥ ሲደረግ በነበረው ትግል የአብዮ
ታውያን በአሸናፊነት መውጣት የአመራር
አካሉን ይበልጥ እያጠራው መጥቷል ።
እዚህ ላይ አንድ አበክረን ልናስተውለው
የሚገባን ነጥብ አለ ። ደርግ ከተለያዩ የጦር
ክፍሉች የተወከሉ ግለሰቦች በአጋጣሚ
በአንድነት የተሰባሰቡበት አካል እንደመ
ሆኑ መጠን በመደብ ጀርባ ፣ ስለትግሉ
ግላቸው አስተያየት ፣ ትግሉ ሊመራበት
በሚገባው ስልት ላይ ፣ እንዲሁም በትግሉ
ዓላማና አቅጣጫ ላይ የተለያየና እንዲያ
ውም ተጻራሪ አስተሳሰቦች የሚታዩበት አ
ካል ነበር ። ያም ሆኖ በየደረጃው ይወሰዱ
የነበሩት ዕርምጃዎች የኢትዮጵያን አብዮት
ዕድገት የሚያረጋግጡ መሆናቸው የደርግ
ኮሚዩኒስቶችን የጠራ የትግል ስልት የሚያ
ሳይ ነው ።

የሠርቶ አደሩ ፓርቲ

በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የኅሊናዊ
ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ከሚለካበት መን
ገድ አንደኛው በድርጅት ረገድ ባለው ሁኔታ
ነው ። ሰፊው ሕዝብ የትግሉ ዓላማ ግልጽ
ሆኖለት በአብዮቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ንቃተ
ኅሊናው ማደጉ ብቻ በቂ አይሆንም ።
የዓላማና የተግባር አንድነት የሚገለጥበት
ድርጅት ያስፈልገዋል ። ይህ ድርጅት ግን
ኛውም ዓይነት መደባዊ ድርጅት ሳይሆን
የሠርቶ አደሩ ፓርቲ እንደሆነ ተደጋግሞ
የሚነገር ሀቅ ነው ። በመሠረቱ ግን የኅ
ሊናዊ ሁኔታዎች አለመሟላት የአብዮቱን
በአሸናፊነት ከዳር መድረስ የሚወስን እንጂ
ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ መጀመር የህሊናዊ
ኃይሎች ተሟልተው መገኘት ግዴታ አይ
ደለም ። ይህ ሊሆን የሚችለው ከአብዮቱ
ስትራቴጃዊ ግብ አንጻር እንጂ ከአብዮቱ
የቅርብ ጊዜ አላማዎች አንጻር አይደለም ።
ይልቁንም የኢትዮጵያ አብዮት ያስገኛቸው
ድሎች ሰፋት የአብዮቱን ስርነቀልነትና
ልዩ ባህሪ ያመለክታሉ ።

በዚህ በኩል ጓድ ሊቀ መንበር መንግ
ሥቱ ኃይለማርያም ከጋዜጠኛ ለቀረበላ
ቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ «የኢትዮ
ጵያን አብዮት ከሌሎች አብዮቶች ልዩ
የሚያደርገው ዓይነተኛ ነገር ያለወዛደሩ
ፓርቲ ሥርነቀል እርምጃዎችን እየወሰደ
እራሱን ከቅልበሳ ለመከላከል መቻሉ
ነው ።»[10] በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ አብ
ዮቱ ሲፈነዳ ሕሊናዊ ሁኔታዎች ተሟ
ልተው ባይገኙም በሂደቱ አብዮቱ ከፍ
ተኛ ድሎችን ከመቀዳጀት ሊያግደው አል
ቻለም ። አመራር አለመኖር ሳይሆን በአጠ
ቃላይ በአመራሩ የሚከናወኑት ተግባሮችና
የሚገኙት ድሎች ያለዚህ አመራር ዕውን
መሆንና ለረጅም ጊዜ እራሱን ከቅልበሳ
ለመከላከል መቻሉ ከጓድ ሊቀ መንበር
አስተያየት ጉልቶ መታየት ያለበት ጉዳይ
ነው ። ይህ ከተባለ ከሦስት ዓመት በላይ
ቢሆንም ዛሬም አብዮቱ የወዛደሩን ፓርቲ
አመራር ሳይቀዳጅ እራሱን ከቅልበሳ መከ
ላከል ብቻም ሳይሆን ተጨማሪ ድሎችን
እያገኘ መምጣቱ ለልዩ ባህርይው የተለየ
ክብደት ይሰጠዋል ። የዚህ ዕውነት መኖር
ግን በደፈናው ልዩ ነው ተብሎ የሚታለፍ
ሳይሆን የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ፣
የኢትዮጵያን ኮሚዩኒስቶችና ባጠቃላይም
የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የዓላማ ጽኑነትና
ቆራጥነት የሚያመለክት ነው ።

የሠርቶ አደሩ ፓርቲ ሳይኖር የኢትዮ
ጵያ አብዮት ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ መድረሱ
የፓርቲውን አስፈላጊነት በመገንዘብ ለም
ሥረታው መደረግ ካለበት ትግል የኢትዮ
ጵያ ኮሚዩኒስቶች የተዘናጉበት አንድም
ጊዜ የለም ። ጓድ ሊቀ መንበር በኢሠፓአኮ
አንደኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባቀረቡት ሪፖ
ርት ውስጥ «አብዮታችን የተጓደለበትን
የፓርቲ አመራር ለመቀዳጀት የተደረገው
ትግል ከአብዮቱ ተነጥሎ የማይታይ ከመ
ሆኑም በላይ በዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ሳቢያ
የተከፈለው መስዋዕትነት ከፍተኛ ነው።»[11]
በማለት በትክክል የገለጹት ለዚህ ጉልህ
ማስረጃ ነው ።

በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ የተለያዩ
የፓርቲ ምሥረታ ዘይቤዎች የተንጸባረቁ

Digitized by Google

ቢሆንም በወቅቱ ተሠንዝሮ የነበረውን ስሌት በመከተል ድርጅቶችን በማዋሀድ በኢማሌድህ በኩል የፓርቲውን ምሥረታ በተግባር ለመግለጽ የተደረገው ሙከራ የኢትዮጵያን አብዮት ልዩ ገጽታና የመደቦችን የኃይል አሰላለፍ በመገንዘብ ረገድ ለነበረው ድክመት አስተዋጽኦ አድርጓል ። በዚህ በኩል የነበረው ችግር ሲጠቃለል በአንዱ ወይም በሌላው አገር ድል አድራጊ የሆነ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ የተመሠረተበት ስልት እንዳለ በኢትዮጵያም ሊሠራበት እንደሚችል ተደርጐ መቅረቡ ነበር ።

በመጨረሻ ግን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒስቶች ጥያቄውን በጥልቀት በመመርመርና ሲያራምዱ የነበረውየፓርቲ ምሥረታ ሥልት ያስከተለውን ጉዳትና ፓርቲው በዚያ መልክ ቢመሠረት የሚያስከትለውን ጥፋት አሳሳቢነት በመገምገም ትክክለኛ የሆነ ሥልት ለመቀየስ በቅተዋል ። በዚህም ለፓርቲው ምሥረታ የተደረገው ትግልና የተከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ አለመቅረቱ ተረጋግጧል ።

የኢሠፓአኮ መቋቋም በኢትዮጵያ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ ለመመሥረት የሚያስችል ከኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ የመነጨ እንደመሆኑ መጠን የአብዮቱ ብሔራዊ ትርጉም ሌላኛው መገለጫ ነው ። ኢሠፓአኮ ለማሌ ሥርጭት መስፋፋትና ለሠርቶ አደሩ ፓርቲ መወለድ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ከመሆኑም በላይ የፓርቲ አሠራር መለማመጃም ጭምር በመሆኑ የተያያዝነው ትግል ፍሬያማ ውጤት እንደሚያስገኝ መገመት ይቻላል ። በዚህ አቅጣጫ እስካሁን የተሠራውን ብንመለከት ለዚህ ተስፋ ጠንካራ መሠረት ይሰጣል ።

ዛሬ ከኢሠፓአኮ ጎን ደግሞ ከሚመሠረተው ፓርቲ በሚገኘው አመራር ሰፊው ሕዝብ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ ከፍ እንዲልና ለሶሻሊዝም ግንባታ በልዩ ልዩ መስኮች የሚደረገው ዝግጅት በአፋጣኝ እንዲጧላ መደረግ ባለበት ትግል ሕዝባዊ ድርጅቶች ታላቅ ድርሻ አላቸው ። ከዚህም ግንዛቤ በመነሳት ቀደም ብሎ በአገር አቀፍ ደረጃ ተመስርተው ከነበሩት በተጨማሪ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራትን በየደረጃው በተሻለ መንገድ በማዋቀር አኢወማና አኢሴማን ለመመሥረት ተችሏል ። በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የነበሩትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ዛሬ አብዮቱ ከደረሰበት ደረጃና ወደ ፊት ከሚጠበቅባቸው ተግባር አኳያ ይበልጥ ዝግጁ ሁነው እንዲገኙ ለማድረግ በአዲስ መልክ ለማዋቀር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለማየት እንደሞከርነው በአብዮቱ ፖለቲካዊ ገጽታ የሚታዩት ሁኔታዎች ከዓላማውና ከተግባሩ አንጻር በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሂደት ውስጥ በዚህ መስክ መኖር ያለባቸውን ሁኔታዎች የሚያንጸባርቁ ቢሆንም፥ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አስገዳጅነት ልዩና ብሔራዊ ክስተቶች ያጋጥማሉ ። በዚህም የሕዝባዊ ድርጅቶች ሁኔታ ከሌላው የተለየ አይደለም ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

ዛሬ ዓለም በምትገኝበት ሁኔታ በየትኛውም ሀገር የሚደረግ እንቅስቃሴና የሚደረግ ለውጥ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መሀል ያለው ትግል ነጸብራቅ እንደሆነ በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል ። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ አብዮትም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፍና የነበረውን የኃይል ሚዛን ይበልጥ ወደ ሶሻሊስቱ ካምፕ እንዲያጋድል ያደረገ የዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ አካል ነው ።

Digitized by Google

በኢምፔሪያሊዝም መዳፍ ውስጥ ተጨብጣ በቆየችና በተራማጅ እንቅስቃሴዎች የሚበረግጉ አድሃሪ ኃይሎች በምትጕራበት ሀገር ለሥርነቀል ለውጥ የተቀጣጠለና በአሸናፊነት ወጥቶ ዛሬ ከሚገኝበት አስተማማኝ ደረጃ ላይ የደረሰ ሕዝባዊ ትግል መካሄዱ የኢትዮጵያ አብዮት ልዩ ባሕሪ የተከሰተበት ሌላው ሁኔታ ነው ።

የኢትዮጵያ አብዮት በውስጥ ፀረ አብዮተኞች የተቃጣበትን ጥቃት ከመበጣጠሱም በላይ በተለያዩ መልኮችና አቅጣጫዎች በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና በአካባቢው አድኅሮት የተቀነባበረውን የቅልበሳ ሤራ በማክሸፍ ለማኅበራዊ ለውጥ በቁርጠኝነት የተነሳው ሰፊው ሕዝብ ለማንኛውም ኃይል እንደማይበገርና ምንም ዓይነት መስዋዕትነት ከሚጠይቅ ትግል ወደኋላ የማይል መሆኑን ያረጋገጠ ታላቅ አብዮት ነው ። ኢትዮጵያ ከኢምፔሪያሊዝም መዳፍ አፈትልካ ለመውጣት ያበቃትን እንቅስቃሴ መጀመሯ ለፊውዳሉ ገዥ መደብ ዱብ ዕዳ የነበረውን ያህል ለኢምፔሪያሊስቶችም ቢያንስ በዚያን ጊዜ ያልጠበቁት ሁኔታ ነበር ። የየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ግፋ ቢል መጠነኛ ጥገናዊ ለውጥ በማስገኘት ላይ ያቆማል ብለው ሲጠብቁ ፣ ይተማመኑበት የነበረው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከወደቀ በኋላም ቢሆን የትግሉ አቅጣጫ ሥርነቀል ለውጥን ለማስገኘት ይሆናል ብለው ከቶውንም የጠረጠሩ አይመስልም ። ይህን ለመረዳት የተሳናቸው በመሆኑም ስትራቴጂካዊ አቀማመጧና ጠቀሜታዋ ከፍተኛ የሆነችው ኢትዮጵያ ከተጽዕኖ ክልላቸው እንዳትወጣ ለማድረግ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን በእንጭጩ ለመቅጨት በተለይ በመጀመሪያው ወቅት የተለየ ትኩረት ሊያደርጉበት አልቻሉም ። ይሁንና የአብዮቱ አቅጣጫ ግልጽ ሆኖላቸው ትኩረት ብቻ ሳይሆን እርምጃ መውሰድ በጀመሩበት ጊዜ ሁኔታዎች ከቁጥጥራቸው ውጭ ስለነበሩ አሜሪካ በኢትዮጵያ ስትራቴጃዊ ጥቅሙን ተገዶ እንጂ ፈልጎ አልለቀቀም ።

ማንኛውም ሕዝባዊ አብዮት የዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ አካል እንደመሆኑ መጠን ለዕድገትና ለድል አድራጊነቱ የብሔራዊና የዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ቅንጅት ይጠይቃል ። በዚህም አንጻር የኢትዮጵያ አብዮት ከውስጥና ከውጪ አድሀሪና ፀረ አብዮት ኃይሎች ቡርቦራና ወረራ እራሱን ሊከላከል የቻለው በሰፊው ሕዝብ ጥንካሬ ቢሆንም በሶቪዬት ኅብረት የሚመራው የሶሻሊስቱ ማኅበረሰብና የዓለም ተራማጅ ኃይሎች አስተዋጽዖ በቀላሉ የማይገመት ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በወቅቱ ለድላችን ወሳኝነት የነበረው መሆኑ አይዘነጋም ። የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት የኢምፔሪያሊዝም ወኪል በመሆን የኢትዮጵያን አንድነት ለማናጋትና ሁኔታውን ለአብዮት ቅልበሳ ለማመቻቸት የፈጸመውን ወረራና በሰሜን ተገንጣዮች እንቅስቃሴአቸውን በማፋፋም ከፈጠሩት ሁኔታ ለመውጣት በተደረገው ትግል በተለይ ሶቪዬት ኅብረት ፣ ኩባና ሕዝባዊት የመን ያደረጉት አስተዋጽዖ ምን ጊዜም ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ሕሊና የማይጠፋ ነው ። ይህን የመሰለና በሌላ ልዩ ልዩ መልኮች የሚገለፀው ድጋፍ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም አቀፍ አብዮት አካል መሆኑንና እሱን ከጥቃት ማዳን በውስጥ የአብዮቱ ሠፈር ጥንካሬ ፀንቶ እንዲቆይ ከመዋጋትና በአጠቃላይም የዓለም አብዮትን ለማጠናከር ከሚደረገው ዓለም አቀፍ ትግል ተነጥሎ የማይታይ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው ።

ለማጠቃለል የኢትዮጵያ አብዮት የሰፊውን ሕዝብ ብልጽግና ለማረጋገጥ ከተለመው ግብ አንጻር በሂደቱ ውስጥ የታዩት ደረጃዎችና ክስተቶች ብሔራዊ ቅርጽ ሊኖራቸው ቢችልም በአብዛኛው በይዘታቸው ዓለም አቀፋዊነት ወይም ሁለንተናዊነት እንዳላቸው ተመልክተናል ። በዚህም መሠረት በትግሉ በሚገኘው ማቴሪያላዊ ለውጥ ቀጥተኛ ተጠቃሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆንም ለዓለም ሶሻሊስት አብዮት እርምጃ አስተዋጽዖ ያደርጋል ።

ለሶሻሊዝም መገንባት የእውነተኛ ሰላም መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን የኢትዮጵያ አብዮት ለዓለም ሰላምና ለዴታንት ከሚታገሉ ኃይሎች መሀል የመጀመሪያው ረድፍ ተሰላፊ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል ። በዓለም የሰላም መስፈን የሚረጋገጠው ከፀብ አጫሪው ኢምፔሪያሊዝም ውድቀት ጋር በመሆኑ በየትም ሥፍራ ለሚደረጉ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎች ያልተቆጠበ ድጋፍ ከመስጠቱም

Digitized by Google

ሌላ ለብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች የሚያደርገው እርዳታና በጠቅላላው በዓለም አቀፍ መድረኮች ፣ ለነጻነት ፣ ለሰላም ፣ ለማኅበራዊ ዕድገትና ለሶሻሊዝም በሚደረገው ትግል ሰፊ ሚና በመጫወት የወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ግዴታውን በመወጣት ላይ ይገኛል ። ይህም የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሶሻሊስት እንቅስቃሴ አካል ለመሆኑ ተጨባጭ ማረጋገጫ ሲሆን በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት አቋሙ መፅናቱ በኢትዮጵያ ለሶሺያሊዝም አሸናፊነት ወሳኝ ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. ማርክስና ኤንግልስ ፣ ምርጥ ሥራዎች ፣ ቅጽ 1 ፣ ገጽ 39
2. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 23 ፣ ገጽ 60- 70
3. የኰምኒስትና የሠራተኞች ፓርቲ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ፣ 1961 ፣ በጂ. ግሌርማን ከመደቦችና ብሔሮች ከገጽ 65 የተጠቀሰ
4. መስከረም ፣ ቅጽ 1 ፣ ቊ. 1 ፣ ገጽ 9፣1973
5. Political systems-Development trends: "The dialectics of politics & economics in non-capitalist development" p. 104,
6. IMCWP, Moscow, 1969, p. 27.
7. መስከረም ፣ ቅጽ 1 ፣ ቊጥር 2 ፣ 1973 ፣ ገጽ 42
8. ኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ፣ ማዕከላዊ ሪፖርት
9. Marxism- Leninism, *On War and Army*, p. 216.
10. ጓድ ሊቀመንበርና የዓለም ጋዜጦች ፣ የካቲት 7 ቀን 1970 ፣ ገጽ 29
11. በኢሠፓአኮ አንደኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማእከላዊ ሪፖርት

Digitized by Google

ተስፋፊነትና ጠባብነት የሶማሌ ገዥ መደብ ዓይነተኛ ገጽታ

ሰሎሞን ዲባባ

ከካፒታሊስት ስርዓት ወደ ሶሺያሊዝም የሚደረገው ሽግግር የዘመናችን ዓይነተኛ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠባይ ነው ። ይህ ሽግግር በሰዎች በጎ ፈቃድ በፖለቲካ ድርጅቶች ፍላጎት ወይንም በመንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚከናወን ሳይሆን በዘመኑ አብይ ትራኔ ላይ የተመሠረተና በዓለም የፖለቲካ የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ውስጥ የሚከሰት የዲያሌክቲክስ የዕድገት ሕግጋት ነፀብራቅ ነው ።

በሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ማግሥት «በእኩልነት» ፣ በወንድማማችነትና «በነፃነት» ስም ከተዋቀረው ዓለም አቀፍ የቡርዧ ስርዓት ጎን «የዓለም ሠርቶ አደሮች ተባበሩ» በሚል ኮሚኒስታዊ መፈክር ሥር አያሌ ጭቁን ሕዝቦች ያሰለፈው የሶሻሊስት ስርዓት እያጎለበተ መጣ ። ቀድሞ በኢምፔሪያሊስት ቅኝ አገዛዝ ሥር ሲማቅቁ የቆዩትም የዓለም ሕዝቦች በብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴዎች አማካይነት ነፃነታቸውን ሲቀዳጁ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በሚገኙ ኮሚኒስትና ሶሺያሊስት ፓርቲዎች ፣ የሞያ ማህበራት ፣ ለሰላም የሚታገሉ ድርጅቶች አማካይነት የተጧጧፈውም ዓለም አቀፍ·ትግል ሰፋትና ጥልቀት እያገኘ መጣ ።

እውነተኛ ነፃነት የሚገኘው ከኢምፔሪያሊስት የኢኮኖሚ ስርዓት ነፃ በሆነ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ የተገነባ የፖለቲካ ነፃነት ሲረጋገጥ በመሆኑ በርከት ያሉ የአፍሪካ የእስያና የላቲን አሜሪካ አገሮች በነፃነት ማግሥት የአርነታቸው ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ለማውለብለብ ቢችሉም አንዳንዶቹ አገሮች ዛሬም ቢሆን በኢምፔሪያሊስት እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር እንዳሉ እንመለከታለን ።

የኢምፔሪያሊዝምን ፀረ ሕዝብና ፋሽስታዊ አስተዳደር የቀመሱ በርከት ያሉ «ታዳጊ» ወይንም «የሶስተኛው ዓለም» አገሮች የፖለቲካ ስትራቴጂውን በመገንዘብ በተለይም ካፒታሊስታዊ የዕድገት ፈለግ መከተሉ የማያዋጣቸው መሆኑን በማጤን የሶሽያሊዝምን የእድገት ፈለግ መከተል ሲመርጡ የቀሩትም የቀድሞዎቹ ቅኝ ገዥዎቻቸው የቀየሱላቸውን የ«ስልጣኔ» ፈለግ

Digitized by Google

በመከተል በካፒታሊስት የዕድገት መስመር
ላይ እንደሚገኙ እናያለን ።

በተለይም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር
ከ1960 ጀምሮ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ካፒ
ታሊዝም የተወላቸውን ቅሪት በመውረስ
በካፒታሊስት የዕድገት ጎዳና ሲጓዙ አንዳ
ንድ የአፍሪካ አገሮችም «የሶሺያሊዝምን»
የእድገት መስመር እንደሚከተሉ አስታ
ውቀዋል ። እነዚህ አገሮች የሶሻሊስት ስር
ዓትን የኢኮኖሚ መዋቅር ጠቀሜታ ቢገነ
ዘቡም ለሶሻሊስት ግምባታ አስፈላጊ የሆኑ
ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተውም በሶሺያሊ
ስት ዶክትሪን ላይ የተመሠረተ የፖለቲካና
የኢኮኖሚ መስመር ሊከተሉ አልቻሉም ። የ
ካፒታሊዝምን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መስ
መር እንዳጥላሉ ሁሉ የሳይንሳዊ ሶሺያሊ
ዝም መሠረትሃሳቦችን ተቀብለው ተግባራዊ
ሊያደርጉት አልቻሉም ። በዚሁ ምክንያት
በአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የሚመሠ
ረት አፍሪካዊ ሶሻሊዝምን አረባዊ ሶሻሊ
ዝምን ለመገንባት ሞከሩ ። በዚህ ሁኔታ
በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ብቻ ሶሺያሊስት ነን
የሚይሉ አገሮች ቁጥር አነስተኛ ሲሆን
የ«ሶሺያሊስት ፓርቲዎችም» ቁጥር በዚ
ያው መጠን ከፍተኛ ነው ። ይህ ሁኔታ በብዙ
የአፍሪካና የላቲን አሜሪካ የእሲያ አገሮች
ውስጥ ውስብስብ የፖለቲካ ሁኔታ ከመፍ
ጠሩም በላይ ስለ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች
ሁሉ ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ በሚደረገው
ጥረት ውስጥ እጅግ አስቸጋሪ ከባቢ መሆኑ
ግልጽ ነው ።

ከላይ ከጠቀስናቸው ሁኔታዎች ግን
ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን መመሪያቸው በማ
ድረግና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በመቀበል
በተግባር በመተርጎም ላይ ያሉ የአፍሪካ
አገሮች ሲኖሩ (ለምሳሌ ኅብረተሰብአዊት
ኢትዮጵያ ፤ አንጎላ ሞዛምቢክ ፤ ኮንጎ ብራ
ዛቪል) በፓርቲ ፕሮግራማቸው ውስጥ ለሶ
ሺያሊዝም ብሎም ለኮሚኒዝም ግምባታ
የሚታገሉ መሆናቸውን የገለጹ ፓርቲዎ
ችም አሉ ።

በእርግጥ ሶሺያሊዝም ከአንድ አገር
ወደ ሌላው አገር በግድ የሚተላለፍና የሚ
ገነባ አይደለም ። የሶሺያሊዝም ግምባታ
ተጨባጩን ሁኔታ በተጨባጭ መንገድ
መተንተንና ተገቢውን የትግል ፈር መቀ
የስን ይጠይቃል ። ሶሺያሊዝም እንደየሀገሩ
ተጨባጭ ሁኔታ በሥራ የሚተረጎም እንጂ
ቀኖና አለመሆኑን ቭላድሚር ኢሊይች
ሌኒን እንዲህ ሲል ያረጋግጣል ።

እኛ የማርክሲዝምን ንድፈ ሃሳብ ፍፁም
እንደተሟላና እንደማይገሰስ አድርገን እን
ቆጥረውም ፣ ይልቁንም ሶሺያሊስቶች በየ
ጊዜው ሊያጠኑትና ሊያሳድጉት ለሚገባው
የሶሺያሊስት ንድፈ ሃሳብ የመሠረት ድን
ጋይ መጣሉን እንቀበላለን ። በኛ እምነት
ነፃ የሆነ የማርክስ ንድፈ ሃሳባዊ እውቀት
ትንታኔ በተለይ ለሩሲያ ሶሺያሊስቶች አብ
ነት ያለው ነው ። ይህ ንድፈ ሃሳብ አጠቃ
ላይ መርህ ብቻ የሚያቀርብ በመሆኑ በእ
ንግሊዝ አገር ከፈረንሣይ ለየት ባለ መን
ገድ በፈረንሣይም ከጀርመን በተለየ ሁኔታ
በጀርመንም ከሩሲያ በተለየ መንገድ በተ
ገባር ሊተረጎም ይችላል ።[1]

እዚህ ላይ «ተጨባጭ ሁኔታ» የሚለው
ቃል ሰፋ ባለ መንገድ መታየት ይኖርበታል
የተጨባጭ ሁኔታ መኖር ተጨባጩን ሁኔታ
በተጨባጭ መንገድ ለመተንተን ዋስትና
ሊሆን አይችልም ። እንዲያውም አንድን
ተጨባጭ ሁኔታ ከተለያየ የአመለካከት
ዘዴና አቅጣጫ ማየት ይቻላል ፤ በዚህም
ምክንያት ሳይንሳዊ የሆነና በተጨባጭ
ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ትንተና እንዳለ
ሁሉ ከሳይንስና ከተጨባጭ ሁኔታ የራቀ
ትንተናም ይኖራል ። የተጨባጭ ሁኔታ
ትርጉም ከሳይንሳዊ የተጨባጭ ሁኔታ
ትንተና የሚነሳ ነው ። ይህ ደግሞ በታሪክ
እድገት ውስጥ ሳይንሳዊነቱ የተረጋገጠው
የማርክሳዊ ሌኒናዊ የተጨባጭ ሁኔታ
ትንተና ነው ።

የሶሻያሊስት ስርዓት ምሥረታ እንደ
የሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል
ማለት የሶሺያሊስት ስርዓት ግምባታ ሁለን
ተናዊ አጠቃላይ ባህርይ የለውም ማለት
አይደለም ። ይህንኑ አስተሳሰብ ሌኒን ሲያ
ጠናክር እንዲህ ይላል ።

በትግል ሰሞን ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የራሱ
የሆነ ነፃ አይዲኦሎጂ ሊያፈልቅ ይችላል
ማለት ስለማንችል ያለን አማራጭ የቡርዧ
አይዲኦሎጂ አለያም የሶሺያሊስት አይዲ
ኦሎጂ ነው ። እስከ ዛሬ ድረስ ሶስተኛ
አይዲኦሎጂ ያለተፈጠረ በመሆኑ ሌላ አማ
ራጭ አይኖርም --- በተፈለገውም መንገድ

Digitized by Google

ቢሆን የሶሺያሊስት አይዲኦሎጂን ማቃለል ወይንም ከመሠረተ ሃሳቡ ቀንጣት ያህል ስንኳ ማፈንገጥ የቡርዧውን አይዲኦሎጂ ማጠናከር ነው ።[2]

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች እንደገለጹት ሁሉ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ንድፈ ሀሳብ የተግባር መመሪያ ከመሆኑም በላይ «የትግልና የኑሮ መሣሪያ እንጂ እንደ እምነት ምልክት በሰው ላይ የሚደረግ ክታብ አይደለም ።»[3]

ሶሽያሊዝምን በአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታ መገንባት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ራሱ መጀመሪያ «የአፍሪካን ተጨባጭ ሁኔታ» ምንነት ማወቅን ይጠይቃል ። በአንድ ክፍለ ዓለም ተካልሎ የሚኖር ሕዝብ በአንድ የተጨባጭ ሁኔታ ሥር ይኖራል ካልተባለ በስተቀር አፍሪካ ከሁለንታዊ የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ሕግጋት በመለስ ለአፍሪካዊያን የተተወች ክፍለ ዓለም አይደለችም ። ይልቁንም አፍሪካና አፍሪካውያን የነባራዊው የዲያሌክቲክስ የእድገት ሕግጋት ተገዥ እንደመሆናቸው የአፍሪካዊነት ኅልውናቸውንም ያገኙት የዚሁ ሁለንታዊ የእድገት ሕግጋት ተገዥ በመሆናቸው ነው ። ይህ ደግሞ ከምኞትና ከተምኔታዊነት ባሻገር ያለ እውነታ ነው ።

ልዩ ልዩ ቅጽሎችን ያስከተሉ የሶሻሊዝም ዓይነቶች ቦግ ድርገም ብቅ ጥልቅ ማለታቸውን ባያቋርጡም ወደ እውነተኛውና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚደረገው ጉዞ ከመጠናከር ወደኋላ አላለም ። በሶሻሊዝም ለዚያውም በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ስም ለመነገድና ለማጭበርበር በየጊዜው መድረክ ላይ ወጥተው ተግባራቸውንና ድርጊታቸውን አጋልጠ ካስተፋቸው ውስጥ በጠባብ ብሔረተኝነትና በተስፋፊነት የተወጠሩት የሱማሌ የገዥ መደቦች ዛሬ ከውርደትና ከውድቀት ጉዞአቸው ከመጨረሻው የሐፍረት አዘቅት ውስጥ በመግባት የኢምፔሪያሊዝም ቡችልነታቸውን ለዓለም ሕዝብ በማያጠራጥርና በማያወላውል አኳኋን እያስመሰከሩ ነው። ይህ ጽሑፍ በዚያድ ባሬ የሚመራው አድሀሪውና አጭበርባሪው የሱማሌ ገዥ መደብ የተጓዘበትን የክህደትና የውድቀት ሂደት ለመገምገምና ትክክለኛ ገመናውን ለማሳየት ይሞክራል ።

የሶማሊያ መንግሥት አመጣጥ

የሶማሊያ መንግሥት አመጣጥ ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት በኋላ በአፍሪካ ቀንድ ከታየው የፖለቲካ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚገመገም ነው ። ይህም ሲባል በየጊዜው በአፍሪካ ቀንድ የነበረውን ማህበራዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚወስነው ይኸው ጉዳይ ብቻ ነው ማለት አይደለም ። ይልቁንም በአፍሪካ ቀንድ አገሮች መካከል የነበረውና በያንዳንዱም አገር ውስጥ የታየው ውስብስብ የፖለቲካ ሁኔታ ከዚሁ ጋር አብሮ የሚወሳ ነው ።

ከአምስቱ ዓመታት የኢጣሊያን ፋሽስት ወረራ በኋላ የኢትዮጵያ ነፃነት ሲረጋገጥ በጊዜው የኢትዮጵያን የኦጋዴን ግዛት በበላይነት ያስተዳድር የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥት የኦጋዴንን አስተዳደር የተረከበው እ. ኤ. አ በኅዳር 1944 በኢትዮጵያ መንግሥትና በእንግሊዝ መንግሥት መካከል በተፈረመው ውል መሠረት ነበር ። በውሉ መሠረት እንግሊዞች የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት አክብረው ነገር ግን በመካሄድ ላይ የነበረው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስኪያልቅ ድረስ የቀድሞውን የእንግሊዝ ሱማሌ ግዛቶችና የኢጣሊያ ሱማሌ ላንድ ተብሎ ይጠራ የነበረውን የደቡብ ሱማሌ ክፍል በማጠቃለል አስተዳደሩ ።

የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያን የኦጋዴን ግዛት በሚያስተዳድርበት ወቅት ይህንኑ የኢትዮጵያ ግዛት ገንጥሎ ከራሱ ሱማሌ ጋር አጠቃልሎ አካባቢውን በሙሉ ለመያዝና ቅኝ ግዛቱንና ጥቅሙን ለማስፋፋት ውስጥ ውስጡን ተንኮል ሲያውጠነጥን ነበር ።

የእንግሊዝ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት ከላይ የተጠቀሰውን ውል በተፈራረመው በሁለተኛ ዓመት አራቱ የጦር ባለ ቃልኪዳን አገሮች (Allied Powers) ባደረጉት ጉባኤ ላይ በየጊዜው የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበ/ው ኤርነስት ቤቪን የሚከተለውን ሀሳብ አቀረበ ።

- - - ኢትዮጵያ የምትስማማበት ከሆነ የእንግሊዝ ሶማሊላንድ ፣ የኢጣሊያን ሶማሊ

ላንድና ከነዚሁ ግዛቶች ጋር ኩታ ገጠም የሆነው የኢትዮጵያ ክፍል በአንድ አውራ አስተዳደር ሥር ማጠቃለል ይቻላል ። በተጠማሪም ዘላኖቹ (ሶማሎች) በዚህ ክፍል ውስጥ የተመዛዘነ ኢኮኖሚያዊ ኑሮ እንዲያካሂዱ የሚያስችላቸው በመሆኑ ጠቃሚ ይሆናል ።[4]

ይህ አባባል የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምን የመሰፋፋት ፖሊሲ በገሀድ የሚያስረዳ ነበር ። ምክንያቱም አካባቢውን በአደራ ለማስተዳደር ሰፊ ዕድል የነበራት እንግሊዝ ስለነበረች ነው ። የእንግሊዝ መንግሥት አሻጥር ይህ ብቻ አልነበረም ። እንግሊዞች አካባቢውን ያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ በአንዳንድ የሶማሌ ጎሣዎች አካባቢ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖችን በማቋቋም በነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች አማካይነት «የታላቋ ሶማሌን» መመሥረት ይሰብኩ ነበር ።

ከነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በግምቦት ወር 1943 በመቃድሾ የተቋቋመው የሶማሊያ ወጣቶች ክበብ » ይገኝበታል ። በ1947 መጨረሻ ላይ ቀደም ሲል የተቋቋመው «የሶማሊያ ወጣቶች ክበብ» ፈርሶ በምትኩ «የሶማሊያ ወጣቶች ሊግ» የተባለው ድርጅት ተመሠረተ ።»[5] የዚህ የፖለቲካ ድርጅት መሠረታዊ አላማዎች ፤

1. የሶማሊያ ዜጎችን አንድነት ማጠናከርና በተለይም የሶማሊያ ወጣቶች ከጎሣና ከነገድ አስተሳሰብ ተላቀው ለአንድ የጋራ ዓላማ እንዲሰለፉ ማድረግ ፤

2. የሶማሊያን ወጣቶች በዘመናዊ ሥልጣኔ ማነጽ ፤ የባህልና የፕሮፓጋንዳ ትምህርት መስጠት ፤

3. የሶማሊያን ቋንቋ ማሳደግና በተለይም «የኦስማኒያ ሶማሊ» ፊደላትን መጠቀምና ማስፋፋት ናቸው ።[6]

ከዚህ የፖለቲካ ድርጅት ጎን «ጀሚያ» የሚባል የፖለቲካ ድርጅት በደቡብ ሶማሊያ የርሻ ተቋሞች አካባቢም ተቋቁሞ ነበር ።[7] ከላይ እንደተጠቀሰው የእንግሊዝ መንግሥት «ታላቋ ሶማሌን ለመመሥረት በሶማሌ ጎሣዎች ውስጥ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ያካሂድ ስለነበር ይኸው «የታላቋ ሱማሌ» ቅዠት በርከት ባሉ የሶማሊያ ጎሣዎች ውስጥ በሰፊው ተሰራጭቶ ነበር ።

ይህ ሁኔታ በዚህ እንዳለ የኢትዮጵያ የኦጋዴን ግዛትና የአካባቢዎቹ ከእንግሊዝ መንግሥት እጅ ኢትዮጵያ ግዛት ሲመለሱ የቀድሞው የጣሊያ ሶማሌላንድ በተባበሩት መንግሥታት አማካይነት በኢጣሊያን የአደራ አስተዳደር ሥር ስትመደብ እንግሊዞች የእንግሊዝን ሶማሌላንድ እስከ 1966 ድረስ ሲያስተዳድሩ ቆዩ ።

በሞቃድሾ ከተማ ላይ የተቋቋመው «የሶማሊያ ወጣቶች ሊግ» በሶማሌ ዜጎች መካከል ከፍተኛ የቅስቀሳ ሥራ ከማካሄዱም በላይ በኢትዮጵያ የኦጋዴን ግዛት ውስጥ ሰርገው በመግባት የአካባቢው የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሁሉ ከአንድ «የታላቋ ሶማሌ» ግዛት ውስጥ እንደተጠቃለሉ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆዩ ።

ከአሥር ዓመት በኋላ ሰኔ 1960 የእንግሊዝ ሶማሌ ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ በአራት ቀን ልዩነት ውስጥ ማለትም ሐምሌ 1 1970 የኢጣሊያን ሶማሌ ነፃነቷን ለማግኘት ቻለች ። ካዚህ በኋላ በዚሁ ዓመት በተደረገው ስምምነት ሁለቱ ግዛቶች ተዋህደው የሶማሊያ መንግሥት ሊመሠረት ቻለ።

የሶማሊያ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ የሶማሊያ መሪዎች ከኢምፔሪያሊስቶች የወረሱትን «የታላቋን ሶማሌን» አደገኛ በሽታ ተሸክመው በተግባር ለመተርጐም ከፍተኛ መራሯጥ ማድረጉን ተያያዙት ። በተለይም በነሐሴ ወር 1967 የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሆና የተሾመው ኢብራሂም ኢጋል የኬኒያን ሰሜናዊ ክፍል ጅቡቲንና የኦጋዴንን የኢትዮጵያ ግዛት በማጠቃለል «ታላቋን ሶማሌ» ለመመሥረት ከፍተኛ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ጀመረ ። ኰሎኒያሊስቶች የተከተሉትን «የታላቋን ሶማሌ» ችግኝ «ታሪክ ፈጣሪዎቹ» የሶማሊያ መሪዎች እየኰተኰቱ ለማሳደግ ሞከሩ ።

የሶማሊያ መንግሥት ሲቋቋም የብሔራዊው ሸንጎ አባላት ቁጥር ፍጹም በሕግ አልተወሰነም ነበር ። ይህም የተደረገው «የሶማሊያ ግዛቶች» ሁሉ ውህደት ከፈጠሩ በኋላ ሌሎቹም አካባቢዎች የራሳቸውን ተወካይ ይል

ካሉ በሚል ግምት ነበር ። ብሔራዊው ስን
ደቀ ዓላማ አምስት አገሮች በሶማሊያ ግዛት
ሥር ለወደፊት የሚጠቃለሉትን ክፍሎች
የሚያመለክቱ ናቸው ። በአገሪቷ ሕገ
መንግሥትም ውስጥ የሶማሊያ ሪፑብሊክ
በሕጋዊና ሰላማዊ መንገዶች ሁሉ በመጠ
ቀም የሶማሌ ዜጎችን ሁሉ አንድ ላይ ለማጠ
ቃለል ጥረት የሚደረግ መሆኑን ሲያመለ
ክት የትም ቢሆኑ ባሉበት የሶማሊያ ሪፑ
ብሊክ ሶማሊዎች ዜግነታቸው የሚጠበቅ
መሆኑን ያመለክታል ።[8]

በየጊዜው የተነሱት የሶማሊያ መሪዎች
ሁሉ ይኸው ከላይ የተጠቀሰውን የሶማሊያ
የመስፋፋት ፖሊሲ ሲያራምዱ ቆዩ ። በመ
ጀመሪያ ኢትዮጵያን ከዚያም የኬንያንና
የጅቡቲን ድንበሮች እየጣሱ በየጊዜው
ግጭቶችን መፍጠርን ስራዬ ብለው ተያያ
ዙት ። በ1953 በ1956 በልዩ ልዩ አጋጣሚ
ዎች በመጠቀም ባደረጉት ወረራ ቀንዳቸ
ውን እየተመቱ ቢመለሱም ከስህተታቸው
ፈጽሞ ሊታረሙና አርፈው በሰላም ለመኖር
የሚፈልጉ ሆነው አልተገኙም ።

የዚያድ ባሬም መንግሥት እ. ኤ. አ.
በ1969 ከተመሠረተ በኋላም ሳይቀር የሶማ
ሊያ መሪዎች በዚሁ የመስፋፋት ፖሊሲያ
ቸው ከመግፋት አልተገቱም ። የዚያድ
ባሬን አስተዳደር ከበፊቶቹ የሚለየው የቀ
ድሞዎቹ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመሰለፍ
የመስፋፋት ግባቸው ሳይሳካላቸው ቢቀር
እርሱ ግን «ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን እከ
ተላለሁ በማለት «የታላቋ ሶማሌን» ሰን
ደቅ በገሀድ ማውለብለቡን መቀጠሉ ነው ።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት አንድ አስ
ፈላጊ ጥያቄ አለ ። የዚያድ ባሬ መንግሥት
ሶሺያሊዝምን ለመከተል የመረጠው በምን
ምክንያት ነው ? ይህንን ጥያቄ ሰፋ ባለ መል
ኩ መመለስ ቢቻልም ባጭሩ እንቃኘዋለን ።

የዚያድ ባሬ መንግሥት በመፈንቅለ
መንግሥት አማካይነት ሲመሠረት በጊዜው
በኢትዮጵያ የነበረው የፊውዶ ቡርዥው
መንግሥት ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም
ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው ። ከሶማሊ
ያም አንፃር ሲታይ ዘመናዊ የጦር ኃይል
ስለነበረው ለሶማሊያ የመስፋፋት ፖሊሲ
አመች ሁኔታ አልተፈጠረም ነበር ። የሶማ
ሊያም መንግሥት በየጊዜው የኦጋዴንን
የኢትዮጵያ ግዛት በጦር ኃይል ለመያዝ ያደ
ረገው ሙከራ አልሰመረለትም ።

የማናቸውም የሶማሊያ መሪዎች የፖለ
ቲካ ፖሊሲ «ከታላቋ ሶማሌ» ሕልማቸው
የሚነሳ መሆኑ ተደጋግሞ የተወሳ ጉዳይ
ነው ። የሶማሊያ መሪዎች «ግቡ የዓላማውን
መዳረሻ መንገድ ይወስናል» በሚል ማኪያ
ቬሊያዊ ፖሊሲያቸው « የታላቋ ሶማሌ »
ዓላማቸን ውበሥራ ለመተርጐም «ሳይንሳዊ
ሶሺያሊዝምን» እንከተላለን በማለት ለፈፉ።
ሐቁ ግን አንድ በሶማሊያ ላይ ሰፊ ጥናት
እንዳካሄዱ ምሁር አባባል !

ለሶማሊያ መሪዎች የሶቪዬት ኅብረተ ወዳ
ጅነትና ትብብር የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን
መሠረተ ሃሳብ ጠምሮ ለታላቋ ሶማሊያ
ዓላማቸው ማሳኪያ መንገድ ብቻ ነበር ።[9]

ለዚህም ዓላማቸው የ17 ዓመት ዝግ
ጅት በማድረግ የኢትዮጵያ አብዮት ገና
ሳይጠናከር ለብዙ ጊዜ በአካበቱት የጦር
መሣሪያ በመጠቀም በ1969 በአብዮታዊት
ኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት እጅግ አሳፋሪ
ወረራ በቂ ታሪካዊ ምስክር ነው ።

የሶማሊያን «ሶሺያሊዝም» ትክክለኛ
ገጽታ ለማየት እንድንችል የሶማሊያን አብ
ዮት አይዲዮሎጂካዊ መሠረት ከሳይንሳዊ
ሶሺያሊዝም መሠረተሃሳቦች አንፃር መተ
ንተን አስፈላጊ በመሆኑ በሚቀጥለው የዚህ
ጽሑፍ ክፍል ይህንኑ «የሶማሌን ሶሺያሊ
ዝም» ምንነት በሰፊው ለማየት እንሞክራ
ለን ።

የሶማሊያ ሶሺያሊዝም ርዕዮተዓለማዊ መሠረት ከሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም መሠረተ ሃሳቦች አንፃር

የማንኛውም ሀገር የውስጥና የውጪ
ፖሊሲ ሀገሪቷ ከምትከተለው የፖለቲካ
የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች መሠረታዊ
ፖሊሲዎች የሚመነጭ ነው ። ይህም መን
ኛውም ሀገር በዓለም አቀፍ የፖለቲካና
የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ውስጥ የሚኖረውን
ስፍራ ይወስናል ። የሶማሊያም ሁኔታ በዚሁ

Digitized by Google

የአስተሳሰብ ማዕዘን ውስጥ የሚታይ ጉዳይ እንጂ ልዩ ክስተት አይደለም ።

እ. ኤ. አ. ጥቅምት 15፣1969 በተደረገው መፈንቅለ መንግሥት ፕሬዚዳንት አብዱ ራሺድ ዓሊ ሽርማርኬ ሲገደል በጊዜው ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ራጅ ኢብራ ሂም ኢጋል እስር ቤት ተጥሎ በሜጀር ጀኔ ራል ዚያድ ባሬ የሚመራ ወታደራዊ መን ግሥት ስልጣን ያዘ ። ከዚህም በኋላ ዚያድ ባሬ በሶማሊያ አብዮታዊ ምክር ቤት አማካ ይነት «የፖለቲካ ስልጣኑን በጁ አደረገ ።

በዚያድ ባሬ የተመራው ይኸው ወታደ ራዊ መንግሥት ስልጣን እንደያዘ የፖለ ቲካ መመሪያው ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም እን ደሚሆንና ዋናው ዓላማው በልዩ ልዩ ጎሣ ዎች ተከፋፍሎ የቆየውን የሶማሊያን ሕዝብ አንድ ለማድረግና ፍትህና ወንድማማችነት በሶማሊያ ማስፈን መሆኑን አስታወቀ ። ይሁንና በተግባር ግን የዚህ ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ነው ሲፈጸም የነበረው ።

በ1976 እ. ኤ. አ በጥቅምት ወር «የሶማ ሊያ አብዮታዊ ምክር ቤት» ፈርሶ በምትኩ «የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ ተመሠረተ። ፓርቲው ከተቋቋመ በኋላ ከላይ የጠቀስነውን ዓላማ በሰፊው በተግባር ላይ የሚያውል መሆኑን በመጥቀስ በሶማሊያ ሕዝብ መካከል የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሥራዎችን ማካሄድ ጀመረ ። በፓርቲው መርሀ ግብ ውስጥ እንደተጠቀሰው ፤

የሶማሊያ ለብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ ዓላማ የሶማሊያን ሕዝብ ወደ ብልፅግናና ወደ ለዲስ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት ደረጃ ለማሸጋገር ሲሆን በሶማሊያ ውስጥ እኩልነትን ፡ ማኅበራዊ ፍትህን በማስፈን የሰው በሰው መበዝበዝን ጠርሶ ለማጥፋት ነው ።[10]

ዛሬም ቢሆን ትናንት ይህ ዓላማ በተ ግባር መተርጎሙንና አለመተርጎሙን ግን ልናውቅ የምንችለው የዚሁ ዓላማ ማስፈ ጸሚያ ይሆናል ስለተባለው «የሶማሊያ ሶሺያሊዝም» ምንነት ሰፋ ባለ መንገድ ስንመለከት ነው ።

ዚያድ ባሬ በሶማሊያ ስለሚመሠረተው የሶሺያሊስት ስርዓት በሐሰኔ የፖለቲካ ትም ህርት ሲከታተሉ ለቆዩት የሶማሊያ ወጣ ቶች ገለጻ ሲያደርግ በተለይም የሶማሊያን ሶሺያሊዝም ምንነት ሲገልጽ እንደሚከ ተሉት አስቀምጦታል ።

የኛ ሶሺያሊዝም የሶማሊያ ሶሺያሊዝም ፣ ለፍሪካዊ ሶሺያሊዝም ወይም የእስላም ሶሺያሊዝም ለይደለም ፤ ይልቁንም በሰው ልጅ ልምድና እውቀት የዳበረው የመጀ መሪያው ዓይነት ሶሺያሊዝም ነው ። የኛ ሶሺያሊዝም በራሱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚ መራ ሶሺያሊዝም ነው ።[11]

ይህ መቼም ከሞላ ጎደል ጤናማ አስተ ሳሰብ ነው እንበል ። ይሁን እንጂ እውነተ ኛው የዚያድ አቋም ይህ አይደለም ። የዚ ያድ ባሬ «ሶሺያሊዝም» ምንድነው ምንድር ነው ? መሠረተ ሃሳቡስ በርግጥ እርሱ እንዳለው «የመጀመሪያው ዓይነት» ሶሺያ ሊዝም ነው ፤ ለዚህ ጥያቄ ራሱ ዚያድ ባሬ መልሱን ሲሰጥ እንደዚህ ይላል ፤

ሶሺያሊዝም የተጀመረው የት ነው? ያፈለ ቀውስ ማን ነው? ይህንን ጥያቄ በሚመለከት ለያሌ ሰዎች በውዥምብር ውስጥ ወድ ቀዋል ። እኛ እንደሚመስለን የሶሺያሊዝም ምንጭ የእስላም ሕዝብ ነው ፤ መሠረተ ሃሳቡም የመነጨው ከእስላም ሃይማኖት ነው ።[12]

በዚያድ አመለካከት በዓለማችን የሶሺ ያሊስት ስርዓት ግምባታ የተጀመረው ከእ ስልምና ሃይማኖት አመጣጥ ጋር ከሆነና የሶሺያሊዝምም መሠረት የእስላም ሕዝብ ከሆነ ፤ 1ኛ/ የሶሺያሊስት ስርዓት በዓለም ላይ መስፈን የጀመረው ከታላቁ የጥቅምት የሩሲያ አብዮት በፊት በሰባተኛው ምዕ ተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ መሆኑ ነው ፤ ምክንያቱም የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት የጀመረው ከላይ በተጠቀሰው ዘመን በመሆኑ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የእስላም ሃይማኖት የሶሺያሊዝም መሠረት ከሆነ የእስልምናን ሃይማኖት የተቀበለ ሁሉ በዚህ ብቻ ሶሺያ ሊስት ሊሆን ይችላል ማለት ይሆን ? ፊት ካቀረብነው ትንተና እንደምንረዳው በሶ ማሊያ የሚመሠረተው ሶሺያሊዝም «የሶማ ሊያ ሶሺያሊዝም ፤ አፍሪካዊ ሶሺያሊዝም ወይንም የእስላም ሶሺያሊዝም» ሳይሆን

የመጀመሪያው ዓይነት ሶሺያሊዝም ነው
ከተባለ ይህ የሶማሊያው ሶሺያሊዝም ከየት
ተነስቶ የት ሊያርፍ ነው ።

ዚያድ ባሬ ባንድ በኩል የእስልምና
ሃይማኖት የሶሺያሊዝም መሠረት መሆኑን
በግልጽ ሲያስረዳ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ
ንን ቃሉን በሚያስገርም ሁኔታ ሲያጥፈው
እናያለን ። ዚያድ በሶሺያሊዝምና በእስል
ምና ሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት
ሲያስረዳ እንዲህ ይላል ፤

ሶሺያሊዝም እንደ እስልምና ሃይማኖት ከሰ
ማይ የወረደ መልዕክት ለይደለም ይልቁንም
ሰዎች በምርት መገልገያዎች ሲጠቀሙ የ
ሚፈጥሩትን ግንኙነት ስርዓት ባለው መንገድ
የሚያቀነባብር ነው ። [13]

እንግዲህ ሶሺያሊዝም እንደ እስልምና
ሀይማኖት ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ቃል
ካልሆነ የእስልምና ኃይማኖት የሶሺያሊስት
ንድፈ ሀሳብ ምንጭ ሊሆን የቻለው በምን
ተአምር ነው ? የዚያድ የንድፈ ሀሳብ ችግር
ይህ ብቻ አይደለም ። አንዳንዴም ያመል
ጠውና ትክክለኛውን ነገር ተናግሮ በአደ
ባባይ የለፈፈውን ሀሳቡን ሲያፈርስ እን
ዲህ ይላል ።

---ከኛ ቀደም ብለው ሶሽያሊዝምን በተ
ግባር ያዋሉ ሀገሮች ሶሽያሊዝምና ኃይማኖት
አብረው አይሄዱም ብለዋል ፤[14]

በማለት እራሱ ተወናብዶ ሌላውንም
ያወናብዳል ። ዚያድ ባሬ ስለ ሶሺያሊዝም
ያለው የተወገረገረ አስተሳሰብ በዚህ ብቻ
የሚወሰን አይደለም ። ዚያድ ስለ ሶማሊያ
ሶሺያሊስቶች ዓላማ ሲያብራራ ፤

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ደጉንና ክፉ
ውን ለመለየት እንዲችል አእምሮ ሰጥቶታል ።
ስለሆነም --- ሰው በሰው ከሚበዘበዝበት
ስርዓት ይልቅ እኩልነት የሰፈነበትን ኅብረ
ተሰብ ለመፍጠር ተነሳስተናል ። [15]

ይላል ። እንደ ዚያድ አመለካከት የሶሺያሊ
ስት ስርዓት ምሥረታ ጥላን በፈጣሪ ተረቶና
ጸድቶ በሰዎች አእምሮ በኩል ተፈፃሚነት
ያገኛል ለማለት ካልሆነ በስተቀር የሶሺ
ያሊዝም መሠረቱ ሰብዓዊ ስነ ምግባር ላይ
ሆን የሰብዓዊነት ባህርዩ የሶሺያሊዝም
አንድ ገጽታ ብቻ ነው ። ይህም ብቻ አይ
ደለም ። ዚያድ ስለ ሶሺያሊዝም መሠረት
አጣርቶ አለማወቁን የሚያስገነዝበን ስለ
መደቦችና የመደብ ትግል ያለው አሳዛኝ
ሀሳብ ነው ። ዚያድ ባሬ በሶማሊያ ስለ
መደቦች አሰላለፍ ሁኔታ ሲናገር

በማርክሲስተች አስተሳሰብ ከሄድን በሶማ
ማሊያ ኅብረተሰብ ውስጥ መደቦች የሉም ፤
እኛ ዘላናች ገበሬዎች ለነስተኛ ለሰሪዎችና
ወታደሮች ነን ። [16]

በማለት የራሱን አስተያየት ሰንዝሯል ።
በዚያድ ባሬ የመደብ ትንተና መሠረት ዘላ
ናች ፤ ገበሬዎች አነስተኛ አሰሪዎችና ወታ
ደሮች ከመደቦችና ከመደብ ትግል ውጪ
ናቸው ። እዚህ ላይ «በማርክሲስቶች አስተ
ሳሰብ» ማለቱ የሚገርም ቢሆንም የሰጠው
ማጠቃለያ ደግሞ እጅግ የሚያስገርም ነው ።
የእውነተኛ ማርክሲስቶችና የሳይንሳዊ ሶሺ
ያሊዝም አቋም እጅግ የሚያስገርም ነው ።
የእውነተኛ ማርክሲስቶችና የሳይንሳዊ ሶሺ
ያሊዝም አቋም ግን ጨርሶ ከዚህ የተለየ
ነው ። እዚህ ላይ የቪዬትናም ኮሚኒስት
ፓርቲ ዋና ፀሐፊ የሆኑት ጓድ ሌዱዋን የተ
ናገሩትን መጥቀስ በቂ ይመስለናል ። ጓድ
ሌዱዋን መደቦችንና የመደብ ትግልን በሚ
መለከት በአጠቃላይም የማርክሲስቶች ተግ
ባር ምን መሆን እንዳለበት ሲያስገነዝቡ

በማርክሲስት አመለካከት አኳያ ኮሚዩኒስ
ቶች የትገላቸውን እስትራቴጂና ታክቲክ ሲቀ
ይሱ ለሠራተኛው መደብ ጥቅም ቅድሚያ
በመስጠት በኅብረተሰብ መደቦች መካከል
የሚኖሩትን ግንኙነቶችና ልዩነቶች አጣርተው
ማወቅ ይኖርባቸዋል ። አብዮታዊ ስሚታ
ቸውንና ሳይንሳዊ ዕውቀትን በማቀናጀት
ማርክሳዊውን የመደብ ትግል መርህ ጠን
ቀቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል ። [17]

በማለት ማርክሲስቶች ለመደቦችና ለመ
ደብ ትግል ንድፈ ሀሳብ ተገቢውንና አስፈ
ላጊውን ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው
ተናግረዋል ። የዚያድ ባሬን ቅጥፈት ይበ

Digitized by Google

ልተ ቁልጭ ብሎ የሚታየው ስለ ሶሺያሊዝም አቋሙን በሚገልጽበት ጊዜ ነው ። ይህንንም በሚመለከት ዚያድ ሲናገር ፤

ሶሽያሊዝም የማይጠቀመን ሆኖ ሲገኝ ለሽቀንጥረን እንጥለዋለን ፤ በዚህ ፋንታም ሌላ መንገድ እንሻለን መርሁ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ግን እንቀበለዋለን ። [18]

ይለናል ። የዚያድ ባሬ የፖለቲካ አቋም ከውጭ ሲያዩት እጅግ የተምታታ ቢሆንም ከታላትና በየጊዜው ከሚለዋውጣቸው ሽፋኖች በስተጀርባ ግን በጠባብነትና ተስፋፊነት ላይ የተመሰረተ የከረረ ብሔረተኝነት ሆኖ ይገኛል ። ዛሬ «ሶሺያሊዝም የማይጠቅመን ከሆነ አሽቀንጥረን እንጥለዋለን» ያለውን ሀሳብ በተግባር ተርጉሞ ከቀንደኛ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር በማበር በአፍሪካ ቀንድ ለሰላምና ለዕድገት የቆሙ ሀገሮች የሚያደርጉትን ጥረት ለማደናቀፍ ሲጣጣር በገሀድ እያየነው ነው ። የበግ ለምድ መልበስ የተኩላን ተኩላነት አይለውጠውም ። ዚያድ ባሬ ስለ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም በነበረው የተጭበረበረ አስተሳሰብ ውስጥ ወድቆ ሲጮህ ራሱ ፈጠረው ድምጽ የገደል ማሚቶ ተደናግጦ ይታያል ።

በመሠረቱ አብዮታዊ ተግባር ቀለል ጉዳይ አይደለም ። ይህንን ዕውነታ ጃክ ዊዲስ “New Theories of Revolution” በተባለው መጽሐፍ ውስጥ በዚህ መልክ አስቀምታጦል ፤

አብዮት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ። የሰዎች ሕሊናዊ ፍላጉት ወይንም በድፍረት የተሞላ የአብዮታዊ መፈክሮች ድርድር አይደለም ። አብዮታውያን የሕዝቡን ማለትም የሠራተኛውን የገበሬውን የተማሪውንና የምሁራኑን ስሚት ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል ። የሕዝብ መሪዎች የሚሠሩት ስህተት በቀጥታ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ የሚወድቅ በመሆኑ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ። [19]

ዚያድ ባሬ እንደሚለው ሳይሆን ፤

ማርክሲዝም (ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም) ተጨባጩን ሁኔታ በትክክል የሚተነትን በመሆኑ ከሌሎች ሶሽያሊስት ንድፈ ሀሳቦች ለየት ያለ ነው ። የአብዮትን ነባራዊ የዕድገት ሂደት በማጤን ፤ ሰፊው ሕዝብ የአብዮት ኃይልና የፈጠራ ችሎታም ምንጭ በመሆኑ በትግል ወቅት የወሳኝነት ሚና እንዳለው ያስተምረናል ። ይኸው ትንታኔ በማርክሳዊ የታሪክ አቀራረብ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ በያንዳንዱ የአብዮት ወቅት ስለሚፈጸሙት አቢይ ጉዳዮች ሰፊና በስርዓት የተቀነባበረ ትምህርት ይሰጣል ። [20]

የሶማሊያን ጉራማይሌ ሶሻሊዝም የዛሬ ወዳጆቹ እንኳ ሳይቀሩ የተቹት ጉዳይ ነው ። ከአራት ዓመት በፊት (1977) ለሥራ ጉዳይ ወደ ግብጽ ፤ ሱዳን ፤ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ሄደው የነበሩ የአሜሪካ ኮንግሬስ አባሎችም በሶማሊያ ስላዩት ነገር ይህንን ሪፖርት ጽፈው ነበር ።

የሶማሊያ አብዮታዊ ምክር ቤት ሳይንሳዊ ሶሽያሊዝምን እከተላለሁ ይላል ። እኛ እንዳየነው ከሆነ ግን በአገሪቷ ውስጥ ካፒታሊዝም እያቀጠቀጠ ነው - - - የሶማሊያ መሪዎች ብዙውን ጊዜያቸውን ያጠፋት የራሳቸውን - - ሶሽያሊስታዊ - - የኢኮኖሚ ዕድገት ከማፋጠን ይልቅ ለኦጋዴኑ ጦርነት ዝግጅት በማድረግ ነው ። [21]

ስለ ሶማሊያ «አብዮት» አይዲዮሎጂካዊ መሠረት ሰፋ ያለ አመለካከት ሊኖረን የሚችለው በማንኛውም ሶሽያሊስት አብዮት ውስጥ ተፈፃሚነት የሚያገኙ ሕጐች ምን ምን እንደሆኑ በመመልከት በዚህ አንፃር በሶማሊያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመገምገም ስንችል ብቻ ነው ። ዛሬ ሶሽያሊዝምን ለመገንባት በማንኛውም አገር የሚደረገው ጥረት የሚመራው በግምባር ቀደሙ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ መሪነት ሲሆን የዚሁ ግምባር ቀደም ድርጅት ሳይንሳዊ አመራር ወሳኝ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ለሶሽያሊዝም ግምባታ መሠረት ለመጣል የሠራተኛውና የገበሬው መደብ ተግባራዊ አንድነትና ኅብረት ወሳኝ ነው ። በተለይም የውጭ ፖሊሲን በሚመለከት ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን በመርህና በተግባር ደረጃ መቀበልና በሥራ መተርጐም እጅግ አስፈላጊ ነው ። በተለይም እንደ ሶማሊያ ባሉ ኋላ ቀር አገሮች ሶሽያሊዝምን ለመገንባት ከተፈለገ ይህ ፈጽሞ ሊዘለል የማይቻል መሠረታዊ መርህ ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው የማንኛውም አብዮት ጥን

ካሬ በአብዮቱ የንድፈ ሀሳብ ጥራት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን አብዮታዊ አይዲዮሎጂ ከሰፊው ሕዝብ ማኅበራዊ ስነ ልቡናና ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና መዳበር መሠረታዊ ነው ። ለሶሻሊዝም የሚደረገውም ትግል ከዚህ መሠረተ ሀሳብ የሚነሳ መሆን ይኖርበታል ።

ስለ ሶማሊያ አብዮት አይዲዮሎጂካዊ መሠረት የበለጠ ልንረዳ እንድንችል የሶማሊያን «አብዮታዊ ሶሻሊስት ፓርቲ» መርሀ ግብር በሰፊው መመርመር ይኖርብናል ። በሚቀጥለው የጽሑፋችን ክፍል ይህንኑ ለመመልከት ጥረት እናደርጋለን ።

«የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ» መርሀግብር

የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ለማንኛውም ሶሺያሊስት አብዮት ግብ መምታት ወሳኝ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ለአብዮቱ ተገቢውን አመራር የሚሰጥ የፖለቲካ ድርጅት ወይንም ፓርቲ መኖር ደግሞ ይበልጥ አንገብጋቢ መሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ጉዳይ ነው ። ግምባር ቀደሙ የፖለቲካ ድርጅት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚችለው ሳይንሳዊ በሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ሲመራ ብቻ ነው ። በአንፃሩ ደግሞ አንድ ፓርቲ ሳይንሳዊ የፖለቲካ ፕሮግራም ስለወጣ ብቻ ታሪካዊ ግዴታውን ይወጣዋል ማለት አይደለም ። ዛሬ ባግሩ ቃላትና በሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም መፈክሮች የሚጠቀሙ በተግባር ግን ፀረ ሶሺያሊስት የሆኑ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ጥቂት አይደሉም ።

«በሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ» መርሀ ግብር ውስጥ እንደተጠቀሰው «የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ» የሶማሊያ ሰርቶ አደሮች ግምባር ቀደም ድርጅት ነው ።[22] በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ መርሐ ግብር ውስጥ «የሶማሊያ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ጦር ኃይሎች የሶማሊያ ሰፊ ሕዝብ አካልና ግምባር ቀደም ድርጅት ነው» የሚል በመርሐ ግብሩ አንቀጽ 28 ላይ ሰፍሮ ይገኛል ።[23]

«የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ» የሶማሌ ሰርቶ አደሮች ግምባር ቀደም ድርጅት ከሆነና የሶማሊያ ጦር ኃይሎች የሰፊው ሕዝብ አካልና ግምባር ቀደም ከሆኑ በፓርቲውና በጦር ኃይሎቹ የፖለቲካ ሚና መካከል ያለው ልዩነት ምን ይሆን? ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ የሶማሊያ ጦር ኃይሎች አመራር አንደኛው ተግባር «በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ብሔራዊ ስሜትን ፣ አብዮታዊ መንፈስና የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን አስተሳሰብ ማስራጨት ነው» ይላል ። እዚህ ላይ የጦር ሠራዊቱን «ብሔራዊ ስሜት» ማጠናከር ቀዳማይ ተግባሩ ሲሆን የ«ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን» ሀሳብ በጦሩ ውስጥ ማስፋፋት በሁለተኛ ደረጃ ብቻ የሚታይ ነው ።

እነዚያድ ባሬ «ብሔራዊ ስሜት» የሚሉት «የታላቋ ሶማሊያ» ብሔራዊ ስሜት ነው ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በሶማሊያ የታየውም «የብሔራዊ ስሜት» መንፈስ ይኸው ነው ። የሶማሊያ ጦር ኃይሎች ሚና በመርሐ ግብሩ ውስጥ ሲቀጠስ ስለ ሶሺያሊስት አርበኝነት ፣ በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት አኳያ የሶማሊያ ጦር ኃይሎች ሚና ምን መሆን እንዳለበት ጨርሶ አልተጠቀሰም ።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ነጥብ አለ ። ብሔርተኝነት (Nationalism) በታዳጊ አገሮች ውስጥ ፀረ ኮሎኒያል ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት ሊኖረው ስለሚችል በዚህ አንፃር የሚደገፍ ነው ። ይሁን እንጂ የቡርዧውና የፊውዳሉ መደቦች የበላይነታቸውን ባረጋገጡባቸው አገሮች ብሔርተኝነት ዞር ዞር የቡርዧው ብሔርተኝነት ከመሆን አይደንም ።

በሶማሊያ ጦር ሠራዊት ውስጥ የሚሠራጨው «ብሔራዊ ስሜት» ከሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ጋር የሚጣጣም ከሆነ የጦር ኃይሎቹ ተግባር «የብሔራዊ ስሜት» መግሪያ ከመሆን ባሻገር በአንቂነት፣ በአደራጅነትና በአምራችነት መስክም የሚሰለፉ መሆን ይኖርባቸዋል ። ይህንን በሚመለከት በፓርቲው መርሐ ግብር ውስጥ የተጠቀሱ ነጥብ ጨርሶ የለም ።

የሶማሊያን የውጭ ፖሊሲ በሚመለከት በመርሐ ግብር መግቢያ ላይ ፓርቲው ከአብዮታዊ ኃይሎችና ከሶሺያሊስት አገ

Digitized by Google

ሮች ጋር ግንኙነቱን እንደሚያጠነክር ከመግለጹ ሌላ ስለ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ፣ በሰላም አብሮ ስለመኖር ፖሊሲና ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን በመዋጋት ረገድ ከኮሚኒስት ፓርቲዎች ፣ ከተራማጅ የፖለቲካ ቡድኖችና ከብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ጋር መደረግ ስላለበት የጠበቀ ተግባራዊ ግንኙነት ምንም የተጠቀሰ አንቀጽ አለመኖሩ የዚህን ፓርቲ ፕሮግራም ቁንጽልነት የሚያንፀባርቅ ከመሆኑም ሌላ ፓርቲው የራሱ የተደበቀ ፍላጐት ያለው ያስመስለዋል ።

በፓርቲው መርሐ ግብር በአንቀጽ 35 በተራ ቁጥር 6 ላይ በሶማሊያ አብዮት ውስጥ የሴቶችን ሚና በሚመለከት የሰፈራው ቃል እንዲህ ይላል ። «የፓርቲው ዓላማ (የሶማሊያ ሴቶች) --- ለሴቶች ጥያቄ እንዲታገሉና ከፍተኛ ብሔራዊ ስሜትና የሶሽያሊዝምን መርሀ እንዲጨብጡ ማድረግ ነው»[24] ይላል።አሁንም ቢሆን የሴቶችን ሚና በሚመለከት ትኩረት የተሰጠው «ለብሔራዊ ስሜት ነው»። የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሽያሊስት ፓርቲ «መርሐ ግብር የሶማሊያ ሴቶች ከሚወክሉት መደብ በመለስ ሁሉንም «በሴቶች ጥያቄ» ስር የሚያሰልፍ ከመሆኑም በላይ ሶሽያሊዝምን በመርሀ ደረጃ ብቻ እንዲቀበሉ የሚጋብዝ ነው ።

የፓርቲ መርሐ ግብር የፓርቲውን የሩቅና የቅርብ ዓላማዎችንና ግቡን በትክክል ማንፀባረቅ ያለበት ከፍተኛ ሰነድ ነው ። በሰነዱ ውስጥ የሚሰፍሩት የፓርቲው ዓላማዎች ግብ መምታት በፓርቲው ድርጅታዊ ጥንካሬና በአባላቱ የንድፈ ሀሳብ ጥራት ላይ የሚመሰረት የመሆኑን ያህል በዚህ ረገድ የሚፈጸም ቅንጣት ያህል እንኳ ስህተት የፓርቲውን ደካማ ጐን የሚያሰፋ ከመሆኑም በላይ ፓርቲው ለቆመለት ዓላማ ጽኑ አቋም እንዳይዝ ያግደዋል ።

ዛሬ በሶማሊያ የምናየው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ የመነጨው ከሶማሊያ የመስፋፋት ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን አገሪቷን በግምባር ቀደምትነት እመራለሁ ከሚለው «ፓርቲ» አድሀሪነት ነው ።

ሶማሊያ በእውነት የምትከተለው ሶሽያሊዝም ከሆነና ፓርቲው በፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋሙ በርግጥ የፀና ከሆነ የሌሎችን መሬት ቆርሶ የመውሰድ በሽታ ፣ ጠብ አጫሪነቱ ትንኮሳው ወረራው ምንድን ነው? በመሠረቱ «የሶማሊያን ሶሽያሊዝም» በሰላም አብሮ መኖርን የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ መጠቀምን የሕዝቦችን ወንድማማችነት የማያውቅና የማይቀበል ከሆነ ምኑን ሶሽያሊዝም ሊባል ይችላል ፣ ማንስ እንደዚህ ዓይነቱን ውጥርጥር ያለና ጨቅላ የሆነ ብሔርተኝነት ሶሽያሊዝም ብሎ ላንድ አፍታ እንኳን ሊቀበለው ይችላል?

ከፓርቲው አይዲዮሎጂካዊ ቀውስ ጋር ተደምሮ መታየት ያለበት ሌላው ገጽታ ጉዳይ ደግሞ በሶማሊያ መንግሥት ውስጥ የሚንፀባረቀው የሕልውና ቀውስ (Identity Crisis) ነው ። የሶማሊያ መንግሥት የሳውዲት አረብ ፔትሮ ዶላር ተመጽዋች በመሆኑ የእስልምና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት መሆኑን ከመቀበሉም በላይ (የ1960 የሶማሊያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1 ቁጥር 3) የአረብ ሊግ አባል ነው ። የሚገርመው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በመሆን ብቻ የ«አረብነትን» መታወቂያ ተቀብላ በ1974 የአረብ ሊግ አባል የሆነችው አፍሪካዊት ሀገር ሶማሊያ ብቻ ነች ። መቼም እስላም የሆነ ሁሉ አረብ ነው ከተባለ የሶማሊያ ሰፊ ሕዝብ አረብ እንጂ ሶማሊያ አይደለም ማለት ነው ።

ሶማሌዎቹ ሲያሰኛቸው «ፍጹም አፍሪካውያን» ይሆናሉ ሳያዋጣ ሲቀር ደግሞ «አረቦች» ይሆናሉ ። ይሁንና የዚህ ሁሉ የሕልውና ቀውስ መሠረት ምንድር ነው? ውጤቱስ ምን ይሆናል ። በመሠረቱ ሶማሌዎች የራሳቸውን ታሪክ ገና እየፈለጉ ስለሚነግሩንና «የሶማሌ ብሔር» እየፈጠሩ በመሆናቸው መጠበቅ ያስፈልግ ይሆናል ። ከ1960 በፊት ያልነበረን የሶማሌ መንግሥትም ሆነ ብሔር ዛሬ ለመፍጠር የሚቻለው «በታላቋ ሶማሌ ፖሊሲ» መሆኑ ከተከሰተላቸው ውሎ አድሮአል ። የዛሬውም «የሶማሌ ሳይንሳዊ ሶሽያሊዝም» «የታላቋ ሶማሌ ፖሊሲያቸው ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም ።

እንደገና ወደ «ሶማሊያ አብዮታዊ ሶሽያሊስት ፓርቲ» መርሐ ግብር እንመለስ ። በፓርቲ መርሐ ግብር ውስጥ ከሚጠቀሱት አብይ ጉዳዮች አንዱ የፓርቲው

የኢኮኖሚ አጠቃላይ መርህ ነው ። በዚህ መርሐ ግብር ውስጥ ግን በሶማሊያ ምን ዓይነት የምርት ግንኙነት እንደሚስፋፋና በዚህም ረገድ የፓርቲው አጠቃላይ ሚና ምን እንደሆነ የተገለጸ ነገር ካለመኖሩም በላይ ፓርቲው በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ሚና እንደሌለው አድርጐ የሚያቀርብ ነው ።

በብዙ የዋሆች አመለካከት ሶማሊያ ቀድሞ ሶሺያሊስት መስላ ትታይ ነበር ። ቀድሞ ከነበረው ከኃይለ ሥላሴ ፊውዶ ቡርዧ ስርዓት አንፃር እንኳን ብትታይ ሶማሊያ ያኔም ሶሺያሊስት አልነበረችም ፣ ዛሬም ቢሆንአይደለችም ። የዚያድ ባሬ ወታደራዊ ቡድን በመፈንቅለ መንግሥት ስልጣን ከያዘ በኋላም ሆነ በፊትም ሶማሊያ ከማርክሲዝም ይልቅ ሀሳባዊነትን ከወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ይልቅ ጠባብ ብሔርተኝነትን በሰላም አብሮ ከመኖር ፖሊሲ ይልቅ ጦርነትን ስታስፋፋ እንደቆየች የዛሬዎቹ ወዳጆችዋ ሳይቀሩ ያረጋግጣሉ ።

ሶማሊያና የኢትዮጵያ አብዮት

በታሪክ ውስጥ ብዙ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ያጋጥመናል ። በሕዳር ወር 1817 ቦልሸቪክ ፓርቲ በሶቪዬት ሩሲያ ሥልጣን በያዘ ከሁለት ሳምንት በኋላ በጊዜው የነበሩ ቀንደኛ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች (Entente Powers) በፓሪስ ከተማ ከፍተኛ ስብሰባ አደረጉ ። የዚህ ስብሰባ ዋንኛው ዓላማ በሶቪዬት ሩሲያ የተቋቋመውን የሠራተኞች መንግሥት ገና በእንጭጭ ለማስቀረትና ሶሺያሊዝም በሩሲያ ምድር እንዳይገነባ ለማገድ ነበር ።

የእንግሊዝ ፣ የፈረንሳይና የአሜሪካን መንግሥት ምንም እንኳ በጊዜው ዋንኛው ጠላታቸው ጀርመን ብትሆንም ከጀርመን ወረራ ይልቅ ከፍተኛ ድንጋጤ የጣለባቸው ከተቋቋመ ወር ያልሞላው የሶቪዬት ሥልጣን ነበር ። በታህሣሥ ወር መጨረሻ ላይ (1917) ፈረንሣይና እንግሊዝ ሶቪዬት ሩሲያን ለመከፋፈልና በራሳቸው የተጽእኖ ክልል ለማጠቃለል ተስማሙ ። ለዚሁ አድሀሪ ተግባራቸው ተጨማሪ ኃይል ለማግኘት የኋላ ኋላ ከጃፓን ወራሪ ጦር ጋርም ግምባር ፈጠሩ ።

ከ60 ዓመት በኋላ (1977) በአፍሪካም ቀንድ ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጠረ ። ዋና ዋናዎቹ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ከአካባቢው አድሀሪ የአረብ መንግሥታት ጋር በማበር በኢትዮጵያ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አብዮት ለማኮላሸት ተነሳሱ ። በ1917-18 በሶቪዬት ሩሲያ ላይ ከበባና ወረራ እንደ አደረጉ አሁንም የኢትዮጵያን አብዮት ለመምታት አድሀሪያን ከውስጥና ከውጭ አሰባሰበው አስታጥቀው አደራጅተው ለቀቁብን ።

የኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳት በዓለም የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ለውጥ በማስከተሉ የአብዮቱ ወዳጆችና የለየላቸው ጠላቶቻችንም እንደየፍላጐታቸውና እንደየፖለቲካ አቋማቸው የኢትዮጵያን አብዮት በከፍተኛ ትኩረት ይመለከቱ ነበር ።

በተለይም 1977 የኢትዮጵያ አብዮት በውስጥና በውጭ የአድሀሪ ኃይሎች ሴራ ተወጥሮ በነበረበት ሰዓት የግብጽ አድሀሪ መንግሥት ፣ የሶማሊያ ተስፋፊዎችና የአረብ ፔትሮዶላር ኃይሎች አንድ ላይ በማበር የሶማሊያ አድሀሪ መንግሥት በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ያነሳውን የፈሪ ብትር ለማጠናከር ተነሳሱ ። ኢምፔሪያሊስቶች በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በግብጽ፣ በሳውዲት አረቢያና በሶማሊያ ተስፋፊዎች አማካኝነት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማፋለስና አብዮቱን በጅምሩ ለማስቀረት ከላይ ከታች ተሯሯጡ ። ይህንን አድሀሪ ወረራ በተግባር ለመተርጐም የሳውዲት አረብ መንግሥት 400 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል ገባ ። የሳውዲት አረብ መንግሥት ሳማሊያ እንድትገፋበት አስፈላጊውን የሎጂስቲክስ እርዳታ ለመስጠት ከመስማማቱም በላይ ምናልባት ሶማሊያ በጦርነቱ አሸናፊ ከሆነች በሶማሊያ ቁጥጥር ስር የሚሆነውን የኢትዮጵያን መሬት ለማልማት 500 ሚሊዮን ዶላር ለሶማሊያ ለመስጠት ተስማማ ።[25] ይህ እርዳታ በ1973 ከነበረው የሶማሊያ ብሔራዊ ገቢ ጋር ሲተያይ የ264 ሚሊዮን ዶላር ብልጫ አለው ።

የሶማሊያ ወራሪዎች ቀደም ሲል ጂቡቲን ፣ የኬንያን ሰሜናዊ ክፍልና የኢትዮጵያን የኦጋዴን ክፍል በ«ታላቋ ሶማሌ» ግዛታቸው ውስጥ ለማጠቃለል ከነበራቸው አድሀሪ ምኞት አልፈው የኢትዮጵያን ግዛት እስከ አዋሽ ወንዝ ዘልቀው ለመቁረስ መጣደፍ ጀመሩ ።

የሳውዲ አረቢያም አድሀሪ መንግሥት ከሌሎች አድሀሪ አረብ መንግሥታት ጋር በማበር «የአረብ የልማት መዋጮ» (Arab Fund for Development) በማ ዘጋጀት ለሱዳንና ለሶማሊያ ከፍተኛ የገ ንዘብ እርዳታ አደረጉ ።[26]

ከላይ የጠቀስነው በኢምፔሪያሊስት ኃይሎችና በአድሀሪ የአረብ መንግሥታት የተቀነባበረው አድሀሪ ሴራ መሠረታዊ ዓላማ የኢትዮጵያን የባህር ክልል በቁጥጥ ራቸው ስር በማድረግ «የቀይ ባህርን የአ ረብ ሐይቅ ለማድረግ ተነሳሱ ። ይህንኑ ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ሶማሊ ያን፣የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖችንና ሌሎ ችንም የአካባቢውን የጠባብ ብሔርተኞች ድርጅቶችን በአንድ እዝ ስር አጠቃልለው ግምባር ለመፍጠር ከመሞከራቸውም በላይ ራሱን «የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ድርጅት» ብሎ የጠራውን የስደተኛ መጫፍንት ድርጅት በሞራልና በማቴሪያል እርዳታ አጠናከሩት ።

ይህ የስደተኛ መጫፍንት ድርጅት በኢ ትዮጵያና በሱዳን ጠረፍ አካባቢ በመመሸ ግና የጦርነት ዝግጅት በማድረግ በ10,000 የሱዳን የምድር ጦርና ታንከኛ ክፍል በመጠናከር በሁመራ ፣ በአማሀጀር ፣ በተ ሰነይና በሌሎችም አካባቢዎች ያደረጉት አድሀሪ ሙከራ ዛሬም ትዝ ይለናል ።

የሶማሊያ አድሀሪ መንግሥት መሪዎች ወደ ፔኪንግ ፣ ዋሽንግተን ፣ ፓሪስና ለን ደን በመሄድ «የታላቋ ሶማሌ» ዓላማቸውን በተግባር ለመተርጐም ከፍተኛ ጥረት ከማ ድረጋቸውም በላይ የጅቡቲንና የኢትዮጵያ የጋራ ጥቅም ለማስቀረት ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ አፈራረሱ ፣ በከፍተኛ ወጪ የተሰሩ ድል ድዮችንም አፈራረሱ ።

ከዚህም ሁሉ በላይ መወሳት ያለበት ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ባወጀችው አድ ሀሪ ጦርነት ላይ የአሜሪካን አቋም ምን እንደነበረ ነው ። በማርች 1978 ላይ የሶማ ሊያ አድሀሪ ጦር በአብዮታዊ ጦራችን ፣ በአብዮታዊው ሚሊሺያ በሰፊው ሕዝብ ደጀን ተሰላፊነት ከተመታ በኋላ በሶማሊያ መንግሥትና በአሜሪካን መንግሥት መካ ከል የተፈጠረው ግንኙነት ሰፋትና ጥል ቀት እያገኘ መጣ ።[27]

በዚሁ ዓመት (1978) በአሜሪካን አገር የሶማሊያ አምባሳደር ከፕሬዚዳንት ካርተር ጋር ከተወያየ በኋላ በዶክተር ኪብን ካህል የሚመራ አንድ የአሜሪካን የመልዕክተ ኞች ጓድ ወደ ሶማሊያ ተላከ ። ዶክተር ካህል በዚሁ ወቅት ከዚያድ ባሬ ጋር ባደረ ገው ንግግር በሁለቱ አድሀሪ መንግሥታት መካከል መሠረታዊ ስምምነት ተደረሰ ። ይኸውም የሶማሊያ መንግሥት ከአሜሪካ የጦር መሣሪያ የሚገዛበትን ሁኔታ የሚጠና መሆኑን የሚያስረዳ ስምምነት ነበር ።[28]

የአሜሪካን መንግሥት ዋና ፍላጐት በሶማሊያ ወደቦች ማለትም በበርበራና በኪስማዩ በመጠቀም የሕንድ ውቅያኖስ አካባቢንና የፔርሽያን ባህረ ሰላጤ በመቆ ጣጠር በአካባቢው ያሉትን ነዳጅ አምራች አገሮች በቁጥጥሩ ስር በማድረግ በመካከ ለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የፖለቲካ የበላይነት ማግኘት ነው ። የአሜ ሪካን መንግሥት በዲያጐ ጋርሲያ ያቋቋ መውን የጦር ሰፈር ማጠናከሩም ከዚሁ ዓላማው ጋር የተያያዘ ነው ።

የአሜሪካን መንግሥት በተለይ በኢት ዮጵያ ፣ በየመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክና ሌሎች በአካባቢው ያሉትን ተራማጅ እን ቅስቃሴዎች ለማፈን ያለውን አድሀሪ ፍላ ጐት ለሟሟላት ከሶማሊያ መንግሥት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ከማድረጉም በላይ በነ ሐሴ 21 ቀን 1980 በሶማሊያ መንግሥትና በአሜሪካን መንግሥት መካከል በተፈረ መው ውል መሠረት የአሜሪካን መንግሥት ለሶማሊያ ከ20 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገ መት ወታደራዊ ዕርዳታ ሰጥቷል ።» በተ ጨማሪም የአሜሪካን የባህር ኃይልና ያየር ኃይል በበርበራና በኪስማዩ «የፈጣን ጣልቃገብ» ጦር ሰፈር እንደሚሠራቱ የአ ሜሪካን መንግሥት በዚህ ዓመት የ25 ሚሊ ዮን ዶላር እርዳታ ለሶማሊያ መንግሥት ሰጥቷል ።

የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ አብ ዮት ላይ የወሰደው አቋም ከላይ በጠቀስና ቸው የፖለቲካ ሁኔታዎች አኳያ የሚታይ እንደመሆኑ መጠን የሶማሊያ መንግሥት በሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ስም ለ17 ዓመታት

Digitized by Google

ሰፊውን የሶማሊያ ሕዝብ ሲያወናብድ ከቆየ በኋላ ዛሬ ትክክለኛ ባህርዩን ለዓለም ሕዝብ በገሀድ አሳይቷል ። የኢትዮጵያ አብዮት እንደፈነዳና የሶሻሊስት አቅጣጫ እንደያዘ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮች በተለይም ከሶማሊያ ጋር በሰላም በወዳጅነት ፤ በወንድማማችነት ፤ በጋራ በሁለቱ አገሮች የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች አልምተው ለመጠቀም ፈቃደኛ መሆንዋና በመካከላችን ያሉትም ችግሮች በዚህ ትብብር መፍትሄ ለማግኘት የሚችሉ መሆኑን በሚገባ ገልጾ ነበር ። ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ አድሀሮት ግንባር በመፍጠር በቅርብና በኅብረት ለሶሻሊዝም ለመታገልና ሙሉ አድርም በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ወደ ሁለቱ ሕዝቦች ባንድ መንግሥት ስር መኖር የሚያመራ ሀሳብ አቅርባ ነበር ። በሶሻሊዝም ስም የሚነግደውና የሚያወናብደው አድሀሪው የሶማሊያ የገዥ መደብ ግን ለዚህ የሰጠው አፀፋ ሰርጎ ገብነት ትንኮሳ ፤ ጠብ አጫሪነት ፤ ወረራ ነው ። ይህ ሐቀኛና አብዮታዊው የኢትዮጵያ አቋም ዚያድ ባሬንና ግብረ አበሮቹን ያጠለቁትን የውሸት ቀይ ካባ አውልቆ ከሶሻሊስት ሰፈር ተባረው ትክክለኛውና እውነተኛው ስፍራቸው ከቀንደኛው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እግር ስር አስቀምጧቸዋል ።

በቅርቡ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሪነት በሜዲተራኒያን ባህር ፤ በፔርሺያን ባህረ ሰላጤ አካባቢና በሕንድ ውቅያኖስ ፤ በግብጽ ፤ በሱዳንና በሌሎችም አድሀሪ አረብ አገሮች ተባባሪነት የሚካሄደው "Bright Star" የተሰኘው የጦር ልምምድ በኢትዮጵያ ፤ በደቡብ የመንና በሊቢያ አረብ ጀማሀሪያ ላይ የተቃጣ ትንኮሳ መሆኑ በግልጽ የታወቀ ነው ፤ ታዲያ የሶማሊያ «የሽያሊስቶች» የሶሽያሊዝም ልፈፋ ውጤት በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጉያ ውስጥ መግባት መሆኑ ዛሬ የአደባባይ ምስጢር ነው ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

የሶሻሊስት ሥርዓት ግምባታ እጅግ ውስብስብና ውጣ ውረድ የበዛበት መሆኑ የታመነ ነው ። በተለይም እንደ ሶማሊያ ባሉ ኋላ ቀር አገሮች ሶሻሊሊዝምን መገንባታ እጅግ ከባድ መሆኑ እሙን ነው ። ሶማሊያ በሚመለከት ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ከተምኔታዊ ሶሻሊዝም አስተሳሰብና ከሀሳባዊነት ጋር ተምታቶ የቀረበ በመሆኑ የሶማሊያ አብዮታዊ ሶሺያሊስት ፓርቲ «ከታላት ገድገዳ በስተጀርባ በመቆም «ሶሻሊስት» ነኝ ለማለት ቢሞክርም ዛር የምናየው ሀቅ ይህ አይደለም ።

ሶማሊያ በብዙ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች የተወጠረች እንደመሆኗ በጎረቤት አገሮች ላይ ደግሞ ያላት አቋም ይህንን ሁኔታ እያባባሰው ሄዷል ። እነ ዚያድ ባሬ ከጎሣ አስተሳሰብ ተለቀው የሶማሊያን ሕዝብ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚችሉት «ከታላቋ ሶማሌ» የመስፋፋት ፖሊሲያቸው ሲላቀቁ ብቻ ነው ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ሶማሊያ ከወደቀችበት አዘቅት የመውጣት እድሏ እጅግ የመነመነ ነው ።

ከጎረቤት አገሮች ጋር በሰላም አብሮ መኖርና በኢኮኖሚ እድገት አኳያ ኅብረት መፍጠር ለሶማሊያ ሰፊ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ወሳኝ ከመሆኑም በላይ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አስተማማኝ ሰላም ሊገኝ የሚችለውም ይህ ሁኔታ ሲሟላ ብቻ ነው ። በዚያድ ባሬ የሚመራው መንግሥት የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ የሶማሊያንና የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ሲያፋጅ ሊኖር አይችልም ። የሶማሊያ ተራማጅ ኃይሎች ኅብረት ፈጥረው የዚያድ ባሬን መንግሥት ገርስሰው እስካልጣሉ ድረስ የሶማሊያ ሰፊ ሕዝብ ኑሮ በጭራሽ ሊሻሻል አይችልም ። በተቃራኒው ወደ ውድቀት አዘቅት ውስጥ እየሰጠመ ነው ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጨቋኙን የፊውዶ ቡርዧው መንግሥት በተባበረ ክንዱ ገርስሶ እንደ ጣለ ሁሉ የሶማሊያ ተራማጆችም የኢትዮጵያን ፈለግ ቢከተሉ የሁለቱ ጭቁን ሕዝቦች ኅብረት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም ። በዚያድ ባሬና በአጫፋሪዎቹ ላይ ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ የሱማሊያ ድርጅቶች በማፋፋም ላይ ያሉት ትግል በቅርብ ጊዜ ውስጥ ድልን እንደሚቀዳጅና ሰፊውን የሱማሊያ ሕዝብ ነፃ በማውጣት ከወንድሙ የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ሕዝብ ጋር በሰላምና በወንድማማችነት እንደሚያቀራርበውና አብሮ ለመኖር እንደሚያበቃው አይጠረጠርም ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. V.I Lenin, *Collected Works*, Vol. IV p. 212.
2. V.I Lenin, *Collected Works*, Vol. V. p. 384.
3. ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀመንበር የአብዮታዊው ጦር አዛዥ ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ሪፖርት ፤ የካቲት ፤ 1973 ፤ ገጽ 45።
4. Margery Perham, *The Government of Ethiopia*, London, 1947, p. 447.
5. I.M. Levis, The *Modern History of Somaliland*, New York, Praager Publishers, 1965 p. 104.
6. ከላይ ከተጠቀሰው ።
7. ከላይ ከተጠቀሰው ።
8. Area Handbook for Somalia, Foreign Area Studies, Washington, American. University, 1969, p. 226.
9. Masfin Woldemariam, *Somalia: The problem Child of Africa*, Artistic Printing press, Addis Abeba September 1977, p. 399.
10. Statute of the Somali Revolutionary Socialist Party, Somali Democratic Republic- Mogadishu, October 1976, p. 1.
11. General Saiyad Barre, *My country and My people*, Vol. 1 Published by the Ministry of Information and National Guidance Mogadishu, 1974, p. 85.
12. ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገጽ 15 ።
13. ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገጽ 75 ።
14. General Saiyad Barre, *My country and My People*, Vol II, / Published By the Ministry of Information and National Guidance, Magadishu, 1971, p. 4.
15. ፊት ከተጠቀሰው ገጽ 9 ።
16. ፊት ከተጠቀሰው ።
17. Le Duan, *Selected Writings*, Foreign Languages publishing House, Hanoi, 1977, p. 66.
18. General Saiyad, *My country and My people*, Vol. II, p. 75.
19. Jack Woodis, New Theories of Revolution, International publishers, New York, 19, p. 84.
20. Lenin, *Collected Works*, Vol. X, p. 84.
21. War In the Horn of Africa; A First Hand Report on the Challenges for the united states Policy, Report of A fact finding Mission to Egypt, Sudan, War In the Horn of Africa; A First Hand Report on the Challenges for the United States Policy, Report of A fact finding Mission to Egypt, Sudan, Ethiopia, Somalia and Kenya, December, 1977, p. 19.
22. Statute of the Somali Revolutionary Socialist Party, Mogadishu, October 1976. p. 2.
23. ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገጽ 32 ።
24. ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገጽ 35 ።
25. The Ethiopian Revolution and the Struggle Against U.S Imperialism, World View publishers, By Workers World News Paper, New York 1978. p .7.
26. ከላይ ከተጠቀሰው ።
27. "The Horn of Africa" Review of African Political Economy, New York, p. 20.
28. ከላይ ከተጠቀሰው ።

Digitized by Google

ባህልና ንድፈ ሀሳባዊ ግንዛቤው

መሐመድ ሳላህ

ባህል የሚለው የአማርኛ ቃል በእንግሊዝኛ ካልቸር የሚለው ቃል ከአዘለው ጽንሰ-ሀሳብ ጋር ወይም ይህ ጽንሰ-ሀሳብ ከሚሰጠው ትርጉምና በውስጡ ከሚገኙ ነገሮች አንፃር ሲታይ ሙሉ በሙሉ አይገጣጠምም ። ከዚህም ሌላ ባህል በተራ አማርኛ አገባቡ የሚታወቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና አሁንም ያለ ነገር ቢሆንም የሚፈጠሩ ነገሮችን እንደሚያጠቃልል ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም ። በዚህም አንፃር ሲታይ ካልቸር ካዘለው ጽንሰ ሀሳብ ይለያያል ። በተጨማሪም ባህል ፣ ልማድና ወግ ከሚባሉት ቃላት ጋር ያለው ልዩ ተመሳሳይነት ጥርት ባለመንገድ በውል የሚታወቅ አይመስልም ።

በደስታ ተክለወልድ ከተዘጋጀው አዲስ የአማርኛ መዝገበ-ቃላት ውስጥ ባህል የሚለውን ቃል ልማድ ፣ ደንብ ነው ሲል ይተረጉመዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ ልማድ ለሚለው ቃል ይሄው መዝገበ ቃላት የሚሰጠው ፍቺ «ልማድ ማለት ዐመል ፣ ደንብ ፣ ሕግ ፣ ወግ» ነው ይልና ተጨማሪ ማብራሪያ ሲሰጥ «ልማድ ትንባሆ ፣ ጫት ፣ ቡና ፣ ጠጅ፣ ዐረቂ ልዩ ልዩ መብልና መጠጥ በያንዳንዱ ሰው ዘንድ ዘወትር ተፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ ልማድ ይባላል ። ልማድ የተለመደ ፣ የተጠና ፣ የታወቀ ፣ እውቅ ፣ ሥራዩ ተብሎ የታወቀ» ነው ይላል ።

ከዚህ ትርጉም ውስጥ በርካታ ነጥቦችን ለመረዳት የሚቻል ይመስለናል ። በመጀመሪያ ደረጃ ባህል ፣ ልማድና ወግ ተመሳሳይ እንደሆኑ እንመለከታለን ። በሌላ በኩል ግን መዝገበ-ቃላቱ ወግ ምን እንደሆን ሲፈታ «ወግ እጅግ የቆየ የዘገየ ዜና ወሬ ፣ ነገር ፣ የታሪክ ዓይነት ፣ እንዲህ ነበር እየተባለ የሚነገር ፣ የሚወራ ደንብ ፣ ሥርዓት ፣ ልማድ» እንደሆነ አድርጎ ስለሚተረጉም ወግ አፈ-ታሪክና ከዚህ በፊት የነበረ አለበለዚያም በአሁኑ ወቅት ድርጊቱ በመፈጸም ላይ ቢገኝም እንኳን ሙሉ በሙሉ በአላፊ ጊዜ ውስጥ ብቻ ተወስና (በጊዜ አንፃር) የሚገኝ ወይም የሚባል ነገር እንደሆን ያሳያል ። የአሁኑን ወይም በመባል ላይ ያለን ነገር እያመለከትም ማለት ነው ።

ሌላኛው ከዚህ ትርጉም ውስጥ ለመረዳት የሚቻለው ልማድ ሱስ እንደሆነና ሱሱን ለማርካት የምንገለገልባቸውን የፍ

Digitized by Google

ጀታ እቃዎችን ማመለከቱን ነው ። ከዚህ ትርጉም ጋር ተያይዞ ልማድ «በያንዳንድ ሰው ዘንድ» የሚል በመሆኑ ግላዊ ጉዳይ ስለመሆኑ እንጂ ማህበራዊነቱን የሚጠቁም አይደለም ። «ሥራዬ ተብሎ የሚታወቅ» ነው ስለሚል ልማድን እውቀት እንደሆነም ሲያሳይ በሌላ በኩል ግን ፈሊጥ ለሚለው ቃል የሚሰጠው ትርጉም» ዕውቀት ፤ ዘዴ ፤ ነው ይላል ። ከዚህም የተነሳ ልማድና ፈሊጥ እውቀት በመሆናቸው ተመሳሳይነት እንዳላቸው ለመመልከት ይቻላል ።

እዚህ ላይ ግን ልማድና ፈሊጥ በዕውቀትነታቸው የተነሳ ተመሳሳይነታቸውን ለመመልከት ብንችልም በዕውቀቱ ምንጭ አንፃር ስንመለከታቸው ልዩነት እንዳለ ለመገመት የሚያስችል ሀሳብ አለ ። ልማድን እንደ እውቀት አድርጐ ሲወስድ የዚህ ዕውቀት ምንጭ ግን ሆን ተብሎ አንድን ነገር በተደጋጋሚ በማድረግ ወይም በመጠቀም የሚገኝን ዕውቀት መሆኑን እንረዳለን ። የፈሊጥ ዕውቀትነት ግን ከየት እንደሚመጣ በቀጥተኛ መንገድ አያመለክትም ። ይሁን እንጂ «ሞኝ ያገኘው ፈሊጥ ውሻ የደፋው ሊጥ . . .» የሚለውን ተረት ለማብራሪያ እንደ ምሳሌነት ስለሚያቀርብ የፈሊጥ ዕውቀትነት ከብልሀት ወይም ብልጥ ከመሆን ጋር የተዛመደ ወይም ተመሳሳይ ሊሆን የሚችል ዕውቀትን እንደሆነ ለመገንዘብ የሚቻል ይመስላል ።

ከትርጉሙ የምንመለከታቸው ነጥቦች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም ። ደንብ ፤ ሕግ ሥርዓት የሚሉት ቃላት በመገኘታቸውና እነዚህ ቃላት ደግሞ ያላቸው ትርጉም ሲታይ የባህልን ምንነት ይበልጥ ውስብስብ ያደርገዋል ።

የተፈጥሮና የማህበራዊ ህግጋት ስርዓት በሚባልበት ጊዜ ማህበራዊ ሕግና ሥርዓት ለማለት ነው ። ደንብ የሚለውም ቃል ከሰዎች ጠባይ (behavior) ጋር የተዛመደና ይህንንም የሚገልጽ በመሆኑ ማህበራዊ ነው ። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። ይኸውም ሕግ ተብሎ በትርጉሙ ውስጥ ሲሰጥ በመንግሥት የሚወጣ የፍታብሔር ወይም የወንጀል ሕግም ለማለት አይመስልም ። ምክንያቱም የተወሰነ ልማድን መከበርና አለመከበር ወንጀል ነክ ካልሆነ በስተቀር አንቀጽ ተጠቅሶ የሚያስቀጣ አይደለም ። ይህም ሲባል ደግሞ የተወሰነ ልማድን አለማክበር አያስቀጣም ወይም የማናቸውም ልማድ አለመከበር ያስቀጣል ወይም የግድ ቅጣትን የሚያስከትል ነው ማለት አይደለም ።

ይህ ብቻ አይደለም ሕግ ያለን «ልማድ» ባህል ፤ ደንብን ወዘተ የሚያስጠብቅ እንጂ እራሱ ባህል አይደለም ። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረውም የተወሰኑ ልማዶች መከበራቸውና አለመከበራቸው በሕግ የሚያስቀጣ ወይም የማያስቀጣ ሊሆን ይችላል ብለናል ። የተወሰኑ «የተለምዶ ሕጐች» በፍታብሔር ወይም ወንጀል ሕግ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው ። ስለሆነም አንቀጽ ይኖራቸዋልና እንዚህን ደንቦች አለማክበር የሚያስቀጣ ይሆናል ፤ በሌላ በኩል ግን በርካታ «የተለምዶ ሕጐች» (Customasy Laws) በሕግ ውስጥ ያልታቀፈ ወይም ሕግ ስለነርሱም የሚያነሳው ወይም የሚጠቅሰው ከሌለም ግን የእነኝህ ደንቦች መጣስ ግላዊ ጉዳይ አለበለዚያም ሕብረተሰቡየሚያወግዘው ብቻ በመሆን ይቀራሉ እንጂ የሚያስቀጡ አይደሉም ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች አንዳንድ ነገሮችን ለመመልከት የሚቻል ይመስለናል ። በአንድ በኩል ሕግ ያሉ ልማዶችን ፤ ወጐችንና ባህሎችን ሁሉንም እንዳሉ ሳይለወጡ እንዲከበሩ አያደርግም ። ስለሆነም ልምዶች ፤ ወጐችና ባህሎች በሕግ በመጠበቃቸው ሳይለወጡ በመቅረት በጣም ጊዜ እንዳያልፉባቸውና ይህም በህብረተሰቡ ላይ ችግር እንዳይፈጠር ለማድረግ ይረዳል ። በአንዳንዶቹ ልማዶች ላይ ደግሞ ሕግ ዝም በማለቱ መለወጣቸው ጠቃሚ ሆኖ ሲለወጡ ስለማይቃወም የለውጥ እድል እንዲኖር ያደርጋል ። በሌላ አነጋገር ሕግ ባህልን በራሱ የእድገት ሕግ መሠረት እንዲያድግ የሚያደርግ እንጂ እራሱ ባህል እንዳልሆነ ለመመልከት ይቻላል ።

ለምሳሌ በሠርግ ጊዜ አንድ ሙሽራ በልማድ ለሙሽራይቱ ወይም ለቤተሰቦቿ በሠርጉ ቀን ሊደረግላት ወይም ሊደረግላቸው የሚገባውን ነገር ሳያሟላ ቢቀር አይቀጣም ማለት አይደለም ። በፍርድ ቤት ባይሆን እንኳን በቤተሰብ ሸንጐ ይቀጣል ። ምክን

Digitized by Google

ያቱም ህብረተሰቡ እነዚህን ነገሮች የሚያበረታታ ወይም የሚደግፍ አይደለምና ነው። በሌላ በኩልም ሽማግሌ ወይም አንዲት ባልቴት ሲመጡ በእድሜው ከነርሱ ያነሰ ሰው በማክበር ከወንበር አለመነሳት ወይም ለነርሱ እንዲቀመጡ ወንበር አለመልቀቅ የሚያስቀጣ ሳይሆን ውግዘትን፣ እርግማንን የሚያስከትል ይሆናል እንጂ በፍርድ ቤት አያስቀጣም ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ መከበር ያለባቸው ልማዶች ሳይከበሩ የቀሩ እንደሆነ በሕግ የሚያስቀጡ አሉ ።

እዚህ ላይ በመጀመሪያ አያስቀጣም ያልነውን ጉዳይ በመካድ ያስቀጣል በማለት ለመሻር ወይም የመጀመሪያውን ሀሳብ የሚቃረን ሀሳብ ማቅረባችን አይደለም ። ለምሳሌ አንድ ጤነኛ የሆነ ሰው በአደባባይ ራቁቱን ሲሄድ ቢገኝ ራቁት መሄድ ልማድ ባይሆንም የሕዝብን ስነ ምግባር (Public Morality) የሚነካ በመሆኑ ይቀጣል ። ይህ ግን የሚያስቀጣው ሆን ተብሎ የሕዝብን ስሜት ለመንካት ወይም ለማስቆጣት የተደረገ ወንጀልም በመሆኑ ነው ። የልማድና ደንብ ጉዳይ እንደ የሕዝብ የእድገት ደረጃና ታሪክ ፤ የአየር ጠባይ፤ ሃይማኖት ወዘተ የተለያየ በመሆኑ አንዳንድ ቦታ ራቁት መሆን የተለመደ በመሆኑ በነውርነት የማይታይ ወይም ድርጊቱ የሚያስወግዝ ሊሆን ይችላል ። ይህ ደግሞ ልማድና ደንብ ማህበራዊ እንደሆኑና የተወሰነ ሥነ ምግባራዊ መመዘኛ (Morale evalution) እንዳለው ያሳየናል ።

እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ይሄኛውን ልማድ ማክበር አያስቀጣም ወይም ያኛውን አለማክበር ያስቀጣል ለማለት አይደለም ። እዚህ ሁሉ ትንታኔ ውስጥ ለማግባት ያስገደደን ባህል ፤ ልማድና ወግ ለሚባሉት ቃላት በአማርኛ የሚሰጠው ትርጉም ግልጽ አለመሆኑን ለማስመልከት ነው ። የቃላቶቹ ትርጉም ተመሳሳይነትና ልዩነት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ተቃራኒም ናቸው ። እንዲሁም ግልጽ ያልሆኑና ልቅ ትርጉም አላቸው ። በሌላ በኩልም ካልቸር ከሚለውና ይህ ጽሑፍ ለማሳየት ከሚሞክረው ትርጉም ጋር የተለዩና የማይጣጣሙ ናቸው

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እኛ ባህል የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት በእንግሊዝኛው ካልቸር በሚለው ቃል በትንታኔው ውስጥ በተሰጠው አገባቡ ብቻ በመወሰን ነው ። ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል በዚህ ወቅት ትርጉሙን ከመስጠት እንድንቆጠብ እንገደዳለን ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ባህል (ካልቸር) ምን እንደሆነ ፤ በትርጉሙ ውስጥ ምን ምን ነገሮችን እንደሚያቅፍና የነዚህ ክፍሎች የተናጠልና የወል ባህርያት ምን እንደሆኑ ማሳየት ነው ። ከዚህ በተረፈ ባህል መቼና እንዴትስ እንደሚፈጠር ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ማሳየትና ባህል ከስልጣኔ ጋር ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ለመጠቆምም ሙከራ ያደርጋል ። እንዲሁም የባህልና የኪነትን የመደብ ባህርያት ርዕዮተ ዓለማዊና ሌሎች አገልግሎቶችን በማሳየትና ከነዚህም መሠረታዊ ሀሳቦች በመነሳት በጽሑፉ ሁለተኛ ክፍል የተጠቀሰውን ርእስ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማገናዘብ ሙከራ ይደረጋል ።

በመጨረሻም ይህ ባህልን በሚመለከት የቀረበው ፅሑፍ የመጀመሪያ ሙከራ በመሆኑ ይበልጥ ሊብራራ ፤ ምርምርና ጥናት ሊደረግበት የሚገባው እራሱን የቻለ የጥናት መስክ እንደሆነ አንባቢያንን ለማሳሰብ እንወዳለን ።

ባህል ምንድን ነው ?

በርካታ ትርጉም ከሚሰጣቸውና በኅብረተሰብ ተመራማሪዎች መሀከል ክርክርን ከሚፈጥሩት ማኅበራዊ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ባህል የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ነው ። ለምሳሌ የተለያዩ ሕዝቦች ያላቸው ባህላዊ ልዩነት የሚመነጨው ወይም የሚወሰነው ከየአካባቢው ልዩነት ነው የሚል አባባል አለ ። እንደነኚህ ሰዎች አባባል የባህል ትርጉም መስጠት ያለበት ወይም ምንነቱ መወሰን ያለበት ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ በመነሳት መሆን ይገባዋል ። ይህ ዓይነቱ የባህል ግንዛቤ የባህልን መንስዔ በጅኦግራፊያዊ ክልል በመወሰን ባህል የተፈጥሮ ክስተቶች ውጤት እንደሆነ አድርጎ ያቀርባል። ነገር ግን የተፈጥሮ አካባቢ በባህል ላይ መጠነኛ ተጽዕና ያደርግ እንደሆነ እንጂ

Digitized by Google

አይወስነውም ። ምክንያቱም በአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ አካባቢ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የተለያየ ባህል ስለሚኖራቸውና የአካባቢው ባሕርይ ሳይለወጥም የነዚህ ሕዝቦች ባህል ተለውጦም ስለሚገኝ ነው ።

በአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የተፈጥሮ አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች የተለያየ ባህል ሊኖራቸው ይችላል ፤ እንዲሁም በጣም በተለየ አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች ደግሞ ከነዚሁ ጋር ተመሳሳይ ባህል ሊኖራቸው ይችላል ። ይህም የሚያሳየን የባህል ልዩነትም ሆነ ምንነት ምክንያቱ የተፈጥሮ አካባቢ አለመሆኑን ነው ። በአውሮፓ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች ተመሳሳይ በሆነ የጅኦግራፊ ክልል ውስጥ ቢገኙም በባህላቸው ግን የተለያዩ ናቸው ። በጣም ልዩነት ባለው የጅኦግራፊ ክልል ውስጥ የምትገኘዋ አውስትራሊያ ከአውሮፓውያን ጋር በጣም ተመሳሳይ ባህል አላት ። አሜሪካም እንዲሁ ።

ሌሎች ደግሞ የሕዝቦች ባህል ልዩነት ውስጣዊ የሆኑ የዐመል ማለትም የቁጡነት፣ ገራምነት ፤ ግንፍልነትና ለዘብተኝነት ስሜት (ልዩነት) የተነሳ ነው ይላሉ ። በነርሱም አባባል የዚህ ምክንያት ደግሞ በቆዳና በዓይን ቀለም (ከለር) ዓይነት፣ በፀጉርና በከንፈር ስፋት ወይም ቀይነት ልዩነት ፤ በአፍንጫ ሰልካካነትና ድፍጥጥነት የሚለያዩ ዘሮች ሊለያዩ የቻሉት ከማኅበራዊ ስነ ልቦና ልዩነት የተነሳ ነው ይላሉ ።

እርግጥ የሰው ዘር ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ጭምር ሊለያዩ ይችላሉ ። ነገር ግን በዘሮች መሀከል ይህን የመሰለ ልዩነት ቢኖርም በደማቸው፣ በአጥንት፣ በስሜትና በነርቭ ሲስተማቸው ግን አንድ ናቸው ። ይህም በሰዎች መሀከል ካሉት ውጫዊና ቀላል ልዩነቶች ይልቅ ውስጣዊና መሠረታዊ በሆኑት ነገሮች አንፃር ያላቸው ተመሳሳይነት እንደሚበልጥ ያሳየናል ። በመሆኑም የሰዎች ባህል ልዩነት ምክንያት ውስጣዊ አይደለም ። በሕዝቦች መሀከል ያለ የጠባይ ልዩነት ምንጭ ሰዎች በመሆናቸው ሳይሆን የተለያየ ባሕል ስላላቸው ነው ።

የተለያዩ ሕዝቦች ያላቸው የጠባይ ልዩነት በባህላቸው አማካኝነት ለመግለጽ ቢቻልም የባህሎቻቸው ልዩነት ግን የማህበራዊ ስነ ልቦናቸውን ልዩነት ሊገልጽ አይችልም ። ምክንያቱም የስነ ልቦናቸው ልዩነት የባህላቸው (Sychosomatic) መግለጫው እንጂ ምክንያቱ አይደለምና ነው ።

ከላይ የተገለፀውን ለማጠቃለል የተለያዩ ጐሳዎች ወይም ዘሮች ልዩ ልዩ የሆኑ ጠባዮች ሊኖራቸው ቢችልም ሕዝቦች በዓለም ገጽታ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ ናቸውና ምክንያቱ ጆግራፊያዊ ወይም ከሰው ውስጣዊ ባህርይ የተነሳ ሳይሆን ከባህላቸው መለያየት የተነሳ ነው ። ስለሆነም የባህላቸውን መለያየት ለመገምገም ወይም ለመግለጽ የምንችለው ሰዎች ከሚኖሩበት ማኅበራዊና ኢኰኖሚያዊ ስርዓት አንፃር ነው ።

እንግዲህ እስከ አሁን ድረስ ለመግቢያ ያህል ያየነው ስለ ሕዝቦች ባህል መለያየት መንስኤ ናቸው ተብለው የሚገመቱትን የተሳሳቱ ምክንያቶች ነው ። ይህንና ሌሎች ባህልን አስመልክተው የሚነሱትን በተለይም «ባህል ያለው ማነው?» የሚለውን ጥያቄ ስለባህል ምንነት ከገለጽን በኋላ እንስተን ለመወያየት እንሞክራለን ።

የዌብስተር እንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ባህል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በሚከተለው መንገድ ይተረጉመዋል ።

ማረስ ፤ መኰትኰት ፤ በትምህርት አማካኝነት የሰዎችን የአዕምሮና ስነ ምግባራዊ ችሎታ ማዳበር ፤ አስተሳሰብን ፤ ንግግርን ፤ ገቢርን ፤ የጥንት እቃዎችንና የሰውን እውቀት የመገብየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ችሎታን የሚያሳይ የተቀነባበረ የሰዎች ጠባይ ነው ። የአንድ ዘር ሃይማኖታዊ ወይም ማኅበራዊ ቡድን የተለምዶ እምነቶችን የሚያሳይ ነው ይላል[1]

ከዚህ ትርጉም ባህል ወይም በእንግሊዘኛ ካልቸር የሚለው ቃል የማረስ ወይም የመኰትኰትን ተግባር ከሚያሳየው ቃል ማለትም (ካልቲቬት) ወይም (አግሪካልቸር) ከሚለው ቃል ጋር ዝምድና እንዳለው እንረዳለን ። በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ ባህልን መፍጠር የጀመረው ስራስርንና ቅጠላ ቅጠልን በቀጥታ እንደተፈጥሮ ስጦታነታቸው ከመጠቀም አልፎ በእርሻ ተግባር ላይ በመሰማራት ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች

Digitized by Google

ተፈጥሮን በመለወጥ ከጀመረበት ወቅት እንስቶ እንደሆነ ነው ። እዚህ ላይ ሰው ከተግባር በፊት ወይም ተገንጥሎ በመኖር ከቆየ በኋላ በተግባር ላይ መሠማራት ጀመረ ለማለት ሳይሆን አሁን ሰው የምንለው ፍጡር የአሁን ባህርዩን በተግባር አማካኝነት አስገኘ ለማለት ነው ።

ባህል የሰው ተግባር ውጤቶች በተፈጥሮ መልካቸው ከሚገኙ ነገሮች ተለይተው ህልውና ማግኘት እንደጀመሩ የሚያሳይ ትርጉም ነው ።

በዚህ ትርጉም በቀጥተኛ መንገድ ያልተጠቀሰው የሰዎች የአእምሮአዊና ሥነ ምግባራዊ ችሎታ እንዴት ሊመነጭ እንደቻለና የዚህም መሠረት ምን እንደሆነ ነው ። ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው ሲል የባህልን ነባራዊነትና አንጻራዊ ነጻነት ቢገልጽም ባህልን ከዘር ፤ ከሀይማኖትና ከእምነት ጋር በማዛመድ ባንድ በኩል በመግቢያው እንደተገለጸው ትክክለኛ የባህል ግንዛቤ እንደሌለው ስንረዳ በሌላ በኩልም ቢሆን ባህልን በእምነት መስክ ብቻ እንደወሰነው እንገነዘባለን ።

ስለ ባህል መዝገበ ቃላቱ የሰጠው ትርጉም አንዳንድ የባህል ክፍሎችን ያቀፈና እንዲሁም አንዳንድ ባህርያቱን የጠቆመ ቢሆንም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ስነጽሑፍ ውስጥ ጽንሰ ሃሳቡ የሚያቅፈውን ሃሳብና የሚያስተላልፈውን መልዕክት የሚያበስር አይደለም ።

በሌላ በኩል ግን የፍልስፍና መዝገበ ቃላት ይህንኑ ጽንሰ ሃሳብ እንደሚከተለው ይተረጉመዋል ።

ባሕል በታሪክ ግስጋሴ ውስጥ አንድ ኅብረተሰብ ፈጥሮአቸው የሚገኙ የጠቀላላው ማቴሪያላዊና ሕሊናዊ ፋይዳዎች (ቫልዮስ) የእነርሱንም አመራረት ፤ ፍጆታና ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ዘደን የሚያሳይ ነው ። በዘልማድ ባሕል ማቴሪያላዊ ባሕልና (ማሽኖች ፤ በምርት መስክ የሚገኝ የአመራረት ልምድ እንዲሁም ሌሎች ማቴሪያላዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ነገሮች) ሕሊናዊ ባሕል (በኪነት ፤ ስነ ጽሑፍ ሳይንስ ፤ ፍልስፍና ፤ ትምህርት - - ረገዶች የሚገኙ ውጤት) ተብሎ ይከፋፈላል ። 2

ከዚህ የባህል ትርጉም ውስጥ ለመረዳት የሚቻለው

1. ባህል የታሪክ ክስተት እንደሆነና የሚያሳየው ዕድገትና ለውጥ መሠረቱ የማኅበራዊ ስርዓቶችን ለውጥ የሚከተል እንደሆነ ፤

2. የባህልን ማቴሪያላዊ መሠረት እንደሚክዱት የምሁሮችና የሕሊናዊ ውጤት እንደሆነ አድርገው እንደሚተረጉሙት የሃሳባዊያን የተሳሳቱ ቲዮሪዎች ሳይሆን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የማቴሪያላዊ ምርት የሕሊናዊ ባህል መሠረትና ምንጭ ስለሆነም ባህልን የሰፊው ሕዝብ የሥራ ውጤት አድርጐ እንደሚወሰድ ነው ።

የባህል አካሎች የሰው ልጅ ተግባር ውጤቶች እንደመሆናቸውና ተግባር ደግሞ ግላዊ ሳይሆን ማኅበራዊ እንደመሆኑ ባህል ማኅበራዊ ውጤት ይሆናል ። እንደማኅበራዊነቱ ደግሞ በኅብረተሰብ ውስጥ የሚከሰት ነው ። ስለሆነም የሰው ልጅ ከእንስሳው ዓለም ተገንጥሎ መውጣትና የመንጋነቱን ባሕርይ ትቶ ኅብረተሰብን እንደ አንድ ማኅበራዊ ድርጅት እንዳለው ሕዋስ መፈጠር መቻል ከሰው ልጅ አምራች መሆን ታሪክ ተነጥሎ የማይታይ መሆኑን እንረዳለን ። በቁሳዊም ሆነ በኅሊናዊ መልክ የሚገኙ የባህል ክፍሎች የሰው የምርት ተግባር ውጤት ናቸውና በአንድ በኩል ባህል ከኅብረተሰብ የተገነጠለ ሕይወት እንደሌለው ሁሉ በሌላ በኩል ግን ስለኅብረተሰብ ዕድገትና እንቅስቃሴ የሚደረግ ጥናት ከባህል ጥናት ጋር ያለውን ዝምድና ለመመልከት እንችላለን ።

ሰው በቀጥተኛ መንገድ ለሕልውናው እንዲረዱት የሚያመርታቸውና የሚጠቀምባቸው ወይም እንኝህኑ ነገሮች ለማምረት ሲል የሚጠቀምባቸው ሆነው አካላዊ ህልውና ያላቸው ወይም ማቴሪያላዊ የሆኑ ነገሮች በሙሉ የሰው ማቴሪያላዊ ባህሎች ናቸው ። የእነዚህ ነገሮች አመራረት ፤ ስርጭትና ፍጆታ እንዲሁም የተመረቱት ነገሮች የሚኖራቸው ባህርይና ዓላማ እንደ ህብረተሰቡ የእድገት ደረጃና በዚያም ወቅት እንዳለው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ዓይነት የተለያየ ይሆናል ።

Digitized by Google

በጥንታዊ ጋርዮሽ ስርዓት ውስጥ የሰው
ፍላጐት ብዛትና ዓይነት በርካታና ውስብ
ስብ ባለመሆኑ የሚያመርታቸውም ነገሮች
እንዲሁ በርካታና ውስብስብ አልነበሩም ።
ለማምረት የተገለገለባቸው ማቴሪያላዊ ነገ
ሮች እንዲሁ ቅርጻቸውን ብቻ በመለወጥ
የሚገለገልባቸው ሹል ድንጋዮች ፤ እንጨ
ቶች . . . ወዘተ ነበሩ ። በባርያው ፤ በፊው
ዳሉና በካፒታሊስቱ ስርዓቶችም የተገኙት
ማቴሪያላዊ ፤ ውጤቶች የተሻሉ ፤ በርካታና
በዓይነትና በደረጃቸውም ከፍተኛ ነበሩ ።
ምክንያቱም እያንዳንዱ ትውልድ ማቴሪ
ያላዊ ነገሮች ከቀደምቱ ትውልድ የሚቀበ
ላቸውና የሚያሻሽላቸው በላያቸውም የሚ
ጨምርባቸውና ለአዲሱ ሁኔታ በሚያመች
መንገድ የሚያደራጃቸው ስለሆኑ ነው ።

ተግባር በሚባልበት ወቅት በምርት
ማለትም በሥራ ፤ ማኅበራዊ ስርዓትን ለመ
ቀየር የሚደረግን የፖለቲካና የኢኮኖሚ
ትግልንና በምርምርና ጥናት መስኩች በሙ
ሉ የሚደረጉትን ፣ እንቅስቃሴዎች የሚያቅፍ
እንደመሆኑ ፤ እነዚህን የተጠቀሱትን ማከ
ናወንና በዚህም እንቅስቃሴ ውስጥ የሚፈ
ጠሩ ማቴሪያላዊ ነገሮች በየትኛውም ኅብረ
ተሰብ ይሆን በማንኛውም የእድገት ደረጃ
የሰው ልጅ ማቴሪያላዊ ባህል እድገቶች
ናቸው ። ከዚህ አንጻር ሲታይ ማቴሪያላዊ
ባህል በማያቋርጥ እድገት ሂደት ውስጥ የሚ
ገኝ እንደመሆኑ ተራማጅ ነው ። ይሁን
እንጂ የማቴሪያላዊ ባህል የተራማጅነት
ባህርይ ከምን የተነሳ እንደሆነ ስለማቴርያ
ላዊና ሕሊናዊ ባህሎች ልዩነት ዝቅ ብለን
በምናነሳበት ወቅት በሰፊው ለማየት እንሞ
ክራለን ።

በኅብረተሰብ የእድገት ግስጋሴ ውስጥ
የሰው ልጅ በሕሊናዊ የሕይወት መስኩም
ቢሆን እንዲሁ እድገትን እያሳየ መጥቷል ።
ሰዎች በተግባር ላይ ሲሰማሩ ግንኙነት
የሚፈጥሩት በማምረቻ መሣሪያዎች አማ
ካኝነት ከተፈጥሮ ጋር ብቻ ሳይሆን በማም
ረቱ ፣ በልውውጡና በፍጆታውም መስኮች
ጭምር በመሆኑ በመሀከላቸው የምርትና
ሌሎችም ግንኙነቶችን ይፈጥራሉ ። ከዚ
ህም የተነሳ ምንም ያህል የተለያዩና በቅን
ብራቸው ደረጃ ከፍና ዝቅ ያሉ ቢሆንም
ስለ አካባቢያቸው ተፈጥሮና ስለ ኅብረተሰብ
የተወሰኑ አመለካከቶች ይኖራቸዋል ። ኅብ
ረተሰብንና ተፈጥሮን የሚገነዘቡት የሚተ
ነትኑበትና የሚረዱበት አመለካከት ፣ ከተ
ግባርም በቀጥተኛ መንገድ የሚያገኙት
እውቀት ፣ ልምድና ችሎታ አላቸው ።
በነዚህም አማካኝነት ማኅበራዊ ሕይወታ
ቸውን ሀዘንና ደስታን ፣ ጋብቻን ፣ የእለት
በእለት ኑሮአቸውን ፣ ተፈጥሮን ወዘተ
የሚገልጹባቸው መንገዶችና ዘዴዎች አሏ
ቸው ።

ስብስብ ባለ መንገድ ከላይ የተጠቀሱ
ትን ብናስቀምጣቸው በፍልስፍና ፣ በኪ
ነት ፣ በርዕዮተ-ዓለም ፣ በእውቀት ፣ በሳይ
ንስ ፣ በማኅበራዊ ሥነ-ልቦና ወዘተ ሊጠቃ
ለሉ የሚችሉ የሕሊናዊ ሕይወት የእድገት
መስኮች አሏቸው ። በማኅበራዊ ምርት
ተግባር ላይ የተሰማሩ እንደመሆናቸው
በዚህ ላይ የሚመሠረቱና በነርሱም የሚ
ወሰኑ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና እድገትን
ይፈጥራሉ ። የተለያዩት የማኅበራዊ ንቃተ
ሕሊና መስኮች የሚኖራቸው ማኅበራዊ
ሚና የተለያየ ቢሆንም ሁሉም ግን በወቅቱ
የሚገኘውን የሰዎች ማኅበራዊ ሕሊና ያን
ፀባርቃሉ ። በመሆኑም ማቴሪያላዊ የሆኑት
የምርት ኃይሎች በሚያሳዩት እድገት የተ
ነሳ ከማኅበራዊ ሥርዓቱ ጋር የምርት ግንኙ
ነቶች የሚለወጡ ናቸውና የሰውም ሕሊ
ናዊ ሕይወት ባህርዩና ዓይነቱ አብሮ ይለ
ወጣል ። ይሁን እንጂ የሕሊናዊ ባህሎች
የሚያሳዩት ለውጥና ፍጥነት እንደ ማቴሪ
ያላዊ ባህሎች አይደለም ። ሕሊናዊ ባህሎች
በማቴሪያላዊ ባህሎች ላይ ቢመሠረቱምና
በነርሱ ቢወሰኑም ዘግይተው የሚለወጡ
በመሆኑ አንፃራዊ ነፃነት እንዳላቸው ለመ
ገንዘብ ይቻላል ።

ከላይ ለማሳየት የሞከርነው ባህል ማኅ
በራዊ እንደሆነ ፣ ማቴሪያላዊና ሕሊናዊ
ተብለው በተለምዶ ሊከፈሉ የሚችሉ ሁለት
ክፍሎች እንዳሉት ነው ። አቀራረቡ ዘር
ዘር ባለ መንገድ ባለመሆኑ ባህል የሚባ
ለው ጽንሰ ሃሳብ ምን ባህርያት እንዳሉት
ለማየት አመቺ አልነበረም ። ከዚህ በመቀ
ጠል ደግሞ ትንታኔውን መሠረታዊ በሆኑ
የባህል ባህርያት ላይ በመገንባት ለማቅረብ
እንሞክራለን ።

ከሁሉም በፊት በባህል ውስጥ ሊጠቃ
ለሉ የሚችሉ ክስተቶች በሙሉ የሰው
ተግባር ውጤቶች እንደሆኑ እንረዳለን ።
ባህልን ለመተርጐም በሰጠነው ትንታኔ ላይ

እንደለተመከተው ባህል የሰው ልጅ ተግባር በተፈጥሮ መልካቸው ከሚገኙ ነገሮች ተለይተው የራሳቸውን ሕልውና ጠብቀው መገኘት ከጀመሩበት ወቅት አንስቶ የተፈጠሩ ነገሮችን የሚጠቁም ነው ። እንስሳትን የሰው ልጅ አጥምዶ ፣ ገርቶና አልምዶ በማራባት ፣ ሜካውን መንጥሮ ኵረብታውን ንዶ የእርሻ መሬትን በማዘጋጀት ፣ ቤትን በመሥራት ፣ ለአካሉ መሸፈኛ ልብስን በመሥራት ፣ መጓጓዣን ፣ ወፍጮን ፣ ድልድዮችን ፣ ፋብሪካና ኢንዱስትሪዎችን ፈጠረ ። እነኝህን በሙሉ ስንመለከታቸው የሰው ተግባር ውጤቶች እንደሆኑ ግልፅ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህም በመሆኑ የሰው ተግባር ውጤቶች ከተፈጥሮ ክስተቶች እንዲለዩ በማድረግ ተግባር ክስተቶችን በሁለት እንደከፈላቸው እንረዳለን ።

ተግባር ማንኛውንም ነገር በሁለት ክፍሎች እንዲከፈል አደረገ ፤ ይኸውም ማኅበራዊ ክስተቶችና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ። በመሆኑም ባሕል የሚለውን ፅንስ ሃሳብ ኅብረተሰብ ከሚለው ፅንስ ሀሳብ ጋር በተመሳሳይነት እንድንጠቀምበት ወይም እንድንተረጉመውና የሰው ሕልውና አበይት ባሕርዩ ባሕል አድርገን እንድንገነዘብ መሠረት ይሰጣል [3]

በኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ክስተቶች ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ በመሆናቸው የኅብረተሰብ እድገት የማኅበራዊ ክስተቶችን እድገት ያስከትላል ማለት ነው ። የሰው አምራች መሆንና የኅብረተሰብ አመሠራረት በጣምራ የተከናወኑ እንደመሆኑ ባህል ከሰው ልጅ ስልጣኔ ጋር አብሮ ለብዙ ጊዜ የቆዩ ወይም ባህል ከስልጣኔ ጋር አንድ ባይሆንም ተመሳሳይ እንደሆነ እንመለከታለን ።

ኅብረተሰብ ራሱ ሰውን እንደሰው የሚፈጥረውን ያህል ፤ ኅብረተሰብም የሰው ተግባር ውጤት ነው ። ተግባርና የርሱንም ውጤት አጠቃቀም በይዘታቸውና በሕልውናቸው ስልት ሁለቱም ማኅበራዊ ናቸው ። [4]

ይህ ጥቅስ የሚያሳየን ኅብረተሰብ እንኳን ሳይቀር የተግባር ውጤት እንደሆነና የተፈጥሮ ሰባዊ ገጽታ ማለትም ኅብረተሰብ የሚኖረው ለሰው ብቻ እንደሆነ ነው ። ተፈጥሮ እንዳለ በሰው ተግባር እስካልተለወጠ ድረስ ኅብረተሰብ በሚለው መጠሪያ ውስጥ ሊጠቃለል አይችልም ።

በባህል ውስጥ የሚጠቃለሉ ነገሮች በሙሉ ተፈጥሮአዊ ምክንያት ያላቸው ውጤቶች አይደሉም ። በተግባር አማካኝነት የተፈጥሮ መልካቸውን በመቀየር የሰው ፍላጐትን ለማርካት በሚያስችል ሁኔታ የሚገኙ ነገሮች አሉ ። እነዚህምበዚህተግባር ሂደት ውስጥ ሰው የተፈጥሮ አካል በመሆኑ ሊያገኛቸው የማይችል ነገር ግን በተግባር ውስጥ ፈጥሮ የሚገለገልባቸው ነገሮች ናቸው ። ስለ ዓለም የሚያገኘው እውቀት ፣ ስለ ማኅበራዊ ሕይወቱ የሚያከማቸው ግንዛቤ ፣ በምርምር የሚያገኘው ልምዱ በጠቅላላው አመለካከቱ ስሜቱ ሁሉም ለሰው ከውጭ የሚሰጡት ወይም የሥነ ሕይወታዊ እድገቱ ውጤት አይደሉም ።

ባህል ከሰው ተገንጥሎ ወይም ከኅብረተሰብ ውጭ የራሱን ሕልውና በመጠበቅ ሊኖር የሚችል ክስተት አይደለም ። ማኅበራዊ ክስተት ነው ፣ ከሰዎች ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ጋር ተዛምዶና ውጤትም ሆኖ በኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ይሁን እንጂ ባህል አንድ ጊዜ ከተፈጠረ በኋላ የራሱ የሆነን የእድገት ሕግጋት ተከትሎ የሚሄድ ክስተት ነው ። ሕልውናውን ጠብቆ የሚገኝ እንጂ የአስተሳሰቦችን ይዘት በመሆን ብቻ የሚገኝ አይደለም ።

ባህል የራሱን ሕልውናና የእድገት ሕግጋት ጠብቆ የሚያድግ ከሆነ ደግሞ ነባራዊ ነው ማለት ነው ። የባህል ነባራዊነቱ ነባራዊ ከሆኑት የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ቢያመሳስለውም ባህል በነባራዊነቱ ብቻ የሚኖር ሳይሆን እንደ ማኅበራዊነቱም ከሰው ወይም ከኅብረተሰብ ጋር ብቻ ተቆራኝቶ የሚገኝ ነው ። ነባራዊ የተፈጥሮ ክስተቶች ለሕልውናቸው የሰውን መኖር የማይጠይቁ ወይም የግድ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም። እንዲያውም የተፈጥሮ ክስተቶች ከሰው በፊት የነበሩና ያሉ ከሰውም በኋላ ሊኖሩም የሚችሉ ናቸው ። ባህል ግን የዚህ ዓይነቱ ክስተት አይደለም ።

የተፈጥሮ ክስተቶች ጭፍንና ከፍተኛ ለውጥ ሳያሳዩ እንዳሉ የሚደጋገሙ ሲሆን ባህል ግን የሰዎች ዓላማና የፈጠራ ችሎታ እንቅስቃሴ ውጤት ነው ። ባህል ሳይለዋ

Digitized by Google

ወጥ እንዳለ የሚያደጋግም ሳይሆን እየተሻ
ሻለና እያደገ የሚሄድ ክስተት ነው ።

ባሕሎች በማያቋርጥ ለውጥ ላይ የሚገኙ
እንጂ ሳይለወጡ (እስታቲክ) ሆነው የሚገኙ
አይደሉም ። 5

የባህል መለወጥ ምክንያቶች በርካታ
ናቸው ። በአንድ በኩል በአንድ ኅብረተ
ሰብ ውስጥ በተለያዩ መስኮች የሚደረግ
ለውጥ በሌላ በኩልም ደግሞ የማኅበራዊ
ሥርዓቱ ለውጥ ሲሆን ይህም ባህሉን እን
ዲለውጥ ብቻ ሳይሆን እንዳያድግም ያደር
ገዋል ።

ያለንበት ዘመን ሳይንስና ቴክኖሎጂ
በጣም ያደገበትና የተስፋፋበት ዘመን ነው።
በአንድ አገር ውስጥ የሚፈጠር አዲስ ነገር
የሚያስከትለው ውጤት በአንድ አገር ክልል
ውስጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመላው
ዓለም ውስጥ ለውጥ የሚፈጥር ወይም በተ
መሳሳይ መስኮች ነገር ግን በበርካታ አገ
ሮች ውስጥ መሻሻሎች እንዲደረግ ተጽ
እኖን የሚያሳድር ነው ። በአገሮች መሀከል
የንግድ ፣ የጉብኝዎች ፣ የሳይንስና የባህል
ልውውጥ ስለሚካሄድ በነዚህና በተመሳ
ሳይ ምክንያቶች የአንድ አገር ባህልም
ሊሸጋገር ይችላል ።

ሌላው በባሕል ውስጥ የሚጠቃለሉ ክስ
ተቶች ባሕርይ የሰው ልጅ ዓለምን የመገን
ዘብና የተፈጥሮ ኃይሎችን ለርሱ በሚጠ
ቅመው መንገድ እየለወጠ በቁጥጥሩ ሥር
ለማስገባት የሚያስችል መሆኑ ነው ።
የቴክኖሎጂና የሳይንስ ውጤት ዓላማ
ተፈጥሮን ለመግራት ማስቻል ነው ።
የኅብረተሰብን እድገት ሕግጋት በመረዳት
የኅብረተሰብን እድገት ጠቃሚ በሆነ መን
ገድ በመቀየር ለማደራጀት ማስቻል ነው ።

ሰው ዓለምን ለመለወጥ ያለው ችሎታ
አምርቶ በሚገለገልባቸው የሥራ ቁሳቁሶች
ጥራትና ብዛት እንዲሁም በዚህ ሂደት
ውስጥ በሚያጠራቅመው ሳይንሳዊ እውቀት
ላይ ይመሠረታል ። እነዚህ የተጠቀሱት
ደግሞ የሰው ልጅ ማቴሪያላዊና ሂሊናዊ
ባሕሎች ናቸው ። በነዚህም መስክ የሰው
ልጅ የሚያሳየው እድገት የባሕሉ እድገት
ይሆናል ።

ባሕል የሰውን ልጅ ምንነት (ኤስንስ)
ሳይለውጥ ነገር ግን በዓለም ውስጥ የሚጫ
ወተውን ሚና ከፍ የሚያደርግ ክስተት
ነው ። ከጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት አንስተን
እስከ አሁን ድረስ በማናቸውም የማኅበራዊ
ሕይወት መስክ የሰው ልጅ ከፍተኛ እድገት
እንዳሳየና ከጊዜ ወደጊዜ ስለተፈጥሮ ምን
ነት ሳይንሳዊ እውቀት እያገኘ በመምጣት
ይበልጥ ተፈጥሮን እንደገራ እናያለን ።
በዚህ ሂደት ውስጥ ግን የሰው ምንነት
ለውጥ አላሳየም ። እንቅስቃሴውም በመ
ሬት ውስጥ ተወስኖ የቀረ እንቅስቃሴ ብቻ
ሳይሆን ወደ ህዋውና ሌሎች አካሎች ድረስ
ሄዷል ።

ባሕል ሰው ተፈጥሮ የሰጠችውን አካ
ላዊ ችሎታዎች የተወሰነ አወቃቀርና የአ
ሠራር ስርዓት ባላቸው ነገሮች የሚተካ
ነው ። ለባሕል ሌላ ትርጉም ብንሰጥ እን
ዲህ ብለን ለመተርጐም እንችላለን ።
ባሕል ማለት ማናቸውም የሰውን ተፈጥ
ሮአዊ አካል የተወሰነ አወቃቀርና የአሠራር
ስርዓት ባለው ነገር ወይም መንገድ የሚ
ተካ ነው ። በዚህ ዓይነት መንገድ ባህልን
መተርጐም ባሕልን ማቴሪያላዊና ሕሊናዊ
ባሕል ብሎ ከመክፈል ችግር ያድነናል ።

ከላይ ከተጠቀሰው የባሕል ትርጉም
ስንነሳ ባሕል የተፈጥሮንና የሰውን ኃይል
በመለወጥ ልዩ ባሕርይ የሚሰጥና ተፈጥሮ
አዊ በሆነ መንገድ ሊገኙ የማይችሉ ነገሮ
ችን ለማገኘት የሚችል ክስተት ነው ።
ሳይንስን በምሳሌነት ብንወስድ የሰውን
የአእምሮ ችሎታ በማዳበር በመሬት ውስጥ
ያሉትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ከመሬት በብዙ
ሺህ ወይም ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ርቀው
የሚገኙ ነገሮችን እንዲያውቅና እንዲዳስስ ፣
በዓይኑ ብቻ ለማየት የማይችለውን ጥቃ
ቅን ነገሮች አጉልቶ ለማየት እንዲችል ፣
በእጆቹ ብቻ ለማንሳት ወይም ለማንቀሳ
ቀስ የማይችለውን ለማንሳትና ለማንቀ
ሳቀስ እንዲችል ወዘተ ያስችላል ። ረጅም
ጊዜና ከፍተኛ ጉልበት የሚጠይቁትን ጉዞ
ዎችና ነገሮች በአጭር ጊዜና በትንሽ ጉል
በት እንዲያከናውን ያስችላል ። ተፈጥሮ
አዊ አካሎች በመሆናቸው ለማከናወን የማ
ንችላቸውን ነገሮች የባሕል አካሎች (ካል
ቾራል ቢንግ) በመሆናችን እንድናከናውን
ያደርገናል ።

Digitized by Google

የሰው ተግባር ውጤት በመሆን ባህል ብለን የምንጠራቸው ነገሮች የተፈጥሮ ሂደቶች የማይሰጡትን ችሎታ ለሰው በማበርከት የሰውን ሕይወትና አስተሳሰብ ሥርዓት እንዲይዙ ያደርጉለታል ። አንድ የአልጀብራ የእኩልነት አረፍተ ነገር በርካታ ሁኔታዎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ በማናቸውም ሁኔታ ትክክል የሆነን ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የአስተሳሰብ ሥርዓት ነው ። በልዩ ልዩዎቹ የተፈጥሮ ሳይንሶች ውስጥ የሚገኙ ሕግጋትና መርሆዎችምእንዲሁ የባህል ክስተቶች የሰውን ኃይል የሚያጉላሉና የሚተኩ ናቸው ቢባልም ፣ የሰውን ተፈጥሮ አካሎች ዋጋ ቢስ ያደርጋሉ ማለት ግን አይደለም። ሥራውን ያቃልላሉ ከዚህም የተነሳ ለምርምርና ለእረፍት የሚፈለግን ጊዜ ያራዝማሉ ። ስለሆነም ሰውን ይጠቅማሉ እንጂ ሰውን እንዲተኩ ይሆናሉ ወይም ለመተካት ይችላሉ ማለት አይደለም ።

የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሰውን አካላዊና አእምሮአዊ ተግባር ቢተኩም ፣የነርሱም የሥራ መስክ ምንም ያህል እየሰፋ ቢሄድም የሰው አገልጋይነታቸውን ወይም የባህል ክስተትነታቸውን ባህርይ አይለውጠውም ። ሁሉም የሰው ሥራ ውጤቶች ናቸው ። ሰው ማኅበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ከዚህም የተነሳ የሚያመዛዝን ነው ። በባህል ውስጥ የሚታቀፉ ነገሮች ትዕዛዝ ተቀባዮች እንጂ ማኅበራዊ ኃላፊነት የሚሰማቸውና የሚያመዛዝኑ አይደሉም ።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የነዚህ ሁለት ክፍሎች ተመሳሳይነትና ልዩነት ምን እንደሆነ ለማየት እምክራለን ።

ፋብሪካዎች ፣ ኢንዱስትሪዎች ፣ ድልድዮች ፣ ቤቶች ፣ ልብስ ፣ የማምረቻ መሣሪያዎች ፣ ወዘተ በሕላዊ ባህሎች ውስጥ ሊጠቃለሉ አይችሉም ። በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጥሮ ስጦታዎችም አይደሉም ። ነገር ግን ከሰው ልጅ ማቴሪያላዊ ባህል ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው ።

ኪነት ፣ ፍልስፍና ፣ ርዕዮተ-ዓለም ፣ ትምህርት ፣ ሥነ ምግባርን ፣ ፖለቲካን ፣ ሕግን... ወዘተ እነዚህን ስንመለከት ደግሞ ልክ እንደ ማቴሪያላዊ ባህሎች የተፈጥሮ ስጦታዎች አይደሉም ። በሌላ በኩልም በሰው ልጅ ማቴሪያላዊ ባህል ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ አይደሉም ። ሕሊናዊ ባህሎች በተለያዩ መንገዶች ቅርጻቸውን ቀይረው ነባራዊ ሕልውና ሊያገኙ ቢችሉም ፣ የሕሊናዊ ባህሎች መሠረታዊ ባህርይ ቃሉ እንደሚያመለክተው የሕሊና ክስተቶች መሆን ነው። የወቅቱን የሰዎች ማኅበራዊ ህልውና በማንፀባረቅ የሚገኙ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና መልኮች ናቸው ።

ማቴሪያላዊና ሕሊናዊ ባህሎች ተፈጥሮአዊ ምክንያት የሌላቸው ውጤቶችና የሰውን አካላዊና አዕምሮአዊ ችሎታ በማጉላት ሰው ተፈጥሮን እንዲቆጣጠር የሚያስችሉ በመሆናቸው ተመሳሳይ ናቸው ።

ሁለቱም ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ ወይም ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ሊተላለፉ የሚችሉ በመሆናቸው ማኅበራዊ ቅርሶች ፡ የማያቋርጥ ዕድገት ላይ ያሉና በተለይም ሕሊናዊ ባህል አንፃራዊ ነፃነት ያለው በመሆኑም ተመሳሳይ ናቸው ።

ሁለቱም ማኅበራዊ ክስተቶች እንደመሆናቸው ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ወይም ከአንድ አገር ወደ ሌላው የሚተላለፉ ብቻ ሳይሆን ሽግግራቸው የሚከናወነው ማኅበራዊ በሆነ መንገድ ነው ።

የባህል ማኅበራዊ ቅርሥነት የሚመነጨው ሥነ ሕይወታዊ በሆነ መንገድ የሚተላለፍ በመሆኑ ሳትይሆን ሰዎች እየተማሩ የሚያስተላልፉ በመሆኑ ነው ። [6]

በደመ ነፍስ ናሥነ-ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ከአባት ወይም ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፉ አይደሉም ።

«--- ባህል ከሥነ ሕይወታዊ ነገሮች የሽግግር ዘዴ ውጭ የሚገኝ ነው በምንልበት ጊዜ ሽግግሩ የሚከናወነው በማኅበራዊ መንገድ መሆኑን ለመጠቆም ሲሆን ኤክስትራ-ስማቲክ ነው ፡ የምንለው ደግሞ ከማንኛውም ሰው ውጭ የሚገኝና እንዲያውም መልሶ በርሱ ላይ እንደሌሎች የህዋ አካሎች ተጽዕኖ የሚያደርግበት በመሆኑ ነው ።»[7] ይህ ጥቅስ ባህል እንዴት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚሸጋገር ከመጥቀሱ አልፎ እራሱም ባህል በተለይም ማቴሪያላዊ ባህል ነባራዊ ህልውና እንዳለው የሚያሳይ ነው ። ለባህል ህልውና የትኛውም የሰው ሥነ-ሕይወታዊ ክፍል እንደማያስፈልገው ወይም

Digitized by Google

የሰው ሥነ-ሕይወታዊ አካሎች ባህልን ለማቆየት ወይም ለማሸጋገር ያላቸው ሚና ይበልጥ እያየለ በመሄድ ላይ እንዳለ የሚመለከት ነው ።

የሰው አካሎች የባህል ክፍሎች በተለይም የማቴሪያላዊ ባህል ክፍሎች አይደሉም ።

«እጅ የሥራ ማከናወኛ አካሎችን ብቻ ሳይሆን የሥራም ውጤት ነው ።»[8] እጃችን የሥራ ውጤት ቢሆንም እንደማንኛውም የሥራ ውጤት ሆነው እንደሚገኙ ነገሮች በባህል ውስጥ የሚጠቃለል አይደለም ። ምክንያቱም በመጀመሪያ ባህል ከኅብረተሰቡ ተገንጥሎ ሊታይ ባይችልም አንድ ጊዜ ህልውና ካገኘ የራሱን የዕድገት ሕግጋት ተከትሎ የሚኖር ሲሆን ከዚህ አንፃር እጅ ሲታይ የዚህ ዓይነት ባህሪይ የለውም ።

ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው ማኅበራዊ በሆነ መንገድና አንድ ጊዜም ከተፈጠረ ለህልውና የሰውን አካል የማይፈልግ ሲሆን እጅ ግን ከሰው ጠቅላላ ሥነ ሕይወታዊ አካል ተገንጥሎ ሊገኝ የማይችል ነው ። ይህ የተጠቀሰው ትንታኔ እጅን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ማንኛውንም የሰው ስነ ህይወታዊ አካሎች የሚመለከት ነው ። ከዚህም የተነሳ ሰው ራሱን በሥራ አማካኝነት ቢፈጥርም ራሱ ግን ባህል አይደለም ። ይህ ቢባልም በባህል አማካኝነት ካልቸራል (ቢንግ) ሊሆን አይችልም ማለት ግን አይደለም ። ምክንያቱም የተፈጥሮ አካል ወይም ፍጡር በመሆኑ ሊያከናውነው የማይችለውን ተግባር በፈጠራቸው ነገሮችና ባጠራቀመው ዕውቀት አማካኝነት ግን ሊያከናውን ይችላልና ፣ ነው ።

ሕሊናዊ ባህል ፡

ሕሊናዊ ባህል የምንላቸው የሰዎች ሕሊናዊ እንቅስቃሴ ውጤቶችን ማለትም ሳይንስን ፣ ማኅበራዊ ሥነ ልቦናን ርዕዮተ ዓለምን ፣ ኪነትን ፣ ሥነ ምግባርን ፣ ሕግን ወዘተ... እንዲሁም በነዚህ መስኮች የሚደረጉትን አመራረት ፣ ሥርጭትና ፍጆታን የሚያጠቃልል ነው ። ሕሊናዊ ባህል የተጠቀሱት የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና መስኮች ከንዋኔ የሚፈጽሙበትንና የሚገልጹበትን ተቋሞች ፣ ት/ቤቶች ፣ ቤተ መጽሐፍቶችና የምርምር ማዕከሎች ፣ ትያትር ቤቶች ፣ መንግሥት ፣ ሙዚየሞች...ወዘተ የሚያቅፍ ነው ።

ሕሊናዊ ባህል የአንድ የተወሰነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን ባህርያት ምልክቶችን ያቀፈ ፣ የፈጠሩትን መደቦች ጥቅም የሚያንፀባርቅና ከዚህም የተነሳ ሥርዓቱን ለማጠናከርና ሳይለወጥ እንዳለ እንዲቆይ ከሚያገለግለው የላዕላይ መዋቅር ጋር ግንኙነት አለው ። እንደሚታወቀው ሁሉ በማንኛውም ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ ላዕላይ መዋቅር ተገንብቶበት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የማንፀባረቅና የማጠናከር ገቢርን ያከናውናል ። ስለሆነም ልዩ ልዩዎቹ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና መልኮች የመደብ ባህሪይ ያላቸው በመሆኑ ከሚገለገሉባቸው ተቋሞችና ድርጅቶች ጋር አንድ ላይ የላዕላይ መዋቅር አካሎች ሆነው ይገኛሉ ።

ይሁን እንጂ የሕሊናዊ ባህል ከላዕላይ መዋቅር ጋር ግንኙነት ቢኖረውም ከላዕላይ መዋቅር ጋር አንድ አይሆንም ። ምክንያቱም ላዕላይ መዋቅር የሕሊናዊ ባህል ክስተት የሆኑ ነገር ግን የመደብ ጠባይ የሌላቸውን ክስተቶች ስለሚያቅፍ ነው፡። የሕሊናዊ ባህል ክስተት ሆነው ነገር ግን የመደብ ጥቅምን ባለማንፀባረቃቸው የተነሳ የመደብ ባህርይ የላቸውም ከሚባሉት ለምሳሌ የተፈጥሮ ሳይንሶችና ዕውቀቶች ጥቂቶቹ ናቸው ።

በኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ባህሪያት ያላቸው ማኅበራዊ ክስተቶች ይገኛሉ ። ከነዚህም ውስጥ ባህል አንዱ ነው ። አንዳንዶቹ ማኅበራዊ ክስተቶች በመሠረቱ የመደብ ጠባይ ያላቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በባህሪያቸው የመደብ ጠባይ የሌላቸው ናቸው ። ታዲያ ከነዚህ አንፃር ሲታይ ባህል ምን ዓይነት ጠባይ አለው?

- - - ሁለተኛው የማኅበራዊ ክስተቶች ክፍል ደግሞ የማንኛውም የማኅበራዊ ሥርዓት

Digitized by Google

መዋቅራዊ ክፍሎች ሆነው የሚገኙ ነገር ግን በተፃራሪ መደቦች በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ብቻ የመደብ ባሕሪይ ያላቸው ክስተቶች ናቸው ። ከነዚህም ውስጥ የምርት ግንኙነቶች ፣ ሥነ-ምግባር ፣ ርዕዮተ ዓለም ኪነት ወዘተ-- ይገኙበታል ። ስለነዚህ ዓይነቶች የማኅበራዊ ክስተቶች የሚደረግን የመደብ ትንታኔ በሚመለከት ማጤን የሚገባን የመደብ ጠባያቸውንና የመደቡ ትግል የኅብረተሰብ መዋቅራዊ ክፍሉ ተጠባጭ የታሪክ መግለጫ መልካቸውን እንጂ ሙሉ በሙሉ እንደሚያጠፋቸው ነው ።[9]

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ባህል እንደ ማኅበራዊ ክስተትነቱ ሁልጊዜ የመደብ ባህሪይ ያለው አለመሆኑ ነው ። ባህል በቅድመ መደብ ፣ በመደብና በመደብ አልባ ሥርዓቶች ውስጥ የሚገኝእንደመሆኑ በመደብ ሥርዓቶች ውስጥ ብቻ የመደብ ጠባይ የሚኖረው ነው ። ስለሆነም በመደብ ሥርዓቶች ውስጥ በተለይም ሕሊናዊ ባህል በመደቦች መሀከል ያለን ቅራኔ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ የባህል ርዕዮተዓለማዊ ይዘት የመደብ ባህሪይ እንዲኖረው ያደርገዋል ። በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶች ውስጥ ባንድም ሥርዓት እንኳን ቢሆን በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና ልዩ ልዩ የተግባር መስኮች መኖር የተነሳ ባህል በመደቦች እንዲሁም በማኅበራዊ ቡድኖች መሀከል ያለውን ትግልና የትግል ታሪክ የሚያንፀባርቅ ነው ።

ከላይ በሰፈረው ጥቅስ ውስጥ እንደተጠቀሰው ባህል ከመደቦች ጋር ሳይሆን ከአንዳንድ ቡድኖች ጋር ያለው ግንኙነት የተለየ ጠባይ እንዲኖረው ያደርገዋል ።

ባሕል ከተወሰነ የታሪክ ማኅበረሰብ (ጐሣ ፣ ነገድ ፣ ሕዝብ ፣ ብሔር) ፣ ያለው ግንኙነት ልዩ ቅርፅ እንዲኖረው ሲያደርግ ከተወሰነ ማኅበራዊ ሥርዓት ጋር ወይም የመደብ ጥቅም ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ ባሕልን የርዕዮተዓለማዊ ይዘት እንዲኖረው ያደርጋል ።[10]

የዚህም ምክንያት የኅብረተሰብ ሕሊናዊ ባህል በማቴሪያላዊ ምርት ላይ የሚመሠረትና በርሱም የሚወሰን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በኅብረተሰብ ውስጥ የሚካሄደውን የማቴሪያላዊ ምርት ተግባር በወቅቱ ምን መልክ ይዞ እንደሚገኝ ካላወቅን ከማቴሪያላዊው የምርት ተግባር ጋር ተዛምዶ የሚገኘውን የሕሊና ቅርፅና እርሱም መልሶ በማቴሪያላዊ ምርት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለማወቅም ስለማንችል ነው ።

ማቴሪያላዊ ምርት (ራሱ) ያለውን ልዩ ታሪካዊ ቅርፅ ምን እንደሆነ ጠንቀቀን ካላጤንን ከርሱ ጋር ተያይዞ ሆና በሚገኘው ኅሊናዊ ምርት ዘርፍ ያለውን ልዩ ባሕሪይ ለማወቀም ሆነ ለንዱ በሌላኛው ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕና ለመረዳት ለንችልም ።[11]

ስለሆነም በጣም ባልዳበረ የምርት ግንኙነት ላይ ተዋቅሮ በነበረው የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ማለትም የሰዎች ሕሊናዊ ባህል በወቅቱ በዚያው ደረጃና መጠን ያልዳበረና ጨቅላ ሆኖ እናገኘዋለን ። በማኅበራዊ ሕይወት መሀከል ምጐጣ ወይም ነገድ ስለነበረ እያንዳንዱ ሰው የማሰብ ግዴታ ስላልነበረበት ሰዎች የተለያየ ሕሊና አልነበራቸውም ። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ የዓለም አመለካከት አልነበረውም ። ምክንያቱም -፣

እዚህ (ማለትም በጥንታዊ ጋርዮሽ ውስጥ (የራሱ) ለሳቢና ግብ ወሳኝ ጐሣው ነው ። እያንዳንዱ ሰው የማሰብ ግደታ የለበትም ምክንያቱም የሕይወት መለከሉ (ኤለመንት) ጐሣው ነው ። የሕይወቱ መለከሉ ደግሞ በግለሰቡ ላይ ግብታዊ በሆነ መንገድ ይሠራበታል ። ማለትም በደመነፍስ እንጂ ንቁና ግልፅ በሆነ መንገድ ለልነበረም ።[12]

ሕሊናዊ ባህል የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ፈርጅ እንደመሆኑ የዕድገት ደረጃው ኅብረተሰብ በደረሰበት የማቴሪያላዊ ምርትና የማቴሪያላዊ ባህል ዓይነትና ደረጃ የሚወሰን ይሆናል ።

ከዚህም የተነሳ ለመደቦች መፈጠር የሚያስፈልገው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መሟላት ፣ በዚህም ሂደት በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መፈጠር የተነሳ የሕሊናዊ ምርት በይዘቱና ቅርጹ ከፍተኛና ውስብስብ ከመሆን አልፎ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚያካሂዱት የከንዋኔ መስክ ሆኖ መጣ ። ከመንግሥት መፈጠር ጋር ሕጋዊና ፖለቲካዊ ንቃተ ሕሊና ፣ የተለያዩት መደቦች ንቃተ

Digitized by Google

ሕሊና በተለይም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የበላይነት ያለው መደብ በንቃተ ሕሊናው የበላይነት ያለው ሆኖ መጣ ።

---በሥራ ክፍፍልና የአዕምሮ ሥራ ከጉልበቱ ሥራ መገንጠል ንድፈ ሃሳባዊ ንቃተ ኅሊና (ፍልስፍና ፤ የተለያዩ ሳይንሶች) ብቅ አሉ ። የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ዕድገት በውስጡ ክፍፍሎችንና አንፃራዊ ነፃነት ያላቸውና በመደብ ሥርዓተ ማኅበሮች የሚያድጉ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ቅርጾች ፤ ፖለቲካ ፤ ሕግ ፤ ሥነ-ምግባራት ፤ ሃይማኖት ሳይንስ ፤ ኢስቴቲክስ ፤ ፍልስፍና ብቅ አሉ ።[13]

ቁም ነገሩ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና መልኮች ምን እንደሆኑ ለማመልከት ሳይሆን እራሳቸውም የሕሊናዊ ባህል ክፍሎች እንደመሆናቸው እንዴት እንደሚከሰቱና የአመሠራረታቸው መሠረትና ባህሪያቸው ምን መልክ እንዳለው ለማሳየት ነው ። ከተጠቀሱት ልዩ ልዩ ጥቅሶች ለመረዳት የሚቻለው የሰው ልጅ ሕሊናዊ ባህል የዕድገት ደረጃና የክፍፍል መሠረቱ ቁልፍ ፥ ባህሉ እንደሆነና እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የሕሊናዊ ባህል መልክ ፥ ባህሪይና ተግባሯን ለመረዳት የግድ በወቅቱ ሰፍና የሚገኘውን የማቴሪያላዊ ምርት ባህሪይን ማወቅ አማራጭ የሌለው መሆኑን ለመጠቆም ነው ።

የህሊናዊ ባህል እድገት ከሕብረተሰብ እድገት ጋር ተጣምሮ የሚያድግ ቢሆንም በውስጡ ግን ማኅበራዊ ሥነ ልቦናን ርዕዮተ ዓለምን ወዘተ የሚያቅፍ ነው ። የሕብረተሰብ ህሊናዊ የሕይወት መስክ ከሌሎች የማኅበራዊ የሕይወት መስኰች ጋር ግንኙነት ያለው ብቻ ሳይሆን አንድ እራሱን የቻለ የዕድገት መስክ በመሆኑ በጥሞና ሊጠና የሚገባው ነው ። ማኅበራዊ ስነ ልቦናና ርዕዮተዓለም በህሊናዊ ሕይወት መስክ ቢጠቃለሉም ሁለቱ የተለያዩ ናቸው ።

ማኅበራዊ ስነ ልቦና ሰዎች ከሚኖሩበት የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የውስጥ ሁኔታዎች ፤ ከዕለት በዕለት ኑሮዋቸውና ተግባራቸው ፥ ጥቅማቸው ፤ ፍላጐታቸው የዕለት በዕለት ኑሮዋቸውን የሚያንፀባርቁት የስሜታቸው ፤ የግምታቸው ፤ የአመለካከታቸውና የአስተሳሰባቸው አዝማሚያ ጠቅላላ ድምር ነው ። በመሆኑም ከጠባብ የሥራ ክፍፍላቸውና ልምዳቸው አጠራቅመው ከሚገኝ ችሎታ የማያልፍ ነው ። ሁለንተናዊ ይዘትና ንድፈ ሃሳባዊ መሠረት የሌለው ነው ። ስለሆነም ማኅበራዊ ስነ ልቦና የብዙሀን ንቃተህሊና ነው ። ይሁን እንጂ በመደብ በተከፋፈለ ሕብረተሰብ ውስጥ ማኅበራዊ ሥነ ልቦና የመደብ ባህሪይ አለው ። የወዝ አደሩ መደብ በካፒታሊስቱ ሕብረተሰብ ውስጥ የመረዳዳትና የወል ስሜት ያለው የማኅበራዊ ሥነ ልቦና ሲኖረው ከበርቴው ደግሞ የግለኝነት የማኅበራዊ ሥነ ልቦና አለው ።

ብሔሮችም ቢሆኑ የብሔራዊ ንቃተ ሀሊናቸውን ተፅዕኖ የሚያሳድሩበት የማኅበራዊ ሥነ ልቦና አላቸው ። አንድ ብሔር ከሌላ ብሔር የሚለየውና የብሔሩን ልምድ ፤ አስተሳሰብ ፤ ግምት ወዘተ የሚገልፅበት ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ይኖረዋል ፤ ይሁን እንጂ ፤

ብሔራዊ ንቃተ ኅሊና ከመደብ ንቃተ ኅሊና አንፃር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኛል ። የመጀመሪያ መልኩ እንኳን ከዕለት የኑሮ ሁኔታ ፤ የወል የመኖሪያ አካባቢና ሰዎች ከሚናገሩት የወል ቋንቋ ወዘተ - - - ተፅዕኖ ሥር ቅርፅ ይዘ ይገኛል ።[14]

ይህ ጥቅስ የሚያሳየው የመደብና የብሔራዊ ንቃተ ህሊናዎች የተለያዩ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ሁለት ተፃራሪ መደቦችን ባቀፈ ብሔር ውስጥ አንድ ዓይነት የመደብ ማኅበራዊ ንቃተ ህሊና ብቻ እንደማይገኝም ጭምር ነው ። አንድ ብሔር ህልውናው የሚከሰትበት ወይም የሚገለፅበት አንድ ብሔራዊ ንቃተ ህሊና ሳይኖረው ህልውናውን ለመገመት አስቸጋሪ የመሆኑን ያህል ፤ በውስጡም የሚገኙ መደቦች ሊኖራቸው በሚችለው የመደብ ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ላይም ብሔራዊ ንቃተ ህሊና ተጣምሮ እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ የመደቦቹን የማኅበራዊ ሥነ ልቦና ቅርጽ ያስይዘዋል ።

ስለሆነም ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ልዩ ዕውቀትን ወይም ከፍተኛ የሆነ የአስተሳሰብ ሥርዓትን የሚጠይቅ አይደለም ። ብሌላ በኩል ግን ርዕዮተዓለም ፤

ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ ከፍተኛ (ከማኅበራዊ ሥነ ልቦና አንፃር ሲታይ) የሆነ ማኅበራዊ

Digitized by Google

ሂደትን የምንረዳበት የመደብ ንቃተ ኅሊና ደረጃ ነው ። የርዕዮተዓለም መሠረታዊ መለዮ የሆነው የመደብ ጥቅምን ማወቂያ ፤ ጥቀል በሆነ መንገድ የሚገልጹትን የንድፈ ሃሳባዊ መልኮች ሥርዓት የሚያስይዝ ነው ።[15]

ቀደም ባለው ጥቅስ ስለማኅበራዊ ንቃተ ህሊና ቅርፅ ይዞ መምጣትና በዕድገቱ ውስጥ አንፃራዊ ነፃነት ያላቸው የማኅበራዊ ንቃተ ህሊና መልኰች መፈጠር ጋር ያለው ግንኙነት ተገልጿል ። ከፍተኛ የንድፈ ሀሳብና የመደብ ጥቅምን ትንታኔ የሚጠይቁ የማኅበራዊ ንቃተ ህሊና መልኰች ስርዓት የእለት ኑሮና ተግባር ከሚያመነጩት ዕውቀት ባሻገር ናቸው ።

የምሁራን (ኢንተሌክቹዋልስ) ምርት ሰቀፎት የሚገኘው መላውን የህሊና ምርት መስክ ሳይሆን ከሁሉም በፊት በመጀመሪያ ደረጃ በምሁራን የምርት መስክ ማለትም በሙያቸው የተሠማሩ የተወሰኑ ሰዎች እንቅስቃሴ ውጤትን ነው ። የነዚህ ሰዎች ክንውን በመሠረቱ መልክ ያለው ፣ ልዩ በሆኑ ማኅበራዊ ተቋሞችና ሥርዓት ተደራጅቶ የሚገኝ ነው ። ሁለተኛ የነዚህ ቡድኖች ክንዋኔ ውጤት የሆነው ንቃተ ህሊና ከሰዎች የዕለት ኑሮና ተግባራዊ ክንዋኔ ጋር ሳይገነጣጠል ከሚገኘው ንቃተ ኅሊና የሚለይበት ልዩ መልክ ያለው ነው ። ይህ ነው በማቴሪያላዊ ምርት ሂደት ውስጥ ግብታዊ-የብዙሀኑ የኅብረተሰብ አባላት ንቃተ ኅሊናና በተወሰኑ ምሁራኖች ንቃተ ኅሊና መሀከል ያለው ልዩነት - - ።[16]

አንድ ሕብረተሰብ ብዙሀን አባላት ከሚገኙበት የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ሁኔታዎች ፣ ከተግባራቸው ከዕለት ኑሯዋቸው የተነሳ የሚያገኙት የማኅበራዊ ሥነ ልቦናና ምሁራኖች ከሚኖራቸው ንቃተ ህሊና የተለየ ብቻ ሳይሆን በደረጃውም ዝቅተኛ ነው ። ከዚህ አንፃር ሲታይ የአንድ ማኅበራዊ አብዮት ተግባር ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው ። ሕዝባዊ ምሁራንን መፍጠር የብዙሀኑ የንቃተህሊና ደረጃ ከፍተኛ ወደ ሆነ የመደብ ንድፈ ሀሳባዊ የንቃተ ህሊና ደረጃ ማሳደግ ነው ። ይህ ደግሞ ከባህል አብዮት ጋር የተዛመደና የርሱም ውጤት ነው ።

ይህ ግን በቀላሉ የሚከናወን አይደለም ። ምክንያቱም በአንድ በኩል የመደብ ንድፈ ሀሳባዊ ንቃተ ህሊና ፤

ትክክለኛ የሆነ የፕራክሲስ (Praxis) ግንዛቤ የሚያሳየው መላውን የሰው ታሪክ እንደ ተግባራዊ ማኅበራዊ ህልውና እንዲሁም መላውን የፍልስፍናን ታሪክ መገንዘብ እንደ ቀድመ-ሁኔታ አስፈላጊ መሆኑን ነው ለማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ነው በራሱ የግብታዊ ክልል ውስጥ የተያዘና አንፀባራቂ ያልሆነ የተግባራዊ ክንዋኔ ግንዛቤ ወደ ትክክለኛ የፍልስፍና ፕራክሲስ ደረጃ ሊያድግ የማይችለው ።[17]

ብዙሀኑ ሕዝብ የሰውን ልጅ ደረጃ አመጣጥን ፤ ተግባርንና ማኅበራዊ ህልውናን ለመገንዘብ የሚያስችል የንድፈ ሀሳባዊ ጥንካሬ እንዲያገኙ የሚያስችል ሁኔታ ስለማያገኙ በዚህ የማኅበራዊ ሕይወት መስክ የህሊናዊ ባህላቸው ዝቅተኛ ይሆናል ማለት ነው ።

የብዙሀኑ የንቃተ ህሊና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ የሚያደርገው በማኅበራዊው ሥርዓት ውስጥ ባላቸው ሥፍራ ተበዝባዥ በመሆናቸውና ስለሥራም በሚሰጠው አነስተኛ ግምት የተነሳ ነው ። በባርያውና በፊውዳሉ ሕብረተሰቦች ውስጥ ሥራ ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው በመሆኑ በዚህ የሥራ መስክ የሚታይ የህሊናዊ ዕድገትም ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው እንዲያውም የሚንቋሸሽና ለዕድገቱና መስፋፋቱ ከፍተኛ እንቅፋት የሚፈጠርበት ነው ። ይህንንም ለመገንዘብ በአገራችን ውስጥ በዕደ ጥበብና ሌሎች መሰል የሥራ መስኮች የነበረ ማጥላላትና ማግለል እራሱን የቻለ ማሥረጃ ነው ።

የማቴሪያላዊ ምርት ተግባር ሰውን የማቴሪያላዊ ነገሮች ባርያ ያደርጋል ። ስለዚህም በግሪስ በባርያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስጥ ሥራ ለነፃ ሰዎች ፋይዳ ቢስ ነው ። ሥራ የቁስአካል ተገዢ በመሆኑ የማምረት ተግባር የባሪያዎች ነው ። ነፃ ሰዎች በደስታ እንደ ፈላስፎች ወይም እንደ ፖለቲከኞች መኖር አለባቸው (በነፃ ዜግነታቸውም) በነዋሪነታቸው ወይም አባልነታቸው እራሳቸውን

Digitized by Google

በማሰላሰልና በፖለቲካ እንቅስቃሴ ማሠማራት ከአዳዲስ ሀሳቦች ጋር ማስታወቀና የሰዎችን እንቅስቃሰ. ንቁ ሆነው መቆጣጠር አለባቸው ።[18]

ይህ የአርስቶትል አባባል ነው ። ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የጉልበት ሥራ ከዓዕምሮ ሥራ የተለየና የዓዕምሮ ሥራም በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚከናወን መሆኑንና ስለጉልበት ሥራም በወቅቱ ዝቅተኛ ግምት እንደነበረው ብቻ ሳይሆን በጉልበት ሥራ መስክ ሊገኝ የሚችል ዕውቀት ፤ ልምድና ችሎታ ዝቅተኛ ግምት ተሰጥቶት እንደነበር ነው ።

እንዲያውም ይህ ዓይነቱ ዝቅተኛ ግምት አምራቹ ክፍል በሀሊናዊ ዕውቀቱና በሀሊናዊ ባህሉ እንዳያድግ ፤ የሚያስገኘውም ውጤት እንዳይስፋፋና እንዳይሠራጭ ከፍተኛ እንቅፋት እንደነበረበትም የሚያሳይ ነው ።

ማቴሪያላዊ ባህል

ማቴሪያላዊ ባህል የምንለው ሰዎች በቀጥተኛ መንገድ ፍላጐታቸውን ለማርካት የሚያመርቷቸው ሆነው ነባራዊ ህልውና ያላቸውን ነገሮች በሙሉ ናቸው ።

የማቴሪያላዊ ባህል ክስተቶች በባህሪያቸው የመደብ ጥቅምን የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው በይዘታቸው የመደብ ባህሪ የላቸውም ። የተግባር መገልገያዎች ፤ ህንፃዎች፤ድልድዮች፤ፋብሪካዎች መኪናዎች ትራክተሮች፤ ወፍጮዎች፤ቤቶች ወዘተ የማቴሪያላዊ ባህል ምሣሌዎች ናቸው ። ነገር ግን እነዚህ በምሣሌው ውስጥ የተጠቀሱትም ሆኑ ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮች የጨቋኝ ወይም የተጨቋኝ መደብ ሊሆኑ አይችሉም።

ይህም ሲባል ግን አጠቃቀማቸው ወይም በህብረተሰብ ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለው ዓላማ የመደብ ባህሪይ የለውም ማለት አይደለም ። የተለያዩ ተፃራሪ መደቦች ለሚፈልጉት ዓላማ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ ። ነገር ግን የእነዚህ ነገሮች ምንነት ግን አይለወጥም ። ማቴሪያላዊ ባህሎች ለመጥፎ ወይም (አድሀሪ) ለበጐ (ለተራማጅ) ዓላማ ከንዋኔ ቢውሉም እነርሱ በራሳቸው ግን ጥሩ ወይንም መጥፎ አይደሉም ።

ማቴሪያላዊ ባህሎች በተግባር ውስጥ የተለወጡ የተፈጥሮ ሳይንሳዊ ዕውቀቶች ናቸው ። የተፈጥሮ ሳይንሶች ዕውቀት ይዘት ደግሞ የመደቦችን ጥቅም የማያንፀባርቅ በመሆኑ በመሠረቱ በመደብ ሥርዓቶችም ሆነ በመደብ አልባና በቅድመ መደብ ሥርዓቶች ውስጥ የመደብ ባህሪይ የለውም ። ስለሆነም ቴክኖሎጂ ማቴሪያላዊ የሆነ የተፈጥሮ ሳይንሶች ዕውቀት በመሆኑ የመደብ ባህሪይ የለውም ። በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚፈጠሩ ማቴሪያላዊ ነገሮች እንዲሁ የመደብ ጠባይ የሌላቸው ፤ የተግባር መገልገያዎችና የማቴሪያላዊ ባህል ክስተቶች እንደሆኑ ተጠቅሳል ። እነርሱም የምርት ኃይሎች ማቴሪያላዊ ክፍል ናቸው ። ከዚህም የተነሳ በአንድ በኩል ሰው ከማቴሪያላዊና ከአካባቢው ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነትና የዚህንም ግንኙነት ንቁነት (activities) ያንፀባርቃሉ ። ሰው በተፈጥሮ ላይ ምን ያህል የበላይነት እንዳለው ተፈጥሮንም ምን ያህል ሰው እንደተቆጣጠረ ወይም ሊቆጣጠር እንደሚችል ያሳያሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ምርት ኃይል ማቴሪያላዊ ክፍልነታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው ። ይህም በመሆኑ ማቴሪያላዊ የምርት ኃይሎች የአጠቃላይ የሕብረተሰብ ዕድገት ወይም የታሪክ ግስጋሴ መሠረት ናቸው ማለት ነው ።

ሰው ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት የሚጠቀምባቸው ነገሮች ሁሉ ራሳቸው የምርት ውጤቶች እንደመሆናቸው ከሕብረተሰቡ ጋር አብረው የሚያድጉ ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰብም የሚያሳየው ዕድገት መሠረትም ጭምር ናቸው ። ስለሆነም ማቴሪያላዊ ባህል ከሥልጣኔ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል ቢባልም በአንድ የተወሰነ የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሕዝቦች ወይም አገሮች አንድ ዓይነት ሥልጣኔ ወይም ባህል አላቸው ማለት አይደለም ።

---ስለዚህ የሰዎች ምን መሆን ፤ ምርታቸውን በምን እንደሚያመርቱና እንደትስ እንደሚያመርቱ ከሚሉት ሁለት ነጥቦች ጋር የተዛመደ ነው ።[19]

ይህ የሚያሳየው አገሮች በተመሳሳይ የምርት ኃይሎች የእድገት ደረጃ ላይ ቢገኙም በምርት ኃይሎቻቸው አጠቃቀምዘዴ ችሎታና ብቃት ሊለያዩ ስለሚችሉ በባህ

Digitized by Google

ላቸውም እንደሚለያዩ ያሳየናል ። ምክን ያቱም ፤

- - - በዚህ ርዕስ ሥር (በምርት ኃይሎች ፤ ውስጥ) የሰዎች ልምድና የተግባር ማከና ወኛዎችን የመጠቀም ቻሉታ ፤ በዚህ አቀ ጣጣ ልምድ ያገኙና ተመሳሳይ ችሉታ ያላቸው ሰዎች ይገኛሉ ። [20]

ስለሆነም ሰዎች የሚኖራቸውን ፤ ዕው ቀት ፤ ልምድና ችሎታ እንዲሁም የምርት ማከናወኛዎችን ብቃትና ጥራት ባለው መን ገድ የመጠቀም ችሎታ የተለያየ በመሆኑ በተመሳሳይ የምርት ኃይሎች ደረጃ ላይ መገኘት የባህል አንድ አይነት መሆን መነሻ አይሆንም ።

የተፈጥሮ አካባቢ በሰዎች እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ ተግባር ላይ ወሳኝነት እንኳን ባይሆን ተፅዕኖ የማሳደር ሚና ስላለው በሥነ ልቦናቸውና ይህም በሚገለፅበት መንገድና ማቴሪያላዊ ገፅታ የአገሮችና የሕ ዝቦች ባህል ሊለያዩ ይችላል ።

የምርት ኃይሎች ከትውልድ ወደ ትው ልድ የሚተላለፉና ከህብረተሰብ ጋር አብ ረው የሚያድጉ በመሆናቸው ከሥልጣኔ ጋር ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ ብለናል ። ስለሆነም የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ የሕብረተሰብን የሥልጣኔ ደረጃ ያሳያሉ ማለት ነው ። የምርት ኃይሎችም የዕድገት ደረጃ በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ደረጃ ይገለጻል ። ለምሣሌ የውኃና የንፋስ ወፍጮ የፊውዳል ሕብረተሰብንና በዚህም ውስጥ ያለን የሥራ ክፍፍል ባህሪይ ሲያሳዩ የካ ፒታሊስቱን ሕብረተሰብ ፋብሪካዎች ኢንዱ ስትሪዎች ፤ ማሽኖች ያሳዩናል ። የምርት ኃይሎች ግን ከምርት ግንኙነቶች ተገን ጥለው የሚገኙ ባለመሆኑ የምርት ኃይሎች በሕብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ወይም አወ ቃቀር ላይ ያላቸው የወሳኝነት ሚና በምርት ግንኙነቶች አማካኝነት ነው ማለት ነው ።

በተለያዩ ብሔሮች መካከል ያለ ግንኙነት እያንዳንዱ ብሔር የራሱን የምርት ሀይሎች ፤ የሥራ ክፍፍልና በውስጡ ያሉትን ግንኙነቶች ባሳደገበት ደረጃ ላይ ይመሠረታል ። ይህ አባባል በድምሩ ተቀባይነት አለው ። ነገር ግን አንድ ብሔር ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙ ነት ብቻ ሳይሆን የራሱ የብሔሩ ጠቅላላ ውስጣዊ አወቃቀር የሚወስነው ምርቱ በደ ረሰበት የዕድገት ደረጃና በውስጣዊና በው ጫዊ ግንኙነትም ነው ። [21]

ማቴሪያላዊ የሆኑት የምርት ኃይሎች የአንድ ሕብረተሰብ ማቴሪያላዊ ባህል እን ደመሆናቸው አንድ አገር በዕድገቱ የደረሰ በትን ደረጃና ሥልጣኔ እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖረውን የግንኙነት ዓይነ ቶችና የራሱንም ማኅበራዊ አወቃቀር ያሳ ያሉ ማለት ነው ።

እያንዳንዱ ትውልድ ማቴሪያላዊ ባህ ሉን ከበፊቱ ትውልድ ተቀብሎ የራሱንም የሚጨምርበት እንጂ ካለፈው ትውልድ ምንም ሳይቀበል የራሱ የሆኑ ማቴሪያላዊ ባህሎችንና የምርት ኃይሎችን አይፈጥርም።

በባህል ላይ ምንም ዓይነት ጥፋት ቢደርስ በትም ፤ መልሶ ባህልን ማቋቋም አስቸጋሪ ቢሆንም በባህል ላይ የሚደርስ ጥፋት ግን የባህል ሙሉ ለሙሉ መጥፋት ማለት አይሆንም። ሊጠፋ የሚችለው የባህል የተ የተወሰነ ማቴርያላዊ ክፍል ብቻ ነው [22]

በባህል ማቴሪያላዊ ገጽታ ላይ ምንም ያህል ከባድ ጉዳት ወይም ጥፋት ቢደርስበ ትም በህሊናዊ ገጽታው ግን ከቶውንም ሊጠፋ አይችልም ። በባህል ላይ የሚደርስ ጥፋት ከታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው በተፈጥሮ አደጋዎች ወይም በጦርነቶች አማካይነት የሚደርስ ነው ። በዚህ በኩል በተደጋጋሚ በባህል ላይ ጥፋት የደረሰ ቢሆ ንም ፣ ባህልን ሙሉ ለሙሉ ጠፍቶ አያው ቅም ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ከበርቴ ዎች ትርፍን ለማጋበስ በሚያደርጉት እድ ሀሪ እንቅስቃሴ በአገሮች መሀከል ጦርነቶች ይነሳሉ ። በነዚህ ጦርነቶች የተነሳ ባህል ከባድ ጥፋት ቢደርስበትም ጦርነቱ የሚያ ስከትለው ጉዳት ኤንግልስ እንዳለው የወዝ አደሩን መደብ አሸናፊነት ማስከተል አለ በለዚያም ለወዝ አደሩ መንግሥት ምሥ ረታ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች መፍጠር ነው ። ከበርቴው ትርፍን ከማሳደድ ፍላጎቱ የተነሳ ከሚፈጠሩ ጦርነቶችና በባህል ላይ ከሚደርሰው ጥፋት አንፃር ሲታይ የወዝ አደሩ መደብ የሚያደርገው ትግል መፍትሄ የሚያገኘው የፖለቲካ ሥልጣንን ሲጨብ ጥና የዕድገቱን የፖለቲካ መሥመር ርዕዮተ

Digitized by Google

ዓለማዊ አቅጣጫ በፓርቲው አማካኝነት
ፈር ሲያስይዝ ነው ።

ከላይ የሰፈረው ጥቅስም ሆነ ከታች የተ
ሰጠው የርሱ ትንታኔ የወዝአደሩ አብዮትና
የወዝ አደሩን መንግሥት ምሥረታን ከጦር
ነት ጋር ለማዛመድ ወይም የከበርቴው
መደብ የሚፈጥራቸው ጦርነቶች ውጤት
አድርጐ ለመውሰድ አይደለም ። በካፒታሊ
ስቱ ሥርዓት ውስጥ ከሚነሱ ጦርነቶች የተ
ረፉት ባህሎች ሶሻሊዝምን ለመገንባት ለሚ
ደረገው ትግል መነሻ ወይም መሠረት
ሆነው ያገለግላሉ ማለት ነው ።

ሰዎች ከከበርቴው መደብ ምንም ሳንማር
ሶሻሊዝም ድል ሊያደርግ ይችላል ብለው
ሲናገሩ ስሰማ ይህ የመሀከለኛው አፍሪካ
ነዋሪ ሥነ ልቦና እንደሆነ አውቃለሁ ።
እኛ እንገነባዋለን ብለን የምንገምተው ሶሻ
ሊዝም የሚመሠረተው ከካፒታሊስቱ በምና
ገኘው ሰፊ (ላርጅ እስኬል) ባሕል አማካ
ኝነት በምንቀስመው ትምህርት ነው ። ያለ
ፖስታና የቴሌግራፍ አገልግሎት ያለ ሰፊ
ትላልቅ ማሽኖች ሶሻሊዝም ትርጉም የለሽ
ባዶ ቃል ነው ።[23]

እዚህ ላይ ባህል ተወራሽ ፤ እንደ ሥል
ጣኔ ፤ እንደእውቀትም ጭምር ሊታይ እንደ
ሚችል ያሳያል ። ይሁን እንጂ የከበርቴውን
ባህል ወይም ሥልጣኔ እንዳለ ያለምንም
ለውጥ የሶሻሊስት ሥርዓትን የግንባታ
ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ያገለግላል ማለት
ግን አይደለም ። ይህ ሲባል ደግሞ ከካፒ
ታሊስቱ ሥርዓት የሚወረሰው ባህል በሙሉ
ይለወጣል ማለት አይደለም ። የቴክኖሎጂ ፤
የፋብሪካዎች ፤ የኢንዱስትሪዎች ወዘተ
ቴክኒካዊ አደራጀት በካፒታሊስቱም ሆነ
በሶሻሊስቱ ሥርዓት ተመሳሳይ ነው ። ስለ
ሆነም በዚህ ረገድ የሚደረግ ለውጥ አይኖ
ርም ። ይሁን እንጂ የተጠቀሱት ነገሮች
የሚይዙት ማኅበራዊ ዓላማና የሚጫወቱት
ሚና ግን ይለወጣል ።

የማቴሪያላዊና የህሊናዊ ባህሎች ልዩነት

ማቴሪያላዊና ህሊናዊ ባህሎች የባህል
ሁለት አካሎች ቢሆኑም ተመሳሳይ ጠባይ
ቢኖራቸውም ሁለቱ ግን አንድ አይደሉም
ሰው በሚያመርትበት ጊዜ ዕውቀቱን ልም
ዱንና ችሎታውን ስለሚጠቀምና ይህም
የሥራው ውጤት ሆነው በሚገኙ ነገሮች
ተሰግርቶ የሚገኝ በመሆኑ ሁለቱ የማይነ
ጣጠሉ ናቸው ። አይገነጣጠሉም ማለት
ግን ሁለቱ አንድ ናቸው ማለት አይደለም ።
ማቴሪያላዊ ባህሎች በምርት ተግባር ላይ
በሚውሉበት ጊዜ ወይም በቀጥተኛ መን
ገድ የሰውን ፍላጐት በሚያረኩበት ጊዜ
ይሰበራሉ ፤ ያረጃሉ እንዲያውም ሊጠፉ
ወይም ሊፈጁ ይችላሉ ። ስለሆነም ሕብረተ
ሰቡ እነርሱን ደግሞ ደጋግሞ እንዲያመርት
ወይም እንዲያሻሽላቸው ይገደዳል ። ህሊ
ናዊ ባህሎች ግን ምንም ያህል በተደጋጋሚ
በጥቅም ላይ ቢውሉ ወይም አገልግሎቶችን
ቢሰጡ የሚጠፉ ወይም የሚፈጁ ባለመሆ
ናቸው በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ ሊው
ሉ ይችላሉ ።

መኪና ፤ ሸሚዝ ፤ ምግብ ፤ ቤት ወዘተ
አንድ ጊዜ ተመርተው በፍጆታ ላይ በሚ
ውሉበት ጊዜ አጭርና ረጅም ጊዜ ቢቆ
ዩም ያረጃሉ ፤ ይሰበራሉ ፤ ከዚያም ወይም
በዚህ ጠቄሜታ ውስጥ ያልቃሉ ። በሌላ
በኩል የተፈጥሮና የማኅበራዊ ክስተቶች
የዕድገት ሕግጋት እውቀቶች ፤ በኪነት
መስኮች የሚገኝ እውቀት ምንም
ያህል በተግባር ላይ ቢውል አይጠፉም፣
አይሰበርም ወይም አይፈጅም ።

እርግጥ ነው የህሊና ባህሎች የማኅበራዊ
ህልውና ነፀብራቅ ቢሆኑም የአስተሳሰባችን
ይዘት በመሆን ብቻ የሚገኙ ባለመሆናቸው
ነባራዊ ሆነው የማቴሪያላዊ ገፀታ አላቸው ።
ማለትም በመጽሐፍት ፤ በድርሰት ፤ በስዕል
በቋንቋ ወዘተ . . . መልክ የሚገኙ ናቸው ።

ማቴሪያላዊና ህሊናዊ ባህሎች የሚመ
ረቱ ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት ላይ እንዲ
ውሉ የሚሰራጩም ጭምር ናቸው ። የማ
ቴሪያላዊ ባህሎች ስርጭት የሚከተለው
መስመር ሸቀጦች የሚከተሉትን መስመር
ነው ። ከአምራች ወደ አከፋፋይ ከዚያም
ወደ ቸርቻሪ በመጨረሻ ወደ ሸማች ሊሆን
ይችላል ። ወይም ከአምራች ወደ ቸርቻሪ
በመጨረሻም ወደ ሸማች ሊሆን ይችላል ።
በሶሻሊስት አገሮች ደግሞ ከአምራች ተቋም
ወደ ሸማች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በነ
ርሱም አማካኝነት ለሸማች አባሎች ሊደ
ርስ ይችላል ። የህሊናው ባህሎች ስርጭት

Digitized by Google

የሆነ እንደሆነ ግን በት/ቤትች ፤ ጋዜጦች ፤ መጽሔቶች፤በባህል ተቋም ወዘተ.... አማካኝነት ይሰራጫል ።

ባህል ማኅበራዊ ክስተት በመሆኑ ከኅብረተሰቡ ጋር ተዛምዶ የሚገኝ ቢሆንም ማቴሪያላዊ ባህል በመሠረቱ ወይም በተፈጥሮው የመደብ ጠባይ የለውም። ህሊናዊ ባህል ግን በሰዎች አስተሳሰብ ፍላጐትና ጥቅም የሚገልጽ በመሆኑ የመደብ ጠባይ አለው ።

ማቴሪያላዊ ባህል በሰውና በተፈጥሮ መሀከል ያለውን ግንኙነት ሲያሳይ ህሊናዊ ባህል በሰዎች መሀከል ያሉ ግንኙነቶችን በከፊል የሚያሳዩ ናቸው ። ከዚህም የተነሳ ህሊናዊ ባህል የሰዎችን ማኅበራዊ ሕይወት በማንፀባረቅ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ማኅበራዊ ሥርዓቱንም ለመለወጥ በሚደረገው ትግል ውስጥ የትግል መሣሪያ በመሆን የሚያገለግል ነው ። ከዚህ አንፃር ባህል እንደ ርዕዮተዓለም ሊታይ እንደሚችል እንረዳለን ።

---ባሕል ከወቀቱ ችግሮች ፣ ከኅብረተሰቡ ዋነኛ ፍላጐቶች ተገንጥሎ ሊኖርና ሊያድግ አይችልም ። ኅብረተሰብን በአዲስ በሚደራጀት በሚደረገው ጥረት ውስጥ አንቀሳቃሽ ኃይልና ፣ በሰው ሕልውና ውስጥ በሚከሰቱ መሠረታዊ የችግር መስኮች ውስጥም የእንቅስቃሴ መልክ ነው ።[24]

ሰዎች በሕብረተሰብ ውስጥ ካላቸው ስፍራና ከሚጫወቱት ሚና ልዩነት የተነሳ የራሳቸውም የሆነ የዓለም ግንዛቤና መለካከት ይኖራቸዋል ። በዚህ አንፃር ሲታይ የተለያዩ መደቦች ያላቸው ባህል በተለይም የህሊናዊ ባህል ልዩነት መለኪያ ርዕዮተ ዓለም ሊሆን ይችላል ማለት ነው ።

በማናቸውም ብሔራዊ ባሕል ውስጥ ባልዳበረ መልካቸው እንኳን ቢሆን ሠርቶ አዳሪዎችና ተበዝባዥ ብዙሀን ስለሚገኙ ፣ የኅይወት ሁኔታው ደግሞ በግድ የዲሞክራሲና የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ስለሚፈጠር የዲሞክራቲክና የሶሻሊስት ባሕል ክፍሎች ይገኛሉ ።[25]

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው እያንዳንዱ ብሔር የራሱ ብሔራዊ ባህል እንዳለውና በውስጡም የሁለት ተፃራሪ መደቦች ባህሎች እንደሚገኙ ብቻ ሳይሆን ባህል እንደ ርዕዮተ ዓለምም ሊያገለግል እንደሚችል ነው ። በኢኮኖሚው ጠንካራ የሆነ መደብ በመንግሥት አማካኝነት በፖለቲካውና በባህሉ ፤ በርዕዮተ ዓለሙም መስኰች የበላይነት ያለው መደብ ይሆናል ። ማቴሪያላዊና ኤኮኖማያዊ መሠረቶች ላዕላይ መዋቅራዊ የበላይነት ይሰጡታል ። ከዚህም የተነሳ ህሊናዊ ክስተት ሆነው የላዕላይ መዋቅር አካል በሆኑትም ጭምር የበላይነት ይኖረዋል ። ታዲያ አንድ ብሔር ሁለት ባህሎች ቢኖሩትም የበላይነት ያለው ባህል አንድ በመሆኑ የወዝ አደሩ መደብ ባህል ፤ እንደ አንድ የጠቅላላው ባህል ክፍል ብቻ ሆኖ የሚገኝ ነው ። ከዚህ አንፃር ሲታይ የወዝ አደሩ መደብ ባህል አሸናፊ ሊሆንና ጥንካሬ ሊያገኝ የሚችለው ለከበርቴው መደብ ባህል ባለው አልበገር ባይነት ወይም በዚህ ረገድ የራሱን ባህል እንደ ርዕዮተ ዓለም በከበርቴው ላይ በማስፈን ብቻ ሳይሆን የወዝ አደሩን መደብ መንግሥት ለዚሁ ዓላማ በገነባው ማቴሪያላዊ መሠረት በማነፅና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የአምራችነት ደረጃ ከፍ በማድረግ ብቻ ነው ። ሰፋፊና ዘመናዊ እዱስትሪ በመገንባት እንዲሁም ለዚህ ተስማሚ የሆነ የሥራ አደረጃጀት በመፍጠር አዲሱን ባህል ሊገነባ ይችላል ።

ህሊናዊ ባህል ከማቴሪያላዊ ባህል ጋር አብሮ የሚያድግ ቢሆንም በዕድገቱ ሂደት ውስጥ የሚያሳየው ፍጥነት ግን ከማቴሪያላዊ ባህል የተለየ ነው ። የማቴሪያላዊ ባህል ፈጥኖ ሲቀየር ህሊናዊ ባህል ግን ሊዘገይ ይችላል ። ይህም አንፃራዊ ነፃነቱን የሚያሳየን ነው ። ከህሊናዊ ባህል አንፃራዊ ነፃነት የምንረዳው በአንድ የተወሰነ ወቅት በሕብረተሰብ ውስጥ ከሚገኙት መሠረታዊና መሠረታዊ ካልሆኑ መደቦች ጋር ተዛምደው በርካታ ባህሎች እንደሚገኙ ነው።[26]

በነዚህ የባህል ክፍሎች መሀከል ሊኖር የሚችል ግንኙነትና መቀራረብ በሕብረተሰቡ ውስጥ እንደሚገኘው የፖለቲካ ሁኔታ ፤ የመደቦች ጥንካሬና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚገኘው ሁኔታ ይወሰናል ።

የባህል ዕድገት ሂደት በድምሩ ሲታይ ተራማጅ ነው ። ተራማጅነቱ ግን የሚታየው በየወቅቱ ሰው በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበ

Digitized by Google

ላይነትና ቁጥጥር ከፍ በማድረግና በዚህም ረገድ ሰው ከተፈጥሮ ኃይሎች ቁጥጥር፥ነፃ እየወጣ መሄዱን የሚጠቁም በመሆኑ ነው ። ባህል የተግባር ውጤት ቢሆንም በርሱ አማካኝነት የሚገኘው ውጤትና አመቺ ሁኔታ ለሰው ጠቃሚ ነው ማለት ነው ። ከዚህ መሠረታዊ የባህል ዕድገት አንፃር ስንነሳ በመሣሪያዎች በተለይም ሥልጣኔንና ሰውን በሚያጠፉ መሣሪያዎች መስከ የሚደረግ ዕድገት የባህል ዕድገት አይደለም ። ከነዚሁ ውስጥ ደግሞ እንደ ኒውትሮን ቦምብም ፣ ዓይነት መሣሪያዎች ሰውንና ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ብቻ የሚያጠፉ ንብረትን ግን የማይነኩ መሆን ከሰው ይልቅ ንብረት ከፍተኛ ዋጋ የተሰጠው መሆኑን የሚያሳዩና የኢምፔርያሊስቶች ባህል ምን ያህል የዘቀጠ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው ።

ባህል ያለው ማነው ?

እስከአሁን ባህል ምን እንደሆነ ፣ ባህሪያቱና አቅፎቸው የሚገኙ ክፍሎች እነማን እንደሆኑ ፣ የነርሱም ተመሳሳይነትና ልዩነት ምን እንደሆነ ለማየት ሞክረናል ። በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው «ባህል ያለው ማነው)?» የሚለውን ጥያቄ በመቀጠል ለመመለስ እንሞክራለን ።

በሀገራችንም ምንም ያህል ጉልቶ የሚታይ የክርክር ነጥብ ባይሆንም አንዳንድ የሕብረተሰብ ተመራማሪዎች የባህልን ማኅበራዊ ክስተት በመካድ እንስሳት ጭምር ባህል በተለይም ማቴሪያላዊ ባህል እንዳላቸው ለማሳመን ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ ።

እንደነዚህ ተመራማሪዎች አባባል ከሆነ ባህል ማኅበራዊ ክስተት ሳይሆን ሥነ ሕይወታዊ (Biological) ክስተት ነው ። በዚህ አንፃር ሲታይ ባህል ስነ ህይወታዊ ከሆነ ነባራዊ የሆነ የተፈጥሮ ክስተት መሆኑ ነው ። የተፈጥሮ ክስተት ከሆነ ከሰውና ከሕብረተሰብ የተገነጠለና ህልውናውን ጠብቆ የሚኖር ክስተት መሆኑ ነውና ዕድገቱ እንደ ሥነ ሕይወታዊነቱ በደመ ነፍስ ይሆናል ማለት ነው ።

ማንኛውም ነገር ቀላልና ግልፅ ወደ ሆኑ መስተጋብሮች ዝቀ ሊደረግ ይችላል ። በሰውና በእንሰሳት መሀከል ምንም ልዩነት የሌለውን ያህል እንሰሳትም ማሽኖች ናቸው ።[27]

እዚህ ላይ እንስሳትና ሰው ተመሳሳይ መሆናቸው የተጠቀሰው በውስጥ አካሉ ቻቸውና በሚያካሂዱት መስተጋብሮች ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በሰውና በእንስሳት ፣ መሀከል ምንም ልዩነት እንደሌለ የሰውም እንቅስቃሴ ውጤቶችና ባህሪያቶች ከተመሳሳይ የእንስሳዎች ድርጊትና ውጤትም እንደማይለይ ለማሳየትም ጭምር ነው ።

ይኸው የተጠቀሰው የህዋሳት ስነ ሕይወታዊ ተመራማሪ ከባክቴሪያዎች አንስቶ ሰውንም ጠምሮ ሁሉም ያላቸው ኬሚካላዊ ሚሽነር ባመዛኙ ባወቀቀርም ሆነ በገቢር ተመሳሳይ ነው ።-- ህይወት ያላቸው ነገሮች ደግሞ ኬሚካላዊ ማሽኖች ናቸው ፣ ጠቅላላው ሕይወት ያላቸው ነገሮች ደግሞ የሚተረጉሙት በተወሰኑ ኬሚካላዊ መስተ ርብሮች አማካኝነት ነው ።[28]

በማለት በእንስሳትና በሰው መሀከል ምንም ልዩነት የለም በማለት ይከራከራል ። ነገር ግን የኃላፊነት ፣ የግዴታ የትክክል ወይም የስህተተኛነት ስሜት እንስሳዎች አላቸውን ? ዕውቀት ልምድንና ችሎታን ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ችሎታ ይኖራቸው ይሆን ? ካላቸው በምን ዘዴ ያስተላልፉታል ? እነዚህንና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የምናደርገው ጥረትና የምናገኘው ውጤት በተጨባጭ በእንስሳትና በሰው መሀከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማየት ያስችላልን ።

ሰውን ከእንስሳት ጋር የሚያመሳስሉት ዘርካታ ነገሮች አሉ ፣ ይህ ግን የሚያሳየን የእንስሳት ባህሪ ከሰው ጋር ባላቸው ተመሳሳይ ባህሪያት ሲገለጽ እንደሚችል ሲሆን ሰው ግን ሊገለፅ የሚችለው ከእንስሳት በሚለይባቸው ባህሪያት እንደሆነ ነው ።

ሰው እንሰሳ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰው ልዩ ተፈጥሮ (Uniqueness) የሚመሠረተው ከማንኛውም እንሰሳ ጋር በማይጋራ ቸው ባሕሪያት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።[29]

እንስሳት ሁሉ እራሳቸውን እንደ አካባቢያቸው የሚለውጡ ብቻ ሲሆኑ ሰው ግን አካባቢውን ከፍላጎቱ ጋር በሚጣጣም

Digitized by Google

መንገድ እንደወቅቱኒና ችሎታው ይለውጠዋል ። ይህ ደግሞ የመላው ማቴሪያዊው ዓለም ሁለንተናዊ ባህሪይ ሳይሆን የሰው ልጅ ብቻ ልዩ ባህርይ ነው ። በተፈጥሮ ውስጥ በምክንያትና ውጤት ግንኙነት ሊገለጹ የሚችሉ ክስተቶች ቢኖሩም የጭፍን እንቅስቃሴ ውጤቶች ሲሆኑ በሰው ወይም ሕብረተሰብ ውስጥ የሚገኙት ደግሞ የንቁና የፈጠራ እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው ። ከዚህም የተነሳ ሰውን ልዩ የሚያደርገው አዳዲስ ነገሮችን እያንዳንዱ ትውልድ ከቀደምቱ የመቀበሉ ጉዳይ ነው ።

በሌላ በኩል ግን በሥነ ሕይወት ጥናት ውስጥ አንድ ህዋስ በህይወቱ ዘመን ያገኛቸውን (Acquired)ነገሮች ሊያወርስ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊያስተላልፍ እንደማይችል የታወቀ ነው ። እንደ እንስሳ ወይም ዕፅዋት ከአካባቢው የተወሰኑ የአየር ፀባይ ለውጥ የተነሳ የሚያሳየውን ለውጥ ወደ ሚቀጥለው ትውልድ ሊያስተላልፍ አይችልም ። ምክንያቱም ፀባይ ሊተላለፍ የማችለው በጂንስ አማካኝነት በደመ ነፍስ መንገድ ስለሆነ አዳዲስ ነገሮች (እንስሳዎች ካኗቸው) በጂንስ ውስጥ ወይም ላይ የማይገኙ ወይም ተፅዕኖ የማያደርጉ ስለሆነ ነው ።

ስለሆነም የሥኑ ሕይወታዊ ጸባዮች በተፈጥሮ ውስጥ ሊተላለፉ የሚችሉት በደመ ነፍስ ብቻ ሲሆን በሰው ወይም በሕብረተሰብ ዘንድ ግን በተለየ መንገድ ነው ። ቋንቋ መወያያ ፤ ሃሳብ መለዋወጫ ፤ ሂስ መስጫ . . . ብቻ ሳይሆን የጥቂቶች እውቀት ለብዙሀን የሚተላለፍበት መሣሪያ ፤ የአንድ ትውልድ እውቀት ፤ ልምድና ችሎታ ወደ ሌላ ትውልድ የሚተላለፍበት ነው ። ነባራዊ ህልውና በወቅቱ የሌላቸው ነገሮች እንኳን መጠሪያቸው በሆኑ ቃላት አማካኝነት ነባራዊ ህልውና ያላቸውን ያህል የምንገነዘብበት ፤ ትዝታ የሚፈጠርበት ታሪክ የሚወሳበት አንድ እራሱን የቻለ የታሪክ ፤ የወግ ፤ የልምድ ፤ ዕውቀት ፤ ችሎታ ወዘተ . . . ማጎደር ነው ።

ቋንቋ የሰዎች አስተሳሰብ ፤ የአእምሮዋቸው እድገትና የፈጠራ ችሎታቸው መሠረት የሆነ ማኅበራዊ ክስተት ነው ። እንስሳት ግን ከዚህ ክልል ውጭ የሚገኙ ናቸው ። ዓላማና እቅድ ማውጣት ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ነገሮችን የመፍጠርና የመጠቀም ችሎታ የሰው ልጅ በጋራ ሲኖር ፤ ሲሠራ ፤ ሲያስብና ከዚህም ጋር የተነሳ አዕምሮው እያደገ ሲመጣ የፈጠረው ውጤት ነው ። እንስሳት ከሰው እጅግ በጣም የረዘመ እድሜ በመሬት ላይ ቢኖራቸውም ይህንን ግን (ሊያከናውኑ) አልቻሉም ። ይህም የሚያሳየን ሰው ሥነ ህይወታዊ ክስተት ቢሆንም ምንነቱ (essence) ግን ማኅበራዊ እንደሆነ የሚያሳይና በሥነ ህይወታዊ ባህሪዩ ከእንስሳት ጋር ቢመሳሰልም በተግባር አማካኝነት ባገኘው ማኅበራዊ ባህሪዩ ከነርሱ የሚለይ መሆኑንም ጭምር የሚያሳየን ነው ። ስለሆነም ሰው የሚገልጸው ከእንስሳት ጋር ባለው የጋራ ሥነ ህይወታዊ ባህሪዩ ሳይሆን ከእንስሳት በሚለየው ማህበራዊ ጸባዩ ነው ።

ሰው ምግብን ፤ መጠለያን ማግኘት ፤ ከጠላት እራስን የመከላከልና የማግኘት ጥረቱ ከእንስሳት ጋር የሚያመሳስሉት በመሆኑ ሰው ከእንስሳት አይለይም የሚሉ አሉ ። እንስሳትና ሰው የሚመሳሰሉት በዚህ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በርካታ ነገሮችም ጭምር ነው ። ተመሳሳይነታቸው ግን አንድ አያደርጋቸውም ። ምክንያቱም ሰው በስነ ህይወታዊነቱ የተነሳ ለመኖር የሚያስፈልጉት ነገሮች ከእንስሳት ጋር ቢያመሳስለውም እነዚህን ለማግኘት በሚያደርገው እንቅስቃሴና በሚጠቀመው ዘዴና መሣሪያ ከእንስሳት ይለያያል ። እንስሳት በተፈጥሮ አካሎቻቸው ሲጠቀሙ ሰው ግን መሣሪያዎችንም ጭምር ይጠቀማል ።

እንስሳት በመሣሪያዎች ቢጠቀሙም ምንም ዓይነት እንስሳ መሣሪያዎችን ፈጥሮ አይጠቀምም ። ቤንጃሚን ፍራንክሊን እንዳለው «ሰው መሣሪያን የሚፈጥር እንስሳ ነው ።» መሣሪያዎችን የመጠቀም የሰው ብቸኛ ጸባይ ባይሆንም መሣሪያዎችን ፈጥሮ ወይም ሠርቶ መጠቀም ግን ብቸኛ የሰው ጸባይ ነው ።

ንቁ ሆኖ መሣሪያዎችን መጠቀምና ለዓላማ እንዲያመቹ አድርጎ መሣሪያዎችን መፍጠር ብቸኛ የሰው ልጅ ጠባይ ነው ።[30]

ከዚህም የተነሳ እንስሳት ባህል የሌላቸው ስለማያስፈልጋቸው ወይም ጥቅም ስለማያገኙበት ነው ። ምክንያቱም የተፈጥሮ ስጦታ ተጠቃሚ እንጂ አምራቾች ስላል ሆኑ ነው ። የማቴሪያላዊና ህሊናዊ ባህሎች ከምርትና ከተግባር ጋር የተያያዙ በመሆናቸው እንስሳትም ደግሞ ከተግባር ውጭ መሆናቸው በነዚህ የሥራና የተግባር መስ

Digitized by Google

ኮች ሊገኙ የሚችሉ እድገቶች ሊኖራቸው አይችልም ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ የተፈጥሮ ተመራማሪዎች እንስሳትም ቢሆኑ አንዳንድ ነገሮችን ለማግኘት የተወሰኑ ነገሮችን የሚጠቀሙ ናቸውና እንስሳትም ባህል በተለይም ማቴሪያላዊ ባህል አላቸው ይላሉ ። ለምሳሌ አንድ በጥናት (exeperiment) ውስጥ ያለ ቺምፖንዚ በመርፌ ውስጥ ክር ሲያስገባ ታይቷል ፤ እንዳይደረስ ተደርጐ የተሰቀለን ሙዝ ዱላን በመጠቀም ሙዙን አውርዶ በልቷል ፤ በሮኬት ውስጥ በመሆን ዓለምን ዞሯል ፤ እንዲሁም ጋሻና ጦርን በአደጋ ጊዜ ራሱን ለመከላከል ከመጠቀም ፤ ጀንደን ምግብ ለመሰብሰብ ከመጠቀም ምን ያግደዋል በማለት ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በማስረጃነት በማቅረብ የእንስሳትን መሳሪያዎችን የመጠቀም ችሎታ በማሳየት እንስሳት ማቴሪያላዊ ባህል አላቸው በማለት ሊያሳምኑን ይሞክራሉ ።

ጉዳዩ ግን የተባለውን እንኳን በደምሩ እንዳለ ማከናወን ተቻለ ብንል እንሰሳት በሙሉ ግን የተጠቀሰውን ያከናውናሉ ወይ ወይሚለው ጥያቄ ያመራናል ። በሌላ በኩልስ ቢሆን እንስሳት መሣሪያዎችን ተጠቀሙ ማለት ፈጠሩት ማለት ነውን ? መሣሪያዎችንስ ተጠቀሙ ማለት ሰው ለምርምር የሚያስፈልገውን ሁኔታ ፈጥሮላቸውና (እንዲያከናውኑ) ገፋፍቶቸው በመንቀሳቀሳቸው ነውን ?

ዱላን ቆርጦ መገልገል ተፈጥሮን በቀጥተኛ መንገድ መጠቀም እንጂ ለውጦ መገልገል አይደለም ። ይህን ማለትም ተፈጥሮን በቀጥተኛ መንገድ መጠቀም ማንኛውም ሕይወት ያለው ፍጡር ዕፅዋትንም ጨምሮ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ተፈጥሮን ስለሚጠቀሙ ዕፅዋትንም ባህል አላቸው ወደሚለው የተሳሳተ መደምደሚያ ያመራናል ።

እንስሳት ማቴሪያላዊ ባህልየላቸውም ። ምክንያቱም ማቴሪያላዊ ባህል ከተግባር ብቻ ሳይሆን ከህሊናዊ ባህልምሊገነጠል የማይችል በመሆኑ ነው ። ለመሆኑ የትኛው እንስሳ ነው እውቀት፣ልምድና ችሎታን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፈ? እንስሳት አስመስሎ የማድረግ (IMITATION) እውቀት አላቸው፣ ለማለት ቢቻልም እንኳን ይህም የራሳቸው የዓለም ግንዛቤ ወይም የተግባር ውጤት አይደለም ። በመስታዎት ውስጥ እንደሚገኝ ምስል ወይም እንደ ገደል ማሚቱ የተሰጠውን መልሶ የሚሰጥ እንጂ የተቀበለወን አሻሽሎና ሕይወት ሰጥቶ የሚመልስ አይደለም ።

በሁለተኛ ደረጃም እያደገና እየተሻሻለ ከትውልድ ወደ ትውልድ የማይተላለፍ ነው ። ምክንያቱም ከውጭ የተገኘ ስለሆነ ነው ። ይህ ብቻ አይደለም ። ሕሊናዊ ባህል ሁልጊዜ በቋንቋ ፤ በመጽሐፍ ፤ በኪነት ወዘተ.... መልክ ተሰፋፍቶ የሚገኝ ማቴሪያላዊ ገፅታ አለው ። ከዚህም አንፃር ነባራዊ ነውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቋንቋ መልክ ይተላለፋል ።

ቋንቋ መልዕክት ማስተላለፊያ ነው ። እንደሚታወቀው ሁሉ ሀሳብ (በንግግርም ሆነ ድምፅ በሌለው መንገድ) የሚገለጸው በቃላት አማካኝነት ነው ። ሰው ድምፅ በማውጣት ወይም ባለማውጣት ፤ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ጊዜ የሚያስበው በቃላት አማካኝነት ነው ። ቋንቋ ከሌለ ማሰብ ስለማይኖር እንስሳት ቋንቋ ስለሌላቸው ሊያስቡ አይችሉም ማለት ነው ። በአደጋ ጊዜ በድንጋጤ በሚያደርጉት አንዳንድ እንቅስቃሴ እንስሳት ሊግባቡ ይችላሉ ቢባልም ይህ ግን በደመ ነፍስ የሚደረግ ሲሆን ሰው ከዚህ ሌላ የአደጋውን ምንነት ተረድቶ አሰላስሎና ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት የሚያስችለው ቋንቋ አለው ። እንስሳት ግን የላቸውም ።

በቋንቋ አማካኝነት መልዕክት ማስተላለፍ መረጃዎችን የማከማቸትና ሀሳቡን የማሳደግ ሁኔታ ይችላል ። ይህ የሚከናወነው ሥነ ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን ቋንቋ በውስጡ አስፍሯቸው በሚገኙት ቃላት አማካይነት ነው ። የሚወክሉት እዎንታ ራሱ ቋንቋ ማኅበራዊ በመሆኑ በቋንቋ የሚደረግ የመልዕክት ማስተላለፍም ማኅበራዊ ነው ። ስለሆነም ሕሊናዊ ባህል እንስሳት የሌላቸው ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ በመሆኑ ከሰው ጋር ተዛምዶ የሚገኝ ክስተት ነው ።

የመሣሪያዎችን አጠቃቀምና ከርሱም ጋር ተዛምዶ የሚገኙ ነገሮችን አስመልክቶ በሰውና በእንስሳት መካከል ያለው ሌላ አንዱ ልዩነት የእንስሳት መሣሪያዎችን መጠቀም ሁኔታዊና (Conditional) ጊዜያዊ መሆኑ ነው ። ማለትም መሣሪያው ካ

ጠገባቸው ከተወገደና የፈለጉትን እርምጃ ከወሰዱ በኋላ ስለመግሪያውም ሆነ ስለልምዱ ግንዛቤ አይኖራቸውም ። ሰው ግን ቋንቋና ባህል ያለው በመሆኑ መግሪያው ካጠገቡ ባይኖርም ዓላማውን ከግቡ ካደረሰ በኋላ ልምዱና ሀሳቡ ከርሱ ጋር ይገኛሉና የነኚህ ነገሮች ምስል በአዕምሮ ውስጥ ይገኛል ። ለእንስሳት ግን የአንድ ነገር ከእዮታ ውጭ መሆን ከአእምሮ ውጭ መገኘት ጋር አንድ ነው ። ለምሳሌ አንድ አውሬ የልጁ ሬሳ ካጠገቡ እስካልተወሰደ ድረስ እንጂ ከተወሰደ በኋላ ሀዘኑም ከበድኑ ጋር አብሮ ይሄዳል ወይም ይጠፋል ፣ ሰው ግን እንዲህ አይደለም ።

እንስሳት ሥነ ምግባር ፣ ሃይማኖት የኃላፊነት ስሜት ፣ ሥልጣኔ የላቸውም ። ስለባህል ምንነት ባደረግነው ትንታኔ ውስጥ ባህል ተፈጥሮአዊ ምክንያት ያለው ውጤት ሳይሆን የተግባር ውጤት መሆኑን ከዚህም የተነሳ ማኅበራዊ ክስተትና በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ ባህል በተለይም ሕሊናዊ ባህል የመደብ ፀባይ እንዳለው አይተናል ። ባህል የሰው ተፈጥሮን የመገንዘብ ችሎታ እያጐላ ሰው ተፈጥሮን እንዲቆጣጠር የሚያደርግ ነው ። ባህል የተግባር ውጤት ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና የሚያድግና ሽግግሩም በማኅበራዊ መንገድ መሆኑን አይተናል ። በባህል ውስጥ የሚጠቃለሉ ክስተቶች የተጠቀሱት ባህርያት ያላቸው በመሆኑ እንስሳት ባህል እንደሌላቸውና ሊኖራቸውም እንደማይችል ተረድተናል ።

ባጠቃላይ ባህል ያለው ሰው ብቻ ነው ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ባህል ኪነትና ሥነ ጽሑፍ በተለይ ሕሊናዊ ባህል ባጠቃላይ ምን እንደሚመስልና ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት የባህል ለውጥ ከንዋኔን አጠር ባለ መንገድ በሚቀጥለው የዚህ ፅሑፍ ክፍል ለመመልከት እንሞክራለን ።

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

1. The Webster English Dictionary
2. Dictionary of Philosophy, Progress Publishers, Moscow, 1967
3. V. Kelle and m. Kovalson, *Historical materialism*; *An Outline of Marxist Theory of Society*, Moscow, Progress Publishers, 1973, P. 100
4. K. Marx, *Economic and Philosophic Manuscript of* 1884, Moscow, progress Publishers, P. 100
5. George M. Foster, *Traditional Cultures and the Impact of Technological Change*, P. 16
6. *Ibid*, P. 12
7. Leslie A, Withe, The Science of Culture, P. 122
8. Marx and Engles, Selected Works, Vol. 3, Moscow, Progress publishers, 1976, P. 67
9. K. Kovalsen, Ibid, p. 155
10. *Ibid*, P. 137.
11. Karl Marx, *Theories of Surplus Value* Part 1, Moscow 1969, P. 285.
12. A. F. Losev, *History of Ancient Esth,-tetics*, Moscow, 1963, P. 107.
13. K. Kovalsen, P. 223.
14. G.G LCzer man, Classes and Nations, Moscow, P. 18.
15. Problems Of Contemporary World, Political Theory and Political Practice No. 80. 1979, P. 81.
16. Social Science, No. 1, Moscow, 1981, P. 129.
17. Adolfo Sanhez Vasquez, The Philosophy of Praxis, London., 1977, P. 10
18. *Ibid*, P. 12
19. Marx and Engles, The German Ideology, Moscow, 1976, P. 37
20. Oskar Iemge, Political Economy, Vol. 1, Waeszawn, 1963, p, 10
21. *Op. cit*, p, 38
22. V.I Lenin, col, Works, Vol. 27, p, 129
23. *Ibid*, p. 310.
24. A. Arnoldov, On the path of cuural progress, Moscow Progress publishers, 1974. P. 10
25. *Op. cit*, p. 24
26. Rayond Williams, *Problems in Materialism and Culture*, London, 1980, p, 41 quoted in the *Uniqueness of man*.
28. George Gaylovd Simplson, *The Meaning of Evolution*, ibid.,
29. Grahame Clark, From savagrey to Civilization, Ibid p,7.
30. Karl Marx and F. Engles, Collected works, Vol. 5, 1976, p. 59.

Digitized by Google

Digitized by Google

በሰሜን ኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተጠናክሮና በመንግሥትነት ተዋቅሮ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መስፋፋት እንደ ጀመረ በክፍል አንድ መጥቀሳችን ይታወሳል ። በዚህኛው ክፍል ደግሞ ከ19ኛ ክፍለ ዘመን በፊት በደቡብ ኢትዮጵያ በማቆጥቆጥና በማደግ ላይ የነበሩትን ሥርዓተ ማኅበራት የዕድገት ሂደት በማብራራት ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ታሪክ አንጻር ለማገናዘብ እንሞክራለን ። በዚህ ጽሑፍ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚባለው ደቡብ ደቡብ ምዕራብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያን ባንድነት ነው ።

ደቡብ ኢትዮጵያ ከ16ኛ ክፍለ ዘመን በፊት ፤

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከተካሄደው የኦሮሞ ፍልሰት በፊት ደቡብ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ ሲዳማ በመባል ይታወቅ ነበር ። ይህ የጂኦግራፊ ክፍል ከአባይ ግርጌ በስተ ደቡብና ከዋቢ ሸበሌ ወንዝ መፋሰሻ መካከል የሚገኝ ነው ። በዚህ ክልል ውስጥ የካም (ኩሽ) ነገድ ዝርያ የሆኑና ሲዳማ በሚል አጠቃላይ መጠሪያ ስም የሚታወቁ ሕዝቦች ይገኙ ነበር ። ሲዳማ ለደቡብ ኢትዮጵያና በክልሉ ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ ኦሮሞ ላልሆኑ ሕዝቦች የተሰጠ ስያሜ ነው ።

ስለደቡብ ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ ጥናት ያካሄዱ የታሪክ ተመራማሪዎች ሲዳማ ብዙ ንዑሳን ክፍሎችንና ጎሳዎችን ያጠቃለለ እንደነበረ በተለያዩ ጊዜያት ባካሄዱት ጥናት ገልፀዋል ። በዚህም መሠረት ቀበሌያዊ ልዩነቶችን የሚያንጸባርቁ ነገር ግን ምንጫቸው አንድ የሆነና በሚከተሉት ሰባት ንዑሳን ክፍሎች የሚከፈሉ ቋንቋዎች ይነገርበት የነበረ አካባቢ እንደሆነ ተረጋግጧል ። እነዚህም

ሀ/ ሲዳሞ ፣ ደራሳ ፣ ሐዲያ ፣ ከምባታ ፣
ጥንባሮ ፣ አላባ

ለ/ ወላሞ ፣ ጎፋ ፣ ኩሎ ኮንታ ፣ ዛላ ፣
ኩየራ ወይም ባዴቱ ፣ ሐረር ፣
ቁጣ ፣ ጋሞ

ሐ/ ጣራ ፤

መ/ ባስኬቶ ፣ ዘሴ ፣ ደቆ

ሠ/ የጎንጋ ቡድን — ከፋ ፣ ሸናሻ ፣
ቦሻ ፣ ወይም ጋሮ ፣ ማኦ ፣ ወይም
ኦንፈሎ ሻቆ ወይም ሞቻ

ረ/ የጊሚራ ቡድን — ሾኮ ፣ ቤኔሾ ፣
ሺ ወይም ዲዙ ፣ ቃባ ፣ ናኦ ፣ ማጂ

ሰ/ ያማ ወይም ጃንጀሮ ናቸው [1]

ከዚህም በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳርቻ ኒሎቲክና ኒሎ ሐማቲክ ጎሳዎች ይገኛሉ ። እነዚህም እንጋሻ ፣ ጉሌ ፣ በርታ ፣ ጉኑር፣ አድሁክ ፣ ኪማ ፣ ኮይሮ ፡ ፈንግ፣ ባካ ፣ ሻንጋማ ፣ ሳማኩ ፣ ቦዲ ፣ ባቻ ፣ ሙርሲ ፣ የሱሪ — ሱራማ — ሜካን ና የአሜቶ ቡድኖችን የሚያጠቃልሉ ናቸው [2] ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የሶማሌና የኦሮሞ ጎሳዎችም የሰፈሩበት አካባቢ ነው ።

እንደሚታወቀው ሁሉ በየትም ሥፍራ የሚገኝ የኅብረተሰብ ታሪክ በምርት ዕድገት ደረጃ የተወሰነ ነው ። ምርት የኅብረተሰብ መዋቅርና የእያንዳንዱ ማኅበራዊ ቅንብር ይዘት መሠረት ነው ። ከዚህም በላይ ከአንዱ ማኅበራዊ ቅንብር ወደ ሌላው የሚደረገው ሽግግርና ታሪክም የሚጓዝበት አቅጣጫ ከምርት ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው ።[3] ሆኖም በታሪክ ሂደት ውስጥ የተመጣጠነ ዕድገት ባለመኖሩ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ የደረሱ ቀበሌዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። በዚህም ሂደት ውስጥ የሚከሰቱት የምርት ግንኙነቶችና የምርት ኀይሎች የራሳቸው የተለየ ባሕሪይ ይኖራቸዋል ። የደቡብ ኢትዮጵያም ነገዶች ፣ ጎሳዎችና በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩት ብሔረሰቦች በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችና ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ሊገኙ የቻሉበት ምክንያት ቀደም ሲል ከጠቀስነው ሁኔታ የመነጨ ነው ።

ከሥርዓተ ማኅበራት ዕድገት አኳያ የማንኛውም ኅብረተሰብ ዕድገት መነሻ የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ነው ። የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት የተለያዩ ገጽታዎችንና የዕድገት ደረጃዎችን ያቀፈ ነው ። ማርክስ «ጥንታዊ ኮሚውኖች በአንድ መልክ የተገነቡ አይደሉም ። ዳሩ ግን በዓይነትና በዕድሜ የሚለዩና እንዲሁም ተከታታይ የዝግታ እድገትን የሚያሳዩ ብዙ ማኅበራዊ ቡድኖች ይመሠርታሉ ።» [4] እንዳለው ሁሉ ከተለያዩ ውጫዊ ፣ የአየር ንብረት ፣ የመልክአ ምድርና ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች የተነሳ እንደ ሰሜኑም ሁሉ በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩ ጎሳዎች የጥንታዊ የጋርዮሽን ሥርዓት የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች የሚያንፀባርቁ ነበሩ ።

በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ድንበር ላይ የሚኖሩት ጎሳዎች በዝቅተኛ

Digitized by Google

የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ስር ነበሩ ።
እነዚህ ጎሳዎች የአንጋሳ — ማአ ቡድን ፤
የሱሪ — ሱራማ — ሚካን ቡድንና የታ
ችኛው ኦሞ ሕዝቦች የሚባሉት ናቸው ።
በተጠቀሱት ጎሳዎች ዘንድ ከጥንታዊው
ኮሚውን መከሰት ጋር የቡድናቹ መኖር
«በደም ፣ በቋንቋና አኗኗር በጋራ የተሳሰረ
ነው ።»[5] ለምሣሌ የአንጋሳና — ማአ ቡድን
(ጉሌ ፣ ማአ ፣ በረታ ፣ ጉሙዝ ፣ አድሁክ ፣
ኮሞ ፣ ጋንዛ ፤ ወዘተ ጎሳዎችን ያቀፈ
ነው ።) ዘንድ አነስተኛው ክልል ውስን
የሆነው ቤተሰብ ነው ። በዚህ ቡድ
ን ቤተሰብ የሚባለው ባል ሚስትና
ልጅን የሚያጠቃልል ነው ። መንደሮች
የሉም ። የሃይማኖት መሪዎች የመወሰን
ሥልጣን ያላቸው ቢሆንም ሥልጣናቸው
በጎሳው ሽማግሌዎች የተገታ ነው ። ተፈጥ
ሮን ማምለክ የጠነከረ ነው ። በሱሪ —
ሱራማ—ሚካን ቡድን (ሱሪ ፣ ቲርማ ፣ ጥድ፣
ዚልማሙ ፣ ሙርዙ ፣ ሚካን ፣ መሰንጎ)
ዘንድም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል ። ከዚ
ህም በቀር የጎሳ አለቆች መንደሮችን በሰ
ላምና በጦርነት ወቅት የመምራት ኃላፊነት
አለባቸው ።[6] የሱሪ ወንዶችና አዛው
ንቶች በዕድሜ ክልል የተቀናጁ ናቸው ።
አዲስ ቅንጅት በየአስር ዓመት ይደረጋል ።
ቅንጅቶቹ ስምንት ናቸው ።[7] ቅንጅቶች
በመንደር ላይ የተመሠረቱ ናቸው ።
እነዚህ ቅንጅቶች የጎሳውን የጦረኝነት
ዝንባሌ የሚጠቁሙ ናቸው ። ተፈጥሮን
ማምለክ የተለመደ ነው ። እርሻ (አልፎ
አልፎ አደን) በሁለቱም ቡድኖች ዘንድ
የኢኮኖሚው መሠረት ነው ። የታችኛው
ኦሞ ሕዝቦች (ገለብ ፣ ሬሺያት ፣ ዳትናክ ፣
ቡሜ ፣ ማርሲ) ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው
ቡድኖች በአንዳንድ ሁኔታዎች ቢመሳሰ
ሉም በከብት አርቢነት የሚኖሩ ኋላ ቀር
ሕዝቦች ናቸው ። ሁሉም ጎሳዎች አባዊ
ናቸው ። በእነዚህ ጎሳዎች ዘንድ የአመራረቱ
ዘይቤ እጅግ ኋላ ቀር ነው ። እንደዚሁም
ከሚያንጸባርቁት ሃይማኖት አንጻር የተፈ
ጥሮ የበላይነት ያየለ መሆኑን የሚያረጋግጥ
ነው ። በአጠቃላይ የእነዚህ ጎሳዎች እት
ብት ከጥንታዊው ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ
የተላቀቀ አልነበረም ።[8]

ከላይ ከጠቀስናቸው ጎሳዎች ሻል ባለ
ዕድገት ደረጃ ላይ የነበረው የቡርጂ ኮንሶ
ቡድን የሚባለው ነው ። ይህ ቡድን በሁ
ለት የሚከፈል ነው ። በመጀመሪያው ክፍል
ቡርጂ ፣ ኮንሶ ፣ ጋርዱላ ፣ ጊዶሌ ፣ ዳማይ
ወይም ኪሊና ኤርቦሬን የሚያጠቃልል
ነው ። ሌላው ክፍል ደግሞ አማር ፣ ከኪ ፣
ቂሬ ፣ ባቻዳ ና ባናን የሚያጠቃልል ነው ።[9]
የቡርጂ — ኮንሶ ቡድን ኢኮኖሚ በእርሻ
ላይ የተመሠረተ ነው ። በኅብረተሰቡ ውስጥ
የሥራ ክፍፍል አለ ። የእርከን ሥራ ፤ የጉድ
ጓድ ቁፋሮ ፤ የከብት ሥምሪትና መንደርን
ማጽዳት የመሳሰሉትን ከባድ ሥራዎች
ሐሪያ እየተባለ በሚጠራ ማኅበር ይሠራሉ ።
ሌሎች ዕደ ጥበብ መሰል ሥራዎች ደግሞ
በግለሰብ ይሠራሉ ። የኮንሶ ጋብቻ ገዳ
መሰል ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ነው ።
ይህም ጋማ የሚባለውን ዘጠኝ ደረጃዎች
ያሉትንና በየአሥራ ሦስት ዓመት ልዩነት
የሚመሠረተው ሐሪያ የሚባለውን የዕድሜ
ደረጃ የሚያጠቃልል ነው ። ሐሪያ በሚባ
ባለው የዕድሜ ደረጃ የጎሳው አባላት
ማኅበራዊ ፣ ወታደራዊና ሃይማኖታዊ ተግ
ባራትን እንዲቀስሙ የሚደረግበት ነው ።[10]
የኮንሶ ጎሳ ወንዶች ከተወሰነ ዕድሜ ሲደርሱ
ከዕድሜ ደረጃ ሥርዓት ውስጥ ይገባሉ ።
ይህ ሥርዓት የጎሳውን ማኅበራዊ ፖለቲካ
ዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚመራ ነው ።
ጂላ በመባል የታወቀው ሥርዓት ከኦሮሞ
ገዳ ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም
ተግባራዊ ልዩነት አለው ።[11] ጂላ በ5
የዕድሜ ደረጃ የተከፈለና በእያንዳንዱ የዕ
ድሜ ደረጃ የ18 ዓመታት ልዩነት ያሉት
ነው ።[12] የጂላ ሥርዓት የተለያዩ ደረጃ
ዎች በአጠቃላይ የኅብረተሰቡን የጋራ ችግ
ሮች ለመፍታትና ለመቆጣጠር የተቋቋሙ
ናቸው ።[13] ይህ ሥርዓት የጥንታዊ ዲሞክራ
ራሲ ገጽታን የሚያሳይ ነው ። እዚህ ላይ
መታወስ ያለበት የዚህ ዓይነት ድርጅት
አዲስ ሁኔታዎች ካለወጡት በስተቀር ለረ
ጅም ጊዜ የሚቆይ መሆኑን ነው ።[14]

በደቡብ ኢትዮጵያ በምርት ሂደት ው
ስጥ የታዩት አንጻራዊ ዕድገቶች የኢኮኖ
ሚውንና የምርት ግንኙነቱን አጠናከሩ ።
ይህም በኅብረተሰቡ አደረጃጀትና በጎሳው
ንብረት ላይ ተጽዕኖ አሳደረ ። ከዚህም
በላይ ለትርፍ ምርት መምጣት ሁኔታዎ
ችን በማመቻቸት ለማህበራዊ ዕድገት አ
መቺ ሁኔታዎችን ከፈቱ ። የሥራ ክፍፍል
እየሰፋ መምጣት የጎሳውን በዕድሜና በጾታ
መከፈል እያስቀረው መጣ ። በምትኩም በጎ
ሳው ውስጥና በጎሳዎች መካከል ያሉ ልዩነ
ቶች እየጎሉ መጡ ። ይህም የጥንታዊውን
የጋርዮሽ ሥርዓት ውድቀት አቃረበው ።
ከዚህም ጋር የጎሳዎች አንድነት በጠራ የፖ

ለቲካ አንድነት ተለውጦ በክልል ላይ የተ
መሠረተ ውህደት ተፈጠረ ። ኤርንስታ
ቺሩሊ በጥቅል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ
ሕዝቦች (ጊሚራ ፣ ማጂ ፣ ምዕራብ ሲዲማ
ወይም አጌቶ ፤ ሲዳማ — ደራሳ ፣ ከምባታ
ቡድኖች)[15] ከሚላቸው መካከልአ ንዳንዶቹ
ከላይ ከጠቀስነው ደረጃ ሊደርሱ ችለዋል ።

እንደሚታወቀው ሁሉ ለመደብ ኅብረተ
ሰብ መምጣት ዋንኛው ሁኔታ የትርፍ ም
ርት መኖር ነው ። የትርፍ ምርት በቋሚ
ነት መኖር ማኅበራዊ ልዩነትን ያስፋፋል ።
በደቡብ ኢትዮጵያም በተለይም ደግሞ
የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚ
ባሉት ዘንድ በመደቅደቂያ ማምረት እየተ
ለመደ ከመሄድ ጋር ትርፍ ምርት ከሞላ
ጎደል መገኘት ተቻለ ። ይህም ለገዢና
ለተገዢ መደቦች መከፋፈል መሠረት ጣለ ።
የሥራ ክፍፍልም ተፈጥሮአዊ መሆኑ እየቀረ
ማኅበራዊ ሆነ ። በዚህም ከመደብ አልባው
ጎሳዊ ኅብረተሰብ ወደ መደብ ኅብረተሰብ
የሚደረገው ሽግግር እየተቀናበረ መጣ ።
በመጨረሻም የመንግሥት ጽንስ የሆኑ
ትናንሽ ክልሎች ብቅ አሉ ። ከጊሚራ —
ማጂ ቡድን ውስጥ ሲእና ናኦ እንደምሣሌ
የሚቀርቡ ናቸው ።[16] የናኦ ንጉስ ቀያስ
የሚል መጠሪያ ስም ይሰጠዋል ። ይህም
ንጉሥ ሳሳቢ ከሚባለው ጎሳ የሚመረጥ
ነው ። ናኦ በተለያዩ አውራጃዎች ተከፍሎ
በሹሞች የሚተዳደር ነበር ።[17] ከምዕ
ራብ ሲዳማ (አጌቶ) ቡድንም መካከል ይህ
ንኑ ዓይነት ሽግግሮች ተደርገዋል ። በተ
ለይ ወላሞ (ወላይታ) በሚባለው ጎሳ ዘንድ
የተጠናከረ የመደብ ክፍፍል የታየበት ነበር ።
የገዥው መደብ መጠናከር የሥልጣን እርከን
መዘርጋትን አስከትሏል ። የወላሞ ንጉሥ
ታቱ ወይም ቃዎ በሚል መጠሪያ ይታወ
ቃል ። ከንጉሡ በታች ሩራ ራሳ (የባልደ
ራስ ሹም) ፣ ታቼ (አጋፋሪ) ፤ ቃኦ ቃር
(የክብር ዘበኛ ሹም) ሁዱጋ (የአውራጃ
ሹሞች) በተዋረድ ያሉ የሥልጣን እርከኖች
ነበሩ ። ይኸው ዓይነት ሽግግር የዚህ
ቡድን አባል በሆኑት በዛላ ፤ ጎፋ ባዴቱ
ሳንጋማ ጎሳዎች ተከናውኗል ።

በሲዳሞ — ደራሳ — ከምባታ ቡድን
ዘንድ ከላይ የጠቀስነው ዓይነት ሽግግር
ተደርጓል ። በተለይም ሐዲያ የሚባለው ጎሳ
የተጠናከረ አስተዳደር መመሥረት ችሎ
ነበር ። በደቡብ ኢትዮጵያ የተደረገው
ሽግግር በእኩልነት ይተዳደሩ የነበሩ ኅብረ
ተሰቦች ወደ ብዝበዛና ጭቆና ሥርዓት ሥር
እንዲወድቁ አድርጓቸዋል ።[18] በአጠቃ
ላይ የዚህ የሽግግር ውጤት የሲዳማ ትና
ንሽ መንግሥታት የሚባሉትን መመሥ
ረት አስከትሏል ።

የሲዳማ ኪንግደምስ (ግዛቶች)

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማክተ
ሚያ ላይ የታየው የምርት ዕድገት ያስከ
ተለውን ለውጥ ከደቡብ ኢትዮጵያ ሁኔታ
ጋር በማገናዘብ ገልጸናል ። በአጠቃላይ
በወቅቱ በደረሰው የምርት ዕድገት በሥር
ዓቱ ሥር በነበሩ ጎሳዎች ውስጥ ልዩነቶ
ችን ፈጠረ ። በተለይም የምርት መገልገያ
መሣሪያዎች መሻሻልና በግል የሚሰጡት
ጥቅም ማየል በደቦ የማምረት አስፈላጊ
ነትን አስቀረ ። ይህም በጎሳዎች ውስጥ ባሉ
ቤተሰቦች ዘንድ የሀብት ልዩነትን አመጣ ።
የሐብት ክምችት የፈጠረው ልዩነት ደግሞ
«ማኅበራዊ አመራር» ይሰጥ የነበረውን
የአዛውንቶች ጉባዔ በትላልቆቹና በሀብ
ታም ቤተሰቦች አባላት እንዲያዝ ሁኔታውን
አመቻቸ ። እነዚህ «የጎሳ ሹማምንት»
ለኅብረተሰብ የጋራ አመራር የተቋቋሙ
ትን ተቋሞች ለግል ፍላጎትና ሥልጣን
መወጣጫ በማድረግ የጎሳውን ጉዳዮች ሁሉ
መቆጣጠር ከመጀመራቸውም በላይ የኅብረ
ተሰቡን ወታደራዊ ኃይልም ለግል ጥቅም
ማዋል በመቻላቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ
የተዛቡ ሁኔታዎች ታዩ ። እያደርም የጎሳ
ሹማምንቶች የሚባሉት የገዥ መደብ ጥን
ስስ ለመሆን በቁ ። ከዚህም በቀር ኑሯቸ
ቸውን በእርሻ ላይ በመሠረቱ ጎሳዎች ዘ
ንድ የጋራ ይዞታ የሆነው መሬት ዋንኛ
የምርት ኃይል ቢሆንም በማኅበረሰቡ ውስጥ
የግል ይዞታ እየተጠናከረ በመምጣቱ በአ
ባላቱ መብትና ግዴታ ላይ ለውጥ አስከ
ተለ ። በሌላ በኩል በኅብረተሰቡ ውስጥ የግል
ይዞታ ሥር መስደድ የጦርነትና የመስፋፋት
ዝንባሌ በማስከተሉ ባርነት በቤተሰብና
በኅብረተሰብ ውስጥ መከሰት ጀመረ ።[19] እነ
ዚህ ሁኔታዎች ባጠቃላይ በኅብረተሰቡ
ዘንድ ለተጻራሪ ጥቅሞች የቆሙ መደቦችን
ፈጠሩ ። በአጠቃላይ የእዚህ ዕድገት ው
ጤት «የተደራጀና የተሰባሰበ የኅብረተሰብ
ኃይል»[20] ለሆነው ለመንግሥት መከሰት
መሠረት ጣለ

ከላይ የገለጽነው የሽግግር ሁኔታ መፋ
ጠን ወይም መግታት በአጠቃላይ በምርት
ኃይሎች ዕድገት ፤ በመልክአ ምድር አቀማመ

Digitized by Google

ጥና በተለያዩ ታሪካዊ ሁኔታዎች የተገዛ ነው ። በደቡብ ኢትዮጵያም ከ13ኛ ክፍለ ዘመን አካባቢ ጀምሮ በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩት አስራ አራት መንግሥታት ዕድገት ከዚህ አንጻር የሚታይ ነው ። እነዚህ ትናንሽ መንግሥታት በጥቅል የሲዳማ ኪንግደምስ (ትናንሽ ግዛቶች) በመባል ይታወቃሉ ። ሐዲያ ፣ ወላሞ (ወላይታ) ፣ እናርያ ፣ ከፋና ጃንጀር ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

የሲዳማ ግዛቶች ከሚባሉት መካከል ጠንካራ የባሪያ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ሊያድግ የቻለው በከፋና በጃንጀር (ያም) ነው ። በነዚህ ግዛቶች የተከሰተው የመደብ ኅብረተሰብ ማርክስ እስያዊ ስልተ ምርት ከሚለው አንጻር የሚገመገም ነው ። እዚህ ላይ ማስታወስ ያለብን እስያዊ ስልተ ምርት የሚባለው እንደሌሎቹ ስልተምርቶች ሁሉ ዓለም አቀፍ ዕድገት ያለው መሆኑንና ከእስያም ውጭ በተለያዩ ስፍራዎች ሊታይ እንደሚችል ነው ።[21]

የእስያዊ መሰል ሥርዓት ለሚያንፀባርቁ ኅብረተሰቦች ዋንኛው መገለጫ የግል ንብረት አለመኖር መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ለዚህ ሁኔታ መከሰት የሚሰጠው ዓይነተኛ ምክንያት የአየሩ ንብረት ፣ የአፈሩ ተፈጥሮና የአካባቢው በርሀማነት ነው[22] ። ሆኖም የደቡብ ኢትዮጵያን ሁኔታ ከዚህ ጋር ሙሉ ለሙሉ ማገናዘብ ባይቻልም የእስያዊ ስልተ ምርት መሰል ሥርዓት በዚህ አካባቢ ለማቆጥቆጥ አንዳንድ የጂኦግራፊ ሁኔታዎች (የአካባቢው ደን ለበስነት ፤ የአካባቢው አቀማመጥ ወጣ ገብነት ፣ ለመንደሮች መበታተንና መነጣጠል መንስዔ መሆን ፤ የዝናቡ ወራት መብዛት...... ወዘተ) መሠረት ናቸው ።[23]

የከፋና የጃንጀሮ ግዛቶች ኢኮኖሚ በእርሻ ላይ የተመሠረተ ነው ። በነዚህ ግዛቶች የኢኮኖሚው አነስተኛ አካል መንደሮች ናቸው ። መሬትና ሰው ዋንኛዎቹ የምርት ኃይሎች ናቸው ። ሆኖም በሁለቱም ግዛቶች ሰፊው ሕዝብ ነጻ ይዞታ የለውም ። መሬት በሙሉ የንጉሱ ንብረት ስለሆነ በክልሉ የሰፈሩ ሁሉ የንጉሡ ጭሰኞች ናቸው ።[24]

በከፋ የምርት ኃይሎች ዕድገት ያስገኘው ትርፍ ምርት ለማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መምጣት የረዳ በመሆኑ የዕደ ጥበብ አዋቂዎችን መፈጠር አስከትሏል ። ይህም ለንግድ ከንውንና የንግድ መስመር መዘርጋት ረዳ ። ከዚህም ጋር ውስን የሆኑ ከተማ ቀመስ የፖለቲካ መዲናዎችና የንግድ ዕምብርቶች መቋቋም ቻሉ ። ዲንቢራቤሻ፣ዴቻ፣ ጉባ ፣ ቡዳ ፣ ትልልቅ ገበያዎች ነበሩ ። ቦንጋ ፣ ጋዋቶ፣ ሚስቶና ሳሻ ትንንሽ ገበያዎች ሆነው ተቋቋሙ ።[25] እያደርም ከፋ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሀብታም ግዛት በመሆን ከኩሎ ኮንታና ወላይታ ጋር ግንኙነት ፈጠረ ። ከዚህም በቀር በዜይላ ፣ ምጽዋ ፣ ሱአኪን ፣ ጋላባት በኩል የንግድ ግንኙነት ነበረው ።[26]

በመንግሥት ደረጃ በመጠናከር ባለው በከፋ ውስጥ ሥልጣን በንጉሱ እጅ ተሰባሰበ ። ታቶ በመባል የሚታወቁት ነገስታት የሃይማኖት ፤ የፖለቲካ ፤ የዳኝነትና ወታደራዊ ሥልጣን በማጣመር ፈላጭ ቆራጭ ባለሥልጣን ሆኑ ። ንጉሦቹ አስፈሪ ግርማ እንዳላቸው በመቆጠሩ እንደአምላክም የሚሰግድላቸው ነበሩ ። በአጠቃላይ የንጉሡ በዚህ መልክ መታየት «በስውር» ለሚካሄደው ብዝበዛ ሽፋን ሆነ ። ከዚህም በላይ የሰፊው ሕዝብ ከንጉሡ (ከገዥው መደብ) ጋር መቆራኘት በማጠናከሩ አብዛኛው ትርፍ ፣ ጉልበትና ትርፍ ምርት ለገዥው መደብ ብዝበዛ ተመቻቸ ። ብዝበዛውን በበለጠ ለማጠናከር የሹማምንት እርከን ከላይ ወደ ታች በሰፊው ሕዝብ ላይ በመዘርጋት በ12ቱ ክፍለ ግዛቶች ካለው ሕዝብ ግብር በመቀባበል ይሰበስብ ጀመረ ።[27] በዚህ ሂደት የባርያ ሥርዓት ባህሪ ያለው ሁኔታ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰፈነ ።

በጃንጀር ውስጥም የሰፈነው ሥርዓት ከከፋ ጋር የሚመሳሰል ነበር ። የጃንጀር የገዢ መደብ ሕዝቡን ለመስዋዕትነት የሚቀበል ነበር ። እንደከፋም ሁሉ በሰፊው ሕዝብ ላይ የተዘረጋው የሥልጣን እርከን ለገዥው መደብ መጠናከር አይነተኛ መሣሪያ ሆነ ። በዚህ መሠረት ንጉሡ ፣ ባላባት (ታቶ) ፣ ቆር (እርሾ) ፤ እንደራሼ (ጉርሙ) ፤ ገበሬ ፤ ባሪያ — በተዋረድ ያሉ የሥልጣን እርከን ናቸው ። እነዚህ እርከኖች የብዝበዛውን መቀናጀ የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም በላይ የኅብረተሰቡን በመደብ መከፋፈል ያረጋግጣሉ ።

ከዚህ በላይ ባጭሩ ለማሳየት እንደሞከርነው የሲዳማ ግዛቶች ከሚባሉት መካከል አንዳንዶቹ ከፍተኛ ዕድገት ላይ ደርሰው ነበር ። በተለይም ከፋ በአካባቢው በመስፋፋት ልዩ ልዩ ሕዝቦችን ማስገበር ችሉ ነበር ።[28] ሆኖም ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተካሄደው የኦሮሞ ፍልሰት የከፋን

መገለል በማስከተሉ የዚህን ግዛት ዕድገት
ሊያሰናክለው እንደቻለ በጽሑፋችን ው
ስጥ ወደፊት እናሳያለን ።

የኦሮሞ ፍልሰትና ያስከተለው ውጤት

በኢትዮጵያ ውስጥ ከታዩት ታሪካዊ
ሁኔታዎች መካከል ገሚሱ በየጊዜው ከደ
ረሱት ልዩ ልዩ የሕዝብ ፍልሰት ፣ መስ
ፋፋትና ውህደት ጋር የተያያዙ ናቸው ። ከነ
ዚህ ትናንሽና ትላልቅ የሕዝብ ፍልሰቶች
አንዱና ዋነኛው በ16ኛ ክፍለ ዘመን የደረ
ሰው የኦሮሞ ሕዝብ መስፋፋትና መበተን
ነው ። የኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት በኢትዮ
ጵያ ታሪክ ሂደት ላይ ከፍተኛና ወሳኝ ሚና
የተጫወተ ክስተት ነው ።

የኦሮሞ ሕዝብ ይህን እንቅስቃሴውን
ከመጀመሩ አስቀድሞ በምሥራቅ ኢትዮ
ጵያ ዛሬ ሰሜን ሶማሌ በሚባለው የሰፈረ
እንደነበር ይታወቃል ።[29] ነገር ግን በአካ
ባቢው በነበረው የሶማሌ ኀሳ ግፊት የኦሮሞ
ኀሳ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሊገፋ
ቻለ ። አንድ ስለ ኦሮሞ ታሪክ የተመራመሩ
ግለሰብ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚባለው መጽ
ሐፋቸው ይህንኑ ሁኔታ ሲገልጹ ፤

ያፍሪካን ቀንድ ለቀው በሁለቱ ወንዞች
መካከል በበናዲር ሰፍረው ከኖሩ በኋላ እንደ
ገና በሱማሌዎች ወረራ ምክንያት ወደ ሰሜን
ምዕራብ መሰደድ የጀመሩት የጋላ ሕዝቦች
በዋቢ ሸበሌና በጁባ ወንዞች መካከልከሚገ
ኘው የበናዲር ወደብ ለንስተ በስተ ምሥ
ራቅ እስከ ባሌ በስተደቡብ እስከ ሰሜን
ኬንያ በስተሰሜን እስከ እስያ ሐይቅ ባሕ
ርና ወላቡ ተራራ ድረስ ሰፍረው ይገኙ
ነበር ። ብለዋል ።[30]

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ውስጥ
የነበረው የኦሮሞ ኀሳ የኑሮውን አመሠራረት
የገነባው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኝ በእር
ሻና በከብት ርባታ ላይ ነበር ።[31] እያደር
ግን በአካባቢው ተፅዕና ሳቢያ የኀብረተሰቡ
የኢኮኖሚ መሠረት በአብዛኛው የከብት
ርባታ ሆነ ። ከዚህም ጋር የማኅበረሰቡ
አደረጃጀት ገዳ በመባል በታወቀው የዕ
ድሜ ደረጃ ተዋቀረ ።[32] የገዳ ሥርዓት
አምስት የዕድሜ ደረጃ ክፍሎች ያሉትና
በየስምንት ዓመቱ የሚለዋወጥና በአርባ
ዓመት የሚፈጸም ነው ። የገዳ ሥርዓት
መስፈን የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማከ
ተሚያ መቃረብን የሚያመለክት «ከመን
ግሥት መምጣት በፊት ያለ የጥንት ዘመን
መሠረታዊ ማኅበራዊ ጥንቅር ባሕሪ ነው»[33]
በገዳ ሥርዓት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው
ዲሞክራሲም ከጥንታዊ የጋሪዮሽ ሥርዓት
መፈራረስ አኳያና ለጦርነት ከሚደረግ
መሰናዶ አንጻር የሚታይ ነው ።[34]

እንደሚታወቀው ሁሉ የከብት አርቢ
ዎች ኑሮ በንቅናቂ ላይ የተመሠረተ ነው ።
የዚህ ንቅናቄ መሠረት ደግሞ የግጦሽ
መሬት ማነስ ፣ የሕዝቦችና የከብቶች ቁጥር
መብዛት ናቸው ። እነዚህ ሁኔታዎች የሚ
ያሳድሩት ግፊትና ፍላጐት እያየለ መም
ጣት «ተረፈ ሕዝብ ትላልቅ ንቅናቄዎች
እንዲያደርግ ያስገድዱታል ።»[35] በኢት
ዮጵያም ከዋቤና ጁባ ሸለቆዎች አካባቢ
የተነሳው የኦሮሞ ፍልሰት መሠረታዊ ምክ
ንያት ከላይ የጠቀስነው መሆኑን ቀደም
ሲል የተጠቀሱት ፀሐፊ ሲያረጋግጡ ፤

ኦሮሞዎች እላይ በተመለከትነው አኳኋን በ
ወላቡ ዙሪያ ብዙ ትውልድ ካሳለፉ በኋላ
ከልክ ያለፈ ተራብተው ምድር በጠበባቸው ።
ከደረቁ ቤናድር ይዘዋቸው ወደ ወይና ዳጋ
ያመጡዋቸው የቦረና ዘር ላሞች ግጦሽ
ከመላበት ከለምለሙ ወይና ደጋ በደረሱ
ጊዜ ለለመጠን ረቡ ። ስለዚህ ኦሮሞዎች
ከወላቡ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የግጦሽም
መሬት እንደጠበባቸው ለይጠረጠርም ።[36]
ብለዋል ።

ከዚህም በማያያዝ ለጦርነት የተደረገውን
መሰናዶ ሲያስገነዝቡ ፤

በዚህ አኳኋን የኦሮሞ ሕዝብ ለመከላከልና
ለግጦሽ የሚፈልገውን መሬት አስፍቶ ለመ
ያዝ ከሠላማዊ አኗኗር ወደ አርበኝነት
ሀሳቡን መለሰ ። በወላቡ ዘመን ጋሎች
ፈረስ ስላልነበራቸው መከላከያቸው ለፎ
በሚባል እግረኛ ጦር ብቻ ነበር ። ስለዚህ
ከወላቡ ሳይነሱ በገዳ ድርጅት ውስጥ የጦር
ሠራዊትን ማከናወን ዋና ጉዳይ አድርገው
ያዙት ። አባ ዱላ (የዘመቻ አባት ወይም
አዝማች) የተባለው አለቃ መሾም የጀመሩት
በዚህ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ። ብለዋል[37]

የኦሮሞ ፍልሰት የተጀመረው በ1522
አካባቢ ላይ ነበር ። ፍልሰቱ ከአጀማመሩ
ላይ አነስተኛ ቡድኖች ሄድ መለስ የሚሉ
በት ነበር ።[38] ሆኖም የፍልሰቱ መጠንና
ጥንካሬ እያደር ሊጨምር ችሏል ። አለቃ
ባሕሬ የጋላ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው
እንደ ገለጹት ሁሉ በሁለት ዋና ክፍሎች

Digitized by Google

የተከፈሉ የኦሮሞ ቡድኖች የተለያዩ አቅጣጫዎችን በመከተል ተሰማሩ ። ከነዚህም አንዱ ባራይቱማ (ባሬንቱ ባሬጡማ) የሚባለው ቡድን ሲሆን ይህም ወደ ምዕራብ ባሌ በመገስገስ በ1580ዎቹ ወይም በ1590 ዎቹ ዓመታት ድዋሮ ፣ አዳል ፣ ፈጢጋር ፣ ጋን ፣ አንጎቶ የሚባሉትን የምሥራቅ ግዛቶች በመያዝ እስከ አምሐራ ፣ በጌምድርና ደምቢያ ድረስ ዘለቀ ። ቦረና የሚባለው ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በኮይራ ፣ ጋሞ ፣ ዋጅ ፣ ና ዳሞት ውስጥ በማለፍ ሰፊ ግዛት ያዘ ። በሃምሳ ዓመታት ውስጥ ኦሮሞዎች በደንብ ተደራጅተው በነበሩ ግዛቶች ላይ በመዝመት «የንድማም ፣ አንጎታን፤ዳዋሮ ዌድ ፣ ፌጠጋር ፣ ይፋት ፣ ጉራጌ፣ ጋንዛ ፣ ኩንታ ፣ ዳሞት ፣ ወልቃ ፣ ቢዝማ ፣ ከፊል ሸዋንና ውጥንቅጥ ግዛቶችን መቆጣጠር ቻሉ ።»[39] በአጠቃላይ በ1563 ላይ ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በመሰራጨት ከላይ በተጠቀሱት በዛ ያሉ ግዛቶችላይ ቁጥጥራቸውን ለማጥበቅ ችለው ነበር ።[40]

ተክለጻድቅ መኩሪያ ይህን ሁኔታ በበለጠ ሲያብራሩ ፤

> የጋሎች ለነሳስ በረዥም የጦር ግንባር ከብዙ ቦታ ገንፍሎ የተዠመረ ጦርነት ስለሆነ ባንድ ጊዜ ወይም በጥቂት ዓመታት ሳይወሰን ነዋሪነታቸውንና መብታቸውን በነዓጼ ሉስንዮስ ዘመነ መንግሥት እስኪያረጋግጡ ፤ ሰፋፊውን አገር ይዘው ባለቤት እስኪሆኑ ድረስ ጦርነቱ ባጼ ገላዉዲዮስ በአጼ ሚናስና በነአጼ ሠርጸ ድንግልም ዘመን እንደቀጠለ ነበር ። ከሱስንዩስም ወዲህ አልፎ አልፎ ጦርነቱ አልቀመም ነበር ። ነገር ግን ከ፲፰ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ያለው የመጨረሻው ጦርነት ያው ለማራውም ሊላውም ነገድ አልፎ አልፎ ከሚያነሳው ከተለመደ የውስጥ ጦርነት ወይም ከርስ በርስ ከተለመደ ግጭት የሚቆጠር ነው ፤ ብለዋል ።[41]

በመሆኑም በዚህ ፍልሰት ኦሮሞዎች ከመነሻቸው ከደቡብ ሰሜን 900 ማይልስና ከምዕራብ ምሥራቅ ደግሞ 500 ማይልስ ሊሠራጩ ችለዋል ።[42] የኦሮሞ ፍልሰት በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል ሊሰፋና ሊበተን የቻለበት ዋንኛ ምክንያት በግራኝ መሐመድ ጦርነት (1527 እስከ 1542 የተዳከመው የመአከላዊው መንግሥት ይሆን በቁጥርና በኃይል እየጠነከረ የመጣና ከጦርነት ጋር የተቀናጀ ፍልሰት ለመግታት ስለተሳነው ነበር ።

ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ሁሉ የኦሮሞ ፍልሰት የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ዐብይ ክፍል ነው ። በመሆኑም ይህን ከጦርነት ጋር የተቀናጀ ፍልሰት ቢያንስ ከሁለት ዋና ዋና ታሪካዊ ሁኔታዎች አንጻር መገምገም ይቻላል ። እነዚህም ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደትና ከኦሮሞ ብሔረሰብ ዕድገት አኳያ የሚመዘኑ ይሆናሉ ።

የኢትዮጵያ ታሪክ ምንጭ ከሆነችው አክሱም ጀምሮ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የተቋቋሙት የመአከላዊ መንግሥታት መሠረት የሰሜኑ ክፍል ነበር ። እነዚህ መንግሥታት ዛሬ ደቡብ ኢትዮጵያ የምንለውና በዛሬይቱ ኢትዮጵያም ውስጥ የማይደመሩትን ሌሎች ግዛቶች ያስተዳድሩ እንደነበር የታወቀ ነው ። ሆኖም ከኅብረተሰብ ዕድገት አኳያ በኢትዮጵያ በተደረጉት «የሽግግር ወቅቶች» (ከባሪያው ሥርዓተ ማኅበር ወደ ፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር) ዘመን የአገሪቷ የመሬት አቀማመጥ (ተራራማነት፣ ወጣ ገባነት ፡ ደን ለበስነት ፣ በረሀማነት) ወሳኝነት እያየለና የግዛቶች መጠቃለል እየተገታ መበታተኑ አንዳንዴ ሊያመዝን ችሏል ። ያም ሆኖ ይህ ዓይነት ሁኔታ አልፎ አልፎ ያጋጠመበት ወቅት ቢኖርም ኢትዮጵያን ሰሜን-ደቡብ በሚል ክልል ነጣጥሎ በማስቀመጥ ተለያይተው የኖሩ ለማስመሰል መሞከር ስህተት ነው ። በሌላም በኩል በደቡብና በሰሜን መካከል የተዘረጋውንና የረጅም ጊዜ ውጤት የሆነውን የተጠናከረ ግንኙነት ማጤን ተገቢ ነው ። በሀይማኖት ፣ በንግድ ፣ በባሕልና በአስተዳደር ላይ የተመሠረተው ግንኙነት ለደቡብ-ሰሜን አንድነት መሠረት ነበር ። የኦሮሞም ፍልሰት ለጥቂት ጊዜ ይህን ግንኙነት እንዲቋረጥ ቢያደርግም እያደር ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ተጨማሪ ኃይል በመሆን የሕዝቡን መተሳሰርና ውህደት አፋጥኗል ።

የኦሮሞን ብሔረሰብ ዕድገት በሚመለከትም ይህ ፍልሰት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው ። ደጋግመን እንደገለጽነው ፍልሰቱ በአንድ መልኩ ከጦርነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከአካባቢው ጋር የተፈጠረው ግንኙነትና መስተጋብር ማርክስ የገለጸውን በስልተምርትና በጦርነት አሸናፊነት አንፃር ከሚፈጠሩት ሦስት የግንኙነት ውጤቶች መካከል የአንዱን ዓይነት ውጤት እስከ

Digitized by Google

ትሏል ። ይህም «በሁለቱ መካከል መስተጋብር ተካሂዶ የአዲስ ሥርዓትን መምጣት ያስከትላል ።» [43] ያለውን ያጧላ ነበር ።

በዚህ መሠረት ኦሮሞች ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ወደ ባሪያና በአንዳንድ ቦታዎችም የባሪያውን ሥርዓት በመዝለል ከፊውዳል የዕድገት ደረጃ ሊደርሱ ችለዋል ። በአጠቃላይ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ማለትም ከ200 ዓመታት በኋላ ኦሮሞዎች ከዚህ የዕድገት ደረጃ ሊደርሱ በመቻላቸው የራሳቸውን አስተዳደራዊ ግዛቶች መመሥረት ችለዋል ። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በተከሰተው በነበረው አለመረጋጋትና ያልተመጣጠነ ዕድገት ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጦርነት ላይ ነበሩ ። ጦርነቶቹም በሲዳማ ግዛቶችና በኦሮሞዎች መካከል ብቻ ሳይሆኑ እርስ በርስም ጭምር ነበር ። የነዚህ ጦርነቶች ውጤትም በኦሞና በደዴሳ መካከል የተመሠረቱት ፊላጭ ቆራጭ አስተዳደሮች ናቸው ። እነዚህም የኦሮሞ ግዛቶች ይባላሉ ። ከነዚህም መካከል በይበልጥ የሚታወቁት ሊሙ እናርያ ፣ ጉማ ፣ ጉማ ጂማ ካካናጌራ ናቸው ።[44]

በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ እድገው ከነበሩ የሲዳማ ግዛቶች ከፊሎቹ በዚህ ፍልሰትና ጦርነት ሊዋጡና ሊደመሰሱ ችለዋል ። ከፋ ፣ ጃንጀሮ ፣ ወላይታ ደግሞ ከውጭ የነበራቸው ግንኙነት በመቋረጡ በአዝጋሚ ዕድገት ላይ ለረጅም ጊዜ ተገልለው ሊቆዩ ችለዋል ።

የኦሮሞ ግዛቶች (ኪንግደምስ) አመሠራረት ፤

የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት መፈራረስ በሚጀምርበት ወቅት የሚኖረው «ማኅበራዊ ሥልጣን» እና በማቆጥቆጥ ላይ ያለው የመደብ ኅብረተሰብ «ወታደራዊ ዲሞክራሲ» ቅርጽ የሚባለውን ሥርዓት ይይዛል ።[45] በወታደራዊ ዲሞክራሲ ስር የሚኖሩት ሸንጎዎች የጎሳው አባላት በዕኩልነት የሚሳተፉባቸው መሆናቸው እየቀረ ወደ ጠረኞች ሸንጐ ይለወጣሉ ። በአጠቃላይ በዚህ ወታደራዊ ዲሞክራሲ በሚባለው ወቅት የአስተዳደር ማዕከል የነበሩት ሸንጎዎች የወታደርና የሃይማኖት ሹማምንት የከረረ የሥልጣን ትግል የሚያካሄዱባቸው መድረኮች ይሆናሉ ። ከዚህም ጋር የሸንጎው የታጠቀ ኃይል የሥልጣን ምንጭነቱን እያጣ በመሄዱ በምትኩ የሸንጎው መሳፍንት ያለምንም ተቀናቃኝ ያለውን ስልጣን ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር ያደርጋሉ ። ኅብረተሰቡ በመደብ መከፈል እንደጀመረም የጐሳው ሹሞች በነበራቸው ወታደራዊ ኃይል አማካይነት እራሳቸውን ከሕዝቡ በማግለል ከነዚህ ሸንጎዎች ቁጥጥር ነጻ ሆኑ ። በሌላ በኩል የጎሳው ሹም ወታደሮች ወደ ልዩና ቋሚ ወታደራዊ ኃይል ተለውጠው የሹማምንቱን ፍላጎት በሌሎቹ ጎሳዎች ላይ መበየን ቻሉ [46] በዚህ ዓይነት የመጣው የሥራ ክፍፍል የኅብረተሰቡን በመደብ መከፈል ያስከተለ በመሆኑ የሸንጎው ሚና እየጧሸሸ መንግሥት በሚባለው ተቋም ተተካ ።[47]

ከላይ የጠቀስነው ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ በኦሮሞች ዘንድም ተፈጻሚነት አግኝቷል ። ኦሮሞዎች የገዳን ሥርዓት ይዘው ከዘመቱ በኋላ ይዞታቸው መረጋጋት ሲጀምር ለጦርነቱ መቃናት በረዱ አዝማቾች ዙሪያ መሰባሰብ ጀመሩ ። አባ ዱላ ፣ ሞቲ ወይም አባቦኩ በመባል የታወቁት የእነዚህ መሪዎች ሥልጣን በየጊዜው ሊጠናከር በመቻሉ የአስተዳደሩ ማዕከል በመሆን በዚህ አካባቢ ላቆጠቆጡት ግዛቶች መሠረት ሆኑ ።[48] የስልተምርቱ መለወጥ ባስከተለው ሁኔታም የገዳ ሥርዓት መዳከም ጀመረ ። ይህንኑ ሁኔታ ኸርበርት ሊዊስ ሲያረጋግጥ «የገዳ ስብሰባዎች በየጊዜው የሚደረጉ ቢሆንም ፍላጎታቸውን በጠንካራ የፖለቲካ ቡድኖች ላይ መበየን ቀርቶ ውሳኔዎችንም ቢሆን ያለ እነዚህ ቡድኖች ርዳታ ተግባራዊ ማድረግ አልቻሉም» ብሏል [49] ከገዳ ሥልጣን መዳከም አንጻር የተጠናከረው የአባ ዱላ ወይም ሞቲ ሥልጣን በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በሲዳማ ግዛቶች አምሳያ ለተቋቋሙት ለእናርያ ፣ ጉማ ፣ ጎማ ፣ ጌራ ፣ ጂማ ካካ ወዘተ ለተባሉት የፖለቲካ ክልሎች ዕምብርት መሆን ቻለ ። አባ ዱላ ወይም ሞቲ በስሜን የነበሩትን የንጉሦች አይነት ስልጣን ተቀዳጀ ።

ከላይ የጠቀስናቸው የፖለቲካ ክልሎች መቋቋምና መደርጀት እንደጀመሩ ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል ተመቻቹ ። ስለሆነም ከሲዳማ የፖለቲካ ክልሎች የወረሱትን ዘዴ ለዕድገታቸው መወጣጫ አደረጉት ። በዚህም መሠረት የኦሮሞ ፖለቲካ ክልሎች ሞጋ በሚባል ያልታረሰ መሬት የተከበቡ ነበሩ ። ሞጋ ሸፍቶች የሚኖሩባቸውና ጦርነቶችም የሚደረጉበት ሥፍራ ነው ። እያንዳንዱ ክልል ግዛቱን ባስፋፋ ቁጥር አዲስ ሞጋዎች እየተከለሉ የቀድ

Digitized by Google

ሞው ሞጋ ወደ እርሻ መሬት ተለውጦ በአዲስ ሞጋ ይተካል ። ከሞጋዎቹ ወዲህ የመከላከያ መስመር አለ ። ይህ ማግዎችን ፣ ረግረጋግ ስፍራዎችን ፣ ደኖችንና ወንዞችን በሕዝብ ጉልበት የተቆፈሩ ሰፋፊ ቦዮችን ያጠቃልላል ። ከአንዱ የኦሮሞ ክልል ወደ ሚቀጥለው ክልል ማለፍ የሚቻለው በተጠናከረ ፈረሰኛ በሚጠበቁ ኬላዎች በኩል ብቻ ነው ። በአጠቃላይ የኦሮሞ የፖለቲካ ክልሎች በዚህ ሁኔታ ተቋቁመው ፊውዳሊዝምን መገንባት ጀመሩ ። በሰሜን እንደታየውም ሁሉ ጦርነቶች የገደው መደብ የመሬትና የገባሮች ጥሙን የሚያረካ በትመገደድ ስለሆኑ በተለያዩ ክልሎች መካከል ዘወትር ይደረጉ ጀመር ። በዚህም ትግል ውስጥ ተጠናክረው ከወጡት መካከል ጂማ ጀሬን የሚባለው ትልቁና ዋንኛው ክልል ነበር ።[50]

እንደማንኛውም የኦሮሞ ክልሎች የጂማ ጀሬን የኢኮኖሚ መሠረት እርሻ ነበር ። ከእርሻ ጋር ተያይዞ ያደገው የግል ንብረትም ለፊውዳሊዝም ግቶትቶት መነሻ ነበር። ስለሆነም መሬት በግል መያዝ ከመቻሉ ጋር ኅብረተሰቡ በመደብ ተከፈለ ። አባ ላፋ የሚባለው የመሬት ከበርቴ መደብና ቁብሲሳ በመባል የሚታወቁት ገባሮች የፊውዳሊዝም ሥርዓት መሠረት መያዝ ማረጋገጫ ናቸው ። ከዚህም በቀር ይህንኑ ሥርዓት ለማጎልበት ጂማጅሬን (ሁሉም የኦሮሞ ግዛቶች ይህንኑ ይከተላሉ) ትናንሽና ቆሮ በሚባሉ ክልሎች ተሸንሽኗ ። ቆሮ የኦሮሞ ግዛቶች የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የአስተዳደር አነስተኛውአካልና መሠረትም ነው ። እያንዳንዱ ቆሮ እንደገና ግሲራ በሚባሉ መንደሮች የተዋቀረ ነበር ። ጂማ ጀሬን 60 ቆሮዎች ነበሩት ። በአጠቃላይ ቆሮ በኦሮሞ ግዛቶች ላደገው ፊውዳሊዝምና ወደ ላይም ለተዘረጋው የሥልጣን እርከን መሠረት ነበር ።[51] ለምሳሌ ባሪያ ፣ ቆቴ ቡላ ፣ (እርሶ አደር ፣ ገበሬ) ፤ አባ ጃርሜ (ብያጃርሜ) አባ ሰኘ ፤ አባ ገንዳ ፤ አባ ቆሮ ፤ አባ ጅፋር ከታች ወደ ላይ ያሉ የሥልጣን እርከኖች ናቸው ። በዚህ የሥልጣን እርከን አግባብነትም አስተዳደሩና ግብሩ በቅብብሎሽ ይካሄድ ነበር ። በዚሁ ሁኔታ ያደገው የጂማ ጀሬን (ጂማ አባ ጅፋር) ኢኮኖሚም ትርፍ ምርት ከግስገኙቱ ጋር የሥራ ክፍፍሉ ሊያድግ በመቻሉ ከንግድ መምጣት ጋር ሁለንታዊ እኩያ በመታየቱ የንግድ መአከሎችና የፖለቲካ መዲናው (ጂሬን) የተደራጀ ዕድገት ማሳየት ጀምረው ነበር ። ከዚህም በላይ እንደ ሲዳማ ግዛቶችም ሁሉ ከሰሜን ኢትዮጵያ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበርው ።

በአጠቃላይ በደቡብ ኢትዮጵያ ከ1875 በፊት የነበሩት የምርት ግንኙነቶች ውስብስብ ነበሩ ። ከዚህም በላይ ደቡብ ኢትዮጵያ በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበራት የእድገት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ኅላዎችና ብሔረሰቦች የሚኖሩበት ሥፍራ ነበር ። ስለሆነም ፊውዳሊዝም እንደሰሜን በደንብ አልዳበረም ነበር ። በተጨማሪም በደቡብ ኢትዮጵያ ትናንሽ የፖለቲካ ይዞታዎች የነበሩበትና እነዚህም በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ስለነበሩ አንዳቸውም ቢሆኑ እንደሰሜኑ ወደ መጠቃለል ደረጃ አልደረሱም ነበር ።[52] ከዚህም በቀር ደቡብ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የባሪያ ንግድ ምንጭ ነበር ።

በኢትዮጵያ የማዕከላዊ መንግሥት መጠናከር

በኢትዮጵያ ሁኔታ ለተከሰተው ማዕከላዊ መንግሥት መሠረት የሆነችው ሸዋ እንደነበረች ገልጸናል (መስከረም ቁ.5) ። ሸዋ የማዕከላዊ መንግሥትን ለመምራት ያበቋት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩ ። ከነዚህም ምክንያቶች ውስጥ የመጀመሪያው ከ1769 እስከ 1855 ባለው ጊዜ ውስጥ የሰሜን መሳፍንቶችን ሲያራኩት በነበረው የሥልጣን ትግል ውስጥ የሸዋ አለመሳተፍ ነው ። ሸዋ ከዚህ ትግል መገለል የፊውዳል የፖለቲካና የኢኮኖሚ መሠረትን ሊያደራጅ በመቻሉ ለጠንካራ የገዥ መደብ ግደባ ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል ። በሌላም በኩል የሸዋ መሪዎች ከውጭ ኃይሎች ጋር የመሠረቷቸው ልዩ ልዩ ግንኙነቶች የሸዋን የበላይነት አስገኝቷል ። የዚህ የውጭ ግንኙነት ውጤትም በአንድ በኩል ሲታይ የጦር መሣሪያ ንግድና ክምችት በሸዋ ቁጥጥር ሥር እንዲውል የፈጠረው ሁኔታ ነው ። ይህም ሁኔታ የሸዋን ወታደራዊ ኃይል በዘመናዊ መልክ እንዲደራጅ አድርጓል ። በመጨረሻም ሊጠቀስ የሚገባው ምክንያት የሸዋ የጂኦ ግራፊ አቀማመጥ ነው ። ሸዋ በኢትዮጵያ ዕምብርት ላይ የተመሠረተች በመሆኗ የንግድ መስመሮችን ፤ የሕዝብ ንቅናቄዎችን ፤ የፖለቲካ ትግሎችን መቆጣጠር አስችሏታል ።

Digitized by Google

ከዚህም በላይ ይኸውማዕከላዊ አቀማመጥ ሰፊውን የኢትዮጵያ ግዛት ከመሐል ሆኖ ለመቆጣጠርና ለመምራትም አብቅቷታል ።

የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ በሸዋ አመራር የተካሄደ ቢሆንም የዚህ ምሥረታ ሂደት ከታሪካችን ጋር የተገናዘበ እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው ። በ19ነኛው ክ. ዘመን በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መንግሥት ቢቋቋምም ሂደቱ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣና ለነጻነትና ለአንድነት የተደረገ የትግል ውጤት ነው ። ስለሆነም በሸዋ የተመራው የማዕከላዊ መንግሥት የሕዝቦችና የግዛቶች ውህደት ነው ።

ከፊውዳሊዝም ወደ ደቡብ መስፋፋት ጋር ዳግማዊ ምኒልክ ከ1875 እስከ 1898 ባለው ጊዜ ውስጥ በውዴታና በግዴታ በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩትን የፖለቲካ ክልሎች አዋሀዱ ። በዚህ ውህደት ወቅት ጦርነቶች አልተደረጉም ማለት አይደለም ። ብዙ ሕዝብና ንብረት ያለቀባቸው ጦርነቶች በከፋ ፣ ወላይታ ፤ አርሲ ፤ ሐረርና ጉራጌ ተደርገዋል ። ሚኒልክ በደቡብ የነበሩትን የፖለቲካ ክልሎች በአንድ አመራር ሥር ከዋሉ በኋላ ለቁጥጥርና ለብዝበዛ የሚያመች አስተዳደር ዘረጉ ። ምኒልክ በደቡብ የዘረጉት አስተዳደር የሰሜኑን ፈር የተከተለ ነበር ። እንደሰሜኑም ሁሉ በደቡብ የተዘረጋው የአስተዳደር መሠረት ፖለቲካዊ ወታደራዊ ስለነበር የሰሜኑ የገዥ መደቦች ድጋፍ አልተለየውም ። ማርካኪስ ይህንኑ ሁኔታ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያስገነዝብ «......የመንግሥቱ መስፋት የመኳንንቱን የመሾም ዕድሎች አበዛው ። የመኳንንቱ መደብና የመሬት ይዞታቸው ያለቅጥ ሰፋ ።............ የሰሜኑ መኳንንት የደቡብም የመሬት ከበርቴ ሆነ ።» ብሏል ።[53]

የማዕከላዊ መንግሥት ምስረታን ለመፋጠንና መንግሥቱንም ለማጠናከር በደቡብ በተወሰደው እርምጃ ፊውዳሊዝም ከሰሜን ኢትዮጵያ የተለየ መልክ ይዞ በአዲስ ሁኔታ ተከሰተ ። የዚህ ዓይነት ሁኔታ መምጣትን ሪቻርድ ፓንክረስት ሲገልጹ «የጦርነቱ ፍጥነት ፤ ወታደሮችን በሥፍራው የማኖር ፍላጎት ፤ ከአዲስ አበባ ያለው ርቀት እና በአስተዳዳሪዎቹና በደቡብ ሕዝብ መካከል ያለው የባሕል ልዩነት በአንድነት ከሸዋና ከሰሜን የተለየ የመሬት ሥሪት ሊያስከትል ችሏል ።» ብለዋል[54] በዚህ መሠረት በደቡብ ኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ጭሰኝነት (የቁጥር ገባር) ከምንለው ደረጃ ደረሰ ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ለጭሰኝነት መከሰት መሠረቱ የተዘረጋው አዲስ የመሬት ስሪት ነው ። በዚህ ስሪት መሬት ከሞላ ጎደል ከሦስት ተከፈለ ። ሁለቱ እጅ ለመንግሥትና ቀሪው አንድ እጅ ደግሞ ለቀድሞዎቹ የገዢ መደቦችና ለአገሬው ተወላጆች ዋለ ።[55] ከዚህ ድልድል ጋርም ሰፊው አርሶ አደርም እየተቆጠረ ለሚኒልክ የጦር አለቆች ፣ ሹማምንቶችና ወታደሮች በሥልጣን ተዋረድ ተደለደለ ። ለምሣሌ በዚሁ ድልድል መሠረት ራሶችና ደጃዝማቾች እያንዳንዳቸው 1000 ጭሰኞች ፤ ፊታውራሪ እስከ 300 ጭሰኞች ፤ ቀኛዝማች እስከ 150 ጭሰኞች ፤ ወታደሮች (ነፍጠኞች) ከ10 እስከ 20 ጭሰኞች አገኙ ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ለተከሰተው ፊውዳሊዝም መሠረቱ ማደሪያ (መተከያ) የምንለው ስሪት ነው ። ማኅተመ ሥላሴ ማደሪያ የሚባለውን ስሪት ሲገልጹ «መንግሥት የሚያዝበት ካንዱ ወደ ሌላው የሚዘዋወር ማለት ነው ። በየደንቡ የመንግሥት አሽከር ስለ ደመወዝና ቀለብ ማደሪያ አድርጎ የሚበላው ነው ። የመሬቱም ልክ እንደ ሰውነቱና እንደ አገልግሎቱ መጠን ከአንድ እስከ ሦስት ጋሻ ይደርሳል ። ሹማምንት ከሀምሳ አለቃ እስከ ሻምበልነት ድረስ ከ10 እስከ 30 ጋሻ ተቀብለው ማደሪያ አድርገው ይኖራሉ ። በዚህም ዓይነት በየወረዳው ሁሉ የመንግሥት አሽከር ተተክሉ ይገኛል» ፣[56] እንዳሉት ሁሉ አርሶ አደሩ በዚህ ድልድል መሬቱን ከመነጠቁም በላይ በጭሰኝነት ሥርዓት ቀንበር ሥር ወደቀ ። ጭሰኛ የሚባለው የደቡብ አርሶ አደር «ለመልከኛው እንደ ውለታው ዐይነት የጉልበት ሥራ ፤ ማር ፣ ወይም ጨው ይከፍላል ። ይኸንኑም የጭሰኛ ምድር መልከኛው ርስት አድርጎ የተከለው እንደሆነ ሊሸጠው ሊለውጠው ይችላል ፤ በሪምነት በቁጥር የተተከለ ጭሰኛ ግን እንደ ውለታቸው መልከኛ ተነሣ ባለው ጊዜ ይለቃል ። በማደሪያውም የያዘ መልከኛ ከማደሪያው ሁዳድ እየከፈለ ለጢሰኛ ይተካል ። ይኸውም መልከኛ በሹመቱ እስከ አለ ድረስ ይዞት ይቆያል ፤ አዲስ ተሿሚ መልከኛ በገባ ጊዜ ግን ማደሪያው ስለሆነ የፊተኛው መልከኛ ጢሰኛውን ሊነቅለው ይችላል ። ግብሩንም የጉልበት ሥራ ያሠራዋል ፤ ትንሽም ገንዘብ ያስከፍ

Digitized by Google

ለዋል ።»[57] ባጭሩ የጭሰኛ ሥርዓት በደቡብ መስፈን ሰፊው ሕዝብ የኑሮ ዋስትና እንኳን ሳይኖረው ከባድ ብዝበዛ እንዲካሄድበት አደረገ ።

በደቡብ ከተደረገው የመሬት ድልድል ግብቲያ ላይ ሁለት ዋና መደቦች ተከሰቱ ። እነዚህም የጭሰኛውና የፊውዳል የመሬት ከበርቴ መደብ ናቸው ።

ጭሰኛ የሚባለው የደቡብ አርሶ አደር እንደሰሜኑ አርሶ አደር የጉልበትና የግይነት ኪራይ ይከፍላል ። ሆኖም የመሬት ባለቤትነት መብት የሌለው ፣ በማኅበራዊ ኑር ውስጥ ሊካፈል የማይችልና በማንኛውም ጊዜ የሚባረር ነው ። ከዚህም በቀር ጭሰኛው ባላባት ለሚባሉት የጥንት የጎሹ መሪዎች እርቦ ይሰፍራል ፣ ገጸ በረከት ይሰጣል ። አባ ቆሮ ሙዶም አባ ቡርቃ የሚባሉት እነዚህ ባላባቶች በደቡብ የሚካሄደውን ብዝበዛ የሚያቀናጁ ናቸው ።

ሚኒሊክ በዚህ ሁኔታ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙትን ብሔረሰቦች ያቀፈ መንግሥት ከመሠረቱ በኋላ የዚህን ግዛት ማዕከላዊነት የሚያጠናክሩላቸው መሠረቶች መጣል ጀመሩ ። ይህን እርምጃ ሰናነሳ ማስታወስ የሚገባን በወቅቱ ኢምፔራያሊዝም ወደ ኢትዮጵያ ሠርጎ መግባት መጀመሩንና ካፒታሊዝም በፊውዳሊዝም ላይ ፣ መለበጡን ነው ። በዚህ መሠረት ከኢምፔሪያሊስቶች አገር በገባው ካፒታል ተመርኩዞ የመንግሥቱን መሠረት የሚጠግኑና የሚያደራጁ መሠረተ ልማት ዘረጉ።) እነዚህም ቴሌፎን ፣ መንገዶች ፣ የሐዲድ መስመር ፣ የገንዘብ እትመት ፣ ባንክ እና ቢሮክራሲ ፣ (የሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም ናቸው ። ከተሞችም የተቋቋመውን መንግሥት እንደ ሚያገለግሉ ሆነው ተመሠረቱ ። ለምሳሌ ከ1887 እስከ 1910 ባለው ጊዜ 37 ከተሞች [58] በደቡብ ኢትዮጵያ ተቆርቁረው ነበር ። እነዚህ ምሽግ ከተሞች ስለነበሩ የፊውዳሊዝም የብዝበዛ ማጠናከሪያ ማዕከል በመሆን ለሥርዓቱ መደርጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደረጉ ።

የመአከላዊ መንግሥት ምሥረታ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ከነበረው የኢምፔሪያሊስቶች ርብርቦሽና መራኮት አንጻር ሲታይ ተራማጅ ነው ። ይኸውም የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የመጀመሪያው እርምጃ በመሆኑ በወቅቱ ኢትዮጵያን ከበውና ለመቀራመትም አሰፍስፈው ከነበሩት ኢምፔሪያሊስቶች ወረራ ፣ ጭርና ደባ ሰፊውን ሕዝብ ሊያድን በመቻሉ ነው ። ከዚህም በላይ ከኢትዮጵያዊነት ስሜት መዳበር (ብሔራዊ ንቃተ ሕሊና የሚባለው) ጋር አገሪቷ የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል መድረክ ሆና ልትቆይ የቻለችው መአከላዊ መንግሥት ለመመሥረት በተወሰደው እርምጃ ነው ። በሌላ በኩል ግን የመአከላዊ የፊውዳል መንግሥት መጠናከር ቅራኔ አዘል ሁኔታዎችን አስከትሏል ። በጭሰኛ/ገባር መሠረት ላይ የተዋቀረው መንግሥት የፊውዳል የምርት ግንኙነቶችን ለማጠናከር ባለው ፍላጎት በዘረጋው የመንግሥት አውታሮች አማካይነት ብዝበዛውን አባባሰው ። የመደብ መዋቅሩም ውስብስብና የተወገረገረ እየሆነ መጣ ። ኢትዮጵያ ብዙ ብሔረሰቦችን ያቀፈች ብትሆንም የጥቂት ብሔረሰቦች የበላይነት የሌሎች ብሔረሰቦችን ጭቆና አባባሰው ። የብሔረሰብ ጭቆና መሠረት እያገኘ መጣ ። ከዚህም በቀር ቀድሞ በአብዛኛው በዓይነት ብቻ ይከፈል የነበረው ግብር በገንዘብም እየተተካ መጣ ። ይህ በበኩሉ አርሶ አደሩ ምርቱን ለገበያ በርካሽ እንዲያቀርብ አደረገው ።

ከኢምፔሪያሊዝም ሠርጎ መግባት ጋራ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ካፒታል ባስከተለው ለውጥ የሸቀጥ ምርት ተፈላጊነት እያደገ በመምጣቱ የሰፊውን ሕዝብ ምዝበራ አባባሰው ። ከዚሁ ጋራ ተያይዞ በ1907 ሚኒሊክ ያወጡት «መሬትን መሸጥና መለወጥ አዋጅ»[59] መሬት ሸቀጥ መሆኑን አበሰረ ። በዚህም ሳብያ የፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች ወደ ከተሞች መስደድ ጀመሩ ። ከዚህ ጊዜም ጀምሮ በተካሄደው የመሬት ማካበት ዘመቻ ጥቂቱ ሀብታም አብዛኛው ሕዝብ ግን በድህነት ሊማቅቅ ቻለ ። ከዚህ በተጨማሪም የገዥው መደብ ቅንጦት እየለመደ በመምጣቱ የኑሮ ጣዕሙና የፍጆታ ዝንባሌው እየተለወጠ ሰፊውን ሕዝብ ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ መበዝበዝ ጀመረ ። ባጭሩ የዚህ ብዝበዛ መጠናከር የፈጠረው የመደብ ቅራኔ በኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ጊዜ ለታዩት የመደብ ትግሎች መሠረት ሆነ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. G.F BECKINGHAM and G. W. B. Hunting Ford • *Some Records of ETHI OPIA*, 1593-1646, London 1954-p L- Li
2. Ernesta Cerubli, *Peoples of Sw West Ethiopia and Its Border land*, London, Africa Institute, 1956.
3. V.Kelle and M. Kovalson — *Historical Materialism — An outline of Marxist Theory of Society*, Progress Publishers, Moscow, 1972, p. 99
4. Quoted in Umberto Melotti — *Marx and The Third World*, Macmillan press LTD, London, 1977, p. 29
5. Karl Marx, Grundrisse, English Translation p. 472
6. E. Cerulli, p. 45
7. E. Cerulli, p. 46
8. Barry Hindess and Paul Q Hirst, *Pre Capitalist Modes of Production*, London, p. 69 — 77
9. E. Cerulli, p. 52
10. Ibid, p. 58
11. Ibid, p. 59
12. Ibid, p. 59
13. Ibid, p. 60
14. Emmanuel Terray — Marxism and "Primitive" Societies, New York and London, 1972, p. 67
15. E. Cerulli — p. 85
16. Ibid, p. 91
17. Ibid, p. 91
18. Karl Marx and Frederick Engles, Selected Works, Progress Publishers, Moscow, 1970, Vol. III p. 277
19. Historical Materialism Basic Problems— (unspecified Publishing Date and Author) p. 160
20. Karl Draper — Karl Marx's Theory of Revolution — *State and Bureaucracy*, *Monthly Review Press*, New York and London, 1977, p. 252
21. Draper, p. 537
22. Quoted in Umberto Melotti p. 54
23. Tri continental — No. 67, 68, Habana, Cuba, 1980, p. 126
24. G.W.B. Hunting Ford — *The Galla of Ethiopia — The Kingdoms of Kafa and Janjero*, London, International Africa Institute, 1955, p. 109
25. Ibid — p. 111
26. " p. 111
27. " p. 122
28. " p. 124
29. ይልማ ዴሬሳ—የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ፤ አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 1959 ፤ ገጽ 213
30. በዚሁ መጽሐፍ ፤ ገጽ 215
31. Von Eike Haber land, Galla Sud — *ATHIOPIENS*, Stuttgart, 1963, p. 773
32. Ibid, p. 777
33. Karl Marx and F. Engles; Selected Works, Vol. 3, p. 518
34. Historical Materialism Basic Problems, p. 160
35. D.I. Valentey, *An Outline Theory of Population*, Progress, Moscow, 1977, p.39
36. ይልማ ዴሬሳ ፤ ገጽ 225
37. በዚሁ መጽሐፍ ፤ ገጽ 225
38. በዚሁ መጽሐፍ ፤ ገጽ 225
39. Herbert S. Lewis, *A Reconsideration of The Socio-Political System of the Western Galla*, Journal of Semetic Studies, Extract from, Vol. 9, No. 1, 1964 p. 139
40. J.S. Trimingham, *Islam in Ethiopia*, Frank Call; London, 1976, p. 94
41. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ የግራኝ አሕመድ ወረራ ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1966 ገጽ 809
42. Herbert S. Lewis; *Historical Problems in ETHIOPIA and the Horn of Africa*, Reprinted From *ANNALS OF THE NEW YORK ACADEMY OF SCIENCES*, Vol. 96 Article 2, January 20, 1962, p. 506
43. Karl Marx, *A Contribution to the Critique of Political Economy*, Progress Publisher Moscow, 1977, p. 202 — 203
44. Mordechai Abir, Ethiopia — *The Era of The Princess*, Longmans, London, 1968, p. 75
45. Historical Materialism — Basic Problems, p, 160
46. Ibid, p, 161
47. Karl Marx and Frederick Engles, Selected Works, Vol. 3 p. 326
48. Abir, p. 75
49. Herbert S. Lewis — A Reconsideration......, p. 142
50. Abir, p. 91 - 92
51. Ibid, p. 83
52. Legesse Lemma, *Political Economy of ETHIOPIA* 1875 — 1974; Agricultural, Educational and International Antecedents of the Revolution, (unpublished Doctrate Dissertation) 1979, p. 46 - 7
53. John Markahis, Ethiopia — *Anatomey of A Traditional Polity*, Oxford University Press, Addis Ababa, 1974 p. 90 - 91
54. Richard Pankhrust, *State and Land in Ethiopian History*, Oxford University Press, Addis Ababa, 1966, p. 136
55. Markakis, p. 108
56. ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ፤ ዝክረ ነገር ፤ አዲስ አበባ ፤ 1942 ፤ ገጽ 114
57. በዚሁ መጽሐፍ ፤ ገጽ 218
58. Hist. Miscallanea — No. 13, *Urban Development in Ethiopia*, Ethiopian Studies, p. 2 - 10
59. Richard Pankhrust, p. 156 - 162

Digitized by Google

Digitized by Google

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

MC OVER
85
...ION

- የሰላም ጥያቄና ዴታንት
- የእብሪተኞች ባዶ ጩኸትና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት
- ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ወደ ኋላቀር አገሮች ካፒታል የሚዛመትባቸው መልኮች
- ባሕልና ንድፈ ሃሳባዊ ግንዛቤው

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕየተዓለም መጽሔት
ቅጽ 2 ቁጥር
መጋቢት 1974

Digitized by Google

Digitized by Google

ቘ2623QP
9.
Meskerem

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 8
መጋቢት 1974

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

▲ የዝግጅት ገጽ 3

▲ የሰላም ጥያቄና ደታንት 13

—ሰለሞን ብርሃኔ

▲ የአብሪተኞች ባዶ ውኸትና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት 24

—ተስፋዬ አብዲ

▲ ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ወደ ኋላቀር አገሮች ካፒታል የሚዛመትባቸው መልኮች 37

—አያሌው ከበደ

▲ ባህልና ንድፈሃሳባዊ ግንዛቤው (ክፍል 2) 52

—መሐመድ ማላ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ያለ አብዮቲዊ ንድፈ ሃሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም !

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ባህሪ መባባስ

ኢምፔሪያሊዝም አሁን በደረሰበት ደረጃ በሦስት ዋና ዋና ቀውሶች ተወጥሮ ይገኛል። ለመጀመሪያውና ለመሠረታዊው ቀውስ መነሻ የሆነው ዓለም በሁለት ተጻራሪ ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች መከፈሏ ነው። ይህ እውን የሆነው በታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት ቢሆንም፣ በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ሶሺያሊዝም የዓለም አቀፍ ሥርዓት ለመሆን በመቻሉ የኢምፔሪያሊዝምን ቀውስ በከፍተኛ ደረጃ እያከረረው መጥቷል። ከዚህም አልፎ በአሁኑ ጊዜ የሶሽያሊስት ማኅበረሰብ አገሮች ቁጥር እየጨመረ፣ የኢኮኖሚና የወታደራዊ ኃይላቸው እየዳበረ፣ የሶሻሊዝም ዓለምአቀፋዊ ተጽዕና እየጐለበተ በመምጣቱ፣ ይህ ሁኔታ ኢምፔሪያሊዝምን ሊወጣው ከማይችልበት ማጥ ውስጥ ጨምርታል።

የኢምፔሪያሊዝም አጠቃላይ ቀውስ እንዲያመረቅዝ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች መካከል ሁለተኛው በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት መንኮታኮት ሳቢያ በዛ ያሉ ኋላ ቀር ሀገሮች ብሔራዊ ነፃነታቸውን መጐናጸፋቸው ብቻ ሳይሆን፣ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ከኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ለመላቀቅ የሶሽያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል የሚያካሂዱት ትግል መጧጧፍ ነው።

ካፒታሊዝም የዓለም አቀፍ ሥርዓት ሆና እንዲዳብር ካስቻሉት ምክንያቶች አንዱ ዓለምን በሞላ በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ሥር ማድረጉ መሆኑ የታወቀ ነው። ለዚህም የእንግሊዝ የቡርዧ መደብ የብሪታንያ የበላይነት ሰፍና በነበረበት ወቅት «በብሪታንያ ሥርወ መንግሥት ሥር ፀሐይ አትጠልቅም» በማለት ይደነፋ እንደነበረ ማስታወሱ በቂ ሊሆን ይችላል። የቅኝ ግዛት ሥርዓት ለካፒታሊዝም ዕድገት ወሳኝ የነበረውን ያህል ለኢምፔሪያሊዝምም ሕልውና ወሳኝ ነው። ወሳኝነቱም የሚለካው ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያደርሱ እየታወቀ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ዓለምን ደግመው ደጋግመው ለመከፋፈልና በቅኝ አገዛዝ ሥር ለማድረግ በተደጋጋሚ የዓለም ጦርነቶችን ማስነሳታቸው ነው።

በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ኢምፔሪያሊስት አገሮች የጠበቁት ውጤት ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን በሚዳክሙ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን በሶቭዬት ኅብረት የተመሠረተውን የሶሻሊስት ሥርዓት መቀልበስና በሱም አርአያነትና ድጋፍ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉ ሕዝቦችና አገሮች ለአርነት የሚያካሂዱትን ፀረ—ኮሎኒያል ትግል በአጭሩ ለመቀጨት ነበር።

ሆኖም የጦርነቱ ውጤት ኢምፔሪያሊስቶች እንደጠበቁት አልነበረም። እንዲያውም ውጤቱን ከጠበቁት እጅግ ተለይቶ አገኙት። ሶቭዬት ኅብረት የሀያ ሚሊዮን ዜጐቹዋን መስዋዕትነት በመክፈል የጀርመን ኢምፔሪያሊዝምን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣትና የፋሽስት የፖለቲካ መዋቅሩን በማፈራረስ፣ በዛ ባሉ የምሥራቅ አውሮፓ አገ

Digitized by Google

ሮች ሶሺያሊዝም እንዲመሠረት ረዳች። በምሥራቅም ቢሆን የጃፓን ሚሊተሪዝምን በማንኮታኮት ለቻይናና ለኮሪያ አብዮቶች ድል አድራጊነት ከፍተኛ ዕርዳታ አደረገች። ይህ ብቻ ሳይሆን የታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት የአበራውን የነፃነት ፋና በመከተል በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሶሺያሊዝም በአሸናፊነት በመውጣቱ፣ ለፀረ ኮሎኒያል ትግሉ ተመቻችቶ በነበረው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ በመጠቀም፣ በዛ ያሉ አገሮች ባካሄዱት ፀረ ኮሎኒያል ትግል የኢምፔሪያሊዝም የቀኝ አገዛዝ ሥርዓት ተንኮታኮተ።

በተለያየ መንገድ የሚበዘብዛቸው አገሮች መኖር ለኢምፔሪያሊዝም ሕልውና ወሳኝ በመሆኑ፣ በኃይል ላይ የተመሠረተው የቀኝ አገዛዝ ሥርዓት ቢንኮታኮትም፣ ባለው የኢኮኖሚ፣ የቴክኒዎሎጂ፣ የፋይናንስና የመሳሰሉት ሁኔታዎች የበላይነት በመጠቀም፣ በትግል ብሔራዊ ነጻነታቸውን በተቀዳጁ አገሮች ላይ የእጅ አዙር የቀኝ አገዛዝ ቀንበሩን ዘረጋ። ይህም የኢምፔሪያሊዝም የታክቲክ ለውጥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መፈረካከስ ጀመረ። የኩባና የቬትናም ሶሺያሊስት አብዮቶች ድል፣ በኋላም በአፍሪካ በእስያና በላቲን አሜሪካ የሶሺያሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች መበራከት፣ የኢምፔሪያሊዝም የደም ሥር በሆነው የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ አደጋ በማስከተሉ የኢምፔሪያሊዝምን አጠቃላይ ቀውስ ይበልጥ እያከረረው መጣ።

ኢምፔሪያሊዝም ከተዘፈቀባቸው አጠቃላይ ቀውሶችና ከእነዚህም የቀውስ ዓይነቶች መካከል በሶስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው ኢምፔሪያሊዝም አሁን በደረሰበት የመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታልዝም ደረጃ የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ በሥራ አጥነትና በዋጋ ንረት ተቀስፎ በመያዙና የኢኮኖሚውም ዕድገት እያቀለቀለ መሄዱ ነው። የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ምንም ዕድገት የማያሳይበት ደረጃ ላይ በመድረሱ በኢምፔሪያሊስት አገሮች በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መደብ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በካፒታሊስቱ መደብና በመላው ሠራተኛ ሕዝብ መካከል ያለው ቅራኔ እየተባባሰ በመምጣት ላይ ነው። ይህ ሁሉ ሲጠራቀም በአሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊዝም የደረሰበት ቀውስ ከምንጊዜውም ይልቅ እየከፋ መምጣቱን ያመለክታል። ይኸን ሁኔታ በመገምገም ነው እንግዲህ እ.ኢ.አ. በ1976 በበርሊን ከተማ በተካሄደው የአውሮፓ የኮሚኒስቶችና የሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ ኢምፔሪያሊዝም «ወታደራዊና ፖለቲካዊ ቡድኖቹንና ተቋሞችን እንዲያንሠራሩ ቢያደርግም፣ በጦር መሣሪያ እሽቅድምድም ቢገፋበትም፣ የሞኖፖሉ ችን ኢኮኖሚያዊ ውህደት ቢያጠናክርም፣ የጥገና ለውጥ በማድረግም ሆነ በጭቆና ቢጠቀምም ከገባበት ቀውስ ሊወጣ አይችልም፣» ሲል የገለጸው። ይኸ ታሪካዊ ሐቅ ቢሆንም ኢምፔሪያሊስቶች ለታሪክ ትክክለኛ ግንዛቤ ስለሌላቸውና ኑሮአቸውም ስለ ማያውቀ ሊቀበሉት አይፈልጉም።

የኢምፔሪያሊዝም ቀውስ በኢኮኖሚው ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ፖለቲካው፣ ርዕዮተዓለሙና ሥነ ምግባሩ ሁሉ ቀውስ ላይ ናቸው። ይኸ ሁኔታ አዲስ ሳይሆን ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊትና ጦርነቱ ሊነሳ አካባቢ በጥቂት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ማለትም በጀርመን በጣሊያ እንዲሁም በጃፓን የተከሰተ ነበር።

እነዚህ የሁለተኛውን ዓለም ጦርነት የቀሰቀሱ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የዓለም አቀፋን የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ክፉኛ ባናጋው ታላቁ የኢኮኖሚ ዝቅጠት (1929—1933) በመባል በሚታወቀው ወቅት ኢኮኖሚያቸው ከሌሎቹ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ይልቅ ክፉኛ ተንኮታኩቶ በነበረበት ጊዜ፣ የሚከተሉት ርዕዮተዓለም፣ ፖለቲ

Digitized by Google

ካም ሆነ ለጠቃላይ ሥነምግባራቸው ለፋሽዝም መሠረት ጣለ ። በነዚህም ለገሮች በወቅቱ ተነስቶ የነበረውን ቀውስ በኮሚኒስቶችና በዲሞክራቲክ ኃይሎች እንደመጣ በማስመሰል «ኮሚኒዝምን ለመዋጋት» በሚል መፈክር ሥር አልም ያሉ ቀኝ ለክራ ሪዎች የመንግሥት ሥልጣን ያዙ ።

በጀርመን፣ በጣሊያን እንዲሁም በጃፓን ውስጥ እነዚህ ፋሽስቶች ሥልጣን እን ደያዙ እንደዋነኛ ተግባራቸው ለርገው የወሰዱት የውስጥ ፖሊሲ ኮሚኒስቶችንና ዲሞ ክራቲክ ኃይሎችን መጨፍጨፍ ሲሆን፣ የውጭ ፖሊሲያቸው ደግሞ ቀደም ሲል በለ ንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ያጡትን የቅኝ ግዛት ማስመለስ ፣ በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ የተገነባውን ሶሻሊዝም መቀልበስና በዓለም ላይ የበላይነትን መቀዳጀት ነበር።

ይኸን ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ፋሽስቶች የወሰዱት እርምጃ በፖለቲካ ውና በርዕዮተዓለሙ መስክ ፀረ—ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ማሠራጨትና በሌሎች ለገ ሮች ላይ ጥላቻን መቀስቀስ ሲሆን፣ በኢኮኖሚው መስክ ደግሞ ኢኮኖሚያቸውን ወደ ጦር ኢኮኖሚ መቀየር ነበር ። ፋሽስቶች ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ከመቀስቀሳቸው ቀደም ብሎ በታሪክ ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መጠን የጦር መሣሪያ በከፍተኛ ደረጃና በየጊዜው በመሥራት ለከማቸተው እንደነበር ይታወሳል ። ለሁንም ቢሆን ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ታሪክ እራሱን እየደገመ ነው ።

በለሁኑ ጊዜ በሁለቱ ተጻራሪ ዓለምለቀፋዊ ሥርዓቶች ማለትም በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል በሚካሄደው ትግል የሶሻሊስቱ ማኅበረሰብ እየተጠናከረ ሲመጣ በዚያው ልክ ዓለምለቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እየተዳከመ በመሄድ ላይ ነው ። በለሁኑ ወቅት ከዓለም የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት የሶሻሊስቱ ሥርዓት ድርሻ ከካፒታሊስቱ ዓለም ለጊዜው በልጦ ባይገኝም፣ መጠኑ ከጊዜ ወደጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል ። እ.ኤ.ለ. በ1950 የሶሻሊስት ማኅበረሰብ ለገሮች ከዓለም የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ሃያ በመቶውን ብቻ ሲያመርቱ ፣ በ1975 ድርሻቸው ወደ ለርባ በመቶ ለድጓል ። በለንዳንድ የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች ሶቭዬት ኅብረት ለሚሪካንንም በልጧል። የሶቭዬትና የለሚሪካን ኢኮኖሚ ዕድገት ከሚወስኑት ነቁጦች መካከል ዋነኛውን ማለ ትም የሥራ ምርታማነትን መጣኔ ብንመለከት፣ የሶቭዬት ኅብረት ከለሚሪካ በልጦ እናገኛለን ። እ. ኤ. ለ. 1951—1975 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ለማካይ የሆ ነው ዓመታዊ የሥራ ምርታማነት የዕድገት መጣኔ በሶቭዬት ኅብረት 6.2 በመቶ ሲሆን፣ በለሚሪካ ግን 3.2 በመቶ ነበር ። ይኸ ሁሉ የሆነው በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት የሶቭዬት ኅብረት ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ነው ።

በሌላ ለንጻር በለሁኑ ወቅት የለሚሪካን ብቻ ሳይሆን የመላው የካፒታሊስት ዓለም ኢኮኖሚ ከፍተኛ ቀውስ ላይ ነው ። የዋና ዋና ካፒታሊስት ለገሮች ኢኮኖሚ ዕድገት በማቀ ልቀል ላይ ይገኛል ። ሥራ ለጥነት እየጨመረ ሲሄድ በዚያው ልክ የዋጋ ንረት እያሻቀበ በሚሄድ ላይ ነው ። ለሁን በያዝነው ዓመት በካፒታሊስት ለገሮች ውስጥ ያለው ለማካይ የዋጋ ንረት ወደ 9.2 በመቶ ተጠግቷል ። የካፒታሊስቱ ዓለም የፋይናንስ ተቋም የከረረ ቀውስ ውስጥ ገብቷል ። በለሁኑ ጊዜ በለሚሪካ ውስጥ ብቻ ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጉ ሥራ ለጦች ለሉ ። በለጠቃላይ የኢኮኖሚ ትብብርና የልማት ድርጅት ለባል በሆኑት ሃያ ለራት ካፒታሊስት ለገሮች (ለሚሪካንንም ጨምሮ) የሥራ ለጡ ቁጥር በለሁኑ ጊዜ ወደ ሃያ ስድስት ሚሊዮን እንደሚጠጋ ይገመታል ።

የኢምፔሪያሊስት አገሮች ዓለም አቀፉ ኩባንያዎች እ.ኤ.አ. ከ1970 እስከ 1978 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ከታዳጊ አገሮች በመመዝበር ያጋበሱት ትርፍ 1,218 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፣ ይህም በኢንቬስትመንት መልክ ወደ ታዳጊ አገሮች በሚያስገቡት በእያንዳንዱ የአሜሪካ ዶላር ላይ በግምት ሁለት ዶላር ከአርባ ሳንቲም አትርፈውበታል ማለት ነው። የበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ከታዳጊ አገሮች ጋር ባላቸው ያልተመጣጠነ ንግድ ሳቢያ በአሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከታዳጊ አገሮች በዓመት ወደ ሰላሳ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያህል በመዝረፍ ላይ ናቸው።

ተመሳሳይ ነቁጦችን በብዛት ለመጥቀስ ቢቻልም፤ እዚህ ላይ ለመጠቀም የተፈለገው ኢምፔሪያሊዝም የሚያካሂደውን ብዝበዛና የብዝበዛውንም መጠን አይደለም። የተፈለገው በዚህ መልክ ለኢምፔሪያሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ድጋፍ ሲሰጥ የቆየው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በዚህ መንገድ ሊቀጥል አለመቻሉንና በየቦታው እየተፍረከረከ መሆኑን፣ ይህም ሁኔታ የኢምፔሪያሊዝምን አጠቃላይ ቀውስ በይበልጥ እያፋፋመው እንደመጣ ለማስገንዘብ ነው።

የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓትን በማፍረክረክ ላይ የሚገኘውም የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ሀገሮች መበራከትና የሚያካሂዱትም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትግል በየጊዜው በኢምፔሪያሊዝም ላይ ድል እያጎናጸፋቸው መምጣቱ ነው። በላቲን አሜሪካ የኒካራጉዋ አብዮት በአሸናፊነት መውጣት፣ የኤል ሳልቫዶር ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መጠናከር፣ በአፍሪካ የኢትዮጵያ አብዮት መጠናከርና ሌሎችም የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ሀገሮች መበራከት፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የፍልስጤምንና የሌሎች ዓረብ ሕዝቦች ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—ጽዮናዊ ትግል መጠናከር፣ በእስያ የካምፑቺያና የአፍጋኒስታን አብዮቶች መጠናከር፣ ከዚህም በተጨማሪ በዓለምአቀፍ ደረጃ የፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግሉ መጠናከር፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ክልሉን በማጣበብ የኢምፔሪያሊዝምን ቀውስ ከፋና እንዲያመረቅዝ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ይህ ሁሉ ሁኔታ ተጠራቅሞ ኢምፔሪያሊዝም ቀደም ሲል በዓለም ላይ የነበረውን የበላይነቱን ያሳጣው በመሆኑ፣ የበላይነት ቦታውን ለማስመለስ በማሰብ የጦብ አጫሪነት ባህሪውን እያባባሰው በመምጣት ላይ ይገኛል። በተለይም ሬጋን ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፣ የመሣሪያ ክምችትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ከመደገፉ ይልቅ ማሰናከልን፣ አዳዲስ የወታደራዊ ጦር ሠፈሮችን መቀርቀር፣ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት አቋማቸው ጠንከር ብሎ በሚገኙ አገሮች ድንበሮች አካባቢ ለትንኮሳ የታቀደ ወታደራዊ ልምምድ ማድረግን፣ ከበባን ማጠናከር ወዘተ ... የመሳሰሉ ድርጊቶችን በመፈጸም በዓለም ላይ ለሰላምና ለደኅንነት የሚደረገውን ጥረት በማሰናከል ዓለም አቀፍ ውጥረት እንዲፈጠር የተቻለውን ያህል በማድረግ ላይ ይገኛል።

ቀደም ሲል እ.ኤ.አ. በነሐሴ 1980 የወጣውና «የፕሬዚዳንታዊ ድንጋጌ ቁጥር 59 ("*Presidential Directive No. 59*") በመባል የሚታወቀው ድንጋጌ «የተወሰነ የኒዩክሊር ጦርነት» ለማካሄድ የወጣ መመሪያ መሆኑ ይታወሳል። የሬጋን አስተዳደር በአሁኑ ወቅት በመከተል ላይ ያለው ፖሊሲ ሲገመገም ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደ ይመስላል። የሬጋን ወታደራዊ ዶክትሪን ፋሽስታዊ ብቻ

Digitized by Google

ሳይሆን ኢሉብአዊ የሆነ ዶክትሪን ነው ። በአሁኑ ጊዜ የሚሊታሪ ቴክኒዎሉጂ በደረስ
በት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ማናቸውንም ዓይነት የኒዩክሊር ጦርነት ማስነሳት ማለት
የሰው ልጅን ሕልውና መጻረር መሆኑ ግልጽ ሆና ሳለ፥የሬጋን አስተዳደር «በተወ
ሰነ አካባቢ ሊገደብ ስለሚችል የኒዩክሊር ጦርነት» በማውራት ብቻ አልተቀጠበም ።
ይህን ዓይነት «በክልል የተወሰነ» የኒዩክሊር ጦርነት ማድረግ «የሚቻል» ብቻ ሳይ
ሆን ከዚህ ዓይነት ጦርነት «በአሸናፊነት ለመውጣት» እንደሚቻልም በማናፈስ ላይ
ይገኛል ።

ሁኔታውን አደገኛና አስጊ የሚያደርገው « በክልል ሊወሰን ስለሚችል የኑክሌር
ጦርነት» የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ብቻ አይደለም ። በአሁኑ ወቀት ዓለምን ይበልጥ አስ
ጊ ሁኔታ ላይ የጣለው የአሚሪካን ባለሥልጣናች ጦርነትን በግልጽ በመጋበዝ ላይ
መሆናቸው ነው ። የአሚሪካ ፕሬዚዳንት አማካሪ የሆነው ሪቻርድ ፓይፕስ በቀርቡ
የአሚሪካንን «የተወሰነ የኒዩክሊር ጦርነት» ዓላማ በሚመለከተ በሬውተር ለቀረበለት
ቃለ መጠየቅ ሲመልስ፥ «የኮሚኒስት መሪዎች የኮሚኒስት ሥርዓታቸውን ለምዕራቡ
ዓለም በሚስማማና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መለወጥ፥ አለበለዚያም ወደ ጦርነት መሂ
ድ ይኖርባቸዋል፥ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም፥» ብሉ ነበር ። ይህ እጅግ አደገኛ የሆነ
ፖሊሲ ነው ።

የኒዩክሊር ጦር መሣሪያ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ጠንቀቀው የሚያውቁ የአ
ሚሪካ፥የሶቭዩት፥የእንግሊዝ፥የጃፓን የሌሎችም አገሮች ሳይንቲስቶች፥የሕክምና ሊ
ቆችና ፊዚሽያኖች የኒዩክሊር ጦርነት እንዳይነሳ ለመከላከል የሚደረገው ጥረት ከከ
ሸፈ፥በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ምን ያህል የሚያስከፉ ጥፋት ሊደርስ እንደሚችል
በተጨባጭ ማስረጃ በብዙ አጋጣሚዎች አብራርተዋል ። የኒዩክሊር ጦርነትን ለመከላከል
በሚል በቀርቡ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የፊዚሽያኖች ስብሰባ ላይ የቀረበው ዘገባ፥
የኒዩክሊር ጦርነት በአሁኑ ጊዜ ቢነሳ ጦርነት በተነሳ በጥቂት ሰዓታትና ቀናት ውስጥ
ብቻ ቁጥሩ ይህን ያህል ነው ብሉ ለመገመት የሚያዳግት ሕዝብ ወዲያውኑ የሚሞት
ከመሆኑም ከላይ፥ የሚተርፉትም ቢሆኑ የተቃጠሉ፥ የቀሰሉና በኒዩክሊር ራድየሽን
ለማካይነት ጤናቸው ለሁልጊዜም የተበከለ እንደሚሆን ያስረዳል ።

የሚሊተሪ ቴክኒዎሉጂ አሁን በደረሰበት ደረጃ የኒዩክሊር ጦርነት በቦታ ክልል
ሊወሰን የማይችል ከመሆኑም በላይ አንድ ጊዜ ከተነሳ የጦርነቱ ተካፋይ ያልሆኑት
የአብዛኞቹ አገሮች ሕዝቦች ከመውደማቸውም በተጨማሪ የኒዩክሊር ራድየሽን በሰው
ውስጣዊ ሕዋሳት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት የተነሳ ለወደፊቱ የሰው ልጅ የተሟላ
ዕድገት የተሰናከለ ይሆናል ።

እዚህ ላይ ስለኒዩክሊር ጦርነት አስከፊነት የገለጽነው የሚያደርሰውን ጥፋት ከፍ
ተኛነት ለማሳሰብ ብቻ አይደለም ። በአሁኑ ወቀት በሁለቱ ተጻራሪ ዓለም አቀፋዊ
ሥርዓቶች መካከል ያለው የኒዩክሊር መሣሪያ በዓይነትም ሆነ በመጠን ተመጣጣኝ
በመሆኑ፥የኒዩክሊር ጦርነት ቢነሳ አሸናፊም ሆነ ተሸናፊ ሊኖር እንደማይችልና ጦር
ነቱ ከጠቀላላ ጥፋት በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ውጤት ሊኖረው እንደማይችል
ለማስገንዘብ ነው ። በመሆኑም በሁለቱ ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች መካከል ያለው አጠ
ቃላይ የኃይል ሚዛን አለመዛባት ለዓለም ሰላም ዋስትና መሆኑ ግልፅ ነው ።

•ሶቭዩት ኅብረትና ሌሎች ሰላም ወዳድ አገሮች አሁን ያለው የኃይል መመጣ
ጠን ለሰላም ዋስትና መሆኑን በመገንዘብ የጦር መሣሪያ እሽቀድምድም እንዲቆምና

Digitized by Google

እና ያለውም ክምችት በየጊዜው ተቀንሶ፣ የጦር መሣሪያን ለመሥራት የሚወጣው መጠኑ እጅግ ብዙ የሆነ ሀብት ለኢኮኖሚ ግንባታና የሕዝቦችን ማኅበራዊ ኑሮ ለማሻሻል እንዲውል ይታገላሉ። በአንጻሩ ደግሞ ኢምፔሪያሊዝም በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በአሁኑ ወቅት የሰፈነውን የተመጣጠነ የኃይል ሚዛን ወደሱ እንዲያጋድልና የወታደራዊ የበላይነት እንዲኖረው፣ በዚህም በመጠቀም ያጣውን ዓለም አቀፋዊ የበላይነት እንደገና ለማስመለስ በመጣጣር ላይ ይገኛል።

ይህን ግቡን ለማሳካት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኢሰብአዊነቱን በገሀድ እንዲከሰት ያደረገውን፣ ሰውን እንጅ ዕቃን የማይጐዳውን የኒውትሮን ቦንብ በጦርነት ላይ ለማዋል በብዛት እንዲመረት፣ ወደ ስድስት መቶ የሚጠጉ የመካከለኛ እርቀት ሚሳይሎች በምዕራብ አውሮፓ እንዲተከሉ፣ በብዙ ሺህ ቢሊዮን የሚገመቱ አዳዲስ የሚሳይል ሲስተሞች፣ ስትራቴጂክ ቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች፣ በኒዩክሊር ኃይል የሚንቀሳቀሱ አይሮፕላን ተሸካሚ መርከቦች፣ ሚሳይል የሚወነጭፉ የውሀ ውስጥ መርከቦች (ትራይደንት ሰብማሪን) ሌሎችም የጦር መሣሪያዎች እንዲሠሩ ወስኗል። ለዚህ ሁሉ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የወታደራዊ ባጀቱ አሁን ካለው በ1.5 ቲሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲያድግ መድቧል። ይህን የሚያክል የወታደራዊ በጀትና የጦር መሣሪያ ክምችት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ አያውቅም። ይኸ ገንዘብ ለልማት ቢውል ብዙ እንዱስትሪዎችን ብዙ ሆስፒታሎችን፣ ብዙ፣ ት/ቤቶችን፤ ብዙ የልማት ተቋሞችን የኃይል ማመንጫዎችን፣ መንገዶችን ወዘተ... በመሥራት እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ከኋላ ቀርነት በማላቀቅ የብዙ ሚሊዮን ሕዝቦችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በረዳ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ የኬሚካል የጦር መሣሪያዎችን ለመሥራት ስድስት ሺህ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መድቧል።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ባሕሪ መባባስ የጦር መሣሪያ እሽቅድምድምን በማጧጧፍ ብቻ አልተወሰነም። እራሱን እንደ ዓለም የጸጥታ አስከባሪ ፖሊሲ በመቁጠር፣ በዓለም ውስጥ በየተኛውም አህጉርና አካባቢ፣ ሕዝቦች ለፍትሕና ለማኅበራዊ ለውጥ፤ አገሮች ለነጻነትና ለእኩልነት የሚያካሂዱትን ትግል ለማጨናገፍ በመቀበዝበዝ ላይ ይገኛል።

— የኩባን የሶሻሊስት ግንባታ ጥረት ለማሰናከልና በኩባ ላይ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ውጥረት ለመፍጠር የሚያካሂደው የፀረ—ኩባ ዘመቻ፤

— በፖላንድ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ለፀረ—ሶሻሊስትና አድኃሪ ኃይሎች የሚሰጠው የፕሮፓጋንዳና የማቴሪያል ድጋፍ፤

— የሊቢያን የባሕር ክልል በመጣስና፣ የጦር አይሮፕላኖቹዋን መትቶ በመጣል የፈጸመው ያገጠጠ ትንኮሳ፤

— የኮሪያን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአየር ክልል በተደጋጋሚ በስለላ አይሮፕላኖቹ በመጣስ የሚፈጽመው የጠብ አጫሪነት ድርጊት፤

— የኤልሳልቫዶርን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማፈን በዚያ አገር ውስጥ ለሚገኘው ፋሽስታዊ አገዛዝ በገፍ መሣሪያ በማቀበል የሚያስፈጽመው ዕልቂት፤

Digitized by Google

— በሬጋን አስተዳደር አይዞህ ባይነት ደቡብ አፍሪካ በአንጐላ ላይ የከፈተው የወረራ ጦርነትና አልፎ አልፎም በሞዛንቢክ እና በዛምቢያ ላይ የሚፈጽመው የውንብድና ተግባር ፤

— የፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር በማደራጀት በተራማጅ አገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት መዘጋጀትና በየቦታው አዳዲስ የጦር ሠፈሮችን ማቋቋም ፤

— በኢትዮጵያ፡ በሊቢያና በዲሞክራቲክ የመን ላይ የተቃጣ፡ በአሜሪካን አስተባባሪነት ፡ በአካባቢው አድኃሪ መንግሥታት ተባባሪነት በቅርቡ የተካሄደው «ብራይት ስታር» በመባል የታወቀውና ሆን ተብሉ ለትንኮሳ የታቀደው የጦር ልምምድ ፤

— በካምፑቺያና በአፍጋኒስታን ለፀረ—አብዮት ኃይሉች በቀጥታና በእጅ አዙር የሚሰጠው ድጋፍ ወዘተ . . . ሁሉ በቅርቡ በሬጋን መሪነት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን ሰላም ለማደፍረስና ጥፋት ለመጋበዝ የወሰዳቸው እርምጃዎች ናቸው ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የጠብ አጫሪነት ድርጊቶች የሚያመለክቱት ተስፋ የማይቆርጠው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዓለምን በሱ ፍላጐት አንጻር ለመቅረጽ እንደገና በአዲስ መንፈስ የተነሳሳ መሆኑን ነው ።

የኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ባሕርይ እየተባባሰ መምጣቱ ሌኒን ቀደም ሲል «ኢምፔሪያሊዝም ማለት ጦርነት ማለት ነው» ሲል ያስቀመጠውን ትክክለኛ አባባል ያስታውስናል ። በተለይም በአሁኑ ወቀት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ሰላምን ለማደፍረስ ብቻ ሳይሆን ዓለምን ወደ አጠቃላይ ጥፋት ለማምራት በመወራጨት ላይ ስለሚገኝ ለዓለም ሰላም የቆሙ ኃይሉች በሙሉ አንድነታቸውን በማጠናከር ፡ ለሰላም የሚያደርጉትን ትግል በይበልጥ ማፋፋም ይኖርባቸዋል ።

ሶሻሊስትና ተራማጅ ሀገሮች እንዲሁም በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ዲሞክራሲያዊ ኃይሉች ለሰላም የሚያደርጉትን ትግል እያጠናከሩ በመጡ ቁጥር የኢምፔሪያሊዝም የጦረኛነት ባህሪ ለዓለም ሕዝቦች በሙሉ ቁልጭ ብሉ በመታየት ላይ ነው። በዓለም ላይ በአሁኑ ወቀት ለተፈጠረው ከፍተኛ ውጥረት በኃላፊነት ከመጠየቅ ለማምለጥ ፡ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሶቭዩት ኅብረትን ለውጥረቱ መነሻ እንደሆነ አድርጐ ለማቅረብ ይሞክራል ።

የጦር መሣሪያ ክምችትን ለመቀነስ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ውይይት ሲካሄድበት ቆይቶ በመጨረሻ በካርተር አስተዳደር ወቀት የተፈረመውንና የጦር መሣሪያ ክምችትን ለመቀነስ በተደረገው ጥረት ረገድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን የሶልት ሁለት ስምምነት የተለያዩ ተልካሻ ምክንያቶች በመስጠት እስካሁን እንዳይጸድቅ ያደረገው እራሱ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሆኖ ሳለ ፡ በኒኩሊር መሣሪርያ መጀመርያ መጠቀምን ለማውገዝ በሶቭየት ህብረት የቀረበውን ሃሳብ ውድቅ ያደረገው የአሜሪካ መንግሥት ሁኖ ሳለ ፡ የኒኩሊር መሣሪያዎችን ዓይነትና ጥራት በየጊዚው በማሻሻሉ ረገድ ወሳኝ የሆነውን የኒኩሌር መሣርያዎች ሙከራ ለማስቀረት የተጀመረውን ጥረት በገሃድ በማሰናከል ላይ ያለው የአሜሪካ መንግሥት ሁኖ ሳለ ፡ በአሁኑ ጊዜ በጀኔቭ፡ በአውሮፓ የመካከለኛ ርቀት የኒዩክሌር ሚሳይሉችን መጠን ለመቀነስ በመካሄድ ላይ ያለውን ውይይት እንዲሁ በተልካሻ ምክንያት ለማቋረጥ በመዛት ላይ ያለው እራሱ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሆና ሳለ ፡ በአሁኑ ወቀት በዓለም ውስጥ ለተፈጠረው አደገኛ ውጥረት ሶቭዩት ኅብረትን ተጠያቂ ለማድረግ አይችልም ።

Digitized by Google

የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት የሶቪዬት አቋም ግልጽ ነው። ይኸውም በአሁኑ ወቅት በሶቪዬት ኅብረትና በአሜሪካ መካከል ያለው የኒዩክሊር ኃይል ሚዛን ተመጣጣኝ የሆነ ደረጃ ላይ በመድረሱ የዚሁ ሚዛን ተመጣጣኝነት እንዳለ እንዲጠበቅና ተጨማሪ የኒዩክሊር መሣሪያዎች ሥራ እንዲቆም፣ ያለውም ቢሆን በስምምነት በሁለቱም በኩል በእኩል መጠን እየተቀነሰ እንዲሄድ የሚል ነው። ሐቁ ይህ ለመሆኑ በዋርሶና በኔቶ የጦር ቃል ኪዳን አባል አገሮች መካከል ስላለው የወታደራዊና የጦር መሣሪያ የኃይል ሚዛን የሚያጠኑ እንደ ስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲቲዩት ያሉት ምዕራባውያን ድርጅቶች የሚያረጋግጡት ነው። ይሁንና የሬጋን አስተዳደር ጆሮ ዳባ ልበስ በማለትና ለሰላም የሚደረገውን ጥሪ ከምንም ባለመቁጠር የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ቀደም ሲል ያጣውን ዓለም አቀፍ የበላይነት አስመልሳለሁ በሚል ድንፋታ የጦር መሣሪያ እሽቅድምድምን ተያይዞታል።

የሬጋን አስተዳደር ስለ ጦርነት ያለው ዶክትሪን የተዛባ የመሆኑን ያህል ስለ ሰላምም ያለው ዶክትሪን ትክክል ሊሆን አይችልም። ሬጋን በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የማይፈልግ መሆኑን በገሀድ ከድርጊቱ ለማወቅ ቢቻልም፣ ስለሰላም ያለውን አመለካከት እንመልከት። ሬጋን በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ አሜሪካ ምንጊዜም በወታደራዊ ኃይሉ ብቁ ሆና መገኘት አለበት ባይ ነው። ለሬጋንና በሱ ለሚመራው የአሜሪካን አስተዳደር «ወታደራዊ ብቃት» ሲባል አሁን በሶቪዬት ኅብረትና በአሜሪካ መካከል ሰፍና የሚገኘውን የኑክሊር ኃይል ተመጣጣኝነት (Parity) እንዳለ በመጠበቅ፣ የጦር መሣሪያ ክምችትን ቀስ በቀስ መቀነስ ማለት አይደለም። ለሬጋን አስተዳደር «ወታደራዊ ብቃት» ማለት ሁልጊዜም የስትራቴጂክ ጦር መሣሪያዎችን ዓይነት ማሻሻልና ቁጥራቸውን መጨመር ማለት ነው። በሌላ በኩል የሬጋን አስተዳደር በአሁኑ ወቅት በአሜሪካና በሶቪየት ህብረት መካከል ያለው የስትራቴጂክ ጦር መሣሪያ ተመጣጣኝነት የተፋለሰና ሚዛኑም ወደ ሶቪየት ህብረት ያጋደለ መሆኑን በማናፈስ የሃሰት ፕርፓጋዳው ተያይዞታል። ይህንንም ቅጥፈት በማስታከክና የኒኩሊር ሃይል ተመጣጣኝነትን (Parity) ለማስመለስ በሚል ሽፋን፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በወታደራዊ ሃይል የበላይነትን ለመቀዳጀት አዳዲስ የኒኩሊር መሣሪያዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል።

ሁኔታው ይህ ለመሆኑ ሬጋንም ሆነ ሌሎች ከፍተኛ የአሜሪካ ባለሥልጣናች በየአጋጣሚው ከሚሰጡት መግለጫ መረዳት ይቻላል። ሬጋን ባለፈው ዓመት ማለትም በታኅሣሥ ወር 1981 በአንድ አጋጣሚ ባደረገው ንግግር ውስጥ «የበላይነትን ለመቀዳጀት ኃይላችንን ማከማቸት አለብን» ሲል፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ዊይንበርገር ደግሞ በዚያው ዓመት በሰኔ 22 ባደረገው ገለጻ፣ በቅርቡ ተሠርተው የወጡት የኒዩክሊር ሚሳይል ሲስተሞች «ለማሸነፍ ያሉን እርግጠኛ መተማመኛዎች ናቸው»፣ በማለት ደንፍቷል። በሌላ አጋጣሚ አሌክሳንደር ሂግ «ለማስጠንቀቅ ያህል ኔቶ የኒዩክሊር መሣሪያ ሊተኩስ ይችላል» በማለት መዛቱ ይታወሳል።

በዓይነቱ እየተሻሻለና በቁጥሩ እየጨመረ የሚሄደው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የኑክሊር የጦር መሣሪያ ከዚህ ዓይነት የአሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣናች ድንፋታ ጋር እንዴት ለዓለም ሰላም ዋስትና ሊሆን ይችላል?

በአንፃሩ ለሰላም የሚታገሉ ኃይሎች የሚያራምዱት አቋም «በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የጦር መሣሪያንና የወታደራዊ ኃይል ብቃትን በየጊዜው ማሻሻል» የሚለውን ሳይሆን በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን በአንድነት ለሰላም መታገል የሚለውን ነው።

Digitized by Google

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ አብዮታውያን በግንባር ቀደም የፖለቲካ ድርጅታቸው በኢሠፓአኮ አማካይነት፣ የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲና መንግሥት ለዓለም ሰላም ያደረጉትን ትግል፣ አሁንም በማቀረብ ላይ ያሉትን ትክክለኛ የሰላም ጥሪ ሙሉ በሙሉ ይደግፋሉ። በምዕራብ አውሮፓ ያሉ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ለሰላም በማድረግ ላይ ላሉት ትግል፣ የዓለም ሰላም ምክር ቤት፣ የዓለም የሙያ ማኅበራት ፌደሬሽን፣ የዓለም የዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌደሬሽን፣ ሌሎችም ለዓለም ሰላም በመታገል ላይ ላሉ ኃይሎች ሁሉ የትግል አንድነታቸውን ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከበባና ዛቻ ከተቃጣባቸው አገሮች መካከል አንደኛዋ እንደመሆኗ መጠን፣ ኢሠፓአኮ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን እያገጠጠ የመጣ የጠብ አጫሪነት ድርጊት በጥብቅ ያወግዛል። የኢትዮጵያ አብዮት ለሰላምና ለዕድገት ከቆሙ የሶሻሊስት ሀገሮች፣ ተራማጅ እና አብዮታዊ የእስያ፣ የላቲን አሜሪካና የአፍሪካ ሀገሮች እንዲሁም በኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ውስጥ ከሚገኙ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ያለውን የትግል አንድነት በይበልጥ በማጠናከር በያዘው የፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል እስከ መጨረሻው ድረስ ይገፋበታል። በአሁኑ ወቀት እየተባባሰ በመሄድ ላይ ያለው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ድርጊትም በዓለም የሰላም ኃይሎች የተባበረ ክንድ መገታት እንደሚናርበትና እንደሚገታም ያምናል።

Digitized by Google

Digitized by Google

የሰላም ጥያቄና ዴታንት

—ሰሎሞን ብርሃኔ

(ሶፕራል ሥጋ ፋብሪካ—አሥመራ)

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለዓለም ሰላም የተደረገው ትግልና ጥረት ረጂም ዕድሜ ያለው ነው ። ይሁን እንጂ ባለፉት ዘመናት ውስጥ ሰላም ሲባል ዘለዓለማዊ ሳይሆን በሁለት ጦርነቶች መካከል ያለጊዜ ሆኖ ቆይቷል ።

አሠቃቂው የጦርነት ቀለበት ሰንሰለትም ሳይበጠስ (ከጦርነት በፊት—የጦርነት ጊዜ—ከጦርነት በኋላ)ሲሽከረከር ቆይቷል። የስዊሱ ታሪክ ጸሐፊ ጂን ጃኩዊሲ ቢቤል እንዳለው በ5500 ዓመታት ውስጥ በዓለም ላይ ሰላም የሰፈነው ለ292 ዓመታት ብቻ ነው ። በአውሮፓ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ እስካሁን የ36 ዓመታት የሰላም ጊዜ የተገኘ ሲሆን ይህ በክፍለ ዓለሙ ታሪክ ረጂሙ የሰላም ጊዜ መሆኑ ነው ። በነዚሁ 36 ዓመታት ውስጥ ግን በሌሎች ክፍለ አህጉራት በተለይ በእስያ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ በኢምፔርያሊስቶች ቆስቋሽነትና ተሳታፊነት ወደ 150 የሚጠጉ የአካባቢ ጦርነቶች ተካሂደዋል ፣ በአንዳንድ አካባቢ ጦርነቶች አሁንም እንደቀጠሉ ናቸው ።

በዓለማችን ውስጥ በተለያየ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ትላልቅና ትናንሽ መንግሥታት ይገኛሉ ። አንዳንዶቹ የኑክሌር የጦር መሣሪያ ባለቤት ሲሆኑ ፣ ሌሎቹ የላቸውም ። ከፊሎቹ ለረጂም ጊዜ የተጠናከረ የጦር ኃይል ያላቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ብሔራዊ ነፃነታቸውን ከተቀዳጁ ወዲህ ገና የራሳቸውን የጦር ኃይል በመገንባት ላይ ይገኛሉ ።

እነዚህ አገሮች ሁሉ በድምሩ « በዓለም ሰላም እንዲሰፍን እንመኛለን » የሚሉ ቢሆኑም ፣ እስካሁን ከታየውና አሁንም ካለው ተጨባጭ የዓለም ሁኔታ የትኞቹ በርግጥም ለዓለም ሰላም እንደታገሉና የትኞቹ ለጥ

ፉት ጦርነት እንደሚዘጋጁ ለመረዳት አያ ዳግትም ።

ቀንደኞቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮችና በሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድር ጅት (ናቶ) ሥር የተሰበሰቡት የካፒታሊ ስት አገሮች ሰላምን የሚያውቁት ከዓለም አቀፍ የመደብ ጥቅማቸው አኳያ ነው ።

ዩን ወደእምዩ » « የእንቶኔን እከክ ወደእ ንቶኔ ልከክ » በማድረግ ሶሻሊስት አገሮች ለጦርነትና ለወረራ እየተዘጋጁ እንደሆነ አድርገው ይለፍፋሉ ። ሀቁ ግን የዚህ ተጻ ራሪ ነው ።

በታሪክ ውስጥ እንደታየው በጦርነትጊዜ ከፍተኛ ጉዳት የሚደርስበትና ዋንኛውን የጦርነት መቅሰፍት በቀጥታም ሆነ በተዘ

ጦርነት ምን ያስከትላል ?		
አንደኛው የዓለም ጦርነት	የሞቱ ሰዎች 10 ሚሊዮን አካለ ጎደሎ የሆኑ ሰዎች 20 ሚሊዮን	ወጭ ከ260 እስከ 360 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር
ሁለተኛው የዓለም ጦርነት	የሞቱ ሰዎች ከ50 ሚሊዮን በላይ አካለ ጎደሎ የሆኑ 90 ሚሊዮን	ወጭ ከ3300 ቢሊዮን እስከ 4000 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር
እ.ኤ.አ. ከ1946 ጀምር እስከ አሁን ድረስ በዓለም ውስጥ በግምት 150 ያህል ጦርነቶች ተካሂደዋል ።	የሞቱ ሰዎች ከ10 ሚሊዮን በላይ	ባለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት እነዚህን ጦርነቶች ለማካሔድና የጦር መሣሪያ ለማከማቸት በዓ ለም አቀፍ ደረጃ 7550 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጭ ሆኗል ።

Supplement to New Times, A Survey, January, 1982

ለነዚህ አገሮች ሰላም ሲባል ከጦር መሣሪያ ሽያጭ የሚያገኙትን ከፍተኛ የሞኖፖል ትርፍ የሚገረር መሆን የለበትም ። ለነዚህ አገሮች ሰላም ሲባል ስቅኝ አገዛዝና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ከያዟቸው ኋላቀር ሀገሮች የሚቦጠቡጡትን ጥሬ ሀብትና ርካሽ ሸቀ ጣሸቀጦቻቸውን የሚያራግፉበትን ገበያ የሚነካ መሆን የለበትም ። በሌላ ወገን ሶሻሊስት አገሮች ለሰላም ያላቸው አቋም ግልጽና የማያሻማ ነው። ሶሻሊዝምና ሰላም አይገነጣጠሉም ። ይህ የሚባለው ያለምክ ንያት አይደለም ። እንደሚታወቀው በሶሻ ሊዝም ውስጥ የምርት ማከናወኛዎች የጋራ (ማኅበራዊ) ሀብት ናቸው ። ይህም ማለት በዚህ ሥርዓት ውስጥ ለትርፍ ያለ ፍላጐት የጦርነት ምንጭ አይደለም ። ኢምፔሪያሊ ስቶች በዚና ማሠራጫዎቻቸው « የአብዮ

ጥፋሪ መንገድ የሚቀምሰው ሠራተኛው ሕዝብ ነው ። አንድ ሀገር የሌላውን ሀገር በወረራ በመያዝ አሸንፎ ትኝ ግዛት በመ መሥረቱ የአሸናፊው ሀገር ሠራተኛ ሕዝብ የሚያገኘው ጥቅም፣እስከ ዛሬ በዓለም ታሪ ክ አልነበረም ወደፊትም አይኖርም ።

ከዚህ ሀቅ ስንነሳ ሠራተኛው ሕዝብ ከጦ ርነት የሚያተርፈው እልቂትንና ችግርን ብቻ እንደሆነ እንረዳለን ። ስለዚህ ይህ መደብ ሥልጣን በያዘባቸው ሶሻሊስት ሀገ ሮች ሕዝቡና መንግሥቱ ለጦርነት ሳይሆን ለሰላም እንደሚታገሉ ያለው ታሪካዊና ነባ ራዊ ሐቅ በርካሽ የፕሮፓጋንዳ ጋጋታ ሊሸ ፈን አይችልም ። በሶሻሊስት አገሮች የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች እንዳሉ የሚካድ አይ ደለም ። እነዚህ አገሮች የጦር መሣሪያዎ

Digitized by Google

ችን እያሻሻሉና ዘመናዊ እያደረጉ መሆና
ቸውንም ሆነ የመከላከያ ኃይላቸውን
እያጠናከሩ እንደሆን የሚሸፈን አይደለም።
ይሁን እንጂ ይህን ማድረጋቸው በራሱ ግባ
ቸው ሳይሆን እያነጠጠ የመጣውን የኢም
ፔሪያሊዝም የወራ ስጋት ለመከላከል እን
ዲያስችላቸው ነው ።

በ1950ዎቹ ዓመታት በምሥራቁና በም
ዕራቡ መካከል ተፈጥሮ በነበረው ቀዝቃዛ
ጦርነት በዓለም ላይ ከፍተኛ ውጥረትና
ስጋት አንዣቦ ነበር። በምዕራቡ ክፍል ያሉ
መንግሥታትና የፖለቲካ ኃይሎች የጦር
መሣሪያን በከፍተኛ መጠንና ዓይነት እያ
መረቱ በመምጣታቸው በመንግሥታትና
በሕዝቦች መካከል ከፍተኛ ስጋትና አለመ
ተማመን ተፈጠረ ። ይህን እየተባባሰ የመ
ጣውን ውጥረት ለመቀነስና ለማርገብ ዴታ
ንት (የውጥረት መርገብ) አማራጭ የማይገ
ኝለት ፖሊሲ ነበር ።

ይህ ፖሊሲ የአንድ ወይም የተወሰኑ ሀገ
ሮችን ጥቅም ብቻ የሚያስከብር ፖሊሲ
ሳይሆን በተለያየ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ
የሚገኙ ሕዝቦች በሰላም አብሮ ለመኖር
የሚያስችላቸው ፖሊሲ መሆኑ ቢታመንበ
ትም ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች መሪነት
እያደገ የመጣው የጦር መሣሪያ ክምችትና
እሽቅድምድም በአሁኑ ወቅት ዴታንትን
እየተፈታተነው ነው ።

በዓለም ላይ እስካሁን የተደረጉት ፖለቲ
ካዊ ስምምነቶችና ድርድሮች በሰላም አብሮ
ለመኖር የሚለውን መርህ ተግባራዊ ለማድ
ረግ የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።
በነዚህም ስምምነቶች አማካይነት በዓለም
ላይ አመቺ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲፈጠር
የሚቻለው ጥረት ሁሉ ተደርጎ ቀድሞ ከነበ
ረው ሁኔታ የተሻለ ዓለም አቀፋዊ ግንኙ
ነትን መፍጠር ተችሎ ነበር። ከዚህ አኳያ
እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፖለቲካዊ ዴታንት
በደህና ሁኔታ ላይ ቢገኝም ወታደራዊ ዴታ
ንት ግን አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል ። በዚህ
ሁኔታም ከፖለቲካዊ ዴታንት ይልቅ ወታ.
ደራዊ ዴታንትን ተግባራዊ ማድረግ አስ
ቸጋሪ እየሆነ ሄዷል ።

የወታደራዊ ዴታንት ተግባራዊ መሆን
የሞኖፖል ካፒታልን የመደብ ጥቅምና
የኢምፔሪያሊስት ሀገሮችን የአስተዳደር
መዋቅር በቀጥታ የሚነካ በመሆኑ ፣ ይህ
ፖሊሲ ተግባራዊ እንዳይሆን እነዚህ ሀገ
ሮች የማያደርጉት ጥረት የለም ። በዘመና
ችን ገና የሚታየው የጦር መሣሪያ እሽቅድ
ምድም የዚህ ጥረታቸው ዋነኛ መሣሪያ
ነው ።

የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም የታሪክ
ሂደትን ለመጉተትና ካፒታሊዝምን ከማኅ
በራዊ.ለውጥ ለማዳን በአብዮታዊ ኃይሎች
ላይ ተጽእና ለማድረግ የአድኅሮት ኃይሎች
የሚጠቀሙበት ዓይነተኛ የመደብ መሣሪ
ያቸው ነው ። ኢምፔሪያሊዝም ባለፉት ዓመ
ታት በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ
የደረሰበትን ክሰረት በጦር መሣሪያ እሽቅ
ድምድም ለማቻቻል የተቻለውን ሁሉ ያደ
ርጋል ። ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ ወታደ
ራዊ ዴታንትን ተግባራዊ ለማድረግ ውስ
ብስብና አዳጋች ሁኔታዎች ያጋጥማሉ ።

ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዴታንት የአን
ድና የተመሳሳይ ሂደት ሁለት ገጾች በመሆ
ናቸው ተገነጣጥለው አይታዩም ። የመጀ
መሪያዎቹ የወታደራዊ ዴታንት ፍሬያማ
ርምጃዎች ሊገኙ የቻሉት በፖቲካዊ ዴታ
ንት በተፈጠሩት አመቺ ሁኔታዎች ነው ።
ፖለቲካዊ ዴታንት ሊጠናከር የሚችለ
ውም ወታደራዊ ዴታንት ፍሬያማ ሲሆን
ነው ።

የኢምፔሪያሊዝም እያረጀና እያፈጀ
መምጣት የሶሻሊዝም እያደገና እያበነፈ
መሄድ የማይቀር ታሪካዊ ሐቅ ቢሆንም፣በአ
ሁኑ የዓለም ሁኔታ ሶሻሊስት አገሮች ኢም
ፔሪያሊዝምን በጦር መሣሪያ እንወዳደር
ብለው አይጋብዙም ። በአንፃሩ ግን በሰላም
አብሮ መኖር በሚለው መርህ ሥር በዓለም

Digitized by Google

ላይ ሰላም እንዲሰፍን የውይይት መድረኮችን በመፍጠር የሰላም ስምምነቶች እንዲገኙ የሚቻለውን ሁሉ ይጥራሉ ።

የለየላቸው የኢምፔሪያሊስት አፈቀላጤዎች ዴታንት «የሕልም እንጀራ» የሆነ ተግባራዊ ያልሆነ ፖሊሲ እንደሆነ ሲለፍፉ የግራ ተስፈንጣሪዎች የነበሩት የቻይና ኰሚኒስት ፓርቲ መሪዎች ደግሞ ቀደም ሲል ለሰላም የሚደረገው ድርድር በዓለም ላይ እንደሚደረግ ድርድር አድርገው ሲያናፍሱ ከቆዩ በኋላ ፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የቻይና ኰምኒስት ፓርቲ አመራርን የያዙት የቀኝ አድርባዮች የዴታንት ወይም የውጥረት መርገብ ሁኔታ «ለሶቭየት የበላይነት ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው» በማለት የኢምፔሪያሊስቶችን ጦረኝነት በመደገፍ ላይ ናቸው ።

ይሁን እንጂ የታሪክ ሐቅ እንደሚያረጋግጠው በሰላም አብሮ መኖር የሚለው መርህ ኢምፔሪያሊዝም ከአፍንጫ እስከ ጥፍሩ በረቀቁ የጦር መሣሪያዎች በታጠቀበት በዚህ የውጥረት ዘመን ትክክለኛ የሶሻሊስት ኃይሎች መርህነቱ እየተከሰተ ከመሄዱም ሌላ ፣ እስካሁን በዓለም ላይ የተሄዱት በርካታ የጦር መሣሪያ ቅነሣ ስምምነቶችም ለዓለም ሰላም ፍሬያማ ውጤቶችን አስገኝተዋል ።

እስካሁን ከተደረጉት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንዳንዶቹን በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል ።

የአንታርክቲክ ስምምነት

ይህ ስምምነት በ1961 (እ.ኤ.አ.) የተደረገ ሲሆን ፣ በስምምነቱም መሠረት የአንታርክቲክ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ለሰላማዊ አገልግሎቶች እንዲውል ተደንግጓል ። ከዚህም በላይ ስምምነቱ በአንታርክቲክ አካባቢ ወታደራዊ ጦር ሠፈሮችን ማቋቋም የጦር መሣሪያን ማከማቸትና ወታደራዊ ልምምድ ማድረግን ይከለክላል ።

በከባቢ አየር ፣ በጠፈርና በባሕር ወለል የኑክሌር መሣሪያዎች ሙከራ እንዳይደረግ የተደረገ ስምምነት ።

ይህ ስምምነት የመጀመሪያው የኑክሌር መሣሪያ ቅነሳ ስምምነት ሲሆን፣ ስምምነቱ ቻይናና ፈረንሣይን ሳይጨምር በ100 ሀገሮች ተደጋፊነትን ያገኘ ነው ። ስምምነቱ በነዚህ ሀገሮች በ1963 (እ.ኤ.አ.) የተፈረመ ሲሆን ፣ ዋንኛ ፍሬ ውሎቹም በዓለም ውስጥ የኑክሌር መሣሪያ እንዳይስፋፋና የመሬት ከባቢ አየርም በራዲዮ አክቲቭ እንዳይበክል የሚደነግጉ ናቸው ።

የጠፈር ምርምርንና ጠፈርን ለሰላማዊ ገልጋሎት ለማዋል የተደረገ ስምምነት ።

ይህ የጠፈር ስምምነት በ1967 (እ.ኤ.አ.) የተደረገ ሲሆን በስምምነቱም መሠረት ለመሬት ቅርብ በሆኑ የጠፈር አካላት ላይ የኑክሌር የጦር መሣሪያዎች እንዳይጥከሩ ፣ እንዳይከማቹና የጦር ልምምዶችም በጠፈር ውስጥ እንዳይደረጉ ይከለክላል ።

በላቲን አሜሪካ የኑክሌር የጦር መሣሪያዎችን መሥራትና ሙከራ የሚከለክል ስምምነት ።

ይህ ስምምነት እያንዳንዱ የላቲን አሜሪካ ሀገር በራሱ ጥረትም ሆነ በውጭ ድጋፍ የኑክሌር የጦር መሣሪያ በሀገሩ ውስጥ እንዳይሠራ ሙከራ እንዳያደርግ ወይም ሙከራ እንዲደረግ ለውጭ ኃይል ሀገሩን እንዳይፈቅድ የሚደነግግ ስምምነት ነው። ይህ ውል እንደ ብራዚልና አርጀንቲና ባሉ የላቲን

Digitized by Google

አሜሪካ ሀገሮች በመጣሱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን ባይችልም ሶቭዬት ኅብረት እንደገና በ1978 «ፕሮቶኮል [2]» የተባለውን ውል በተጨማሪ በመፈረሟ በአካባቢው የኑክሌር መሣሪያ አደጋና ሥጋትን በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ተችሏል ።

የኑክሌር መሣሪያዎች እንዳይስፋፉ የሚከለክል ስምምነት ፤

ይህ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስምምነት በ98 ሀገሮች የተፈረመ ሲሆን በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገውም በ1970 (እ.ኤ.አ.) ነው ። በዚህ ውል መሠረት የኑክሌር የጦር መሣሪያዎችና ሌሎችም የኑክሌር መሣሪያዎችን የኑክሌር መሣሪያ ለሌላቸው አገሮች ማስተላለፍን ወይም ራሳቸው እንዲሠሩ ማገዝን ፣ ወይም የሌላቸው ሀገሮች ካላቸው ሀገሮች መቀበልን ይከለክላል ። በስምምነቱም ላይ ዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ድርጅት የኑክሌር ኃይልን ለሰላም ግዊ ገልጋሎቶች እንዲውል እንዲቆጣጠርና ውሉንም እንዲያስፈጽም ተወስኖአል።

የኑክሌር የጦር መሣሪያዎችና ሌሎችም የጦር መሣሪያዎች በባሕር ውስጥ እንዳይከማቹ የሚደነገግ ስምምነት ፤

ይህ ስምምነት በ1972 (እ.ኤ.አ.) የተፈረመ ሲሆን ፣ በስምምነቱም መሠረት ከላይ የተጠቀሱት ዘመናዊ መሣሪያዎች በባሕርና በውቅያኖስ ወለል ላይ እንዳይከማቹና እንዳይሞከሩ የሚደነገግ ሲሆን ይህም የባሕርና የውቅያኖስ ውሃ በሬዲዮ አክቲቭ እንዳይበከል የሚያደርግ ስምምነት ነው ።

የባክቴሪዮሎጂካል (ባዮሎጂካል) እና የቶክሲን (Toxin) የጦር መሣሪያዎችን መመረትና መከማቸትን በመቃወም እነዚህ መሣሪያዎች እንዲጠፉ የተደረገ ውል ፤

ይህ ስምምነት ከ100 በላይ በሆኑ ሀገሮች በ1975 (እ.ኤ.አ.) የተፈረመ ሲሆን በስምምነቱም መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰው ልጅ ከፍተኛ ጠንቅ የሚሆኑትን ከላይ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች ለማስወገድ በመቻሉ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ፍሬያማ ስምምነት ነው ።

ስትራቴጂያዊ የጦር መሣሪያዎችን ለመቀነስ የተደረገ ስምምነት ሶልት 1ና 2፣

በዚህ ስምምነት ሁለቱም ወገኖች ለአገር አቋራጭ ባለስቲክ ሚሳይሎች (Inter Continental Balistic Missile Systems, ICBMS) አዳዲስ ጣቢያዎች እንዳይመሠረቱ ከመስማማታቸውም በላይ በሰብ ማሪን ላይ የሚጠመዱ ሚሳይል ላውንቸሮችንና የባለ ባለስቲክ ሚሣይል ሰብመሪኖችን ቁጥር ለመቀነስ ተዋውለዋል ። ይህ ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገው ከ1972 እስከ 1977 ሆኖ ፣ በውሉ ላይ በሌላ ሁለተኛ ተከታይ ስምምነት (ሶልት 2) እንዲቀጥል ተወስኖ ነበር ። የሶልት 2 ድርድር በ1974 (እ.ኤ.አ.) ተጀምሮ በፕሬዚዳንት ካርተር አስተዳደር ወቅት ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ፣ እስካሁን ድረስ ስምምነቱ በሬጋን አስተዳደር የጦርረኝነት መንፈስ ምክንያት ሊፀድቅ አልቻለም ።

የኑክሌር ጦርነትን ለመከላከል የተደረገ ስምምነት ፤

ይህ ስምምነት ሁለቱም ወገኖች የኑክሌር ጦርነት እንዳይነሣ በሙሉ ኃይላቸው ጥረት እንዲያደርጉ የሚደነገግ ሲሆን

Digitized by Google

ውሉ በተግባር እንዲውል የተወሰነው ከ1973 (እ.ኤ.አ.) ጀምሮ ሲሆን የሚያልቅበት የጊዜ ገደብ የለውም ። [1]

እነዚህ ውሎችና ስምምነቶች እስካሁን በዓለም ከተደረጉት ዋና ዋናዎቹና የተወሰኑት ብቻ ሲሆኑ ከዚህ ሌላ የጦር መሣሪያ ቅነሣ ጥያቄ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ስብሰባ፣ በተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያ ቅነሣ ጉባኤ ፣ በጄኔቫው የጦር መሣሪያ ቅነሣ ኰሚቴ እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያቶች በተለያዩ ቦታዎች በተካሄዱት ስብሰባዎች ሰፊ ውይይትና ስምምነት የተደረገበት ጥያቄ ነው ።

እስካሁን በተደረሱት ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ አጥጋቢ ውጤት ተገኝቷል ለማለት እንደማይቻል ሁሉ ፤ እነዚህ ስምምነቶች በሙሉ ፍሬቢስና ናቸው ማለትም አይቻልም ። ዛሬ በዓለም ገጽ አንዳንድ አካባቢዎች ከኑክሌር መሣሪያዎች ነፃ ሊሆኑ የቻሉት እነዚህ ስምምነቶች በመደረጋቸው ነው ። ኤ.ቢ.ሲ. በመባል ከታወቁት የጦር መሣሪያዎች ውስጥ አንዱና እጅግ አደገኛ የሆነው የባዮሎጂካል የጦር መሣሪያ ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ መደረጉና የኬሚካል የጦር መሣሪያዎችንም ለማስወገድ ጥረት መቀጠሉ የነዚህ ስምምነቶች ውጤት ነው ።

እነዚህ ሁሉ ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ ተከብረው በሥራ ላይ ቢውሉ ኖሮ ዛሬየሚታየው አስጊ የዓለም ሁኔታ ባልተፈጠረ ነበር ። ለስምምነቶቹ አለመከበር ምክንያት የሆኑት አሁንም በኔቶ ሥር የተሰባሰቡት የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ናቸው ።

እስካሁን ከነበረውና አሁንም ካለው አጠቃላይ የዓለም ሰላም ሁኔታ የምንረዳው የኢምፔሪያሊዝም ሕልውና ከወረራ ጦርነት ጋር የተቆራኘ እንደሆነና ለሰላም ውጥረቱም የመጀመሪያው ተጠያቂ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እንደሆነ ነው ። በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚመሩት የኔቶ አባል ሀገሮች ለዓለም ሰላም መስፈን ጥረት ከማድረግ ይልቅ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ማካበትንና ወታደራዊ ባጀታቸውን ከዓመት ዓመት በማሳደግ የጦር መሣሪያ እሽቅድምድሙን ተያይዘውታል ።

የኔቶ ወጭ

ከፍተኛ የወታደራዊ ወጭ ያላቸው አገሮች	በ1980 የነፍስ ወከፍ ፍጆታ /በዶላር/
አሜሪካ	527
ምዕራብ ጀርመን	378
ኖርዌ	335
ቤልጅየም	334
ኔዘርላንድስ	314
ብሪትን	276

በ32 ዓመታት የህልውና ጊዜው ውስጥ የኔቶ (NATO) ወታደራዊ ወጭ 3 ቲሪሊዮን ነው ። ወታደራዊ ወጭው እ. አ. አ. በ1949 19 ቢሊዮን ዶላር የነበረው በ1981 ወደ 225 ቢሊዮን ዶላር አድጓል ።

Supplement to New Times, A Survey, Jaunuary, 1982

ከታመኑ ምንጮች ለመረዳት እንደሚቻለው በዘመናችን በዓለም ውስጥ ያሉ ሀገሮች ለጦር መሣሪያ በዓመት የሚያወጡት ወጪ 400,000 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን በየቀኑ ለዚሁ የጥፋት ሥራ 100.000 ሚሊዮን ያህል የአሜሪካ ዶላር ይጠፋል ።

እ.ኤ.አ. ከ1970 ጀምሮ የአሜሪካንን የወታደራዊ ባጀት ዕድገት ምን ያህል እንዳደረሰ ከሚከተለው ማየት ይቻላል ። አሀዙ በቢሊዮን የሚቆጠር ነው ። [2]

1970	1972	1974	1976	1978
77.8	76.4	85.3	104.4	119.4

እ.ኤ.አ. ባለፈው ዓመት ማለትም በ1981 የአሜሪካ ወታደራዊ ባጀት ወደ 170 ቢሊዮን ዶላር [3] አድጓል ። ከዚሁ ጋር አያይዞ በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊ

Digitized by Google

ዝም ከሀገሩ ውጭ በመሠረታቸው የጦር ሠፈሮች ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጦር ኃይል ማደራጀቱ ለዓለም ሰላም አስጊ ሁኔታን መፍጠሩን እናያለን ።

በ1981 (እ.ኤ.አ.) በቀረበው የፔንታጎን መረጃ መሠረት የአሜሪካን የውጭ የጦር ኀይል ብዛት(ወታደሮች) 502.600 ነው ።[4] ይኸም ሲከፋፈል የሚከተለውን መልክ ይይዛል ።

1. በላቲን አሜሪካ ፤

ፓናማ ካናል ዞን	9,000
ፓርቶሪኮ	3,700
ጉዋንታናሞ	2,200
አጠቃላይ	14,900

2. በአውሮፓ

በጀርመን ፌዴራል	
ሪፑብሊክ	244,300
በእንግሊዝ	24,000
በኢጣልያ	11,900
ስፔን	9,000
ቱርክ	5,300
ግሪክ	4,400
አይስላንድ	2,900
ሆላንድ	2,600
ቤልጅየም	2,100
ፖርቱጋል	1,400
በሌሎች ሀገሮች	1,200
ስድስተኛው ፍሊት	22,300
አጠቃላይ	331,700

3. በፓሲፊክና ሩቅ ምሥራቅ ፣

ጃፓንና ኦኪናዋ	46,000
ደቡብ ኮሪያ	38,000
ፊሊፒንስ	13,400
ጉአም	9,100
ሚድዌይ	500
አውስትራሊያ	600
ሌሎች ቦታዎች	500
ሰባተኛው ፍሊት	15,00
አጠቃላይ	124,000

4. ሌሎች አካባቢዎች ፣

ቤርሙዳስ	1,400
ዲያጎ ጋርሲያ	1,400
ግብፅ	500
ሳውዲአረብያ	800
ካናዳ	700
ሌሎች ሀገሮች	5,300
የባሕር ኃይል	21,500
አጠቃላይ	31,600

ይህ ቁጥር ቀደም ሲል የካርተር አሁን ደግሞ የሬጋን አስተዳደር በወሰድዋቸው እርምጃዎች በከፍተኛ ደረጃ እንደጨመረ ለመረዳት አያዳግትም ። የአሜሪካና የኔቶ ወታደራዊ ወጭ በአሁኑ ጊዜ ወደ 3 ቲሪሊዮን[5] ተጠግቷል ። ይህ ከፍተኛ ወታደራዊ ወጪ ለበጎ ሥራና ለሰላማዊ ግልጋሎት ቢውል ኖር ዛሬ የሚታዩት የዓለም ኅብረተሰብ መሠረታዊ ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ በተቃለሉ ነበር ። ይህን ለመረዳት የሚከተለውን ቻርት መገምገም ይበቃል ።

Digitized by Google

GUNS INSTEAD OF BUTTER



Supplement to New Times, A Survey, January, 1982

በአጠቃላይ ካርል ማርክስ እንዳስገነዘበው ለወረራ ጦርነት የሚወጣ ወጭ የአንድን ሀገር ሀብት ውቅያኖስ ውስጥ እንደመክተት የሚቆጠር ነው ።

የኔቶ አባል ሀገሮች በዓለም የሰላም ስምምነት መድረኮችና በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤዎች ስለዓለም ሰላም አስፈላጊነት ቢናገሩም ፣ በተግባር እንደታየውና እንደሚታየው ለዓለም ሰላም ያበረከቱት አስተዋጽኦ የለም ። የነሱ አስተዋጽኦና ለዓለም የሚያቀርቡት ገጸ በረከት አዳዲስና ዘመናዊ ፀረ ሰው የጥፋት መሣሪያዎችን መሥራትና በየሀገሮቻቸው ያለውን የሠራተኛ ሕዝብ የድካም ፍሬ ለጥፋት ሥራ ማዋል ነው ። የኔቶ አባል ሀገሮች በየጊዜው በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች የሚያሳልፉአቸው ውሳኔዎች የዓለምን ሰላም የሚያጠናክሩ ሳይሆኑ የሚያደፈርሱ ናቸው ። ጥረታቸውና ርምጃቸው ሁሉ የወደፊቱን የዓለም ሁኔታ ሰላማዊ ለማድረግ ሳይሆን ይበልጥ ሥጋትና አለመተማመንን በሕዝቦች መካከል ለመፍጠር ነው ።

እነዚህ ሀገሮች ግንቦት 30 እና 31 1981 በዋሽንግተን ባደረጉት ስብሰባ « የረጂም ጊዜ የመከላከያ ፕሮግራም » የተሰኘውን ፀረ ሰላም ፕሮግራም አውጥተው ነበር ። ይህ ፕሮግራም በሁለት ደረጃዎች የተከፈለ ሲሆን፥አንደኛው ደረጃ እ.ኤ.አ.) ሌላው በ1995 (እ.ኤ.አ.) በ1984 የሚገባደዱ ናቸው ።

በዚህ ስብሰባ ከተወሰኑት ውሳኔዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ። [7]

—እያንዳንዱ የኔቶ አባል ሀገር ወታደራዊ ወጪውን በ3% እንዲያሳድግ ፣

—ምርጥና ዓይነተኛ የሆኑ የኑክሌር መሣሪያዎችን አባል ሀገሮቹ እንዲሠሩና እንዲያከማቹ (ለምሳሌ ኒውትሮን ቦምብ)

—የባሕር ኃይላቸው ንእንዲያጠናክሩ

—የአየር ኃይልንና የአየር መከላከያን እንዲያጠናክሩ ፣

—የሎጂስቲክስ ኃይልን እንዲያጠናክሩ፣

—የማጥቃት ዝግጅትን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሳድጉ የሚሉ ናቸው ።

ኔቶ አባል ሀገሮች በዘመናዊ የጦር መሣሪያ ራሳቸውን የሚያጠናክሩት የሶሻሊስቱን ካምፕ በተለይም የሶቪዬት ኅብረት « የወረራ አደጋ » ለመቋቋምና የሚሊተሪ ተመጣጣኝነትን ለመጠበቅ ነው በማለት ለጦር መሣሪያ እሽቅድድሙ ዋንኛ ምክንያት ሶቪዬት ኅብረት እንደሆነ ች ሰፊና የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ ያካሂዳሉ ።

ይህ ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ በካፒታሊስት ሀገሮች ያሉ ሕዝቦች ስለዓለም ሰላም ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥና ሶሻሊስት ሀገሮች ለሰላም ፣ ለዲታንትና ለጦር መሣሪያ ቅነሣ ያላቸውን ትክክለኛ አቋም ተቀባይነት ለማሳጣት የሚሰ ነዘር ከንቱ ሙከራ ከመሆኑም ሌላ በእውነት ላይ ያልተመረኰዘ ነው ።

እስካሁን የታየው ታሪካዊ ሐቅ የሚያረጋግጠው በየጊዜው እያደገ ለመጣው የጦር መሣሪያ እሽቅድድም ምክንያቶቹና የእሽቅድድሙ መሪ የኔቶ አባል ሀገሮች እንደሆኑ ነው ። በኔቶ የመጀመርያዎቹ 30 ዓመታት ህልውና ውስጥ የኔቶ ወታራዊ በጀት ፣ 2625 ቢሊዮን ዶላር [8] ሲሆን ይሽም ወጭ ፣

—በደቡብ አሜሪካ የሚገኙ አገሮችን አጠቃላይ የብሔራዊ ምርት ስድስት እጥፍ ፣ መላ የአፍሪካ አገሮችን አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት ደግሞ 13 እጥፍ ያህላል ፣

Digitized by Google

—በአሁኑ ወቅት በዳበሩ የካፒታሊስት
አገሮች ውስጥ ላሉ ሥራ አጦች ቢካ
ሬል ለእያንዳንዳቸው 150.000 የአሜ
ሪካ ዶላር ያሀል/ይደርሳል ፤

—በአሜሪካ ውስጥ ዓመታዊ የጤና አገ
ልግሎት ወጭን አምስት እጥፍ ፤ ለት
ምህርት የተመደበውን ወጭ ደግሞ
መቶ ሰማንያ እጥፍ ያሀል ይሆናል ። [9]

በ1945 የአሜሪካን አቶም ቦምብ በሂር
ሽማና በናጋሳኪ ላይ ተጣለ ። ይህ የጦር
መሣሪያ ለዓለም ሰላም ጠንቅ መሆኑንና
መመረትም እንደሌለበት በማሳሰብ ሶቪዬት
ኅብረትድርጊቱን በጥብቅ አወገዘች ። ምዕ
ራባውያን የሶሻሊስቱን ካምፕና የዓለምን
ሕዝብ ተቃውሞ ባለመቀበል ድርጊቱን
በመቀጠል ይህን የጥፋት መሣሪያ መሥ
ራቱን እንዲያውም ማሻሻሉን ስለቀጠሉ
በት የኢምፔሪያሊዝምን አደጋ ለመቋቋም
ሶቪዬት ኅብረትም ከአራት ዓመት በኋላ
የአቶሚክ ቦምብ ባለቤት ሆነች ። በ1949
የሶሻሊስቱን ካምፕ ለማጥቃትና የሶሻሊዝ
ምን መስፋፋት ለማገድ የሰሜን አትላንቲክ
የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት ተመሠረተ ።
ይህንኑ የአድኅርት ግንባር ለመቋቋም
ሶሻሊስት ሀገሮችም ከስድስት ዓመት
በኋላ የዋርሶውን የመከላከያ ድርጅት ለማ
ቋቋም ተገደዱ ።

የዋርሶ ውል መፈረሙም ለወረራ ሳይ
ሆን የኔቶን የወረራ አደጋ ለመቋቋም መሆ
ኑን የሚያመለክተው በዚህ ድርጅት መመ
ሥረቻ አንቀጽ ላይ የኔቶ ውል ከፈረሰ የዋ
ርሶ ውልም እንደሚሠረዝ የሚያረጋግጥ
አንቀጽ መኖሩ ነው ።

በ1960ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ላይ በአሜ
ሪካን 1900 ያሀል አገር አቋራጭ ሚሳይሎ
ችና በርካታ ሚሳይል ተኳሽ ሰብመሪኖች
ተደራጁ ። ይህንኑ ለመቋቋም ሶቪዬት ኅብ
ረትም የአጸፋ ርምጃ በመውሰድ በተመሳ
ሳይ ኃይሏን አጠናከረች ። ባለፉት ሰባዎቹ
ዓመታት ውስጥ የሸንገተን ዘመናዊ
የኑክሌር ሚሳይሎችዋን ቁጥር በእጥፍ ስት
ጨምር ሶቭዬትም ኅብረት በአጸፋው የሚ
ሳይል ኃይሏን አጠናከረች ።

እንግዲህ ካለፉት ሁኔታዎች ሁሉ መገን
ዘብ የምንችለው ከ1945 ጀምሮ ለመሣሪ
ያ አሽቅድድሙ መሪ ሆና የቆየችው ሶቭዬት
ኅብረት ሳትሆን አሜሪካ እንደሆነች ነው ።
አሁን በደረስንበት ደረጃም የአሜሪካን አስ
ተዳደር የኒውትሮን ቦምብ ለማምረት ዕብ
ሪተኛ ውሳኔ አስተላልፎአል ። ይህን ድር
ጊት መላው ሰላም ወዳድ ሕዝብ ያወገዘው
ሲሆን የዓለምን ሕዝብ ተቃውሞ ባለመቀ
በል ይህ ጠንቀኛ መሣሪያ እስከተመረተ
ድረስ ሶሻሊስት ሀገሮችም እራሳቸውን ለመ
ከላከልና ለዓለም ሰላም ዋስትና ለመስጠት
የመከላከያ ኃይላቸውን ቢያጠናክሩ ፤ ከዚህ
ለሚከተለው የጦር መሣሪያ አሽቅድምድም
ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ።

የኒውትሮን ቦምብ አደገኛነት

በአሁኑ ጊዜ ለዓለም ሰላም እጅግ አሳሳቢ
ሁኔታ የፈጠረው በአሜሪካን አስተዳደር
ውሳኔ የኒውትሮን ቦምብ መሠራት ነው ።
የኔቶ ፖለቲከኞች በተደጋጋሚ እንደሚያ
ሳዝኑት የኒውትሮን ቦምብ ካለፉት የኑክ
ሌር መሣሪያዎች መጠነኛ የቴክኒክ መሻ
ሻል ብቻ የተደረገበት እንደሆነና አስጊም
እንዳልሆነ ነው ። ይህ አባባል እያደገ የመ
ጣውን የዓለም ሕዝብ ተቃውሞ ለመቋቋ
ም የተሰነዘረ ሲሆን ሐቁ ግን የዚህ ተቃ
ራኒ ነው ።

የኒውትሮን ቦምብ ምንም እንኳን የቀድ
ሞዎቹ የአቶሚክና የሀይድሮጅን ቦምቦች
ቤተሰብ ቢሆንም ዓይነቱ አዲስና እጅግ
አደገኛ ፀረ ሰው ልጅ የኑክሌር የጦር መሣ
ሪያ ነው። በዓይነቱ አዲስ ነው የተባለበትም
ያለፉትን ማለትም ቀደም ሲል የተሠሩትን
የኑክሌር መሣሪያዎችና የራዲዮ ሎጂካል

Digitized by Google

መሣሪያዎችን ፀባይና ዓይነት እጣምር የያዘ በመሆኑ ነው ። ከዚህም ሌላ የዚህ መሣሪያ የአጥፊነት ኃይሉ ባለፉት ጊዜያት ከተሠሩት በብዙ እጥፍ የሚጨምር ሆኖ ከፋብሪካዎች ሕንፃዎችና ሌሎችም የሰው ልጅ ሀብቶች መሐል የሰውን ልጅ ብቻ መርጦ የሚያጠፋ ነው ።

ዛሬ የዓለም ሕዝብ ለሰላም ከፍተኛ ትግል በሚያካሂድበትና የጦር መሣሪያ ቅነሳ ጥያቄ የጊዜው ዋንኛ ጥያቄ በሆነበት ጊዜ የሬጋን አስተዳደር በማን አለብኝነት ይህ ቦምብ እንዲመረት መወሰኑ ኢምፔሪያሊዝም ለዓለም ሰላምና ለዴታንት ያለውን አፍራሽ አቋም በግልጽ የሚያሳይ ነው ።

እየተባባሰ የመጣውን በዓለም ሰላም ላይ የደረሰውን አስጊ ሁኔታ ለማስወገድ የዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች እና መንግሥታት ዛሬም ከፍተኛ የሆነ ትግል በማካሄድ ላይ ናቸው ። አብዮታዊት ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ የማያወላውል አቋም እንዳላት በተለያዩ አጋጣሚዎች ለዓለም ሕዝብ አሳውቃለች ። በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የጦር መሣሪያ ቅነሳ እንዲደረግና በአጠቃላይም ዴታንት ተግባራዊ እንዲሆን በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤና በሌሎችም ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ለዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች የትግል አንድነት ጥሪዋን በተደጋጋሚ አሰምታለች ።

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይህን አስመልክተው ሲናገሩ ፦—

« በዚህ ዓለም በምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ጋር አንድነቷን ማጠንከር በሰላም አብሮ የመኖርና የዴታንት አቋሟን ተገፋበታለች »[10] በማለት አስገንዝበዋል ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው ባካሄዳቸው ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ለዴታንትና በአጠቃላይ በሰላም አብሮ መኖር የሚለውን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን ጽኑ አቋም ለዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ገልጧል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. *Political Détent and The Armed Race*, Panorama, DDR 1978, p. 10.
2. *US News and World Report*, 1977.
3. *The Arms Race: The Danger, The Burden, The Alternative*, New Times, A survey, January 1982, p. 19.
4. *US News and World Report*, quoted in New Times, Ibid., p. 9.
5. Stockholm International Peace Research Institute (SIPRI), Ibid., p. 13.
6. Ibid., p. 20.
7. From an Analysis by the Institute of International Politics and Economics: IPW, Berichte 8/78.
8. New Times, op. cit., p. 15.
9. Ibid.,
10. 1ኛ የኢሠፓአኮ ጠቅላላ ጉባዔ ፣ ማዕከላዊ ሪፖርት ፣ ሰኔ 1972

Digitized by Google

የእብሪተኞች ባዶ ጩኸትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ዕውነታ

ተስፋዬ አብዲ

ኢምፔሪያሊዝም ማለት ... ሰፊው ሕዝብ በሶሻል ትምክህተኞች የሚታለልበትና በመታለል የሚጨቆንበት ጊዜ ነው ። ይህም ማለት «በብሔሮች ነፃነት» «በብሔሮች የራስን ዕድል የመወሰን» - እና «በአባት ሀገር መከታ» ሰበብ በርካታ የዓለም ብሔሮችን በአምባገነኖች የመጨቆንን ትክክለኛነት የሚያውለበልቡ ግለሰቦች ያሉበት ወቅት ነው ።[1] ሌኒን

ይህንን ሌኒናዊ ሐቅ ከሠራተኛው ሕዝብ የመደብ ትግል ታሪክና በተቃራኒውም ትግሉን ለማደናቀፍ ከሞከሩ የቡርዧ አለሁ ባይ ቅጥረኞች የማወናበድ ሚና በጉልህ መረዳት ይቻላል ።

በተለይ ማኅበራዊ አብዮቶች ሲፋፋሙና ቡርዧው የሚጨብጠውን ሲያጣ ፣ የሠራተኛውን የመደብ ትግል አናት ለመምታት በግንባር ቀደምትነት የብሔር ጥያቄን ያነሳል ። በመደብ ትግሉ ሂደት የቡርዧው የብሔር ጥያቄ ምንም እንኳ ከጥቅም ማጋበሻ የገቢያ ክልል የውጭ ከበርቴን ገድቦና በሩን ዘግቶ ለብቻው ለመበዝበዝ ከሚያደርገው መስገብገብ የመጣ ቢሆንም ፣ ለጭቁኑ ሕዝብና ለመደብ ትግሉ የሚበጅበት ወቅትም ይኖራል ። ይህም የሚሆነው የአድኃሪ ሥርዓትን ከባድ የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበር በማንኮት ወደ ተራማጅ ሥርዓት ለመገስገስ ሲረዳና የመደብ ትግሉን በማፋፋም የሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ በተለይም የሠራተኛውን መደብ ከጭቆናና ከብዝበዛ ነፃ ማውጣት የሚያቃርብ ሲሆን ብቻ ነው ። በአንፃሩ ግን የመደብ ትግሉ ፀረ ካፒታሊስትነት ሲከሰትና ዲሞክራሲያዊ ይዘት ያለው መሆኑን ሲመለከቱት ትግሉን ለማደናቀፍ በብሔር ጥያቄ ስም ትግሉን ለመበታተን በማቀድ የተሸፋፈነ ጥያቄ የሚያነሱ እንደአሉ የአብዮቶች ታሪክ ያረጋግጣል ። የፀረ አብዮት ኃይሎች ዓላማ በግልጽ እንደሚታወቀው አብዮቱን በውጥን ለመቅጨት ፣ አብረውም የሚጓዙ መስለው በት

Digitized by Google

ግሉ ውስጥ በመሠለፍ የትግሉን አቅጣጫ ለማሳሳት የሚታጣ (የሚውጠነጠን) ተንኩል ነው ።

ይህን መሰል ደባ የተቃጣበት የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮትም መሠረታዊ የሆነ ማኅበራዊ ለውጥ ያስገኘ አብዮት ሲሆን ፣ ከጥቂት ቅሪቱ በስተቀር ፊውዳሊዝምን ከሥሩ መንግሎ ያንኮታኮተና ካፒታሊዝምን በማሽመድመድ የኢምፔሪያሊስቶችን ተስፋ በአጭር የቀጨ ፀረ አድኅሮት ትግል መሆኑ በተግባር የታየ ነው ። ነገር ግን ይህን የአብዮቱን ሥር ነቀልነት ፣ ጠንካራ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ አድኅሮት ይዘት የተመለከቱ የአንድነትና የአብዮት ጠላቶች መሠሪ የማስመሰያ ዘዴዎችን በመጠቀም የመገንጠል ጥያቄን ፣ የብሔርተኛነት ስሜትን ፣ የአካባቢ ጠባብነትንና የትምክህተኛነትን አመለካከት በየብሔረሰቡና በየመንደሩ ለማስፋፋት ሲሯሯጡ ይታያሉ ። በብሄረሰብ ጥያቄ ስም የቋንቋ ፣ የሃይማኖት ፣ የባህል የመሳሰሉትን ልዩነቶች ሽፋን በማድረግ የሕዝቡን ንቃተ ሕሊና ዝቅተኛነት በመጠቀም አድኃርያንና ወኪሎቻቸው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የአብዮቱ ፍሬ ተጠቃሚ እንዳይሆን ገንጥለው በማስቀረት ለመበዝበዝ የሚጠቀሙበት አንዱ ዘዴ ነው ።

እንደሚታወቀው በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረው ንጉሣዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ግናቸውንም የዲሞክራሲያዊ መብት በማፈን ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጨቁንና ሲበዘብዝ ቆይቷል ። ኢትዮጵያ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች አገር እንደመሆንዋ አድኃሪው ሥርዓት « ከፋፍለህ ግዛ » በሚለው ዘይቤው ብሔረሰቦችን በመከፋፈልና እርስ በርስ እንዲጋጩ እንዲናናቁ በማድረግ እስከፊ የብሔረሰብ ጭቆና ቀንበር አጋድሞባቸው እንደነበር የትናንት ትዝታ ነው ። ይሁንና ይህ ለዘመናት ሲካሄድ የነበረው ጭቆናና ብዝበዛ ጽዋውን ሞልቶ በየካቲት 1966 ሕዝባዊው አብዮት ከፈነዳ ወዲህ አብዮታችን በሂደቱ ለሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሰፋ ያሉ ተጨባጭ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አስገኝቷል ፣ በማስገኘትም ላይ ነው ። ሆኖም በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ድሎች ጥቅማቸው የነጠፈባቸው ፀረ ሕዝቦች የታሪክን ጉማ ወደ ኋላ ለማሽከርከር መሣሪያቸው አድርገው ሊጠቀሙ ከሞከሩባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የብሔር ጥያቄ እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ነው ።

ተስፋፊዎችና ኰሎኒያሊስቶች ጠንስሰውት የሄዱት ተንኰል በሰሜን ኢትዮጵያ ቀንደኛ የፀረ አብዮት ደባ በመሆን ብቅ ያለው ወዲያውኑ አብዮታችን ሕዝባዊነቱን በተግባር ማረጋገጥ እንደጀመረ ነበር ። ኢምፔሪያሊስቶችና የአካባቢው አድኅሮት ኃይላት ቀደም ሲል የንጉሣዊውን አገዛዝ ጥገኝነት ለማጠናከር በኋላም አብዮቱን ለማፈን እንዲያመቻቸው ለኤርትራ ገንጣይ ቡድኖች የውንብድና ተግባር ሁኔታዎችን አመቻቹ ። ለገንጣዮችም አስፈላጊውን ድጋፍ ሲሰጡ ቆዩ ። ይሁን እንጂ በአድኃሪው ሥርዓት አገዛዝ ወቅት የገንጣዮችን እንቅስቃሴ እንደ ማስፈራሪያ እንጂ ለንጉሣዊ አገዛዝ አስጊ ሁኔታ ሊፈጥር እንዲችል አላደረጉትም ነበር ። ምክንያቱም የፊውዶ ቡርዥዋው አገዛዝ የኢምፔሪያሊስቶች ቡችላ በመሆኑ የሱን መውደቅ አይፈልጉም ነበር ። ሕዝባዊ አብዮታችን ሲፈነዳ ግን ፣ የጥቅማቸው ተፃራሪ መሆኑን ስለተገነዘቡ ኢምፔሪያሊስቶች የመገንጠልንና የብሔረኝነትን ስሜት በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ብሔረሰቦች ውስጥ የማስፋፋት ጥረታቸውን በሰፊው የተያያዙት ። ለዚህም በጥቅም የተገዙና ራሳቸውም ከሐዲ የሆኑ የአድኅሮት ኃይሎችን ከውስጥ በማጠናከር በብሔርና በቅኝ ግዛት ጥያቄ ስም የፀረ አብዮት ሴራቸውን እንዲያያዙት አደረጉ ።

በአብዮታችን ሂደት ውስጥ የብሔር እና የብሔረሰብ ጥያቄ ፣ በአጠቃላይ የኤርትራ ጉዳይ በተለይ በሰፊው የተወሳና የተተነ

Digitized by Google

ተነ ቢሆንም ፣ አሁንም ከጥያቄው ወቅታ
ዊነት አንፃር መመሪያችን የሆነው የማሌ
ሳይንስ ጥያቄውን እንዴት እንደሚያየው
አጠር ባለ ሁኔታ መቃኘቱ አግባብ ያለው
ነው ። እንደሚታወቀው ማርክሲዝም ሌኒ
ኒዝም የብሔሮችን እና የብሔረሰቦችን
የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትንና
ይህም መብት እስከ መገንጠል ድረስ
ሊደርስ እንደሚችል ያምናል ፤ ይደግፉ
ልም ። ድጋፉ ግን የተመሠረተው ወይም
የሚመሠረተው እንቅስቃሴው የሠራተኛ
ውን መደብና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የነፃ
ነት ፈለግ እስከተከተለ ድረስ ብቻ ነው ።
ምክንያቱም የብሔሮች እና ብሔረሰቦች
መብት ጥያቄ ሠራተኛውን ሕዝብ ከመ
ደብ ጭቆና ነፃ ከማውጣቱ ጥያቄ ተነጥሎ
ሊታይ አይችልምና ነው ።

ስታሊን ይህን ሁኔታ እንደሚከተለው ገል
ጾታል ።

የብሔሮች ጥያቄ የወዝ አደሩ አብዮትና
በአጠቃላይም የወዝ አደሩ የበላይ ገዥነት
ጥያቄ አካል ነው ። . . . የብሔሮች የመብት
ጥያቄ የተለየ ጥያቄ ሳይሆን የወዝ አደሩ አብ
ዮት አጠቃላይ ችግር አካል ነው ። በመሆ
ኑም ከዚህ አጠቃላይ ችግር አንፃር መታየት
ያለበት ጉዳይ ነው ።[2]

ለብሔሮችና ለብሔረሰቦች ነፃነት የተ
መጣጠነ ዕድገትና እኩልነት የሚያስገኘው
መላ የብሔረሰብ ክፍሎችን (በተለይ ሁዉላ
ቀር ብሔረሰቦች) ባልተዛባ የዕድገት ጉዳና
ላይ በማራመድ ከኋላ ቀርነታቸው እንዲላ
ቀቁ ሊያደርግ የሚችለው የሶሻሊስት ሥር
ዓት ብቻ ነው ። የብሄረሰቦች የራስን
ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከመደብ
ትግሉ ጋር በጥብቅ የተያያዘና የተቆራኘ
ነው ። በመሆኑም ይህን መንፈስ በማጣ
መም የብሔር የራስን ዕድል በራስ የመ
ወሰን መብትን ለቡርዧው መደብ እንዲያ
ገለግል በማድረግ የመደብ ትግሉን ለማዳ
ከምና የሠርቶ አደር ሕዝቦችን አንድነት
ለማናጋት እንደ መሣሪያ የመጠቀምን አዝ
ማሚያ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አጥብቆ ይቃ
ጋዋል ። የራስን ዕድል በራስ የመወሰን
ጥያቄ ለሶሻሊዝም የሚደረግን ትግል የሚ
ረዳ መሆን እንዳለበት ሲያስገነዝብ ሌኒን
እንዲህ ይላል ፣ « ለዚህ ዓይነቱ ዲሞክራሲ
ያዊ መብት ነው በጨቋኙ ብሔር ውስጥ
ያሉ ዲሞክራሲያዊ ኃይላት ለተጨቋኙ
ብሔር የመብት ጥያቄ እስከ መገንጠል
ድረስ መደገፍ አለባቸው ። በሌላ በኩል
ደግሞ የተጨቋኙ ብሔር ዲሞክራሲያዊ
ኃይላት ከጨቋኙ ብሔር የሠራተኛ መደ
ብና ዲሞክራሲያዊ ክፍሎች ጋር አንድነት
መፍጠር አለባቸው ። ያለዚያ በጨቋኙ
ብሔር ውስጥ ያሉ ተጨቋኝ መደቦች ከመ
ደባዊ ንቃት ሕሊና ማነስ የተነሣ ሳያውቁ
በራሳቸው ቡርዧ ጋር በማበር ሌሎች
ጭቁን ብሔሮችን በመውረር ለበዝባዥ
መነጋጋ ይዳርጓቸዋል »[3]

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በመርህ መገን
ጠልን ይደግፋል ። የሚደግፈው ግን ቡር
ዧውን ለመምታትና አድሀሮትን ለመታ
ገል ፣ ጭቆናን ለማስወገድ እንጂ ሠራተኛ
ው ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅ
በራዊ ጥንካሬ እንዳይኖረው ለማድረግ
አይደለም ። የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ
የመወሰን መብት የሚለው ዓላማ በማርክ
ሲስቶች አመለካከት ለፀረ ዲሞክራሲ
ለፀረ ሶሻሊዝምና ፀረ አብዮት ዓላማ
ሊውል አይችልም ፤ ይህንን አዝማሚያ አብ
ዮተኞች በጽኑ የሚታገሉት ነው ። እንዲ
ያውም እስከ መጨረሻው መመታት ያለበ
ትና የዚህን መሰል የቡርዧ ብሔርተኛነት
አራማጆችን በትግል መመንጠር አብዮ
ታዊ ግዴታ መሆኑን ያስተምራል ።

የቡርዧ አቀንቃኞችና ፀረ ሕዝብ ዕብሪ
ተኞች ግን ባለማወቅ ሳይሆን ከግል ጥቅም
ጋር በተሳሰረ መሠሪ ዓላማ በመነሳት ስሜ
ታዊ በሆነውና በማስመሰልያ ይዘቱ አጭ
በርብር በሚያነሳሳው ዘዴያቸው በመጠ

ቆም በዘር ፣ በቋንቋ ፣ በባህልና . . . በመሳሰሉት ላይ ሰበብ በማድረግ ፣ ብዝበዛን ባንድነት በመታገል ፈንታ ሠራተኛው ሕዝብ ሳያውቀው ለብዝበዛ ፖሊሲያቸው እንዲቆም ያደርጋሉ ። አንድ ቋንቋ ስለተናገረ ፣ አንድ ነገድ ስለሆነ ፣ ወይንም በአንድ አካባቢ ስለተሰባሰበ ብቻ ፣ የተጨቆንክ ብሔር (ብሔረሰብ) ነህና ተገንጠል ! ! ፣ ተነስ «ለነፃነትህ» ታገል ! ! የሚል የመከፋፈል ስሜታዊ ግፊት ያደርጉበታል ፣ የተሳሳተ ስሜት በውስጡ ይነዙበታል ። የግል ሀብት ባለቤትነትና የአድኃሪ ሥርዓት ደባ ባንድነት ሕይወቱን ያዳሸቀውን ጭቁን ሕዝብ ለልዕልናው በጋራ በመታገል ፈንታ በቋንቋ ፣ በዘር ፣ በሃይማኖት --- እየተከፋፈለ እርስ በርሱ እንዲፋጅ ፣ አለመተማመንና ጥላቻ በመካከሉ እየተስፋፋ እንዲሄድ ያደርጋሉ ። ይህ ቡርዧው ጥቅሙን ለመጠበቅ የሠራተኛውን እንቅስቃሴ ለማኰላሸት የሚጠቀምበት ዓይነተኛ ዘዴ ነው ።

በመሠረቱ የብሔር ጥያቄ የመደብ ጥያቄ ነው ። የብሔር ጥያቄ የነፃነት ፣ የዕኩልነትና የፍትህ ጥያቄ እንጂ ቋንቋን ፣ ሃይማኖትን ፣ ጉሣን ፣ አካባቢን ተከትሎ የሚነሳ ጥያቄ አይደለም ። የብሔር ጥያቄ የመደብ ጥያቄ ፣ የነፃነትና የእኩልነት ጥያቄ አካል ስለመሆኑ በይበልጥ ለመረዳት በቅድሚያ የብሔርን ምንነት አነሳስና ልዩ ባሕርያት መመልከት ጠቃሚ ነው ።

ብሔር ምንድን ነው ?

ብሔር በመሠረቱ በአንድ አካባቢ የሚኖር ፣ አንድ መግባቢያ ቋንቋ ያለው ፣ ተመሳሳይ ስነ ልቦናዊ ዘይቤ ያለው ፣ በከፍተኛ ኢኮኖሚ የተሳሳሰረና በታሪክ የተቀራኘ የጸና ማኅበረ ሰብ ነው ። ማኅበረሰብነቱ ግን በዘር ወይም በነገድ ላይ የተመሠረተ አይደለም ። ሰዎች ሲፈልጉ ባንድነት የሚኖሩ ሳይፈልጉ ደግሞ እንደፈለጉ በቀላሉ የሚበታተኑት ቀላልና ልል የሰዎች ስብስብ አይደለም ። ብሔር በአጋጣሚ የተሰባሰቡ ሰዎች ክምችት ሳይሆን በረጅም ጊዜ ታሪክና ትውልድ የተገነባ የፀና ማኅበረ ሰብ ነው ። ስለዚህም በአብዛኛው ብሔር ከተለያዩ ዝርያና ነገዶች ከተውጣጡ ሕዝቦች የተመሠረተ ነው ።

ጆሴፍ እስታሊን ለብሔር የሰጠው ሳይንሳዊ ትርጉምና ትንታኔ እንደሚከተለው ነው ።

ብሔር በመሠረቱ አንድ ማኅበረሰብና የአንድ ማኅበረሰብ ሕዝብ ነው ። ይህ ማኅበረሰብ ዘርና ጉሣን ነገድን አይመለከትም። ለምሳሌ የአሁኑን የኢጣልያ ብሔር ብንመለከት ከሮማውያን ፣ ከኢትሩስካኖች ፣ ከቲውቶኖች ፣ ከግሪኮች ፣ ከዓረቦች . . . ብሔረሰቦች የተመሠረተ ነው ። የፈረንሳይ ብሔር የተመሠረተው ከሮማውያን ከብሬቶኖች ጀርመኖች ፣ ጉሞሉች . . . ብሔረሰቦች ነው ።

ስለዚህም አንድ ብሔር በዝርያና በጉሣ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በታሪክ የተሳሰረና የተገነባ ማኅበረሰብ ነው ። ይህም በአጋጣሚ የሚገኝ በቀላሉም የሚገነጣጠል ጊዜያዊ የሰዎች ጥርቅም ሳይሆን በታሪክ የተገነባ በጥብቅ የተሳሰረና የፀና ማኅበረሰብ ነው ።

አንድን ብሔር ባንድነት ተሟልተው ብሔር የሚያሰኙት ልዩ ባሕርያት አሉት ፣

1. ያለ አንድ የጋራ ቋንቋ አንድ ብሔር የማይታሰብ ነው ። ስለዚህም አንድ የጋራ ቋንቋ መኖር ለአንድ ብሔር ከመለያ ጠባዮቹ አንዱ ነው ። ይህ ሲባል ግን አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ የአንድ ብሔር አባላት መሆን አለባቸው ማለት አይደለም ። አሜሪካና እንግሊዝ ለምሳሌ በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚዎች ናቸው ። ነገር ግን በተለያዩ ሀገሮች (የድንበር ክልል) የሚኖሩ በመሆናቸው በሕዝቦች መካከል የማያቋርጥና ፣ ሥርዓት ያለው የረጅም ጊዜ ግንኙነት የላቸውምና አንድ ብሔር መሆን አይችሉም ።

Digitized by Google

2. <u>አንድ የጋራ ሀገር</u> (የጂኦግራፊ ክልል) መኖር ለአንድ ብሔር ሌላው መለያ ጠባይ ነው . .. ይህም በአጭሩ ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው ነው ።

3. ይህ ብቻ በቂ አይደለም . . . <u>የጋራ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ሕይወትና አንድነት የኢኮኖሚ መተሳሰር</u> ደግሞ ከብሔር ልዩ ባሕርያት አንዱ ነው ። ይህም በሰዎች (በማኅበረሰቡ) ውስጥ በሥራ ክፍፍል በመገናኛ በሰዎችና በዕቃዎች ነፃ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ ፣ ውስጣዊ የሆነ የኢኮኖሚ መተሳሰርን ያቅፋል ።

4. የአንድ ሕዝብ ብሔርነት በዚህ ብቻ አይወሰንም ። ከትውልድ ትውልድ እየደረጀና እየበለጸገ የመጣ የማኅበረሰቡ ሥነ ልቦናዊ ዘይቤ (ሳይኮሎጂካል ሜካፕ) ሰዎችንና በአጠቃላይ ማኅበረሰቡን የሚያስተሳስር ልዩ ተጽእኖ አለው ። ይህም መንፈሳዊ ሕይወትን ፣ በማኅበረሰቡ መካከል የባህል መተሳሰርን የሚያጠቃልል ነው ። ስለዚህም <u>በማኅበረሰቡ የጋራ ባህል ውስጥ የሚገለጽ አንድ የጋራ የሆነ ሥነ ልቦናዊ</u> ዘይቤ መኖር የብሔር ሌላው ባሕሪ ነው » [4]

ጆሴፍ እስታሊን ብሔርን ጠቅለል ባለ መልክ ሲገልጸው ፤

አንድ ብሔር የጋራ ቋንቋ ፣ ሀገር ፣ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ፣ በጋራ ባህል የሚከሰት የጋራ ሥነ ልቦናዊ ዘይቤ ያለው ፣ በረጅም ታሪክና ትውልድ የተገነባ ፣ የፀና ማኅበረሰብ ነው » ይላል [5]

አንድ ብሔር እነዚህን ባሕርያት አጠቃሎ ባንድ ላይ ይዞ ሲገኝ ብቻ ነው የአንድን ብሔር የተሟላ ገጽታ የሚያሳየውና ብሔር ሊባል የሚችለው ።

እንግዲህ የማሌ ሳይንስ እንደሚያስረዳው ብሔር ዘርና ጐሣን የሚከተል ሳይሆን ታሪካዊ ፈርጅ ነው ። ባንድ ታሪካዊ ወቅት ማለትም በኅብረተሰብ የተወሰነ የዕድገትደረጃ የሚከሰትና ወቅቱን ሲጨርስ የሚያበቃ ነው ። እንደሌላው ታሪካዊ ክስተት ሁሉ ብሔርም ለሕብረተሰብ የዕድገትና የለውጥ ሕግጋት የሚገዛ ነው ። ታሪካዊ ፈርጅነቱ የሚገለጸውም በማምረትና የምርት ግንኙነቱ ላይ በተመሠረተው የመደብ ትግል አማካይነት ነው ።

ስታሊን የራስን ዕድል በራስ የመወሰንን መብት እንዲህ በማለት አብራርቶታል ። « የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት ብሔሩ ብቻ የራሱን ዕድል ይወስናል ማለት ነው ሌላ ማንም በዚያ ብሔር ሕይወት ውስጥ <u>በኃይል</u> ጣልቃ ለመግባት የብሔሩን ት/ቤቶችና ሌሎች ተቋሞችን <u>ለመደምሰስ</u> ወጐቹንና ልማዶቹን ለመጣስ ቋንቋውን ለመጨቆንና መብቶቹን <u>ለመቀነስ</u> መብት የለውም ። » [6] ብሔር ሲባል ደግሞ ሰፊው ሕዝብ እንጂ እፍኝ የማይሞሉ ጨቋኞችና በዝባዦች እንዳልሆኑ መገንዘብ ያሻል ። የብሔሩ ሕይወት ባህል ፣ ቋንቋ ፣ እምነት ፣ ልማድ ፣ ጥቅም ወዘተ . . . ማለት የብዙኀኑ የሰፊው ሰርቶ አደር ሕዝብ ሕይወት ጥቅም ወዘተ . . . ማለት መሆኑ ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል ። ስለሆነም የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን በሚደረገው ትግል የአብዮተኞችና የዲሞክራሲያዊ ኃይላት ዓላማ በግል የተያዙ የምርት ማከናወኛዎችን በሕዝብ ይዞታ ፣ የግል ብልጽግናን በጋራ ብልጽግና የብሔር ጭቆናን በእኩልነትና በወንድማማችነት መተካትና የሁሉም ቋንቋ የሁሉም ባህል በእኩል እንዲከበርና እንዲስፋፋ አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈል ይሆናል ።

የኤርትራ ሁኔታ

ከዚህ በላይ በቀረቡት ሳይንሳዊ መመዘኛዎች አንፃር የኤርትራን ሁኔታ እንዴት እንመለከተዋለን ? የኤርትራ ጉዳይ የብሔር ጥያቄ ነው ? ወይስ የቅኝ ግዛት ? ወይስ ሌላ ?

Digitized by Google

ገንጣይ ቡድኖች (ጀብሀ ፣ ሻዕቢያ ፣ አልዋህዳ) ኤርትራ ውስጥ ለፈጠሩት ችግር ልዩ ልዩ ስያሜ ሰጥተውታል ፣ የብሔር ጥያቄ ነው ፣ የቅኝ ግዛት ወይም የኰሎኒያሊዝም ጉዳይ ነው ፣ የሃይማኖት ጥያቄ ነው ፣ የአረባዊነት ጉዳይ ነው . . . በማለት አያሌ ቅጽሎችንና ሀገረጐችን በየአገሩና በየስፍራው በተለያዩ ጊዜያት አስተጋብተዋል ፣ እያስተጋቡም ነው ። ምንነታቸውን ዓላማቸውን አቋማቸውን እንደየሁኔታው እንደ የአካባቢው እንደ እስስት ለዋውጠዋል ፣ አሁንም እየለዋወጡ ነው ። ለዓረቦች ዓረብ ፣ ለማርክሲስቶች ማርክሲስት ፣ ለአብዮተኞች አብዮተኛ ፣ ለቡርዧዎች ቡርዧ፣ ለፊውዳሎች ፊውዳልነን . . . በማለት ማወናበዱንና ማስመሰሉን ሥራዬ ብለው ይዘውታል ። በዚህም የማስመሰል ዘዴያቸው እስከ አሁን ድረስ ለመቆየት ችለዋል ።

ወደ ጥያቄዎቻችን እንመለስና ገንጣይ ቡድኖች ቀደም ብሎ ከየካቲት 66 በፊት ጥያቄያችን የብሔር ጥያቄ ነው ፣ አቋማችን ፀረ ፊውዳል ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ነው ፣ ተራማጆች ነን ፣ ሶሻሊስቶች ነን ፣ የመጨረሻው ግባችን መደብ አልባው ኅብረተሰብ ማለትም ኰሙኒዝም ነው ፣ ተራማጅ ማርክሲስት ሌኒኒስት የሆነ ሁሉ ሊደግፈን ይገባል ፣ በማለት የአንዳንድ ሶሻሊስትና ተራማጅ አገሮችንና ንቅናቄዎችን ድጋፍ ለማግኘት ችለው ነበር ። የኢትዮጵያንም ተራማጆች ፤—ዓላማችን አንድ ነው ፣ እኛ የምንታገለው ለሶሻሊዝም ነው ፣ የኤርትራ አስቀድማ ከፊውዳሊዝም መላቀቅ በቀረው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን ትግል ያበረታታል ፣ ያጠናክራልና ድጋፋችሁን ስጡን ፣ ከጐናችን ተሰለፉ ፣ መጀመሪያ እኛ ነፃ እንውጣና ከዚያ ደግሞ እናንተ ተራ በተራ ብሔረሰብ በብሔረሰብ እያላችሁ ነፃ ትወጣላችሁ ፣ በማለት ግማሹን ሲያሳስቱና ድጋፍ ሲያገኙ ግማሹን ደግሞ ግራ አጋብተውት እንደነበር ይታወሳል ።

ይሁንና ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ በተለይም ትግሉ እየተፋፋመ የአብዮቱም ዓላማ ግልጽ እየሆነ ሲመጣ የብሔር ጥያቄና በተለይም የኤርትራ ጉዳይ በዛ ላለ ጊዜ በስፋትና በጥልቀት በመተንተኑና በመብራራቱ እንደዚሁም ገንጣዮቹ በአብዮቱ አንፃር በወሰዱት አቋም ገመናቸው ሊገለጥ ችሏል ። ኤርትራ የሚለው መጠሪያ የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ፈጠራ መሆኑ ፣ ኤርትራ በሚለው የጂኦግራፊ ክልል ውስጥ ከስምንት በላይ የሆኑ የተለያየ ቋንቋ ባህል የኢኰኖሚ ይዞታና የዕድገት ደረጃ ያላቸው ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ፣ ከእነዚህ ብሔረሰቦች አብዛኞቹ በከፊል በቀረው የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸው ገሀድ ወጥቷል ። ኤርትራ የብሔር መለኪያዎችን የማታሟላና ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል ሆና የኖረችና የባሕር በር በመሆኗ ለኢትዮጵያም ሥልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጓ የማይነቃነቅ የታሪክ ሐቅ ነው ። በአጭሩ በእነዚህ ትንተናዎች አማካይነት ኤርትራ የሚባል ብሔር የሌለና በታሪክና በባህል ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል መሆንዋን በግልጽ ለመረዳት ይቻላል ።

ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት ወይም የኤርትራ ጉዳይ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ፣ የሚለውም የገንጣዮች ማወናበጃ መሠረተ ቢስነቱ ይፋ ወጥቷል። በመጀመሪያ አንድ አገር እንዴት አድርጐ የገዛ ራሱን የተወሰነ ክፍል ቅኝ ግዛት ያደርጋል ? ይህ ክፍል በኃይል አለመመጣጠንና በልዩ ልዩ ሁኔታዎች አማካይነት በኰሎኒያሊስቶች እጅ ውስጥ ወድቆ ለተወሰነ ጊዜ ማለትም ለስድሳ ዓመታት ያህል የቆየ ፣ በኋላም ከጥንት አካሉ ጋር መልሶ የተገናኘ ፣ የተዋሀደ በመሆኑ ሁኔታው የቅኝ ግዛት ጥያቄን ከቶ ሊያስነሳ አይችልም ። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ኤርትራን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ከካፒታሊዝም አልፋ

Digitized by Google

ኢምፔሪያሊዝም ደረጃ መድረስ ይናርባታ
ል ፣ ሐቁ ግን ይህ እንዳልሆነ ለማንም ግል
ጽ ነው ። በዚህ ረገድ ቀደም ካለ ጊዜ ጀም
ሮና በተለያየ አጋጣሚ የተካሄዱት ጥናቶ
ችና ትንተዎች ይህንንም የገንጣይ ወንበዴ
ዎች ጥያቄ ተራርሽነት በማያዳግም ሁኔታ
አሳይተዋል ።

ገንጣዮቹ የሚያራግቡት የሃይማኖቱና
የዘርም ጉዳይ መሠረተ ቢስ ማታለያና ግወ
ናበጃ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው ። በተ
ገሩ በትግራይ በወሎ ፣ በጐንደር ፣ በጐጃም
በሸዋ ውስጥ ይገኛሉ ። እነዚህ ሁሉ ቀደም
በተለያየ አጋጣሚ በቀረቡ ጽሁፎች ፣ ትን
ተናዎችና ጥናቶች ውስጥ በሚገባ የተብ
ራሩ ስለሆነ እዚህ ላይ ብዙ ሐተታ የሚ
ያስፈልጋቸው አይደሉም ።

አጽማቸውን እንደ እስስት የሚለዋው
ጡት ገንጣዮች አንገበው በየሥፍራው በመ
ዞር የዓለምን ሕዝብ የሚያወናብዱባቸውን
ዋና ዋና መፈክሮች እና ጥያቄዎች በመጠ



በኤርትራ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለቀይ ኮከብ ዘመቻ ድጋፋቸውን በጋለ ስሜት ሲገልፁ

ቀሩት የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገሮች
እስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች ተከታዮ
ች እንደመኖራቸው በኤርትራም ክፍለ ሀገር
የእነዚህ እምነቶች ተከታዮች ይገኛሉ።በዘር
በመልክ ወይም በቀለም እንደዚሁም በቋን
ቋና በባህል ኤርትራ ከቀሩት የኢትዮጵያ
ክፍላተ ሀገራት አትለይም ። ከላይ እንደተ
መለከተው ትግርኛ ፣ ኩናምኛ ፣ ናርኛ ፣ ሳ
ሆኛ ፣ አፋርኛ ፣ አገውኛ ፣ ወዘተ . . . የሚና
ኑም ቢሆን ከዳሰስን በኋላ አንድ ዓቢይ ጥያ
ቄ ከፊታችን ይደቀናል ። ይኸውም እነዚህ
አወናባጆች ምንድናቸው ? ለማን ወይም ለ
ምንድነው የቆሙት ? ዓላማቸውስ ምንድ፣
ነው ?

በአፍ ነፃ አውጪ ነን ይላሉ ፣ በተግባር
ግን ጨቋኝና አፋኝ ናቸው ፣ የሕዝብ ወገን
ነን ይላሉ ፤ በተግባር ግን ፀረ ሕዝብ ናቸው

በአፍ ተራማጅ ነን ይላሉ ፣ በተግባር ግን
የለየላቸው አድኃሪዎች ናቸው ።

በ1970 በኤርትራ ክፍለ ሀገር የተፈጠ
ረውን ችግር ለመመርመር በአዲስ አበባ በ
ተደረገው ከፍተኛ ጉባኤ ላይ «ማርክሲዝ
ምና የብሔረሰብ ጥያቄ» በሚል ርዕስ የቀ
ረበው ዘገባ በኤርትራ ያለውን ሁኔታ እን
ዲህ በማለት አጠቃልሎት ነበር ፣

«በዓረብ የገዥ መደቦች ድጋፍና በቁጥጥር
ሥር የሚካሄደው ንቅናቄ የኢምፔሪያሊ
ዝም ወኪል ስለሆነ የኤርትራ ሕዝቦች ቀን
ደኛ ጠላት እንጂ ከቶ ምንም ቢሆን ነፃ አ
ውጪአቸው ሊሆን አይችልም ። የኤርትራ
ጭቁን ሕዝቦች የተሟላ ነፃነታቸውን የሚ
ጐናጸፉት ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጋር
ኩብረት የጠነከረ የመደብ አንድነት መስር
ተው ፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ አመራርን ተቀብ
ለው የመደብ ትግላቸውን አፋፍመው በፊው
ዳሊዝም በኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲ
ያዊ ካፒታሊዝም ላይ የማያዳግም ድልን ተ
ቀዳጅተው ፣ በወዝአደሩ መሪነት ሕዝባ
ዊ አምባገነንነት የሰፈነበትን ሥርዓት ሲ
መሰርቱ ብቻ ነው» [7] ገንጣይ ወንበዴዎች
የአካባቢው አድኅሮትና የኢምፔሪያሊዝም
ትጥረኞችና ምንደኞች እንጂ ትንጣት ያህል
እንኳን የኤርትራን ሕዝብ አይወክሉም ።
ጦርነቱን የሚያካሂዱብን ኢምፔሪያሊዝ
ምና አድኅሮት ኃይላት ናቸው ፣ ጦርነቱ
የሚያካሂዱት በቀጥታ ራሳቸው ሳይሆኑ
ንጣዮችን በገንዘብና በጥቅም በመግዛትና
በመቅጠር ነው ። ይኸ በግልጽ መታወቅ
ያለበት ዓቢይ ጉዳይ ነው ።

የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሕዝብ ለኢትዮጵ
ዊነቱ ለሀገሩ አንድነትና ነፃነት ከባድ መ
ስዋዕትነት ሲከፍል ኖሯል ፣ አሁንም ለአ
ብዮታዊት ኢትዮጵያ ሕልውናና አንድነት
በሚደረገው ትንንቅ ውስጥ ተሳታፊ ነው ።
ታሪክንና ባህልን በሚመለከት ከዚህ በታች
የተመለከቱት አንዳንድ ሁኔታዎች ከብዙ
በጥቂቱ የአንድነታችንን ምንጭና መሠረት
እንደዚሁም ለዚህ አንድነት የተደረገውን
ትግል ይጠቁማሉ ።

— በከረን የሚገኙት የቢሌን ጐሳዎች ከላ
ስታ አሸንጌ የፈለሱና በዘራቸውም አ
ገው የሆኑ ናቸው ። ስማቸውም ቴዎ
ድሮስ ወዘተ . . . ነው ።

ኳዚን ፣ አዚን ፣ ቢዚን ወዘተ . . . የተሰቅ
ኙት በንጉሥ ኤዛና የተቀረቀሩ ናቸው
ንጉሥ ኢዛና ደግሞ ከክርስቶስ ልደት
በኋላ በ325 ገደግ የአክሱም ንጉሥ
የነበረ አክሱምም በወቅቱ የኢትዮ
ጵያ ነገሥታት ማዕከል የነበረች ናት።
ዛግር በዛጉዌ ዘመነ መንግሥት የተቆ
ረቆረ ነው ።

— ባህረ ነጋሽ ሹመቱን የሚወስደው ጐን
ደር በመምጣት ነበር ። ባሕረ ነጋ
ሽም የትግራይ የስሜን በጌምድር ፣
የወሎ ፣ ወዘተ . . . ባሕር አካባቢ
ተጀሚ እንጂ የኤርትራ ብቻ አልነ
በረም ።

— በናፒር ኤክስፒዲሽን ጊዜ በሕዝብ ተወ
ክለው ግብር በመያዝ ከኤርትራ ሰዎ
ች ወደ ቴዎድሮስ ተልከዋል ።

— ዳንቦዛሮች የመጡት ከደንቢያ ነው ።

— አርባተ እሥመራ ሐማሴን ከትግራይ
አደማያጐንዲ የመጡ ናቸው ።

— ደቂ አተሹም ከጐንደር የመጡ ናቸው ።

በአጠቃላይ በኤርትራ ቀደም ካለ ጊዜ ጀ
ምሮ ከዘጠኝ በላይ ብሔረሰቦች በአንድነት
የኖሩና ከሌሎቹ ክፍላተ ሀገሮች የሄዱ ሁሉ
እንደሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚኖርባት
ክፍለ ሀገር ናት ።

— ናኩራ እሥር ቤት ውስጥ በኢጣልያን
ጊዜ «ኢትዮጵያ ወይንም ሞት» የተ

Digitized by Google

ሰኘ ጽሑፍ በግድግዳ ላይ ተሰርስሮ በደሴቱ ተጽፏል ፤

— የስገነቲ ተወላጅ የሆኑት እንደ ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ ለአንድነት ዕድሜልክ ተዋግተዋል ፤

— በዓድዋ ጊዜ የኢጣልያንን ወረራ ለመመከት የኤርትራ አርበኞች ከመሐል አገር ሕዝብ ጋር በመሆን ለእናት ሀገር ሕልውና መራራ ትግል አካሂደዋል

— ስመጥር ሐማሴኖች ከኢጣልያን በመሸሽ ወደ ሻሸመኔ በመምጣትና ከነኝህ መሐከልም ሎሬንሶ ትዕዛዝ ጄኔብ ድረስ በመሄድ ለሀገራቸው ሕልውና በመከራከር የእናት ሀገርን መገነጣጠል ከድሮ ጀምሮ ይዋጉት እንደነበር የሚያስረዳ ነው

— ለአንድነት በመቆም ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት በመሆንና መብዘብዝን በመቃወም ማኅበሩን እየመሩ ፣ በሠራዬ አካባቢ እነ ፊታውራሪ አስረስ በሐማሴን አካባቢ እነ ፊታውራሪ ሐጐስ ተምናና ቀኛዝማች ገብሬ ተስፋጽዮን ፣ በአካለጉዛይ የሞሱዝጊ ልጆች (ወልደ ገብርኤልና በርሄ) 32 ጣልያን የገደሉ አርበኞችን መጥቀስ ይቻላል

በኩናማ—እነ ቀኛዝማች ፋይቲንጋ እና ሌሎችም ጫካ ድረስ በመግባት ሠራዊት እየመሩ ለኢትዮጵያ አንድነት እስከነፃነት ተዋግተዋል

— የራቢጣ አል እስለሚያ መሪ የነበረው ከቢሬ ወደ ተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን መዋሐድ ለማፋለስ ሊሄድ ሲል የአንድነት መሪዎች አሥመራ ገድለውት በሱ ቀብር ላይ እስከ ውጊያ ድረስ በተደረገው ትግል ከራቢጣና ከአንድነት ብዙ ሰዎች ሞተዋል። ፀረ ኢትዮጵያ የነበረውን ራቢጣ አንድነቶች ተፋልመውታል

— የኢጣልያን ደጋፊ ንቅናቄ ፕሬዚዳንት የነበረው ቪቶሪዮ በቦምብ የአንድነት ሰዎች ገድለውታል ።

— ኤርትራ ለኤርትራውያን ይል የነበረውን ከፋፋይ ወልደ አብ ወልደ ማርያም 9 ጊዜ አንድነቶች አቁስለውታል (እንግሊዞች ለሴራቸው ሲሉ ይጠብቁት ስለነበረ ሳይሞት ቀርቷል)

ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የኤርትራን ጉዳይ እንዴት ይመለከቱታል ? እስቲ አንድ ምሳሌ እንውሰድና እንመልከት ። ዘአፍሪካን ሚኒስት በተሰኘው የደቡብ አፍሪካ ኰሚኰኒስት ፓርቲ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈ ሐሳብ ማስፋፊያ መጽሔት ላይ ፣ ጆርጅ ጋልፐሪን ፣ ኢትዮጵያ የብሔረሰብ ጥያቄ ጥቂት ገጽታዎች በተሰኘው ጽሑፉ ውስጥ የኤርትራን ጉዳይ በማስመልከት ሲጽፍ ፣

. . . ለጥቂት ጊዜ የኢጣልያን ቀኝ ግዛት የነበረችው ፣ መጠርያዋን ሳይቀር በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የጣሊያን ወራሪዎች የሰጧት ኤርትራ በታሪክ ምንጊዜም የኢትዮጵያ አካልና በሺህ የኢኮኖሚ ፣ የባህልና ታሪካዊ ድር የተሳሰረችናት ። ገንጣዮች ለብቻዋ የበለጸገችና የዓረብ ዓለም አካል የሆነች ኤርትራ እንዳለች የሚያደርጉት ልፈፋ መሠረተ ቢስ ነው ። . . . የገንጣዮች አነሳስ ከኢምፔሪያሊስቶች የቀኝ አገዛዝና የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ፖሊሲና እንዲሁም ከሌሎችም የአድኀሮት ኃይላት ደባ ጋር የተቀራኘ ነው። . . . ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መገንጠልን ምንጊዜም እንደ ፖለቲካ ማምታቻና በራሱ ግብ እንደሆነ በማድረግ ከመደብ አመለካከት አፋቶ ተመልክቶ አያውቅም ። ማርክሲስት ሌኒንስቶች የብሔራዊ መንግሥታትን ችግሮች በመፍታትና ሶሻሊዝምን በማምጣት መሐከል ያለውን የቀርብ መተሳሰር በአንክሮ መመልከት ብቻ ሳይሆን ሶሻሊዝም ከሁሉም ቀድሚያ እንደሚሰጠው ያምናሉ። ይህም የብሔረሰብ ጥያቄ ሊፈታ የሚገ

Digitized by Google

ባው ለሠራተኛው ሕዝብ በሚያመች መንገድ መሆኑን ያመለክታል ። ሌኒን እንዳለው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማለት መበታተንና ጥቃቅን መንግሥታት መመሥረት ማለት አይደለም ። ይህ መብት የሚያመለክተው ያለማቋረጥ ሁሉንም ዓይነት ብሔራዊ ጭቆና መታገል እንደሚያስፈልግ ነው ። የገንጣዮችና የሞግዚቶቻቸው አድራጎት እያመራ ያለው የዛሬውን ምሥራቅ አፍሪቃ በአጠቃላይ እንደገና ወደ መሸንሸን ነው ። በምሥራቅ አፍሪካ ብቻ ኢትዮጵያን ወደ አምስትና ስድስት መንግሥታት መበታተን ፣ ደቡብ ሱዳንንና ሰሜን ኬንያን የመቁረጥና ጅቡቲንም በሁለት የመክፈል ዓላማ ይዘዋል ። . . . የፀረ ኢትዮጵያ ውርጅብኝ መደባዊ ዓላማ ግልጽ ነው ። የኢትዮጵያ ጠላቶች ለሕዝቡና ለአካባቢው ዕጣ የሚቸገሩበት ነገር የለም ፣ ዋና ግባቸው የኢትዮጵያን አብዮት ለማፈንና በዚህ ሰፊና ስትራቴጂያዊ አካባቢ ተራማጅ ኃይሎችን ለመበተን የወጠኑት ነው ። . . . ለታዳጊና የሶሻሊስት የዕድገት ጉዳና ተከታይ ሀገሮች የብሔረሰብን ጥያቄ ሶሻሊስታዊ መፍትሔ መስጠት ትክክለኛ ነው ። . . . ይህም ተግባራዊ እኩልነት የሚረጋገጠው በሥር ነቀል አብዮታዊ የማኅበራዊ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የባህል ለውጥና ለተለያዩ ብሔረሰቦች ዕድገት መፋጠን ድጋፍ በመስጠት ይሆናል . . . ። ይህ የግድ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል ። [8] ብሎ ነበር ።

የኢትዮጵያ አብዮት የገንጣይ ወንበዴዎችን ምንነት በሚገባ ካጋለጠ ወዲህ ቀደም ብለው በነዚሁ ገንጣዮች የማስመሰል ችሎታ ተወናብደው ድጋፍ ይሰጧቸው የነበሩት ሶሺያሊስት ፣ ተራማጅ አገሮችና ንቅናቄዎች ዛሬ እርግፍ አርገው ትተዋቸዋል ፣ እንቅረው ተፍተዋቸዋል ። ቀድሞውንም ቢሆን የገንጣይ ቡድኖች አስታጣቂያዎችና ድጋፍ ሰጭዎች ፣ ገንጣዮች አሁን ያደረሱትን ጥፋት እንዲያደርሱ ሁኔታውን በከፍተኛ ደረጃ ያመቻቹላቸው እነ ሲ. አይ.ኤና የተወሰኑ አክራሪና አድኃሪ የዓረብ መንግሥታት መሆናቸው ግልጽ ነው ።

በታሪካዊው የቀይኮከብ ሁለገብ ዘመቻ ብሔራዊ ጉባኤ ላይ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያን አካል መሆንዋን ፣ ለኢትዮጵያ ብሔረሰብ ዕድገትና ሥልጣኔ ያደረገችውን አስተዋጽኦ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕልውና አንድነትና ነፃነት ለመጠበቅ የከፍለ ሀገሩ ሰፊ ሕዝብ የከፈ[illegible]ዋዕትነት አስመልክተው ሲናገሩ ፣

«የሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በተለይ ኤርትራ ክፍለ ሀገርና አካባቢዎቹ በሀገራችን ታሪክ ልዩ ቦታ አላቸው ። ኅብረተሰቡ ከዚህ ሰፊና ረጅም ታሪኩ በጉም ፣ አስከፊም ተዝታዎች አሉት . . .

በጉ የምንለው ቀደምት ወይም ጥንታዊ የኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች ማለትም ፣ የተለያዩ ነገዶችና ጎሣዎች ከዚያም ብሔረሰቦች ባንድነት ተቃቅፈው ሥርዓተ መንግሥት በመመሥረት ባህልና ሥልጣኔአችንን በማዳበር ፣ አንድነታችንን በመከላከል ፣ ብሔራዊ ድንበራችንንና ነፃነታችንን ከወራሪዎች በመከላከልና በዚህ መራር የአያሌ ዘመናት ትግል ራሳቸውንና ሀገራችንን ለዓለም ያሳወቁ ተግባራት የተከናወኑበት የታሪክ ቅርሶቻችን የቀመጡት ስመጥሩ ጀግኖችና መሪዎችም የበቀሉበት የሀገራችን የታሪክ መሠረትና ማዕከል በመሆኑ ነው ። . . . ይህን የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሥልጣኔአችን እምብርት በመሆኑ የኢትዮጵያችን ልዩ መታወቂያ የሆኑ የባህል ቅርሶች ፣ ሃይማኖቶች ፣ ፊደላትና የመሳሰሉት መሠረታቸው ከዚሁ በመሆኑ በተጨባጭ የተመሰከረለትና ሊካድ የማይችል ነው ። . . . የታሪክ ግንዛቤ ድኅነት ላለባቸው አሁንም ትዕግሥቱ ካላቸው ከጽሑፍ ማስረጃዎች ጀምሮ በጉልህ የቆሙና ከምድር ተቆፍረው የተገኙትን ቅርሶች አገላብጠው እስከማየት ድረስ በቂ ማሳመኛዎች መኖራቸውን እንጠቁማለን [9] ብለው ነበር ።

Digitized by Google

የአሥመራን ማንፌስቶ በመደገፍ በግባ ስታዲዮም ከተደረገው ትዕይንተ ሕዝብ በከፊል

ከዚህም በተጨማሪ በኤርትራ ውስጥ የነበሩ አባት አርበኞች ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ሲሉ ከቅኝ ገዥዎችና ከወራሪዎች ጋር ስለአደረጉት ተጋድሎና ስለተጋድሎአቸውም ገድል በማስመልከት ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በዚሁ የቀይኰከብ ጉባኤ ላይ ሲናገሩ ፤ «የኢትዮጵያ ሐቀኛ ልጆች ከተደራጀ የኢጣልያ ጦር ጋር ገጥመው ወሬሳ የመቱበት ታሪክ ፣ የጀግንነት ታሪካችን ነው ። በኰአቲት ፣ በሰነአፌ ፣ በከረን ፣ በምጽዋ ፣ በጐንደት ፣ በዶግዓሊ ወዘተ . . . የጠላትን አንገት እየቀሉ የወደቁ የኢትዮጵያ ታላላቅ አርበኞች ደም በከንቱ የፈሰሰ አይደለም ። ለነፃነት ፣ ለኢትዮጵያዊነት ለመብትና ለክብር የተከፈለ የደም ዋጋ ነው» [10] ብለዋል ።

ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗ ተደጋግሞ ተገልጿል ። በኢምፔሪያሊስት ሥውር ቅኝ አገዛዝና ብዝበዛ ሥር ኖራለች ። ይህም አሌ የማይባል ሐቅ ነበር ። የኢምፔሪያሊስቶች ቡችላ የነበረው የአሮጌው የገዥ መደብ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የየብሔረሰቡን ጭቁን ክፍሎች ሁሉ ባንድነት ሲበዘብዝና ሲያስበዘብዝ ኖሯል ። አሁን ግን እነዚህ ጭቁን ክፍሎች ባንድነት ተነስተው ያን የጭቆና ሥርዓት ፣ የጨቋኙን መደብ ሥልጣን አንኰታኩተው የሶሻሊስት ግንባታውን ባንድነት ተያይዘውታል ። የተገንጣዮች ዋና ተልዕኮ ይህን ለማፍረስ ፣ ይህን ዓላማ ለማክሸፍ ነው ፣ እንጅ እው

Digitized by Google

ነት የኢትዮጵያን የአንድነት ታሪክ ስተ
ውት ፣ ወይም የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦች
ችግር ከመላ ኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች
ችግር የተለየ ሆኖ አይደለም ። የኢትዮጵያ
ጠቅላላ ችግር ደግሞ ከመላ የዓለም ሠርቶ
አደሮች ችግር የተለየ አይደለም ። ይህን
ሐቅ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ
ማርያም ለቀይ ኰከብ ሁለገብ አብዮታዊ
ዘመቻ ጉባኤ ባሰሙት የፖሊሲ ንግግራ
ቸው ላይ ፦

« የእኛ ችግሮች የኢትዮጵያ የራሷ ተጨ
ባጭ ሁኔታ ልዩ ያደርጋቸው እንደሆነ እንጂ
በነባራዊ ባሕርያቸውና በታሪክ ሂደታቸው
ከተቀረው የዓለም ኅብረተሰብ ችግሮች ጋር
ተመሳሳይ ናቸው ። ስለሆነም ከፍ ብዬ ስለ
ካፒታሊዝም ማደግና ኢምፔሪያሊዝም መወ
ለድ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁሉ ፣ ችግ
ሮቻችን ብሔራዊ ፣ ለህብረተሰባዊና ዓለም አቀ
ፋዊ ባህርይ ያላቸው ናቸው ፣ " ሲሉ ሳይን
ሳዊ ግኝኙነቱን በሚገባ ገልጸውታል ።

ስለዚህም የኤርትራ ችግር የኢትዮጵያ ች
ግር እንደመሆኑ ፣ የኢትዮጵያ ችግር ደግሞ
የወደቀው አድኃሪ ሥርዓት ውጤት በመ
ሆኑ ፣ መፍትሔውም የአድኃሪውን ሥርዓት
የተለያዩ ቅሪቶች በአብዮታዊ ሂደት ማስወ
ገድ ብቻ ነው ። ኢምፔሪያሊዝምና ግብረ
አበሮቹ በዓለም ላይ ካልተደመሰሱና የዓለ
ም ሠርቶ አደሮች መብትና ነፃነት ካልተረ
ጋገጠ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች አልፎም
የኤርትራ ምዝብሮች ነፃ ሊሆኑ አይችሉም።

ከአድኃሪው ሥርዓት ከተወረሱት የብሔ
ረሰብ የጭቆና መንስኤዎች ውስጥ ዋናው
የመሬት ጉዳይ እንደነበር ይታወቃል ። ይኸ
መሠረታዊ ችግር በሥርነቀሉ የመሬት ለአ
ራሹ አዋጅ ቢወገድና በሉም አግካይነት
በተገኙት ዲሞክራሲያዊ መብቶችም (ለም
ሳሌ የሃይማኖት የቋንቋ ፣ ባህል ወዘተ . . .)
ዓበይት የሆኑት ችግሮች በመቃለል ላይ ቢ
ሆኑም ነገሩ ሙሉ በሙሉ መፍትሔ አግኝ
ቷል ማለታችንም አይደለም ። አሁንም ችግ
ሮች አሉ ፣ የዕድገት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆ
ኑትን ብሔረሰቦች ከፍ ማድረግና ከሌሎች
ጋር ማስተካከል ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን
በማስፋትና ተግባራዊ በማድረግ ፣ በባህ
ልና በቋንቋ ረገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ፣
በራስ አስተዳደርም አንጻር ብዙ ወደፊት
መጓላትና መከናወን ያለባቸው ጉዳዮች እ
ንዳሉ እንገነዘባለን ። ይሁንና እነዚህ ሁሉ
ከአብዮቱ ጥንካሬና ወደፊት መግፋት ጋር
ተግባራዊ እየሆኑ የሚሄዱ ናቸው ። ባንድ
ጊዜ የሚከናወኑ አለመሆናቸውን የሌሎች
ሺያሊስት አገሮች ልምድ ያስገነዝበናል ።

ዕድገት ፣ ሶሻሊዝም ፣ ዕውነት ፣ ሰላም ፣ እ
ውነተኛ ሰብአዊነትና ፍቅር ከኢምፔሪያሊ
ዝም ይመነጫል ወይንም ከአድኃሪ ኃይሎ
ች እጅ ይገኛል ብሎ የሚጠብቅ ቢኖር ግብ
ዝና ራሱ የአድኃሪ ሥርዓት ወኪል የሆነ መ
ሆን አለበት ። የሰው ልጆች ታሪክ እንደሚ
ያሳውቀውና በዓለም ዙሪያ የብዝበዛን ቀን
በር ለማንኰታኰት የሚታገሉ የሶሻሊስት
አርበኞች በተግባር እንዳረጋገጡት እውነ
ተኛ የሰው ልጆች ዕድገት ፣ ሰላምና ወንድ
ማማችነትና እኩልነት፣የሶሻሊዝም ብቸኛ
ባሕርያት ናቸው ።

ከዚህ እውነታ በመነሳት ለሕዝብና በሕ
ዝብ ላይ የቆመውን መለየት አያዳግትም ።
በመሆኑም የትኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ
የታየ የጠባብ ብሔርተኞች እንቅስቃሴ ከየ
ትኛውም የሕዝብ ወገን ከሆኑ ዲሞክራሲያ
ዊና ሶሻሊስት ኃይሎች ድጋፍ የለውም፣ ይል
ቁንም በነዚህ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ይህ
ፀረ ሕዝብ ድርጊታቸው እየተወገዘ ነው ።

ቀደም ሲል በተገለጸው ግርክሳዊ የብሔር
ጥያቄ ትንታኔ አንጻር ስንመለከተው በብሔ
ር እንቅስቃሴ ስም በኢትዮጵያ አብዮት ላይ
የተቃጣ የትኛውም የማወናበድ ድርጊት የ
ሠራተኛውን ሕዝብ መሠረታዊ ዓላማ የሚ
ቃረንና የአድኅሮትን መሠረት ሊያጠና
ክር የሚሞክር እንጅ ለሠራተኛው ሕዝብ
ትግል የሚበጅ አይደለም ።

Digitized by Google

ለኢምፔሪያሊስቶችና ለወኪሎቻቸው ወትሮም ቢሆን የሰፊው ሕዝብ ርስ በርስ መተላለቅ ደስታቸው ነው ። ለምሳሌ የግላ ይደቴርስ የርስ በርስ መፋጀት ለሮማ ንጉሦች የመደሰቻ (የመዝናኛ) ቲያትራ ቸው ነበር ። አሁንም ቢሆን ተገንጣዮች በአጠቃላይ የኢትዮጵያና በተለይ የየብሔ ረሰቡ መተራመስና መፋጀት ቢሳካላቸው ጥቅም የሚያስገኝላቸው የደም ገበያቸው ሲሆን ፣ አለዚያም እስከተወሰነ ጊዜ ሲፋጁ ቁማሩ በሕዝብ ሕይወት ላይ መጫወት ስለሆነ መጨረሻ ላይ ወኪሎቹ ጌቶቻቸው ወደ አዘጋጁላቸው መዲና መኰብለልና አያሳጣቸውም ። ስለዚህም የሕዝብ መፋ ጀት ለነሱ የጥቅም ገበያቸው በመሆኑ ስሜት አይሰጣቸውም ።

የቀይኰከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ የ ኤርትራን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ የታቀደ ፤ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕ ዝብ በሙሉ ልብ የደገፈው እንቅስቃሴነው። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የአብዮታዊት ኢትዮጵያን የማያወላውል አ ቋም ለወዳጅም ሆነ ለጠላት እንዲሁም ለሰ ፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ ባለ መንየድ አስቀምጠውታል ። የኤርትራ ችግር የብ ሔር ጥያቄ አይደለም ። የቅኝ ግዛት ወይም የሃይማኖትና የዘርም ጉዳይ አይደለም።ኢምፔሪያሊዝምና አድኅሮት በውክልና አንድነ ታችንን ፣ አብዮታችንን ፣ ነፃነታችንን ለመ ግፈፍና ለመድፈር የሚያካሂዱብን የእጅ አዙር ጦርነት ነው ። በመሆኑም ትግሉ መ ራራና ውስብስብ ነው ፣ ኢምፔሪያሊዝምና የዓረብ አድኅሮት ኃይላት ምንደኛ ገንጣዮ ችን ማደራጀታቸውን ማሰባሰባቸውን ፣ ማ ሰልጠናቸውን ፣ ማስታጠቃቸውን ገንዘብና መሣሪያ በገፍ መላካቸውን የሞራልና የፖ ለቲካ ድጋፍ መስጠታቸውን አያቋርጡም ። ይሁንና ወሳኞቹ እነሱ አይደሉም ፣ የዚህ እውነታ በቪየትናም ፤ በካምፑቺያ ፤ በላኦስ በሌሎችም ሥፍራዎች እንደታየው ፣ ወሳኙ ለሐቀኛ ዓላማና በሶሺያሊዝም ብቻ ለሚገ ኘው እውነተኛ ነፃነት ኅብረቱን አጽንቶ የ ሚታገለው ሕዝብ ቁርጠኝነት ነው ።

ኢትዮጵያ የሶሻሊዝምን ፈለግ የምትከተ ል አብዮታዊ አገር እንደመሆንዋ የሶሻሊስ ት አገሮችና የተራማጅ ኃይሎች ሙሉ ድጋ ፍ አላት ፣ ይህ በተግባር የተረጋገጠ ነው ። በዚህ ግብ ግብ ውስጥ ዋነኛውና ወሳኙ ኃይ ል የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የፖለቲካ ንቃቱ የድርጅት ብቃቱና አንድነቱ ነው ።የኢምፔ ሪያሊዝምና የአድኅሮት የውክልና ጦርነት ቀር... ከተነሳ ሰፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ሊቆም እንደማይችል ታሪክ በተደጋጋሚ አረጋግጧል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 21 ገጽ 409
2. ጆሴፍ ስታሊን ፣ ማርክሲዝምና የብሔር ጥያቄ ፣ ገጽ 285—286
3. ሌኒን ፣ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ፣ ገጽ 409
4. ጆሴፍ ስታሊን ፣ ከላይ የተ ጠቀሰው ፣ ገጽ 18—22
5. ጆሴፍ ስታሊን ፣ ከላይ የተ ጠቀሰው ፣ ገጽ 22
6. ጆሴፍ ስታሊን ፣ ከላይ ከተ ጠቀሰው ፣ ገጽ 36
7. የመደብ ትግልና የመገንጠል ጥያቄ በኢ ትዮጵያ በኤርትራ ክፍለ ሀገር የተፈጠ ረውን ችግር ለመመርመር በአዲስ አ በባ የተደረገ ጉባኤ ላይ «ማርክሲዝ ምና የብሔረሰብ ጥያቄ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የተጠቀሰ
8. ጆርጅ ጋልፐሪን ፣ ዘ አፍሪካን ኰሚኒስት ፣ ቁጥር 83 ፣ 1980
9. ሠርቶ አደር ጋዜጣ ፣ ቁጥር 68 ፣ ልዩ እትም ፣ 1974
10. ሠርቶ አደር ጋዜጣ ቁጥር 68 ፣ ልዩ እትም ፣ 1974
11. ሠርቶ አደር ጋዜጣ ፣ ቁጥር 68 ፣ ልዩ እትም ፣ 1974

Digitized by Google

ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ወደ ኋላቀር አገሮች ካፒታል የሚዛመትባቸው መልኮች

አያሌው ከበደ

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር ናቸው ።

ባሁኑ ጊዜ ያለውን ካፒታል ወደ ውጭ የሚላክበትን ሁኔታ በመጠኑ ለመረዳት ከ1870 እስከ 1945 ድረስ የነበሩትን የካፒታል አላላክ ሁኔታዎች ባጠቃላይ መመልከቱ ጠቃሚ ነው ። ይህም ጽሑፍ ከ1870 1945 የነበሩትንና ከ1945 ወዲህ ያሉትን ካፒታል ወደ ውጭ የሚላክባቸውን ሁኔታዎች በማነፃፀር በአሁኑ ወቅት የካፒታል አላላክ ሁኔታዎች ለመመርመር ሙከራ ያደርጋል ።

የ19ኛው ምዕተ ዓመት ሊገባደድ 30 ዓመታት ያህል ሲቀሩት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በዘመናዊ ኢንዱስትሪ የአደረጃጀትና የአመራረት ሥልቶች በመጠቀም የምርት ውጤት መጠኑን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በከፍተኛ ደረጃ አሳደገ ። በተለይም በኃይል ማመንጫ ኢንዱስትሪ ፥ በኤሌክትሪክ ሞተር ኢንዱስትሪ ፥ በስቲልና በብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ፥ በቅመማ ቅመም (Chemical ኢንዱስትሪዎችና በትራንስፖርት ኢንዱስትሪዎች መስኩች የተደረጉት የቴክኖሎጂ ለውጦች ከወዝ አደሩ የሥራ ምርታማነት ማደግ ጋር ተያይዘው የምርት ውጤቶችን መጠን በዓይነትና በጥራት በከፍተኛ ደረጃ አሳደጉ ። ለምሳሌ በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ በ1850ዎቹ ዓመቶች የጨርቅና የሱፍ ምርት በዘመናዊ ፋብሪካ አማካይነት በሰፊው የተመረተበት ጊዜ ነበር ። ከነዚህም ሌላ በዚሁ ጊዜ የጫማ ምርት በተለይ የቦት ጫማ ምርት በፋብሪካ አማካኝነት በሰፊው ተመርቷል ። በእንግሊዝ ሀገር ገበያ ውስጥ የጨርቃጨርቅና የሱፍ ምርት በሰፊው ከመቅረቡም በላይ በ1850ዎቹ ዓመቶች ከእንግሊዝ ወደ ውጭ ከተላኩት ምርቶች ውስጥ እስከ 60%[1] የሚሆነውን የሸፈነው ይኸው ዓይነቱ ምርት ነበር ።

በዚሁም ጊዜ ከፍተኛ የመስፋፋትና የማዳበር ሁኔታ ከታየበት የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ የብረታ ብረት በተለይም የባቡር ሐዲድና የባቡር ምርት ከፍተኛውን

Digitized by Google

ሥፍራ የያዘ ነበር ፡፡ በእንፋሎት ሞተር የሚጓዘው ባቡር በ1814 ተሠርቶ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የባቡር ሐዲዶች የመዘርጋትና የመስፋፋት ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ በእንግሊዝ ውስጥ ለመዳበር ችሏል ፡፡ በ1860 በእንግሊዝ ውስጥ 10,000 ማይልስ ያህል የባቡር ሐዲድ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘረጋ ፡ ይህ የባቡር ሐዲድ ምርት ኢንዱስትሪ መስፋፋት የብረት ምርት ውጤትን ማደግ አብሮ አስከትሏል ፡፡ ለምሳሌ ከ1866—1872 የነበረውን የዓለም የብረትን ምርት ውጤት መጠን ብናይ ከ8.9 ሚሊዮን ቶን እስከ 14.4 ሚሊዮን ቶን አድጐ እናገኘዋለን ፡፡ በወቅቱ እነዚሁ ሁሉ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የታዩት ዕድገቶች የካፒታል መስፋፋትንና ለካፒታሊስቶች የደለበ ተረፈ እሴትን በቀላሉ እንዲገኙ መረዳት አያዳግትም ፡፡ በወቅቱ በእንግሊዝ ሀገር የባቡር ሐዲድና የምርት ድርጅቶች ባለቤቶች የነበሩ ካፒታሊስቶች በሀገር ውስጥ በተጀመረው የባቡር ሐዲድ መዘርጋት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ከመቻላቸውም በተጨማሪ ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችና ወደ አሜሪካ ብቻ እንኳን ከ1856—1865 35 ሚሊዮን ፓውንድ የሚያወጣ ከ1865—1875 ደግሞ 83 ሚሊዮን ፓውንድ የሚያወጣ የባቡር ሐዲድ መላካቸው የምርት ውጤቱን ስፋትና ያገኙት ንምየትርፍ መጠን በቀላሉ ያሳያል ፡፡ [2]

በእንደዚህ ዓይነት የዘመናዊ ኢንዱስትሪ የተደራጀ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ በተዋቀረባቸው የካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ የነበሩት ብሔራዊ ገበያዎች ዘመናዊ ኢንዱስትሪ በገፍ ያቀረባቸውን የፍጆታ ሸቀጦችም ሆነ የካፒታል ሸቀጦች በተገቢው መጠን ማንሳት አልተቻላቸውም ፡፡ በተለይም በርካታ ተረፈ እሴት (Surplus Value) ለኢንዱስትሪያል ካፒታሊስቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ያስገኙ የነበሩት የካፒታል ሸቀጦች አምራች ተቋሞች የገበያ መጠን እያነሰ መምጣት የተከማቸውን ትርፍ የማዋያና በፍጥነት ትርፍ የሚያስገኝ መድረክ ማጣት ለካፒታሊስቶቹ ችግርን ማስከተሉ አልቀረም ፡፡

ለምሳሌ የባቡር ሐዲድ የመዘርጋቱ ሁኔታ ጋር በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ ባብዛኛው በአጭር ጊዜ ውስጥ በመጠናቀቁ የባቡር ሐዲድ አምራች ድርጅቶች በሀገር ውስጥ ገበያ ምርታቸውን ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ችግር ገጠማቸው ፡፡ በሌላም በኩል በወቅቱ የነበረው የእንግሊዝ የወዝ አደሩ መደብ የገቢ መጠን ዝቅተኛ ነበር ፡፡ በወቅቱ በእንግሊዝ ፡ በአሜሪካና በጀርመን የወዝ አደሩ መደብ ገቢ ቀደም ሲል ያገኝ ከነበረው ከ20—39% ቀንሶ ነበር ፡፡ [3] ስለዚህም የአብዛኛው ሕዝብ በድኅነት ደረጃ ላይ የነበረ በመሆኑ የጨርቅ የሱፍና የቆዳ ፋብሪካዎች በገፍ ያመረቱትን ሸቀጦች በቀላሉ ማንሳት አልተቻለም ፡፡ በርግጥ በወቅቱ በርካታ የኢንዱስትሪ ከተሞች በመገንባታቸውና የከተማ ልማትም በመስፋፋቱ የነዋሪዎች ቁጥር እየጨመረ የመጣ ቢሆንም የሀገር ውስጥ ገበያው ግን የቀረቡትን የጨርቅ የሱፍና የቆዳ ውጤቶች ለማንሳት አልቻለም ፡፡ በመሆኑም የካፒታል ሸቀጦችን (Capital Goods) የሚያስመርተው ካፒታሊስትም የፍጆታ ሸቀጦችን በብሔራዊ ገበያው ውስጥ ለማስነሳት ችግር ገጠመው ፡፡

ይህ የገበያ ውጥረት በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ በወቅቱ ተጀምሮ የነበረውን ካፒታል ማስፋፋት ሁኔታ እያጣበበው መጣ ፡፡ ሁኔታውም በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ከ1873 ጀምሮ በገሀድ መታየት ጀመረ ፡፡ የተመረቱት የምርት ውጤቶች በብሔራዊ ገበያዎች ውስጥ መነሳት አለመለል የሸቀጦችን ዋጋ መውደቅ አስከተለ ፡፡ ምሳሌ ያብረታ ብረት ዕቃዎች የዋጋ ተመን በ1880 በ60%ሲቀንስ የከሰል ደግሞ በ40% ሊቀንስ ችሏል፡፡ የነዚህ ሁሉ ውጤቶች ደግ የበርካታ የካፒታሊስት የምርት ድርጅቶ

Digitized by Google

ችን መዘጋትና መክሰር አስከተለ ። ከ1873 1883 በነበሩት ጊዜዎች ውስጥ ብቻ በእንግሊዝ ሀገር በነበረው የኢኮኖሚ ቀውስ የተነሳ 400 የጨርቃ ጨርቅ ኩባንያዎች ከስረው ተዘግተዋል ። ይህ ወቅት በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ያስከተለው ቀውስ ከፍተኛ ስለነበረ ታላቁ ቀውስ (The Great Depression) በመባል ይታወቃል ። ከዚህም የተነሳ በካፒታሊስት ሀገሮች መካከል ይካሄድ የነበረው ንግድም በወቅቱ ሊቀንስ ችሏል ። እንግሊዝ በ1876 ወደ አሜሪካ የላከችው የምርት ውጤት መጠን በ1872 ከላከችው ግማሽ ያህል ነበር ።[5] የሀገር ውስጥ የገበያ ሁኔታዎች መጣበብ በካፒታሊስቶች መሀከል የሚካሄደውን ፉክክር አባባሰው ። እነዚህ የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ካስከተሉት ውጤቶች ውስጥ ዋናዎቹ የካፒታሊስት የሞኖፖል የምርት ድርጅቶችን ማዋሀድና የዘመናዊ የኢንዱስትሪ ዕድገት ወዳልደረሰባቸው የተለያዩ የዓለም ክፍሎች ትርፍ ካፒታሎቻቸውን በገፍ የማውጣት ተግባሮች ነበሩ ።

በሞኖፖሊ የተደራጁት የካፒታሊስት የምርት ተቋሞች በሞኖፖሊ ያልተደራጁትንና ለመደራጀት ያልቻሉትን የካፒታሊስት የምርት ተቋሞች በቀላሉ በገበያ ውድድርና በሌሎች ዘዴዎች በመርታት የሞኖፖል ትርፍ ማካበትና የበለጠ የአመራረት ሥልታቸውን የቴክኒክ ይዞታ ባፋጣኝ ማሳደግ ቻሉ ። የሞኖፖሊ አደረጃጀት ዘርፍ በምርት ሥራ መስክ ብቻ ሳይሆን በባንክ ተቋሞች ፣ በካፒታሊስት ንግድ ተቋሞችና በሌሎች የአገልግሎት ኢኮኖሚ ዘርፎችም ተሰራጨ ። በአሜሪካ ውስጥ በርካታ ሞኖፖሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመሠረቱ ። በአሜሪካ የትረስቶቹ መብዛት በትረስት ባልታቀፉት ካፒታሊስቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተሉ በ1880 ዓመቶች መጨረሻ ላይ ፀረ ትረስት ሕጐች በአሜሪካ ውስጥ ሊወጡ ችለዋል ። በጀርመንም ከ1870—1905 ባለው ጊዜ ብቻ 400 ካርቴልስ ተቋቋሙ ። በጀርመን ውስጥ በተለይ የብረታ ብረትና የከሰል ኢንዱስትሪዎች በሞኖፖል ተደራጁ ። በእንግሊዝ ከ1880 ጀምሮ የዓለም አቀፍ የሐዲድ አምራች ድርጅቶች ማኅበር በመመሥረት በመሀከላቸው የገበያ መከፋፈል ስምምነት አደረጉ ። በዚህም ሥልት የሞኖፖል ካፒታሊስት የምርትና የአገልግሎት ኢንተርፕራይዞች በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ የሞኖፖል ትርፍ በማግኘት ካፒታላቸው እየተቆለለመጣ ። እየሰፋ የመጣውን ትርፍ ካፒታላቸውን ለመጠቀምና ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት ፤ በተለይም የካፒታል ጥንቅሩ ማደግ ያስከተለውን የሞኖፖሊ ትርፍመጠን (Rate of Monopoly Profit) የመቀነስ አዝማሚያ ችግር ለማስወገድ ዓይነተኛ መፍትሔ ሆኖ ያገለገለው የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ዕድገት ወዳልደረሰባቸው የተለያዩ የዓለም ክፍሎች ትርፍ ካፒታላቸውን በገፍ የማውጣቱ ተግባር ነበር ።[6]

በዚሁም ምክንያት የኋላቀር አገሮችን የኢንቬስትመንት መድረክ የካፒታል ሸቀጦችና የፍጆታ ሸቀጦች ማራገፊያ ቦታ ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ቅኝ ግዛቶችን የመያዝና በከፍተኛ ደረጃ የመበዝበዝ ተግባር የሞኖፖሊ ካፒታሊስት መንግሥታት ዋናና ተቀዳሚ ተግባር ሆነ ። በተለይ እንግሊዝ ፈረንሳይና ጀርመን ከ1880 ጀምሮ ለዚሁ ጉዳይ የሰጡት ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ነበር ። በዚህም ሂደት አፍሪካና እስያ ከፍተኛ የሽሚያ መድረኮች ሆኑ ። በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ያሉት ሀገሮች ከኢትዮጵያና ላይቤሪያ በስተቀር በጥቂት ጊዜ ውስጥ በሞላ በቅኝ አገዛዝ ሥር ወደቁ ። የኢትዮጵያም ቢሆን ሰሜናዊ ክፍሏ በቅኝ ገዥዎች ተይዞ ነበር ።

እንግሊዝ በእስያ ውስጥ በርማን ፣ ማላያንና ሌሎቹን ጨምራ ስትይዝ፥ ፈረንሳይ የተወሰኑ የቻይና ግዛቶችን ያዘች። ጀርመንም እንዲሁ የተወሰኑ አካባቢዎችን በቁጥጥር ሥር አደረገች ። ወደነዚህ ሥፍራዎች የሚ

Digitized by Google

ላከውም ካፒታል እያደገ መጣ ። ለምሳሌ እንግሊዝ በ1906 ወደ ቅኝ ግዛቶች 104 ሚሊዮን ፓውንድ ስትልክ ፣ በ1907 141 ሚሊዮን በ1910 ደግሞ 255 ሚሊዮን ፓውንድ ለመላክ ቻለች ።

ይህ ወደ ውጭ የሚላክ ካፒታል በርግጥ በወቅቱ በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ያልዳበሩ የነበሩትን የኢኮኖሚ ክፍሎች ማለትም የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችን ለማሳደግ መርዳቱ ግልጽ ነው ። ለምሳሌ በወቅቱ የኅብረተሰቡን የጤናና የትምህርት አገልግሎት በማስፋፋት በኋላቀር ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ የምርት ሥራ ዘርፎችን በማሻሻልና ሌሎች በርካታ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስፋፋት በኩል ከፍተኛ ወጪ ሊደረግ ይችል ነበር ። ሆኖም የሞኖፖሊ ካፒታሊስቶቹ ዓላማ አፋጣኝ ትርፍ በቀላሉ ሊያስገኙ ወደ ሚችሉት የትርፍ መስኮች ማሰማራት በመሆኑ ፣ ካፒታል በልማት ኋላቀር ወደሆኑ የአፍሪካ ፣ የእስያ ፣ የደቡብ አሜሪካ አገሮች ተላከ ። ከዚህም የተነሳ ለሥራ ክፍያ ከወጣው ወጪ እጅግ ዝቅተኛነትና አነስተኛነት የተነሳ በተለይ ከአፍሪካ ፤ ከእስያና ከደቡብ አሜሪካ ሰፊ ትርፍ በቀላሉና በገፍ እንዲታፈስ አስቻለ ። ይህንን ሁኔታ በሚመለከተው ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል ። ለምሳሌ እንግሊዝ እ. ኤ. አ. ከ1870 እስከ 1913 ወደ ውጪ ልካው የነበረው የኢንቬስትመንት ካፒታል 2.4 ቢሊዮን ፓውንድ (በወቅቱ የገንዘብ ልውውጥ መጠን 12 ቢሊዮን ዶላር) ሲሆን ፣ ይኸው የኢንቬስትመንት ካፒታል በዚሁ ጊዜ ውስጥ ያስገኘው ትርፍ 4.1 ቢሊዮን ፓውንድ ነበር ።[8] ከዚህ ማስረጃ እንኳን በቀላሉ ለመገመት እንደሚቻለው ካፒታልን ወደ ውጪ መላክ ለሞኖፖሊስቶች ምን ያህል ከፍተኛ ትርፍ የማስገኛ ምንጭ እንደሆነ ነው ።

ካፒታል ወደ ውጪ ሲላክ የሚያስከትለው የመስፋፋት እንቅስቃሴ ብቻውን የሚታይ ሳይሆን ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር መጎናዘብ የሚያሻው ነው ። የካፒታል ወደ ውጭ መላክ የሸቀጦችን አብሮ መላክና ገበያን የማድራት ሁኔታም ያስከትላል ። የሞኖፖል ካፒታል ልዩ ጠባዮች ከሆኑት ውስጥ የጥሬ ዕቃዎች ምንጮችን በቁጥጥር ሥር ማዋል ፤ የገበያ መስኮችን (የሀገርም ውስጥ ሆነ የውጭውን) በቁጥጥሩ ሥር ማዋልና ለነዚህ ሁኔታዎች መሳካት የሚያስፈልጉትን ማናቸውንም ርምጃዎች መውሰድ በጉልህ ከሚታዩትና ከታዩት ጠባዮች ውስጥ ናቸው ። እነዚህን ሁኔታዎች ለማሟላት ሞኖፖል ካፒታሊዝም የውጭ ገበያዎችን ፣ የጥሬ ሀብትና ርካሽ የሰው ጉልበት ምንጭ የሆኑትን አገሮች በቅኝ ግዛት መያዝ ፣ የሞኖፖል ካፒታሊስት ሀገር ገበያዎችን ደግሞ በፕሮቴክሺኒስት ፖሊሲ ሥር ማዋል ፣ የማያቋርጥ ሰፊ የትርፍ ትርፍ ማግኛ ሥልቱ ነው ። የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የውጭ ፖሊሲም እነዚህን ጥቅሞች የሚያስከብሩ ናቸው ። በመሆኑም በኢምፔሪያሊስት አገሮች መሀከል የቅኝ ግዛቶች የመያዝ ሽሚያ እየተካረረ መጣ ። ከ1914-1918 በኢምፔሪያሊስቶች መሀከል የተካሄደውንም ጦርነት ከቀሰቀሱት ምክንያቶች ውስጥ የቅኝ ግዛት ሽሚያው ዋነኛው ነበር ። በወቅቱ አብዛኛዎቹ የቅኝ ግዛቶች (በአፍሪካና በእስያ) በእንግሊዝና በፈረንሳይ ይዞታ ሥር ነበሩ ። የጀርመን ኢኮኖሚ ደግሞ በወቅቱ እያደገ በመሄድ ላይ ስለነበር የውጭ ገበያ ፍላጐቱ ፣ የርካሽ የጥሬ ሀብትና ርካሽ ጉልበት ፍላጐቱ በዚያው መጠን አደገ ። ለዚህም ፍላጐቱ መሟላት ጀርመን የቅኝ ግዛት ይዞታ ሽግሽግ እንዲደረግ በመፈለጓና ይህ ፍላጐቷ ደግሞ በሰላም ሊሳካ ባለመቻሉ ፣ የግድ በጦርነት የቅኝ ግዛት ሥፍራዎችን ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ላይ ለመውሰድ ተነሳሳች ። ይህ ሁኔታ ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ዋነኛውን አስተዋጽኦ አድርጓል ።

Digitized by Google

የካፒታል ወደ ውጭ መላክ ፥ በተላከበት ሀገር ውስጥ ለሞኖፖል ካፒታሊስቶች ጥሬ ሀብት ምንጭ በመሆን የልዩ ልዩ እንዱስትሪ ይዞታዎች ፤ የዘመናዊ የመጓጓዣ ድርጅቶች ፥ የባቡር ሐዲድና የባቡር ኩባንያ ፥ የመርከብ ድርጅትና የመርከብ አገልግሎት ኩባንያዎች ፥ የመንገድ ሥራ ድርጅት ኩባንያዎች ፥ የመገናኛ ድርጅት ኩባንያዎች ፥ የመብራትና የውሃ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ፥ የዘመናዊ የእርሻ ድርጅቶች (የጥጥ ፥ የትምባሆ ወዘተ . . .) ፥ የሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ፥ የባንክ የኢንሹራንስና የንግድ ድርጅቶች ወዘተ . . . ባለቤትነትና ርካሽ ጉልበትንና የቅኝ ግዛት ገበያን በማስገኘት ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቶላቸዋል ። ትርፍ ካፒታል የተላከባቸው ሥፍራዎች ለሸቀጦች ገበያም አመቺ ሆነው አገልግለዋል ። ለምሳሌ እንግሊዝ የላከችውን የሸቀጥ መጠን ብንመለከት ወቅቱ ለሸቀጥ ግራገፊያ አመቺ ሆኖ እንደነበር መረዳት እንችላለን ። በ1895 ፥ 226 ሚሊዮን ፓውንድ በ1900 ፥ 282 ሚሊዮን ፓውንድ ፥ በ1906 ፥ 76 ሚሊዮን ፓውንድ ፥ በ1910 ፥ 430 ሚሊዮን ፓውንድ የሚያወጡ ሸቀጦች ወደ ውጭ ልካለች ። ከ1870 እስከ 1900 ባሉት ጊዜዎች ውስጥ ከካፒታሊስት ሀገሮች ወደ አፍሪካና እስያ ተልኮ የነበረው የኢንቨስትመንት ካፒታል ለቀጥታ ምርታማ ሥራ የዋለ ብቻ ሳይሆን ፥ የብድር ካፒታልም ነበር ። በወቅቱ እንግሊዝ ለቱርክ ፥ ለግብጽ ፥ ለፔሩ ፥ ለሕንድ ፥ ለቻይና ወዘተ . . . በርካታ ካፒታል በብድር መልክ ሰጥታለች ። ወደ ውጭ የተላከው ካፒታል በየዓመቱ የማያቋርጥ ሞኖፖል ትርፍ ለሞኖፖሊስቶች ከማስገኘቱም ባላይ ተጨማሪ የካፒታል ወጭ በማድረግ አዳዲስ የትርፍ ማግኛ ድርጅቶችን እንዲያቋቋሙ አስችሏቸዋል ። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የካፒታል አላላክ መልኮች ባብዛኛው እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ድረስ ይካሄድ የነበሩ ሲሆን ከ1945 በኋላ ግን የካፒታል አላላክ ሁኔታዎች የተለዩ መልኮችን እየያዙ መጥተዋል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ወዲህ ከታዩት አዳዲስ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የካፒታል አላላክ ሥልቶች በአዲስ መልኮች መቅረብ ነው ። ይህን ሁኔታም ያስከተሉት በወቅቱ በዓለም ላይ የተፈጠሩት አዲስና አብዮታዊ ሁኔታዎች ናቸው ። በተጨማሪም ከሀገር አቀፍ የካፒታሊስት ኩባንያዎች ወደ ዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ኩባንያዎች የተደረጉት ሽግግሮችና የካፒታሊዝም ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ሕግጋት ሂደቶች ለአዲሶቹ የካፒታል አላላክ መልኮች መከሰት የራሳቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ላይ የሶሻሊስት ዓለም መፈጠርና የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት መናጋት የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም ከፍተኛ ሥጋትና ውጥረት ውስጥ ጣለው ። በ1945 የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፖላንድ ፥ ዩጐዝላቪያ ፥ ቡልጋሪያ ፥ ሩማንያ ፥ ቼኮዝሎቫኪያ ፥ ሀንጋሪ ፥ አልባንያ ቬትናም ፥ በ1949 ደግሞ ኰርያ ፥ ቻይና ፥ የሕዝባዊ ሪቪብሊክ መንግሥታት ሲቋቋሙ ቀደም ሲል ተቋቁመው ከነበሩት ከሶቪዬት ኅብረትና ከሞንጐሊያ ጋር ተዳምረው 25% የሚሆነውን የዓለም የመሬት አካል የያዙና 33% የሚሆነው የዓለም ሕዝብ ያቀፉ በመሆን የሶሻሊስት ዓለም ሊፈጠር ቻለ ።[10] በተጨማሪም በ1945 ኢንዶኔሽሽያ ፥ በ1947 ደግሞ በርማ ሕንድ ፥ ታይላንድ ፥ ፊሊፒንስ ፥ ሲሎን ፥ ሶርያ ፥ ሊባኖስ ፥ በ1949 ደግሞ ሊቢያ ፤ በ1959 ሞሮኮ በ1952 ግብጽ ፥ በ1953 ሱዳን ፥ በ1956 ቱኒዚያና በ1957 ጋና ፥ በ1958 ጊኒ ፥ በ1960 ደግሞ 17 የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ በመላቀቅ ነፃ ብሔራዊ መንግሥታት አቋቋሙ ። ስለዚህ ቀደም ሲል ኢምፔሪያሊዝም በቀጥታ ተጽዕኖው ሥር አድርጓቸው

Digitized by Google

የነበሩት የዓለም ሥፍራዎች እየጠበቡና
እያነሱ መጡ ። በዚህም የተነሳ ቀደም ሲል
በኢምፔሪያሊስቶች መሀከል ይካሄድ የነ
በረው የተካረረ የሽሚያ ትግል እነዚሁን
ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ወደ ማሰባሰብና
ማስተባበር አመራ ። በዚህም ትብብር አግ
ካኝነት ያለውን የኢምፔሪያሊስት ዓለም
መጠበቅና ከኢምፔሪያሊስት ዓለም የወ
ጡትን አገሮች መልሶ ወደ ኢምፔሪያሊስ
ስት ምህዋር የማስገባት ጥረቱ ቀጠለ ። በዚ
ህም ጥረት ውስጥ የኢምፔሪያሊስቶችን
ዓለም የማደራጀቱንና የመምራቱን ኃላፊ
ነት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተረከበ ።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በጦርነቱ
ማብቂያ ላይ ከኢምፔሪያሊስት ዓለም ውስጥ
በከፍተኛ የኢኮኖሚ የፖለቲካና የቴክኖ
ሎጂ መሠረት ተጠናክሮ የወጣ የኢምፔሪ
ያሊስት ኃይል በመሆኑና ሌሎቹ የኢምፔሪ
ያሊስት ሀገሮች በጦርነቱ ፍጻሜ ላይ በከ
ፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ የገቡ ስለ
ነበሩ አሜአሪካ (ለምሳሌ ያህል እንግሊዝ ፤
ፈረንሳይ ፡ ምዕራብ ጀርመን ፡) ኢጣልያ ፡
ጃፓን ፡ የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም የማደ
ራጀትና የመጠበቅ ኃላፊነቱን በቀላሉ ለመ
ረከብ ችሏል ። ለዚህም የትሩማን የመጋ
ቢት 1947 መመሪያና «የማርሻል ፕላን»
የሰኔ 1947 መመሪያ ዋናዎቹ ሥልቶች
ነበሩ ። የትሩማን መመሪያ የተመሠረ
ተው « . . . የታጠቁ አነስተኛ ኃይሎች
በነፃ ሕዝቦች ላይ የሚያደርጉትን ማንኛ
ውንም ዓይነት ተፅዕኖ የአሜሪካ መንግ
ሥት በቀጥታ ይዋጋል »[11] በሚለው
ፖሊሲ ነበር ። በዚህም ፖሊሲ አማካኝ
ነት አሜሪካ በየሀገሩ ያሉትን በራሳቸው
ኃይል አብዮታዊ ኃይሎችን ለመቋቋም
አቅም ያጡ አድኃሪዎችን በሙሉ በመ
ደገፍ ዓለም አቀፍ አድኃሪ ጣልቃ ገብነ
ቱን ተያያዘው ። በተለይም በወቅቱ ለም
ዕራብ አውሮፓ አሜሪካ ሰፊ ወታደራዊና
ፖለቲካዊ ድጋፍ ቢሰጥም ፡ የምዕራብ አው
ሮፓን አድኃሪ ኃይሎች በበቂ ለመንከ
ባከብና ለመጠበቅ ሰፊ የኢኮኖሚ ድጋፍ
ማስፈለጉ የጐላ ነበር ። የምዕራብ አው
ሮፓ ካፒታሊስት አገሮች ኢኮኖሚ በጦ
ርነቱ የተነሳ ከፍተኛ ውድቀት ደርሶ
በት ስለነበር አሜሪካ እነዚህን አገሮች
በኢኮኖሚ መስክ የማቋቋም ተግባሩን በሰ
ፊው ተያያዘው ። « ማርሻል ፕላን » የዚህ
የኢኮኖሚ ተግባር ዋና ይዘት ነበር ።
በመሆኑም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት
ፍጻሜ በኋላ አሜሪካ ዋናው አበዳሪ መን
ግሥት ሲሆን ዶላርም ዋነኛው የካፒታሊ
ስት ዓለም የመለዋወጫ ገንዘብ ነሆ ።

ቀደም ሲል በእንግሊዝ ፡ በፈረንሳይ ፡
በቤልጅግ ፡ በሆላንድና በሌሎች የኢምፔሪ
ያሊስት የጦር ኃይሎች ይጠበቁ የነበሩትን
የአፍሪካ ፡ የእስያና የሌሎች አካባቢዎች
ንም የመጠበቁን ኃላፊነት አሜሪካ ተረ
ከበ ። እነዚህን የቀድሞ ቅኝና ጥገኛ የነበሩ
ትን የኋላቀር አገሮች ደግሞ አሜሪካ «ፖይ
ንት ፎር» በተባለው ፕሮግራሙ አማካኝነት
የቴክኒክና የኢኮኖሚ ርዳታ በሚል ሥልት
የሥውር ቅኝ ግዛቱ በማድረግ ሊይዛቸው
በቃ ። የአሜሪካ ሞኖፖል ካፒታል ዓለም
አቀፍ የኢንዱስትሪ ተቋሞችን ይበልጥ
በማደራጀት በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ
በሰፊው ማስፋፋቱን ተያያዘ ፤ የአሜሪካ
ዓለም አቀፍ ባንኮችም እንዲሁ በሰፊው
በኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ውስጥ ደሩ ። አሜ
ሪካ ዋነኛውና ተቀዳሚው የካፒታል ላኪ
ሀገር ሆነ ። በ1960 ብቻ የነበረውን የዋናዎ
ቹን ሰባት የሞኖፖል ካፒታሊስት ሀገሮች
ካፒታልን ወደ ውጭ የሚልኩበትን መጠን
በምናይበት ወቅት አሜሪካ ከፍተኛውን
ሥፍራ ይዞ እናገኘዋለን ። በዚሁ ዓመት
እንግሊዝ 24.5% ፤ ፈረንሳይ 4.7% ምዕ
ራብ ጀርመን 1.1% ፡ ሆላንድ 4.2% ስዊድን
0.9% ካናዳ 5.5% ፡ አሜሪካ 59.% ነበር ።[12]
አሜሪካ ካፒታልን ወደ ውጭ በመላክ
ቅድሚያ ሥፍራ የያዘ ብቻ ሳይሆን ፡ የፋ
ብሪካ ውጤት ሸቀጦችን በመላኩም በኩል
ከኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ውስጥ ከፍተኛ
ውንና የመሪነቱን ሥፍራ ለመያዝ ችሏል ።

Digitized by Google

ለምሳሌ በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ
ላይና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ
ወዲህ በዋናዎቹ ሞኖፖል ካፒታሊስት ሀገ
ሮች የተላኩትን የኢንዱስትሪ ሸቀጦች መ
ጠን ስንመለከት ፤ ከሁለተኛው ዓለም ጦር
ነት ወዲህ በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ አሜ
ሪካ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ወደ ውጭ በመ
ሸጥ በኩል የመሪነቱን ቦታ እንደያዘ ያሳ
ያል ።

በ1913 የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ወደ ውጭ
የተላኩበትን መጠን ስናይ አሜሪካ 13%
እንግሊዝ 30.2% ፥ የቀድሞይቱ ጀርመን
26.6% ፥ፈረንሳይ 12.1%፥ ኢጣልያ 3.3%፥
ጃፓን 2.3%፥ ሌሎች 12.5% ነበሩ።በ1950
በካፒታሊስት ዓለም ውስጥ የኢንዱስትሪ
ሸቀጦች አላላክን ስንመለከት ደግሞ አሜ
ሪካ 26.6% ፤ እንግሊዝ 24.6% ፌዴራል
ጀርመን 7.0% ፈረንሳይ 9.6% ፥ ኢጣልያ
3.6% ፥ ጃፓን 3.4%፥ ሌሎች 25.2% ሆና
እናገኘዋለን ።[13] ስለዚህም ከሁለተኛው
ዓለም ጦርነት ወዲህ የካፒታሊስቱን ዓለ
ም የማደራጀቱና የመጠበቁ ተግባር በአ
ሜሪካ ግንባር ቀደም መሪነት መካሄዱ ይበ
ልጥ ጉልህ ይሆናል ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ
ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ፥ በአሜሪካ
መሪነት በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ ካፒ
ታል ወደውጭ የሚላክበት ሁኔታ የተለየ
ገጽታ አለው ።

እነዚህ አዳዲስ የካፒታል አላላክ መል
ኩች እንዲከሰቱ ካስቻሏቸው ምክንያቶች
ውስጥ የመጀመሪያው የሶሻሊስት ዓለም
መፈጠርና የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ብቸኛና
ዘመናዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ያለመሆኑ
ጉዳይ ይበልጥ ገሀድ መውጣቱ ነው ። የካ
ፒታሊስት ኢኮኖሚ ታሪካዊ ውሱንነትና
የቅኝ ግዛት ሥርዓት መናድና መፈራረስ ፥
ነፃ የብሔራዊ መንግሥታት በቀድሞዎቹ
ቅኝ ግዛቶች ውስጥ መከሰት ፤ እነዚህ አዲስ
ነፃ ብሔራዊ መንግሥታት ደግሞ የሞኖፖል
ካፒታሊስቶችን የተለያዩ የብዝበዛ ሥል
ቶች በጥበቅ መቃወምና መቋቋም መጀመ
ራቸው በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል

ነው ። ከዚሁ ጋራ በተያያዘ ሁኔታ የተወሰኑ
ሀገሮች የካፒታሊስት የዕድገት ጐዳናን
በመተው ሶሻሊስታዊ የዕድገት ጐዳናን
መከተላቸው ፤ ለልማታቸው በሚያደርጉ
ትም ጥረት ከሶሻሊስቱ ዓለም የፋናንስ፤የቴ
ክኒክ ሌላም ዓይነት ድጋፍ ማግኘት መቻ
ላቸው ፤ በኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻቸው ውስጥ
የግል ካፒታሊስት ይዞታንና የውጭ ካፒ
ታሊስቶችን የብዝበዛ መረብ የሚቆራርጥና
የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸውንም የሚገድ
ቡና የሚቆጣጠሩ ሕጐችና ደንቦች ማውጣ
ታቸው ፥ በነዚህ ፖሊሲዎችም መመራት
መጀመራቸው ፥ የኢምፔሪያሊዝምን የእጅ
አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘመን እያሳጠረው በመ
ምጣት ላይ ይገኛል ።

ከዚህም የተነሳ እነዚህን ሁኔታዎች ለመ
ቋቋም በሚያስችሉ ሥልቶች በመደራጀት
የሞኖፖል ካፒታሊስቶችን ስትራቴጂክ
ጥቅምና ሕልውና ሊያስጠብቁ የሚችሉ የወ
ቅቱ የካፒታል አላላክ መልኩች ሊከሰቱ
ችለዋል ። ከነዚህም መካከል ፥

ሀ.የሀገር ውስጥ ካፒታልን በተሳታፊ
ነት ባቀፉ በውጭ ሞኖፖሊስቶች
ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሆኑ የኢኮኖሚ
ተቋሞችን መመሥረት ፥

ለ.የውጭ ካፒታል በተላከባቸው ሀገሮች
ውስጥ ያሉትን መንግሥታት በልዩ
ልዩ ዘዴ በተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁና
በጥቅም እንዲደለሉ በማድረግ የውጭ
ኢንቬስትመንት ጥበቃ ማረጋገጫ
ውሎችን ማስፈረም ፤

ሐ. የሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥ
ታት የጋራ ይዞታ ያለባቸውን ዓለም
አቀፍ የሞኖፖል ድርጅቶች በማቋቋ
ምና በነዚህም ድርጅቶች አማካኝነት
በልዩ ልዩ መልኩች ካፒታልን መላክ፥

መ. ዓለም አቀፍ ሞኖፖል ካፒታሊስት
ድርጅቶችን በማቋቋም ካፒታል እን
ዲልኩ ማስቻል ፥

Digitized by Google

ሠ. የሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥታት ከየሀገራቸው ወደ ውጭ ካፒታላቸውን ለሚልኩ ካፒታሊስቶች ማንኛውንም ድጋፍና ትብብር መስጠት (ከውርስ ነፃ እንዲሆኑና ከተወረሱም ሙሉ ካሣ እንዲሰጣቸው ማድረግ ፡)

ረ. በሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥታት አማካኝነት በርዳታ ስም ካፒታል መላክ ፡

ሰ. ካፒታል ከሚላክባቸው ሀገሮች መንግሥታት ጋር ጠንካራ የፖለቲካና የወታደራዊ ግንኙነት መመሥረትና የትብብር ውሎችን ማድረግ ።

ሸ. በኋላቀር አገሮች ውስጥ የውጭ ካፒታል የሥውር ቅኝ አገዛዝ ጠንካራ መሠረት እንዲሆን ማስቻሉ ጉላ ብለው የሚታዩት የወቅቱ ካፒታል አላላክ መልኩች ናቸው ።

የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኮች ስትራተጅክ ግባቸው የግል የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት በየኋላቀር አገሮቹ ውስጥ ሊጠናከር እንዲችል ማድረግና ኋላቀር አገሮች ለውጭ የካፒታል ኢንቨስትመንት አመቺ አካባቢ እንዲሆኑ ማስቻል ። በየኋላ ቀር ሀገሮች ውስጥ ያሉት የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ይዞታዎች እንዲዳከሙና እንዳይጠናከሩ ማድረግ ፡ ባጠቃላይ በኋላቀር አገሮች ውስጥ «የክፍት በር» ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግና የውጭ ካፒታሊስቶች ያለምንም ችግር ከፍተኛ ትርፍ እንዲዝቁ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማረጋገጥ ናቸው ።

ቀደም ሲል በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት እንደልብ ሞኖፖል ካፒታሊስቶች በባለቤትነትና በበላይነት በመያዝ ይጠቀሙባቸው የነበሩት የጥሬ ሀብት ምንጮች ፡ የርካሽ የሥራ ኃይል ምንጮች ፡ የገበያ ምንጮችና የኢንቨስትመንት ካፒታል ማዋያ ሥፍራዎች የነበሩትን የኋላ ቀር አገሮች ዛሬ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ባብዛኛው በመፍረሱ እንደበፊቱ በቀላሉ ሊጠቀሙባቸው አልቻሉም ። ስለዚህም በተለወጠው የዓለም ሁኔታ ውስጥ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥልትንና አዲሶቹን የካፒታል አላላክ መልኮች በመጠቀም ዛሬም ኋላ ቀሩን ዓለም ይበልጥ ኋላ ቀር በማድረግና የዳበረውን የካፒታሊስት ዓለም አሁንም ይበልጥ በማዳበር ሞኖፖል ካፒታሊዝም የከፋ ብዝበዛውን በማከናወን ላይ ይገኛል ።

ከወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኮች ውስጥ የተወሰኑትን በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር ባለ ደረጃ ማየቱ የበለጠ ሁኔታዎችን ያስተዋውቃል ። ከወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኮች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሥውር ቅኝ አገዛዝ መሣሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ በመዋል ያለው «ርዳታ» (AID) እየተባለ ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች በተለይም ከአሜሪካ ወደ ኋላቀር አገሮች የሚላከው ካፒታል ነው ።

ይህ «ዕርዳታ» እየተባለ የሚላከው ካፒታል ለሞኖፖል ካፒታል የሞኖፖል ትርፍ መሰብሰቢያ አመቺ የኢኮኖሚ ፡ የፖለቲካና የወታደራዊ ሁኔታዎችን በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ ለመፍጠርና ይህንንም ለመጠበቅ እንደሚያስችል ሆኖ የታቀደና የሚሠራበት ሥልት ነው ። «ዕርዳታ» በመባል የሚታወቀውን ካፒታል ተቀባይ የሆኑት አገሮች «ስጦታ» እስካልሆነ ድረስ ተገቢውን ወለድ በስምምነቱ መሠረት የመክፈል ግዴታ ይኖርባቸዋል ። በተጨማሪም «ዕርዳታውን» ለማግኘት በተለይ ለውጭ ካፒታሊስቶች በራቸውን ክፍት በማድረግ አመቺ የውጭ ኢንቨስትመንትን የማያስተናግድ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መከተል ይኖርባቸዋል። ይህ «አመቺ የኢንቨስትመንትን ሁኔታ መፍጠር» ማለት ደግሞ የውጭ ሞኖፖሊስቶች በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚያካብቱትን ትርፍና ትርፋቸውንም ያለምንም ችግር እንዲያስወጡና እንዲያስገቡ ማስቻል ማለት ነው ። በተጨማሪም (ለዚህም ማረጋገጫ) «ዕርዳታ» ሰጪ ሞኖፖል

Digitized by Google

ካፒታሊስት መንግሥታት ከኋላቀር አገሮች መንግሥታት ጋር «የውጭ የግል ኢንበስትመንት ደኅንነት ማረጋገጫ ውሎች» (Investment Guaranty Treaties) ይዋዋላሉ ። በዚህም ውል መሠረት የውጭ ሞኖፖሊስቶች የትርፍ ሥራ እንቅስቃሴና የባለቤትነት ይዞታ እንደማይወረስ ፣ ትርፍንና ንብረትን የሚነኩ ሕጋዊ እርምጃዎች እንደማይወሰድባቸውና መብታቸውን ለመንከባከብ መንግሥታቶቹ ሕጋዊ ግዴታዎች ይገባሉ ። ለምሳሌ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲህ ዓይነቱን ውል ከአሜሪካ ጋር (እ.ኤ.አ.)በ1951 በ1962 እና በ1968 ተውዋሉ ነበር ።[14]

«ዕርዳታ» እየተባለ የሚላከው ካፒታል አብዛኛውን ጊዜ የሚውለው ከ«ዕርዳታ» ሰጪዎቹ ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የጦር መሣሪያዎች ለመግዣ ፣ (አንዳንዴም ያረጁና በግጣሪያ መሸጫ ዋጋ የሚሸጡ የጦር መሣሪያዎች ለመግዣ) የኋላቀር አገሮች መንግሥታትን የከፍያ ሚዛን እጥረት ለመሸፈንና ለሌሎችም አስተዳደራዊ ወጪዎች የሚውሉ እንጂ በሙሉ በኢኮኖሚ ነክ ተቋሞች ላይ የሚውል አይደለም ። በኢኮኖሚ ነክ ተቋሞች ላይ እንኳን ውሏል ከሚባለው ውስጥ ባብዛኛው በመሠረተ ልማት ግለትም መንገዶች (የባቡርና የካሚዮን) ፣ የአይሮፕላን ማረፊያዎች ፣ ወደቦች ፣ የመገናኛ የትምህርት ነክ ተቋሞችን በመዘርጋቱ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ፣ ከዚህም ሌላ በአገልግሎት ሥራ መስኮችና የንግድ ድርጅቶችን በማቋቋሙ ላይ የሚያተኩር ነው ። ስለዚህም «በዕርዳታ» መልክ ኢምፔሪያሊስቶች ወደ ውጭ የሚልኩት ካፒታል ቀጥተኛ በሆነ ማቴሪያላዊ ምርት መስክ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው ። ከዚህም በላይ ደግሞ በየጊዜው የሚሰጠው «ዕርዳታ» የየበፊቱን « ዕርዳታ » ወለድ ለመክፈል የሚውል ነው ።

በተጨማሪም «ዕርዳታ» በሚል ስም የሚላከው ካፒታል የሞኖፖል ካፒታሊስቶችን «ትርፍ» ሸቀጦች በኋላቀር አገሮች ውስጥ ለማሸጥ ዋና ዘዴ ነው ። ምክንያቱም «ዕርዳታ» ሰጪ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት «ዕርዳታ» ተቀባዩ ኋላቀር አገር ከሀገሩ ሞኖፖሊስቶች ላይ ሸቀጦችን የሚገዛበትን ሁኔታ የሚያረጋገጥ የቅድሚያ ውል እንዲገባ ያደርጋል ። ለዚህ በተለይ ዋና ምክንያት ከሆነው ውስጥ አንዱ የኋላቀር አገሮች የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙት በአብዛኛው ከሚሸጡአቸው ጥሬ ዕቃዎች (ከእርሻና ከማዕድናት) ስለሆነና እነዚህም ሸቀጦች በካፒታሊስቱ ዓለም ገበያ ዋጋቸው በየጊዜው እያቆለቆለ መሄዱ የምንዛሪ አቅማቸውን ስለአዳከመውና በቀጥታ የሚፈልጉአቸውን የልዩ ልዩ የፋብሪካ መለዋወጫ ዕቃዎችንም ሆነ ሌሎች የልማት መሣሪያዎችን በበቂ ለመግዛት ስለማይችሉ «ዕርዳታ» ተብሎ የተላከው የብድር ካፒታል ከ«ዕርዳታ» ሰጭው አገር ዕቃዎችን ለመግዛት እንዲውል ይደረጋል ። ይህንን በሚመለከት የቀድሞው የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንትና ሊቀመንበር የነበረው አሜሪካዊው ኢጉዊን ብላክ የተናገረውን መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል ። «የውጭ ዕርዳታ ፕሮግራማችን ለአሜሪካ ንግድ ጉልህ ጥቅም ያስገኛል ።

ይኸውም ፣

1ኛ ለአሜሪካ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ፈጣንና በቂ ገበያ ያስገኛል ፣

2ኛ ለአሜሪካ ኩባንያዎች አዲስ የባሕር ማዶ ገበያ ይፈጥራል ፣

3ኛ የኋላቀር ሀገሮች ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች የነፃ ገበያ ሥርዓት አቅጣጫ እንዲይዙ ያደርጋል ፣ በዚህም የአሜሪካ ኩባንያዎች ሊከብሩ ይችላሉ» ብሎ ነበር ።

Digitized by Google

ባጠቃላይ «ዕርዳታ» እየተባለ የሚላከው ካፒታል ለሞኖፖል ካፒታሊስቶች የፖለቲካ ፥ የወታደራዊና የኢኰኖሚ ጥቅም ማስገኛ ዋና መሣሪያ የሆነ የወቅቱ የካፒታል አሳላክ መልክና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንጂ የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች እንደሚለፍፉት ለኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ልማት ዕድገት በማሰብ የሚደረግ «ዕርዳታ» አይደለም ። የ«ዕርዳታውን» ዓላማ በሚመለከት ረዘም ላለ ጊዜ የአሜሪካ «የውጭ ዕርዳታ» ጉዳይ ኃላፊ የነበረ ዲ. ኤ. ፊዚገራልድ የተባለ በአሜሪካ (US News and World Report) ለተባለ ጋዜጣ ላይ በየካቲት ወር 1963 ለቀረበለት ቃለ መጠይቅ የሰጠውን መልስ ማየቱ ጠቃሚ ነው ። ይህ ግለሰብ አብዛኛው በውጭ ርዳታ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ወቀሳ ወቃሾቹ የውጭ ዕርዳታው ዓላማ ኢኰኖሚ ዕድገት ለማስገኘት እንደሆነ አድርገው በማሰባቸው የተነሳ ነው ። ዓላማው ግን በፍጹም ይህ አይደለም ። [17] ብሏል ። በተጨማሪም የአሜሪካ መንግሥት በ1963 ባወጣው የውጭ ዕርዳታ ሕግ (Foreign Assistance Act) ላይ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል ። « . . . ከፕሬዚዳንቱ (ከአሜሪካ ፕሬዚዳንት) ጋር የውጭ ኢንቬስትመንት ማረጋገጫ ፕሮግራም ውል ስምምነት ላላደረገ ፥ ለማንኛውም በዝቅተኛ ዕድገት ላይ ለሚገኝ ሀገር መንግሥት ከህዳር 31/1963 ጀምሮ በዚህ ሕግ መሠረት ምንም ዓይነት ዕርዳታ አይሰጥም ። . . .» እነዚህ ሁለት ማስረጃዎች የ«ዕርዳታ» ዓላማዎች ምን መሆናቸውን በጉልህ ያስረዳሉ ፤ የሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥታት «ዕርዳታ» አዲሱ የካፒታል አሳላክ መልክ ነው ሲባልም ይህንኑ ጉልህ ሐቅ በመመርኰዝ ነው ።

ሌላው የካፒታል አሳላክ መልክ በሞኖፖል ካፒታሊስት መንግሥትታና በተለይም በአሜሪካ ከፍተኛ ካፒታል የተቋቋሙትና ዛሬ ከፍተኛዎቹ ዓለም አቀፍ የብድርና የፊናንስ ድርጅቶች የሆኑት የሚልኩት የብድር ካፒታል ነው ። ከነዚህ ውስጥ ዋናዎቹ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (I.M.F.) የዓለም ባንክ (I.B.R.D.) እና አይ. ዲ. ኤ. ናቸው ።

የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት (I.M.F.) የተቋቋመው በብሬቶን ውድስ ስምምነት መሠረት በ1944 ሲሆን ሥራውን ግን በሚገባ የጀመረው እ. ኤ. አ. ከኅዳር 27/1945 ጀምሮ ነው ። በተቋቋመበትም ወቅት የነበረው መነሻ ካፒታል 8,800 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ፤ ይህም ካፒታል የተዋጣው ከዩናይትድ ስቴትስ 2750 ሚሊዮን ዶላር ፥ ከእንግሊዝ 1,300 ሚሊዮንዶላር ፤ ከቤልጅግ 225 ሚሊዮን ዶላር፥ከሆላንድ 275 ሚሊዮን ዶላር ፥ ከካናዳ 300 ሚሊዮን ዶላር ፥ ከፈረንሳይ 450 ሚሊዮን ዶላር በመሆን ነበር ። ድርጅቱ ገና ሲቋቋም አሜሪካ በድርጅቱ ውስጥ የነበረው የባለቤትነት ይዞታ ድርጅቱን ለመቆጣጠር አስችሎታል ። በዚህም የተነሳ በወቅቱ በድርጅቱ ውስጥ የአሜሪካ ድምጽ 37.9 %ነበር ። [18] ይህ ድርጅት ከአጀማመሩ አንስቶ በካፒታል ላኪ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ቁጥጥር ሥር የዋለ በመሆኑ በብድር መልክ የሚሰጠው ካፒታል አንዱ የወቅቱ የካፒታል አሳላክ መልክ ነው ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ባብዛኛው የሚያበድረው የአጭር ጊዜ ብድር ከመሆኑም በላይ ብድር የሚሰጠውም፤አባል ሀገሮች በተለይ የክፍያ ሚዛን (Balance of Payment) ቀውስ ወይም እጥረት ሲገጥማቸው ፥ በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ የውስጥ የገንዘብ ሥርዓታቸው ቸው ሲናጋ፤የውጭ ንግድ ግንኙነታቸው ጤናማ ሳይሆን ሲቀርና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሲያጋጥማቸው ነው ። ብድሩም የሚሰጠው አባል አገሮች ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው ። ይሁንና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ብድር የሚጠይቁ ኋላቀር ሀገሮች ፤

Digitized by Google

ልዩ ሁኔታ ካልኖረ በስተቀር ፣ ድርጅቱ የሚሰጠውን ብድር ለማግኘት የተወሰኑ የዚህኑዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት «ቴክኒካል ምክሮችን መቀበልና ግዴታዎችንም ማሟላት ይኖርባቸዋል ።

ስለ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (I.M.F.) አጠቃላይ አሠራርና ይዘት ወደፊት በሌላ ጽሑፍ የምንመለከተው ሲሆን እዚህ ላይ ለመጠቆም የተፈለገው በዚህ የገንዘብ ድርጅትና በተመሳሳይ «የዓለም አቀፍ» ተቋሞች የሚሰጠው የብድር ካፒታል አንዱ ካፒታል ወደ ውጭ የሚላክበት መልክ መሆኑን ነው ።

የዓለም ባንክ (I.B.R.D.) አመሠራረት ዓላማና የአሠራር ሁኔታ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እምብዛም የራቀ አይደለም። ልዩነቱ የዓለም ባንክ የረዥም ጊዜ ብድር ሰጭመሆኑ ነው ። የዓለም ባንክ የተመሠረተው በብሪተን ውድስ ውስጥ በሐምሌ 1944 በተደረገው ስብሰባ አማካኝነት ነው።ሆኖም ይፋ ሥራውን የጀመረው በኅዳር 1945 ነበር ። የዓለም ባንክ ሲመሠረት የነበረው ካፒታል 5,950 ሚሊዮን ዶላር የነበር ሲሆን የዚህ የመነሻ ካፒታል ባለቤቶች አሜሪካ 3175 ሚሊዮን ዶላር ፣ እንግሊዝ 1300 ሚሊዮን ዶላር ፣ ፈረንሳይ 450 ሚሊዮን ዶላር ፣ ካናዳ 325 ሚሊዮን ዶላር ፣ ቤልጅግ 225 ሚሊዮን ዶላር ፣ ሆላንድ 275 ሚሊዮን ዶላር ፣ አውስትራሊያ 200 ሚሊዮን ዶላር ነበሩ ። [19] የዓለም ባንክ ሲቋቋም አሜሪካ በድርጅቱ ውስጥ 1/3 ኛ ድምጽ ስለነበረው የዓለም ባንክን ፖሊሲ ከመጀመሪያው አንስቶ በከፍተኛ ደረጃ ለመቆጣጠር አስችሎታል ። [20]

በዓለም ባንክ ውስጥ ከፍተኛውን የአመራር ሥፍራ የያዙት የዲሬክተሮች ቦርድ አባሎች ናቸው ። እነዚህ ቁጥራቸው 21 ሲሆን ስድስቱ በመንግሥቶቻቸው የሚወከሉ ናቸው ። እነርሱም ከአሜሪካ ፣ ከእንግሊዝ፣ከምዕራብ ጀርመን ፣ ከፈረንሳይ፣ከጃፓንና ከሕንድ ሲሆኑ ሌሎቹ አሥራ አምስቱ ተመራጮች ናቸው ። የዲሬክተሮች ቦርድን የሚመራው የዓለም ባንክ ፕሬዚንት ነው ። አሜሪካ ይህንን ቦታ ያለማቋረጥ ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ። ለምሳሌ በ1968 የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ሆኖ የተመረጠው ቀደም ሲል (ከምርጫው (በፊትት)የአሜሪካ የመከላከያ ሚ/ር የነበረው ማክናማራ ነው ። [21]

የዓለም ባንክ የካፒታል ይዞታ በ1965 በጠቅላላው 21,669 ሚሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አሜሪካ የ6350 ሚሊዮን ዶላር ባለቤት ነበረች ። የዓለም ባንክ በ1968—170ሚሊዮን ሊ.ዶ.የተጣራ ትርፍ ሲያገኝ በ1970 ደግሞ 213 ሚሊዮን ዶላር የተጣራ ትርፍ አግኝቷል። [22] የዓለም ባንክን ብድር ለማግኘት የግል ኩባንያዎችና ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ድርጅት ዋስ (ተያዥ) ማቅረብ ግዴታቸው ሲሆን፤የዓለም ባንክም በተራው በተያዥነት ለተበዳሪዎች ይዋሏል ። የዓለም ባንክ ልዩ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር ለመንግሥታዊ የኢኮና ይዞታዎች ብድር ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም ። የዓለም ባንክ በተለያዩ ሀገሮች ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን በተለይ በኋላቀር አገሮች ውስጥ የግል ካፒታሊስት ይዞታን ለማስፋፋት ዋነኛ መሣሪያ ነው ። የዓለም ባንክ የረዥም ጊዜ ብድሮች ማቅረብ የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልክ ነው ።

የዓለም ባንክ የወለድ መጠን ከ5.5በመቶ እስከ 6.5 በመቶ የሚደርስ ሲሆን በተለይ በ1970 7 በመቶ ደርሶ ነበር ። ከ1960 እስከ 65 ባሉት ጊዜዎች እጅግ ወደኋላ በቀሩ አገሮች(Least Developed Countries)የተከፈለው የወለድ ሂሣብ 627 ሚሊዮን ዶላር ያህል ነበር ። ከዚህ ሌላ አይ. ኤፍ.ሲና አይ.ዲ.ኤ. መጥቀሱ ጠቃሚ ነው ። [23]

አይ ኤፍ ሲ (International Finance Corporation) የተቋቋመው በ1959 ሲሆን የዓለም ባንክን ተግባራት ለማገዝና በኋላቀር

አገሮች ውስጥ የግል ካፒታሊስት ይዞታን ለማጠናከር ነው ። አይ. ኤፍ.ሲ. በኋላቀር አገሮች ውሰጥ ላሉ ካፒታሊስቶች የመንግሥታቸውን ተያዥነት ሳይጠይቅ ብድር ይሰጣል ። የዓለም ባንክ በኋላቀር አገሮች ለግል ኩባንያዎች ብድር የሚሰጠው ግን የብድር ጠያቂዎቹ መንግሥት ወለዱ እንደሚከፈል ተያዥ ሲሆን ብቻ ነው ።

አይ ኤፍ ሲ የወለድ መጠኑ ከዓለም ባንክ ያነሰ ነው ። የአይ ኤፍ ሲ አባል ለመሆን የዓለም ባንክ አባል መሆን ያስፈልጋል ። በ 1965 የ400 ሚሊዮን ዶላር ብድር አይ. ኤፍ. ሲ. ሰጥቶታል ።[24] ስለዚህ የአይ ኤፍ ሲ የሚሰጠው የብድር ካፒታል የወቅቱ ሌላ የካፒታል አላላክ መልክ ነው ።

ሌላው የብድር ካፒታል የሚልከው ድርጅት አይ.ዲ.ኤ. የተባለው ነው ። ይህ ድርጅት የተቋቋመው በ1960 ሲሆን ፡ አባሎቹም 17 የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና 50 ኋላ ቀር አገሮች ናቸው። አሥራ ሰባቱ ሀገሮች አሜሪካ ፡ እንግሊዝ ደቡብ አፍሪካ አውስትራሊያ ፡ አውስትሪያ ፡ ቤልጅግ ፡ ካናዳ ፤ ዴንግርክ ፡ ፊንላንድ ፡ ምዕራብ ጀመን ፡ ፈረንሣይ ፡ ጣሊያን ፡ ጃፓን ፡ ሉክዘምበርግ ፡ ሆላንድ ስዊድን፡ ኖርዌይ ናቸው። በአይ.ዲ.ኤ የመነሻ ካፒታል መዋጮ ላይ የአሥራ ሰባቱ አገሮች ይዞታ ከጠቅላላው 76 በመቶ ሲሆን ፡ ይህም 763 ሚሊዮን ዶላር ነው ። ከዚህ ውስጥ የአሜሪካ ድርሻ 320 ሚሊዮን ዶላር ነው ። የ. አይ. ዲ ኤ መነሻው ካፒታል 1.000 ሚሊዮን ዶላር ነበር ።[25] አይ ዲ ኤ ብድር በሚሰጥበት ወቅት ተቀባዩ ሀገር የሚገዛውን ዕቃ ከተወሰነ አገር ብቻ የመግዛት ግዴታ አለበት ። በመሆኑም አይ ዲ ኤ የብድር የመስጠት ተግባርም የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልክ ነው ።

የውጭ ካፒታሊስቶች ካፒታላቸውን በላኩበት አገር ውስጥ ያሉትን የአገር ውስጥ ካፒታሊስቶች በተባባሪ ባለቤትነት በማዳበል የሚያደርጉት የካፒታል ኢንቨስትመንት ተግባር ሌላው የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልክ ነው ። በዚህ አንጻር አሁንም ለሞኖፖል ካፒታሊስት አገሮች ኢንዱስትሪዎች በተለይ ስትራተጅክ የሆኑትን የጥሬ ሀብት ሥፍራዎችና ጥሬ ሀብቶች (ለምሳሌ አልሙኒየም ፡ ነዳጅ . . . ወዘተ) ለመያዝ የሚጠቀሙበት ዋና ስልት ነው።ከነዚህ ሌላ ዓለምአቀፍ በሆኑ ድርጅቶች አማካይነትና የሞኖፖል ካፒታሊስቶች ከፍተኛ መሪነት ባለባቸው በአካባቢ ደረጃ በተቋቋሙ ዓለም አቀፍ ወይም አኅጉር አቀፍ የኢኰኖሚ ድርጅቶች አማካይነት የሚደረገው የካፒታል ኢንቨስትመንት ሁኔታ ሌላው ጉልሁ የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልክ ነው ። በተለይም በዚህ አንጻር የተወሰነ የካፒታል ኢንቬስትመንት በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ በማድረግ የመገጣጠሚያ ፋብሪካዎችንና የፍጆታ ሸቀጦች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ለኋላ ቀር አገሮች የኢንዱስትሪ ዕድገት ከፍተኛ ጥረት እያደረግን ነው በማለት ኢምፔሪያሊስቶችና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎቻቸው ይለፍፋሉ ። ይህ ተግባር በተለይ ግልጽ የሆነ የዘመኑ የጥገኝነት የመፍጠሪያ ስልት ነው ። ምክንያቱም የመገጣጠሚያ ኢንዱስትሪዎቹ ጥሬ ዕቃዎቻቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎቻቸውን የሚያገኙት ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ነው ። የፍጆታ ሸቀጦች የሚያመርቱትም ኢንዱስትሪዎችም ቢሆኑ መለዋወጫ ዕቃዎቻቸውን ቴክኖሎጂአቸውንና ጠቅላላ ማሽኖቻቸውን የሚያመጡት ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ነው ።

ካሉት የካፒታል ላኪ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ አሜሪካ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ አገር ነው። ወደ ውጭ ከሚላከው የአሜሪካ ካፒታል ውስጥ ደግሞ ባሁኑ ጊዜ በብዛት ወደ ምዕራብ አውሮፓ አገሮችና ወደ ሌሎች የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች የሚላክ በመሆኑ ወደ ኋላቀር አገሮች የሚላከው ካ

ፒታል እያነሰ መምጧል የሚል አስተያየት አስከትሏል ። ነገር ግን ሁኔታው የተዘ ምዘ የካፒታል አላላክ ስልት መሥመር የ መከተል እንጂ ወደ ኋላቀር አገሮች የሚላ ከው ካፒታል ከቀድሞው የቀነሰ አይደለም። የአሜሪካ ሞኖፖል ካፒታሊስቶች ካፒታላ ቸውን በተለይ ወደ ምዕራብ አውሮፓና ወደ ጃፓን በመላክ በተለይ ምዕራብ አውሮፓና ጃፓን ቀደም ሲል ለረዥም ጊዜ በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ በፈጠሩአቸው የንግድና የካ ፒታል መላኪያ መሥመሮች ውስጥ በመ ጠቀም በቀላሉ ካፒታላቸውን ወደ ኋላ ቀር አገሮች በመላክ ላይ ናቸው ።

ለምሳሌ ወደ እንግሊዝ የሚላከው የአሜ ሪካ ካፒታል በቀላሉ ወደ ጋራ ገበያ (Com non wealth) አገሮች ይሄዳል ፤ ወደ ሌሎ ቹም የቀድሞ የቅኝ ገዥዎች ወደነበሩት የአ ውሮፓ ካፒታሊስት አገሮች የሚላከው የአ ሜሪካ ካፒታል በቀላሉ በነዚህ አገሮች በኩል ወደ ቀድሞ የነዚህ አገሮች ቅኝ ግዛ ቶች ወደነበሩትና አሁን የካፒታሊስት የዕ ድገት ጐዳናን ወደሚከተሉት ታዳጊ አርገች ይላካሉ ። ከዚህ ሌላ የአውሮፓ የኢኰኖሚ የጋራ ተራድኦ (EEC) ከኋላ ቀር አገሮች ጋር በፈጠረው የንግድና የኢኰኖሚ ግንኙ ነት መሠረት ወደነዚህ አገሮችም በቀላሉ የአሜሪካ ካፒታል ይላካል። ወደ ጃፓን የሚ ላከውም የአሜሪካ ካፒታል በቀላሉ በጃፓን በኩል ወደሩቅ ምሥራቅ አገሮች ይገባል ። ከዚህ ሌላ ደቡብ አሜሪካ የአሜሪካን ኢም ፔሪያሊዝም ካፒታል በሰፊው የተሰማራበት አህጉር ነው ።

ካፒታልን ወደ ውጭ በመላክ ሞኖፖል ካፒታሊስቶች የሚያጋብሱት ሀብትና ካፒ ታሉ የሚላክባቸው አገሮች የሚደርስባቸው ብዝበዛ በተለይ በኋላ ቀር አገሮች ሕዝቦችና በኢምፔሪያሊዝም መካከል ያለው ትግል እየተካረረ እንዲሄድ ከሚያደርጉት ምክን ያቶች መካከል ዋንኛው ነው ። ከአሜሪካን ብቻ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ የተላከ ውን ካፒታልና ያስገኘውን የትርፍ መጠን መመልከት የሚካሄደውን የብዝበዛ መጠን አጉልቶ ያሳያል ።

የአሜሪካን ኩባንያዎች ከ1950 እስከ 63 ባለው ጊዜ ብቻ 17.4 ቢሊዮን ዶርላር ወደ ውጪ ሲልኩ በዚሁ ጊዜ ለአሜሪካ ኩባንያዎች ገቢ የሆነውና ከውጭ በትርፍ መልክ የተገኘው 29.4 ቢሊዮን ዶላር ነበር ። [26] በሌላ በኩል ከኋላቀር አገሮች ብቻ የአሜሪካ ኩባንያዎች የዛቁትን ሀብት ስንመለከት የሚከተለውን እናገኛለን። ከ 1957 እስከ 1969 ወደኋላቀር አገሮች የተላከው የአሜሪካ ካፒታል 1830 ሚሊ ዮን ዶላር ሲሆን ፤ በዚሁ ጊዜ የአሜሪካን ኩባንያዎች በዚሁ ካፒታል ላይ ያገኙት ትርፍ 6000 ሚሊዮን ዶላር ነበር ። [27]

የኋላቀር አገሮች ብድር እየተባለ ለሚላ ክላቸው ካፒታል የሚከፍሉትም የወለድ ዕዳ እንደዚሁ እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለ ነው ። ለምሳሌ በ1966 ብቻ የኋላቀር አገሮች በሞላ 800 ሚሊዮን ዶላር የወ ለድ ዕዳ ክፍያ አድርገዋል ። እ. አ. አ. በ 1967 ብቻ የኋላቀር አገሮች 3.9 ቢሊዮን ዶላር የወለድ ዕዳ ክፍያ ነበረባቸው ። [28] የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኮች የእ ጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው ። ኢምፔሪያሊስት አገሮች የኋላቀር ሀገሮችን ጥሬ ሀብትና የሥራ ኃይል በመ በዝበዝ ከፍተኛ ሞኖፖል ትርፋቸውን በየ ጊዜው ለማግኘት በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለው የሶሻል የፖለቲካና የኢኰኖሚ ሁኔታ አመቺ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ተደጋጋሚ እርምጃዎችን ይወስዳሉ ።

በተለይም ከኋላቀር አገሮች በዝባዥ መ ደቦች ጋር በመተባበር ለባዕድ ካፒታል ተ ስማሚ የሆነ ሁኔታ በመፍጠር የውጪ ኢን በስትመንት የማስገባት ፖሊሲ እንዲወጣ ፤ የካፒታሊስት ኢኰኖሚ ግንኙነቶች እንዲ ጠናከሩና ለካፒታሊስት ኢኰኖሚ አመቺ የፖለቲካ ሁኔታዎች እንዲሰፍኑ የተቀነባ

Digitized by Google

በሩ እርምጃዎችን ወይሰዳሉ። የእነዚህ ሁኔታዎችም መጓላት ለወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኩ ችተገባራዊነት አስፈላጊ ነው። ሆኖም የወቅቱ የካፒታል አላላክ መልኩች ያለግጸረጥ በኋላቀር አገሮች ውስጥ መተርጉም ግለት የኋላቀር አገሮች በኋላቀርነታቸው እየገፉ እንዲሄዱ ፣ ዘወትር ዋጋቸው እያቆለቆለ በመሄድ ላይ ያሉ ጥሬ ዕቃዎችና የእርሻ ውጤቶች ላኪዎችና በየጊዜው ዋጋቸው እያደገ የሚሄዱትን የኢንዱስትሪ ዕቃዎችና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት ገዥዎች እንዲሆኑ የሚያደርጉና የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጥገኞች በመሆን የሚያስቀራቸው ነው።

በየጊዜው ኋላቀር አገሮች የሚገጥሟቸውንም የተወሳሰቡ ችግሮች ለማቃለልም ከሞኖፖሊ ካፒታሊስት አገሮች በሚቀርቡት «ዕርዳታዎችና» ብድሮች አማካይነት ፣ ኢምፔሪያሊስቶች ኋላቀር አገሮችን ዘወትር «የዕርዳታ» ና የብድር ወለድ ከፋዮች በማድረግ ሁኔታው እየተባባሰ የኋላቀር አገሮችን ሰፊ ሕዝቦች ለአስቃቂ ኑሮ እየዳረጋቸው ነው። በየጊዜው ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የኋላቀር አገሮች ሰፊ ሕዝቦች በረሀብ በበሽታና በእርዛት በማለቅ ላይ መሆናቸውን ስናይና በሌላውበኩልም ሞኖፖል ካፒታሊስቶች በተለያዩ መኩልች ወደ ኋላቀር አገሮች በሚገቡት ካፒታል አማካይነት የሚያካብቱትን ድልብ የሞኖፖል ትርፍ ስንመለከት ሁኔታው ምንያህል አስቃቂ እንደሆነ ለመረዳት ምንም አስቸጋሪ አይሆንም።

በሞኖፖል ካፒታሊስቶች ላይ ተቃውሞ የሚያነሱትን የኋላቀር አገሮች ተራማጅ ኃይሎች ለመደምሰስ ኢምፔሪያሊስቶች ከኋላቀር አገሮች በዝባዥ መደቦች ጋር በመተባበር በየጊዜው የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። በኋላቀር አገሮች ውስጥ ኋላቀርነትን ከሥረ መሠረቱ ለማስወገድ ፣ የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግን በመከተል አብዮታዊ ትግል የሚያደርጉትንም አብዮታዊ መንግሥታት ለማዳከምና ለማስቀልበስ የተቀነባበረ የፀረ አብዮት ሴራ ፣ በተለይም የኢኮኖሚ አሻጥር ያካሂዳሉ። ለዚህም ግባቸው በተለይ የሚከተሉት የፀረ አብዮት ስልት የመንግሥታዊና የኅብረት የኢኮኖሚ ይዞታዎችን በተቀነባበረ መንገድ ማዳከምና የግል ካፒታሊስታዊ ይዞታ በተቻለ መጠን እንዲጠናከርና ሥር እንዲሰድ ማድረግን ነው።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Maurice Dobb, *Studies in the Development of Capitalism,* New York; International Publishers, 1976, p. 265; p. 295.
2. Ibid., pp. 296 - 297, p. 302.
3. Ibid., pp. 334.
4. Ibid., pp. 306.
5. Ibid., p. 309.
6. Ibid., p. 310.
7. Ibid., p. 316.
8. *"Socio — Cultural Transformation in developing Countries"*, 22nd Congress of the International Institute of Sociology September, 1969, p. 8.
9. Maurice Dobb, op. cit., p. 316.
10. A. Z. Manfred, *A short History of the World, Volume II* Moscow: Progress Publishers, 1974, p. 332.
11. N. Sivachyov and E. Yazkov, *History of the USA since WW I,* Moscow: Progress publishers, 1976, p. 217.

Digitized by Google

12. Harry Magdof, *The Age of Imperialism,* New York, Monthly Review press, 1969, p. 56.

13. *Ibid.* p. 55.

14. Patrick Gilkes, *The Dying Lion,* London: Jalian Freedom publishers Ltd., 1975, p. 157.

15. Harry Magdoff. *op. cit.*, p. 176.

16. *U.S. News and World Report*: February 25, 1963, p. 4.

17. Hary Magdoff. *op. cit.*, p. 128.

18. Vasily Vakhrushev, *Neo-colonialism: Methods and Manoeuvres,* Moscow: Progress Publishers, 1973, p. 204.

19. Cheryl Payer, *The Debt Trap,* New York; monthly Review press, 1974, pp. 50 - 75, pp. 117 - 166, p. 202.

20. Vasily Vakhrushev, *op. cit.*, p. 142.

21. Ibid., p. 140.

22. Ibid., pp. 143 - 144.

23. Ibid., p. 145.

24. Ibid., p. 158.

25. Ibid., p. 161.

26. 22nd Congress of the International Institute of Sociology, *op. cit.*, pp. 8-9.

27. Vasily Vakhrushev, *op. cit.*, p. 49.

28. Harry Magdoff, *op. cit.*, p. 150.

Digitized by Google

ባሕልና ንድፍሃሳባዊ ግንዛቤው

(ክፍል ፪)

— መሐመድ ሣላ

ባህል ማኅበራዊክ ስተት እንደመሆኑ ከወቅቱ የኅብረተሰብ ችግሮች ተገንጥሎ ለማደግ የሚችል ክስተት አይደለም ። ባህል የሰፊውን ሕዝብ ርዕዮተ ዓለማዊ አስተሳሰቦችና ፍላጐቶች ሲገልጽና ለብዙኃኑ በሚጠቅም መንገድ ሥርጭት ሲያገኝ ሕዝባዊ ባህል ወይም ብሔራዊ ባህል ይባላል ።

በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ የሁለት ባህሎች አንዱ የበላይነት ያለው የገዥ መደብ ባህልና ሶሻሊስታዊና ዲሞክራቲክ ባሕሪይ ያለው የሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ የባህልክፍል መገኘት ፣ አብዮታዊ ኃይሎች የባህልን ባሕሪይና የዕድገት አቅጣጫ ጠንቅቀው መረዳት እንዳለባቸው ያመለክታል ። ምክንያቱም ከሁሉም በላይ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የከበርቴው ባህል በማኅበራዊ ተግባሩ የርዕዮተ ዓለም ትግል ማካሄጃ መሣሪያ በመሆን የሰፊውን ሕዝብ አስተሳሰብ ወይም አዕምሮ ለማላሸቂያ የሚጠቀምበት ነው ። ከበርቴው ሆን ብሎ በባህል አማካኝነት በሚያሳድረው ተጽዕኖ የተነሳ የሰፊውን ሕዝብ ንቃተ ኅሊና የተዛባ ፣ ምሥቅልቅሉ የወጣ እንዲሆን ፣ በውዥንብር ውስጥ እንዲገባና ከተሳሳቱ ሐሳቦች ጋር እንዲቀራኝ ያደርገዋል ። ከበርቴው ይህንን ለማድረግ የሚችለው በየሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችና በሕዝብ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ወዘተ . . . አማካኝነት ነው ።

«የማቴሪያላዊ ምርት ማከናወኛ ባለቤትነትና ቁጥጥር ያለው መደብ በኅሊናዊ ምርት ማከናወኛዎችም ላይ ቁጥጥር አለው ።» ይህም በመሆኑ ከበርቴው በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የግለሰቦችንና የማኅበራዊ ቡድኖችን አስተሳሰብ ስሜትና ፀባይ ፣ የአኗኗር ፈሊጥና ደንብ ለርሱ በሚጠቅም መንገድ ለመቆጣጠር ያስችለዋል ። ግለሰቦችና ማኅበራዊ ኃይሎች በዚህ ዓይነቱ የባህል በተለይም የኅሊናዊ ባህል ክስረትና ውዥንብር ውስጥ በሚገ

Digitized by Google

ኙበት ጊዜ በሚፈጠረው የኑሮና የሕይወት
ምስቅልቅል የተነሳ ዕውነተኛ መነሻ
ቸውን ለመገንዘብ ባለመቻሉ ገብታዊ
የሆኑ ማኅበራዊ ተቃውሞዎችን ያነሳሉ ።

በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ውስጥ ሰፍና
በሚገኘው ገላዊ የባለቤትነት ግንኙነት
የተነሳ የከበርቴው ባህል የሸቀጥነት ባሕ
ሪይ ይታይበታል ። ለዚህም ነው የምዕራብ
አውሮፓ ባህል የሸማች ባህል በመባል የሚ
ታወቀው ። ለከበርቴው ባህል የፍጆታ ሸቀ
ጦች ባሕሪይ ያለውና ለሽያጭ የሚመረት
በመሆኑ ፤ እንደማንኛውም ሸቀጥ በገበያ
ውስጥ ተፈላጊና ይህንንም ፍላጐት ለማር
ካት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል ። ከዚ
ህም የተነሳ የሸማቾች ባህል ወይም«የብዙ
ኃን»ባህል የሚባለው ባህል ከላይ የተጠቀሰ
ውን የሸቀጥ ባሕሪይ ለማሟላት ለሸማቹ
ደስ የሚል ፣ ምቹና በቀላሉ ሊያገኘው የሚ
ችል መሆን አለበት ። እነዚህ ደግሞ ከሰው
ማቴሪያላዊና ህሊናዊ ፍላጐትጋር እምብ
ዛም ተመሳስለው አይገኙም ።

ምክንያቱም በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችና
በልዩ ልዩ መንገዶች በሚካሄደውና በሚደ
ረገው ከፍተኛ ማስታወቂያ የተነሳ በሸማቹ
ሥነ ልቦና ላይ ተጽዕኖ እንዲያድር ይደረ
ጋል ። ማስታወቂያ በብዛትና በተደጋጋሚ
ሲካሄድ በሸማቹ አዕምሮ ውስጥ ፍላጐትን
ሰው ሠራሽ በሆነ ሁኔታ በመፍጠርና እን
ዲሰርፅ በማድረግ ሰው ሸቀጦችን እንዲ
ገዛ «ይገደዳል» ። በዚህ ሁኔታ ሸቀጦች
የሚሸመቱት ለተደረገው ማስታወቂያ
ምላሽ በመሆን ነው ።

ከዚህ የምንረዳው ባህልን እንደ ርዕዮተ
ዓለምና እንደ ርእዮተ ዓለም ትግልመካሄጃ
መሣሪያ ልንጠቀምበት እንደምንችል ነው ።
አለፍ ብለን ለመጥቀስ እንደሞከርነው በካ
ፒታሊስት ስርዓት ካፒታሊስቱ የምርት ማከ
ናወኛ መሣሪያዎች ባለቤትነት በመሆኑ በገ
ለሰቦችና በማኅበራዊ ቡድኖች የአኗኗር
ፈሊጥ ፣ አስተሳሰብ ፣ ገምቶች ወዘተ…ላይ
ተጽዕኖ በማድረግ ለርሱ በሚያመቸው መን
ገድ «ሥርዓት» ሊያሲዛቸው ይሞክራል ።
የርሱንም አስተሳሰቦች ፣ እምነቶችና ፍላጐ
ቶች በማሠራጨት የሰውን አዕምሮ ያደነ
ዝዛል ። የዚህ ተግባራዊ ክንዋኔ ደግሞ ትን
ብር ያለው የአስተሳሰብ ሥርዓትን የሚጠ
ይቅና የሌሎችን የአስተሳሰብ ሥርዓት የሚ
ያኖጋ በመሆኑ፤ባህል እንደ ርዕዮተ ዓለምና
የርዕዮተ ዓለም ትግል ማከናወኛ መሣሪያ
ነት ያገለግላል ።

ባህል በሌላ በኩል በመደብ ኅብረተሰ
ቦች ውስጥ መደቦች ባላቸው ሥፍራና በሚ
ያከናውኑት ተግባር የተለያየ ነው ። በመ
ሆኑና መደቦች ስለ ዓለም ያላቸውን ግንዛ
ቤና ማኅበራዊ ሁኔታዎች እንዳሉ ለማቆየት
ወይም ለመቀየር በሚኖራቸው የርዕዮተ
ዓለም ልዩነት የተነሳ በማንኛውም ብሔር
ውስጥ ሁለት ባህሎች እንደሚገኙ ሌኒን
ያስተምረናል ።[1]

ባህል ባጠቃላይ ኪነትና ሥነ ጽሑፍ
በተለይ ከካፒታሊስቱ ሥልተ ምርት ጋር
የተጣጣመ ግንኙነት ኖሯቸው የሚያድጉ
ክስተቶች አይደሉም ። ኅሊናዊ ምርት በማ
ቴሪያላዊ ምርት የሚወሰንና በርሱም ላይ
የሚመሠረት ቢሆንም ፤ ከፍተኛ የማቴሪያ
ላዊ የምርት ደረጃ ግን ሁል ጊዜ ከፍተኛ
ደረጃ ላይ የሚገኝ የኅሊናዊ ምርትን ይፈ
ጥራል ወይም ያስከትላል ማለት አይደለም ።
ይህም ሲባል ግን የሳይንስ በተለይም የተ
ፈጥሮ ሳይንስ እንደኅሊናዊ ክስተትነቱ
ከምርት ተግባር ጋር በቀጥተኛና በቅርብ
የተያያዘ በመሆኑ ከምርት ተግባር ጋር
አብሮ አያድግም ማለት አይደለም ። በሌላ
በኩል ግን ኪነትና ሥነ ጽሑፍ ከማቴሪ
ያላዊ የምርት ተግባር ጋር በተዘዋዋሪ
መንገድ የተያያዙ በመሆናቸው እንደተፈ
ጥሮ ሳይንሶች ከማቴሪያላዊ ምርት ጋር
በተመጣጣኝ ሁኔታ ወይም ደረጃ አድ
ገው አይገኙም ።

Digitized by Google

ከዚህ የምንረዳው ቁምነገር ኪነትና ሥነ ጽሑፍ አንፃራዊ ነፃነት እንዳላቸው ብቻ ሳይሆን ፣ ከካፒታሊስቱ ሥልተ ምርት ጋር እንደማይጣጣሙና ከማቴሪያላዊ ምርት አንፃር በተለይም ከካፒታሊስቱ ሥርዓት ማቴሪያላዊ ምርት አንፃር ሲታዩ ፣ ወደኋላ ቀርተው ወይም እውንታን በተዛባ መንገድ በማንፀባረቅ ላይ እንደሚገኙ ነው ። ካርል ማርክስ እንዳለው ፤ ማቴሪያላዊ ምርት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ለተወሰኑ የኅሊናዊ ምርት ክፍሎች ለምሳሌ ለኪነትና ፓይትሪ ተፃራሪ ነው ።

ኪነትና ሥነ ጽሑፍ ከማቴሪያላዊ ምርት ይልቅ በጣም ዳብረው ወይም ቀድመው የመገኘቱ ጉዳይ የካፒታሊስቱ ሥልተ ምርት ልዩ ባሕርይ አይደለም ። እንዲያውም በነሱ አለመጣጣም ምክንያት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ኪነትና ሥነ ጽሑፍ ወደኋላ የመቅረት አዝማሚያ ያሳያሉ ። በግሪክ ውስጥ ከሦስትና አራት ሺህ ዓመታት በፊት የማቴሪያላዊ ምርት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት ወቅት ፣ እንኳን ከፍተኛ የሆነ የኅሊናዊ ምርት ፣ በተለይም ሥነ ጽሑፍና ኪነት ይገኝ ነበር ። ከዚህ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ የማቴሪያላዊ ምርት ደረጃ ያለው ካፒታሊዝም እንኳ ከዚህ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ደረጃ ላይ የሚገኝ ኪነትና ሥነ ጽሑፍ የለውም ። በሌላ በኩል ደግሞ ሶሻሊስት ሥርዓት ከደረሰበት የማቴሪያላዊ ምርት ደረጃ ጋር ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ ኪነትና ሥነ ጽሑፍ አለው ።

የባህልን ደረጃ ከፍ በማድረግና የሕዝብን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችል መንገድ ለማሠራጨት የሚደረገው ጥረት ይህንን ችግር በፈጠረው በራሱ በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ይኸ ችግር ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ባለው የሽግግር ወቅትም ይዛመታል ።

ከዚህም የተነሳ የባህል አብዮት ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ሽግግር ውስጥ የመደብ ትግሉ አካል በመሆን የወዝ አደሩ መደብ በአሮጌው የቡርዧው ባህል ምትክ አዲሱን የሶሻሊስት ባህል የሚፈጥርበት ሂደት ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ ወዝ አደሩ የቡርዧውን መደብ ባህል እንዳለ የሚሽረው ወይም የተቀበለውን በቀጥተኛ መንገድ የሚገለገልበት አይደለም ። ከከበርቴው ባህል በጐ የሆነውን ማለትም የሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታን የሚያግዘውንና የሚያፋጥነውን ተቀብሎ ከሥርዓቱ ጋር በሚጣጣም ፣ እንዲሁም ለሰፊው ሕዝብ አገልግሎት በሚዳረስ መንገድ ይጠቀምበታል ። ባህልን በተለይም ከተፈጥሮ ሳይንስ የሚመነጨውን ኅሊናዊ ባህል ለጥቂቶች ጠቃሚነት ከመዋል ወደ ብዙኃን አገልጋይነት ይለውጠዋል ። ብሎም ለዚሁ የብዙኃን ባህል ወደ ከፍተኛና አዲስ ደረጃ ማደግ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ለመፍጠር ግልጋሎት ላይ ይውላል ።

የባህል አብዮት ከጠቅላላው የሰው ልጅ የረጅም ጊዜ የባህል ዕድገት አንፃር ሲታይ ከፍተኛ የሆነ አብዮታዊ እመርታ ነው ። የባህል አብዮት ዓላማ የሰውን ስብእና ጠብቆና ፍላጎት አርክቶ በተሟላ መልኩ የሰውን የመፍጠር ችሎታ ለማዳበር በመሆኑ ፣ ግብታዊ ሳይሆን ብቃትና ጥራት ያለው ፣ ድርጅት የሚያስፈልገው ፣ ረጅም ጊዜን መራራ ትግልንና የማያሰልስ ጥረትን የሚጠይቅ ሂደት ነው ።

ለባህል አብዮት ተግባራዊነት የፖለቲ ሥልጣን ወደ ሠራተኛው መደብ መሸጋገር ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ የሆነውን ያህል ፣ የባህል አብዮት በተራው ከሚያስከትለው የባህል ደረጃ እድገት ኀብረተሰቡን ወደ ሶሻሊዝም ለማሸጋገ ፣ የሥራን ምርታማነት ከፍ ለማድረግና ሰፊውን ሕብዝ በመንግሥት አስተዳደርና በኢኮኖሚው መስክ ያለውን ተሳትፎ ለማዳበር የሚረዳ በሽግግር ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው የመደብ ትግል ግራመጃ መሣሪያ ነው ።

Digitized by Google

በዚህ የሽግግር ወቅት በባህሉ መስክም የሚደረገው ትግል በሌሎች መስኩች ከሚደረገው ትግል ጋር የተያያዘ ብቻ ሳይሆን በጣም ውስብስብና ጥንቃቄንም የሚጠይቅ ነው ።

በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከወዝ አደሩ መደብና ከገበሬው ክፍል በርካታ የሆኑ ሕዝባዊ ምሁራንን ለመፍጠር ስለማይቻል፣ የሠራተኛውን መደብ የማቴሪያላዊና የኅሊናዊ ባህሉን ደረጃ በማሳደግ የመመራመርና የመፍጠር ችሎታውን ለማዳበር የቡርዧው ኢኰኖሚያዊም ሆነ ርዕዮተ ዓለማዊ ጥቅሙ የማይፈቅድለት ከመሆኑም በላይ ፣ እንዲያውም የሠራተኛው መደብ የዚህ ሥርዓት የባህል ውጤቶች ተቋዳሽ አያደርገውም ። ይሁን እንጂ ባህል በበቂ ባላደገበት ሥርዓት ውስጥ ያሶሻሊስት አብዮት ሊካሄድ አይችልም በማለት የሶሻሊስት አብዮትን የሚከዱትን የምዕራብ አውሮፓ የሶሻል ዲሞክራቶችንና ሜንሽቪኩችን ሌኒን አጥብቆ ታግሏል ።

በሌላ በኩልም ደግሞ «አዲስ» «ፍጹም ወዝ አደራዊ ኪነት» በቡርዧዋ ኪነትና ባህል ፈንታ መፍጠር አለብን የሚሉትንም «የፕሮሌቴኩልት» የተሳሳተ የባህል አመለካከት አውግዞ ፣ ታግሏል ። ይህ አመለካከት የባህልን ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከዝቅተኛ የማኅበራዊ ሥርዓት ወደ ከፍተኛ የማኅበራዊ ሥርዓት መሸጋገርን የሚክድ በመሆኑ የተሳሳተ ነው ።

የሶሻሊስት ባህል አዲስ ብቻ ሳይሆን ሰው አሁን ከደረሰበት ደረጃ አንፃር ከፍተኛ ባህል እንደመሆኑ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት ።

አንደኛ ባህልን ሕዝባዊ ማድረግ ፣ ይህም የሚከናወነው ከሁሉም በፊት ማንኛውንም የኅሊናዊ ሀብት ክምችት ፣ በሳይንስና በኪነት ረገድ የተገኙትን ውጤቶች የሕዝብ በማድረግ ነው ። የሰፊውን ሕዝብ የትምህርትና የባህል ደረጃ ከፍ በማድረግ የመፍጠር ችሎታውን ለማሳደግ የሚረዳ ስራ አድማስ በመፍጠር ነው ።

የሶሻሊስት ባህል በባሕሪው ሕዝባዊ በመሆኑ በዓላማውና በተግባሩ ለሠፊው ሕዝብ ጠቃሚ ካልሆነው የቡርዧ ባህል የተለየ ነው።ምክንያቱም የባህል አብዮት በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ በሰፊው ሕዝብና በባህል መሀከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ እንዲሁም ባህልን የሕዝብ አገልጋይ ስለሚያደርግ ነው ።

ሁለተኛ ፣ የሶሻሊስት አብዮት ኰሚኒስታዊ ሥነ ምግባርን የሚገነባና በሳይንሳዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ሠራተኛውን ሕዝብ ከአድኃሪ አስተሳሰቦችና ኢሳይንሳዊ አመለካከቶች አርነት የሚያወጣ ነው ። በሌላ አነጋገር የካፒታሊስቱ ሥርዓት የኅሊናዊ ባህል በሠራተኛው ሕዝብ አዕምሮ ውስጥ የፈጠረው ተጽዕኖ ይደመስሳል ። ይህንን ሐቅ በማስመልከት ሌኒን እንዲህ ይላል ።

ማይም ሰው ከፖለቲካ ተሳትፎ ውጭ የሚገኝ በመሆኑ በመጀመሪያ መማር ይኖርበታል ። ያለ ትምህርት ፖለቲካ ሊኖር አይቻልም ፣ ትምህርት ከሌለ የፈጠራ ወሬ ሀሚታ ፣ አፈታሪክና ምክንያት የሌላቸው ጥላቻዎች እንጂ ፖለቲካ አይኖርም ።[1]

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሌኒን መሠረታዊ ሐሳብ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ መማር እንዳለበት በግልጽ የሚያስረዳ ቢሆንም መማር በሚልበት ጊዜ ግን ማንበብና መጻፍ እንዲሁም የአራቱን መደብ ስሌት ዕውቀት መገብየት ብቻ ግን አይደለም ። ከዚህ መሠረታዊ ዕውቀት ባሻገር የሥራ ምርታማነትን ለማሳደግ

Digitized by Google

አዳዲስ ቴክኖሎጂን ለመፍጠር ሠራተኛው ሕዝብ በመንግሥት አስተዳደርና በኢኮኖሚ መስክ ያለውንም ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ነው ።

ሦስተኛ ፤ ሶሻሊስት ባህል ሰብአዊና በይዘቱም ሆነ በማኅበራዊ ተግባሩ ከፍተኛ ሥነ ምግባር ያለው ነው ። የባህል አብዮት በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ የሚከናወን ቢሆንም በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ በሕዝቦች መሀከል ያለውን ያልተመጣጠነ የባህል ዕድገት ደረጃ ከማጥበብ አልፎ እኩል ለማድረግ የሚከናወን እንቅስቃሴ ነው ።

ሌላው የሶሻሊስት ባህል ሰብእና የሚገለጽበት መንገድ የሰፊውን ሕዝብ ችሎታ ለማዳበር «ሁሉም ነገር ለሠራተኛው» የሚል መሠረታዊ ዓላማ ያለውና ለዚህም ተግባራዊነት የማያሰለስ ጥረት የሚደረግ በመሆኑ ነው ።

አራተኛ ፥ በይዘቱ ሶሻሊስታዊ ፥ በቅርጹ ብሔራዊ ባህልን ለመፍጠር የሚያስችል ዓላማ ስላለው የሶሻሊስት ባህል ዓለማአቀፋዊ ባሕርይ አለው ። በሕዝቦች መሀከል ያለውን ያልተመ ጣጠነ የባህል ዕድገት ደረጃ በማጥፋትና ያላደገ ባህል ያላቸውን ሕዝቦች ባህላቸው እንዲያድግ ያደርጋል ። የባህል አብዮት ማቴሪያላዊ ባህል ብሔራዊ ቅርጹን እየቀየረና ድንበሩን እያለፈ እንዲሄድ በማድረግ የሌሎች ሕዝቦች ባህል አካል እንዲሆን አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ባህል ይበልጥ ሁለንተናዊ እንዲሆን ያደርገዋል ።

ቋንቋን ለምሳሌ ብንወስድ ብሔራዊ ባህልን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። ሕዝቦች የራሳቸውን ባህል የሚገነቡትና የሌሎች ሕዝቦችንም ባህል የሚረዱት በቋንቋ አማካይነት ነው ። ይሁን እንጂ በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰቦች የኢኮኖሚ የእድገት ደረጃቸው ያልተመጣጠነ እስከ ሆነ ድረስ የቋንቋቸው ማኅበራዊ አገልግሎት ደረጃ ያልተመጣጠነ ነው ። ይህንን ያልተመጣጠነ የዕድገት ደረጃ በማጥበብ ፥ የዕድገት ችግሮችን ማጥፋት የባህል አብዮት አንድ እራሱን የቻለ ሰፊ የትግል መስክ ነው ።

የባህል አብዮት አጠቃላይ የድገት አቅጣጫዎች

የባህል አብዮት የሰፊው ሕዝብ ባህል የሚያድግበት ፥ ሕዝባዊ ምሁሩንና ካድሬዎች በብዛትና በጥራት የሚፈልቁበት ፥ ሳይንስ ፥ ሥነ ጽሑፍና ኪነት ሕዝባዊ ዓላማንና ፍላጐትን ተከትለው የሚያድጉበትና ፥ ሠራተኛው ሕዝብ በሶሻሊስታዊ ንቃት የሚኰተኰትበትና ርእዮተአለሙንም ከግል ሕይወቱ ጋር የሚዋሀድበት የረጅም ጊዜ ሂደት ነው። ሰፊውን ሕዝብ በቡርዧው ሥርዓት ውስጥ ይደርስበት ከነበረው የባህል ጭቆና ነፃ የሚያወጣውና በዚህም ሂደት ውስጥ ለሚፈጥረው አዲስ ባህል ባለቤት የሚያደርገው ነው ።

ይሁን እንጂ በባህል አብዮት አማካይነት የሚፈጠረው አዲሱ የሶሻሊስት ባህል ከቡርዧው ባህል የተለየ ብቻ ሳይሆን በጣም ከፍተኛ በሆነ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝና የላቀም ጭምር ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሰውን ሰብአዊ የሚያደርግ ነው ። በአዲስና በከፍተኛ ደረጃ ላይ የተዋቀረ ባህል እንደመሆኑ በሁለንተናዊ የዕድገት ሕግጋት የሚገዛ ነው ። ሶሻሊዝም ካፒታሊዝምን በመሻር የሚገነባ ሥርዓት እንደመሆኑ አዲሱ የሶሻሊስት ባህል ከአሮጌውና ከተሻረው

Digitized by Google

ሥርዓት የሚወርሳቸውና ቀደር የሚገለገልባቸው ባህሎች አሉት ። የሶሻሊስት ባህል ተራማጅ ባህሎችን ከካፒታሊስት ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ከቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓቶችም ይወርሳል ። ለምሳሌ የተፈጥሮ ሳይንስ ግኝቶችንና የቋንቋ ዕውቀትን ፣ የሎጂካዊ አስተሳሰብን ፣ ደንቦችን ፣ ቴክኖሎጂን ወዘተ . . . ይወርሳል ። ይህም የዚህን ባህል ተራማጅነትና የደረጃውን ከፍተኛነት ከማሳየቱም በላይ ከሰው ልጅ ተራማጅ ባህሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያል።

የአዲሱ ባህል ባለቤትና ገንቢ የሆነው የሠራቱኛው መደብ የቅድመ ሶሻሊስት የመደብ ሥርዓቶች ባህልን ይወርሳል በምንልበት ጊዜ ግን ከወዝ አደሩ መደብ ርእዮተዓለምና የመደብ ጥቅም አኳያ እየታየ እንደሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል ።

የባህል አብዮቱ ከቀድሞው ሥርዓት የወረሳቸውንም ሆነ በአዲስ መልክ የሚፈጥራቸውን ባህል ስንገመግም ሂደቱ የሚከተሉትን የዕድገት አቅጣጫዎች ይከተላል ።

— ማይምነትን ጨርሶ በማጥፋት የሰፊውን ሕዝብ የትምህርት ደረጃ በየጊዜው ማሳደግ ፣

— ከሠራተኛውና ከገበሬው ውስጥ በማያቋርጥ የሥልጠና ፕሮግራም አማካይነት ሕዝባዊ ምሁራንን በብዛት ማፍራት ፣

— ሳይንስ እንዲያድግ ፣ በምርት መስክም እንዲያገለግል በማድረግ የሚገኙትን ውጤቶች የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎትና የሶሻሊዝምን ግንባታ ሂደት እንዲያገዙ ማድረግ ፣

— ሥነ ጽሑፍና ኪነት በተሟላ መልክ እንዲያድጉ በማበረታታት ግዙፍ የባህል ሀብትን ወደ ሕዝብ ንብረትነት መለወጥ ፣

— በሰፊው ሕዝብ ውስጥ የፈጠራ ክንዋኔዎች እንዲያብቡና ሠራተኛው ም ሕዝብ ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚያሳየውን ታታሪነት በማበረታታት ሰፊና ተከታታይ የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ትምህርት መስጠት ናቸው ።

እነዚህ ከላይ የሰፈሩት ነጥቦች ዝርዝር ባይሆኑም የባህል አብዮት በሚካሄድበት ወቅት በአመዛኝ ትኩረት የሚሰጣቸው አጠቃላይ የዕድገት አቅጣጫዎች ናቸው ።

ባህልና ኪነት

የባህልን ምንነት ለመግለጽ በተደረገው ሙከራ ላይ እንደተመለከተው ኪነት በሀሊናዊ ባህል ውስጥ ሊጠቃለል እንደሚችል አይተናል ። ስለሆነም በኪነት መስክ የሚደረግ ዕድገት የኅብረተሰቡ ኅሊናዊ ሕይወት የዕድገት መስክ ከመሆኑም በላይ የዚሁም መስክ ዕድገት መገለጫ ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል ።

ኪነት የባህል አንድ አካል በመሆኑ የባህል አጠቃላይ ባሕርያት በርሱም ላይ የሚታይ ነው ። በባህልና በኅብረተሰብ ኢኮኖሚ መሀከል ያሉትን የግንኙነት መልኮች በሁለት አጠቃላይ ሐሳቦች አንፃር ከዚህ በመቀጠል ለማየት እንሞክራለን ። እዚህ ላይ ግን መታወቅ ያለበት ጉዳይ የግንኙነቶቹ መልኩች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት ሳይሆን ዋቂቶቹን ብቻ ለመጠቆም መፈለጉን ነው ።

ኢኮኖሚ የአንድ አገርን ወይም ብሔርን ባህል (ኪነት) ይወስናል ቢባልም ባህሉ እንዲፈጥር ያደረጉት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ሲለወጡ ባህሉም (ኪነት) አብሮ ይጠፋል ማለት ግን አይደለም ። ምክንያቱም የምርት ተግባር ከንዋኔ ሁልጊዜ የሚፈጸም

Digitized by Google

በመሆኑ በግያቋርጥ ዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙና የዚህም (ባህል) ዕድገት መሠረት ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ ነው።ከዚህም የተነሳ ሥራና ትግል ሁልጊዜ የሚኖራቸውን ያህል ባህልና ኪነትም ሁልጊዜ እያደጉና እየተስፋፉ ይሄዳሉ።በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ይዞታ ቅርጽ ላይ ተመሥርቶ የሚገነባው የአመራረትና የኢኮኖሚ አደረጃጀት በምርት ግንኙነቱ የሚወሰን በመሆኑ የሚለዋወጥ ነው ። ስለሆነም የምርት ግንኙነቱ አጠቃላዩን የሰውን ልጅ የዕድገት ገስጋሴና የግስጋሴውን ደረጃ የሚያመለክት ነው ። ከዚህም የተነሳ ባህልና ኪነት የሚኖራቸውን የመደብ ባሕርይ ከምርት ግንኙነቱ ጋር እየለወጡ በመሄድ ወደ አዲሱ ሥርዓት በመሻሻል እየተሸጋገሩ ያድጋሉ ።

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ግልጽ ሊሆን ይገባል።ከቀደሙት ትውልዶች የተወረሱትንና አዲሱ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የፈጠራቸውን ባህሎችንና የኪነት ክፍሎችን መለየት ያስፈልጋል ። ምክንያቱም ካለፈው ሥርዓት የሚተላለፉት የባህልና የኪነት ክፍሎች በአዲሱ የምርት ግንኙነት ላይ የተገነቡ አይደሉም ። ከዚህም በተጨማሪ በአዲሱ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ የተገነባው የአዲሱ ላዕላይ መዋቅር ክፍል አይደሉም ። ይህ ብቻ ሳይሆን ካለፈው ትውልድ ተላልፈው የሚመጡ የባህልና የኪነት ክፍሎች ተራማጅ የሆነውን መደብ ጥቅምን የሚገልጹ ናቸው እንጂ ከላዕላይ መዋቅሩ ጋር ትይዩ ሆነው የሚገኙ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና መልኮች አይደሉም ።

ካለፈው ትውልድ በአዲሱ ትውልድ የተወረሱ ኅሊናዊ የባህል ክፍሎች የአዲሱ ሥርዓት የሌሎች የመዋቅራዊ ክፍሎች ናቸው ። ስለሆነም ላዕላይ መዋቅር የሚያቅፋቸው ክፍሎች (ባህልና ኪነትን ጨምር) የተገነባበትንና ቅርጽ እንዲይዝ ፥ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ ከሚፈልገው የኢኮኖሚ መሠረት ጋር አብረው ሙሉ በሙሉ የሚጠፉ ወይም የሚለወጡ ነገሮችን ብቻ የያዘ አይደለም ።

ከዚህም የተነሳ ተመሥርተውበት የሚገኙት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በመለወጡ ምክንያት አብረው ሳይለወጡ የቀሩትና በአዲሱ ሥርዓት ተወርሰው የሚገኙ የባህልና የኪነት ክፍሎች የተሟላ ባሕሪያቸውን ይዘው የሚገኙት በአዲሱ ባህል ውስጥ ነው ።

ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረው ባህልና ኪነት አንፃራዊነት እንዳላቸው ለማሳየት እንጂ በመጨረሻ ግን ሁለቱም ቢሆኑ በኢኮኖሚው መሠረት የመወሰናቸው ጉዳይ የማይቀር ነው ። ኢኮኖሚያዊው መሠረት በተዘዋዋሪና ራቅ ባለሁኔታ ሁለቱንም ይወስናል ። በባህልና በኪነት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ በርካታ ክስተቶች ከመኖራቸውም በላይ ሁለቱም በኢኮኖሚው መሠረት በመወሰን ብቻ የሚኖሩ ሳይሆን ፤ እነርሱም በተራቸው በኢኮኖሚው መሠረት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ።

በኪነትና ባህል በአንድ በኩል በኢኮኖሚው በሌላ በኩል ያለው የግንኙነት መልክ ይህ ብቻ አይደለም ። ኢኮኖሚው ባህልና ኪነትን ይወስናል ቢባልም ሁለቱም አንድ ዓይነትና ተመጣጣኝ የሆነ ዕድገት አላቸው ማለት አይደለም።በአብዛኛው ኢኮኖሚው ከባህል ይልቅ በፈጣን ዕድገትና በከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ ባህልና (ኪነት)

Digitized by Google

ግን አንፃራዊ በሆነ መንገድ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ ።

ኪነትና ባህል ከኢኮኖሚው ጋር በተመሳሳይ ፍጥነትና የዕድገት ደረጃ ላይ ያለመገኘት ጉዳይ የመደብ ኅብረተሰቦች ዓይነተኛ ባሕርይ ነው ።

ባህል የጭቁን መደቦችን ጥቅም ሲያንፀባርቅ ተራማጅ ይሆናል ። ባህል ከኢኮኖሚው የዕድገት ደረጃ ቀድሞ የመገኘት አዝማሚያንም የሚያሳየው በሶሻሊዝምና ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት ነው ። አብዮታዊ ሁኔታ ተሟልቶ በሚገኝበትና ከዚያም በኋላ አብዮቱ ፈንድቶ አዲሱን ሥርዓት ለመገንባት ፣ አድኃሪ መደቦችንና የምርት ግንኙነታቸውን ለመበጣጠስና ለመደምሰስ ፣ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ለማፋጠን የሚረዳ የምርት ግንኙነት ለመመሥረትና ሕዝቡን በግሌ ርዕዮተዓለም የማስታጠቅ ጥረት የባህልንም ሆነ የኪነትን የእድገት ደረጃ ያሳድጋል ። ይህ ሁሉ ግን የሚከናወነው ከአዲሱ የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት በፊት አለዚያም ገና እየተገነባ ባለበት ወቅት በመሆኑ ተራማጅና ሕዝባዊ ባህል ትይዩ ሆኖ ከሚገኝበት የላዕላይ መዋቅር ጋር በመሆን ከኢኮኖሚው መሠረት ቀድሞ የመገኘትን አዝማሚያ የሚያሳይ ነው ።

እስከአሁን ድረስ ኪነት የባህል አንድ ክፍል በመሆን ከባህል ጋር ያለውን የወል ባሕርይ ለማየት ሞክረናል ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ኪነት ምን እንደሆነና ባሕርዩስ ምን እንደሚመስል ለማየት እንሞክራለን ።

ኪ ነ ት

ኪነት ሰዎች ስለአካባቢያቸው ሊኖራቸው ከሚችለው በርካታ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መልኮች ውስጥ አንዱ ነው ። ኪነት የዕውቀት ዘርፍ ወይም በመንፈስ ክልል ውስጥ ሊጠቃለሉ ከሚችሉት የንቃተ ኅሊና መልኮች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ባለው ዓላማና እውንታን በሚያንፀባርቅበት መንገድ አንፃር ሲታይ ግን የተለያዩ ባሕርያት ያለው ነው ።

ኪነት የሚገልጸው ሰውን ፣ ባሕርዩን ፣ አካቦት ስለሚገኘው ሕይወት ያለውን ግምትና ዝንባሌ ፣ ኅሊናዊ ሕይወቱን ፣ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎችና በዚህም ጊዜ የሚፈጥራቸውን አስተሳሰቦችና የሚገልፃቸውን ስሜቶች ነው ። ሰውና ሕይወቱ የጥናት መስኩ መሆን የኪነት የተለየ ባሕርይ ነው ። ኪነት ከሌሎች የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና መስኮች የሚለየው በሚያጠናው መስክ ክልል ብቻ ሳይሆን በአጠናን ዘዴውም ጭምር ነው ። ኪነት እውንታን የሚገልጸው ወይም የሚያንፀባርቀው ሳይንሳዊና ሎጂካዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን እውንታን በኪነታዊ የምስሎች ቅርጽ በማንፀባረቅ ማለትም ከእውንታ ጋር በጣም በተቀራረበ ወይም እውንታን በጣም በሚወክል መልክ ፣ አለበለዚያም ጥናቱ ስለሚከናወንበት ነገር የሚሰጠው ገለፃ እውንታን በዓይነ ኅሊና ለመመልከት በሚያስችል ሁኔታ በሥነ ጽሑፍ ፣ በመድረክ ፣ በውዝዋዜ ፣ በማሸብሸብ ፣ በኀዘንና በደስታ በአለባበስና በአለቃቀስ ወዘተ . . . መልክ እንዲሁም በሙዚቃና በቅርጻ ቅርጽ አማካይነት ነው ።

ኪነት ሁኔታዎችንና ክስተቶችን መስለው በሚታዩበት ሳይሆን ሆነው በሚገኙበት መንገድ በተጨባጭ የሚገልጽ ፣ ከእውንታ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማይፃረር መንገድ የሚያንፀባርቅ ነው ።

Digitized by Google

የኪነት ባለሙያው ዕውነታ የሚያንፀባርቀው የዕውነታን ዓይነተኛ ባሕርያት በመጨበጥ ስለ ዕውነታ ባለው ዝንባሌ ላይ ተመሥርቶ ከዕውነታ ጋር በተዛመደና በተጨባጭ መንገድ ነው ። ማለትም ለኪነት ሥራው ርዕዮተ ዓለማዊ ይዘት በመስጠት ነው ። ይህም ኪነት ዕውነታን የመገንዘቢያ ወይም የማወቂያ ክስተት እንደሆነ ያሳያል ።

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሁሉም የኪነት ሥራ የሚገልጸው ሰውን ብቻ ባይሆንም ዋነኛው የኪነት ዓላማ ግን ሰውንና ሕይወቱን መግለጽ ነው ። ኪነት ማናቸውንም ነገር ወይም ክስተት ለመግለጽ ቢችልም የሚያንፀባርቀውን ነገር የሚገልጸው ግን እንዳለና ለራሱ ሲባል ሳይሆን በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ባለው ጠቀሜታ አንፃር ሰብአዊ በማድረግ ነው ። የሰውን ፍላጐት ለማርካት በሚያስችል መንገድ ፣ አኗኗሩንና ሕይወቱን ይበልጥ ለማሳየት በሚያስችልና ከሰው ሕይወት ፣ ትግልና ዓላማ አንፃር በማስተያየት ነው ። ይህ ባይሆንማ የተለያዩት ተጨባጭ ሳይንሶችና ፍልስፍና የሚያንፀባርቁትና የሚገልጹት ያው ኪነት የሚገልጸውን በመሆኑ በመሃከላቸው ምንም ልዩነት ሊኖር አይችልም ነበር ። ኪነት ፣ የተለያዩ የሳይንስ ዘርፎችና ፍልስፍና በወል የሚያንፀባርቁት የጋራ ዓላማ ቢኖራቸውም የሚያተኩሩበት ዘርፍና አገላለጻቸው በተለያየ መንገድ ነው ።

የተለያዩ የሳይንስ ዘርፎችና ፍልስፍና ዕውነታን በፅንሰ ሐሳቦች ሲገልጹ ፣ ኪነት ግን ይህንኑ ዕነውታ የሚንፀባርቀው ፈጠራ በተምሳባቸው እዩታ (Images) አማካይነት ነው ። ከዚህም የተነሳ ኪነት ዕውቀት ልትሆን የምትችለው በፈጠራ እስክበለፀገች ድረስ ብቻ ነው ። ማለትም ሰውንና ሕይወቱን ተጨባጭ ፣ ሕያውና በትክክለኛ እይታው አንፃር በማንፀባረቅ አዲስ ዕውነታን ለመፍጠር ስትችል ነው ። ዕውነትን ልታገለግልና የሰብአዊ ዕውነታን አስፈላጊና ሐቀኛ ገጽታ ለማስገኘት ስትችል ነው ።

የኪነት ባለሙያው የሚገኝበት ኅብረተሰብ ማኅበራዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩበትና የርሱም ርዕዮተዓለማዊ አቋም በኪነት ሥራው ውስጥ የሚንፀባረቅ በመሆኑ ፣ ኪነት የርዕዮተ ዓለም ባሕርይ ይኑረው እንጂ ኪነት እራሱ ግን ከርዕዮተ ዓለም ጋር አንድ አይደለም ። አንድ የኪነት ሥራ የኪነት ባለሙያውን የመደብ ምንጭ ሊያሳይ ቢችልም የኪነት ሥራው ግን ባለሙያው የመነጨበት መደብ ከታሪክ መድረክ ላይ ከጠፋ በኋላም ሕልውናው የሚያበቃ አይደለም ። ስለሆነም ኪነታዊ የፈጠራ ሥራ የሚያንፀባርቀውና መንፀባረቅም የሚቀጥለው የመነጨበት ማኅበራዊና ታሪካዊ ሁኔታ ከጠፋ በኋላም ጭምር ነው ።

የኪነት ርዕዮተዓለማዊ ባሕርይና የመደብ ምንጭ የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል መግለጫ ነው ። በሌላ በኩል ግን በአንድ ወቅት በተለያዩ ሥፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች ወይም በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ በሚገኙ ሕዝቦች መሀከል ኪነት ግንኙነትን ለመፍጠር የሚችል በመሆኑ ፤ ኪነት ሁለንተናዊ ባሕርይ አለው ። ይህ የኪነት ሁለንተናዊ ባሕርይ ተጨባጭነት የሌለውና ከጊዜ ውጭ የሆነ ሳይሆን ፤ በግላዊው ወይም በተጨባጩ የኅብረተሰብ ሁኔታ አማካይነት የሚከሰት ሰብአዊ ሁለንተናዊነት ነው ። የፀራአውያን (የግሪክ) የኪነት ሥራዎች የባሪያ አሳዳሪውን ርዕዮተዓለም

Digitized by Google

ተጽቁመው ለመኖር እንደቻሉ ሁሉ ፤ አሁንም በአንድ በተወሰነ የማኅበራዊ ሥርጭት ዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ አገር ኪነት የወቅቱን ርዕዮተዓለም ተጽቁሞ ሊኖር ይችላል ። የሌላ አገር ሕዝብንም አኗኗር ዘዴ ሊያስተዋውቅ ይችላል ።

ርዕዮተዓለም እየተወለደ ፣ እያደገና እየሞተ ሲሄድ ዕውነተኛ የኪነት ሥራ ወይም ኪነት ግን ሕያው ነው ።

እዚህ ላይ በአረጀ ኪነትና በአረጀ ኅብረተሰብ ኪነት መሀከል ያለውን ልዩነት ግልጽ ማድረግ ይኖርብናል ። ኪነት ከአንድ ሥርዓት ወደ ሌላ አዲስና ተራማጅ ሥርዓት ሊሸጋገር እንደሚችልና በአዲሱ ኅብረተሰብ ውስጥም ያለውን ሥፍራ የተመለከትን በመሆኑ ዳገመኛ አንመለስበትም ።

የአርጅና ኪነታዊና ማኅበራዊ ግንዛቤ አንድ አይደለም ። አንድ የኪነት ሥራ አረጀ የሚባለው ከፍተኛው የዕድገት ደረጃውን ደርሶ የመፈጠር ችሎታውን በማጣት ወይም የሰዎችን ንቃተ ኅሊና ለማዳበር ወይም ለማስተማር ፣ ለመቀስቀስ ተስኖት እያሽቆለቆለ በሚገኝበት ጊዜ ነው ። በሌላ በኩል ግን ኪነት ታዳጊና ተራማጅ ኅብረተሰብን፤ በኢኮኖሚ እየበለፀገ ከፍተኛና ፈጣን ማኅበራዊ ዕድገትና ግስጋሴን እያሳየ የሚገኝን ኅብረተሰብን ሊገልጽ ይችላል ። እንዲሁም ኪነት ያረጀ፣ጭቆናና ብዝበዛ የሰፈነበትን ፣ ዕድገቱንና ተራማጅነቱን ጨርሶ አድኃሪ የሆነ ኅብረተሰብን ሊገልጽ ይችላል ። ኪነት በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስጥ በባሪያው ላይ ይደርስ የነበረውን ኢሰብአዊ ሁኔታ ፣ የጭቆናና የብዝበዛ ግፍ ፣ ባሪያው ይደርስበት የነበረውን ግርፋት ፣ ግድያ ስቅላት ፣ እንደሚናገር የማምረቻ መሣሪያነት ተቆጥሮ ከእንስሳትና ከቁሳቁስ ጋር አንድ እንደሆነ ተደርጎ ይታይ የነበረበትን አሰቃቂ ሁኔታ ያሳያል ። ይህንንም ሁኔታ በመግለጽ የመደብ ኅብረተሰብን በአጠቃላይ፤የባሪያ አሳዳሪውን ሥርዓት በተለይ ሊገልጽ ይችላል ። ኪነት ሕዝብን በማስተማርና በመቀስቀስ ጭቁኑ ሕዝብ በዝባዥ መደቦችን እንዲታገል አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

ከዚህም በተጨማሪ ኪነት ሰፊው አምራች ሕዝብ ፣ የተለያዩ ብሔረሰቦች በፊውዳልና በካፒታሊስት ኅብረተሰቦች ውስጥ የሚገኙበትን ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ፈጠራ በተሞላበት ፣ ስሜትን በሚነካና ለትግል ለማሠለፍ በሚያስችል መንገድ በተለያየ ሁኔታ በማቅረብ ሰፊው ሕዝብ ቁርጠኛ ትግል በማካሄድ ተራማጅ ለሆነ ኅብረተሰብ እንዲታገል ጥሪ ሊያደርግ ይችላል ።

ኪነት በአዲሱ የሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ የሚኖረውን ፍትሕ ፣ እኩልነትና አርነት ፣ ዲሞክራሲ ወዘተ . . . በማሳየት ሕዝቡ ይህንን ሥርዓት በመገንባቱ ተግባር ላይ እንዲሠለፍና፤ በማይዝል ክንዱና በማይደርቀው የኃይል ምንጭ ቁርጠኛ አስተዋጽኦውን እንዲሰጥ ሊያስተምር ይችላል ። በአንፃሩም አሁን በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ እንደሚታየው ለሽያጭና ለትርፍ ሲባል በሚዘጋጁት የኪነት ሥራዎች እንደሚታየው የሕዝቡን ሞራል የሚያዳሽቅ ፣ ሕዝቡን በማስተማር ከመቀስቀስ ይልቅ ስሜቱን የሚበርዝ ፍላጐቱን የሚገድል፤ አለበለዚያም አውገርግር በማቅረብ የወደፊት ሕይወቱን ጨለማ በማስመሰል ተስፋ እንዲቆርጥና ትጥቁን እንዲፈታ ለማድረግ ግልጋሎት ላይ ሊውል ይችላል ።

እንግዲህ እስከ አሁን ለማሳየት እንደሞከርነው ኪነት ተራማጅና አዲስ ኅብረተሰብን ወይም ያረጀ ኅብረተሰብን ወይምጊዜው ያለፈበትን ሁኔታ ሊገልጽ ይችላል ። ይሁን እንጂ ኪነት ያረጀ ኅብረተሰብን በመግለጹ ወይም በማንፀባረቁ ያረጀ ኪነት ነው አይባልም ። የኪነት እርጅና የማስተ

ግር ፣ የመቀስቀስና የፈጠራ ሥራን ለግዳ
በር አለመቻል ነው ።

ኪነት የሚገልፃቸው ሁኔታዎች አሁን
በዓለም ውስጥ በዕውን የሚገኙ ነገሮች ብቻ
ሳይሆን ከረጅም ጊዜ በፊት የነበሩ አሊያም
ገና ወደፊትም ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች
ሊሆኑ ይችላሉ ። ከዚህም የኪነትን አንፃ
ራዊ ነፃነት ለመመልከት ይቻላል ።

ኪነት እንደሌሎቹ የማኅበራዊ ንቃተ
ኅሊና መስኮች ማለትም ርዕዮተዓለም ፣ ፖለ
ቲካና ሕግ ወዘተ . . . ሳይሆን ከኢኮኖሚው
መሠረት ጋር ያለው ግንኙነት ራቅ ያለ በመ
ሆኑ በዕድገቱ ውስጥ ከፍተኛውን ሚና
የሚጫወቱት በኅብረተሰብ ውስጥ ያሉት
የፖለቲካና የኅሊናዊ ሕይወት ሁኔታዎች
ናቸው ። በኅብረተሰብ ውስጥ ያለው የፖለ
ቲካ ሁኔታ አመቺና ዕድገትን የሚያፋጥን፣
አድኃሪ ኃይሎችን የሚታገልና የሕዝቡንም
የመንፈሳዊ ሕይወት የሚያበረታታ ከሆነ
ኪነት ለማደግና ለመስፋፋት ይችላል ።
እንዲያድግ እንቅፋት ከተፈጠረበት እው
ነታን በተጣመመ መንገድ የሚገልጽ አዝ
ማሚያ ስለሚኖረው የሕዝቡን ፍላጐት
የማያረካ ሊሆን ይችላል ። ይህም በመሆኑ
ኪነት በኢኮኖሚ አድገታቸው ባልገፉ አገ
ሮች ውስጥ ባደገ መልኩ ሊገኝና በበለፀ
ጉት የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ደግሞ
በዝቅተኛ ወይም በጣም በተዛባ መልኩ
ሊገኝ ይችላል ማለት ነው ።

የኪነት ሐቀኝነቱ ሕዝባዊነቱ ነው ።
ታላላቅ የሚባሉት የኪነት ፣ የሥነ ጽሑፍና
የሙዚቃ ድርሰቶችና ሥራዎች የሰፊውን
ሕዝብ ፍላጐት ፣ የኑሮ ሁኔታና ስሜት የሚ
ገልጹ ናቸው።በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ
ከአብዮታችን በፊት የነበሩት ድርሰቶችና
ሙዚቃዎች ወይንም ኪነት በአጠቃላይ የሰ
ፊውን ሕዝብ ስሜቶች አልፎ አልፎ አል
ገለፁም ለማለት ባይቻልም ፣ በአብዛኛው
ግን ኪነት ሲያንጸባርቅ የነበረው በወቅቱ
የነበረውን የፊውዳል ሥርዓት ፖለቲካ ፣
ባሕልንና አመለካከትን ነበር ።

ድኅረ አብዮት ኪነት ግን የሚገልፃቸው
ሁኔታዎች ፣ የሚያስተላልፋቸው ሐሳቦችና
ያለው የሰፊው ሕዝብ ወገናዊነት በጣም
ከፍተኛ ነው ። የኪነት ባለሙያዎች በጦር
ሜዳ በመዝመትና በደጀን ተሠልፈው ሕዝ
ቡን በመቀስቀስ ወዘተ . . .ከፍተኛ ሚና
ከመጫወታቸው በላይ ባለፉት ሰባት ዓመ
ታት ውስጥ ኪነት ያሳየው ዕድገት አሀዛዊ
ብቻ ሳይሆን በዓይነትም ጭምር ትልቅ
እመርታ አሳይቷል ።

የኪነት ባለሙያዎችና ደራሲያን አው
ቀውም ሆነ ሳያውቁ ፣ ወደውም ሆነ
ሳይወዱ የተወሰኑ መደቦችን ፍላጐት ፣
የዓለም አመለካከት ፣ ግምቶችና ዝንባሌ
ዎች ኪነታዊ በሆነ መንገድ ይገልፃሉ ።
ይህም ኪነት እንደ አንድ የርዕዮተዓለም
መልክነቱ በመደብ ኅብረተሰብ ውስጥ የመ
ደብ ፀባይ እንዳለው ያሳያል ። በሌላ በኩ
ልም ኪነት በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ
የሚታዩትን ክስተቶች የሚተነትንና የሚ
ያመዛዝን በመሆኑ ክስተቶችን ውብ ፣
ቀንጆ ወይም አስቀያሚ ፣ አስደሳች ወይም
አስከፊ ፣ ክቡር ወይም ዝቅተኛ አለበለ
ዚያም ወራዳ አድርጐ የሚቀርብ በመሆኑ
ኪነት አስተማሪ ነው ። ስለሆነም የኪነት
ማኅበራዊ አገልግሎት በማኅበራዊ ሕይ
ወት ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖና በሚጫ
ወተው ሚና ይከሰታል ማለት ነው ።

ሳይንስና ኪነት የሚያንፀባርቋቸው ሐሳ
ቦች በዘመኑ የሚገኙትን ተራማጅ አስተ
ሳሰቦች ነው።የነዚህም አስተሳሰቦች ምንጭ
የሰፊው ሕዝብ ሕይወት ፣ የትግልና የተግ
ባር ልምድ በመሆኑ ሳይንስና ኪነት የሚ
ያሳዩት ዕድገትና በሥራዎቻቸውም የሚገ
ልጿቸው ሐሳቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ መራቀቅ

Digitized by Google

ከኅብረተሰብ ዕድገት ተገንጥሎ የሚታይ
አይሆንም ።

ማርክሲዝም ሌኒንዝም የሳይንስ ሊታው
ንቶችና ግለሰብ/የኪነት ባለሙያተኞች በኅ
ብረተሰብ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ያላ
ቸውን የመፍጠርና የማደራጀት ችሎታና
የሚጫወቱትን ሚና በምንም ዓይነት መን
ገድ የሚክድ አይደለም ። በሌላ በኩልም
ማርክሲዝም ሌኒንዝም የአዕምሮ ሠራተኞ
ችን ሕልውናና የሚያከናውኑት ተግባር
በሙሉ ያለሰፊው ሕዝብ ማቴሪያላዊ
ምርት ፈጽሞ ሊታሰብ እንደማይቻልም
ያስተምራል ።

ይሁን እንጂ የተጠቀሰውን የሰፊውን
ሕዝብ ወሳኝ ሚና መቀበል ማለት ያንዳንድ
ታዋቂ ግለሰቦችን ፣ ተሰጥኦ ያላቸውን የኪ
ነት ሰዎችና ባለሙያዎችን ሚና መካድ
ማለት ግን አይደለም ። ሳይንስ በሳይንስ
ሊቆች ፣ ኪነት በግለሰብ ወይም በቡድን
የኪነት ባለሙያዎች የፈጠራ ሥራዎች
እንዳደጉና በዚህም ሳቢያ በኅብረተሰብ
ባህላዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እን
ዳደረጉ የሚካድ አይደለም ። ይሁን እንጂ
በኪነት ሥራው ውስጥ ባለኪነቱ ለመግ
ለጽ የሚሞክራቸው ሐሳቦችና ዓላማው
አድርጎ የተነሳባቸው ግቦች የሚመነጩት
ከኅብረተሰብና ኅብረተሰቡ ከሚገኝበት
ዓለማቀፋዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ነው ።
እራሱ የኪነት ባለሙያተኛው የተወሰነ
የማኅበራዊ ግንኙነት ውጤት በመሆኑም ፣
የሚገልፃቸው ሐሳቦችና ለሥራው የሚሰ
ጠው ቅርጽና ውበት የወቅቱ የማኅበራዊ
ኑሮ ሁኔታዎች መግለጫ ናቸው ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. V.I. Lenin, CW. Vol. p. 24
2. Karl Marx, Theories of surplus value, Progress Publishers, Moscow, 1963, part 1, p, 285
3. V.I. Lenin, CW. Vol. 33, p. 78

Digitized by Google



Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER
1985
INSTITUTION

- የኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና የኢምፔሪያሊዝም ደባ
- የብሔራዊ ሃብት ቁጥጥር አንዳንድ መሠረታዊ ሃሳቦች
- ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል
- አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ
- የቅኝ አገዛዝ የመጨረሻዎቹ ቅሪቶች

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት
ቅጽ 2 ቁጥር 9
ሰኔ 1974

Digitized by Google

Digitized by Google

ET274FQ1
Meskerem No. 9
9

መስከረም

ቅጽ 2 ቁጥር 9
ሰኔ 1974

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገጽ 3
- የኢትዮጵያ አብዮትና የኢምፔሪያሊዝም ደባ 14
  —ዶ/ር ንጉሤ አየለ
- የብሔራዊ ሀብት ቁጥጥር አንዳንድ መሠረታዊ ሀሳቦች........ 35
  —ደምሴ ኃይሌ
- ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል ከ18ኛው ምዕተ ዓመት—1950ዎቹ (ክፍል አንድ) 46
  —ኢሳይያስ ደምሴ
- አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ. 66
  —ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ
- የቀኝ አገዛዝ የመጨረሻዎቹ ቀሪቶች 91

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የስፓኝ ቀኝ ገዥዎች ወይም በላቲን አሜሪካ ሕዝቦች አጠራር «ኩንክዊስታዶረስ» በመባል የሚታወቁት አቀኚዎች መላውን ደቡብ አሜሪካ በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉበት ጊዜ ጀምር፣ የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ታሪክ በአንድ በኩል የብዝበዛና የጭቀና ታሪክ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፀረ ቀኝ አገዛዝና የፀረ እጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ የተጋድሎ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን።

በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ከአህጉሩ ቀኝ አገዛዝን ለማስወገድ በተደረገው የነፃነት ትግል እንደ ሌሎች የደቡብ አሜሪካ አገሮች የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮችም ተካፋዮች ነበሩ። በነሲሞን ቦሊቫር፣ በነ ሳን ማርቲን እንዲሁም በኩባዊው ታጋይ ሆሴ ማርቲን የተመሩትን የነፃነት ትግሎች አርአያነት በመከተል፣ የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች «ብር በሌለበት ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ አይገባም» በሚለው መፈክር ሥር ሕዝቡን ሲበዘብዙ ጥሬ ዕቃውን ሲዘርፉ የነበሩትን የስፔን ቀኝ ገዥዎች ለማስወጣት መስዋዕትነት የተሞላበት መራራና ውስብስብ የነፃነት ትግል ሲያካሂዱ ቆይተዋል።

የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች ሕዝቦች በ19ነኛው ክፍለ ዘመን ላይ ባካሄዱት መራራ ፀረ ቀኝ አገዛዝ ትግል የስፔንን የቀኝ አገዛዝ ቀንበር ሰባብረው በመጣል አብዛኞቹ 'ነፃ' መንግሥታት ቢመሠርቱም፣ ከነፃነት በኋላ በሥልጣን ላይ የተፈናጠጡት የየሀገሩ ፀዝባዥ መደቦች ለሌላ ዓይነት ባርነት ዳረጉአቸው። በስፔን እግርም የእንግሊዝ በኋላም የአሜሪካን ካፒታሊዝም በነዚህ አገሮች ውስጥ የቀኝ ግዛት መረባቸውን በመዘርጋት የእነዚህን አገር ሕዝቦች ሥውርና አስከፊ ጭቀናና የብዝበዛ ቀንበር አሸከሟቸው።

የአሜሪካን ካፒታሊዝም መላውን ላቲን አሜሪካ በተለይም ደግሞ የማዕከላዊ አሜሪካንና የካሪቢያን አገሮችን በጥቅም ክልሉ ሥር ለማድረግና ለመበዝበዝ ሙከራ ማድረግ የጀመረው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በነበረው በሞንሮ አማካይነት «የሞንሮ ዶክትሪን» በ1823* ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ነው። 'የሞንሮ ዶክትሪን' መሠረተ ሐሳብ 'አሜሪካ ለአሜሪካኖች' የሚል ሁኖ የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በአሜሪካ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ ለማገድ የተሰነዘረ ቢሆንም፣ ይህ አባባል በወቅቱ በከፍተኛ ደረጃ ካፒታሉን በማስፋፋት ላይ ለነበረው የሰሜን አሜሪካ የቡርዧ መደብ ደቡብንም ሆነ ሰሜኑን የአሜሪካ አህጉር ለሰሜን አሜሪካ /ያንኪ/ የቡርዧ መደብ 'የጓሮ አትክልት ቦታ' ለማድረግ የታለመ ነበር። ይህ ፖሊሲ ተሸፋፍኖ ይቀረብ እንጅ ዓላማውም ሆነ

---

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው።

Digitized by Google

ውጤቱ የዩናይትድ ስቴትስን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በላቲን አሜሪካ ላይ ማስፈን ነበር።

በሌላ በኩል የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች በካሪቢያን የሚገኙ አንዳንድ አገሮችን ቅኝ በማድረግ ብቻ ሳይወሰኑ የስፔን የፊውዳልና የአቀባባይ ቡርዧውን መደብ ለእንግሊዝ ካፒታል በአቀባባይነት እንዲያገለግል በማድረግ፣ በዚህ ሊዛጥር የሰሜን አሜሪካን ካፒታሊዝም መስፋፋት ሲቀናቀኑ ቆይተዋል። በተለይም የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን፣ የካሪቢያን አገሮችንና ቀደም ሲልም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበረውን ሰሜን አሜሪካን የሚያገናኘውን የባሪያ ንግድ መሥመር በበላይነት ይቆጣጠሩ ነበር። የለንደን፣ የሊቨርፑልን፣ የግላስጐንና የሌሎች የእንግሊዝ ከተሞች የባሪያ ነጋዴዎች በተለይ በካሪቢያን አገሮች በሚያካሂዱት የባሪያ ንግድ በወቅቱ ከፍተኛ ትርፍ ያካብቱ ነበር። በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ በተከናወነው የኢንዱስትሪ አብዮት መሳካት እንግሊዝ በካሪቢያንና በማዕከላዊ አሜሪካ አካባቢ በባሪያ ንግድ ያካበተችው ትርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበረው በታሪክ የተመዘገበ ነው።

በሰሜን አሜሪካ የብሪታንያ ቅኝ ገዥነት ተወግዶ ካፒታሊዝም ካንሰራፋ በኋላ የሰሜን አሜሪካ የባሪያ አመላላሽ መርከቦች ከቦስተንና ከሌሎችም ምሥራቃዊ ከተሞች ራም የሚባል ከሸንኮራ አገዳ ጭማቂ የሚሠራ አረቂ ወደ አፍሪካ በመውሰድና በልዋጩ ባሮች ይዘው ወደ ካሪቢያን አገሮች በመምጣት ይሸጡላቸው ነበር። እነዚህ በካሪቢያን አገሮች ውስጥ የተሸጡ ባሮች ሸንኮራ እንዲያመርቱ ይደረጋል። ከሸንኮራው ጭማቂ የሚገኘው ሞላሰስ ወደ ሰሜን አሜሪካ ተልኮ በሰሜን አሜሪካ የመጠጥ ፋብሪካዎች ወደ ራምነት ይለወጣል።

እዚህ ላይ ስለዚህ ጉዳይ የጠቀስንበት ምክንያት ይህ ነጥብ በራሱ የተለየ ትኩረት የሚጠይቅ ሆና ሳይሆን፣ ከዚህ ዓይነት የባሪያ ንግድ የተገኘው ትርፍ በሰሜን አሜሪካ በቦስተንና በፕሮቪደንስ ግዛቶች ውስጥ የተቋቋሙት የብረታ ብረት ሥራ የጉጆ ኢንዱስትሪዎች፣ ጆርጅ ዋሽንግተን የአሜሪካንን አብዮት ሊያካሂድ የቻለበትን ጠበመንጃ ሠርተው ያወጡ ከመሆናቸውም በላይ፣ ሰሜን አሜሪካ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛትነት ነፃ ከወጣም በኋላ ይኸው ሁኔታ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሽኩቻን አስከትሎ እንደነበር ለመጠቆም ነው።

የካሪቢያን አገሮች ቀደም ሲል ለሰሜን አሜሪካ አሥራ ሶስቱ ግዛቶች ያበረከቱት ሸንኮራ አገዳ ብቻ አልነበረም። ለሰሜን አሜሪካ ታዳጊ ኢንዱስትሪዎች የሚሆን ጥሬ ዕቃ፣ ቡና፣ ሙዝ፣ ሌሎች ፍራፍሬዎችና የቀባት እህሎችም አቀራቢዎች ነበሩ። እንዲያውም እነጓቲማላ፣ ሆንዱራስ፣ ኮስታሪካ፣ ፓናማ፣ ሀይቲና የመሳሰሉት በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ካፒታል ሥር በመውደቅ ለአሜሪካና ለአውሮፓ ገበያዎች ፍራፍሬዎችና በተለይም ሙዝ በማቅረብ ሲበዘበዙና ሲመዘበሩ ቆይተዋል። ከዚህም በመነሳት ነው እነዚህ አገሮች 'የሙዝ ሪፐብሊኮች' የሚለውን መጠሪያ ያገኙት።

እንደሌሎቹ የደቡብ አሜሪካ አገሮች የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች አጠቃላይ ችግር የቀድሞ ቅኝ ገዥዎችና የአሁኑ የእጅ አዙር ቅኝ ገዥዎች ያስከተሉት ችግር ነው። የኢምፔሪያሊስቱ አገሮች በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም

Digitized by Google

ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች በነዚህ አገሮች ውስጥ ከሚገኙ አቀባባይ ከበርቴዎች ጋር እጅና ጓንት በመሆን ከፍተኛ ብዝበዛ ሲያካሂዱ ቆይተዋል፤ አሁንም በማካሄድ ላይ ናቸው።

ከመሆኑም በላይ፣ ጊዜ የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች መሠረታዊ ችግር ይኸው፣ የዓለም አቀፍ የካፒታሊስቱ ገበያ የደለደላቸው በአንድ ወይም በሁለት ምርቶች ላይ የተገነባው ኢኮኖሚያቸው ለዕድገት አመቺ ያለመሆኑ፤ እንደ ዩናይትድ ፍሩትና የመሳሰሉት የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች መፈንጫ መሆናቸውና ዋና ዋና የምርት ማከፋፈያዎች የሀገር ውስጥ ለዝባዡ መደቦችና የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የግል ሀብት መሆናቸው ነው።

እንዲያውም በአንዳንዶቹ የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች ዋናው የመሬት ከበርቴ ዩናይትድ ፍሩት የተባለው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ኩባንያ ነው። በነዚህ አገሮች የመብራት ኃይል፣ ውሀ፣ ቴሌፎን፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎትና ሌሎችም የአገልግሎት ሰጭ ሳይቀሩ ድርጅቶች በአሜሪካን ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር ናቸው።

በ19ነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ዊሊያም ወከር የተባለ ትላልቅ የአሜሪካ ባለባንኮች ለነበሩት ለነሞርጋንና ጋሪስን ወኪል የነበረ ግለሰብ ቅጥረኛ ወታደሮችን በመምራት ማዕከላዊ አሜሪካን ወረረ። በአሜሪካ መንግሥት ድጋፍ የማዕከላዊ አሜሪካ ሕዝቦችን በተደጋጋሚ ጨፈጨፈ፣ ዘረፈ። የአሜሪካ መንግሥት ይሰጠው በነበረውም ድጋፍ በመተማመን ራሱን የኒካራጉዋ፣ የኤልሳልቫዶርና የሆንዱራስ ፕሬዚዳንት አድርጐ ሾመ። ይህ ዘራፊና የወንበዴዎች መሪ የሆነ ግለሰብ ከዚህ ድርጊቱ በኋላ ወደ አሜሪካ /ዩናይትድ ስቴትስ/ ሲመለስ የብሔራዊ ጀግና አቀባበል ተደረገለት። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጅኦፖለቲካል አመለካከት የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች ቀደም ካለጊዜ ጀምር የአሜሪካ /ዩናይትድ ስቴትስ/ ቀጥያዎች እንደሆኑ ተደርገው መወሰዳቸውን ነው።

በ1912 የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው ዊሊያም ታፍት «ሦስቱ ከዋክብተችና ጥለቶች (Stripes) እኩል ርቀት ባላቸው ሦስት ነጥቦች ላይ አንዱ በሰሜን ዋልታ፣ ሁለተኛው በፓናማ ካናል /ማዕከላዊ አሜሪካ/ ሦስተኛው ደግሞ በደቡብ ዋልታ /ከማዕከላዊ አሜሪካ በታች ያለውን የደቡብ አሜሪካ ክፍል-አዘጋጅ/ ተተክለው ግዛታችንን የሚያመለክቱበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ከሞራል አንጻር ሲታይ አህጉሩ አሁንም እርግጥ የኛ ቢሆንም፣ ዝርያችን ከሁሉም በላይ በመሆኑ መላው አህጉር የኛ ይሆናል. . .» በማለት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የመስፋፋት ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን የጠነዘ የዘረኝነት አመለካከቱንም ጭምር በገሐድ አስታውቋል። ዊሊያም ታፍት በዚህ ብቻ ሳይቀጠብ የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ዋና ትኩረት ምን መሆን እንዳለበት ሲያብራራ «/የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ/ ለሸቀጦቻችንና ለካፒታሊስቶቻችን ኢንቬስትመንት ትርፍ መገኘቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነ ጣልቃገብነትን መጨመር ይኖርበታል»** ብሎ ነበር።

በዚህ መሠረት የአሜሪካ ኩባንያዎች በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አገሮች ውስጥ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ያዙ፤ የጉምሩክ አገልግሎትን በቁጥጥራቸው ሥር

* Eduardo Galeno, *Open Viens of Latin America*, MR Press, U.S., 1973, p. 121.
** Ibid.

Digitized by Google

አደረጉ ወዘተ . . . ከዚህም አልፈው አሻንጉሊት መንግሥታትን አቋቋሙ፤ በየአጋጣ ውም የአሜሪካ ዜጎችን ደኅንነት ለመጠበቅ በማለት የአሜሪካ መንግሥት በተደጋ ጋሚ ወታደራዊ ጣልቃገብነትን ፈጸመ።

ከ19ነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አገሮች ላይ የአሜሪካ ጣልቃ ገብነት፤የጠመንጃ ኃይል ዲፕሎማሲና የጠመንጃ አፈሙዝ ስም ምነቶች በተደጋጋሚ ተፈጸሙ። ከ1898—1920 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በካሪቢ ያንና በማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮች ውስጥ አሜሪካ ሐያ ጊዜ ጣልቃ ገብ ወታደሮቿን ልካለች። ከእነዚህ ከሐያዎቹ የጣልቃ ገብ ወረራዎች ውስጥ የተወሰኑት በኒካራጓ ላይ የተፈጸሙ እንደነበር የሚታወስ ነው።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አገሮች ያካሄደውን በዛ ያለ ወታደራዊ ጣልቃገብነት የመራው ጀኔራል ስምደሊ በትለር፣ ስለመራው የወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ተልዕኮ ከድርጊቱ በኋላ በ1935 ሲያስታውስ «በሀገራ ችን ውስጥ ካሉት የጦር ኃይሎች ይበልጥ ተዘዋዋሪ በሆነው ማሪን ኮር በመባል በሚታወቀው የጦር ክፍል ውስጥ ለሰላሳ ሦስት ዓመት ከአራት ወር ያህል አገልግ ያለሁ። በዚህም ጊዜ ውስጥ ከምክትል የመቶ አለቃነት ማዕረግ እስከ ሚጀር ጀኔራል ድረስ ደርሻለሁ። ከዚህ ጊዜ ውስጥ አብዛኛውን ያሳለፍኩት ለትላልቅ ከበርቴዎች ለዎል ስትሪትና /ለፊናንስ መሣፍንቶች/ ለባለባንኮች ጋሻ ጃግሬ በመሆን ነው። ነገ ሩን በአጭሩ ለመግለፅ፣ በማስፈራራትና በኃይል በመጠቀም ለካፒታሊዝም ተስማሚ ሁኔታ ፈጥሬያለሁ . . .ናሽናል ሲቲ ባንክ በሀይቲና በኩባ ያለውን ገቢውን እንዲ ሰበስብ /በእነዚህ/ አገሮች ተስማሚ ሁኔታ ፈጥሬለታለሁ . . . ከ1909—1912 ባለው ጊዜ የዓለም አቀፍ ባንክ ባለንብረቶች ለሆኑት ለብራውን ወንድማማች ኒካራጉዋን አጽድቻለሁ፣ በ1916 ለአሜሪካ የስኳር አምራቾች ዶሚኒካን ሪፓብሊክን፣ በ1908 ደግሞ ለአሜሪካ የፍራፍሬ ኩባንያዎች ሆንዱራስን አቀኘቻለሁ »* በማለት በዝርዝርና በግልጽ አስቀምጦት ነበር።

በዚህ መሠረት ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ የአሜሪካንና የአውሮፓን ገበያዎች የፍራፍሬ፣ የቡናና የስኳር ፍላጎት ለማርካት የአሜሪካ ኩባንያ ዎች የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን አገሮች ጫካዎችን ሲመነጥሩ፣ መሬቱ እስኪነ ጥፍ ድረስ ሲያርሱ፣ ከሁሉም በላይ ሠራተኛውን ሕዝብ ክፉኛ ሲበዘብዙ ቆዩ።

በ1933 በጓቲማላ ሁቢኩ የተባለው አምባገነን ከመቶ በላይ የሠራተኛ ማኅበራትና የተማሪ መሪዎችን እንዲሁም የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን አስረሸነ። በጓቲማላ ውስጥ የነበሩ የቀድሞ ነዋሪ ሕንዶች በደቡብ አፍሪካ እንደሚደረገው የይለፍ መታወቂያ እንዲይዙ ሲያደርግና ሌላም ብዙ ግፍ ሲሠራ ከቆየ በኋላ፣ በ1944 በዱዋን አሬቫሎ መሪነት ዲሞክራሲያዊ አመለካከት በነበራቸው ወጣት መኰንኖችና ምሁራን ተገለበጠ። ከ10 ዓመት በኋላ የአሬቫሎ ተራማጅ መንግሥት በኰሎኔል ሩዶልፎ ካስቲሎ አርማስ የሚመራ፣ በአሜሪካ ውስጥ ለዚሁ ተግባር ሲሰለጥን በቆየና በአሜሪካ መንግሥት በታጠቀ የከሐዲዎች ጦር ተወሮ ተገለበጠ። ወረራው በአሜሪካ ኤፍ 47 ቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች የታገዘ ነበር። ይህን ጭፍጨፋ በማ

---

* Eduardo Galeno, *Open Viens of Latin America,* MR Press, U.S., 1973 p. 122

Digitized by Google

ካሂድ ሥልጣን የያዙ ፋሽስቶችና መሰሎቻቸው በጓቲማላ ውስጥ እስከአሁን በሥልጣን ላይ ናቸው ።

በሆንዱራስ የአሚሪካ አምባሳደር የነበረው በሐምሌ 27 ፡ 1961 በአሚሪካ ምክር ቤት ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርቦ በጓቲማላ ቀደም ሲል ስለተደረገው የመንግሥት ግልበጣ ቃሉን ሲሰጥ በ1954 ጓቲማላን 'ነፃ' የማውጣቱን ዘመቻ ካቀናበሩት መካከል እሱ ራሱ ፡ በወቅቱ በጓቲማላ ፤ በኩስታሪካና በኒካራጉዋ የነበሩት የአሚሪካ አምባሳደሮች ይገኙበት እንደነበር ገልጿል ።

በነገራችን ላይ ማዕከላዊ አሚሪካና የካሪቢያን አገሮች /በኩባ ከአብዮቱ በፊት በኒካራጉዋም እንዲሁ ከሳንዲኒስታ ግንባር ሥልጣን መያዝ በፊት/ በዝባዥ መደቦችና ፋሽስታዊ አገዛዛቸው በአሚሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዕርዳታ ላይ የተንጠለጠሉ በመሆናቸው ፡ የመንግሥት መሪ ከሆኑት ፕሬዚዳንቶች ይልቅ ፡ በነዚህ አገሮች ውስጥ በፖለቲካ ተቃዋሚዎች ላይ መውሰድ ያለበትን እርምጃ ፡ መንግሥታቱ መከተል ያለባቸውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወዘተ . . . በሚመለከት ለመሪዎች 'ምክር በመለገስ' ሽፋን የሚወስኑት የአሚሪካ አምባሳደሮች ናቸው ። ይህ ለመሆኑ ምሳሌ መስጠት ይቻላል ። በ1920ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ላይ የሳንዲኒስታ ብሔራዊ ግንባር መሥራች የነበረው አጉስቶ ሲዛር ሳንዲኖ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የደፈጣ ተዋጊዎች በመምራት ለኒካራጉዋ ሕዝብ እውነተኛ ነፃነት ለመታገል ተነሳ ። ለኒካራጉዋ በዝባዥ መደቦች ጥቅም የቆመው የብሔራዊ ጦር የሳንዲኖን የደፈጣ ተዋጊዎች የገጠመው ብቻውን ሳይሆን በአሥራ ሁለት ሺህ የአሚሪካ ጣልቃ ገብ ወታደሮች በመታገዝ ነበር ። ጦርነቱ እስከ 1933 ከተካሔደ በኋላ የሳንዲኖ ጦር እያየለ በመምጣቱ ጦርነቱን በእርቅ ድርድር ለማቆም ተወሰነ ። ሲዛር ሳንዲኖም በወቅቱ የኒካራጉዋ ፕሬዚዳንት ከነበረው አምባገነን ጋር ድርድር ለማድረግ ወደ ማናጉዋ በማምራት ላይ እንዳለ በወቅቱ የብሔራዊ ጦሩ አዛዥ የነበረው ሳሞዛ በመንገድ ላይ አደጋ አስጥሎ ገደለው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳሞዛ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣኑን ይዞ ስለሁኔታው ሲያብራራ፡ ሳንዲኖን እንዲገደል ያደረገው በወቅቱ በኒካራጉዋ የአሚሪካ አምባሳደር በነበረው በአርተር ብሊስ ሉን ትእዛዝ መሠረት መሆኑን አምኗል ። በ1927 የወጣ የአሚሪካ ስቴት ደፓርትመንት መግለጫ አሚሪካ በማዕከላዊ አሚሪካና በካሪቢያን አገሮች ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ሲጠቁም ፤

«(በማዕከላዊ አሚሪካ—አዘጋጅ) ውስጥ ባሉት አምስት ትናንሽ ሪፓብሊኮች ውስጥ ያሉት የኛ ሚኒስትሮች (አምባሳደሮች—አዘጋጅ) ምክር ሰጭዎች ቢሆኑም ምክራቸው ልክ እንደ ሕግ ተቀባይነት አለው . . . የማዕከላዊ አሚሪካን የወደፊቱ ዕድል የምንወስን እኛ ነን ፤ ምክንያቱም ብሔራዊ ጥቅማችን ይህን እንድንፈጽም ያስገድደናልና . . . እስካሁን ድረስ በማዕከላዊ አሚሪካ ውስጥ ሁልጊዜም ግልጽ የሆነ ነገር አለ ፡ ይኸውም እኛ የምንቀበላቸውና የምንደግፋቸው መንግሥታት ሁልጊዜም በሥልጣን ላይ ይቀያሉ ፡ እኛ የማንደግፋቸው ደግሞ ይወድቃሉ ፤ »* በማለት አጠቃሉታል ።

ፋሽስታዊ የሆነ አገዛዛቸውን በማስፈንና የሕዝቦችን ዲሞክራሲያዊ መብት በማፈን የማዕከላዊ አሚሪካና የካሪቢያን አገሮች አምባገነኖች አገራቸውን ለአሚሪካ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አሳልፈው ሸጠዋል ። የኒካራጉዋው አናስታዚዮ ሳሞዛ ፤ እስከ

* El Salvador, A Dossier, CISCAS Publications, 1981, p. 30.

ቅርብ ጊዜ የኤልሳልቫዶርን ሕዝብ ሲጨፈጭፍ የነበረው ማክሲሚላና ሀርናንደዝ፡
የሀይቲው ዱቫልዩር፣ በጓቲማላ ጆርጅ ሁቢኮ ካስቲናዳና ሩዶልፍ አርማስ የሆንዱ
ራሱ አንዲና፣ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በነዚሁ አገሮች በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም
ድጋፍ በቀድሞዎቹ ፋሽስት አምባገነኖች እግር በመተካት ላይ ያሉት አዳዲስ ፋሽ
ስት መሪዎች ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ለአሰቃቂ ብዝበዛ እየዳረጉት ነው። የአሚ
ሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚሰጣቸው ወታደራዊ ድጋፍ ልባቸውን አሳብጦት የአገሬ
ውን ሕዝብ በኃይል በመጨፍጨፍ ሕልውናችንን እናራዝማለን ብለው ቢነሱም
ተስፋቸው የሕልም እንጀራ እየሆነ የቀሙበት መሬት እየከዳቸው ነው።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኒካራጉዋ ሳንዲና በከህደት ቢገደልም እሱ የቀ
ሰቀሰው የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ለሃምሳ ዓመታት ያህል ሳይቋረጥ ሲካሔድ ቀ
ይቶ በሳንዲኒስታ ብሔራዊ ግንባር በሚመራው የኒካራጉዋ ሕዝብ ትግል በድል መደም
ደሙ፣ በአካባቢው አገሮች እንደ ሳሞዛ ያሉ አምባገነኖችና በሕዝብ ደም የተበከሉ
ፋሽስቶች የቀሙበት መሬት በእርግጥ እየከዳቸው በመሔድ ላይ መሆኑን ያመለክ
ታል።

በሌላ በኩል ደግሞ በኤልሳልቫዶር ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በመካሔድ ላይ ያለው
ን ትግል ስንመለከት የኒካራጉዋ ድል በኤልሳልቫዶርም ሊደገም የተቃረበ መሆኑን እን
ገነዘባለን። የኤልሳልቫዶር ሕዝብ ትግል የተጀመረው በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን
ከስፔን ቀኝ አገዛዝ ለመላቀቅ በተደረገው የፀረ ኮሎኒያል ትግል ነው። ከነፃነ
ትም ወዲህ የኤልሳልቫዶር ሕዝብ የትላልቅ ከበርቴዎችን ብዝበዛ በመቃወም በተነ
ሳው አመጽ የማዕከላዊ አሜሪካ አገሮችን ከወገ አጥባቂ ገዥ መደቦች ተጽዕኖ በማ
ላቀቅ በአንድ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሥር ለማዋሀድ በተደረገው እንቅስቃሴና
ማዕከላዊ አሜሪካን የዩናይትድ ስቴትስ ቀኝ ግዛት ለማድረግ ቅጥረኛ ወታደሮችን
በመምራት የመጣውን የአብሪተኛውን የዊሊያም ወከርን ጦርነት በመመከት ተካፋይ
ሆኗል።

አሁን በያዝነው ክፍለ ዘመን የኤልሳልቫዶር ሕዝብ ትግል መፋፋም የጀመረው
በታላቁ የኢኮኖሚ ዝቅጠት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስ
ጥ ከገቡበት ከ1929 በኋላ ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አብዛኞቹ የማዕከላዊ
አሜሪካ አገሮች 'የሙዝ ሪፑብሊኮች' በመባል ቢታወቁም ኤልሳልቫዶር ግን «የቡና
ሪፑብሊክ» ናት። ኤልሳልቫዶር አብዛኛውን የውጭ ምንዛሪዋን የምታገኘው በቡና
ሽያጭ ሁና ሳለ በወቅቱ የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም ክፉኛ አናግተተ በነበረው የኢ
ኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የቡና ዋጋ እጅግ በጣም በማቆልቆሉና ለምግብ እህል ምር
ት የሚውለው መሬት በማነሱ፣ ያለውም በጥቂት የመሬት ከበርቴዎች በመያዙ በሀገ
ሪቱ ውስጥ የኢኮኖሚው ቀውስ እየተባባሰ ሔደ። በዚህ ወቅት ወዝአደሩና ገበሬው
በመደራጀት ለመብታቸው መታገል ጀመሩ። እንዲያውም በ1930 በሚደደይ ሰማንያ
ሺህ የሚሆኑ የእርሻ ወዝአደሮችና ሌሎችም ሠራተኞች ወደ ሳን ሳልቫዶር በመም
ጣት ትዕይንተ ሕዝብ አድርገው ለእርሻ ወዝአደሮች የአነስተኛ ምንዳ መጠን እንዲ
ወሰንና ሌሎችም መሻሻሎች እንዲደረጉ ጠየቁ።

Digitized by Google

በዚሁ ዓመተ ምሕረት /1930/ የሳልቫዶር ኮሚኒስት ፓርቲ በአጉስቲ ፋራቡንዶ ማርቲ መሪነት ተመሠረተ፣ በኢልሳልቫዶር ሠርቶ አደር ሕዝብም ውስጥ ሥር መስደድ ጀመረ። የሳልቫዶር ኮሚኒስት ፓርቲ በሕዝቡ ዘንድ ያለው ድጋፍ እየጨመረ መሔዱን በመመልከት የኢልሳልቫዶር አድኃሪ ኦሊጋርኪ የወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ ከጥቂት ወራት በፊት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሥልጣን ይዞ የነበረውን አራውጆን በመገልበጥ፣ የመንግሥቱን ሥልጣን ምክትል ፕሬዚዳንት የነበረው ፋሽስቱ ጀኔራል ሀርናንደዝ ማርቲኔዝ ጨበጠ።

የማርቲኔዝ ፋሽስታዊ አገዛዝ በሕዝቡ ዘንድ እያደገ ከሔደው የሳልቫዶር ኮሚኒስት ፓርቲ ተቀባይነት ጋር ሊጣጣም ስላልቻለ፤ ኮሚኒስት ፓርቲው በብሔር አቀፍ ደረጃ አመጽ ለማካሔድ ፕላን ነደፈ። ነገር ግን የማርቲኔዝ ሰላዮች አመጽ ከመጀመሩ በፊት እንዲታወቅ በማድረጋቸው ፋራቡንዶ ማርቲና ሌሎችም የኮሚኒስት ፓርቲው መሪዎች ተይዘው ታሠሩ። ሕዝቡ ግን መሪዎቹ ቢታሠሩና አመራር የሚሰጠው ባያገኝም አመጹን ማካሔዱን ቀጠለ። በወታደሩም ውስጥ የኮሚኒስት ፓርቲው ደጋፊዎች ተለቀመው በመያዛቸውና ለማርቲኔዝ ፋሽስታዊ መንግሥት ሁኔታው በማመቸቱ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛና አረመናዊ ጭፍጨፋ ደረሰበት። ገበሬው ከገጠር ወደ ከተማ አደባባዮች እንዲሰባሰብ ተደርጐ የማንታዛ ጭፍጨፋ ተብሎ በሚታወቀው ሰላሳ ሺህ ሰው በግፍ ተጨፈጭፎ ተገደለ። በኒካራጉዋ የአርነት ጦርነት ወቀት የሲዛር ሳንዲኖ ዋና ረዳትና ጸሐፊ የነበረው፣ የማዕከላዊ አሜሪካ ኮሚኒስት ፓርቲና የኢልሳልቫዶር ኮሚኒስት ፓርቲ መሥራች የነበረው ዓለም አቀፋዊው አጉስቲን ፋራቡንዶ ማርቲና ሌሎችም የኢልሳልቫዶር ኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎች ወዲያው ተረሸኑ።

ማርቲኔዝ እንደ ሂትለርና ሞሶሉኒ በሕዝብ ደም የተበከለ ከመሆኑም በላይ የለየለት አምባገነን ነበር። ማርቲኔዝ ድርጊቱ ብቻ ሳይሆን አመለካከቱም ኢሰብአዊ ነበር። ማርቲኔዝ ለሰው ሕይወት ያለውን እጅግ አነስተኛ የሆነ ግምት በዛይማኖት ሽፋፍና ሲያቀርብ « ሰውን ከመግደል ይልቅ ጉንዳንን መግደል የበለጠ ወንጀል ነው፣ ምክንያቱም ጉንዳን አንድ ጊዜ ከሞተ ለዘለዓለም ሙተ የሚቀር ሲሆን የሰው ሕይወት ግን ከሞተ በኋላ በትንሣኤ ጊዜ የሚነሳ በመሆኑ ነው፣ . . .»* በማለት በፋሽስታዊ ድርጊቱ በገሐድ የሚመካ አረመኔ ነበር።

የኢልሳልቫዶርን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ማርቲኔዝ ፋሽስታዊ አገዛዙን ቢያጠናክርም፤ የኢልሳልቫዶርን ሕዝብ ትግል ሊያዳፍን አልቻለም። ማርቲኔዝ በ1944 በተካሔደ አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ ከሥልጣን ሊወገድ ችሏል። በኋላም በማርቲኔዝ እግር እየተተኩ የመጡ አምባገነኖች የሕዝቡን ትግል ለማፈን የተቻላቸውን ሁሉ ቢያደርጉም፤ በፋራቡንዶ ማርቲ የብሔራዊ አርነት ግንባር የሚመራው የኢልሳልቫዶር ሕዝብ ትግል የፋሽስት አምባገነኖችን ዕድሜ በማሳጠር፣ በኒካራጉዋ እንደተደረገው፣ ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ ለውጥ የሚያሰፍንበት ጊዜ እየተቃረበ ነው።

በጓቲማላም በአሁኑ ወቀት አራት የሚሆኑ የፖለቲካና የወታደራዊ ድርጅቶች በጓቲማላ የብሔራዊ አብዮታዊ ኅብረት በሚል ድርጅት ሥር በመሰባሰብና አንድነት በመፍጠር በዚሁ አገር ውስጥ ከ1954 ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባለው

* El Salvador, A Dossier, CISCAS Publication, 1981, p. 7.

ጊዜ ውስጥ ሰባ ሺህ ታጋዮችን በፈጀው ሶሞጣነን መንግሥት ላይ ትግላቸውን እያጧጧፉ ነው። በሆንዱራስም የፍራንሲስኮ ሞርዛን የነፃነት ግንባር የሚባል ተቃ ቁሞ ትግሉን በማፋፋም ላይ ሲሆን፣ በኮስታሪካና በፓናማም የማኅበራዊና የፖለቲካ ቀውሶች በመካረር ላይ ናቸው።

የሞንሮ ዶክትሪን ከወጣበት ካለፈው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ማዕከላዊ አሜሪካንና የካሪቢያን አገሮችን ብቻ ሳይሆን መላውን የደቡብ አሜሪካ አገሮች በሚመለከት የአ ሜሪካ ፖሊሲ ያተኮረው ቀጥተኛ የሆነ የወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን በማድረግ፣ በአ ህጉሩ ውስጥ የወታደራዊ ጦር ሠፈሮችን በማስፋፋት፤ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅቶችን በማደራጀት፣ የኢኮኖሚ ማዕቀብ በማድረግና በመሳሰሉት እርምጃዎች ላይ ነበር። ለዚህም አድኃሪ ተግባሩ ዲሞክራሲያዊ ሽፋን ለመስጠት አልፎ አልፎ ሙከራ አድርጉ ነበር። ለምሳሌ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ 'ለዕድገት ትብብር' /Alliace for Progress/ የተሰኘውን ፕሮግራም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በመላው የደቡብ አሜሪካ አገሮች አበሰረ። በወረቀት ላይ የሰፈረው የዚህ ፕሮግራም ዓላማ የኢኮኖሚ ልማትን ለማዳ በር፣ የመሬት ይዞታን ለማሻሻልና ዲሞክራሲያዊ መንግሥታትን ለመንከባከብ የሚል ሲሆን፣ በተግባር ግን የታየው የዚህ ተቃራኒ ነበር። ይህ ፕሮግራም በላቲን አሜሪካ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ተጽዕና ይበልጥ እንዲጠናከርና ለፋሽስታዊ አምባገነናች በብዛት መፈልፈል አመች ሁኔታ የፈጠረ ነው። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የካርቱና የዱላ ዲፕሎማሲ በስልቱ የተለያየ ቢመስልም በግብ ግን አንድ ነው። ሁለቱም የአ ሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን ተጽዕና በሌሎች አገሮች ላይ ለማስፈን የታቀዱ ናቸው። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የማዕከላዊ አሜሪካንና የካሪቢያን ሕዝቦችን ትግል ለማ ፈን አንድ ጊዜ የካርት ሌላ ጊዜ ደግሞ የዱላ ዲፕሎማሲውን እያፈራረቀ ቢጠቀምም፣ በዚህ አካባቢ ለእውነተኛ ነፃነት በመካሔድ ላይ ያለውን ትግል ለመግታት አልቻ ለም።

ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን በዚሁ አካባቢ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በወታደ ራዊ መስክ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት አላቋረጠም። በአንጻሩም በማዕከላዊ አሜ ሪካና በካሪቢያን አገሮች ለማኅበራዊ ዕድገቱና ብልጽግና በመደረግ ላይ ያለው ትግል በመፋፋም ላይ ይገኛል። በኩባ የሶሻሊስት ሥርዓት መጠናከር፣ በኒካራጉዋና በግሬ ናዳ የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ትግልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አብዮት በአሸናፊነት መውጣት፣ በኤልሳልቫዶር ውስጥ የሚካሔደው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሥር መስደድ፣ በጓቲማላና በሆንዱራስ ውስጥ ካለው እንቅስቃሴ ጋር ተዳምሮ በዚህ አካባቢ የአ ሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን የተጽዕና ክልል እያጣበበው በመምጣት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅቱ የሬጋን አስተዳደር በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አካባቢ በየቦታው በመፈንዳት ላይ ላለው ሕዝባዊ ዕንቅስቃሴ ኩባና ኒካራጉዋን ተ ጠያቂ ናቸው በማለት፣ በነዚህ አገሮች ላይ የጦርነትና የወረራ ዛቻ በመሰንዘር ላይ ነው።

ኩባን በሚመለከት፣ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የፀረ ኩባ ዘመቻ አሁን የተጀ መረ ሳይሆን በኩባ ውስጥ አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ሲካሔድ የቆየ ነው። በተ ለይም ደግሞ ከፕላያ ጊሮን ወረራ መክሸፍ በኋላ፤ ፀረ አብዮት የኩባ ስደተኞችን በአ ሜሪካ አገር በማሰልጠን ወደ ኩባ እየሰረጉ ገብተው የተለያየ አሻጥር እንዲፈጽሙ

Digitized by Google

ለማድረግ ያላቋረጠ ጥረት ከማድረጉም በላይ፥ ከኢኮኖሚ ማዕቀብ ጀምሮ የአብዮቱን መሪዎች ለማስገደል ተደጋጋሚ ሙከራ አድርጓል። ሲ. አይ. ኤ. የተባለው የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ከ1960—1971 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በቅጥረኞቹ አማካይነት ጓድ ፊደል ካስትሮን ለማስገደል ከአሥራ ስድስት በላይ የሚሆኑ የግድያ ሙከራዎች አስደርጓል። ሰውን፥ እንስሳትንና አዝርእትን የሚጐዱ ባክተሪዮሎጅካል ብናኞች በኩባ ላይ በመበተን ከፍተኛ ጥፋት ለማስከተል ሙከራ ከማድረጉም በላይ ቀጥተኛ ወረራ ለማድረግም ይከጅላል።

የኒካራጉዋንም አብዮት ለማስቀልበስ በሺህ የሚቆጠሩ ቅጥረኞችን በአሜሪካ አገር በፍሎሪዳና በካሊፎርንያ የማሰልጠኛ ጣቢያዎቹ ውስጥ በማሰልጠን፥ በጓቲማላና በሆንዱራስ ውስጥ ወደ ኒካራጉዋ በማስረግ የተለያየ አሻጥር እንዲፈጽሙ በማድረግ ላይ ነው። በኤልሳልቫዶርም ውስጥ በአሁኑ ወቀት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በሥልጣን ላይ ላለው ፋሽስታዊ አገዛዝ የሚሰጠውን ወታደራዊ ዕርዳታ በመጨመርና በአማካሪዎች ሽፋን ወታደሮቹን በማስገባት የሚካሔደውን ፀረ ሕዝብ ጭፍጨፋ በመምራት ላይ ይገኛል። ከዚህም አልፎ በቪዬትናም እንዳደረገው በላቲን አሜሪካም ላቲን አሜሪካኖችን እርስ በርስ ለማጨፋጨፍ ሌሎች የላቲን አሜሪካ አገሮች በኤልሳልባዶር የውስጥ ጉዳይ እንዲገቡ በመጋበዝና በመገፋፋት ላይ ይገኛል።

በቅርቡ በአሜሪካ አነሳሽነትና ግፊት ፀረ ኩባና ፀረ ኒካራጉዋ የሆነ የማዕከላዊ አሜሪካ ዲሞክራሲያዊ ኮሚኒቲ የሚባል ትብብር ተፈጥሮአል። አባል አገሮቹም አሜሪካ፥ ኮስታሪካ፥ ሆንዱራስ፥ ኤልሳልቫዶር፥ ቬንዙዋላና ኮሎምቢያ ናቸው።

የአሜሪካ መንግሥት ቃል አቀባይ በቅርቡ በሰጠው መግለጫ «ማዕከላዊ አሜሪካን ለመከላከል ካልቻልን የፋርስ ባሕረ ሰላጤንና በአካባቢው ያለውን ዘይት እንዴት አርገን ልንከላከል እንችላለን?» ማለቱ ይታወሳል። ይህንንም አባባል ተግባራዊ ለማድረግ የአሜሪካ የብሔራዊ ጸጥታ ም/ቤት በካሪቢያን ያለው የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል እንዲጠናከር ትእዛዝ አስተላልፏል። በኅዳር ወር መጀመሪያ ላይ የአሜሪካ የካሪቢያን የወታደራዊ ዕዝ መቋቋሙም በገሀድ ተገልጿል። <u>ዋሽንግተን ፖስት</u> የተባለው የአሜሪካ ጋዜጣ ስለዚህ ወታደራዊ ዕዝ ተግባር ሲጽፍ ተግባሩ «አሜሪካ በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን የዘረጋውን የወታደራዊ መረጃ ስብሰባ ለማቀናጀት፥ በዚያ አካባቢ ያለውን የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል ለማጠናከርና ከኩባም ሆነ በኩባ ከሚረዳው የኒካራጉዋ መንግሥት ጋር ጦርነት ቢከፈት ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ ለማድረግ ነው፤» በማለት አስፍሮ ነበር።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በፓናማ ካናል አካባቢ ቀደም ሲልም የነበረውን የደቡብ ዕዝ ወታደራዊ ኃይልንና በሆንዱራስ፥ በኮሎምቢያ፥ በፓናማና በፖርቶሪኮ ያሉትን የወታደራዊ ጦር ሠፈሮቹን በማጠናከር ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ በማዕከላዊ አሜሪካ ያሉት የሲ.አይ.ኤ. ቀርንጫፎች እንዲሁ በመጠናከር ላይ ናቸው።

በአጠቃላይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በአሁኑ ወቅት በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አካባቢ የሚከተለው ፖሊሲ የዓለም አቀፍ ውጥረትን በከፍተኛ ደረጃ በማባባስ ላይ ነው። ዓለም አቀፍ ኩባንያዎቹ በዚህ አካባቢ የሚያካሔዱትን ብዝበዛ እንዲቀጥሉና አካባቢውም የአሜሪካ 'የጓሮ አትክልት ቦታ' እንደሆነ እንዲቀር፥ በሕዝብ

ደም በመታጠብ ላይ ያሉትን ፋሽስታዊ መንግሥታት ይበልጥ በማጠናከር ከፍተኛ ዕርዳታ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህም በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አካባቢ የሚካሔደውን የነፃነት ትግል ለማዳፈን ባለመቻሉ «የሶቭየትና የኩባ ጣልቃ ገብነት» በሚል ሽፋን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ቀጥተኛ የሆነ ወታደራዊ ወረራ ለማድረግ በመዛት፣ የዓለምን ሰላም በመፈታተን ላይ ይገኛል።

እንደሚታወቀው የቀድሞው የሞንሮ ዶክትሪን ደቡብ አሜሪካ የሰሜን አሜሪካ ተጽዕኖ ክልል መሆኑን ለማረጋገጥና ሌሎች የአውሮፓ ተቀናቃኝ አገሮች አትላንቲክን እንዳይሻገሩ ለመከላከል የታቀደ ነበር። የአሁኑ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አዲሱ ዓይነት ሞንሮይዝም ደግሞ በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አገሮች ውስጥ ከሕዝብ ጭቆናና ብሶት የተነሳ በመቀጣጠል ላይ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በይበልጥ ተፋፍሞ የብዝበዛው ሰንሰለት እንዳይበጠስ በመስጋት፣ ሕዝባዊ ትግሉ ከሶቭየት ኅብረትና ከኩባ ወደነዚህ አገሮች ውስጥ እንዲዛመት የተደረገ በማስመሰል 'ኮሙኒዝም በደቡብ አሜሪካ ውስጥ እንዳይስፋፋ ለመገደብ' በሚል ሽፋን በዚህ አካባቢ ለዕድገት፣ ለሰላምና ለሶሻሊዝም የሚካሔደውን ትግል ለማፈን የተነሳ ነው።

በዚህም መሠረት ኩባን ከተቀሩት የላቲን አሜሪካ አገሮች በመነጠል የማያቋርጥ ውጥረት እንዲፈጠርባት ለማድረግ፣ በኒካራጓ ውስጥ ሰላም እንዳይሰፍን ለማድረግና የሳንዲኒስታን መንግሥት ለመገልበጥ፣ በግሬናዳ ያለውን ተራማጅ መንግሥት ለማናጋት፣ በኤልሳልቫዶር ውስጥ የሚካሔደውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማፈን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ክፉኛ በመራወጥ ላይ ይገኛል።

ይሁንና በማዕከላዊ አሜሪካና በካሪቢያን አካባቢ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚያራምደው የጣልቃገብነት ፖሊሲ ሊወጣው ከማይችልበት ማጥ ውስጥ እየተዘፈቀ ነው። በዚህ አካባቢ ባሉ አገሮች ውስጥ ያሉ ፋሽስታዊ መንግሥታት በሕዝቦቻቸው ጨርሰው የተተፉ በመሆናቸው የፈለጉትን ያህል የወታደራዊም ሆነ ሌላ ዓይነት ዕርዳታ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቢሰጡም ለነፃነት የሚካሔደውን ትግል ለብዙ ጊዜ አፍነው ለማቆየት አይችሉም። ጓድ ፊደል ካስትሮ በመስከረም 1981 በሐቫና በተደረገው የ68ኛው የዓለም አቀፍ ፓርላሜንቶች ማኅበራት ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር በትክክል እንዳስቀመጡት፣ «የጦር መሣሪያ የተራቡትንና የተበዘበዙትን ለመግደል ይችላል። ረሀብን፣ መሐይምነትንና የፍርድ መጓደልን ግን ሊያጠፋ አይችልም»። እነዚህ ሁኔታዎች እስካልጠፉ ድረስ ደግሞ ከነዚህ ሁኔታዎች የሚመነጨውን ሕዝባዊ ትግል፣ ብዝበዛንና በዝባዦችን፣ ጨቋኞችንና አምባ ገነኖችን ለማጥፋት የሚነሳን ሕዝባዊ አመጽ ለመግደል ከቶ አይቻልም።

በመጋቢት ወር 1982 በኒካራጓ ዋና ከተማ በማናጓ በተካሄደው የማዕከላዊ አሜሪካ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትሪቡናል ላይ፣ የትሪቡናሉ ፕሬዚዳንት የማዕከላዊ አሜሪካ ሕዝቦችን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የትግል ታሪክ ሲገመግሙ «የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች በመጀመሪያ በስፔን ጨቋኞች በኋላም በኢምፔሪያሊዝም ለዘመናት ሲበዘበዙና ሲጨቆኑ ቢኖሩም፣ የአልበገርባይነትና የነፃነት ስሜታቸውን ከተውንም አጥ

Digitized by Google

ተው አያውቁም ። አሁንም ቢሆን ከበፊቱ ይበልጥ የሚሉዘርፉቸውን ሁሉ ለመመከት ዝግጁ ናቸው ፤» ብለው ነበር ።

ከማናጉዋ የተካሄደው የማዕከላዊ አሜሪካ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትሪቡናል የማዕከላዊ አሜሪካ ሕዝቦች የተገልና የነፃነት ትግላቸውን ከፍ አድርገው በመያዝ ፤ በዚህ አካባቢ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የጠነሰሰውን የአድኅርት ሤራ እንዲያከሽፉ ጥሪውን አስተላልፎአል ። የኢትዮጵያ አብዮታውያን በግንባር ቀደም የፖለቲካ ድርጅታቸው ለኢሠፓአኮ አማካይነት የማዕከላዊ አሜሪካ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትሪቡናል ላስተላለፈው ጥሪ ሙሉ ድጋፋቸውን የሚሰጡ ከመሆናቸውም በላይ ፣ በማዕከላዊ አሜሪካ በመፋፋም ላይ ላለው ፀረ ኢምፔሪያሊስት የነፃነት ትግል ያላቸውን የትግል አንድነት ይገልጻሉ ።

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና የኢምፔሪያሊዝም ደባ

የካቲት 1966—መጋቢት 1970

ከዶክተር ንጉሤ አየለ

የኢትዮጵያ አብዮት በ1966 መፈንዳቱ
አብዛኛውን የኢምፔሪያሊዝምን ዓለም አደ
ናገጠው ፤ አርበተበተው ፤ ግራ አጋባው ።
በዚህ አላበቃም ። በአፍሪካ ቀንድ የተነ
ሳው አብዮታዊ ሂደት ግንባር ቀደም የኢም
ፔሪያሊስት አገር በሆነችው በዩናይትድ
ስቴትስ ውስጥ በርካታ « የምሁራን » ጽሑ
ፎች እንዲወጡ፣በኮንግሬስ ደረጃ መረጃዎች
እንዲሰባሰቡ፣በዛ ያሉ ሰሚናሮች በጉዳዩ እን
ዲካሄዱ፣በልዩ ትእዛዝ ጥናቶች እንዲደረጉ
ምክንያት ሆኗል።እንዲያውም « ዘ ሆርን
ኦፍ አፍሪካ »[1] የተባለ አንድ መጽሔት
እንዲወለድ ምክንያት የሆነው ይኸው አብ
ዮታዊ ሂደት ነው ። የነዚህ ጽሑፎች የአ
ቋም መግለጫዎችና ጋዜጣዊ ዘገባዎች ሁሉ
ጠቃሚነታቸው የቱ ላይ ነው ቢባል ብቸ
ኛው መልስ በታዳጊው ዓለም ውስጥ አብ
ዮት በተከሰተ ቁጥር የኢምፔሪያሊስቱ
ዓለም ውስጥ የሚታየውን የተወናበደ አቋም
ባሕርይና ጥልቀት ደህና አድርገው ማንፀ
ባረቃቸው ነው ።

ከ1966 በኋላ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ
ስለተሰነዘረው የኢምፔሪያሊዝም ጥቃት
ማተት በመሠረቱ የኢምፔሪያሊስቶች መሪ
የሆነው አሜሪካ ስላደረገው ጥቃት መናገር
ነው ። ሌሎች የኢምፔሪያሊስት አገሮች
ማለትም ብሪታኒያ፣ፈረንሳይ፣የጀርመን ፌዴ
ራል ሪፑብሊክና ኢጣሊያ የኢምፔሪያሊ
ስት ጥቅማቸውን ለመጠበቅና አድኃሪ አላ
ማቸውን እውን ለማድረግ የበኩላቸውን
ሚና ቢጫወቱም በአፍሪካ ቀንድ ሂደት
ውስጥ የቀንደኛ ጣልቃ ገብነት ሚና የተጫ
ወተው አሜሪካ ነው ። የአፍሪካን ቀንድ
በሚመለከት ረገድ ፣ በዚህ አካባቢ በተለ
ይም፣በኢትዮጵያ ከየካቲት 1966 እስከ መጋ
ቢት 1970 የተፈጸሙትን የሁኔታዎች መለ
ዋወጥ ለመግታት አሜሪካ ያደረገው ግፊት
በአምስት ወቅቶች ይከፈላል ፤—

Digitized by Google

1. ከየካቲት 66 እስከ ታኅሣሥ 67፣ መላቅጡ የጠፋበት እርምጃ አልባ ወቅት
2. ከታኅሣሥ 67 እስከ የካቲት 67፣ የግራ መጋባትና የመመሰቃቀል ወቅት
3. ከየካቲት 67 እስከ የካቲት 68፣ የግምገማና የታክቲክ ቅየሳ ወቅት
4. ከየካቲት 68 እስከ ጥቅምት 69፣ የኢምፔሪያሊዝም ጠብ አጫሪነት ወቅት
5. ከጥቅምት 69 እስከ መጋቢት 70፣ የግልፍተኝነት ወቅት

የኢምፔሪያሊስት መላቅጡ የጠፋበትና እርምጃ አልባ ወቅት

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በ1966 በግብተኛነት በጭቆናው አገዛዝ ላይ አምጾ ሲነሳ ይበልጡ ዓለም ሁኔታውን ምን ያስከትል ይሆን በማለት በታላቅ ትኩረትና በጋለ መንፈስ ይጠባበቅ ነበር፣

የኃይለ ሥላሴን ፊውዳል አገዛዝ ለመጣል የተደረገው ዘዴ እጅግ ብልህና ረቂቅ ስለነበር የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም አላማውን ፈጽሞ ሊረዳው አልቻለም ነበር። ስለሆነም ሁኔታውን ባጠቃላይ «ተንኙታቂው መፈንቅል» መጠሪያ ስጥተውት በመገረም ታግሠውት ነበር። እንደሚታወቀው በአፍሪካ አህጉር በርካታ አንዳንዶም ሥር ነቀል ገጽታ የነበራቸው ወታደራዊ የመንግሥት ፍንቀላዎች ተደርገዋል። እነዚህም የአሜሪካንን ወይም የሌሎችን የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጥቅም አልተቃረኑም የሚል አስተሳሰብ ስለነበር ምናልባት የኢትዮጵያም ሁኔታ ከዚህ ያልተለየ ስለመሰላቸው ይሆናል በቆይታ መጠባበቁን የመረጡት። በርግጥ የነበረው ግምት በታዳጊው ዓለም ውስጥ የሚደረጉ ወታደራዊ መፈንቅሎች እንደተለመደው «ሶሻሊስታዊ» «ፀረ ኢምፔሪያሊስታዊ» ወይም «ሕዝባዊ» መግለጫዎችን ከሰጡ በኋላ ምንም እንኳ ወደ አድኃሪነት ያቆለቁላሉ ባይባልም «ለዘብተኞች» ሆነው ይረጋሉ የሚለው ነበር። ስለሆነም በመለዮ ለባሾች መሪነት የተካሄደው የኢትዮጵያም ለውጥ ይህንኑ ቅርጽ እንደሚይዝ ተገምቶ ነበር ማለት ነው። ዳሩ ግን ይህ ግምት የተሳሳተ መሆኑን በ1966 የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት ዕውነተታዎች አረጋግጠዋል።

የኃይለሥላሴ አገዛዝ የነጠፈና የጠቃሚነቱ ጊዜ አልፎአል የሚል አስተሳሰብ ከ1966 በፊት በርከት ላሉ ዓመታት በአሜሪካኖች እየታመነበት መጥቶ ነበር። ለዚህ እምነት ዋናዎቹ ምክንያቶች፦ ባንድ በኩል በቴክኖሎጂ ዕድገት ምክንያት የሳተላይት መገናኛ ዘዴ በመፈጠሩ በአሥመራ የነበረው የመገናኛ ማዕከል ጠቃሚነት በየጊዜው እየመነመነ መምጣቱና በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካ መንግሥት በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የነበረው ልዩ አመለካከት መቀነሱ ነበሩ። በጊዜው በኢትዮጵያ ያሜሪካን አምባሳደር የነበረው ኮሪ በ1956 መግቢያ ላይ የዲፕሎማቲክ ተግባሩን በኢትዮጵያ ሲጀምር የተመከረውን ሲያትት እንዲህ ብሏል፦

አገሪቱ ለፍንዳታ በመቃረቧ ንጉሠ ነገሥቱም ከእንግዲህ ለብዙ ጊዜ ሊኖርወይም ሊያመልጥ ስለማይችል የሚከተለውን ሁኔታ ለመቋቋም መዘጋጀት አለብን የሚባል ምክር ተደጋግሞ ተነግሮኛል። መንግሥታችን ኢትዮጵያን በማስመልከት ባወጣው መመሪያ መሠረት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ያለንን መልካም ወዳጅነት እየጠበቅን ከዚሁ ባሻገር በአዝጋሚ ለውጥም ሆነ በአብዮታዊ ለውጥ እሱን አስወግደው ሥልጣን ሊጨብጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋርም መወዳጀት ያስፈልገናል የሚል ምክር ተሰጥተኝ ነበር። [2]

ከአብዮቱ ፍንዳታ ከአሥር ዓመት በፊት ቀደም አድርጎ «አገሪቱ ለፍንዳታ መቃረ

ቧን «አውቆ» ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር «መል
ካም ወዳጅነት » የመጠበቁን ፖለቲካ ከፍ
ያለ ዋጋ የሰጠው የአሜሪካን መንግሥት
በኃይለ ሥላሴ መውደቅ ያሳየው ተራ ተቃ
ውሞ ከሚጠቁማቸው አንዱ ነገር በአገሪቱ
ውስጥ መካሄድ የጀመረው አብዮታዊ ሂደት
ያደረናገጠው መሆኑን ነው ። ነገር ግን አሜ
ሪካ በጊዜው በቪዬትናም ጦርነት በደረሰ
በት ሽንፈት ምክንያት በመደናገጡ አርፎ
እንዲቀመጥ ተገዶ ነበር ። ሌኒን በትክክል
ያስቀመጠው[3] አብዮታዊ ሁኔታ በ1966
በኢትዮጵያ ተሟልቶ ከመገኘቱም ባሻገር
አብዮቱ የፈነዳው በቪዬትናሙ ሽንፈት
ምክንያት በአሜሪካ ውስጥ ከፍተኛ የሞ
ራል ውድቀት በሰፈነበትና ይህም በኢም
ፔሪያሊስት ዓለም ከፍ ያለ ቀውስ ባስከተ
ለበት ወቅት ነው ።

የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም አብዮታዊ ክስ
ተትን ከመደብ ትግል ወይም ከታሪካዊ
ቁስ አካልነት አንፃር ለማስተዋል ስለማ
ይችልና ስለማይፈቅድ ፥ በአፍሪካ ቀንድ
የተከሰተውን ማኅበራዊ አብዮት ባሕርይ
ጥልቀትና የሚከተለውንም አቅጣጫ በሚ
ገባ መገምገም ተስኖት ነበር ። በዚህ ምክ
ንያት ነበር በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው
ሂደት እምብዛም ሳይጤን በመጀመሪያ በዝ
ምታ የታለፈው ። በተጨማሪም አሜሪካን
አጢኖት ትኩረት ቢሰጠው እንኳ የአብ
ዮቱን ማዕበል ለማብረድ የሚችልበት
ኃይል እምብዛም አልነበረውም ። ከ1960
እስከ 1974 ድረስ በነበሩት አሥራአምስት
ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔ
ታዎችና በአጠቃላይም በሶሻሊዝምና በኢ
ምፔሪያሊዝም መካከል የነበረው የኃይል
ሚዛን ተለዋውጦ ሚዛኑ ወደ ሶሺያሊዝም
አጋድሎ ነበር ።

የግራ መጋባትና የመወናበድ ወቅት
ከታኅሣሥ 1967—የካቲት 1967 ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ታሪክ ከቶ ሊዘ
ነጋው የማይችል ወንጀል በፈጸሙት የኃ
ይለ ሥላሴ መንግሥት ታላላቅ ባለሥልጣ
ኖች ላይ ኅዳር 14 ፥ 1967 አብዮታዊ እር
ምጃ በተወሰደበት ወቅት የኢምፔሪያሊስት
የመጀመሪያ ማጉረምረምና ፀረ ኢትዮጵያ
አቋም ብቅ ማለት ጀመረ ። ሆኖም የተወሰ
ደውን ርምጃ በመቃወም አንዳንድ ተመ
ጻዳቂ መግለጫዎች ከተሰሙ በኋላ ነገሩ
ወደመረሳት ደረጃ ደርሶ ነበር ።

ከዚህ ጥቂት ቆየት ብሎ በታኅሣሥ 11፥
1967 የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ
አገሪቱ ስለምትከተለው የፖለቲካ ፍልስፍና
መግለጫ ሲሰጥ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ መ
መሪያ «የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም» ወይም ኅብ
ረተሰባዊነት ይሆናል ብሎነበር።ይህ እንደተ
ሰማ የኢምፔሪያሊስት አቋም የእፎይታና
የግራ መጋባት ቅይጥ ነበር ። የእፎይታው
ምክንያት «የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም»ወይም
ኅብረተሰባዊነት የሚለው ቃል «ኡጃአማ»፥
«የአፍሪካ ሶሻሊዝም» ወይም ከንዑስ ከበር
ቴዎች ሶሻሊዝም ያልተለየ መስሎ ስለቀረበ
ነው።በአዋጁ ላይ ስለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም፥
ስለመደብ ትግል፥ስለ ፀረኢምፔሪያሊዝም
ትግል አልተነሳም ወይም ከማርክሲዝም ሌ
ኒኒዝም ምንጮች ወይም ጽሑፎች ጥቅሶች
አልተወሰዱም ነበር ። አዋጁ ይህን ሳያደርግ
በቀጥታ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝምን ምንነት
ሲያስቀምጥ « ለዕኩልነት ፤ በራስ ለመተ
ማመን ፤ ለሥራ ክቡርነት ፤ ለጋራ ጥቅም
የበላይነትና   ለኢትዮጵያ   አንድነት »[4]
የቆመ መሆኑን በመግለጥ ተወስኖአል ።

ዳሩ ግን ምንም እንኳ የፍልስፍናው መመ
ሪያ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያንፀ
ባርቅና በአማርኛ መጠሪያ ቢቀርብም ራሱ
« ሶሻሊዝም » የሚለው ቃል መጠቆሙ

Digitized by Google

በአፍሪካ ቀንድ ላይ ለወደፊቱ የሚነሳውን አወዛጋቢ ሁኔታ ይጠቀማል በማለት የካፒታሊስቱ ዓለም ሰግቶ ነበር ። ንጉሡ ከወደቀ በኋላ በሳምንቶች ብቻ በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ የለውጥ ሁኔታዎች ተኸርጉድጉደው ስለመጡ ኢምፔሪያሊዝም ሊገመግማቸውና ሊገታቸው አልቻለም ። በዚያን ወቅት ሶማሊያ ሶሻሊስት ነኝ እያለች በማጭበርበር ላይ ስለነበረች ፣ የሱዳንም ሁኔታ ገና ያልተረጋጋ ስለነበር ፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሂደት ለኢምፔሪያሊዝም ስጋት ከፍ ማለት ምክንያት ሆነ ። ይህ በዚህ እንዳለ ደርግ በማከታተል በ1967 ታላላቅ የግል የማምረቻና ማከፋፈያ ተቋሞችን የመንግሥት ንብረት የሚያደርጉ አዋጆችን ስላወጣ ኢምፔሪያሊዝም በይበልጥ ገራ ተጋባ ፤ ተደናገጠ ።

ታኅሣሥ 23 ፣ 1967 ባንኮች የኢንሹራንስ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ተወረሱ። ጥር 26፣1967 በግል የተያዙ የማምረቻ፣የማከፋፈያና የገንዘብ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ዋሉ። ድርጅቶቹም በአብዛኛው እንዲያውም ሙሉ በሙሉ የምዕራብ አገሮችን «ጥቅም» የሚያስከብሩ ነበሩ ። ከዚያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በየካቲት ወር 1967 የሶሻሊስት ኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ፖሊሲ መመሪያ አወጣ ። በዚህም መምሪያ መሠረት የአገሪቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ተቋሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋሉ መሆናቸውንና «የውጭና የውስጥ የግል ካፒታልን በሥራ ላይ ማዋል እንደሚቻልና ይህም ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም እንደሆነ »[5] ተብራራ ። በተጨማሪም የትኞቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች ፣ ሀ/ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እንደሚያዙ ለ/ የመንግሥትና የውጭ ወይም የመንግሥትና የግል ካፒታል በአንድነት የሚውልባቸው ፣ ሐ/ መንግሥት በበላይነት የሚቆጣጠራቸው የግል ንግድ እንቅስቃሴዎች በመመሪያው በሚገባ ተዘርዝረዋል ። ሆኖም ይህ ሁኔታ በኢምፔሪያሊስቱ ካምፕ ውስጥ መደናገጥን ሲፈጥር ፣ የአብዮቱን ሂደት እና ደናቅፋለን የሚል አጉል ተስፋም አሳደረባቸው ።

የግምገማ ፣ የአድኀሪ ቅስቀሳና የታክቲክ ቅየሳ ወቅት /ከየካቲት 1967—የካቲት 1968/

በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ በአስቸኳይ ማግኘት የምትፈልገውን የጦር መሣሪያ የአሜሪካ መንግሥት ለመስጠት ወይም ለመሸጥ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱ ይህን ያህል የሚያስደንቅ አልነበረም ። የተጠየቀው የጦር መሣሪያ ዋጋ በአሜሪካ ዶላር የሚከፈል ሲሆን እንደ ዋሽንግተን ፖስት ሚያዝያ 1965 ጋዜጣ ቃል አቀባይ ዴቪድ አቶዌይ አባባል ፡- የተጠየቀው የጦር መሣሪያ «ካለምንም ውሳኔ ከአንድ ዓመት በላይ ጥናት ሲደረግበት ቆይቷል ። » ጋብ ብሎ የነበረውም የተገንጣዮች ደባ በማንሰራራት የአስመራን ከተማ ሥጋት ላይ ጣላት ።[6] ኢትዮጵያ እየደማች ሳለ የአሜሪካ መንግሥት ጥያቄውን ዛሬ ነገ እያለ አንተተው ።

ቃኘው «የመገናኛ ጦር ሠፈር »እየተባለ የሚጠራው በአሥመራ እ.አ.አ በ1953 ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የአሜሪካ መንግሥት የጦር አውሮፕላኖች ፣ ከባድና ቀላል የጦር መሣሪያዎች ሲሰጥና የኢትዮጵያን ወታደሮች በፀረ ደፈጣ ስልት ሲያሰለጥን እንዲያውም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የሌጅስቲክ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል። እናም ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ ስለነበራት አቋም ጨርሶ አንስቶትና በይፋም ጠይቆ አያውቅም ። ሆኖም ኢትዮጵያን ከዳር እስከዳር አብዮታዊ ማዕበል ባጥለቀለቃት ጊዜ፣ አሜሪካ በሰሜን ኢትዮጵያ ስለአለው ሁኔታ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀመረ ።

Digitized by Google

የአሜሪካ መንግሥት ለጉዳዩ ሕጋዊና
ተገቢ የሆነ አዲስ አቋም ይሰጥ ይመስል
እ. አ. አቆጣጠር መጋቢት 5 ፥ 1979 የአ
ሜሪካ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ለኢት
ዮጵያ እንዲሸጥ ስለተጠየቀው የጦር መሣ
ሪያና የአሜሪካንም ፖሊሲ ምን መሆን
እንዳለበት የሚወያይ የአንድ ቀን ስብሰባ
አካሄዱ ። በዚያን ወቅት የምክር ቤቱ የዓ
ለም አቀፍ ፖለቲካና ወታደራዊ ጉዳዮች
ንዑስ ኮሚቴ ሊቀ መንበር እንደነበረው
እንደ ፋሴኤል አባባል ፥ ውይይቱ የተደረ
ገው በሚከተለው ምክንያት ነበር ።

ባለፉት 30 ዓመታት በአጠቃላይ አፍሪ
ካን ፤ በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያን በሚ
መለከት ረገድ የአሜሪካ ምክር ቤት ብዙም
ትኩረት አላደረገም ። እነዚህ ዓመታት በምስ
ራቅ አፍሪካና በኢትዮጵያ ፤ በአሜሪካ ሕዝብ
አመለካከት እንዲሁም በሀያላን መንግሥ
ታት ግንኙነቶች ውስጥ ከፍተኛ ለውጦች
የታዩባቸው አመታት ናቸው ። በዚህ ውይ
ይት ላይ መልስ ይሰጥባቸዋል ብለን ከምና
ስባቸው ጥያቄዎች መካከል እነዚህ ለው
ጦች ከኢትዮጵያ ጋር ያለንን ግንኙነት
ወሳኝ ምዕራፍ ላይ አድርሰውት እንደሆነእን
ዲሁም ፖሊሲያችን ምን ዓይነት አቀጣጫ
ዎች ፥ /ካሉ/ መከተል አለበት የሚሉት ይገ
ኙበታል ። ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙ
ነት ለመመርመርና ለኢትዮጵያ ወታደራዊ
ዕርዳታ በምን ደረጃና በምን ሁኔታ መስጠ
ቱን እንደምንቀጥል ተወያይተን ውሳኔ ላይ
ለመድረስ እንዲያስችለን አስፈላጊውን
መረጃ ለምክር ቤቱ ለማቀረብ ይህን ውይ
ይት አዘጋጅተናል ።[7]

ውይይቱ ምንም እንኳ የኢምፔሪያሊስት
የዜና ማሰራጫዎች በኤርትራ ያለውን
ችግር አስመልክተው ፀረ ኢትዮጵያ ዘመ
ቻቸውን በሰፊው ማካሄድ ከጀመሩ በኋላ
የተደረገ ቢሆንም ከንዴትና ከጥላቻ በቀር
የሚያመለክተው አንዳችም የተለየ ነገር
አልነበረውም ። ያም ሆኑ ይህ ኢትዮጵያ
ለመግዛት የጠየቀችውን የጦር መሣሪያ በሚ
መለከት ረገድ የአሜሪካ መንግሥት « የሞ
ራልና የፖለቲካ » ውዥንብር ውስጥ ገብቶ
ነበርና የአሜሪካ ባለስልጣናት አቅማሙ
በት ። በዚያን ወቅት በአሜሪካ የውጭ
ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ተጠባ
ባቂ ሚኒስትር የነበረው መልኬሂ ፦

የጦር መሣሪያውን ሽያጭ የምንፈቅድ
ከሆነ አሁን ባለው የኢትዮጵያ የውስጥ
ጉዳይ ጣልቃ መግባት ነው ተብሉ በአን
ዳንድ ክፍሎች ይገመት ይሆናል ። ጥያቄ
ውን ብንቃወም የጥንት ወዳጃችን በችግር
ላይ በሆነችበት ወቀተ ለመርዳት የተሳነን
መስሉ ይታይ ይሆን? በማለት ተናገሯል ።

ከ1966ጀምሮ በመላው ኢትዮጵያ ከሚካ
ሄዱት አብዮታዊ ለውጦች በስተቀር የኤር
ትራን « ውስጣዊ ጉዳይ » በተለይ የሚመ
ለከት ምንም አዲስ ነገር አልነበረም ። የአሜ
ሪካ መንግሥት ካለምንም አደጋ ወይም
ሥጋት ለጦርና ለስለላ የሚያገለግል ከፍ
ተኛ የሬድዮ መገናኛ አጸቁም ይጠቀም በነ
በረበት በኤርትራ ውስጥ የነበረው ግጭት
ከአሥር ዓመታት በላይ ሲካሄድ ቆይቷል ።
ይኸው መንግሥት በኢትዮጵያ የውስጥ
ጉዳይ ፥ የኤርትራንም ውዝግብ ጨምሮ
ከሀያ ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ጣልቃ ሲገባ
ቆይቷል ። ታዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ ጣልቃ
መግባት የሚለው ይህ አዲስ ሀፍረተ ቢስና
አዛኝ መሳይ አመለካከት ከየት መነጨ ?
የዚህ መልሱ የኢትዮጵያ አብዮት ፈጣን
ዕድገት ነው ። አባባሉ የሚያመለክተው
ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማዘንን ሳይሆን ፥ ለኢም
ፔሪያሊስቱ አለም በጣም አደገኛ የሆነውን
የተጋጋለውን አብዮታዊ ሂደት መፍራትን
ነው ። ስለዚህም የተሞከረው በወቅቱ የአ
ሜሪካ ባለሥልጣናት በሚገባ በሚያውቁት
ኢትዮጵያ በነበራት ድክመት ማለትም ወታ
ደራዊ ሁኔታ ላይ ተጽእና በማሳደር የአብ
ዮቱን አቅጣጫ ለመቀየር ነበር ። እቅዱ የጊ

Digitized by Google

ዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የጦር መሣሪያና መለዋወጫ በአጣፋኝ ስለሚፈልግ « ብቸኛ » የጦር መሣሪያ አቅራቢዎቹን ለማርካት ሲል አብዮታዊውን ግስጋሴ ይገታል የሚል ነበር ።

በኢምፔሪያሊስቶች ለረጅም ጊዜ ተዳፍና ከቆየና ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጉትጉታ ከተደረገ በኋላ ፣ አሜሪካ ኢትዮጵያ ለመግዛት ከጠየቀችው የ31 ሚሊዮን ዶላር የጦር መሣሪያ ግዥ ውስጥ ሲሶው ተፈቀደ ። ያን ወቅት በአስመራ ውስጥና አካባቢ ጉዳት ቢደርስም ግጭቱ ጋብ ያለበት ጊዜ ነበር ። ለማናኛውም የአሜሪካ መንግሥትም እ.አ.አ. በ1953 ስምምነት ለኢትዮጵያ የገባውን ውል አፈረሰ፤ በአብዮቱም ላይ ጉዳትለማ ድረስ ተፍጨረጨረ ።

ስለዚህ ፤ የኢምፔሪያሊስቱ ካምፕ በአጠቃላይና በተለይም የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው አብዮታዊ ለውጥ ጥቅሙ በመነካቱ በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ በረቀቀ ዘዴ ጣልቃ መግባት ጀመረ።

ኢትዮጵያ በአድኀሪ የዓረብ መንግሥታት የሚረዳና የሚገፋፋ አደገኛ ከበባ በተደረገባት በዚህ ወቅት የአሜሪካና የግብረ አበሮቹ ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር መሣሪያ መከልከል በእርግጥ የኢትዮጵያን አብዮት ለማፈን መሆኑ ግልጽ ነው ። ወደ ኋላ እንደምንረዳው የሶማሌን አድኀሪ መሪዎች የልብ ልብ ሰጥቶ ወደ ጦር ጀብደኝነት የገፋፋቸው አንዱ ዓይነትተኛ ምክንያትም ይኸው ነበር ።

1967 እና 1968 በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተጋድሎ የተካሄደባቸው ዓመታት ነበሩ ። በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በታዳጊዎቹ ተራማጅ ኃይሎችና ሥር የሰደዱት የፊውዳሊዝምና የከፊል ከበርቴ አድኀሪ ኃይሎች መካከል በአዲስ አበባ ጉዳናዎችና በሌሎች ከተሞች እንዲሁም በገጠሩ የሞት ሽረት ትግል ተካሂዶአል ። የገጠሩን መሬት የሕዝብ ካደረገው የካቲት 1967 አዋጅና በተለይም የከተማን ቦታና ትርፍ ቤቶችን የሕዝብ ካደረገው ከሐምሌ 1967 አዋጅ በኋላ የፊውዳሉ መንግሥት አድኀሪ ርዝራዦች ይፋ ጦርነት ከፈቱ ። የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በሚያዝያ ወር 1968 መታወጁ ለኢትዮጵያ አብዮት ሶሻሊስታዊ ፈለግ መሠረት ጣለ ። በግንቦት ወር 1968 የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሲቋቋምም የአብዮቱ ርዕዮተ ዓለማዊ አቅጣጫ ይበልጥ እየተጠናከረ መጣ። እነዚህ ሁሉ የአብዮቱን ርምጃ አፋጠኑ ፤ የመደብ ትግሉንም አፋፋሙ ። የ1968 ማብቂያና የ1969 መጀመሪያ በውስጥ የመደብ ትግል አኳያ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ከባዱ መስዋዕትነት የተከፈለባቸው ወቅቶች ነበሩ ። በአብዮትና በፀረ አብዮት መካከል የተካሄደው ትግል በደርግ ውስጥም ተካሂዶአል ። ለዚህም አንዱ ጉልህ ምልክት የደርጉ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የነበረው ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴና ሌሎችም በፀረ አብዮት ድርጊታቸው በሐምሌ ወር 1968 መደምሰሳቸው ነበር ።

ከነሐሴ 4 እስከ ነሐሴ 6 ፥ 1968 በአሜሪካ ምክር ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ ኢትዮጵያንና የአፍሪካን ቀንድ በሚመለከት ስብሰባ አካሄደ ። በዚህም ጉባኤ ላይ « ለዘመናት ሰፍኖ የቆየው የኢትዮጵያ ዘውዳዊ አገዛዝ በአብዮቱ ማዕበል ተጠራርጐ ተወስዶአል ፤ ከዚህም ጋር ኢትዮጵያ በውጭ ፖሊሲያችን ስለምትጫወተው ሚና የነበረውን የረጅም ጊዜ ግምትና ለብሔራዊ ጥቅማችን የነበራት ተፈላጊነት አብሮ ከተሟል ። » በማለት የንዑስ ኮሚቴው ሊቀመንበር ሴኔተር ዲክ ክላርክ ተናገረ ። በይበልጥም « የሶሻሊስት አብዮታዊ ዓላማውን ስለገለጸው የኢትዮጵያ መንግሥት ባሕርይ ፣ ይዘት ፣ ብቃትና ፈለግ» ጉባኤው ጠንቅቆ መመርመር እንዳለበት ይኸው የምክርቤት አባል አስገነዘበ።[8] በነሱ አስተያየት በኢትዮጵያ እየተካሄደ የነበረው ሁኔታ መለካት የነበረበት አብዮት እንዲ

Digitized by Google

ፈንዳ ባደረገው በኢትዮጵያ ሁኔታ ወይም በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ፣ ጥቅምና ችግር አንፃር ሳይሆን በኢምፔሪያሊስት የግል ጥቅም አንፃር ነበር ። የአሜሪካ መንግስት 330 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለኢኮኖሚያዊ «ርዳታ» 278.6 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለወታደራዊ « ርዳታ » በመስጠት « ኢትዮጵያን ላለፉት 25 ዓመታት « በኢኮኖሚያዊና በወታደራዊ መስክ መደገፉን » ከገለጸ በኋላ ሴኔተር ክላርክ እንደሚከተለው ተናገረ ።

የምንሰጠውን ድጋፍ መቀጠሉ ጠቃሚ መሆን አለመሆኑን ማመዛዘን ይገባናል ። በምሥራቅ አፍሪካ የኢትዮጵያን ስትራቴጂያዊና ፖለቲካዊ ሚናና በቀይ ባሕር ፤ በዓረብ ፔኒሱላና በሕንድ ውቅያኖስ ጥቅማችንን ለማስከበር ምሥራቅ አፍሪካ የሚያበረክተውን ከፍተኛ አገልግሎት እንደገና መመርመር ይኖርብናል ።[9]

ከዚህ አባባል ከምንረዳው አንዱ ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አብዮታዊ ዕድገት የመገምገሙ ሐሳብ በአፍሪካ ቀንድ ካሉት ሕዝቦች ፍላጐት አንፃር መሆኑ ቀርቶ ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ዓለም አቀፍ ጥቅም አንፃር መሆኑ ነው ። ሕዝባዊው አብዮት በኢትዮጵያ ውስጥ በግብታዊነት የፈነዳው ነባራዊና ጉልህ በሆኑ ምክንያቶች ነበር ። የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማ ምንጊዜም ቢሆን በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ሳይሆን ጭቁኑ ሕዝብ የተደላደለ ኑሮ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው ። ይሁንና የኢምፔሪያሊስቱ የአስተሳሰብ ዘይቤ እንዲህ ዓይነቶቹን አብዮታዊ ክስተቶች ካላቸው አላማና የራሳቸውን ፍላጐት ከማርካታቸው አንፃር መመልከትና መገምገም አለመደም ፤ ለመልመድም ጠባዩ አይፈቅድለትም ።

በስብሰባው ላይ በጥንቃቄ የተመረጡ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ « ኤክስፐርቶች» ቡድን ተገኝቶ ነበር ። በዚህ «የኤክስፐርቶች » ምርጥ ቡድን ውስጥ ዋክስ ኤንድ ጉልድ በሚለው መጽሐፍ ዝናን ያተረፈው ዶናልድ ሌቪን ፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበረው ኤድዋርድ ፣ በአንድ ወቅት የአሜሪካ መንግሥት በነበረው የረጅም ጊዜ ዕቅድ መሠረት ለኢትዮጵያ መንግሥት « ዋና አማካሪ » የነበረው ሚስተር ጆን ኤች እስፔንሰር ፣ የፖሊስ ኃይል ባልደረባ ሚስተር ቶም ጂ ፋረርና በመጨረሻም ዊሊያም ሻውፈልና በዛ ያሉ ፣ በአማካሪነትና በወሬ አቀባይነት የሚሰሩ ፣ የኮበለሉ ኢትዮጵያውያን ፀረ አብዮተኞች ተገኝተዋል ።

ስብሰባው ፕሮፌሰር ሌቪን በደርግ ላይ ባደረገው ከፍተኛ የተቃውሞ ንግግር ተከፈተ ።

ደርግ - በርካታ የሆኑ በሥልጣን የባለፕ ባለሥልጣኖችን ከሥልጣን አስወግዶአል ፤ በአንዳንድ የደቡብ ክፍላተ ሀገር መሬት ለሌላቸው ብዙ አርሶ አደሮች መሬት አከፋፍሏል ። ቀድሞ እንደሁለተኛ ዜጋ ይታዩ ለነበሩት ለንዳንድ ሕዳጣን ብሔረሰቦች ከፍተኛ መብት ሰጥቷል ።[10]

ሲል ሌቪን ካመነ በኋላ ፣ በሌላ በኩል የደርግ ተግባር « ከፍተኛ ጥፋት » አስከትሏል በማለት ደርግን ሲወነጅል ፣ « በአገሪቱ ውስጥ ባሉ በታላላቅ ጐሣዎች መካከል ያለው ቅራኔ እንዲካረር አድርጓል » ፤ ለመንግሥት « ድጋፍ ሊሰጥ የሚችለውን ማንኛውንም ክፍል አስቀይሟል » ፤ «የማዕከላዊውን መንግሥት ሥልጣን አዳክሟል » ፤ « የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል አመንምኗል » ፤ « ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ውስጥ ያላትን ደረጃ አናግቷል » በማለት ተናግሯል ።

በእርግጥ ፣ ሌቪን በዋሽንግተን ባለሥልጣኖች ፊት ያስተጋባ የነበረው በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥና ውጪ ፀረ አብዮት አማካኝነት በወታደራዊ መንግሥት ላይ

Digitized by Google

ይሰራጭ የነበረውን ነቀፋ ነበር ። ፕሮፌሰር ሌቢን በጽሑፍ ውስጥ አሜሪካ «1ኛ/ ጅቡቲ የራሷን ዕድል በራሷ እንድትወስን ለማድረግ ፥ 2ኛ/ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዲኖራት ዋስትና አግኝታ ለኤርትራ ነፃነቷን እንድትሰጥ ፥ 3ኛ/ ለአፍሪካ ቀንድ አካባቢያዊ ዕድገት ዓለም አቀፋዊ ድርጅት እንዲቋቋም ለማድረግ ያላትን ዓላማ በመሸፈን ለደርግ አነስተኛ የሆነ ወታደራዊ ዕርዳታ በመስጠት » በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ገብነቷን መቀጠል እንዳለባት አሳሰበ ።

የሚቀጥለው ምስክር ጆን ኤች ስፔንሰር በውይይቱ ወቅት ከፋኛ የተናደደና ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል ነበር ። ስፔንሰር ቀባጣሪና ራሱን በራሱ የሚቃረን ነበር ። በጽሑፉ ውስጥ ባለፉት 40 ዓመታት የነበረውን የአሜሪካንና የኢትዮጵያን ግንኙነት ዝርዝር አቀረበ ። ከዚያም ፥ በዚህ ወቅት የአሜሪካንና የኢትዮጵያን ግንኙነት ያሻከሩና ያጠናከሩ ሁኔታዎች ምን እንደነበሩ መዘርዘር ጀመረ ። ሆኖም ሚስተር ስፔንሰር የሰጠው ቃል ያተኮረው የኢትዮጵያን አብዮት ለመደምሰስና የአሜሪካ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ላይ የነበረውን የበላይነትና ተጽእኖ እንደገና ለመመለስ የሚያስችሉትን ምክንያቶችና ዕቅዶች ሁሉ በመጠቃቀስ ባደረገው ንግግር ነበር ።

በተጨማሪም ፥ ስለ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ሞት በስብሰባው ላይ ተነስቶ ስፔንሰር ከመጠን በላይ በሀዘን ተዋጠ ። ስፔንሰር « የምዕራቡ ዓለም ደጋፊ በመሆኑና የትኛውን ፈለግ እንከተል ? ለሚለው ጥያቄ ወደ መስኮብ የሚያመራውን ፈለግ በመቃወሙ የተነሳ የደርግ የፖለቲካ ክፍል ኃላፊ የነበረው የሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ መገደል » [11] መወገዝ አለበት አለ ። ወደፊት አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ስለሚኖራት ግንኙነት ሲናገር ስፔንሰር ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ሁኔታው ግራ ያጋባው ይመስል ነበር ። ከተሰነዘሩት ሀሳቦች በተጨማሪም የኢትዮጵያን አብዮት ለመውጋት ካርቱም የፀረ አብዮት እርምጃዎች ማደራጃ ፥ ማቀናጃና የማጥቂያ ሰፈር ሆና እንድታገለግል ሀሳብ አቅርቦ ነበር ። ስፔንሰር በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ያለው የከረረ ጥላቻና የበቀል ስሜት ከፍተኛ ገጽታውን ያሳየው ኢትዮጵያውያን ቀስ በቀስ በርሀብ ለበቅ ተመተው እስኪንበረከኩና አሜሪካ ያላትን ስልጣንና ኃይል የቱን ያህል እንደሆነ እስኪገነዘቡ ድረስ ለኢትዮጵያውያን የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ «ዕርዳታ » እንዲቋረጥ በማለት በጋለ የበቀል ስሜት ሀሳብ ባቀረበበት ወቅት ነበር ።

በሴናተር ክላርክና ስፔንሰር መካከል የአሜሪካን ጥቅሞች ለማስጠበቅ ዓይነተኛ መግለጫ ስለሆነው ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ « ዕርዳታ » እንደሚከተለው የሀሳብ ልውውጥ ተደርጎ ነበር ፤ « ደርግ በችግር እስኪወድቅ ድረስ ‘ ኢኮኖሚያዊ ’ ዕርዳታ በማቋረጥ ለታክቲካዊ ሁኔታ ወታደራዊው ዕርዳታ እንዲቀጥል ማድረግ ከዚያም አመራሩ እኛን የሚደግፍ ሆኖ ታገኘዋለህ ፤ ይህ ከሆነ ርዳታውን ለመቀጠል የሚያግደን ነገር አይኖርም » በማለት በክላርክ ሊቀመንበርነት ለሚካሄደው ስብሰባ ስፔንሰር አስተያየቱን በመስጠት ውይይቱ እንደሚከተለው ተጀመረ ፤

ሴናተር ክላርክ ፤ የኢኮኖሚውን ዕርዳታ ቶሎ ካቋረጥን ነዋ !

ሚስተር ስፔንሰር ፥ ይህ ከእቅዴ ጋር የሚስማማ ነው ።

ሴናተር ክላርክ ፤ እርግጥ ነው ወዲያውኑ ለረሀብ ታጋልጣቸዋለህ።

ሚስተር ስፔንሰር ፥ በዕውነት ትክክል ነው።

ሴናተር ክላርክ ፥ ይሆን አባባል ለመግለጽ (ለማብራራት) አልፈልግም ። ሆኖም ግን በደ

ርግ ውስጥ ለውጥ ይመጣል በሚል ተስፋ በኢትዮጵያ ውስጥ ረሀብ ለመፍጠር ሆን ተብሎ በሚጠነሰሰው ፖሊሲ ውስጥ ለመሳተፍ እንፈልግ እንደ ሆን እርግጠኛ አይደለሁም ።

ሚስተር ስፔንሰር ፥ በምግብ ወይንም ይህንን በመሳሰሉ ነገሮች አሜሪካ የምትፈጥረውን ረሀብ ማለቴ አይደለም

ሴናተር ክላርክ ፥ የምግብ ዕርዳታውን አታቋርጥም ማለት ነው ?

ሚስተር ስፔንሰር ፥ በኔ ምትክ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ቦታ ላይ ብትሆን ኖሮ ስለ ረሀብ ሳወሳ፥ ስለተፈጠረው ቀውስ ማለትም ገበሬዎች እናመርትም ስለማለታቸው መሆኑን ትገነዘብ ነበር ።

ለዚህም ሁኔታ ምክንያት የሆነው የተወያየንበት ያው የውርስ እርምጃ ነው። እዚህ ላይ ... ሕዝቡ ዳግመኛ እንደ ዝንብ ሊረግፍ የመቻሉን አስቃቂ ሁኔታ ላስወግደው አልችልም ። [12]

ሕዝብን በረሀብ « እንደ ዝንብ በማርገፍ» ለሰብአዊ መብቶች (Human Rights) መታገል « ተሰጥኦ» ያለው ኢምፔሪያሊዝም ብቻ ነው ።

የቀድሞው አምባሳደር ኮሪ የምስክርነት ቃል « ከማስታወሻ ማኅደሩ የወጣ የዕምነት ቃል » [13] ነበር።ወደ ኋላ መለስ ብሎ ሲያስተውለው አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ባላት ፖሊስ አያሌ ነገሮች አሳሳቢና አሳፋሪ ሆነው ያገኛቸው ይመስላል። ከ1960 ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ለአራት ዓመት ተኩል ያህል በኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፈው ዲፕሎማሲያዊ ቆይታውና በተለይም ደግሞ ቀልጣፋና መሠሪይ ተልእኮው መልካም ዝናን አትርፎለት ነበር ። አምባሳደር ኮሪ ስልጣኑን በተረከበኩበት ጊዜ የአሜሪካ « ፖሊሲ ቃኘውን በቁጥጥር ሥር ማድረግ ሲሆን እኛ ሆን ብለን በወታደራዊና በኢኮኖሚያዊ ዕርዳታ ውስጥ እጃችንን አስገብተናል » [14] በማለት ገለጸ ። አሜሪካ የቃኘውን የጦር ሠፈር ለስትራቴጂያዊ ዓላማ ለማዋል ባለው ፍላጎት ላይ በመመስረት ነበር ለብዙ ጊዜ በትረ መንግሥቱን እንደጨበጠ ይቆያል ተብሎ ከተገመተው የቀድሞው ንጉሥ ጋር ፖለቲካዊ ወዳጅነት የመሠረተው በማለት ጠቆመ ። በተጨማሪም የቀድሞው ንጉሥ ባለሟሎቹ ፕሬዚዳንት ኬኔዲን ለመጎብኘት 300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚገመቱ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ሲገዙ (በርግጥ ይህ ዝርዝር በዋሽንግተን 30 ሚሊዮን ብቻ ነው ተብሎ ቢገለጽም) ያሰቡት ሳይሳካላቸው ቀርቶ 600,000 የአሜሪካን ዶላር የሚገመት ዕቃ ብቻ ማግኘት የቻሉበትን በ1963 መጨረሻ ላይ የተከሰተውን ሁናቴ በማብራራት በስውር የሚካሄደውን የኢምፔሪያሊዝምን ዲፕሎማሲ ትክክለኛ ገጽታ አጋለጠ ። ይሁንና ሚስተር ኮሪ ኋሁን ስላለውና ስለወደፊቱም ሁኔታ በይፋ የሚናገረው ብዙም አልነበረም ።

ከኮሪ ቀጥሎ የቀረበው ምስክር ሚስተር ቶም ፌረር በ1968 ታትሞ የወጣው (War Clouds on the Horn of Africa) (በአፍሪካ ቀንድ ላይ የሚያንዣብብ የጦርነት ደመና) የተሰኘው መጽሐፉን በሚያዘጋጅበት ወቅት ስለነበር፥ ለዚሁ ተግባር ራሱን አለማምዶ ነበር ። ሚስተር ፌረር ከሁሉም በላይ ያተኮረው በጂኦፖሊቲክስ፥ በአሜሪካን ስትራቴጂያዊ ጥቅሞችና ዴታንት ላይ ነው ። አብዮትም ሆነ ግጭት ወይም በአፍሪካ ቀንድ ላይ የተፈጠሩትን ማናቸውም ክስተቶች ሁሉ የሚመለከታቸው በዴታንት ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት

Digitized by Google

ተጽዕኖ ፣ በአሜሪካና በሶቭዬት ኅብረት መሀከል ባለው ስትራቴጂያዊ የኃይል ሚዛን ላይ ሊያስከትሉ ከሚችሉት ሁኔታ ወይንም አረቦችንና እሥራኤልን እንዲሁም የቀይ ባሕርንና የኤደን ባሕረ ሰላጤን የባሕር በሮች አዳምር በሚይዘው በጂኦፖለቲካዊ ይዞቱ አንፃር ነው ። ለዴታንት አስጊ ሁናቴን ይፈጥራሉ በማለት ኤርትራን ፣ ኦጋዴንንና በመጠኑም ቢሆን ጅቡቲን በመጠቀስ እነዚህ በአፍሪካ ቀንድ ችግር የሚፈጠርባቸው ናቸው በማለት ጠቁሟል ። በጻፈው መጽሐፍም ሆነ ለምክር ቤቱ በሰጠው የምስክርነት ቃል እንደገለጸው ምዕራቡ ዓለም የኤርትራን ነፃነት መደገፍ አለበት ። ምክንያቱንም ሲያስረዳ « የአረብን ፈለግ የምትከተለው ነፃ ኤርትራ ኖረችም አልኖረችም የእሥራኤልን ጥቅም ለሚጠብቀው ለምዕራቡ ዓለም ስትራቴጂያዊ ጥቅም ለውጥ ያስከትላል ብዬ አልገምትም » [15] በማለት ገልጧል ።

በአፍሪካ ቀንድ ላይ ለተከሰተው ችግር « መፍትሄ » ነው ብሎ ያቀረበው ሚስተር ፋረር በተጨማሪም ኢትዮጵያ ፣ ብሔራዊ ሕልውና እንዲከበር ስለምትፈልግ በኦጋዴን ያለው ችግር መፍትሄ የሚያገኘው « በሶቭዬት ኅብረትና በአሜሪካ የጋራ ግፊት ነው » በማለት ገለጸ ። ሚስተር ፋረር ጅቡቲ በኢትዮጵያና በሱማሌ በጋራ እንድትተዳደር ሀሳብ አቀረበ ። በተጨማሪም ሶቭየት ኅብረት በአፍሪካ ቀንድ የባሕር በሮችን ዘግታለች የሚባለውን የፈጠራ ወሬ ቢጥሞና ከመረመረ በኋላ ይህ « በምዕራባውያን ጭዋሂዎችና በደደቡ የአፍሪካ ደጋፊዎች የሚነገር . . . » ምክንያተቢስ ወሬ ነው በማለት ተናገረ ። በሱማሌ ጉዳይ ኤክስፐርት ነው የሚባለው ሚስተር ፋረር ሱማሌያውያን ለሶቭዬት ኅብረት የሚሟገቱ አይደሉም፤እንዲያውም « ፕሬዚዳንትቲው /የቬየትናሙ/ ያደርግ እንደነበረው ለኛ ሽንጣቸውን ገትረው የቆሙ ናቸው፣ ሌላውን ማግባባትና ለጥቅማቸው ለማዋል የሚችሉ እንጂ ማንም እንደፈለገው ሊያደርጋቸው የሚችል አይደሉም ። ሶቭዬት ኅብረት ተጽእኖ ለማድረግ ከወሰነች ሱማሌዎች በሱማሌያ ግዛት ውስጥ ሶቭዬቶች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለመገታትና ሶቭዬቶችን ከሀገር የማባረር እርምጃ ለመውሰድ ይገደዳሉ» [16] በማለት አስተያየቱን ሰጠ ።

የመጨረሻው ምስክር ሚስተር ዊሊያም ሾውፌል የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ነበር ። አሜሪካ ከኢትዮጵያ ፣ ከሱማሊያ ፣ ከጅቡቲ ፣ ከሱዳንና ከኬንያ ጋር የነበራትን የግንኙነት ታሪክ በአጭሩ አቀረበ ። ሚስተር ሾውፌል ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ሲመልስ « በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች የተጣሱ ቢሆንም በሀገሪቷ ውስጥ ያለው ሰብአዊ መብት በብዙ መልኮቹ ሲታይ በርከት ካሉ አገሮች በመፈጸም ላይ ካለው ሁናቴ የባሰ አይደለም » [17] ሲል ገልጾአል ። ስለ « ሰብአዊ መብቶች » ና ስለ ፖለቲካ እስረኞች የአሜሪካ መንግሥት ኃይለ ቃላት ሳይጠቀም በኢትዮጵያ ላይ ዲፕሎማሲያዊ ተጽእኖ ለማድረግ «መግለጫ አውጥቶ » እንደነበረ ገልጧል ።

ለሶስት ቀናት ያህል በቆየው በዚህ ስብሰባ መዝጊያ ላይ የኮሚቴው ሊቀመንበር በኢትዮጵያ ስላለው « ሰብአዊ መብት » ሲናገር ፡—

ካለእኛ /ካለአሚሪካ/ የማያቋርጥ ወታደራዊ ዕርዳታ ሊኖርና የኤርትራውን ጦርነት ሊቀጥል የማይችለው የኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ እንዲያውም ብቸኛ የጦር መሣሪያ ለቀባዮች እኛ ከሆንን፣ ራሳችሁን በራሳችሁ ማጥፋት ካልፈለጋችሁ በስተቀር ወደፊት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰብአዊ መመብቶችን እየጣሳችሁ፣ እያሠራችሁና እያሰቃያችሁ መኖር አትችሉም፤ ቀይ መስቀል ወይም አምነስቲ ኢንተርናሽናል በአንዳንድ ቦታዎች ተዘዋውረው ጉብኝት እንዲያገርጉ ልትከለክሉ አትችሉም ለማለት ከሚያስችል ደረጃ ላይ ነኝ ብዬ አገምታለሁ፤ [18] ብሎአል ።

Digitized by Google

ሴናተር ክላርክ ኢምፔሪያሊዝም እያረጀና እያፈጀ ካለበት ከአሁኑ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ይልቅ ገና አፍላ በነበረበት በ19ኛው ምዕተ ዓመት አሜሪካ ውስጥ እንደነበር የፖለቲካ ሰው በመሆን ተናገረ ። ለመሆኑ አሜሪካ ከቬየትናም ያገኘችው መራራ ትምህርት እንዲህ በቀላሉና በቶሎ እንዴት ሊዘነጋ ቻለ ?

ይሁንና በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሁኔታዎች ሁለት ዕውነታዎችን ግልጽ እንዳደረጉ መናገር ይቻላል ። አንደኛው የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን አብዮት ለማክሸፍ ወታደራዊ አሻጥር መፈጸሙ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የፈጸመው ወታደራዊ አሻጥርና ደባ ግቡን ሳይመታ መክሸፉ ነው ። ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል ሚዛኑ ወደ ሶሺያሊዝም እንዳዘነበለ ያመለክታል ። አሜሪካም ከእንግዲህ ወዲያ ለኢትዮጵያ « ብቸኛ» የጦር መሣሪያ አቅራቢነቷ አከተመ ። የኢትዮጵያ መንግሥት ራሱን በራሱ አላጠፋም ። ስለሆነም አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ከሚያስችላት « በጣም አስተማማኝ መድረክ » ላይ ተመልሳ ለመውጣት አልቻለችም ።

የ1968(እ.አ.አ. 1976) የሕግ መወሰኛው ስብሰባ ኢትዮጵያን አገልሎ ብቸኛ ለማድረግ ሞክሮ ነበር ። የኢትዮጵያን መንግሥት አጥላልቷል ። የአፍሪካን ቀንድ ትክክለኛ ሁኔታ አዛብቶ አቅርቦአል ። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አብዮታዊ ዕድገት ከስትራቴጂያዊ ጥቅሞች ፣ ከጂኦፖለቲክስ ፣ በአጠቃላይ የ አ ሜ ሪ ካ ኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ከመፃረሩ አንጻር በመመልከት አንቋሽሾዋል ። ይህ ስብሰባ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጭዎች ፀረ ኢትዮጵያ አስተሳሰብና አቋም ይበልጥ እንዲፋፋም አስተዋጽኦ አድርጓል ። በዚህም ምክንያት በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት የኢትዮጵያ አብዮታውያን ወደፊት ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ለሚያደርጉት መራራ ትግል ተዘጋጅተው መጠበቅ እንደሚገባቸው ጠቁሟቸዋል ።

የኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ወቅት

ከየካቲት 1968_ጥቅምት 1969

የሚነዛው ፀረ ኢትዮጵያ ወሬና ያለው « የሕዝብ አስተያየት » በአሜሪካ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚያስከትለው ተጽዕኖ እየታወቀ ከላይ የተጠቀሰው ስብሰባ ሆን ተብሎ የተደረገና መዘዝም ያስከተለ ነበር። የአሜሪካ መንግሥት የሕዝቡን አስተያየት ራሱ በፈለገው መንገድ ለመምራትና ቀስ በቀስ የኢትዮጵያን አብዮት ለማፈን በእርግጥ እየተዘጋጀ ነበር ።

በመስከረም 1968ና ጥቅምት 1969 መካከል የነበረው ወቅት ለለጋው የኢትዮጵያ አብዮት የከባድ ፈተና ወቅት ነበር ። ነጭ ሽብር የተስፋፋበት፣ የተለያየ አሻጥር የሚከናወንበት፣ የአገሪቷን አንድነትና የአብዮቱን ሕልውና የሚያናጋ የተቀነባበረ የውስጥና የውጭ ሴራ የተባባሰበትና የተቀነባበረበት ወቅት ነበር ። በውስጥ አያሌ አብዮታውያን በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ተገድለዋል ። ከውጭም በምዕራብና በሰሜን በሱዳን የተደገፉ አድህሮት ኃይላት ፣ በምስራቅና በደቡብ የሱማሌ መንግሥት ወታደሮች ስርገው በመግባታቸው የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ብሄራዊ ህልውና በከፍተኛ ደረጃ ተፈታተኑት ። በደርግ ውስጥም የተካሄደው የመደብ ትግል በታኅሣሥ ወር 1969 ደርግ በአዲስ መልክ እንዲዋቀር መንገድ ከፈተ ። በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ በጊዜው ይበልጥ አጣዳፊውና ዓይነተኛው ጉዳይ የውጭ ፀረአብዮት ኃይሎችን ወረራ መቋቋምና በአብዮታውያንና በአስመሳዮች መካከል የነበረው ፍጭት አብዮታውያን የበላይነትን እንዲቀዳጁ ማድረግ ነበር ።

Digitized by Google

በ1969 በጥር ወር መጨረሻ ገደማ በደ
ርግ ውስጥ አድብተው አብዮቱን ለቅልበሳ
ያመቻቹና ሲያውጠነጥኑ በነበሩት በነተ
ፈሪ ባንቲና ሌሎች ከፍተኛ ሥልጣን ይዘው
በነበሩ የደርግ አባላት ላይ አብዮ
ታዊ እርምጃ ከተወሰደ ጀምሮ የአሉት ማስ
ረጃዎች ሁሉ የኢምፔሪያሊዝም ጠብ አጫ
ሪነትና ይፋ ተቃውሞ ይበልጥ ጉልህና
ግልጽ እየሆነ መምጣቱን ያሳያሉ ። በአን
ጻሩም የኢትዮጵያ አብዮት እየጐላና ይበ
ልጥ እየጠነከረ ሄደ ። ከእንግዲህ ኢትዮጵያ
ና ኢምፔሪያሊዝም በማይጣጣም ሂደትላይ
መሆናቸው የማያጠራጥር ሆነ ። የኢትዮጵ
ያን አብዮት ለማፈን የአሜሪካ መንግሥት
በየካቲት ወር 1969 ኢትዮጵያ « ሰብአዊ
መብትን » ጥሳለች በማለት [19] ለኢትዮ
ጵያ የሚአደርገውን የወታደራዊ « ዕርዳታ»
የሚቀንስ /የሚያቆም/መሆኑን አስታውቀ ።
በዚሁም ጊዜ ፣ አሜሪካና ሌሎችም የኢም
ፔሪያሊስት አገሮች ለተወረሱት ድርጅቶ
ቻችን « ካሣ» ይከፈለን በማለት ፣ የንግድና
የብድር ቅነሳን ፣ የመዋዕለ ንዋይን ዋስት
ናን መግታትን የሚጠቀልል የኢኮኖሚ
ተጽዕኖ አደረጉ ። በፖለቲካው ረገድ ፣ የኢ
ምፔሪያሊዝም ፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ፣
የነበሩት እንደ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል
ያሉት ሁሉ ፀረ ኢትዮጵያ አቋማቸውን ይበ
ልጥ እያጠናከሩት ሄዱ ። እብሪተኛው የሱ
ማሊያ የገዥ መደብ ለብዙ ጊዜ የተጠናወ
ተውን የግዛት መስፋፋት የዕብሪት ዓላማ
ውን እውን ለማድረግ ኢትዮጵያን ለመው
ረር እየተዘጋጀ ነበር ። ኢትዮጵያን ከሰ
ሜን ፣ ከምዕራብና ከምሥራቅ ለማፈንና
አብዮቱንም ለመቀልበስ በተለያዩ አቅ
ጣጫዎች የተሰለፉት አድኃሪዎች በ1969
መጀመሪያ ላይ መንቀሳቀስ ጀመሩ ። በአጠ
ቃላይ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የአብ
ዮቱ ሕልውና አስጊ ሁኔታ ላይ ወደቀ ።

የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያን አብ
ዮት ለሚወጉ ሁሉ የሞራልና የማቴሪያል
ድጋፍ ለመስጠት በየካቲት ወር ፣ በ1969
መግለጫ በማውጣት በኢትዮጵያ ላይ ጦር
ነት አወጀ ። ከአድኃሪው ሥርዓት የተወረ
ሰው የመከላከያ አቋም ደካማና የአሜሪካን
ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ ስለነበር ፣ በውስጥና
በውጭ የተቀነባበረውንና የተደራጀውን
ጥቃት ለመቋቋም በመጀመርያው ወቅት
በጣም አስቸጋሪ ነበር ።

የግብፅ ፕሬዚዳንት ሳዳት በሰሜን በኩል
ያለ፡ፎካሪ ጠላት ነበር ። በኢትዮጵያና ሱዳን
ወሰን ላይም በብዙሺ የሚቆጠሩ ወታደሮ
ቹን አሰፍሮ ነበር።ሱዳንም በዚያን ጊዜ ኢት
ዮጵያን በጠላትነት ትመለከት ነበር ። ከቀይ
ባሕር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላ
ቸው እንደ ሶርያና ሱማሌ የመሳሰሉት አገ
ሮች የነበሩበት ስብሰባ ቀይ ባሕር የዓረብ
ሐይቅ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ላይ
ለመወያየት በሰሜን የመን ቴይስ ውስጥ ተካ
ሄደ ። ቀይ ባሕር አረባዊ እንደሆነ ሁሉ አፍ
ሪካዊም መሆኑ ችላ ከመባሉም በላይ ጉዳዩ
በዚያ ወቅት የተነሳው በኢትዮጵያ ላይ ተጽ
ዕኖ ለማድረግ ታስቦ መሆኑ ግልፅ ነው ።
ይሁንና እንዲህ ላሉት ግልጽ ደባዎች ሁሉ
የኢትዮጵያ መልስ ቀይ ባሕር በቀይ ደማ
ችን በቀይ ባሕርነቱ ጸንቶ እንዲቆይ እና
ድርጋለን የሚል ነበር ።

በመሆኑም እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች ሥር
ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷን ለመጠበቅ
ና በዙሪያ ከሚያንዣብቡባት የኢምፔሪያ
ሊስት ኃይሎች አብዮትዋን ለማዳን የሶሻ
ሊስት አገሮችን ዕርዳታ ከመጠየቅ በቀር
ሌላ ምርጫ አልነበራትም ። ከዚህም ጊዜ
ጀምሮ ሁኔታዎች በፍጥነት መለዋወጥ መጀ
መሩ። ኢምፔሪዲያሊዝም፣ በግብረአበሮቹና
በቡችሎቹ አማካይነት በአፍሪካ ቀንድ የከ
ፈተው ጦርነት ከኢትዮጵያ ቆራጥ አብዮታ
ዊ፣ ፀረኢምፔሪያሊስት አቋምና በቅርብና
በሩቅ ካሉ ተራማጅ ኃይሎች ጋር በመፋ
ጠጡ ኢትዮጵያ ለጦር መሣሪያ መግዣ
ለአሜሪካ መንግሥት ቀደም ሲል የከፈለ
ችውን ገንዘብ የማይመልስና የጦር መሣ

ሪያ መሸጡን ማቆሙን አሜሪካ በይፋ አስታወቀ ፡፡ በሚያዝያ ወር የኢትዮጵያ መንግሥት የኢምፔሪያሊስት ተጽዕኖ ቅሪት የሆኑትን እንደ ቃኘው ጦር ሠፈርን ፣ የአሜሪካ መንግሥት የጦር አማካሪ ተቋምና የአሜሪካ የባህልና የማስታወቂያ ድርጅትንና የመሳሰሉትን የሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ተቋሞችን ዘጋ ፡፡ ይህም በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግሥት መካከል በ1945 የተፈረመውንና ለ25 ዓመታት እንዲቆይ የታቀደውን የመከላከያ ስምምነት እንዲቋረጥ አደረገ ፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያና በኢምፔሪያሊዝም መካከል የነበረው አንደኛው የግንኙነት ሰንሰለት ተበጠሰ ፡፡

የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታና የወታደራዊ ኃይል ይዞታን በመመልከት የሱማሊያ ሰርጎገቦች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመግባት አሻጥር፤ ዘረፋና ንብረትን የማውደም ድርጊታቸውን አፋፋሙት፡፡በሚገባ ያልታጠቀው የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በሱዳን ድንበር ፣ በቀይ ባሕር አካባቢና በኡጋዴንና በደቡብ በኩል የተነሣውን የአድኃሪያን የወረራ እንቅስቃሴ ለመቋቋም አዳጋች ሆነበት ፡፡ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይህንን አሳሳቢ ሁኔታ ለመቋቋም 300,000 ሚሊሺያዎችን የሚያሰለጥንበት የአጭር ጊዜ መርሐ ግብ በሥራ ላይ አዋለ፡፡

ለረጅም ጊዜ የወረራ ዕቅዱን ሲያዘጋጅ የነበረውና እስከ አፍጢሙ የታጠቀው የሱማሊያ ወታደር « በነፃ አውጪ » የደፈጣ ተዋጊዎች ስም በሐምሌ ወር1969 ታንኮች፣ የጦር አውሮፕላኖች፣ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት በማሰለፍ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ የሆነ አድኃሪ ወረራ አካሄደ ፡፡ ወረራው ኢትዮጵያ ድንገት ሳታስበው የመጣበት ስለነበረ በሚገባ የተጠናከረውንና የተዘጋጀውን የሱማሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ ሠራዊት በመጀመሪያ ላይ ለመቋቋም ያደረገ ውትግል አጥጋቢ አልነበረም ፡፡ ወራሪው ኃይል « ታላቋ ሶማሊያ » በሚለው ወሰን ሳይገታ በምሥራቅ 700 ኪሎሜትር በደቡብ 300 ኪሎ ሜትር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ ከገባ ፡፡ ለወራሪዎቹ የሱማሊያ ገዥዎች «ታላቋ ሶማሊያ»የሚለው ቀደም ሲል የነበረው ሀሳብ በተግባር ሲታይ ጊዜ ያለፈበት ይመስል ነበር ፡፡

በ1969 የነበራቸው ዓላማ ይበልጡኑ ለምመሬቶች ፣ ወንዞች ፣ የኢትዮጵያን አንባዎችና አካባቢዎች እንዲሁም ሱማሊኛ ተናጋሪዎች ያልሆኑ አርሶ አደሮች የያዙትን አካባቢዎች መውረር ነበር ፡፡ በርግጥ በሱማሊያ ወራሪ ኃይሎች ጥቃት ከደረሰባቸው የሐረርጌ ፣ የባሌ ፣ የሲዳሞና የአርሲ ሕዝቦች ውስጥ ከ10 ሚሊዮን የሚበልጡት ሱማሊኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ናቸው ፡፡ በመሆኑም በ1969 የሱማሊያ የገዥ መደብ « ታላቋ ሱማሊያ » የሚለውን አብሪት ፍቺ ሳይቀይረው አልቀረም ፡፡

ሱማሊያ ኢትዮጵያን ከወረረችና ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቃ ከገባች በኋላ [20] ማለትም በሐምሌ 1969፣ አሜሪካ «በመርህ ደረጃ ሱማሊያ ያላትን ድንበር /የትኛውን?/ ለማስከበር ይረዳት ዘንድ ወታደራዊ ዕርዳታ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆኑን አስታወቀ ፡፡ [21] ከወራሪዋ ከሱማሌ ጐን የተሰለፈው አሜሪካ ብቻ አልነበረም ፡፡ የዚህ ሴራ መሪ የሆነው አሜሪካ ፣ በአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ማለትም በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ፣ በጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ፣ በኢጣሊያና እንዲሁም በአድኃሪ ዓረብ አገሮች ማለትም በሳውዲት ዓረብ፣ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ በሚገኙ የዓረብ አገሮች ፣ በግብፅና በኢራን [22] ታጅቦ ነበር ፡፡ በመሆኑም የሱማሊያ ወረራና የግዛት መስፋፋት ዓላማ የታገዘው የተቀነባበረውና የተቀናጀው በኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ነበር ፡፡ ወረራው የተፈጸመባት ኢትዮጵያ ከ1927—28 በሞሶሎኒ ፣ ፋሽስታዊ ወረራ እንደደረሰባት አደጋ ሁሉ እጅዋን ታሥራ እንድትቀር ተደረገች ፡፡ ሱማሊያም ወረራዋን

Digitized by Google

የመጀመረችው በወታደራዊ ኃይልዋ በመመካት ጭምር ነበር ። አንድ ታዛቢ እንደ ተናገሩት «ኢትዮጵያ ለነበርዋት የአሜሪካን ተዋጊ ጀቶች የሚያስፈልጋትን የመለዋወጫ ዕቃዎች ማለቂያቸው ሲቃረብና ከሶቭዬት ኅብረት ከመምጣታቸው ቀደም ብሎ ሶማሊያ ባለ በሌለ ኃይልዋ ኢትዮጵያን አጠቃች ። »[23]

የሱማሊያን ወረራ በሚመለከት ረገድ አሜሪካ የወሰደችው እርምጃ የካርተር አስተዳደር በአፍሪካ በአጠቃላይ በሚከተለው ፖሊሲና በአፍሪካ ቀንድ ካለው ጥቅም አንፃር መታየት አለበት ። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ካርተር ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ ሱማሊያን አባብሎ ከጐኑ በማሰለፍ ፣ ሶቭዬት ኅብረት በአፍሪካ ቀንድ የነበራትን ተደማጭነት በአሜሪካ ለመተካት መንገድ ሲፈልግ ቆይቷል ። ካርተር ፣ ለሁለቱ ባለሥልጣኖቹ ለቫንስና ብረዘንስኪ «በተቻለ መንገድ ሁሉ ሱማሊያ ወዳጅ፟ነችን እንድትሆን ጥረት እንዲያደርጉ ልነግራቸው እፈልጋለሁ »[24] ረሊል አሳስቧል ። ከዚህም በተጨማሪ ሶቭዬት ኅብረትና ሌሎችም አገሮች«በአሁኑ ጊዜም ሆነ ለወደፊቱ ለኛ/ለአሜሪካ/ጠቃሚ በሆኑ የዓለም ክፍሎች ያሏቸውን ተቀባይነት በኃይል ለመቋቋም»[25] እንደሚፈልግ ተናግሯል ። ኢትዮጵያ ለረዥም ጊዜ በታቀደው ወረራ ጉዳት ሲደርስባትና በሱማሊያ ወራሪዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንጹሕ ዜጐችዋ ሲያልቁባትና ይህ ነው የማይባል ንብረት ሲወድምባት አሜሪካና አጋሮችዋ ከምንም አልቆጠሩትም ። እነሱን የሚያሳስባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ሶሺያሊዝም ያለውን ተቀባይነት እንዴት ማስወገድ ይቻላል ? የኢትዮጵያን አብዮት እንዴት ማፈን ይቻላል ? በአካባቢው ምቹ የሆነ እስትራቴጂካዊ ቦታ እንዴት ማግኘት ይቻላል ? በአብዮት ማዕበል እንዳይጠራረጉ የሚሰጉትን በአካባቢው የሚገኙትን አድኃሪ የዓረብ አገሮችና ሌሎች የገዥ መደቦችን ማጽናናትና ማባበል እንዴት ይቻላል ? የሚል ነው ።

የሱማሊያ ወራሪ ኃይል በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው የሕይወትም ሆነ የንብረት ጥፋት ወይም የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ስለመጣሱ እንዲህ ያለው «የተቀደሰ» የኢምፔሪያሊስት ዓላማ ደንታ የለውም ። ጥያቄው ሱማሊያ ይህንን ሁሉ በሚገባና በፍጥነት ታደርገዋለችን ? ለዘለቄታው በወረራ የያዘችውን ቦታ በራሷ ጠብቃ ለማቆየት ተስፋ የሚጣልባት ናትን ? ለፈጸመችው ወረራ ፣ ኢምፔሪያሊስቶች ለሰጧት የጦር መሣሪያ ባለውለታ ናትን ? ሱማሊያ በኬንያ ያላትን የግዛት ጥያቄ እርግፍ አድርጋ በመተው ምዕራቡን ከስጋት ታድነዋለችን ? የሚለው ነበር ። ለማንኛውም ሶማልያ ለራሷ ቀናትም አልቀናትም፣ የኢትዮጵያ ግዛት ተነጠቀም አልተነጠቀም ፣ ኢምፔሪያሊዝም ከሶማሌ ወረራ የጠበቀው ዋናው ቁም ነገር የኢትዮጵያን አብዮት መቀልበስ ነበር ።

ከዚህም በላይ ፣ በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው የ1969ኙ የሶማሊያ ወረራ ከአሜሪካ ጋር በተደረገ መግባባት መሆኑን የሶማሊያና የአሜሪካ ቃል አቀባዮች ባደረጓቸው የሀሳብ ልውውጦች ተጠቁሟል ። ለምሳሌ ፡- በ1970 መስከረም መጀመሪያ ላይ የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም በሶማሊያ ላይ ያደረገውን ጊዜያዊ የጦር መሣሪያ ዕገዳ በማስመልከት ሶማሌዎች አሜሪካኖችን « በተሳሳተ ጉዳና በመምራት ከፍተኛ ውድቀት እንዲደርስብን አድርጋችኋል » በማለት ወቅሰዋቸዋል ። ለዚህ ምላሽ ፣ የወቅቱ የአሜሪካው የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ሪቻርድ ሙስ እንደሚከተለው ተናግሯል ፡—

/ ከሐምሌው ጥቃት / በፊት ከሌሉች ሰገሮች ጋር ሆነን የሶማሊዎችን ሕጋዊ የመከላከያ ፍላጉታቸውን ለማሟላት ፈቃደኞች እንደነበርን ነገረናቸዋል ። ይሁንና

Digitized by Google

ሰርቆ ለስተዋይ የሆነ ሰው በዚህ እኛ በሰጠነው የተሰፋ ቃል ተመክቶ ትልቅ የወረራ ጦርነት ባላካሂደም ነበር ። [26]

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምም ሆነ የእሱ ተባባሪ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በወረራው ወቅት ሆነ በኋላ የሶማሊያን ወረራ አላወገዙም ። እንዲያውም በሶማሊያ ወረራ ለተጉዳችው ኢትዮጵያ ትብብሯን ላሳየችው ኩባ የአሜሪካ መንግሥት መሪዎች ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ድንፋታና ማስጠንቀቂያ አስተላለፉ ። የኢምፔሪያሊስቶች የዜና ማሠራጫዎች የጦርነቱን ሁኔታ በተውገረገረና በተጣመመ መንገድ በማቅረብ ኢትዮጵያ ላይ ተረባረቡ ። [27] እጅግ ድንፋታ የተሞላበት የኢምፔሪያሊስቱ « ነፃ ፕሬስ» የገዥ መደቦችን ፍላጐት ለማገልገል መቆሙን በአፍሪካ ቀንድ ላይ በሰጠው አስተያየት አሳይቷል ። ሁሉም ነገር በእጃቸው ስለነበር ፣ የሶማሊያ ወራሪዎች እንደ ኢምፔሪያሊስቱ ፕሮፓጋንዳ ቢሆን ባሸነፉ ነበር ። ይሁንና ለኢምፔሪያሊዝምና ለሶማሊያ ቡችሎቹ አልሆነላቸውም ፣ ድሉ የሚለየው በጦሩ ሜዳ ነበርና ኢትዮጵያም በመጨረሻ በአሸናፊነት ወጣች ።

የመሸነፍ ዳመና በሶማሊያ ላይ ሲያንዣብብ ተለዋዋጭ መልክ ያለው የኢምፔሪያሊስቱ የዜና ማሰራጫ መልኩን በመቀየር ፣ ቀደም ሲል የተረዳውን ነገር ማስተጋባት ጀመረ ። አንድ ታዋቂ የአሜሪካ ዕለታዊ ጋዜጣ በርዕሰ አንቀጹ ሲጽፍ ፣ « የካርተር አስተዳደር የሶማሊያ እርምጃ ወረራ መሆኑን የሚገነዘብበት የሞራል ጥንካሬ ሊኖረው በተገባ ነበር ብሎ ማንም መገመት ይችላል » ብሏል ። ይህ ፣ በእንግሊዞች አነጋገር እንደሚባለው ፣ የአዞ እንባ ከማንባት በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም ።

መከላከያ በሌላቸው ኢትዮጵያውያን ላይ ባደረሱት ከፍተኛ ጭፍጨፋና ጥፋት ፈንድቀው ፣ ግብዝና እንደነሱ በወረራው የሚደሰቱ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የዜና ሰዎችን በማምጣት ድላቸውን እንዲያናፍሱላቸው በማድረግ የሶማሊያ ወራሪዎች በጊዜያዊ ድል ሲፈነጥዙ ፣ ቁስሉ ያልሻረላቸው ኢትዮጵያውያን ከሶሻሊስት አገሮች በተለይም ከሶቭዬት ኅብረት ባገኙት መሣሪያ ራሳቸውን ያደራጁና ያስለጥኑ ነበር ። በ1970 አጋማሽ ለኢትዮጵያ በማናቸውም መስክ የሚደረገው የሶሻሊስት ዓለም አቀፋዊ የሆነ የፖለቲካ ፣ የፕሮፓጋንዳና የወታደራዊ ዕርዳታ በከፍተኛ ደረጃ ጨመረ ። « አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት! » የሚለውን የጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱን ጥሪ በመቀበል ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጠላቱን ለመደቆስ ፣ የኢትዮጵያን ድንበር ለመጠበቅና አብዮቱን ለማዳን ቆርጦ ተነሳ ። በዚህ ቀውጢ ወቅት በተለይ ሶቭዬት ኅብረት ፣ ኩባ ፣ ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክና ዲሞክራቲክ የመን የወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ግዴታቸውን ለመወጣት ከኢትዮጵያ አብዮት ጐን ተሰልፈው ያበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ታሪክ ሲያስታውሰው ይኖራል ።

የግልፍተኝነት ወቅት
ከጥቅምት 1969—መጋቢት 1970

አሜሪካ ፣ በጠፈርና በየትኛውም አቅጣጫ ባላት ከፍተኛ የሳተላይት የስለላ መሣሪያና አሁንም በአፍሪካ ውስጥ ብቃት ባላቸው የየብስ የስለላ ክፍሎችዋ በመጠቀም በአፍሪካ ቀንድ ያለውን ጦርነት የየዕለት ሁኔታ ለመቆጣጠር በምትችልበት ሁኔታ ላይ ነበረች ። በእርግጥ ይህን ችሎታ የምትጠቀምበት ጠላቶችዋን ለመጉዳትና ወዳጆችዋን ለመጥቀም ነው ። ለምሳሌ ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መከላከያ የሌላቸው ኢትዮጵያውያን እንደ ስፔንሰር አባባል አጋዴን ውስጥ « እንደዝንብ እየረገፉ» መሆናቸውን ቢያውቅም ፣ « ለሰብአዊ መብት» ቆሚያለሁ ይል የነበረው የካርተር አስተዳ

ዶር በምንም መንገድ የሶማሌን እርምጃ
ለመግታት አልፈለገም ። በሌላ በኩል ግን
የአሜሪካ መንግሥት የጦርነቱን ተለዋ
ዋጭነትና በየካቲት 1970 የኢትዮጵያ ው
ያን ከፍተኛ የመልሶ ማጥቃትን ሁኔታ ሲያ
ውቅ በጠቅላላ የጦር ኃይላቸው በኢትዮጵያ
ውስጥ ከመውደሙ በፊት የሶማሊያ ወራሪ
ዎች ባስቸኳይ እንዲወጡ አድርጓል ። ይህ
በከፊል የሚገልጸው ሶማሌዎች ከጅጅጋ ፣
ከጉዴ ፣ ከቀብሪ ደሀር ፣ እና ከሌሎችም
እስከ 700 ኪ.ሜ. ድረስ ወደ ኢትዮጵያ
ዘልቀው ከገቡባቸው ወታደራዊ ጦር ሠፈ
ሮች እንዲለቁ እንዴት አመቺ እንደሆነላ
ቸው ነው ። ስለዚህም ፣ የኢትዮጵያ ነፃ
አውጭ ሠራዊት ጅጅጋን ነፃ ካወጣ በኋላ
እግረመንገዱን ወደ ሌሎች የኦጋዴን አካ
ባቢዎች ሲጓዝ በጣም ጥቂት ከሆኑት ቦታ
ዎች በስተቀር የሚቋቋመው ኃይል አላገ
ኘም ነበር ። ምንም እንኳ ወረራውን እንድ
ንጀምር « አሳስታናለች » ይሁን እንጂ
ጦርነቱን ለማካሄድ የሚያስችሉ መሣሪያ
ዎችን አልሰጠችንም በማለት ሶማሌዎች
አሜሪካንን ደጋግመው ቢወቅሱም ይህ ከፍ
ተኛ ድጋፍ ይበልጥ የሚገልጸው ድል የተ
መታችው ሶማሊያና አሜሪካ ምን ያህል
የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ነው ። እዚህ
ላይ ቁምነገሩ ፣ የአሜሪካ መንግሥት የጦ
ርነቱን ሂደት በዓይኑ ቁራኛ ሲጠባበቅ ከቆ
የና የኢትዮጵያን የመልሶ ማጥቃት ርምጃ
ካየና የፔንታጉንን ወታደራዊ ትንተና ከገ
መገመ በኋላ ሶማልያ የሚደርስበትን ጉዳት
ለመግታትና በ1970 መጨረሻ አዲስ ዲፕ
ሎማሲያዊ ቁማር ለመጀመር መዘጋጀቱ
ነው ። በዚህ ዓይነት ሶማሊያ ኢትዮጵያን
ወግታ መሬት መያዝ ባይቻላትም ኢትዮ
ጵያ በአፀፋው ሶማሊያን « እንዳትወር »
በሚል ሰበብ የሶማሌ ወዳጅና የበላይ ጠባ
ቂ ሆና ለመታየት መራራጮጥ ጀመረ ።

በታኅሣሥ 1969 የሶማሊያ መንግሥት
በኦጋዴን ውስጥ ዘላቂ ድል አገኘሁ እያለ
ማናፈሱን በመተው « ሶማሊያ የጥቃት
ማዕበል ሊወርድባት ነው» እያለ ይጮህ
ጀምር ። አሁን ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነ ። የሶ
ማሊያው ባሬ በሚያደርገው ወረራ የሚፈ
ልገውን ያህል ዕርዳታ አለማግኘቱን ሲገነ
ዘብ ፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ወረራ ልታደርስ
ብኝ ነው ፣ አድኑኝ በማለት የተሟላ ኢም
ፔሪያሊስት ድጋፍ ለማግኘት ሞከረ ። ዚያድ
ባሬ የኢትዮጵያን ግዛት ወርሮ ሳለ እንኳ
« የሰላም ውይይት » ዕናድርግ እያለ ለማ
ሾፍ ደፍሮ ነበር ። ይሁንና የእሱ ጉራ
በ1969 መጨረሻ ላይ በሁለቱ ወገኖች
ስለተፈጠረው ግጭት ጤናማ ግንኙነት ለ
መፍጠር የሚሞክሩ አባላት ያሉበትን በና
ይጀሪያ የሚመራ የአፍሪካ አንድነት ድር
ጅትን የሰላም ተልዕኮ መልእክተኞች ቡድ
ን እንኳ ሳይቀር አስደንቋል ። በ1970 በታ
ኅሣሥ አጋማሽ ሁለት የአሜሪካ የኮንግሬስ
አባላትም « መረጃዎችን ለመፈለግ »
ወደ አፍሪካ ቀንድ ተልከው ነበር ።
ጉዟቸው ግብጽን ፤ ሱዳንን ፣ ኢትዮጵያን ፣
ኬንያን ፣ ሶማሊያንና ጅቡቲን ያጠቃለለ
ነበር ።

በግጭቱ ጊዜ ሁሉ የሳዳት መንግሥት የአ
ፍሪካ አንድነት ድርጅትን መርሆች በመጣስ፣
ላለፉት ብዙ ዓመታት ከሞላ ጐደል ጤናማ የ
ነበረውን የኢትዮጵያንና የግብፅን መልካም
ግንኙነት ወደ ጐን በመተው ግልጽ የሆነ ፀረ
ኢትዮጵያ አቋም ይዟል ። ፕሬዚዳንት ሳዳት
በሱዳን ውስጥ ወታደሮቹን ከማስፈሩና በኢ
ትዮጵያ ላይ « የማስ ፈራሪያ » ቃላት ከመሰ
ንዘር አልፎ ካይሮን የዋሽንግተን ፣ የሪ
ያድና የሞቃዲሾ ቀንደኛ አድሃሪዎች
መገናኛና መዶለቻ አድርጓታል ። የአሜ
ሪካ ኮንግሬስ አባላት ቦንከርና ትሶንጋስ ግብ
ጽን በጐበኙበት ጊዜ ፕሬዚዳንት ሳዳት በአ
ፍሪካ ቀንድ ላይ የሶቭዬት ኅብረት « ቀይ
አደጋ » በማውሳት ከሾልዚንትሲን በል
ጧል ። በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ላይ ያሳ
የው አጉል ጀብዱ 30 ሚሊዮን ዶላር የሚ
ያወጣ የጦር መሣሪያ ለሶማሊያ መስጠቱና
በኅዳር ወር 1969 ሳዳት በርበራን እንዲይዝ

Digitized by Google

ዚያድ ባሬ ያቀረበለትን ጥያቄ እንዳልተቀ
በለው አስረድቷል ። ከዚህም በላይ ሳዳት
የሞቃዲሾውን አሻንጉሊት ዚያድ ባሬን
ምን ያህል መቆጣጠሩን ሲገልጽ ፣ «ባሬ
ኬንያን ከወረረ ልክ አገባዋለሁ » በማለት
ተናግሯል ። በመጨረሻም ሳዳት በአፍሪካ
ቀንድ አሜሪካ ቀጥተኛ የጦር ኃይል
ስለሌላት « በአካባቢው እሱ ኃያልሆና
መገኘት እንዳለበት » [28] ለአሜሪካ ልዑ
ካን ሐሳብ አቀረበ ።

ሁለቱ የምክር ቤት አባላት ቢያንስ ቢያ
ንስ በይፋ የነበራቸው አቋም በአፍሪካ ቀን
ድ በሚካሔደው ግጭት አሜሪካ «የገለል
ተኝነት» አቋም መያዝ እንዳለባት ፣ ለሶማ
ሊያ ወታደራዊ ዕርዳታ መስጠት «በአፍሪ
ካ ውስጥ ስላሉ ወሰኖች የአፍሪካ አንድነት
ድርጅት ካለው አቋም ጋር የሚቃረን በመ
ሆኑ «ለሶማሊያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ
መንገድ» ወታደራዊ ዕርዳታ መደረግ እንደ
ሌለበት ፣ በአፍሪካ ቀንድ የአሜሪካ «ጣል
ቃ ገብነት» ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መሆ
ን እንዳለበትና ሶቪዬት ኅብረት በአፍሪካ
ቀንድ የሚያደረገውን እንቅስቃሴ መቃወ
ሟን አሜሪካ መቀጠል እንዳለባት የሚገ
ልጽ ነበር። ሁለቱ የምክር ቤት አባላት በአ
ሜሪካና በኢትዮጵያ መሐል ያለው ግንኙ
ነት እየሻከረ መሔዱን ካጤኑ በኋላ «ለሁ
ለቱ አገሮች ሕዝቦች ጥቅምና» በኢትዮጵያ
ሶሻሊዝምንም ለመፈታተንና ጥቅማቸውን
ለመጠበቅ በሁለቱ አገሮች መሐል ያለው
ግንኙነት እንዲቀጥል አሳስበዋል ። [29] ይህ
በእንዲህ እንዳለ ፣ በራሱ በካርተር አስተዳ
ደር ፤ በአፍሪካ ቀንድም ሆነ በሌሎች የአ
ፍሪካ አገሮች ውስጥ የአፍሪካ ብሔረተኝ
ነት «በሶቪዬትና በኩባ በሚመራው» ሶሻ
ሊስት አብዮት ላይ ድልን መቀዳጀቱ ፣ አይ
ቀርም በሚሉ በያንግ በሚመሩ የአፍሪካ ጉ
ዳይ አጥኚዎችና አሁንም በቀዝቃዛው ጦር
ነትና በዶሚና ቲዎሪ ማለትም አንድ አገር
ሶሻሊስት ከሆነ ሌላውም ይከተላል በሚል
አስተሳሰብ በማመን፣ በአፍሪካ ያለውን የሶ
ቪዬት ኅብረትንና የኩባን እንቅስቃሴ«ለ
መቋቋም» ጠንካራ እርምጃ መወሰድ አለ
በት በማለት በብሬዝንስኪ በሚመሩ የከ
ሬምሊን ጉዳይ ተከታታዮች መሐል የፖ
ሊሲ ግጭት መኖሩን የኢምፔሪያሊስት ጋዜ
ጦች ይገልጹ ነበር ።

በጥር ወር 1970 መጨረሻ ላይ የኔቶ የ
ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የአፍሪካን ቀንድ
ሁኔታ እንደገና ለመመርመር በዋሽንግተን
ስብሰባ አድርገው ለስምንት ሰዓት ከተወ
ያዩበት በኋላ ፣ የግጭቱ ነባራዊ ሁኔታ የፈ
ቀደላቸውን ውሳኔ አስተላለፉ ። «በአፍሪካ
ቀንድ ላለው ችግር በጦር ኃይል የመጨረሻ
መፍትሔ ማግኘት የማይቻል መሆኑን »[31]
በይፋ አመኑ ። በሐምሌ ወር 1969 እን
ደነበረው ሳይሆን በጥር ወር 1970 የኃ
ይሉ ሚዛን ወደ ኢትዮጵያ በማጋደሉ የኢ
ምፔሪያሊስቱ ዓለም ከአዲሱ ሁኔታ ጋር
ለመጣጣም ይሞክር ጀመር ። ኔቶ ያደረገው
የሰላም ጥሪ ለውዝግቡ ሰላማዊ መፍትሔ
የሚሻ መሆኑን ለመግለጽ የሚያደርገው
የታክቲክ አቀራረብ ነበር ።

በመጨረሻም ፤ ሶማሊያ ከተሸነፈችና
ወታደሮቹዋን ከኢትዮጵያ ግዛት ካስወጣች
በኋላ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ላይ የበቀል ወረ
ራ እንዳታካሂድ አሜሪካ የሶማሊያ አፈቀ
ላጤ ሆና እንድትቀርብ ተገደደች ። በዚህ
መሠረት የአሜሪካን መንግሥት በየካቲት
ወር መጨረሻ ላይ በሚስተር ዴቪድ አሮን
የሚመራ ከፍተኛ የአገር ደኅንነት መልእ
ክተኞች ቡድን ወደ አዲስ አበባ ላከ ። ሚስ
ተር ዴቪድ አሮን በጉብኝቱ ወቅት ከጓድ
ሊቀ መንበር መንግሥቱ ጋር መልእክተ
ኞቹ እንደተነጋገሩ የሶማሊያ ወታደሮች ከ
ኢትዮጵያ ግዛት ከወጡ በኋላ የኢትዮጵያ
ሠራዊት የሶማሊያን ድንበር አልፎ የማይ
ገባ መሆኑን ሊቀ መንበሩ ለአሜሪካ መል
እክተኞች ፤ «በግል» አረጋግጠውላቸዋል
የሚል ዘገባ በአሜሪካ ጋዜጦች ወጣ ።

Digitized by Google

እውነት መናገር ከተፈለገ ፤ አሜሪካና ምዕራባውያን ወዳጆቹዋ በአፍሪካ ቀንድ ይካሄድ የነበረውን ግጭት በዝምታ የተመለከቱ አልነበሩም ። በመጀመሪያ የአሜሪካ ባለሥልጣናት በሶቪዬት በምትረዳው ሶማሊያና በሶቪዬት በምትረዳው ኢትዮጵያ መካከል ያለው ትርኢት እንዴት ግልጽ እንደሚሆን ለማየት በጽሞና መጠበቅ ይቻላል ብለው አሰቡ ። ሶማሊያ የምታካሂደውን ወረራ በማባባስም ሆነ አገሪቱን በመገንጣጠል ወይም በውስጥ የሚነሳውን የፖለቲካ ትግል በመጠቀም የካፒታሊስቱ ዓለም ፍላጎት የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት ፈር ማስለቀቅ ነበር ። ስለዚህ የሶማሊያ ወረራ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ይህን የጸረ አብዮት ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ባላቸው ዓላማ መሠረት በተዘዋዋሪ መንገድ ጣልቃ እንዲገቡ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ። ሶቪዬት ኅብረትም ፣ ባላቸው የወሰን ግጭት የተነሳ አንድ ቀን ሊዋጉ የሚችሉ ሁለት አገሮችን በአንድ ጊዜ መርዳት አስቸጋሪ እንደሚሆንባትና በዚህም « የተነሳ አንድ ወቅት ላይ » ሁለቱንም «እንደምታጣ» ወይም አንደኛውን ወገን በመደገፍ ሌላውን «እንደምትለቅ» ተገምቶ ነበር ። በዚህን ጊዜ ኢምፔሪያሊስቶች በጦርነቱ «ጣልቃ በመግባት» ስማቸው ሳይጉድፍ አንደኛውን ወገን ለመያዝ አቀዱ ። ሆኖም እውነቱ ከዚህ የሐሳባውያን አመለካከትና ትዝት የተለየ ነበር ።

ጦርነቱ ካበቃ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ በተነሳው ግጭት ምክንያት ለራሱ ጥቅም ማስጠበቅ ታማኝ ሊሆን የሚችለውን ወገን ለመደገፍ መሯሯጥ ጀመረ።በተዘዋዋሪ መንገድ ቢረዳም፣አሜሪካ በሰባቱ ወራት ጦርነት ጊዜ ውስጥለ ሶማሊያ በቀጥታ ወታደራዊ ዕርዳታ ያላደረገው ከአሜሪካ መንግሥት ፍላጎትና ዓላማ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ነው።እነኝህ ምክንያቶች የኢትዮጵያ አብዮትና በአፍሪካ ቀንድ የተካሄደው ጦርነት የፈጠራቸው ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ሲሆን ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡-

1. አሜሪካ ከቬትናም ወረራ በፊት ከነበረው የተለየ ኃይል ሆኗል ። እንደሚታወቀው በአፍሪካም ሆነ በሌሎች አህጉሮች ኢምፔሪያሊዝም እያረጀና እያፈጀ ነው ። ስለሆነም በማንኛውም ቦታ ጥቅሙን እንደፈለገው ለማስጠበቅ በሚችልበት ደረጃ ላይ አይደለም ።

2. ሶማሊያ በኬንያ ላይ ያላትን የግዛት አለኝታ ባለማንሳት የነበራት ጠባብ አመለካከት/ ለራሷ ጥቅም ስትል ነው/ አሜሪካ ግጭቱን በሚመለከት ጠለቅ ብላ እንዳታስተውልና የጀብደኝነት እርምጃም ለመውሰድ አስቸጋሪ ሆነባት ። ያም ሆነ ይህ፤ ሶማሊያ የምዕራባውያን ደጋፊ የሆነችውን ኬንያ ለመቀራረስ ቀርቶ ለመውረርም የምታደርገውን ሙከራ አሜሪካ የማትቀበለው ነው ። ኬንያ የመስፋፋትን ፖሊሲ በመቃወም የምታካሂደው የዲፕሎማቲክ ሥራም አስፈላጊ ነበር ።

3. በአፍሪካ ውስጥ የሚኖራቸው አመለካከትና ተቀባይነትም በአሜሪካ ፖሊሲ አውጭዎች ዘንድ ከፍተኛ ግምት ነበረው ። ግጭቱ በሚካሄድበት ጊዜ የአፍሪካ አገሮችን ወሰን በሚመለከት አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ወሰኖች ባሉበት መርጋት አለባቸው በማለት ግዛቶችን በድጋሚ መከፋፈልን በመቃወም የሰጡት ድጋፍ ጠንካራ አቋም ይዞ በመቆየቱ ሶማሊያ በርከት ባሉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባዎች ላይ ተቃውሞ ደርሶባታል ። በዚህ ሁኔታ ከሶማሊያ ጐን ሽንጡን ገትር በይፋ መሰለፍ ለአሜሪካ የሚያዋጣት ፖለቲካ አልነበረም።

4. አሜሪካ፤ በሶማሊያ ውስጥ ያለውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይችል ዘንድ ሶማሊያ በአሸናፊነት ለመውጣቷ እርግጠኛ አልነበረም ። ከወታደራዊ ግምገማ አንጻር

Digitized by Google

ሶማሊያ የምትቀዳጀው ማንኛውም ድል ድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት የሚቆጠር ነው ። በመጨረሻም የነበረው ሁኔታ ፣ በተለይ ሶሻሊስት ሀገሮች ያደረጉት ከፍተኛና ቁርጠኝነት የተመላበት ዕርዳታ የኢትዮጵያን አብዮት ድል ለማቀዳጀት አበቃ ።

5. «የሶቪዬቶች በጦርነት መሳተፍ» የሚለው ማስፈራሪያ የአሜሪካ የምክር ቤትን ድጋፍ ለማስገኘት ጠቃሚ ሊሆን አልቻለም ። ኩባውያን በኢትዮጵያ ወገን ሆነው በጦርነቱ ተካፋይ ከሆኑ አድኃሪ ዓረቦችና ሌሎችም በሶማሊያ ወገን ተካፍለዋል ። የሶቪዬት ኅብረት ጦር መሣሪያዎችን ማቅረብንም ቢሆን ለመከላከያ አገልግሎት እስከዋለ ድረስ የጦር መሣሪያ መጠየቅም ሆነ መቀበል የኢትዮጵያ የማይገሰስ መብት ነበር ።

ይሁን እንጂ በሌሎች ኢምፔሪያሊስት ወዳጆቹዋና በአድኃሪ የዓረብና ሌሎች የመካከለኛ ምሥራቅ መንግሥታት አማካይነት አሜሪካ ያደረገችው ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ ጣልቃ ገብነት ኢትዮጵያን እስከ ተመለከተ ድረስ ብሔራዊ ነጻነቷን የሚደፍር ነበር ።

ለሰባት ወሮች ያህል የቆየው የሶማሊያ ወረራ ፣ ኢትዮጵያ በወሰደችው የመከላከል እርምጃ አማካይነት በሰባት ሳምንታት ውስጥ ድባቅ ተመቷል ። በመጋቢት ወር አጋማሽም ላይ ጦርነቱ ማብቃቱ በይፋ ተነገረ። የሚያስደንቀውም ነገር የጦርነቱ ማብቃት ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የተነገረው በኢትዮጵያ ወይም በሶማሊያ ሳይሆን በአሜሪካ ነበር ። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ካርተር ከሶማሊያው ፕሬዚዳንት ባሬ ጋር በስልክ ከተነጋገሩ በኋላ «የባዕድ ኃይሎች በሙሉ በአስቸኳይ» ከአካባቢው ለቀው እንዲወጡ አሜሪካ የምትጠባበቅ መሆኗን በማስታወቅ በመጋቢት ወር አጋማሽ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡ ። [33]

በመጨረሻም ፣ የኢራኑ ሻህ ከፕሬዚዳንት ካርተርና ከሳውዲት ዓረብ ንጉሥ ጋር ባደረገው ስብሰባ ዋዜማ ያወጣው መግለጫ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የተጠነሰሰውን የአድኃሪዎች ዓለም አቀፋዊ ሴራን ይጠቁማል ። በወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መግለጫውን በጥብቅ ተቃውሟል ። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ በሬዲዮና በቴሌቢዥን ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ባሰሙት ንግግር ላይ እንደገለጹት ይህ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የተቃጣው አድኃሪ ዓለም አቀፍ ሴራ የሚከተሉትን ዓላማዎች ያጠቃልላል ።

1. ኢራን ፣ ሳውዲት ዓረብ ፣ ኩዌትና ምዕራብ ጀርመን የሶማሊያን ወረራ ለማስፋፊያ የሚውል የጦር መሣሪያ ለሶማሊያ ሊሰጡ ፣

2. ግብጽ ፣ ከእሥራኤል ጋር ጦርነት ታካሂድ በነበረበት ወቅት ከሶቪዬት ኅብረት ካገኘችው የጦር መሣሪያ የተቻለውን ያህል ለሶማሊያ ልትሰጥ ፣

3. ሶማሊያም በሳውዲት ዓረብ ፣ በኢራንና በምዕራብ ጀርመን ከሚገኙ የአሜሪካ የጦር ሠፈሮች የምትፈልገውን ያህል የጦር መሣሪያ በኢራን በኩል ልታገኝ ፣

4. ተጨማሪ የጦር መሣሪያዎች ካስፈለጉም ከምዕራብ አውሮፓና ከአሜሪካ ሊገዙ፣

5. ሶማሊያ ፣ እነዚህን የጦር መሣሪያዎች ከተረከበች በኋላ እንኳ ወረራውን ለማስፋፋት ካልበቃች ፣ ኢራን ከሶማሊያ ወራሪ ወታደሮች ጐን ሆና የጦር ኃይሎቿዋ እንዲዋጉ በመላክ በቀጥታ ጣልቃ ልትገባ ፣

6. ኢራን ለምታካሂደው ወረራ አማን እንደመነኛ ሥፍራ ልታገለግልና ሳውዲት ዓረብም የአየር ኃይል ድጋፍ ልትሰጥ ፣

Digitized by Google

7. የፐርሺያ የባሕር ሰላጤ አገሮችን የሚጨምር የፀረ ኢትዮጵያ ወታደራዊ ከበባ በአፋጣኝ መፈጠር ።

አሜሪካ ፤ በጦርነቱ ማብቂያ ሰሞን በአንድ በኩል ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ እርቅን የመፈለግ አዝማሚያ ስታሳይ በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች የኢምፔሪያሊስት አገሮች አማካይነት የምታሳድረውን ተጽዕኖ እየቀጠለች ነበር ።

የአፍሪካ ቀንድ ግጭት በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ነዳፊዎች መሐል ቅራኔንና ግራ መጋባትን ፈጥሮ ነበር ። በዚህም ምክንያት አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ካሉት የሁኔታዎች ዕድገት አንጻር የተከተለው ፖሊሲ ሙል ጭልጭ ያለና በመጨረሻም የውድቀትን ፈር የያዘ ነበር ። በመሆኑም « የአፍሪካን ቀንድ በሚመለከት ያለው የአሜሪካ ዲፕሎማሲ ብቃት የጐደለውና ያልተቀናጀ ነበር» በማለት አንድ የአሜሪካ ባለሥልጣን የተናገሩት እምብዛም አያስደንቅም ።

የአፍሪካን ቀንድ ግጭት በሚመለከት ረገድ፣ ከምዕራብ አድጎሮት ፖሊሲ ከስረት በኋላ ስለተወሰደው፣ ለጥቅማቸው ተስማሚ እርምጃ ሊባል የሚችለውን አንድ የሶማሊያ መንግሥት ቃል አቀባይ እንደሚከተለው ገልጾታል ።

«አሜሪካ ሐሳቧን ሰባት ጊዜ ለዋውጣለች ፤ ፕሬዚዳንት ካርተር መጀመሪያ ቃል ገቡ ። በኋላም በሀገሪቱ ውስጥ ሩሲያ ያላትን ከፍተኛ ቦታ ለመተካት እንደፈለጉ ገለጹልን ። ቀጥለውም «በመርህ ደረጃ» የጦር መሣሪያ ለመስጠት ተስማሙ ፤ መሣሪያው ለመከላከያ አገልግሎት ብቻ መዋል እንዳለበት አስታወቁን ። ከዚያም ዕርዳታ የሚሰጠን ከኦጋዴኑ ጦርነት በኋላ ነው በማለት የጦር መሣሪያ ሊሰጡን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ ። ለጥቀውም ኢትዮጵያውያንና ሩስያውያን ሶማሊያን ከወረሩ ዕርዳታ በእርግጥ እንደሚሰጠን አስታወቁን ። በመጨረሻም በሌሎች ሀገሮችም ላይ ሆነ በኦጋዴን ያለንን የግዛት አለኝታ እንድናነሳ ተጠየቅን የሚያስገቡን ግዴታ በጣም በዛ ። »[34]

በአጠቃላይ ከዚህና ከሌሎች መረጃዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሶማሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር የቻለችው አሜሪካ የጦር መሣሪያ ለመስጠት ለሶማሊያ በገባችው ቃል መሠረት መሆኑን ነው ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. *War Clouds on the Horn of Africa,* (Washington D.C. 1976). J.H. Spencer, *Ethiopia, the Horn of Africa* and *US Policy* (Cambridge mass (1977). M.A. Samuels (ED). "White paper on the Horn of Africa", *The Washington Review of Strategic and International Studies,* (Washington D.C. 1978).

2. *US Senate Hearings,* August, 1976, p. 37.

3. CF. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 21, 1968, Moscow, pp. 214-231, for Lenin's conditions for the existence of a revolutionary situation.

4. *CF. PMG, Declaration of the Provisional Military Government,* Addis Ababa, Feb. 7, 1975 p. 4.

5. *PMG, Declaration on Economic Policy of Socialist Ethiopia, Addis Ababa,* Feb. 7, 1975 p. 4.

6. For a view of why the secessionists made a desperate attempt to bring their war to the streets of Asmara see Proceedings of the *Special Seminar on class struggle and secessionism in Northern Ethiopia* (in Amharic) June 1977, Addis Ababa.

Digitized by Google

7. CF. Op, Cit. (foot note 1 above) p. 1.

8. *Ibid.*,

9. *Ibid.*, p. 2.

10. *Ibid.*, p. 5.

11. *Ibid.*, p. 94.

12. *Ibid.*, p. 99. Much of Mr. Spencer's adumbrations in the Senate hearings have been brushed up and collected between two covers in the form of *Ethiopia*: *The Horn of Africa and US Policy*, Cambridge, 1977.

13. Senate Hearings, Ibid., p. 37.

14. See *Ibid.*, p. 102.

15. See his War Clouds on the Horn, p. 114.

16. See Senate Hearings, Loc. Cit. p. 109.

17. *Ibid.*, p. 126.

18. *Ibid.* p. 138.

19. See the Baltimore Sun, Feb. 25, 1977. See also Legum and Lee, *Conflict in The Horn of Africa*, p. 69.

22. See the Economist, July 30, 1977, see 9 July, 1977, 13 July 1977, 19 July, 1977 for details.

21. See Legum and Lee, OP. Cit., p. 8.

22. See the Economist, July 30, 1977 see also the Sun July 29, 1977 for US President Carter's News Conference Comment on the subject.

23. See Michael Kaufmann's article in New York Times, August 19, 1977.

24. Cited in Washington Post, Sept. 27, 1977.

25. CF. Legum and Lee, OP. Cit., p. 8.

26. See Arnold de Borchgrove's report "Crossed Wires" *Newsweek*, Sept. 26, 1977.

27. For a brief critical analysis of western press coverage of revolutionary developments on the Horn, see the Ethiopian Revolution by World View Publishers, June, 1978.

28. See the Bonker-Tsongas report: *War in the Horn of Africa. A first hand report on the challenges for United States Policy*: US House of Representative, Washington, D.C. Feb. 3, 1978 pp. ff.

29. *Ibid.*, p. 50.

30. See *Africa* 78, February, 1978.

31. See Address by Chairman Col. Mengistu Haile Mariam, Imperialist Aggression from Vietnam to Ethiopia: What the World Learns from such aggressions, Min. of Information and National Guidance, Addis Ababa, 30 January, 1978.

32. See Washington Post, January 22, 1978.

33. See Washington Post, Feb. 27, 1978.

34. Washington Post, April 18, 1978,

Digitized by Google

የብሔራዊ ሀብት ቁጥጥር አንዳንድ መሠረታዊ ሀሳቦች

ደምሴ ኃይሉ

የኤኮኖሚ አስተዳደር መሠረተ ሀሳብ ከሀብት ሥርጭትና ክፍፍል ጋር የተያያዘ ነው ። የሀብት ሥርጭትና ክፍፍል ደግሞ አምራቹ ወገን በማምረትና በምርት ውጤት ክፍፍል ላይ በሚኖረው ተካፋይነትና ባለቤትነት ላይ ያተኩራል ። የአስተዳደሩም ዓላማ ይህንኑ የሚያንፀባርቅ ይሆናል ።

መደብ የለሽ ኅብረተሰቦች በማምረትና በምርት ውጤት ላይ የጋራ ባለቤትነት ስላላቸው የሀብት ሥርጭትና ክፍፍል አስተዳደራቸው ይህንኑ የጋራ ተጠቃሚነት የሚያንፀባርቅ ነው ። በተፃራሪው ደግሞ የመደብ ኅብረተሰቦች ይህን መሰል ግንኙነት ስለሌላቸው (ጥቂቱ ብዙሀኑን ስለሚበዘብዙ) የሠራተኛው የጉልበት ፍሬ ድልድል ያልተመዛዘነና የብዙኃኑ ድርሻ ዝቅተኛ ሆኖ እናገኘዋለን ። ይሁንና እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ነባራዊነት አላቸው ። ማለትም በነባራዊ ሕግ የሚገዛው የኅብረተሰብ ዕድገት ነፀብራቆች ወይም ውጤቶች ናቸው ።

ካፒታሊዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ የኅብረተሰቡን አኗኗርና ግንኙነት የበለጠ የተወሳሰበ ያደርገዋል ። በተጨማሪም የሚኖሩት የተግባር ዘርፎች እጅግ ከመስፋታቸው የተነሣ ፣ እርስ በርስ መያያዛቸው የበለጠ ውስብስብ ስለሚሆን የምርት ውጤቱን አጥጋቢ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚኖረው ቁጥጥር የጠበቀና የረቀቀ ይሆናል ። የማምረት ተግባር ማኅበራዊ ባህርዩ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ ሲሄድ ማኅበራዊ ቁጥጥሩ ከዚሁ ጋር የሚመጣጠን ሊሆን ይገባዋል ።

ቁጥጥር በማናቸውም ሥርዓት ውስጥ ያንን ሥርዓት ከሚገዛው ነባራዊ ሕግ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት ። በዚህም መሠረት ሥርዓቱን የሚያናጉትን የውጭና የውስጥ ሁኔታዎች መቆጣጠር መቻል ይኖርበታል ። ስለሆነም ቁጥጥር ከሥርዓቱ

Digitized by Google

ከራሱ የሚፈልቅ ሆኖ የሥርዓቱን ገጽታዎችና መለያ ባህርዮች ተቀነባብረው እንዲቆዩ በማድረግ የሥርዓቱን ሕልውና ያስጠብቃል ማለት ነው ።

ብዝበዛ ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው ቁጥጥር በምርት ውጤት ክፍፍልና ሥርጭት የንብረት ባለቤትን ጥቅም እንዲያስከብር የታቀደ ነው ። የካፒታሊዝም መሠረታዊ ሕግም ይህን የሚያቅፍ ሲሆን ገዥው መደብ ይኸው ሁኔታ እንዲጠበቅና የሀብት ይዞታው «ዘላለማዊ» ተጠቃሚ እንዲሆን በማኅበራዊ አስተዳደርና ግንኙነት ተፅዕኖ ያደርጋል ።

በማኅበራዊ ኢኮኖሚ ቅንብር ውስጥ ሰዎች በጋራ በማምረታቸው የተነሳ ከሚፈጠሩት ግንኙነት ውስጥ አስተዳደራዊ ግንኙነት ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል ። ይህ መሰሉ የሰዎች ግንኙነት ቁጥጥር በሚከናወንበት ወገንና በተቆጣጣሪው ወገን በተለያዩ መስኮች ይገለጣል ። በዚሁ ግንኙነት አማካኝነት ከምርቱ ውጤት ከፍተኛውን ድርሻ የሚያገኘው በዝባዡ መደብ ግንኙነቱ የሠመረና ቀልጣፋ እንዲሆን በልዩ ልዩ አስተዳደራዊ መሣሪያዎች ይጠቀማል ።

በካፒታሊዝም ውስጥ ሁለት የቁጥጥር መልኮች አሉ ። አንደኛው ግብታዊ ወይም ስታቲስቲካል ሁኔታ የሚባለው ሲሆን ፤ ይኸም በቀጥታ ከሰዎች ተግባር ጋር የማይጣጣምና ከሞላ ጐደል ከነሱ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ነው ።ለምሳሌ በግል ንብረት ይዞታ ላይ የተመሠረተ የገበያ ሕግ ፤ የፍላጐትና የአቅርቦት ግንኙነት በቁጥጥር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ናቸው ። ሁለተኛው ደግሞ የካፒታሊስቱ የነቃ ተሳትፎ ያለበት የታቀደ አስተዳደራዊ የቁጥጥር ሁኔታ ነው። በዚህም አማካኝነት ካፒታሊስቱ በተለያዩ የሀብት ማፍሪያዎች ውስጥ በዘመናዊ የአስተዳደር መሣሪያዎችን በመጠቀም ለተሻለና ለበለጠ የምርት ውጤትና ትርፍ አስተዳደሩን ያቀላጥፋል ።

ዳሩ ግን ካፒታሊዝም የተሻለና የበለጠ የምርት ውጤትና ትርፍ ለማግኘት ሲል ዘመናዊ የአመራረት ዘዴ እየተጠቀመ በሄደ ቁጥር ፤ የአመራረት ማኅበራዊ ጠባይም በዚያው መጠን ይዳብራል ። ይህ የዳበረው የአመራረት ማኅበራዊ ጠባይ ደግሞ ከራሱ ጋር የሚጣጣም ፤ የሚስማማና ነባራዊውን የኅብረተሰብ ዕድገት ህግን የተከተለ የምርት አስተዳደርን ይጠይቃል ። ይሁን እንጂ የግል ንብረት ይዞታና የግል ሀብት ክፍፍል ይህን አስተዳደራዊ ስልት መቀየስ አያስችልምና በግል ሀብት ይዞታ ላይ ተመሠረተው ካፒታሊዝም የፈጠረውን የዳበረ ማኅበራዊ የአመራረት ስልት የሚንከባከብ የቁጥጥር ስልት ለመቀየስ አይችልም ።

የካፒታሊዝም የምርት አስተዳደር የዚህ (ቁጥጥር) ማኅበራዊ ሂደት ተፃራሪና ጥምር ባህርዮችን ያዘለ ነው ። አንደኛ ካፒታሊዝም ማምረትን የሚመለከተው (የሚቆጥረው) ለተወሰነ የቡርዧው ጥቅም ተፈጥሮን በማምረቻ መሣሪያ አማካይነት ለመለወጥ እንደሚያስፈልግ ኃይል አድርጐ ነው። እርግጥ ሥራ የማንኛውም ኅብረተሰብ ዕድገት መሠረት በመሆኑ የሥራ አስተዳደር በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለውን (መኖር የሚገባውን) ዝምድና ለማስገኘት ድርጅታዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን የማሟላት ተግባር ይሆናል ። በካፒታሊዝምም ቢሆን ሥራ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም ። በሁለተኛ ደረጃ ግን በካፒታሊዝም ውስጥ ሥራ ለቡርዧው ምዝበራ የሚውል የተትረፈረፈ ምርት ማስገኛ ተግባር ሲሆን የቁጥጥር ዓላማው ወዝ አደሩ ለቡርዧው የበለጠ ትርፍ የሚሰጥበትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መፍጠርን ያጠቃልላል ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ የቁጥጥርና የአስተዳደር መደባዊ ይዘትም ይኸው ነው ። የቡርዧውን ትርፍ ለማሳደግ ፤ የሠራተኛውን መደብ ይበልጥ መበዝበዝ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ አስተዳደር መሠረታዊ ዓላማ ነው። በካፒታሊዝም ማንኛውም አስተዳደርና

Digitized by Google

የቁጥጥር ሥራ የግል ንብረትንና ብዝበዛን ለማስጠበቅና የካፒታልን ዕድገት ለማስገኘት ሲባል የሚከናወን ተግባር ነው ። ስለ ዚህም ማርክስ እንዳለው የካፒታሊዝም የአ ስተዳደር ሥራ «ጥብቅና ቋሚ ቁጥጥር » ነው ።

ከላይ እንደተገለጠው ሥርዓተ ማኅበሮች ሁሉ ለየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ የቁጥጥርና የአስተዳደር ሥልት አላቸው ። በእያንዳንዱ ሥርዓት ውስጥ የቁጥጥር ዓላማ ሥርዓቱ የተሟላ ባህርዩን ጠብቆ እንዲቆይና የራሱ ሕጐች እንዲከበሩ መከላከልና ማንቀሳቀስ ነው ። ዳሩ ግን የእያንዳንዱ ሥርዓት ሕልውና የሚከበረው ቁጥጥር በመኖሩ ብቻ ሣይሆን ቁጥጥሩ ከአጠቃላዩ ዕድገት እንቅስቃሴ ጋር ተጣጥሞ ሲገኝ ብቻ ነው ። የሥርዓተ ማኅበር ሽግግሮችና የኤኮኖሚ አስተዳደር ቁጥጥር ባህርዮች ከምርት ቅንብሩ ጋር በጽኑ የተሳሰሩ ናቸው ። የማምረት ተግባር በአንድ የኤኮኖሚ አስተዳደርና ቁጥጥር ማስተናበር ሲስናከል የነበረው ሥርዓት ሕልውና ያከትምና የሌላ አዲስ ሥርዓት ሕልውና ይጀምራል። በዚህ ዓይነት አንዱ ሥርዓት ሌላውን እየተካ ኅብረተሰብ ዛሬ ከሚገኝበት ደረጃ ላይ ደርሷል ።

በሶሻሊዝም የሳይንሳዊ ቁጥጥር ሥርዓት መስፈን ሥርዓቱን ከሚገዛው ነባራዊ ሕግ ጋር መታዋወቅን ይጠይቃል ። ኅብረተሰቡ በኮሚኒስት ፓርቲው እየተመራ ትግሉን በየአቅጣጫው በማካሄድ የምርቱ ፣ የፖለቲካው ፣ የማኅበራዊ ኑሮውና የመንፈሳዊ ሕይወቱ ወሳኝ ይሆናል ። በዚህ ኅብረተሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ አስተዳደርና ቁጥጥር በሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ነው። በማንኛውም መስክ የሚከናወነው ተግባር የሥርዓቱን ዕድገትና ጥንካሬ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች ለይቶ ማወቅን ፣ መረዳትንና ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል ። በዚህ መሠረት ሳይንሳዊ አስተዳደርና ቁጥጥር ማለት የሥርዓቱን ተራማጅና አዳጊ ባህርዮች ለይቶ ማወቅና እነዚህን ባህርዮች በልዩ ልዩ የአስተዳደር መሣሪያዎች (በዕቅድ ፣ በቁጥጥርና በአመራር ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ማለት) ይሆናል ። ሳይንሳዊ አስተዳደርና ቁጥጥር በወቅቱ የዕድገት መንስኤ የሆኑትን ቅራኔዎች መረዳትንና መፍታትን ፣ ይህን በማድረግም እንቅፋቶችን በቅድሚያ ማስወገድን ይጠይቃል ። ከዚህም በላይ ሥርዓቱ በየደረጃው ያዋቀራቸውን ክፍሎች ማደራጀት፣ ይህን የማደራጀት ተግባር በየመስኩ ማፋፋምና መሰናከል የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በማስወገድ በሥርዓቱ ውስጥ የልዩ ልዩ ክፍሎችን የርስ በርስ መጣጣም መዋሀድና መተሳሰር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማዘጋጀትን ያጠቃልላል ።

የአንድን ሥርዓት የተለያዩ ክፍሎች መዋቅራዊና ተግባራዊ ግንኙነቶች ማጠናከርና ሥርዓቱን በተደላደለና በተጠናከረ መሠረት ላይ ለማቆም ፣ የማያስፈልገውን በማውጣት ፣ አሮጌውን ፣ ጊዜ ያለፈበትን በማስወገድ ፣ አዳዲስ መመርያዎች የማኅበራዊ እድገት ህግጋት ከሚጠይቁት ጋር ማዛመድና ማጣጣም ያስፈልጋል ። የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ይህን ለማድረግ የሚችል በመሆኑ ሣይንሣዊ የአስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ነው።

የጥምቀቱ አብዮትና የኤኮኖሚ አስተዳደር ፣

ከላይ የተጠቀሱት አጠቃላይ የሆኑ የኤኮኖሚ አስተዳደር ገጽታዎች ናቸው ። አብዮት አንድን ሥርዓተ ማኅበር አፍርሶ በምትኩ አዲስና ተራማጅ ሥርዓት ለመመሥረት የሚደረግ የለውጥ ሂደት ነው ።

የ1917ቱ የጥቅምቱ የሩስያ አብዮት የተረከበው ኤኮኖሚ የአነስተኛ ሸቀጥ ምርት

Digitized by Google

የተንሰራፋበት ኤኮኖሚ ነበር ። በወቅቱ የነበረው የከባድ ኢንዱስትሪ ዕድገት ከም ዕራብ አውሮፓ አገሮች ጋር ሲወዳደር በአ ጠቃላይ መልኩ ዝቅተኛ ነበር ለማለት ይቻ ላል ። የሥራ ምርታማነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበር ። የብሔራዊ የነፍስ ወከፍ ገቢና የሕዝቡ የኑሮ ደረጃም አነስተኛ ነበር። ከዚ ህም ሁሉ በላይ ደግሞ በወቅቱ ሀገሪቱ በኢ ምፔሪያሊዝም በተቀሰቀሰው የዓለም ጦር ነት ውስጥ ተካፋይ ስለነበረች ፥ ይህ ሁኔታ በዚች አገር ላይ ኤኮኖሚያዊ ድቀ ትንና ቴክኒካዊ ኋላቀርነትን ማስከተሉ አልቀረም ።

የሩስያ አብዮት የተነሳበትን ኤኮኖሚ ያዊ ሁኔታ እዚህ ላይ ያነሳነው የጥቅምቱ አብዮት የወረሰውን አስቸጋሪና ደካማ ኤኮ ኖሚ በዝርዝር ለማቅረብ ሳይሆን ፥ አጠቃ ላይ ሁኔታውን በማሳየት በሶቭዬት ኅብረት የኤኮኖሚ አስተዳደር ሁኔታዎች ከምን እን ደመነጩ ለመጠቆም ብቻ ነው ።

የሩስያ ሠራተኛ መደብ በኮሚኒስት ፓር ቲዊ አማካይነት ሥልጣን እንደያዘ በመጀ መሪያ የወሰደው እርምጃ ሕዝቡንና አገሪ ቱን ከጦርነት ማውጣትና ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ሲሆን ፥ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መን ገድ ደግሞ የሕዝቡን የምግብ ችግር ለማስ ወገድ መለስተኛ የኤኮኖሚ እርምጃዎችን በመውሰድ የፖለቲካ ሥልጣኑን ለማጠና ከር አቅዶ ነበር ። ይህን አላማ ለማሳካት አስቀድሞ ቁልፍ የሆኑትን የምርት ማከ ናወኛዎች ወረሰ ። ይህ እርምጃ የበ ለጠ የኤኮኖሚ ውድቀትን ለመግታትና አድኃሪ ኃይሎች የሚያደርሱትን ጥቃት ለመከላከል መንገድ ከፈተ ። እርምጃውን ተግባራዊ ለማድረግና የተፈለገውን ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል የተወረሱትን ኢንዱ ስትሪዎችና የምርት ተቋሞች የሚቆጣጠር የሠራተኞች የቁጥጥር ኮሚቴ ማቋቋም አስ ፈላጊ ነበርና ይህ ኮሚቴ በኅዳር 1917 ተቋቋመ ። የኮሚቴው ተግባር ፥ ዓላማና ኃላ ፊነት ፥ የተቋቋመበትም ሁኔታ በጊዜው በወጣው አዋጅ ውስጥ እንደሚከተለው ሠፍሯል ።

ብሔራዊ ኢኮኖሚው በዕቅድ እንዲመ ራ ለማድረግ የሠራተኞች የቁጥጥር ኮሚቴ በማምረቻ ፥ በግዥ ፥ በሽያጭና በመጋዘን እን ዲሁም በሌሎች ድርጅቶች በፊናንስ ተገባ ሮች እንዲሳተፉ በፋብሪካዎች ፥ በባንክ ፥ በአ ምራቾች የኅ.ሥ. ማኅበራትና በቀጥር ሥራ በሚገለገሉ ወይም በቤታቸው ቀጥረው የሚ ያሠሩ ድርጅቶች ውስጥ ተቋቁመዋል ።[1]

በተወረሱት የምርት ተቋሞች በአስተ ዳደር ክልልና በማምረቻ ተቋሞች ውስጥ የሠራተኛው የቁጥጥር ኰሚቴዎች ከላይ እስከ ታች ተቋቁመው ዝቅተኛውን የም ርት ጣሪያ በመወሰን የድርጅቱን ሂሣብ ፥ ልዩ ልዩ ግንኙነቶችና አስተዳደሩንም በመ ቆጣጠር በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበር ክተዋል ። የምርት እንቅስቃሴ እንዳይቋ ረጥ ታግለዋል ። አድኃሪዎች በኤኮኖሚው ላይ የሚጐነጉኑትን ሴራ በማክሸፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ። ዳሩ ግን የምርት ማከ ናወኛቸው የተወረሰባቸው ቡርዧዎችና የአ ብዮቱን ሂደት የፈሩ አጋሮቻቸው በሠራ ተኛው የቁጥጥር ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላ ፊነት ላይ በማመጽ በየደረጃው በአገሪቱ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ከማሴር አልተ ቆጠቡም ።

የአዋጁ ዓላማ «የኤኮኖሚ ቀውስንና የም ግብ እጥረትን ለመግታት እንዲሁም የሠራ ተኛውን መደብና የገጠሩን ድሀ ሕዝብ የበ ላይ ነቨነት ለማጠናከር »[2] ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት የሠራተኛው የቁጥጥር ኮሚቴዎች ይበልጥ ተጠናክረው የሠራተኛ ውን መደብ የኤኮኖሚና የፖለቲካ የበላይ ነት በማስጠበቅ ረገድ ዓይነተኛ ድርሻ አበርክተዋል ።

በሩስያ አብዮት ውስጥ የኤኮኖሚ አስ ተዳደር መልኮች በሶስት ወቅቶች የተከፈሉ ናቸው ። የመጀመሪያው የሠራተኛው ሕ

Digitized by Google

ዝብ በኮሚኒስት ፓርቲው አማካይነት ሥል
ጣን ሲይዝ የርስ በርስ ጦርነትና ከውጭ
የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር የሚደረ
ገው ግብግብ የሰፈነበት ወቅት ነበር ።
በዚህ ወቅት ሠራተኛው መደብና ፓርቲው
በማንኛውም መስክ በውስጥና በውጭ አድ
ኃሪ ኃይሎች ላይ ወታደራዊ የበላይነት ለመ
ጐናጸፍ የሚያስችለውን እርምጃ በመው
ሰድ ላይ ያተኰረ የጦር ኢኮኖሚ ቁጥጥር
ወቅት ነበር ። ሁለተኛውና ሶስተኛው ወቅ
ቶች ሠራተኛው ሕዝብ የኢኮኖሚና ፖለ
ቲካ የበላይነቱን ሙሉ ለሙሉ ያረጋገጠ
በትና የካፒታልን የበላይነት ለማሸነፍ ከወ
ታደራዊ ትግል ወደ ኢኮኖሚያዊ ትግል
ደረጃ በደረጃ ያመራባቸው ወቅቶች ናቸው።

የሩስያ ሠራተኛ መደብ መጀመሪያ የፖ
ለቲካ ሥልጣኑን ለማደላደል ይወስድ የነ
በረው አስተዳደራዊ እርምጃ ይበልጡኑ
በኃይል ላይ ያመዘነ ነበር ። ወደ ኋላ ግን
የሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን እየተደላደለ
በመሄዱ በካፒታሊስቱ መደብ ላይ በኢኮ
ኖሚ የበላይነትን ለመጐናጸፍ የተወሰደው
እርምጃ የኢኮኖሚና የአስተዳደር ስልቶችን
በማቋቋምና በማጠናከር ላይ የተመሠረተ
ነበር ። በዚህም መሠረት ለሶሻሊስት በመ
ሔዱ በካፒታሊስቱ መደብ ላይ የኤኮ
ኖሚ ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የአስተዳደ
ርና የቁጥጥር ሥልቶችን (ማኔጅመንት)
በመቀየስ ፥ ምርትንና የምርት ውጤት ክፍ
ፍልን እንዲሁም አጠቃላዩን የአገሪቱን
ሀብት ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት
ተዘረጋ ። በዚህ ሁኔታ የተቋቋመው የኤኮ
ኖሚ አስተዳደር ስልት የምርት ኃይሎችን
በአፋጣኝ በማሳደግ ለሶሻሊስት ኤኮኖሚ
ግንባታ መሠረት ለመጣል ያስቻለ ከመሆ
ኑም በላይ ፥ በወቅቱ ሶሻሊዝም በአንድ
አገር ሊገነባ አይችልም የሚለውን የአድ
ኃሪ አስተሳሰብ ፉርሽነት ያሳየ ነው ።

ሌኒን «ጠቅላላውን የመንግሥቱን የኤ
ኮኖሚ አሠራር ወደ አንድ ትልቅ ድርጅት
የመለወጥ ፥ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ
ሰዎች በአንድ ዕቅድ የሚመሩበት በኤኮ
ኖሚ ድርጅት መዘርጋት ከትከሻችን ላይ
የወደቀው የኤኮኖሚ ድርጅታዊ ችግር
ነው ፤» ሲል ኤኮኖሚውን በአዲስ መልክ
በማደራጀት ረገድ በወቅቱ በሠራተኛው
ትከሻ ላይ የወደቀውን ኃላፊነት ገልጾታል።
ይህ የሌኒን አባባል የሠራተኛው የቁጥጥር
ኮሚቴዎች የሚታገሉለትን ዓላማ በግልጽ
ያመለክታል ።

የሩስያ አብዮት ኤኮኖሚውን በአዲስ
መልክ በማደራጀት ረገድ በየደረጃው የወ
ሰዳቸው እርምጃዎች ሠራተኛውን ሕዝብ
ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለማውጣትና
ሶሻሊዝምን ለመገንባት ጥርጊያ ጐዳናን
ከፍተዋል ። ከዚህ አንፃር ሲገመገም የሩ
ስያ አብዮት ሳይንሳዊውን የቁጥጥር ተግ
ባር (የማኔጅመንት) ለመመሥረት የሚያ
ስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ምንነት ለመ
ጀመሪያ ጊዜ ያሳወቀ አብዮት ነው ለማለት
ይቻላል ።

የሶሻሊስት ኤኮኖሚ በዕቅድና በተመ
ጣጠነ የዕድገት ሕግ የሚመራ ከመሆኑም
በላይ ግብታዊ የካፒታሊዝም የኤኮኖሚ
አሠራርን የሚያስወግድ በመሆኑና አጠቃ
ላይ ኤኮኖሚው ለመንግሥት እቅድ እንዲ
ገዛ በማድረግ ለመቆጣጠር የሚያስችል
ሁኔታ ስለሚፈጠር ፥ በሶቭዬት ኅብረት ሳይ
ንሳዊ የቁጥጥር ዘዴ ሊዘረጋ ችሏል ።

ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረ
ገው ሽግግር በአንድ ገጽታው ማርክስና
ኤንግልስ እንዳሉት «. . . በፍላጐትና
በአቅርቦት (Demand & Supply) ጭፍን
ሕጐች በሚገዛው የመካከለኛው መደብ ፖለ
ቲካዊ ኤኮኖሚና በማኅበራዊ ምርት አማ
ካይነት በማኅበራዊ አመለካከት በተገራው
የሠራተኛው መደብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ
መካከል የሚደረግ ትግል ነው ። »[4]

በሶቭዬት ኅብረት የሶሺያሊስት ኅብረ
ተሰብ ግንባታ ይበልጥ እየተጠናከረና ስፋት
እያገኘ በሄደ ቁጥር የመንግሥት የቁጥጥር

Digitized by Google

አካሎች በየደረጃው ተፈጥረዋል ። ሕዝ
ባዊ የቁጥጥር አካሎችም ቢሆኑ በጊዜው
የተገኘውን ዕድገትና ማኅበራዊ ግንኙነት
ለማስተባበር እንዲችሉ ሆነው በአዲስና
በተጠናከረ መልክ ተቋቁመዋል ። በዚህም
መሠረት እ.ኤ.አ. በ1966 መጨረሻ ላይ
ቀደም ብሎ የነበሩት የሕዝባዊ የቁጥጥር
አካሎች በአዲስ መልክ ሲደራጁ ፣ የፓርቲ
ውና የመንግሥቱ የቁጥጥር አካሎች የአ
ብዛኛው ሕዝብ ተሳትፎ እንዲንፀባረቅባ
ቸው ወደ ሕዝብ የቁጥጥር አካልነት ተለ
ውጠዋል ። በዚህም አማካይነት ከከፍተ
ኛው የሶቭዬት ኅብረት የሕዝብ የቁጥጥር
ኮሚቴ ጀምሮ እስከ ቀበሌና የማምረቻ ድር
ጅቶች ድረስ እንደገና በመዋቀር የሕዝብ
ሙሉ ተሳትፎ የሚገለጽባቸው የቁጥጥር
ተቋሞቹ ተዘርግተዋል ። በዚያውም ልክ ኃላ
ፊነታቸውና ተግባራቸው ሰፍቷል ። የሶቭ
ዬት መንግሥት ሕግ በተሰኘው መጽሐፍ
ውስጥ እንደተገለጸው ፣

ፓርቲውና መንግሥት ያወጧቸው መመ
ሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ፣ የሶሻሊስ
ቱን ኢኮኖሚ ዕድገት በማፋጠን የኮሚኒ
ስት ግንባታ የበለጠ እንዲሰምር የሥራ ዲስ
ፕሊንና የሶሻሊስት ሕጋዊነት መከበራቸ
ውን መቆጣጠር ዋነኛው የቁጥጥር ኮሚቴ
ዎች ተግባር ነው ። ሕዝባዊ የቁጥጥር ኮሚ
ቴዎች በሶቭዬት ኅብረተሰብ ውስጥ ማናቸ
ውም አዲስና ተራማጅ ነገር እንዲዳብር በከ
ፍተኛ ደረጃ ያበረታታሉ ፣ ይደግፋሉ ። የተ
ሳሳተውን ነገር የማጋለጥ ፣ አጠቃላዩን ሁኔታ
የማሻሻል ፣ በቢሮክራሲያዊ አሠራር ፣ በማ
ጭበርበር ፣ በተዛባ ማኔጅመንትና አሠራር
ላይ የማያቋርጥ ትግል ማድረግ ተግባራቸው
ነው ። [5]

የኤኮኖሚ አስተዳደር የተለያዩ መልኮች

በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል
ያለው ትግል በተዛባና ግብታዊ በሆነ የዕ
ድገት ጕዳናና በዕቅድ ላይ በተመሠረተ
የማኅበራዊ ዕድገት ጕዳና መካከል የሚካ
ሄድ ትግል ነው ።

በዚህ ትግል ውስጥ የሶሻሊስት ማኔጅ
መንት ተግባር በዕቅድ የሚመራንና የተ
መጣጠነን የኅብረተሰብ ዕድገት ማስገኘት ፣
የኤኮኖሚውን እንቅስቃሴ በሥርዓት መም
ራትና ማስተዳደር ይሆናል ። የሶሻሊስት
ማኔጅመንት ተግባር ሶስት ገጽታዎች
አሉት ። እነሱም ቴክኒካዊ ፣ ሶሲዮ ኤኮ
ኖሚያዊና ሶሲዮ ፖለቲካዊ በመባል ይታ
ወቃሉ ።

ቴክኒካዊ ማኔጅመንት የምርት ኃይሎ
ችን ዕድገት የሚመለከት ነው ። ቴክኒካዊ
ማኔጅመንት በመሠረቱ በሰውና በተፈጥሮ
መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት
ቢሆንም በዚህ ብቻ አይወሰንም ፤ ማኅበ
ራዊ ጕኖችም አሉት ።

ሶሲዮ ኤኮኖሚ ማኔጅመንት የንብረት
ባለቤትነት ግንኙነትን ያመለክታል። የሶ
ሻሊስት ኅብረተሰብ መሠረት ማኅበራዊ
የንብረት ባለቤትነት ነውና በሶሲዮ ኤኮ
ኖሚያዊ ማኔጅመንት አማካይነት የሶሺያ
ሊስቱን ኤኮኖሚ መዋቅር በመዘርጋት ለሶ
ሻሊስት ኤኮኖሚ ግንኙነት መጠናከር ዋስ
ትናን የሚሰጥ ነው ።

ዛሬ አብዮታችን የሰባት ዓመታት ዕድሜ
ያለው ሲሆን በነዚህ ዓመታት ውስጥ በፖ
ለቲካ ፣ በኤኮኖሚ ፣ በባህልና በርዕዮተ
ዓለም መስኮች ውስጥ ሥር ነቀል ርምጃ
ዎች ተወስደዋል ። የቀድሞውን የተዛባና
ያልተስተካከለ የሀብት ሥርጭት ባህሪ ቀስ
በቀስና በየደረጃው በማስወገድ በምትኩ
ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የሥራውና የድካሙ
ውጤት ባለቤት መሆኑ የሚረጋገጥበት
አመች ሁኔታ ተፈጥሯል ።

የሰፊውን ሕዝብ ማኅበራዊም ሆነ ሌሎች
ጊዜያዊ ኤኮኖሚያዊ ችግሮችን ለማስ
ወገድ አስቀድሞ የፊውዳሉን የምርት ግን
ኙነት ማስወገድና በአዲስና ተራማጅ የም

Digitized by Google

ርት ግንኙነት መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፣ አብዮታዊው መንግሥት የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶችን፣ የባንክና የገንዘብ ተቋሞችን ወደ መንግሥትና ሕዝብ ንብረትነት በመለወጥና መሬትን ለአርሶ አደሩ በማድረግ ለአዲስ ሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ መሠረት ጥሏል። አንድ አድኃሪ የምርት ግንኙነትን መስበርና አዲስ ግንኙነት መመሥረት በራሱ የዳበረ ሶሻሊስታዊ ኤኮኖሚን መገንባት ማለት አይደለም። ስለሆነም ሥርዓቱን ደረጃ በደረጃ ወደ ተደራጀና የዳበረ ሶሻሊስታዊ የአመራረት ሥልት እንዲሸጋገር ማድረግ አስፈላጊነው። ለዚህም የገበሬዎችንና የዕደ ጥበብ ባለሙያተኞችን የአመራረት ሥልት ለማዳበር የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማደራጀት በማስፈለጉ በገጠር የሶሽያሊስት የምርት ግንኙነትን የማደራጀቱ ተግባር ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ በመጧጧፍ ላይ ይገኛል።

ሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ማኔጅመንት ከምርት ግንኙነት ጋር የተዛመደ በመሆኑ አዲሱ የሶሻሊስት ኤኮኖሚ የሚዋቀርበትን ስልት ይፈጥራል። የተለያዩ የኤኮኖሚ ድርጅቶችን የሥራ ቅልጥፍና ያሳድጋል። በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የተፋጠነ የኤኮኖሚ ዕድገት እንዲኖርና ቴክኖሎጂ እንዲዳብር የሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ማኔጅመንትን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። የሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ማኔጅመንት፣ የተሻሉ የአስተዳደር ስልቶችን ለመቀየስ፣ የሠራተኛውን ችሎታ ከፍ ለማድረግ፣ የሠራተኛውን የወል ወይም የጋራ ኃላፊነቶች ለማስከበርና ለማስጠበቅ ያስችላል።

የሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ማኔጅመንትና የሶሲዮ ፖለቲካዊ ማኔጅመንት የተያያዙና ተነጣጥለው የማይታዩ ናቸው። በኤኮኖሚውና በፖለቲካው መካከል ያለው ግንኙነት በሁለቱ ግንኙነት አማካይነት ይገለጣል። ሶሲዮ ኤኮኖሚያዊ ማኔጅመንት ደግሞ የሠራተኛውን ፖለቲካዊ ድርጅት ከመመሥረት፣ ከማንቀሳቀስና ከማሳደግ ጋር የተያያዘ ነው።[6] የሶሲዮ ፖለቲካዊ ማኔጅመንት መገኛ ምንጮችና የፖለቲካዊ ግንኙነቶች ባህሪዎች የመደቦችና የሕዝቦች ግንኙነቶች ናቸው። ሌኒን እንዳለው ፖለቲካ በመደቦችና በማኅበራዊ ቡድኖች መካከል ያለ ግንኙነት እንደመሆኑ ሶሲዮ ፖለቲካዊ ማኔጅመንት «የመንግሥት ሥልጣን መዋቅርን»[7] የሚገልጥ ነው።

የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ በብቸኛው የፖለቲካ ድርጅቱ በኢሠፓአኮ እየተመራ ቀደም ብሎ በትግሉ የመሠረታቸውን ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች ይበልጥ እያጠናከረ፣ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ የኤኮኖሚ ግንባታን ይበልጥ እያስፋፋና የብሔራዊ ሀብት አስተዳደር መሠረቶችን እየዘረጋ ነው። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት የቀድሞውን ሥርዓት ግብታዊ የኤኮኖሚ ሁኔታዎች የማግታትና የማስወገድ ብሎም በምትካቸው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የግንባታ ሕግ ላይ የተመሠረቱ የኤኮኖሚና የአስተዳደር መዋቅሮች በማዋቀር ላይ ይገኛል።

በየደረጃው የግል ሀብትንና እሱም የሚያስከትለውን ጠንቆች መዋጋት ማለት አዲሱ የማኅበራዊ የምርት አደረጃጀት እንዲከሰት ማድረግና በጋራ ብልጽግና ላይ የተመሠረተ ኤኮኖሚያዊ ዕድገትን ማረጋገጥ ማለት ነው። ይህ አዲሱን የምርት ግንኙነት የመፍጠርና ሶሻሊስታዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ተግባር ከወል የንብረት ባለቤትነት ጋር የሚጣጣመውን የኤኮኖሚ አስተዳደር የመፍጠር ተግባር እንደመሆኑ፣ በሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ ሂደት ውስጥ ወሳኙንና ዓይነተኛውን ሚና ይጫወታል።

የወቅቱን ትግል የተለየ የሚያደርገው የኢትዮጵያ አብዮት ሂደቱን የሚያደናቅፉትን ኋላቀርና አድኃሪ የኤኮኖሚና የአስተዳደር ባህርዮችን ለመታገል ሰፊው ሕዝብ

Digitized by Google

ከምንጊዜውም ይልቅ ቀርጦ መነሳቱ ነው።
እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው የአብዮ
ቱን ሂደት በመፃረር የቆሙት አድኃሪ የአ
ስተዳደርና የኤኮኖሚ አሰራሮች ከአብዮቱ
ወዲህ የተፈጠሩ አለመሆናቸውና በአንፃ
ሩም የኢትዮጵያ አብዮት ከነዚህ አሠራሮች
ለመላቀቅ የሚያደርገው ትግልም በአንድ
ገጽታው ከቀየ አመለካከት ጋር የሚካሄድ
ትግል መሆኑን ነው ።

የሠርቶ አደሩን የቁጥጥር ኮሚቴ ለማ
ቋቋም በወጣው አዋጅ ላይ በትክክሉ እን
ደተጠቀሰው ፣ «በሶሻሊዝም የቁጥጥር አስ
ፈላጊነት የሚመነጨው የፀረ አብዮተኛ
ችንና የአዲሱን ሥርዓት ጉጂ ባህሎች በመ
ዋጋት የሶሻሊዝምን ግንባታ በአስተማማኝ
ወደፊት ከማራመድ አንፃር ነው ። በሶሻ
ሊስት ሥርዓት ቁጥጥር ሕዝባዊ ሥርዓት
ያለው ሲሆን የሠርቶ አደሩን ፓርቲ የግን
ባታ ዕቅዶችና መመሪያዎች በሰፊው ሕዝብ
ንቁ ተሳትፎ ላይ በመመርኮዝ በትክክል
ተግባራዊ ማድረግና ማረጋገጥ ይሆናል።»

የቁጥጥር ኮሚቴ ተግባር በአራት ዓላማ
ዎች ሊከፈል ይችላል ። እነሱም ፣

1. የምርት መገልገያዎችን የሕዝብ
ሀብት በማድረግ የተወሰዱት እር
ምጃዎች ይበልጥ ፍሬያማ እን
ዲሆኑ ማድረግ ፣

2. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣
ለንብረት ደንታ ቢስ መሆን ፣ ጥን
ቃቄ አለማድረግን ፣ የኅብረተሰብን
ጥቅም በግል ጥቅም መለወጥ፣ ግጭ
በርበርን ፣ ጉቦን ዋልጌነትንና የመ
ሳሰሉትን ሕገ ወጥ ድርጊቶችን
ጨርሶ ማጥፋት ፣

3. የአሠራር ዝርክርክነትን ማስወ
ገድ ፣

4. ሠርቶ አደሩ ራሱን የመቆጣጠር
ባህል እየገነባ በብሔራዊ ሀብት
አጠባበቅና አስተዳደር ተግባሮች
ሙሉ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ፣
ናቸው ።

እነዚህ ዓላማዎች ከብሔራዊ የኤኮኖሚ
ፕላን አወጣጥ ፦ አፈፃፀምና ውጤቱን እስከ
መገምገም ድረስ ያሉትን በርካታ ትግሎች
ሁሉ ያጠቃልላሉ ። በአዋጁ የተለያዩ አን
ቀጾች የተዘረዘሩት ተግባሮች ፣ የአሠራር
ዘዴዎችም የሚያመለክቱት ይህንኑ ነው።
ለአብነት በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ ቁጥሮች
3 ፣ 7 ፣ 12ና 14 የሠፈሩትን ሃሳቦች መጥቀስ
ይበቃል ። በነዚህ ቁጥሮች ሥር የተዘረዘ
ሩት የቁጥጥር ኮሚቴው የወል ተግባሮች
ኮሚቴዎቹ የመንግሥትን መመሪያዎችና
አዋጆችን በማስፈፀም ፣ ዕቅዶችን በሥራ
በመተርጎም ፦ ንብረትን የመቆጣጠርና
ቀልጣፋ አስተዳደር እንዲሰፍን የማድረግን
ትግልን የሚያመለክቱ ናቸው።የተዘረዘሩት
ዓላማዎችና ተግባሮች የሶሻሊስት ቁጥጥር
ንና አስተዳደርን (Control and Manage-
ment) ምንነት በትክክል የሚያመለክቱ
ናቸው ።

መመሪያዎችና አዋጆችን በትክክል ለማ
ስፈጸም የሚወጡትን ዕቅዶች ተግባራዊ
ለማድረግ ፣ ንብረትን በሚገባ ለመቆጣጠ
ርና ቀልጣፋ አስተዳደርን ለማስፈን አስ
ቀድሞ ትክክለኛውን የቁጥጥር ሥርዓት
መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ ነው ። የብሔ
ራዊ ሀብት አስተዳደር ቁጥጥር ተግባራዊ
የሚሆንባቸው ስልቶችና ዘዴዎች የተለ
ያዩ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ሥልቶ
ችና ዘዴዎች እርስ በርስ የተያያዙና አንዱ
ኛውን ከሌላው ነጥለው ለማየት የሚያዳ
ግቱ ናቸው ። የሂሣብ አያያዝ ቁጥጥር
(Auditing) የአፈጻጸም ክትትል (Inspec-
tion) አስተዳደር (Administration) ቁጥ
ጥር ተግባራዊ የሚሆንባቸው መሣሪያዎ
ችና ሥልቶች ሲሆኑ ፣ የአጠቃላዩ የቁጥ

Digitized by Google

ጥር ሥርዓት ተፈፃሚነት በነዚህ ሥልቶች ተግባራዊነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል ።

አንድ በትክክል የተዘረጋ የቁጥጥር ስር ዓት የማንኛውም ድርጅት የገንዘብ እንቅ ስቃሴ በማስረጃ መደገፉንና በሰነድ መሥ ፈሩን ፣ ይህ እንቅስቃሴ ሕግንና ፖሊሲን የተከተለና ከዚያ ውጭ ያልሆነ መሆኑን ይከታተላል ። ይሁን እንጂ የገንዘብ እንቅ ስቃሴ ሕግና ፖሊሲ ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ዓላማ ፣ ከሕዝቡ ፍላጐትና ጥቅም ጋር የተ ገናዘበ ካልሆነ የሰነድ ምስክር ብቻ ተገቢ ውን የገንዘብ እንቅስቃሴ አመልክቷል ማለት አይቻልም ። ስለዚህ ቁጥጥሩ የገን ዘብ እንቅስቃሴ በሠነድ መደገፉን ብቻ ሳይሆን እንቅስቃሴው መንግሥት ያወጣ ውን ሕግና ፖሊሲ የተከተለ መሆኑንም ጨምሮ ማሳየት አለበት ። የሂሣብ አያያዝ ቁጥጥር ተግባርም እነዚሁኑ የሚያከናውን መሆን ይኖርበታል ። አስተዳደርና የክት ትል ተግባሮችም ይህን የገንዘብ እንቅስ ቃሴና የኦዲቲንግ ተግባር የሚያገለግሉ መሆን ይኖርባቸዋል ።

ዛሬ ገኖና ተባብሶ ለሚገኘው የዘረፋና የምዝበራ ተግባር ምክንያት ከሆኑት አንዱ በመሥሪያ ቤቶችና በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር በትክክል በሥራ ላይ ያለመዋሉ ነው ።

በየጊዜው የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድር ጅቶች ንብረትና ገንዘብ ባከኖ ወይም ተዘ ርፎ አጥፊው ሲደረስበትና የምርመራው ውጤት ሲገለጥ የሚታየው ከላይ የተጠቀ ሰው ሥርዓት በአግባቡ ተግባራዊ አለመ ሆኑ ነው ። በሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የሂሳብ ሰነዶችን የሚመዘግበውና ገንዘብ የሚይ ዘው ግለሰብ፣ክፍያን የሚፈቅደውና ከፋዩ፣- ንብረት ገዥና ተረካቢው የተለያዩ ሰዎች መሆን አለባቸው ። ይህንን የመሳሰሉ ተግ ባሮች በሚያከናውኑ ሰዎች መካከል የሥራ ክፍፍሉ የተጠበቀ ሲሆን ሥርዓቱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ይሆናል ። «የአብዮታ ችን አዲሱ የትኩረት መስክ» በተሰኘው አርዕስት በ «ሠርቶ አደር» ላይ እንደሠፈ ረው ፣ «አንድ ግለሰብ አስተዳዳሪና የሂሣብ ሹም ከሆነ ፣ ግምጃ ቤትና የሂሣብ ሹም ከሆነ ፣ ገንዘብ ያዥና የሂሣብ ሹም ከሆነ፣ የግዢጋጃ ቤት ሹምና ገንዘብ ያዥ ከሆነ ፣ የገቢ ተቀባይና የሒሳብ ሹም ከሆነ... ሥር ዓት ያለው የመቆጣጠሪያ ዘዴ በሥራ ላይ ሊውል አይችልም ። » [8]

በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የሶ ሻሊስታዊ ማኔጅመንት መሠረቱ ማኅበ ራዊ የንብረት ባለቤትነት ነው ። በመሆ ኑም ዛሬ በብኩንነት ፣ በምዝበራ ፣ ወዘተ... መልክ የተከሰቱትን ችግሮች ለመቋቋምና ለማስወገድ ዓይነተኛውና ብቸኛው መሣ ሪያ የሕዝብ ንብረት በሆኑ የኤኮኖሚ ተቋ ሞች መካከል የጋራ አሠራርና ግንኙነት መመሥረት ወይም መፍጠር ነው ። ለም ሳሌ ጥሬ ዕቃን በሚያመርቱና እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች ወደ ፍጆታ ዕቃነት በሚለወጡ መካከል ፣ በሚያመርቱና በሚያከፋፍሉ መካከል ፣ በሚገዙና በሚሸጡ የመንግሥት ድርጅቶች መካከል ወዘተ ... ውል ያለው የግንኙነት ፖሊሲን መፍጠር በዚህ ረገድ የሚፈጠረውን ችግር ሊቀንስ ይችላል ።

አብዮታችን ዛሬ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የሕዝ ባዊ ቁጥጥር ስርዓትን መቀየስና የአገሪቱን ሀብት በዕቅድና በፕሮግራም አቀናጅቶ ግን ባታውን ማራመድ ነው ። የሕዝባዊ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና የቁጥጥሩን ተግባራ ዊነት ማረጋገጥ ጠቃሚነቱ የግንባታ ተግ ባርን በዕቅድና በፕሮግራም ለመምራት ብቻ ሳይሆን ፣ የሕዝብ ሀብት የሆኑት የምርት መገልገያዎች የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆኑና ሰፊውን ሕዝብ በተሻለ ሁኔታ እንዲያገለግሉ ለማድረግም ጭምር ነው ።

Digitized by Google

የምርት ኃይሎችን ለማሳደግና የምርት አደረጃጀትን ቀልጣፋ ለማድረግ በሚደረገው ትግል ውስጥ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው ።

እንደሚታወቀው ሁሉ ዛሬ የኢኮኖሚ ግንባታችንን በሚመለከት እያንዳንዱ የኤኮኖሚ ክፍል በተወሰነ የጊዜ ገደብ ሊያከናውነው የሚገባው የሥራ ድርሻ አለው ። በነዚህ የኢኮኖሚ ክፍሎች የሚቋቋሙት የቁጥጥር ኮሚቴዎች የመጀመሪያ ተግባር በዕቅድ የሠፈረው የሥራ ድርሻ በታቀደው መልክና ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ ነው ። ኮሚቴዎቹ አንድ የተሰጠ የሥራ ድርሻ በሚከናወንበት ወቅት የሚያስፈልገው የማቴሪያልና የገንዘብ ወጪ ፣ የሥራው ጥራት ፣ ሥራው የሚከናወንበት የጊዜ ገደብ ወዘተ . . . ዕቅዱን ተከትሎ መከናወኑን ይቆጣጠራሉ ። የቁጥጥር ኮሚቴዎች ሥራን ለማቀላጠፍ የሚቻልበትን ዘዴ በማስተዋወቁም ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ።

አንድን ሥራ ለማከናወን የተመደበውን የሰው ኃይል ፣ የአሠራር ሥልት ፣ የተግባሮች የሠመረ ግንኙነት ፣ የጥሬ ዕቃዎች አጠቃቀም ወዘተ . . . የቁጥጥሩ ኮሚቴዎች የሚያተኩሩባቸው የሥራ መስኮች ናቸው ። በመሆኑም ሠርቶ አደሩን በሙያና በቴክኒክ ማሠልጠን ፣ እንደዚሁም ያለውን የመፍጠር ችሎታ ማዳበር ዕቅዶችን ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ።

በአጠቃላይ የቁጥጥር ወይም የብሔራዊ ሀብት አስተዳደር መሠረተ ሀሳብ ዕቅድ ከማውጣት ጀምሮ በየደረጃው ያለውን የአፈፃፀም ሁኔታ የሚያጠቃልል በመሆኑ ፣ ሰፊ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ከባድ ሥራ ነው ።

የትግላችን አቅጣጫ

እስከ አሁን ድረስ የተደረጉት ጥናቶችና ማስረጃዎች እንደሚያስረዱት የብኩንነትና የምዝበራ ምንጮች (መነሻ ምክንያቶች) ከሁለት አቅጣጫ ሊገመገሙ ይችላሉ ። እነኝህም በመጀመሪያ በኤኮኖሚው ዘርፍ በአስተዳደር ረገድ የተስተካከለ አሠራር አለመኖር ወይም ያለው አሠራር አለመጠናከር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የግል ንብረት ባህርዮች ግፊት መኖር ነው ።

በመጀመሪያ ደረጃ የተጠቀሰው ችግር የሚነሳው በሂሣብ አያያዝና ምርመራ እንዲሁም በአስተዳደር ትክክለኛ አሠራር ካለመቀየሱ ነው ። በዚህም የተዝረከረከና ያልተስተካከለ አሠራር የተነሳ የሕዝብና የመንግሥት ገንዘብና ሀብት ለዘራፊዎች የተጋለጠ ይሆናል ። በሀገራችንም ቢሆን በየመሥሪያ ቤቱና ድርጅቱ ትክክለኛ የሂሣብ አሠራርና ቁጥጥር አለመዘርጋቱ ፣ እንዲሁም ለግለሰቦች ተደራራቢ ኃላፊነት መስጠቱ የቁጥጥር ተግባር እንዲላላና የብሔራዊ ሀብታችን ለምዝበራ እንዲጋለጥ ተደርጓል ። የሀገርን ሀብት በትክክል ለመቆጣጠርና በተገቢው ሥራ ላይ ለመዋል ትክክለኛ የሂሣብ አያያዝና የቁጥጥር ስርዓትን መዘርጋትና የሥራ ክፍፍሉም የተግባሮች የርስ በርስ ቁጥጥር የሚንፀባርቅበት እንዲሆን ማድረግ እጅግ ወሳኝ ነው ።

የግል ሀብት የሰፈነበትን ሥርዓት ሽረው ወደ ሶሻሊዝም ጉዳና የሚያመሩ ሕዝቦች (ከዳበረ ካፒታሊስት አገር በቀር) አዲስ ኢኮኖሚ በመገንባትና በማስተዳደር ረገድ ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥማቸው እሙን ነው ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ካለፈው ሥርዓት ይህን የመሰለ ተግባር ለማከናወን የሚያስችል እውቀትና ልምድ ያልወረሰ በመሆኑ ፣ የግል ሀብት ሥርዓትን ሽሮ ወደ ሶሻሊዝም በሚያደርገው ትግል ውስጥ አዲስ ኢኮኖሚን በመገንባትና በማስተዳደር ረገድ ከፍተኛ ችግር ይገጥመዋል ። ፊውዳሊዝም

Digitized by Google

እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ የተነካ የተደራጀና የተቀላጠፈ የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር ሥልት አልጣለም ።

ያለፈው ሥርዓት ኋላ ቀር አስተሳሰቦች ከሠራተኛው ሕዝብ መካከል ገና ባለመጥፋታቸው ሁኔታውን ያባብሱታል ። ይህ በመሆኑም የችግሩን ቀዳዳ በአስተማማኝ በመድፈን ቀልጣፋ የኢኮኖሚያዊ አስተዳደርና አመራርን ለመመሥረት አስቀድሞ የአሮጌውን ሥርዓት ኋላቀር ልማዶች መዋጋት ያስፈልጋል ። ማኅበራዊ የሆኑትን የምርት መገልገያዎች (የሕዝብም ሆኑ የኅብረት ሥራ ማኅበራት) ለመምራትና ለማስተዳደር አዲስ ሥልት መቀየስ ይኖርበታል። ሕዝቡ በዕውቀት እየዳበረና እየሰለጠነ በአስተዳደርና በምርት ተግባሮች እንዲሳተፍ መደረግ አለበት ። ከአድኃሪና ኋላቀር ባህሎች የሚያላቅቀውንና ለጋራ ብልጽግናና ለዕድገት በሚያደርገው ትግል ውስጥ በመሪያነት የሚያገለግለውን የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ለሰፊው ሕዝብ ማስታጠቅ በዚህ ረገድ ወሳኝነት ያለው ነው ።

ሶሻሊስታዊ የንብረት ግንኙነት እየተመሠረተ ሲሄድ ከዚሁ ጋር አብሮ ማንኛውም ዓይነት ሥልጣን ሕዝባዊ (ማኅበራዊ) እየሆነ ይሄዳል ። ይህ ሁኔታ ወዲያውኑ ሊሰምር ስለማይችል በየደረጃው ማኅበራዊ ክትትልና ቁጥጥር መስፈንና መጠናከር ይኖርበታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በቁጥጥር ተግባር ውስጥ ተሳትፎውን በየጊዜው እንዲያጠናክር ፣ የትምህርትና የንቃት አድማሱን በየጊዜው ማስፋት ያስፈልጋል ። የውይይት ክበቦች የሙያና ሕዝባዊ ድርጅቶች ይህንን በማድረግ ረገድ የሚጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው ። ሌኒን በሕዝባዊ ቁጥጥር ተግባር ውስጥ የሕዝቡን ሚና በሚከተለው አነጋገር በትክክል አስቀምጦታል ።

በተለያዩ ተግባሮች የተሠማሩ የቴክኖሎጂ እውቀትና ልምድ ካላቸው አዋቂዎች ትብብር ካልተገኘ በስተቀር ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር አይቻልም ። ምክንያቱም ሶሻሊዝም ከካፒታሊዝም ይልቅ ከፍተኛ ምርታማነትን ለማስገኘት የሰፊውን ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው ። ሶሻሊዝም እዚህ ደረጃ ላይ እንዲገኝ በራሱ መንገድ ፣ በራሱ ዘዴ ወይም ነገሩን በግልጽ ለማስቀመጥ በሶቭዬት (ሕዝባዊ) ዘዴዎች መመራት አለበት ። [9]

በመሆኑም የሶሻሊስት ኤኮኖሚ ለመገንባት አስፈላጊ የሆነው የቁጥጥርና የአስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊነት በደንብ እንዲረጋገጥና በዚህ ረገድ የሚደረገው ትግል አጥጋቢ ውጤትን እንዲያስገኝ ሰፊውን ሕዝብ በቁጥጥሩ ተግባር በስፋት ማሳተፍ ወሳኝ ነው ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. First Decree of Soviet Power, Compiled by Yuri Akhapkin, p. 36.
2. Ibid., p. 147.
3. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 27, p. 91.
4. K. Marx & F. Engels, Selected Works, Vol. 2, p. 16.
5. Soviet State and Law, Prog. Pub., p. 157.
6. K. Varlamov, *Socialist Management, The Leninist Concept*, Prog. Pub., pp. 155-157.

   157.
7. *Ibid.*,
8. «ሠርቶ አደር» ቅጽ 2 ፣ ቁጥር 12
9. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 27, p. 25.

Digitized by Google

ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል

ከ18ኛው ምዕተ ዓመት እስከ 1950ዎቹ

ክፍል አንድ

ኢሳይያስ ደምሴ

የአውሮፓ መንግሥታት የምሥራቁ ግዛቶችን ለመያዝ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበትን ዘዴ አውቀዋለሁ። በመጀመሪያ ሚሲዮናውያንን ይልካሉ፤ ቀጥለውም ሚሲዮናውያኑን እንዲያግዙ በማለት ቆንስላዎችን ይልካሉ፤ ከዚያም ቆንሲላዎችን እንዲረዱ በማለት ወታደሮች ይልካሉ። እኔ በዚህ ዓይነት መንገድ የምታለል የሒንዱስታን ራጃህ አይደለሁም፤ ይህንን ከማደርግ ይልቅ በቀጥታ ከጦሩ ጋር ግንባር ለግንባር መግጠሙን እመርጣለሁ።[1]

—አጼ ቴዎድሮስ

በኢትዮጵያ የኢምፔሪያሊዝም መከሰት

ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ጋር ትንቅንቅ የጀመረችው ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ መሆኑን ወደኋላ መለስ ብለን ስንመረምር ከራሷ የትግል ታሪክ ብቻ ሳይሆን ሽንፈትና ውርደት እየተከናነቡ ከሄዱት ተስፋፊ ሀገሮች ታሪክ ጭምር መሆኑን እንረዳለን።

ኢትዮጵያ ፣ በመልክአ ምድር አቀማመጧ እስትራቴጂያዊነት፣ በተፈጥሮ ሀብት ብልጽግናዋና ልምላሜዋ ምክንያት ኢምፔሪያሊዝም በተለይም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ብሔራዊ አንድነቷን ለማናጋትና ነፃነቷን ለመገፈፍ ብሎም በመዳፉ ውስጥ አስገብቶ የተፈጥሮ ሀብቷን ለመበዝበዝ ተደጋጋሚ ወረራ ሲሰነዝርባት ቆይቷል። ይህን ቅዠቱን እውን ለማድረግ በአንድ ወቅት የገዥ መደብ አውራ የነበሩትን መሣፍንት በጉማ፣ በቋንቋና በቦታ እየለያየ የእርስ በርስ ግጭትና እልቂት እንዲፈጥሩ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። አንዱ ኢምፔሪያሊስት የጦር መሣሪያ ለአንዱ መስፍን

Digitized by Google

እየሰጠ ሲያጠናክር ፣ ሌላውን መስፍን ገሸሽ በማድረግ ሲያዳክም ፣ አንዱ ኢምፔሪያሊስት አገር ከአንዱ መስፍን ጋር የንግድና የወዳጅነት ስምምነት ሲዋዋል ፣ ሌላው ኢምፔሪያሊስት አገር ደግሞ ሌላውን መስፍን በጦር መሣሪያ እርዳታ እየሸነገለ በምትኩ ወሮታ ለማግኘት ይደራደር ነበር።

በሌላም በኩል ኢምፔሪያሊዝም ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሙን ለማስከበር መረማመጃ አድርጎ ሊጠቀምበት የሞከረው የኢትዮጵያን ሕዝብ ባሕላዊ ፣ ስነልቡናዊና መንፈሳዊ አመለካከቱንና አስተሳሰቡን ፣ «የብዝበዛው ሐዋርያት» በሆኑት ሚሲዮናውያን ፣ አገር ጐብኝዎችና ቆንስላዎች አማካኝነት ወደ ራሱ ባሕልና ሥነ ልቦና ፣ መንፈሳዊ አስተሳሰብና አመለካከት ለመለወጥ ጥረት በማድረግ ነበር። ምንም እንኳን ይህ ዓይነት አቀራረቡ የተጣካ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ውጤት ባይሰጠውም ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ የባሕልና የዕምነት ቅርሶች በመዝረፍና ሰብአዊ መብቱንም በመገፈፍ ኢሰብአዊ ድርጊት ፈጽሟል ።

በ16ኛው ምዕተ ዓመት በተስፋፊነት የታወቁት የኦቶማን ቱርኮች በቀይ ባሕር ጠረፍ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ግዛት በተደጋጋሚ ለመውረር ሞክረዋል ፤ ወረዋልም ። በመጀመሪያ ምጽዋንና ሐረርጌን ከዚያም ደባርዋን ይዘው የተጠናከረ ምሽግ ሠርተው ወደ መሐል አገር ዘልቆ ለመግባት እየተዘጋጁ ሳለ የኢትዮጵያ ጦር አዲዳዕሮ ላይ በ1578 ገጥሞ አይቀጡ ቅጣት በመቀጣት እንዲባረሩ አድርጓቸዋል ። ይሁን እንጂ የቱርክ ጦር ኃይሉን አጠናክሮ ምጽዋንና ሐርጌጐን እንደገና በመውረሩ ፣ አሁንም የኢትዮጵያ ጦር በ1598 ጦርነት ገጥሞ በከባድ መስዋዕትነት በማሸነፍ የድሉ ባለቤት ሊሆን ችሏል ።

ግብጾችም ቢሆኑ በኢትዮጵያ ላይ ያልተሳካ ወረራ ማድረጋቸው አልቀረም። ግን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩን ዳር ድንበር ማስከበር ለሕልውናው ዋስትና መሆኑን በሚገባ ስለሚያውቅ በ1875 ና በ1876 ጐንደትና ጉራዕ ላይ ገጥሞ ድል በመምታት የግብጽን ወራሪ ጦር ደምስሶታል ።

በኢትዮጵያ ላይ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ግፊት አጀማመር

የእንግሊዝ ኰሎኒያልዝም ወደ ኢትዮጵያ ፊቱን መለስ አድርጐ የጥቅም ክልሉን ሊዘረጋ የሞከረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ መጀመሪያ ላይ ቢሆንም ፣ ከዚያም በፊት በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛቱ የምትሆንበትን ሁኔታ አላጤነውም ለማለት አይቻልም ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ስለኢትዮጵያ አንዳንድ ሁኔታዎች ማወቅ የጀመረው ቀደም ብሎ ቢያንስ ቢያንስ ከ18ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ነው ። ጀምስ ብሩስ የተባለው እንግሊዛዊ አገር ጐብኝ የአባይን ወንዝ ምንጭ ለማግኘት በሚል ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ በተለይም ወደ ጐንደር በ1768 መጥቶ የአገሪቷን የፖለቲካ ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታ ከማጥናቱም በላይ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የብራና መጻሕፍትም ይዞ ወደ አገሩ በ1779 መመለሱ የታወቀ ነው ።[2]

ጀምስ ብሩስ ወደ ኢትዮጵያ ያደረገው ጉዞ ለእንግሊዝ ተስፋፊነት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መጠቆሙን ለንጉሡ ከፃፈው «ደዲኬሽን» ከተባለው ጽሑፉ ከመጀመሪያው ቅጽ ላይ ለመረዳት ይቻላል ።[3] ምጽዋ ለወደብ አመቺ መሆኗንና በአካባቢው የሚካሄደውን የወርቅ ፣ የዝሆን ጥርስ ፣ የቡና ፣ የሰም ፣ የማር የእጣንና የመሳሰሉ ሸቀጦችን ልውውጥ[4] በእንግሊዝ መንግሥትም ሆነ ካፒታሊስቶች ዘንድ ፍላጐት እንዲያሳድር ማድረጉ አልቀረም ። ብሩስ የአባይን ምንጭ ለማወቅ ብሎ የተነሣበት ዓላማ እንዲሁ ለዕው

Digitized by Google

ቀት ያህል ሣይሆን አባይ በኢትዮጵያ፥ በሱዳንና በግብጽ ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊ ሕልውና ላይ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ፣ የዚህን ምንጭ ማወቅ ለእንግሊዝ የቅኝ ግዛት መስፋፋት ዓላማ ጠቃሚነት እንደሚኖረው ተገንዝቦ ፣ በዚህ በኩል የሚያደርገው አስተዋጽኦ ዝናን የሚያተርፍለት ከመሆኑም በላይ ሌላም ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል በመተማመን መሆኑ እምብዛም ላያከራክር ይችላል ። የብዙዎቹ አገር ጐብኝዎችም ተቀዳሚ ዓላማ ፣ በተለይ ካፒታል ከብሔራዊ ድንበሩ አልፎ ወደ ሌላው መሸጋገር በጀመረበት ጊዜ ፣ ለካፒታሊዝም የቅኝ ግዛት ዘመቻ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ። ለምሳሌ በ1862 በካርቱም በኩል አድርጐ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው እንግሊዛዊው ሄንሪ ዳፍተን ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ያሰበበትን ዓላማ ሲገልጽ የተናገረውን ማስታወሱ በቂ ይሆናል ። ሄንሪ ዳፍተን ሲናገር «በሚቀጥለው ትረካዬ በመጠኑ የምገልጸው ወደ አፍሪካ ጉዞ ለማድረግ የተነሣሁበት ዓላማ ከኢትዮጵያ በስተደቡብ ወደሚገኘው የኦሮሞ አገር ደርሼ ሕዝቡን በክርስትና ለማሳመንና ወደፊትም ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ለማጥናት ነበር»[5] በማለት የመጣበትን ዓላማ ግልፅ በሆነ መንገድ አስቀምጦታል።

ይህ አባባል በትክክል እንግሊዞችም ሆኑ ሌሎች አውሮፓውያን ጐብኝዎች ፣ ሚሲዮናውያን ወዘተ ... የተለያዩ ምክንያቶች እየሰጡ ወደ ኢትዮጵያ ይምጡ እንጂ ድብቅ ዓላማቸው ግን የየአገራቸውን የተስፋፊነት ተልዕኮ ለመፈጸም መሆኑን ይጠቁማል ።

በሌላም በኩል የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ላይ የነበረውን ቅኝ ግዛታዊ ፍላጐት እንዳይታወቅበት አቀራረቡ ሁሉ ጥንቃቄ የተመላበት ፣ ከራሱ ይልቅ ለኢትዮጵያ እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን አስመስሎ በመቅረብ ላይ ያተኰረ ስለነበረ ፣ በዲፕሎማሲ መስክም ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ማድረጉን አላቋረጠም። ሄንሪ ሶልት የተባለ የዲፕሎማቲክ መልዕክተኛ ከእንግሊዝ ንጉሥ ለኢትዮጵያ ንጉሥ የተላከ ደብዳቤና በጌጥ የተዋበ የመስኮት መስተዋት፥ የማርያም ስዕልና ከእብነ በረድ የተሠራ ጠረጴዛ ስጦታ ይዞ በምጽዋ በኩል ወደ ኢትዮጵያ በ1805 መጥቶ ነበር ። ሆኖም ያንጊዜ በነበረው የገዥ መደቦች የሥልጣን ሽሚያና የፀጥታው ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ወደ ጐንደር ደርሶ ለንጉሡ ለመስጠት ስላቻለለ የትግራይ ገዥ ለነበረው ራስ ወልደ ሥላሴ ሰጥቶ ተመልሷል ።[6] የተልዕኮው ዓይነተኛ ዓላማ የእንግሊዝ ንጉሥ የክርስቲያን ንጉሥ በመሆኑ፥ ከክርስቲያንኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር በሃይማኖትም የሚመሳሰሉ መሆናቸውን በተላከው የማርያም ስዕል ስጦታ አሳምኖ የንግድ ግንኙነት ለመፍጠርና ይህንም አስታኮ እንግሊዝ ያላትን የተስፋፊነት ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ነበር ። ከስጦታዎቹ አንዱ የማርያም ስዕል የሆነበትም ምክንያት ልዩ ምስጢር ነበረው ። ሄንሪ ሶልት ለራስ ወልደ ሥላሴ ስጦታውን ካቀረበ የኋላ «የስጦታዎቻችን ውጤት በሁሉም ክፍሎች ዘንድ ምን ስሜት እንዳሳደረ ቁልጭ ብሎ ታይቷል ። የሃይማኖታችን ትክክለኛነት አጠያያቂ መሆኑ አበቃ ። ወደ አገሪቱ (ኢትዮጵያ) የመጣንበትንም ዓላማ መጠራጠሩን አቆሙ ፣ በምላሹም የእኛ ጠቃሚነት ከፍተኛ ግምት ተሰጠው»[7] ብሎ የተናገረው በስጦታው ውሳጣዊ አላማ ምን እንደነበረ በገሀድ ያረጋግጣል ።

ሄንሪ ሶልት የተላከበት ዓላማ ባለመሳካቱ ቅሬታ ቢሰማውም ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ የቅርብ ረዳቱ ሆኖ የመጣውን ኮፊንን ከራስ ወልደ ሥላሴ ጋር እንዲቆይ ትቶት ሄዷል። ኮፊን በተልዕኮው ገፍቶበት ከራስ ወልደ ሥላሴ በኋላ የትግራይ ገዥ የነበረውን ደጃዝማች ሰባጋደስን አግባብቶ ወታደራዊና ቴክኒካዊ እርዳታ እንዲደረ

Digitized by Google

ግለት እንዲሁም ምጽዋን ከግብጾች እስለ ቅቆ ለመያዝ እንዲረዱት ለእንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ አራተኛ ደብዳቤ እንዲጽፍ አድርጐ ራሱ ይዞ ሄዶ ነበር ። [8]

የኮሬንም ጥረት ሰባጋዲስን ለማጠናከር ሳይሆን ለሰባጋዲስ በሚያደርገው እርዳታ አማካኝነት እንግሊዝ በኢትዮጵያ ውስጥ እጅዋን እንድትሰድ ፣ ለጊዜው የኢኮኖሚ ጥቅም እንዲኖራትና ለዘላቂው ግን ቅኝ ግዛት ለመመሥረት እንዲያስችላት ነበር።

ይህ ወቅት ምንም እንኳ ለይስሙላ ኢት ዮጵያ በአንድ ንጉሠ ነገሥት አገዛዝ ሥር ናት ቢባልም የገዥ መደቦች ከግል ጥቅማ ቸው አኳያ አገሪቷን ከፋፍለው በአምባ ገነ ንነት ይገዙበት የነበረበት ጊዜ በመሆኑ[9] ፣ ለውጭ ወራሪዎች ጥቅምም ጉዳትም ነበ ረው ። ጉዳቱ አገሪቷ በተለያዩ አምባገነን መሣፍንት ተከፋፍላ በመገዛቷ ኢምፔሪያ ሊስቶች ከማዕከላዊው መንግሥት ጋር የጠ በቀ ግንኙነት መሥርተው የነበራቸውን ፍላጐት ለማሟላት ባለመቻላቸውና ግን ኙነትን ቢመሠርቱም እንኳ ንጉሡ በሥል ጣን ላይ ብዙ ስለማይቆይ ፣ የሚተካውም ግንኙነቱን ስለማያጠናው ውጤት አልባ ሆኖ ስለሚቀር ነው። ከዚህም በቀር ከአንዱ መስፍን ጋር የሚደረገው ግንኙነት በሌላው መስፍን ጋር ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው ካለመቻሉም በላይ ፣ ግንኙነቱን የተቀበለ ውም መስፍን በገዥነት ሥልጣን ምን ያ ህል እንደሚቆይ አስተማማኝ ስለአልነበረ ነው።ለኢምፔሪያሊስቶች የሚሰጠውን ጥቅ ም በሚመለከት ረገድ፣እንደ እንግሊዝ ያሉ ተስፋፊዎች አንዱን መስፍን በጥቂት ስጦ ታም ቢሆን ሸንግሎ ቀዳዳ ለማግኘትና እጅ ለመስደድ ስለሚያስችላቸው ነው ።

እንግሊዝ በዘመነ መሣፍንት የነበረውን የመሣፍንት ሽኩቻ ለመጠቀም ሞክራለች። በተለይም በዚያን ወቅት በአካባቢ አገሮች ላይ የነበራት ፍላጐት እያደገ በመምጣቱና ከሌሎች የአውሮፓ ኃያላን ተስፋፊ አገሮች ጋርም በሰሜንና በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ሽሚያ የያዘችበት ወቅት በመሆኑ ፣ የእን ግሊዝ መንግሥት በ1841 በሻለቃ ደብልዩ ሲ ሀሪስን የተመራ ቡድን የሸዋ ንጉሥ ከነ በረው ሣህለ ሥላሴ ጋር የወዳጅነትና የን ግድ ስምምነት እንዲዋዋል በታጁራና በአ ፋር አገር በኩል ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ነበር። ሀሪስንም የሣህለ ሥላሴ መናገሻ ከተማ ወደ ነበረችው አንኮበር መጥቶ ኢትዮጵያ ለን ግድ ልታቀርባቸው የምትችላቸውን የን ግድ ዓይነቶችና ማዕድናት ፣ (ወርቅ ፣ የዝ ሆን ጥርስ ፣ ዝባድ ፣ ቆዳ ፣ ሰም ፣ ውድ ሙጫ ዝንጅብል ፣ መዳብ ፣ የተፈጥሮ ቡና ፣) ከማ ጥናቱም በላይ በኢትዮጵያም ውስጥ ተፈ ላጊነት ያላቸውን የውጭ ሸቀጦችንም ዓይ ነት በዝርዝር አጥንቶአል።ሀሪስን በኢትዮ ጵያ ምሥራቃዊ ጠረፍና ደቡባዊ ክፍል ያለውን አገር በጥንቃቄ ከተመለከተ በኋላ ለእንግሊዝ የካፒታል ኢንቬስትመንት ተስ ማሚ የሆነ ሁኔታ መኖሩን፣በዓይነቱ ከፍ ተኛ የሆነ ጥጥ ፣ የከሰል ድንጋይ በየሚዳው በቅሎ የሚገኝ ቡና መኖሩን ሲጠቁም፣ በአ ንፃሩም የአገሬውን ሕዝብ የአውሮፓ ዕቃ ዎች ፍላጐት ለማርካት ከ100,000 ፓው ንድ እስተርሊንግ ያላነሰ ገንዘብ ማዋል በቂ መሆኑን ያመለክታል ። [10]

በሌላም በኩል የአገሬው ሕዝብ በአ ውሮፓ ዕቃዎች ላይ ሰው ሠራሽ ፍላጐት እንዲያድርበት ለአውሮፓ ኢንዱስትሪዎች ሊጠቅሙ የሚችሉ ጥሬ ዕቃዎችን ማቅረብ የሚችልበትንም ዘዴ እንዲያውቅ ለማድ ረግ የእንግሊዝ ነጋዴዎች አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ከማሳሰቡም በላይ « የፋብሪካ ዕቃዎችን የሚቀበልና በምላ ሹም ጥሬ ዕቃዎችን ማቅረብ የሚችል ግንኛውም ንግድ ለእንግሊዝ ጠቃሚ መሆን አለበት» ብሎአል ። [11]

እንግሊዝ በሩቅ ምሥራቅ አካባቢ በተ ለይም በሕንድ ላይ ቅኝ አገዛዟን ከዘረጋች ረዘም ያለ ጊዜ በመሆኑ ፣ ምሥራቅ አፍሪ

Digitized by Google

ካንና የአፍሪካ ቀንድ ጠረፍ አገሮችን፤ ወደቦችንና አካባቢዎችን እንግሊዛውያን በየጊዜው መጎብኘታቸው አልቀረም ። ከሕንድ የሚነሱት የእንግሊዝ መርከቦችም ወደ ዛንዚባር፣ ምምባሳ፣ ታጁራ፤ ዘይላ፤ ምጽዋ ወዘተ ... ወደ መሳሰሉት ወደቦች እየመጡ ከመሐል አገርና ከደቡባዊ ኢትዮጵያ የሚገኘውን ጥሬ ዕቃ ይወስዱ ስለነበርና፤ በጉብኝትም ሆነ በዲፕሎማቲክ ስም በዘይላ ወይም በታጁራ (በዛሬዋ ጅቡቲ) በኩል ወደ መሀል አገር ከሚመጡት እንግሊዛውያን መረጃዎች በማግኘት እንግሊዝ የኢኮኖሚ ሥልጣን ክልል ለመመሥረት ፍላጎቷ ተነሳሳ ። ሆኖም በዚያን ወቅት ግብጾች በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የአፍሪካ ጠረፍ አገሮች ላይ የበላይነት ስለነበራቸው፣ እንግሊዝ ከሱልጣኖች ጋር በመግባባት ካልሆነ በቀር ችግር እንደሚፈጥርባት ስላወቀች፤ የዛንዚባር ሱልጣንም በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የአፍሪካ ጠረፍ አካባቢ ይዞታ ስለነበረው፤ የብሪቫን ፣ የመርካን ፣ የሞቃዲሾን ፣ ዋርሻይካንና ሌሎችንም ወደቦች ለእንግሊዝ የምስራቅ አፍሪካ ኩባንያ እንዲለቅ ግፊት ስታደርግ ፣ ኢጣልያ ደግሞ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ላይ ቅኝ ግዛት ለመመሥረት ቆየት ያለፍላጐት ስለነበራት ፣ የተባሉትን ወደቦች እንግሊዝ ለእርሷ እንድትተውላትና ኪስማዩን ግን የሁለቱም የጥቅም ክልል እንድትሆን ታግባቹ ነበር ።

የኢጣልያን ጥያቄ እንግሊዝ ከረጅም ጊዜ የጥቅም ዓላማዋ ጋር ስታስተያይ ጥቅም ያለው ሆኖ በማግኘቷ፣ ጀርመንም ጥያቄውን እንድትቀበለው ማግባባት ጀመረች።

እንግሊዝና ጀርመን በሐምሌ 1890 በርሊን ላይ በተፈራረሙት ውል መሠረት ምሥራቅ አፍሪካን ሲከፋፍሉ፣እንግሊዝ ዛንዚባርንና በኋላ ብሪቲሽ ኢስት አፍሪካን የተባለውን አገር ስትይዝ ፣ ቢናዲርን (የኢጣልያ ሱማሌ) ለኢጣልያ ለመስጠት በሁለቱ ኃያላን መንግሥታት መካከል የሀሳብ መግባባት ነበር ። እንግሊዝም በነሐሴ 12 ቀን 1892 በዛንዚባር ሱልጣን ስም ሆና ከኢጣልያ ጋር ባደረገችው ውል መሠረት ኢጣልያ ቤናድርን እንድትይዝ ተደርጓል ።[13]

ሆኖም የቅኝ አገዛዝ ዓላማ የቅኝ ግዛቶችን ጥሬ ሀብት መበዝበዝንና ካፒታልም ወደ ቅኝ ግዛቶች ማስገባትን የሚያጠቃልል ስለነበር ፣ ቅኝ ገዥ አገሮች የቅኝ ግዛት አገሮችን አስተዳደር የብዝበዛውን ተግባር ያለርሀራሄ ለሚያካሂዱ ኩባንያዎች ሰጡ። በዚህም መሠረት የእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ለእንግሊዝ የምስራቅ አፍሪካ ኩባንያ ፣ የጀርመን ምሥራቅ አፍሪካን አስተዳደር ለጌሌልሻፍት ፉር ዶቼ ኮሎና ይሴሽን ኩባንያ ፣ የኢጣልያ ሱማሌን አስተዳደር ለሲቸር ፊሎናርዲ ኩባንያ ተሰጥቷል ።[13] ይህም ዓይነቱ ኢምፔሪያሊስታዊ የአገዛዝ ስልት የኢምፔሪያሊስት አገር ከበርቴዎች በየመንግሥታቸው የበላይ ጠባቂነት በኋላቀር አገሮች ላይ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነታቸውን ለማስፈን አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል ።

ቴዎድሮስና የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም

በሌላም በኩል የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ውስጥ በዲፕሎማሲ መስክ አቀራረቡን በማሳመር ኢምፔሪያሊስታዊ ፍላጎቱን በተግባር ለመተርጎም ሞከርአል ። በ1843 ባልተር ፕላውደንና በካልካታ ውስጥ ነጋዴ የነበረው ጆን ቤል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሁኔታዎችን ካጠኑና ከተመለከቱ በኋላ፣ ፕላውደን እንደገና ወደ እንግሊዝ በ1847 ተመልሶ በመሄድ ለሎርድ ፓልመርስቶን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በሚገባ ገልጾ፣ ለእንግሊዝም የኢንዱስትሪ ዕድገት የጥሬ ሀብት ሰፊ ምንጭ መሆኗን አመልክቶአል። እንዲሁም እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት እንዲኖራት አሳሰበ

Digitized by Google

ራሱ የእንግሊዝ ቆንሲላ ሆኖ እንዲሠራ በመደረጉ በ1848 ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል ።

ፕላውደንም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከመጣ በኋላ በ1849 ከራስ አሊ ጋር በእንግሊዝ ስም የንግድ ስምምነት ተፈራርሞ ፣ ነበር ።[14] በስምምነቱ ላይ ትኩረት የተሰጠው በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካከል የጠበቀ የንግድ ግንኙነት እንዲኖር ሲሆን ግንኙነቱም ከጣልቃ ገብነት ነፃ እንደሆነ ተወስቷል ። ከዚህም በቀር ኢትዮጵያ የተወሰደባትን የባሕር ጠረፍ መልሳ ማግኘት እንደሚገባትና እንዲሁም በቀይ ባሕር ጠረፍ አካባቢ ያለው የንግድ መስመር ከፍትና አስተማማኝ እንዲሆን እንግሊዝ የምትረዳ መሆኗን ስምምነቱ ያወሳል ።[15]

ይሁን እንጂ ስምምነቱ በተግባር ከመተርጐሙ በፊት አፄ ቴዎድሮስ በ1854 ጐንደርን ወግተው ራስ አሊን ድል በማድረግ የመንግሥት ሥልጣን ያዙ ። ፕላውደንና ቤልም ወደ እሳቸው ተዛውረው ረዳትና አማካሪ ሆነው መሥራት ቢጀምሩም፣ በሁለቱ አገሮች መካከል የታሰበው ግንኙነት ለጊዜው ቀዝቀዝ ብሎ ነበር ። ይሁንና ፕላውደን አፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም ለማስተናገድ ዝግጁ እንዲሆኑ መጐትጐቱ አልቀረም ። ፕላውደን ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋራ እንድትቆራኝ ያደረገው ጥረትና አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። የኢትዮጵያን ካርታ በመሥራት የመሬቷን አቀማመጥና ልምላሜዋን የሕዝቧን ባሕል ፣ ጠባይና ታሪክ ገልጾ ወደ እንግሊዝ በመላክ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ላይ የነበረው ትኩረት በጣም እንዲጠናከር ጥረት አድርጓል ።[16]

ፕላውደን የአፄ ቴዎድሮስን ፍላጐትና የሥልጣን መረጋጋት ከተረዳ በኋላ ኢትዮጵያን የእንግሊዝ የጥቅም ክልል ወይም ቅኝ ግዛት ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ የባሕር በሯን ከፍትና አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በሚገባ በመገንዘብ ፣ ሰኔ 25 ቀን 1855 ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር ባደረገው ውይይት የኢትዮጵያን የቀይ ባሕር ጠረፍና ምጽዋን የያዙትን ቱርኮች እንግሊዝ ጣልቃ በመግባት ወግታ ለማባረር የምትችል መሆኑን ስለገለጸላቸው ከስምምነት ላይ ደርሰው ነበር ። ይህንንም ሀሳቡን ወዲያውኑ በዚያን ወቅት የውጭ ጉዳይ ጸሐፊ ለነበረው ለሎርድ ክላሬንደን አስታውቆት ስለነበረ ፣ በቱርክ ለነበረው የእንግሊዝ አምባሳደር ኤስ ዲ ሬድክሊፍ የቱርክ መንግሥት ምጽዋንና አካባቢዋን ለኢትዮጵያ ያስረክብ ዘንድ ግፊት እንዲያደርግ ክላሬንደን አዝዞ ነበር።[17] ሆኖም በዚያን ወቅት ዛሪስት ሩሲያ በቱርክ ላይ የመስፋፋት ዘመቻ እያደረገች ስለነበረ የሩስያም መስፋፋት እንግሊዝ በቱርክ የተጽእና ክልል ሥር በነበሩት አገሮችና በሕንድ ላይ የነበራትንና የሚኖራትን ጥቅም የሚፃረር ሆኖ ስላገኘችው ፣ ሀሳቧን ለውጣ ቱርክ በኢትዮጵያ ላይ የምታካሂደውን ወረራ መደገፍ ጀመረች ።

የእንግሊዝ መንግሥት በሩቁ የታየው ኢምፔሪያሊስታዊ ጥቅም ያልተከሰተለትን ፕላውደንን የተካውና ፣ ከንግሥት ቪክቶሪያ ላፄ ቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤና ጥቂት የጠመንጃና ሽጉጥ ስጦታ ይዞ የመጣው ቆንሲላ ካሜሮንም፣ ግብጾችና ቱርኮች በሰሜን ኢትዮጵያ ግዛት ላይ ያደርሱት የነበረውን ጥቃትና ወረራ እንግሊዝ እንድትቃወም ደጋግሞ ለእንግሊዝ መንግሥት አሳስቧል ። ይሁንና በወቅቱ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ኧርል ራስል ግብጾችና ቱርኮች በኢትዮጵያ ላይ በሚፈጽሙት ወረራና ጥቃት በምንም ዓይነት ጣልቃ እንዳይገባ ለካሜሮን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶት ነበር ።[18]

ኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት መሆን አለባት ብሎ ይሟገት የነበረው ሲ ማርክ

Digitized by Google

ሀምም ፣ ራስል ስለ ኢትዮጵያ የነበረውን ፖሊሲና አመለካከት በሚመለከት ረገድ ሲጽፍ «ኢትዮጵያን ከቱርኮች ወረራና ጥቃት ለማዳን በመርዳት ፋንታ በተቻለ መጠን ከኢትዮጵያ ጋር ኅብረት ከመፍጠር ማፈግፈግ የሚመርጥ ነው ፤» [19] ብሎ ነበር ።

«... ኅብረት ከመፍጠር ማፈግፈግን...» ሲል በመሠረቱ ኧርል ራስል በኢትዮጵያ ላይ ፍላጐት ሳያድርበት ቀርቶ ሣይሆን ፣ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ያለዚያም የጥቅም ክልል የማድረጉን ጉዳይ እንግሊዝ የምት መለከተው በዓለም ዙሪያ ከምታካሂደው የመስፋፋት ዘመቻዋና ካለው አጠቃላይ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊስታዊ ጥቅሟ አን ፃር መሆን እንዳለበት አርቆ በመመልከቱ ነበር ። ይልቁንም በዚህ ወቅት እንግሊዝ ለጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎቿ የሚሆን ጥጥ ታገኝ የነበረው ከአሜሪካ ስለነበርና የዚ ህም ዘላቂነቱ ስለአጠራጠራት ፣ እንደ አማ ራጭ ገበያ አድርጋ የያዘቻት በቱርኮች ተጽ እኖ ሥር የነበረችዋን ግብጽ ነበረና ፣ ከኢ ትዮጵያ ይልቅ ከቱርክ ጋር ጊዜያዊ የሆነ ወዳጅነት መፍጠሩ የእንግሊዝ ወቅታዊ ጥቅሟ ያስገድድ እንደነበረ ተገንዝቧል ።

በአንፃሩ ግን ፕላውደንና ካሜሮን የተ መለከቱት ፣ እንግሊዝ ከተቀናቃኞቿ ፈረ ንሣይ ፣ ጀርመን ፣ ኢጣልያ ፣ ወዘተ... ቀ ድማ በኢትዮጵያ ላይ የብዝበዛ መረቧን የምትዘረጋበትንና ቀይ ባሕርንም በቁጥ ጥሯ ሥር የምታውልበትን ሁኔታ ሲሆን፣ ይህንንም ሲያቅዱ እንግሊዝ ካላት ዓለም አቀፋዊ ጥቅሟ ነጥለው በማየት ነበር ለማ ለት ይቻላል ። ይህ ሲባል ግን ራስልም ቢሆን እንግሊዝ ኢትዮጵያን ጥገኛ ለማ ድረግ ፈጽሞ መሞከር የለባትም ማለቱ አልነበረም ።

በሌላም በኩል አይሁዳውያንን ወደ ክር ስትና ለመለወጥ የለንዶን ማኅበር አባላት የሆኑት ሚሲዮናውያን ማለትም እስተርን ፣ ሮዚንታል ፣ ብራንዴስና እስቴይጀር በጐ ንደር የሚገኙትን ፈላሻዎች የክርስትና ትምህርት አስተምረን እናጠምቃቸዋለን በሚል ሰበብ በ1860 ገደማ ወደ ኢት ዮጵያ መጥተው ነበር ። የእነዚህን ሚሲ ዮናውያን እውነተኛ ተልዕኮና በኢትዮ ጵያ ውስጥ የሚያካሂዱትን ተግባር ፀሚ ገባ በቅርብ ሆኖ የተከታተለውና የአ ጤነው ከአፄ ቴዎድሮስ ጋርም ለብዙ ጊዜ የቆየው ፈረንሣዊው ኤም ቡሲደን ፣ ሰዎቹ ሚሲዮናውያን ሣይሆኑ የእንግሊዝ መንግሥት ሰላዮችና ሽብር ፈጣሪዎች ከመ ሆናቸውም በላይ ፣ ኢትዮጵያን የእንግሊዝ ጥገኛ ለማድረግ በምስጢር ከኤደን የጦር መሣሪያ እያመጡ ለመሣፍንቱና ለባላባ ቶች በማደል የእርስ በርስ ጦርነት እንዲ ፈጠር በከፍተኛ ደረጃ እየቀሰቀሱ ፣ ለእን ግሊዝ ጣልቃ ገብነት ቅድመ ሁኔታዎችን ያዘጋጁ እንደነበር በሚገባ ጠቁሞአል ። [20]

እንግሊዝ ለኢምፔሪያሊስት ዓላማዋ የቱርክ መንግሥት እንቅፋት እንዳይሆን ባትና በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን በቁጥጥሯ ሥር ለማዋል ስትል ፣ ቱርኮች በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸሙት ወረራ ሙሉ ተባባሪ የሆነ ችበት ጊዜ ጥቂት አልነበረም ። በኢየሩሳ ሌም የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስ ቲያን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት የቱ ርክ ባለሥልጣኖች ያለምንም ምክንያት ቀምተው ለአርመኖች ከመስጠታቸውምና በወቅቱ በነበረው ወረርሽኝ በሽታ ምክን ያት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ለቀው ሲወጡ በገዳማቱ ውስጥ የነበሩትን ልዩ ልዩ ጠቃሚ መጻሕፍትና ጽሑፎችን ከማ ቃጠላቸውም በላይ መነኮሳቱን «ኢትዮ ጵያ የቱርክ ቅኝ ግዛት ስለሆነች እናንተም የቱርክ ዜጎች ሁሉ» እያሉ አሰቃይተዋ ቸው ነበር ። መነኮሳቱም እንግሊዝ የክር ስቲያን አገር ስለሆነች ስቃያችንን አይታ የቱርክን መንግሥት ታማልደናለች በሚል እምነት በኢየሩሳሌም ለነበረው ለእንግሊዝ ቆንስላ ፊንና ለእንግሊዝ ጳጳስ ሳሙኤል

Digitized by Google

ጕባት ጉዳዩን አመልክተው ነበር። ሁለቱም
ሊረዱአቸው ፈቅደው ከቱርክ መንግሥት
ጋር ንግግር ጀምረው ሳለ የእንግሊዝ መን
ግሥት ከቱርክ ጋር ያለውን የጥቅም ግን
ኙነት በመመልከት በምንም ዓይነት እጃ
ቸውን እንዳያስገቡ ከማስጠንቀቁም በላይ፥
ከቱርክ መንግሥት ጋር ኢትዮጵያውያንን
ለመርዳት ሲል ውዝግብ የፈጠረውን ቆን
ሲላ ፊንን በሌላ ቆንሲላ ተክቶታል ። [21]
እዚህ ላይ መገንዘብ የሚቻለው እንግሊዝ
በአንድ ወገን ለኢትዮጵያ የውሸት ወዳጅ
ነት እያሳየች በሌላ በኩል ግን ወራሪዋ
ቱርክ በኢትዮጵያ ዜጐች ላይ የምትፈጽ
መውን ወረራና ግፍ እያበረታታች እንደነ
በረ ነው ።

ይህ በዚህ እንዳለ ፥ እንግሊዝ በግብጽ
ላይ ያደረባት ፍላጐትና ጥቅም እያደገ
መጣ ። የቱርክን ተስፋፊነት በማደናቀፍ
በይዞታዋ ሥር የነበሩትንም እስትራቴጂ
ያዊ ቦታዎችና አገሮች እያስለቀቀች ፥ እን
ደአመቺነቱ በቀጥታ በመያዝ ወይም በሌላ
ኃይል በማስያዝ እንግሊዝ የተጽእኖ ክል
ሏን ማስፋፋት ጀመረች ። በዚህም መሠ
ረት እንግሊዝ በቱርክ ሱልጣን ላይ ከፍተኛ
ግፊት በማድረግ ግንቦት 20 ቀን ፥ 1868
ቱርክ ምጽዋን ለግብጽ እንድታስረክብ
አደረገች ። በዚህ ውለታዋም ከግብጽ ጥጥ
መግዛት ቻለች ። በእንግሊዝ ግፊትና ቡራ
ኬም ግብጻውያን የኢትዮጵያ ግዛት የነበ
ሩትን አዱሊስ አጠገብ የምትገኘዋን ዙላ
ንና አምፊላ ቤይን ከመያዛቸውም በላይ
በ1875 የሐረርን ከተማ ለመያዝ ቻሉ ። [22]

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በቀይ ባህ
ርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ ያለውን
እስያንና ሰሜን ምሥራቅ አፍሪካን ቅኝ
ግዛት ማድረግ እስትራቴጂያዊና ወሣኝ
መሆናቸውን ተገንዝቦ መሯሯጥ የጀመረ
በት ወቅት የ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተ
ኛው አጋማሽ ሲሆን ፥ በኢትዮጵያ ላይም
የጥቅም ክልሉን ለመዘርጋት ጥረቱን የጀ
መረበት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በዚሁ
ዘመን ነበር ። በዚህም ወቅት የእንግሊዝ
ኢምፔሪያሊዝም የተስፋፊነት ዓላማውን
ለማሟላት ከተጠቀመባቸው ስልቶች አንዱ
ገጽታ ዲፕሎማሲያዊ አቀራረብን ሽፋን
በማድረግ ነበር ። በዚህም ስልቱ ከአፄ
ቴዎድሮስ ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነትን
ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ። የዲ
ፕሎማቲክ ግንኙነትን የማስፋፋቱ ፍላጐት
የመነጨው ከተስፋፊዋ እንግሊዝ በኩል
ብቻ ሣይሆን ሆን ተብሎ በተላኩት
በእንግሊዝ ሚሲዮናውያን ፥ አገር ጐብኚ
ዎችና ቆንሲላዎች ጉትጓችነትና ቀስቃሽ
ነት በኢትዮጵያም በኩል ነበር ። የዚህ
ዓይነቱም ግንኙነት ምክር ጠንሳሾች በአፄ
ቴዎድሮስ አደባባይ በባለሟልነት ይፋልሉ
የነበሩት ፕላውደን ፥ ቤል ፥ ካሜሮንና ሌሎ
ችም እንግሊዛውያን ነበሩ ። በእነዚህ የእ
ንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ተስፋ አስፈፃሚ
ዎች ጉትጐታና ቅስቀሳ የተነሣ ከፍተኛ
አድናቆትና ጉጉት ያደረባቸው አፄ ቴዎ
ድሮስም በአስቸኳይ ከእንግሊዝ ጋር ወዳ
ጅነት ፈጥረው አገራቸውን በሥልጣኔ
ጐዳና ለመምራት በጐ ፈቃድ ሲያሳዩ ፥ በእ
ንግሊዝ በኩል ይመከርና ይዘከር የነበረው
ግን ኢትዮጵያን ወሮ ወይም በሌላ ኃይል
አስወርሮ ለጊዜው የተጽእኖ ክልል ለዘሌ
ቄታው ግን ቅኝ ግዛት ማድረግ ነበር ።

አፄ ቴዎድሮስም ይህንን የረቀቀ የእን
ግሊዝ የውስጥ ተንኰል በትክክል በተረዱት
ጊዜ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ቀደምት
መልዕክተኞች የነበሩትን እንግሊዛውያንና
የቀሩትንም አውሮፓውያን ለማሠር በቁ ።

ይህም ቆራጥ እርምጃ እንግሊዝን ሁለት
ነገሮች ሳያሳስባት አልቀረም ። አንደኛው
ይህን አጋጣሚ እንደ በቂ ምክንያት አድ
ርጐ ኢትዮጵያን ወሮ በመውጋት ቅኝ ግዛት
ማድረግ ሲሆን ፥ ሁለተኛው ደግሞ የእንግ
ሊዝ ተቀናቃኝ የነበሩት የአውሮፓ ኃያላን
መንግሥታት በተለይም ፈረንሣይ በግብጽ

Digitized by Google

ላይ የነበራትን ቅኝ ግዛት የማድረግ ፍላጐት
እንግሊዝ እያጠበበች በመምጣቷ ፈረንሳይ
ከ1850ዎቹ ማከተሚያ ጀምሮ በኢትዮጵያ
ላይ የጥቅም ክልሏን ለመዘርጋት በምሥ
ራቃዊ የኢትዮጵያ ግዛት አካባቢ ታንዣ
ብብ ነበርና፤ የእንግሊዝን እርምጃ በየዕለቱ
እየተከታተለች አጸፋውን ለመውሰድ ዝግ
ጁ ነበረች ። በዚህ የተነሣ ከፈረንሣይ
ጋር ወቅታዊ ያልሆነና ውርደትን የሚያስ
ከትል ግጭት ፈጥሮ ከውድድሩ መድረክ
ከመውጣት ይልቅ እስረኞቹን አስፈትቶ
መውሰዱ የተሻለ አማራጭ ነው የሚል እን
ደነበር ከዝርዝር ሁኔታዎች መረዳት ይቻ
ላል ።

አንደኛውን ሀሳብ በሚመለከት ረገድ
የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም አፈቀላጤ
ፀሐፊዎች ሳይቀሩ የናፒየር ወታደራዊ ቡ
ድን አፄ ቴዎድሮስን በሚያዝያ 1868 ድል
ከአደረገ በኋላ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ሳያ
ደርግ ለቆ በመሄዱ ወቅሰውታል ። ማርክ
ሀም የናፒየር ወታደራዊ ቡድን ኢትዮጵ
ን በቅኝ ግዛትነት መያዝና ቱርኮችንም
ከኢትዮጵያ ጠረፍ አባሮ በቀይ ባህር ጠረፍ
ላይ የምትገኘውን ምፅዋን እንደ ኤደን ነፃ
ወደብ ማድረግ እንደነበረበት አመልክቶ፤
ይህንን ሳይፈጽም በመቅረቱ ወቀሳውንና
ቅሬታውን አሰምቶአል ። [23]

ያም ሆኑ ይህ ከናፒየር ቡድን ወደ ኢት
ዮጵያ መምጣት በፊት እንግሊዝ በኢትዮ
ጵያ ላይ የኢኮኖሚ ሥልጣን ክልል ለመ
ዘርጋት ፍላጐት አልነበራትም ፣ ወይም
ፍላጐቷን ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ አላ
ደረገችም ማለት፣እንግሊዝ በአፄ ቴዎድሮስ
ዘመንም ሆነ ከዚያ በፊት ከኢትዮጵያ ጋር
የነበራትን ግንኙነትና የግንኙነቱን ዓላማ
ጠለቅ ብሎ አለማጤን ይሆናል ። ናፒየር
እስረኞችን ለማስለቀቅ በሚል ሰበብ ወታ
ደራዊ ቡድኑን ይዞ መጥቶ አፄ ቴዎድሮ
ስን ከወጋ በኋላ መውሰድ የሚኖርበትን
እርምጃ ከሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ ኢትዮ
ጵያ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የምትሆንበት
መንገድ መሻት እንዳለበት ከእንግሊዝ
መንግሥት መመሪያ እንደተሰጠ ይገመ
ታል ።

ሆኖም ናየፒር ከአገኘው ድል በኋላ ኢት
ዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ያልሞከረበት
1ኛ/ አፄ ቴዎድሮስ በመሣፍንት አት
ኩኝ ባይነትና የግል ጥቅምና ክብር ፈላጊ
ነት የተቆራረሰችዋን ኢትዮጵያ አንድ ለማ
ድረግና ማዕከላዊ አመራር ለመስጠት በወ
ሰዱት ቆራጥ እርምጃ ጥቅማቸው የተነካባ
ቸውና በጠላትነትም ሲመቻቸው ይወጉ
አቸው የነበሩት የላስታው ዋግ ሹም ጐበዜ፣
የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ፣ ወልቃይቴው
ጣሰው ጐበዜ ፣ የሸዋው ምኒሊክ ፣ የጐጃሙ
ራስ ደስታና የወሎዋ ወ/ሮ ወርቂቱ ምንም
ናፒየር የጋራ ጠላታቸው የሆኑትን አፄ
ቴዎድሮስን እንዲአጠፉላቸው ቢፈልጉም፣
ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ቢሞክር
ግን ሁሉም ግንባር ፈጥረው እንደሚወጉ
ትና [24] ሊመከትም የማይችል መሆኑን ተ
ገንዝቦ ስለነበር፤ 2ኛ/ናፒየር ምንም እንኳ
ከኢትዮጵያውያን ጋር ሲነፃጸር የበላይነት
ያለው የጦር መሣሪያ ቢይዝም ወታደሮቹ
በቁጥር አነስተኛ ስለነበሩ ፣ በምንም ዓይ
ነት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ የሚ
ያስችል ኃይል እንዳልነበረው መገንዘቡ፤
3ኛ/ ፈረንሣይ አቦክን (ጂቡቲ) ከአንድ የአ
ካባቢው ባላባት ላይ በ10,000 ማርያትሬዛ
ብር ገዝታ [25] የተጽእኖ ክልሏን በኢትዮ
ጵያ ላይ ለማስፋፋት በማድባት ላይ መከ
ሆኗም በላይ በአፄ ቴዎድሮስ አደባባይ
ቆንሲላዋን አስቀምጣ የእንግሊዝን ፖለቲ
ካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ሁሉ በጥ
ንቃቄ ተቆጣጥራ ነበርና፣ናፒየር ቅኝ ግዛት
ለማድረግ ቢቃጣ የሚያስከትለውን ሁኔታ
በቅድሚያ መገምገሙ እንደ ምክንያቶች
ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው ።

Digitized by Google

ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ እንግሊዝ ከፈረንሳይ ጋር ያደረገችው ፉክክር

ናፒየር ኢትዮጵያን በዚህ ወቅት ቅኝ ግዛት አድርጎ ለመያዝ አለመሞከሩ የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም ከሽንፈት እንዳዳነው ሊቆጠር ይችላል ። በተለይም በዚያን ወቅት የስዊዝ ካናል በፈረንሣዮች እጅ ሥር የነበረበትና በግብጽም ውስጥ የፈረንሣይ ካፒታል ሥር እየሰደደ የመጣበት ወቅት በመሆኑ ፣ ስዊዝ ካናልም የቀይ ባሕርንና የሕንድ ውቅያኖስን አካባቢ አገሮች በቁጥጥር ሥር ለማዋል እስትራተጂያዊ መስመር በመሆኑ የበላይነቱን ለመያዝ የተፋፋመ ኢምፔሪያሊስታዊ ፉክክር በአካባቢው ይካሄድ ነበር ። በመሆኑም እንግሊዝ በኢትዮጵያ ላይ በወቅቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ሰፋ ያለ ጦርነት ብታካሂድ ከመሸነፍ እንደማትድን ለመገመት አያዳግትም ።

በሌላ በኩል እንግሊዝ ግብጽን ከፈረንሣይ ጋር በጋራ ከ1876 ጀምራ ስታስተዳድር ከቆየች በኋላ በ1882 በብቸኝነት በቁጥጥሯ ሥር በማድረጓ ፤ ይህ እርምጃ እጅግ ያስቆጣት ፈረንሣይ ፣ የእንግሊዝን ካፒታል ተቀናቃኝነት በየአቅጣጫው ለማዳከምና ለመቆጋት ከፍተኛ ጥረት ታደርግ ጀመር ። እንግሊዝ በሰሜን አፍሪካ ይበልጡንም በስዊዝ ካናል አካባቢ አገሮች ላይ የፈረንሣይ ቀንደኛ ተቀናቃኝና የጥቅም በሯን ዘጊ እየሆነች በመምጣቷ አዲስ የጥቅም ክልል ለመፈለግና የተቀናቃኟን የእንግሊዝን ሩጫ ለመግታት ስትል ፈረንሣይ ፊቷን ወደ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ አገሮች መለስ አደረገች ። ይህም በአፍሪካ ቀንድ አገሮች ላይ ጥቅሟን ለመዘርጋት የሚያስችላት ብቻ ሣይሆን በሩቅ ምሥራቅ ላይ የኢኮኖሚ ሥልጣን ክልሏንም ለማስፋፋት እጅግ አድርጎ እንደሚያግዛት በማወቅ የታጁራ ባሕረ ሰላጤን አካባቢ በቁጥጥሯ ሥር ለማድረግ ወሰነች ። እንግዲህ ፈረንሣይ ይህን አካባቢ በሥሯ ማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ፣ የሚያስገኝላትና ለሩቅ ምሥራቅም መረማመጃ እንደሚሆናት ከመገንዘቧም በላይ ኢትዮጵያንም በኢኮኖሚ ሥልጣን ክልሏ ውስጥ ለማጠቃለል አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥርላትም በማመን ነበር ።

ፈረንሣይ ምንም እንኳ አቦክን (ጅቡቲን) የያዘችው በ1862 ቢሆንም ፣ በኋላ የፈረንሣይ ሶማሌ ብላ የሰየመችውን ግዛት የመሠረተችው በ1881 ነበር ። ኢጣሊያም የፈረንሣይን ፈለግ በመከተል አሰብን ጁሴፔ ሳፔቶ አማካኝነት ከአንድ ሱልጣን ላይ በ1869 በመግዛት በውድድሩ ውስጥ ገባች።

የፈረንሣይን በሰሜን አፍሪካ ላይ ተስፋፊነት እንግሊዝ በ1882 ግብጽን የራሷ ጥገኛ በማድረግ እልባት ከአደረገችበት በኋላ ፣ ፈረንሣይና ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ምሥራቅ ያለውን አገር እየያዙ የጥቅም ክልላቸውን መዘርጋት ስለጀመሩ ፣ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ዘልቀው የግብጽና የሱዳን ሕዝቦች ሕይወት የሆነውን የአባይን ወንዝ በቁጥጥራቸው ሥር ከአደረጉ ፣ ግብጽንም ሆነ ሱዳንን ሊይዙ ይችላሉ የሚል ስጋት እንግሊዝ አደረባት ። በዚህም የተነሣ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የጥቅም ክልሏን ለመዘርጋት ከፍተኛ ጥረት ከአደረገች በኋላ በ1884 ገደማ የዘይላን አካባቢ ያዘችና የእንግሊዝ ሱማሌ የተባለውን ቅኝ ግዛት መሠረተች ።[26] ከዚህም በኋላ በወቅቱ የንግድ ማዕከል የነበረችውን ሐረርንና አካባቢዋን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ እንግሊዝና ፈረንሣይ ፉክክር ገጠሙ ።

የፈረንሣይ ሱማሌ ጠቃሚነት ከኢትዮጵያ አንፃር ካልሆነ በቀር እስከዚህ ፋይዳ የሌለው መሆኑን የተገነዘበችውና የእንግሊዝና የኢጣሊያም በአካባቢው እየተስፋፉ መምጣት ከፉኛ ያሰጋት ፈረንሣይም በ1888 ገደማ ከእንግሊዝና ከኢጣሊያ ጋር ሐረርንና አካባቢዋን በጥገኝነት ለመያዝ የሚያግድ የምስጢር ስምምነት እንዲደረግ ጠየ

Digitized by Google

ቀች ። እንግሊዝም እራሷ ሐረርን ጥገኛ ላለማድረግ ስትስማማ «ኢጣሊያ ሐረርን ጥገኛዋ አታድርግ» በሚለው ሃሣብ ግን የማትስማማ መሆኗን ገልፃ አሻፈረኝ አለች ። እንግሊዝ የሐረርን በኢጣሊያ መያዝ የደገፈችበት ዓይነተኛ ምክንያት ፈረንሣይ ቀንደኛ ተቀናቃኟ በመሆኗ እርሷን ከውድድሩ ውጭ ለማድረግና ለማገድ አስባ እንደነበር ግልጽ ነው ።[27] ከዚህም በቀር ኢጣሊያ ለፉክክሩ አዲስ መጥ ከመሆኗም በላይ፣ በአፍሪካ ያላት የቅኝ ግዛት ይዞታ ለእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስታዊ ጥቅም ከፈረንሣይ ጋር ሲወዳደር በወቅቱ ይህን ያህል አደገኛ ሆና ባለማገኘቱ ነው ።

ከዚህ በኋላ እንግሊዝና ፈረንሣይ በኢትዮጵያ ጥቅማቸውን ለማስፋፋት የሚያደርጉት መራሯጥ በኢትዮጵያ የገዥ መደቦች ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኝ አንዱ ለአንዱ እንቅፋት በመሆን ሥውር ደባቸውን መገላለጥ ያዙ ። እንግሊዝ በኢትዮጵያ ላይ ያሰበችውን ተንኮልና ወረራ ፈረንሣይ አጋልጣ ለኢትዮጵያ መንግሥት ስትጠቁም እንግሊዝም እንደዚሁ ታደርጋለች ። ኢትዮጵያ ከወራሪዎችና ከተስፋፊዎች ራሷን ለመከላከል በምትወስደው እርምጃ ፈረንሣይ ሃሣቧን ስትደግፋት እንግሊዝ ከጠላቷ ጋር ትሰለፋለች ። ያም ሆነ ይህ ሁለቱም ወቅቱን እየገመገሙ በየፊናቸው የሚያሳዩት ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ ለኢትዮጵያ የታሰበ ሳይሆን ከራሳቸው ከቅርብና ከሩቅ ጥቅማቸው አንፃር የታቀደ ነበር ።

አፄ ምኒሊክ በምዕራብ በኩል የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን እስከነጭ አባይ ወንዝ ድረስ መሆኑን ገልጸው ሲከራከሩ ፈረንሣዮች ደጋፊዎቹ ነበሩ ። እንግሊዝ ግን በ1897 ሰር ሬነል ሮድ የተባለ መልእክተኛዋን ወደ አፄ ምኒሊክ ልካ ተቃውሞዋን በዝርዝር ከመግለጿም በላይ ኢትዮጵያ ጥያቄውን የምታነሣ ከሆነ እንግሊዝም የአባይን ወንዝና ሸለቆውን በቁጥጥሯ ሥር ለማዋል የምታደርገውን ጥረት ቀዝቀዝ የምታደርግ መሆኑን አስታውቃ ለማግባባት ሙከራ አድርጋለች ። ሆኖም ተስፋፊዋ እንግሊዝ በአንድ በኩል ይህንን ዓይነት ሃሣብ እያቀረበች ሳለ በሌላ በኩል ደግሞ በ1898 ካቢንዳሽ በሚባለው የጦር አዝማች የተመራ 500 ሰዎች ያሉበት ወራሪ ጦር አዘጋጅታ የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ግዛት ጥሶ እንዲገባ በማድረጓ በከፋው አገረ ገዥ የተመራ የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሥፍራው ሄዶ አባሮታል ።[28]

ይህ ዓላማ ሲከሽፍባት እንግሊዝ በ1902 ለተስፋፊነቷ መግቢያ ቀዳዳ አገኛለሁ በማለት በባሮ ወንዝ አጠገብ የሚገኘውን ኢታንግ የተባለውን ቦታ ኢትዮጵያ በኪራይ መልክ እንድትሰጣት ጠይቃ ሳይሳካላት ቀርቷል ።[29] ይህ እንግዲህ በ1898 በወረራ መልክ ልትይዝ የሞከረችው ምዕራባዊው የኢትዮጵያ ግዛት ሆኖ ሣለ ይህን ቦታ ለጊዜው በኪራይ መልክ መያዟ ለሦስት ነገሮች ጥቅም እንደሚሰጣት አውቃ ነበር ። ይኸውም 1/ ኢትዮጵያ ወሰኔ ነጭ አባይ ነው ያለችውን ተግባራዊ እንዳታደርገው ለማገድ አመቺ ከሚሆንላትም በላይ የነጭ አባይን ሸለቆ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ያግዛታል፣ 2/ በአባይ ምንጭና አካባቢው ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ያስችላታል፣ 3/ኢትዮጵያን በየአቅጣጫው ማለትም በምሥራቅ፤በምዕራብና በሰሜን ከባ ጥገኛዋ ለማድረግ በምታደርገው ውድድር እስትራቴጂዊ የበላይነት እንዲኖራት ያግዛታልና ነው ።

በአንፃሩም ፈረንሣይ ካፒታሏን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባቱና የጥቅም ክልሏን በማስፋፋቱ ረገድ በእንግሊዝ ላይ ብልጫ እያሳየች ሄደች ። የፈረንሣይ ከበርቴዎች በታጁራ ባሕረ ሰላጤ አካባቢ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ከተመሠረተ ጀምሮ ካፒታላቸውን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበርና ይህንን ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ከጂቡቲ አዲስ አበባ የሚደርስ የባቡር ሃዲድ ለመዘርጋት ከኢትዮ

Digitized by Google

ጵያ መንግሥት ኮንሴሲዮን እንዲያገኙ ያላ
ሰለሰ ጥረት አድርገዋል ። ምኒልክም የባ
ቡር ሃዲዱን የመዘርጋት ሥራ በኤም ኢልግ
አማካኝነት ዱፓርቺና ቪጎራውክስ ለተባለ
የፈረንሣይ ኩባንያ በ1894 ሰጥተው ነበር።
ሥራው የተጀመረው ግን በ1897 ነው። ይሁ
ንና ኩባንያው በመካከሉ የገንዘብ ችግር
ስለደረሰበት ሥራውን እንዲያቋርጥ ተገ
ደደ ። የፈረንሣይ መንግሥትም ለኩባን
ያው ለጊዜው እንኳ የገንዘብ እርዳታ ሊያ
ደርግለት ባለመቻሉ ኩባንያው ቦንድ አው
ጥቶ መሸጥ ሲጀምር «የብሪቲሽ ኒው አፍ
ሪካን ኩባንያ» ቦንዱን በመግዛት በኩባን
ያው ውስጥ እጁን ሰደደ ። [30] በ1901 ገደማ
የእንግሊዝ ከበርቴዎች በኩባንያው ውስጥ
በሚገባ ሥር በመስደዳቸውና ቀስ በቀስም
ወደ መቆጣጠሩ ደረጃ በመድረሳቸው የእ
ንግሊዝ መንግሥት በቀጥታ የጂቡቲ አዲስ
አበባን የባቡር ሃዲድ በተቋረጠው ፈረን
ሣዊ ኩባንያ ውስጥ የጥቅሙ ተካፋይ እን
ዲሆን ጥያቄ አቀረቡ ። [31]

እንግሊዝም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም
በኢትዮጵያ ላይ የነበራትን የብዙ ጊዜ የጥ
ቅም ክልል የማድረግ ፍላጎቷን ለማሟላት
የጂቡቲ አዲስ አበባ የባቡር ሃዲድ በእንግ
ሊዝ ሱማሌ ውስጥ ካለችዋ ከዘይላ ወደብ
ጋር መያያዝ እንዳለበትና እንግሊዝም በሃ
ዲድ የመጠቀም መብቷ እንዲከበር ፤ ይህ
የማይሆን ከሆነ ግን ፣ ሀ/ የኩባንያው ባለቤ
ትነት የሁለቱ አገሮች ሆኖ በአስተዳደሩም
ቦርድ እንግሊዝ እንድትኖርበት ለ/ ፈረን
ሣይና እንግሊዝ በሃዲዱ በጋራ የመጠቀም
መብት እንዲኖራቸው ሐ/ የጂቡቲ ወደብ
ነፃ የሆነ ኢንተርናሽናል ወደብ እንዲሆን
በማለት ለፈረንሣይ ሃሳቧን አቀረበች ። [32]

እንግሊዝ ከራሷ ጥቅም አንፃር ተነስታ
በፈጠረችው ውዝግብ የተነሣ ኢትዮጵያ
የባቡሩ ሃዲድ ሥራ በፍጥነት ተጠናቆ በ
ሥራ ላይ ሲውል ሊኖራት የሚችለውን
ጥቅም ወደኋላ ጎቷተባት ። ከዚህም በላይ፣
ይህ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከታትና ኮንሲ
ሲዮኑን የሰጠችው ኢትዮጵያ ሆና ሳለና
ውይይቱም መደረግ ያለበት ከእርሷ ጋር
መሆን ሲገባው፡ ምንም ዓይነት መብት ሳይ
ኖራቸው ሁለቱ አገሮች ይህንን በማስመል
ከት ውዝግብ በመጀመራቸው፡ ሁኔታው በኢ
ትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደመግባት
ያህል ነበር ። ይህ ድርጊት እጅግ ያናደዳ
ቸው እቴ ምኒሊክ የእንግሊዝን ፣ የፈረንሣ
ይን ፣ የኢጣሊያንና የሩሲያን አምባሳደሮች
ሚያዝያ 5 ቀን 1905 ጠርተው በሃዲዱ ሥራ
ላይ እንግሊዝና ፈረንሣይ የፈጠሩትን ችግር
በማስመልከት «የባቡሩን ሃዲድ ሥራ አስ
ተማማኝ ለማድረግ የማንንም አገር እርዳታ
ሳልጠይቅ ወይም ሳልቀበል የሃዲዱን ሥራ
ራሴ ማካሄድ እገደዳለሁ» [33] በማለት ማስ
ጠንቀቂያ ሰጡ ። እብሪተኛው የእንግሊዝ
አምባሳደር የነበረው ጆን ሃሪንግተን ግን የሃ
ዲዱ ሥራ የሁሉም አገሮች ካፒታል ላለበት
የንግድ ኩባንያ ካልተሰጠ በስተቀር የኢት
ዮጵያ ነፃነት ዋስትና የማይኖረው መሆኑን
በማስመልከት ንግግር አደረገ ። [34] ይህ
የሚያሳየው የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም
ተቀናቃኙ የነበረውን የፈረንሣይ ኢምፔ
ሪያሊዝም ለማደናቀፍ ብቻ ሣይሆን ኢት
ዮጵያን በመዳፉ ውስጥ አስገብቶ ብዝበዛ
ውን ለማካሄድ ከመቋመጡ የተነሣ የአገሪ
ቷን ነፃነት ለመድፈር የቀጥታ ወረራንም
አልሞ እንደነበረ ነው ።

የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የአ
ውሮፓን ወዝአደር እየበዘበዙ ያካበቱትን
ካፒታልና ሸቀጥ የሚያውሉበትና የሚያ
ራግፉበት ፣ ለመበዝበዣ ኢንዱስትሪዎቻ
ቸውም የሚያገለግል ርካሽ ጥሬ ዕቃ በገፍ
የሚዘርፉበት ገበያ ለማግኘት ሲሉ የአፍሪ
ካን አህጉር ለመቀራመት ከፍተኛ ውድ
ድር አድርገዋል ። ይልቁንም አፍሪካን
በብሎክ (በቀጠና) ለመከፋፈል እርስ በራሳ
ቸው በፖለቲካና በወታደራዊ መስክ ከፍ
ተኛ ትግል አካሂደዋል ።

እንግዲህ በዚህ አንጻር ክፍፍሉ እንዲደ
ረግ የታቀደው ፣ ሀ/ ጀርመን ፣ ከአትላንቲክ

Digitized by Google

እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያለውን የአፍሪካ
ክፍል ፥ ለ/ፈረንሣይ ፥ ከሜዲትራኒያን ባሕ
ር እስከ ጊኒ ባሕረ ሰላጤ ፥ ከጊኒ ባሕረሰላጤ
እስከ ኤደን ባሕረ ሰላጤ ያለውን ክፍል ፥
ሐ/ፖርቱጋል ከአንጐላ እስከ ሞዛምቢክ
ያለውን ፥ መ/እንግሊዝ ፥ ከኬፕ ኦፍ ጉድ
ሆፕ እስከ ካይሮ ድረስ ያለውን ፥ ሠ/ ኢጣ
ሊያ ከቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ
ያለውን የአፍሪካ ክፍል በሥሩ በማድረግ
እያንዳንዱ ኢምፔሪያሊስት አገር አፍሪ
ካን በዞን (በቀጠና) ለመያዝ ነበር ። [35]

በዚህ ዓይነቱ ኢምፔሪያሊስታዊ ዕቅድ ኢ
ትዮጵያን ለማጠቃለል ይራወጡ የነበሩት አ
ገሮች እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ኢጣሊያ ነበሩ።
ሦስቱም አገሮች የእያንዳንዳቸውን «ድርሻ»
በቀጠና በመንደፍ ኢትዮጵያን በራሳቸው
የጥቅም ክልል ውስጥ አስገብተው የብዝ
በዛ መረባቸውን ለመዘርጋትና ኢምፔሪያ
ሊስታዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር በየፊና
ቸው ጥረት አድርገዋል ።

በደቡብና በምሥራቅ አፍሪካ የእንግሊዝ
ቅኝ ግዛት መሥራች የሆነው ከበርቴው
ሲ.ስል ሮድ ዋና ዓላማው አድርጎ
የተነሳው ኬፕ ታውንንና ካይሮን በባ
ቡር ሐዲድ በማገናኘት የብዝበዛ መዋቅ
ሩን ለማዋቀርና ሐዲድ የሚያልፍበትን
አገርና አካባቢ ሁሉ በእንግሊዝ የኢኮ
ኖሚ ምህዋር ሥር እንዲውል ለማድረግ
ነበር ። ሆኖም የሐዲዱ ሥራ ከኬፕ ታውን
እስከ ታንጋኒካ ፥ ከካይሮ እስከ ሱዳን
ቢደርስም በዕቅዱ መሠረት ሊቀጥል አል
ቻለም ። የዚህ ምክንያት የሐዲዱ መሥ
መር አቋርጦ ከሚያልፍባቸው አገሮች መ
ካከል የጀርመን ኢስት አፍሪካና ኢትዮጵያ
ስለሚገኙበትና የእነዚህ አገሮች በእንግ
ሊዝ ይዞታ ሥር አለመዋል ለታቀደው ዓላ
ማ ግብ መምታት ትልቅ ዕንቅፋት መሆኑ
ነው ። ሐዲዱ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ እን
ኳ በሆነው በነጭ ዓባይ ሸለቆ ውስጥ አቋ
ርጦ እንዳይሠራ ሸለቆው ረግረጋማ ሥፍራ
ስለሚበዛበት ለሥራው አመቺ አልነበረም።
ይህ ከበርቴው ሲስል ሮድም ሆነ እንግሊዝ
ከፍተኛ ጥቅም እናገኝበታለን ብለው ያመኑ
በት የሐዲድ ሥራ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ
የግድ ማለፍ እንዳለበት ሲታያቸው፣ የሚያ
ልፍበት አካባቢም በቁጥጥራቸው ሥር ማ
ዋል ያለበት መሆኑም ተገንዝበዋል ። ሆኖ
ም ይህ ዕቅድ በቀላሉ ተግባራዊ የሚሆን
አልነበረም ። ምክንያቱም ዕቅዱንና ዓላማ
ውን የምትዋጋው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን
በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት የነበራ
ትና ቀንደኛ ተቀናቃኟ የነበረችው ፈረ
ንሣይም ጭምር ስለነበረች ነው ።

በሌላ አነጋገር እንግሊዝ ከሰሜን አፍሪ
ካ ከግብጽ እስከ አሁኑ ደቡብ አፍሪካ ለመ
መሥረትና ኬፕ ታውንና ካይሮን በባቡር
ሐዲድ ለማገናኘት ስታቅድ ፥ ፈረንሣይ ደ
ግሞ በተቃራኒው ከምዕራብ አፍሪካ ከኮንጐ
ግዛት በወገቡ አቋርጦ የሚሔድ ግዛት እን
ደምትፈልግ ግልጽ አደረገች ። ይህም ማለ
ት ፈረንሣይ የምትፈልገው ከፈረንሣይ ኮ
ንጐ ጀ ምሮ በሱዳንና በታንጋኒካ (ታንዛኒያ)
መካከል የሚሠራውን የኬፕ ካይሮን የባ
ቡር ሐዲድ አቋርጦ ወደ ፈረንሣይ ሱማሌ
የሚደርስ ግዛት ነበር ። ይህ ዕቅድ ሁለቱን
ኃያላን ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በከ
ፍተኛ ደረጃ አፋጭቶአቸዋል ።

ፍጭቱ የተካሔደው በአካባቢው በአ
ካል በመገኘት ብቻ ሳይሆን በየአገራቸውም
ውስጥ በፖለቲካ መድረኮች ላይ የሚጐሸሸ
ሙና የማስጠንቀቂያ ምልክት ያላቸውን
ዲስኩሮች በማድረግም ነበር ። ኢ.ግሬይ
የተባለው የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ም/ሚ
ኒስትር በመጋቢት 28 ቀን 1895 በምክር
ቤቱ ውስጥ ባደረገው ዲስኩር ፥ የእንግ
ሊዝና የግብጽ የኢኮኖሚ ምህዋር የዓባይን
ወንዝና አካባቢውንም የሚያጠቃልል መ
ሆኑን ገልጾ ተቀናቃኙዋ ፈረንሣይም ይህን
አውቃ መቀበል እንዳለባትና ወደ ዓባይ
ወንዝ አካባቢም ልትልከው ያሰበችውን ቡ
ድን መላክ እንደሌለባት አስጠንቅቆአል ።

Digitized by Google

ይህ ፥ በተለይም ሰሜንና ምሥራቅ አፍ
ሪካን መቀራመቱን በማስመልከት ፥ በእን
ግሊዝና በፈረንሣይ መካከል የተፈጠረው
ኢምፔሪያሊስታዊ ውድድር ስምንት ዓመ
ታት (1896-1904) ያህል ሲወስድ ሁለ
ቱ አገሮች ለጦርነት ፍልሚያም የተዳረሱ
ባቸው ወቅቶች እንደነበሩም ይታወሳል ።
እንግሊዝ በሎርድ ኪቺነር የሚመራ ጦር
ከኡጋንዳ እስከ ፋሾዳ ያለውን የዓባይን ሸ
ለቆ እንዲይዝ በ1898 ከኦምዱርማን ወደ
ፋሾዳ ስትልክ ፥ ፈረንሣይም በሻምበል ማር
ቻንድ የሚመራ ወታደራዊ ቡድን ከፈረን
ሣይ ኮንጐ ወደ ፋሾዳ ልካ ነበር። እንዲሁም
ሌላው የፈረንሣይ ወታደራዊ ቡድን ከኢት
ዮጵያ ተነስቶ ወደ እዚሁ ቦታ እንዲያመራ
ታስቦ ነበር ። ቡድኑ ከአዲስ አበባ ሳይነሳ
በመቅረቱ በሁለቱ አገሮች ወታደራዊ
ቡድኖች መካከል የታሰበው ጦርነት ሳይ
ቀሰቀስ ቀርቷል ። እንዲያውም የፈረንሣይ
ወታደራዊ ቡድን ፋሾዳን ለቆ በመሔዱ
በዚህ አካባቢ ኢምፔሪያሊስታዊ ውድድር
ለጊዜው ጋብ ሊል ቻለ ።[36]

እንግሊዝ ፥ ፈረንሣይ በአፍሪካ ላይ የም
ትቀናቀናት በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን
በተለያየ አቅጣጫ መሆኑን በማጤን ከዓ
ባይ ወንዝ አካባቢ እንዳትደርስ ለማድረግና
ለመስፋፋት አመቺ ሁኔታ ሊፈጥርላት የሚ
ያስችለውንም መንገድ ለመዝጋት አንድ
ዕቅድ አወጣች ። በአፍሪካ ውስጥ በመስፋ
ፋት ተግባራቸው ላይ አዝጋሚነት የሚታ
ይባቸውንና ጥቅሟንም በመጻረር ረገድ በ
ጣም አደገኛ ናቸው የማትላቸውን ኢምፔ
ሪያሊስት አገሮች ፈረንሣይን በማጥቃቱ
ዘመቻዋ ተባባሪ ይሆኗት ዘንድ ፥ ቤልጅግ
ባሕር ኤል ገዛልንና አካባቢውን፥ ኢጣሊያ
ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት እንድታደርግ ተስ
ማማች ። ይህም ፈረንሣይን እጅግ አስቆ
ጣት ። ይሁን እንጂ እንግሊዝ የፈረንሣይ
ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባና ጥቅ
ሟንም እንዳታስፋፋ ከፍተኛ ጥረት ብታ
ደርግም ሊሳካላት አልቻለም ። በጂቡቲ አ
ዲስ አበባ የባቡር ሐዲድ መዘርጋት ምክን
ያትና ለኢትዮጵያም የውጭ ንግድ ቁልፍ
ሆነችው የጂቡቲ ወደብ በፈረንሣይ ቁጥ
ጥር ሥር በመሆኗ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊ
ዝም መሯሯጥ፥የፈረንሣይን የኢኮኖሚ የጥ
ቅም ክልል በተለይም በምሥራቅና በመ
ሐል አገር ኢትዮጵያ ላይ መስፋፋቱን በም
ንም ዓይነት አልገታውም ።

ይህ በዚህ እንዳለ ፥ የእንግሊዝ ኢምፔሪ
ያሊዝም በግብጽና በሱዳን ላይ የበላይነቱን
እየያዘ ሲመጣ ዓረቦች «የናይል ዕርጐ» እ
ያሉ የሚጠሩአት የኢትዮጵያ እስትራተጂ
ያዊነት በግብጽና በሱዳን ላይ ለዘረጋው የ
ብዝበዛ መረብ አስተማማኝነት ምን ያህል
ጠቃሚ እንደሆነ ይበልጥ ጕልቶ እየታየው
ሔደ ። ውልፍ እንዳለው በእንግሊዝ ኢም
ፔሪያሊዝም አመለካከት የኢትዮጵያ እስት
ራተጂያዊነት አንደኛ ፥ የዓባይ ወንዝ ምን
ጭ መገኛ በመሆኗና ሁለተኛ ፥ የባሕር ጠረ
ፍ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ መካ
ከል ያሉትን የኤደንንና የባብኤል መንደ
ብን ባሕረ ሰላጤዎች ያካለለች በመሆኗም
ነበር ። ከዚህም በስተቀር እንግሊዝ በሕን
ድ ላይ ያላትን ጥቅም ለማስከበር የሚያስ
ችላትን መሥመር ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ
እስትራተጂያዊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እ
ንዳለው በሚገባ ተመልክታው ነበር ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንድትወር ያደረገው ማ ደ ፋ ፈ ር

ስዊዝ ካናል ከተከፈተ በኋላ የፈረንሣይና
የእንግሊዝ ካፒታሊዝም በግብጽና አካባቢ
አገሮች ላይ ውድድር ሲጀምሩ የኢጣሊያ
ኢምፔሪያሊዝምም አለፍ ብሎ በኢትዮጵያ
በተለይም በቀይ ባሕር ጠረፍ ግዛቷ ላይ በ
1882 ገደማ እግሩን አሳረፈ ። የፈረንሣይን
ኢምፔሪያሊዝም ውጥረት ውስጥ የከተተ

Digitized by Google

ው የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምም ይህንን
እንደመልካም አጋጣሚ አድርጎ በመው
ሰድ ፈረንሣይ በኢትዮጵያና በአካባቢ አገ
ሮች ላይ ያደረባትን ፍላጎት እውን ለማድ
ረግ የምታደርገውን መሯሯጥ ለመግታት
ኢጣሊያንን መሣሪያ አድርጎ ይጠቀም ጀ
መር ።

ውልፍም ይህን በማስመልከት «ኢጣሊያ
በምጽዋ ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ አልነበራ
ትም ፤ ያለ እንግሊዝ ፈቃድና ስምምነት
ምጽዋን ልትይዝ አትችልም ነበር ። ይልቁ
ንም ኤም ኤቴንና ሌሎች ፈረንሣውያን ኢ
ጣሊያ ምጽዋን የያዘችው በእንግሊዝ ጋባ
ዥነት ነው ያሉትን እንቀበለዋለን ፤ »[37]
ብሎ ነበር ። እንግሊዝም ኢጣሊያ በኢ
ትዮጵያ ላይ ጥቅሟን እንድታስፋፋ የጋበዘ
ችውና ያደፋፈረችው ራሷ ኢትዮጵያን ቅኝ
ግዛት ለማድረግ ካለመፈለግ አንጻር ሳይ
ሆን፤በሰሜን በናሥራምቅ አፍሪካ ማለትም
በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ
አገሮች ላይም ይዞታዋ ሲረጋገጥ በኢትዮ
ጵያ ላይ አሁን ይዞታ እንዲኖረው ያደረገ
ችውን የኢጣሊያ ኢምፔሪያሊዝም በጦር
ኃይልም ቢሆን ወግታ ማባረር የምትችል
መሆኗን በቅድሚያ በመገምገም ነበር።ከዚ
ህም በቀር ፣ የኢጣሊያ የቀይ ባሕር አካባ
ቢን መያዝ ፣ የእንግሊዝ ካፒታሊዝም በግ
ብጽ ውስጥ ሥር እየሰደደና ወደ ሱዳንም
እየገፋ በመምጣቱ የተቆጣችው ፈረንሣይ
ወደ ሰሜን እየዘለቀች ቅኝ ግዛት እንዳታስ
ፋፋ ስለሚያደርጋትና ይህም ለእንግሊዝ
ሱዳንን መያዝ ጥሩ አጋጣሚ እንደሚሆን
እንግሊዝ ታምን ነበር ።[38]

በ1882 ገደማ ፣ የእንግሊዝ አርቢ ፓ
ሻን መሣሪያ አድርጎ ግብጽን በጥገኛነት
መያዝ ለሱዳን መሐዲዎች ጥሩ አጋጣሚ
ሰጣቸው ። የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም
ግብጽን በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ ቀድሞ
በግብጽ ተወራ በነበረችው ሱዳን ላይ ቅኝ
አገዛዝን ለመዘርጋት ሲሞክር ከፍተኛ ተቃ
ውሞ ስለገጠመው በእንግሊዛዊው ጄኔራል
ዊሊያም ሂክስ የሚመራ 10 ሺህ ጦር ወደ
ሱዳን ላከ።ሆኖም ቅኝ አገዛዝ የመረራቸው
መሐዲዎች ኃይላቸውን በማስተባበርና በ
ማጠናከር ስለገጠሙት የሒክስን ጦር እን
ኮታኩተው ጣሉት ። ይሁንና ፣ ሱዳን የግ
ብጽ ቅኝ ግዛት ስለነበረች አሁንም የእኔ
መሆን አለባት ብሎ የተነሳው የእንግሊዝ
ኢምፔሪያሊዝም የሁኔታዎችን መመቻ
ቸት ሲጠብቅ ቆየና እንደገና በ1885 በእ
ንግሊዛዊው ጎርዶን የተመራ ጦር ወደ ሱ
ዳን ላከ ። የጎርዶን ጦርም ከደርቡሾች ጋር
ገጠመና ድል ተመታ ። ጎርዶንም በጦር
ነቱ ላይ ተገደለ ። ይህ የደርቡሾች በኢም
ፔሪያሊዝም ጦር ላይ ድል እየተቀዳጁ መ
ምጣት የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም ከከ
ፍተኛ ሥጋት ላይ ጣለው ። በሱዳን ውስጥ
በስድስት ከተሞች ላይ መሽጎ ይኖር የነበ
ረው የግብጽ ጦር እንዲሁም ባለሥልጣና
ችና አንዳንድ አውሮፓውያን የድል ባለ
ቤት በሆነው የሱዳን ጦር ተከበቡ ። የግብ
ጽን ሰፊ ሕዝብ መመዝበር የጀመረው የእ
ንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምም በራሱ ጥረት
ብቻ የተከበበውን የግብጽ ጦርም ሆነ አው
ሮፓውያንን ማዳን የማይችል መሆኑን ሲገ
ነዘብ ፤ ሬር አድሚራል ዊሊያም ሂዌትን
ከአፄ ዮሐንስ ወታደራዊ ዕርዳታ እንዲጠ
ይቅ ወደ ኢትዮጵያ በአፋጣኝ ላከ ።

ሂዌትም ሰኔ 3 ቀን 1884 ከአፄ ዮሐ
ንስ ጋር ኢትዮጵያ ለእንግሊዝ ወታደራዊ
ዕርዳታ የምታደርግበትን ሁኔታ ከተነጋገረ
በኋላ ከዚህ በሚከተለው አኳኋን ከስምም
ነት ላይ ደረሱ ። ይኸውም 1. በሱዳን ወሰን
በኩል ግብጾች ይዘውት የነበረው ቦገስ
የተባለው ግዛት ለኢትዮጵያ እንዲመለስ ፤
2. ኢትዮጵያ የንግድ ሸቀጥም ሆነ የጦር መ
ሣሪያ በእንግሊዝ ዋስትና በምጽዋ ወደብ
በኩል እንድታስመጣ ፤ 3. ቦገስ በተባለው
ግዛትና አካባቢው ውስጥ የግብጽ ወታደ
ሮች ይዘዋቸው የነበሩት ሕንጻዎችና ምሽ

Digitized by Google

ጐች እንዳሉ ኢትዮጵያ እንድትረከባቸው
ሲሆን ፤ በአጸፋውም ኢትዮጵያ ከሰላ ፤ አም
ደብ ፤ መተማ ፤ አልጌደን ፤ ከረንና ጌሊ ላይ
ተከቦ የነበረውን ጦርና ሌሎችንም ሰዎች
መሐዲዎችን ወግታ በምጽዋ በኩል እንድ
ታስወጣ ነበር ። ሆኖም በስምምነቱ መሠ
ረት በራስ አሉላ አባ ነጋ የተመራው የኢት
ዮጵያ ጦር ወደ ተጠቀሱት ከተሞች ሔዶ
መሐዲዎችን በመውጋት ተከቦ የነበረውን
ጦር ከስድስቱም ከተሞች በነጻ አስወጥቶ
በምጽዋ በኩል ወደ ግብጽ ሲልክ እብሪተ
ኛዋና ተስፋፊዋ እንግሊዝ ግን ስምምነቱን
ፈጽማ ሳታከብር ቀረች ። የእንግሊዝ ካቢኔ
በምስጢር ባደረገው ስምምነት መሠረት
የፈረንሣይን በአፍሪካ ውስጥ መስፋፋት
ለመግታት የሚል ሰበብ ሰጥቶ የምጽዋን
ወደብና አካባቢዋን ለኢጣሊያዊው ጄኔ
ራል ሬር አድሚራል ኬይሚ የካቲት 3 ቀን
1885 እንዲሰጥ አደረገ ። [39]

ይህን የ1884ቱን ስምምነት ጠለቅ ብ
ለን ስንመለከተው ልንረዳው የምንችለው
እንግሊዝ ገና ከመጀመሪያው ተንኮልና ደባ
አስባ የተዋዋለችው እንደነበር ነው ። ምን
ም እንኳ ውሉ በወደቡ አካባቢ የውጭ ኃይ
ል እንደማይኖር ቢጠቁምና በሌላም አነጋ
ገር የኢትዮጵያ ይዞታ መሆኑን ቢያሳይም ፣
«በእንግሊዝ ዋስትና . . . መላክም ማስ
መጣትም ትችላለች» የሚለው ግልጽ ያል
ሆነ ሐረግ በእንግሊዝ በኩል ሆን ተብሎ
የገባ ከመሆኑም በላይ ፤ እንግሊዝ በምጽዋ
ወደብ ላይ የሆነ ሥልጣን እንዲኖራትና አ
ጋጣሚም ስታገኝ ኢትዮጵያን ለመውረር
ወይም ለማስወረር እንዲያስችላት ያቀደ
ችው ነበር ። ይህም ቢሆን ቅሉ እንግሊዝ
የምጽዋን ወደብና አካባቢዋን ለሌላ ኢም
ፔሪያሊስት አገር አሳልፎ የመስጠት መብ
ት እንዳላት ስምምነቱ ፈጽሞ አያሳይም ።
አፄ ዮሐንስም መጀመሪያ የጠየቁት የም
ጽዋ ወደብ ከማንኛውም ወራሪ ኃይል ነጻ
ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ነበር።«በእ
ንግሊዝ ዋስትና» የሚለውንም ሐረግ አፄ
ዮሐንስ የተረዱት በእንግሊዝ የበላይ ተቆጣ
ጣሪትነና ሥልጣን ሥር ሳይሆን ሌላ ወራሪ
ኃይል ምጽዋን እንዳይዝና እንዳይወር የእን
ግሊዝ ዕርዳታ እንደሚደረግላት ነው ማለ
ት ይቻላል ።

ሆኖም «ወርቅ ላበደረ ጠጠር» እንደሚ
ባለው ሁሉ ኢትዮጵያ ስምምነቱን በማክ
በር ከፍተኛ የሰው ሕይወት መስዋዕትነት
የከፈሉ ጦርነቶችን አካሂዳ ወራሪ የነበረ
ውን የግብጽ ጦርና የአውሮፓን ኢምፔሪ
ያሊዝም የጥፋት መልእክተኞች የነበሩትን
አውሮፓውያን ከመሐዲዎች ከበባ አድና
በሰላም ለእንግሊዝ ስታስረክብ ፤ እንግሊዝ
ያደረገችው ውለታ ግን ለወራሪው የኢጣ
ሊያ ኢምፔሪያሊዝም የባሕር ጠረፋችንና
ወደባችንን አሳልፎ መስጠት ነበር ። ይህም
ፍጹም ክህደት ነበር። ይህ አድራጐት እጅግ
ያሳዘነውና ያበሳጨው በኢትዮጵያ የእን
ግሊዝ ቆንሲላ የነበረው ኤ.ቢ. ዋይልድ ፦
በማንኛውም ለመለካከት ለንፃር በአጼ
ዮሐንስ ላይ የተፈጸመውን ድርጊት ተመል
ከቱ ፤ ለንዲት ቀንጣት እምነት እንኳ ለያሳ
ይም ፣ በእኔ ለስተያየት በለፍሪካ ውሰጥ ከ
ፈጸምናቸው ለያሌ ወንጀሎች መካከል እጅ
ግ ለስከፊ ከሆኑት ለንዱ ይህ ነው ። ... እን
ግሊዝ ለጼ ዮሐንስ ማንኛውንም ለገልገሉት
እስኪሰጡ ድረስ ከተጠቀመችባቸው በኋላ
ለኢጣልሊያ በችሮታ ለሳልፋ ሰጠቻቸው ።
ሐቁ ግን ለእንግሊዝ ሰፊ ሕዝብ ተደብቆ
ለል ። ስማችን እንዳይጠፋ ይህ እውነት
ባይሆን ኖሮ በወደድኩ ነበር ። ግን እንዳ
ጋጣሚ ሆኖ ይህ እውነት ነው ። ይህ በ18
ኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ በለፍሪካ ወይም
በሕንድ ውስጥ ከተፈጸመው ክህደት ሁሉ
የበለጠና ለስከፊ ከሆኑት መካከል ለንዱ
መሆኑን ያሳያል ፤ [40] ብሎ ነበር ።

ይህ በራሷ ዜጋና ጥቅሟን እንዲያስከብር
በላከችው ቆንሲላዋ ስለ እንግሊዝ ኢምፔ
ሪያሊዝም ሥውር ደባና ተንኮል የተሰጠው
ምስክር ፤ እንግሊዝ በጊዜው እንደ ኢትዮ
ጵያ ካሉ አገሮች ጋር ስታደርገጋቸው የነ

Digitized by Google

በሩ ውሎችና ስምምነቶች መሸንገያና መደለያ ከመሆናቸውም በላይ የምታከብራቸውም የብዝበዛና የጭቆና ፍላጐቷን እስከረኩላት ድረስ መሆኑን በግልጽ ያሳያል ።

በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም አጋዥነትና አደፋፋሪነት በምጽዋ ወደብ አካባቢ እጁን ያስገባው የኢጣሊያ ኢምፔሪያሊዝም ቀስ በቀስ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ለመስረግና መሐል አገሩንም በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ በማሰቡ በ1887 ሲ. ሰለምበት የተባለውን ኢጣሊያዊ «የንግድ ቡድን» እየመራ ከምጽዋ 50 ማይልስ ያህል ራቅ ብሎ ወደ መሐል አገር ዘልቆ እንዲገባ አደረገ ። ሰለምበትም በራስ አሉላ ሰዎች ተያዘና ታሠረ ። በምጽዋ የነበሩት ኢጣሊያኖችም መታሠሩን ሲሰሙ ጦር መርተው መጥተው ከራስ አሉላ ጋር ዶጋሊ ላይ ገጠሙና ድል ተመቱ፣ 50 ኢጣሊያኖችም በጦርነቱ ተገደሉ ።

ከዚህ በኋላ ራስ አሉላም ኃይላቸውን አጠናከረው ምጽዋን ለማስለቀቅ ቆርጠው መነሳታቸውንና ኢጣሊያኖችም ዶጋሊ ላይ ድል መመታታቸውን እንግሊዝ ስትሰማ ፣ የጠነሰሰችው ተንኮልና ደባ ግቡን ሳይመታ ሊከሽፍ ነው ብላ በመደናገጥ በአስቸኳይ ጌራልድ ፖርታልን ወደ ኢትዮጵያ ላከች ። ፖርታልም ሁለቱን መንግሥታት ለማስታረቅና በአካባቢውም ሰላምን ለማስፈን በሚል ሰበብ ከንግሥት ቪክቶሪያ ለአፄ ዮሐንስ የተጻፈ ደብዳቤና ለራስ አሉላም ጭምር የተላከ ስጦታ ይዞ መጣ ።[41]

ፖርታል ኅዳር 1887 ከራስ አሉላ አባነጋ ጋር አሥመራ ላይ በተገናኘ ጊዜ የመጣበትን ትክክለኛ ሐሳብና ለንጉሡ የተጻፈውን ደብዳቤ እንዲነግራቸውና እንዲያሳያቸው ራስ አሉላ ቢጠይቁት አሻፈረኝ፣ ስላለ «የመጣኸው ስለኢጣሊያኖች ጉዳይ መሆኑን አውቃለሁ. . .ኢጣሊያኖች ወደ ሰሀቲ መምጣት የሚችሉት ራስ አሉላ የሮም ገዥ ሲሆን ብቻ ነው. . .ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ ድል መትቻቸዋለሁ ። እንደገና ከመጡም አሁንም ድል እመታቸዋለሁ ። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው ። የንጉሡ (የአፄ ዮሐንስ) ወዳጅ ነኝ እያለች የምታታልለዋ እንግሊዝ ምጽዋን ለኢጣሊያ አሳልፋ ሰጥታለች ፤ »[42] በማለት እንግሊዝ የፈጸመችውን ደባና አሁን ደግሞ ጠንስሳ የላከችውን ተንኮልና የመሸንገያ ሐሳብ ትክክለኛ ገጽታውን በማጋለጥ መልእክተኛውን የሀፍረት ማቅ እንዲከናነብ አድርገውታል ።

ከዚህም በቀር ብልሁ ጀግና ራስ አሉላ የፖርታል አመጣጥ ተንኮል ያለበት መሆኑን በሚገባ በመገንዘብ እርሱን ከመንገድ መሪ ጋር ወደ አፄ ዮሐንስ ከላኩት በኋላ ፖርታል የመጣው ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር በሚያደርጉት ጉዞ ዕርዳታ ለመስጠትና የእንግሊዝም ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ላይ በመሆናቸው ለዝግጅት ጊዜ እንዲያገኙ ለማድረግ መሆኑን ገልጸው ፣ እንዲሁም የፖርታል ቡድን እንደጠላት እንጂ እንደ ወዳጅ መታየት እንደሌለበት የሚያሳስብ ደብዳቤ ጽፈው በጉን መልእክተኛ ወደ አፄ ዮሐንስ ልከዋል ።[43]

አፄ ዮሐንስም ቢሆኑ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም የ1884ቱን ስምምነት ጥሶ የፈጸመውን ደባ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት አሁን ላቀደው ወጥመድ የሚበገሩ አልነበሩም ። ለአፄ ዮሐንስ ከንግሥቲቱ የተጻፈው ደብዳቤ የያዘው ሐሳብ ሀ/ በአሳወርታና በሃባብ ብሔረሰቦች (በአሁኑ ኤርትራ ክ/ሀገር ውስጥ ያሉ ብሔረሰቦች) ላይ ኢጣሊያ የመቆጣጠር መብት (Protectorate) እንዳላት ኢትዮጵያ አውቃ እንድትቀበል፥ ለ/ ሰሀቲና ውያ የኢጣሊያ ግዛቶች ሆነው ከነዚህም ጀምሮ ወደ መሐል አገር የአንድ ቀን መንገድ ያህል የሚያስኬደው አገርም በተጨማሪ ግዛትነት ለኢጣሊያ እንዲሰጥ ፣ ሐ/ጊንዳ በኢትዮጵያ እጅ ሆና እንደወሰን እንድትሆንና ሁለቱም ወገኖች ድንበር ተ

ካለው በእንግሊዝ አስማሚነት እንዲዋዋሉ
መ/ ሰንሂት የኢጣሊያ ግዛት እንድትሆን፤
ሠ/ ኢትዮጵያና ኢጣሊያ የሰላም የወዳጅነ
ትና የንግድ ውል እንዲፈራረሙና ኢጣሊ
ያም በኢትዮጵያ ላይ ወረራ እንዳታደርግ
የሚጠይቅ ሲሆን ፤ የውሉንም መከበር እን
ግሊዝ እንድትቆጣጠር» የሚል ነበር ።[44]
ከዚህም በስተቀር ራስ አሉላ ለእንግሊዝም
ሆነ ለኢጣሊያ ተስፋፊነት ትልቅ ዕንቅፋ
ት መሆናቸውን በሚገባ የተገነዘበው ፖር
ታል ራስ አሉላ ከባሕረ ነጋሽ ግዛታቸው
ተሸረው ወደ መሀል አገር ቢሾሙ በኢት
ዮጵያና በኢጣሊያ መካከል ሰላም የሚወ
ርድ መሆኑን ለአፄ ዮሐንስ በመግለጽ ለማ
ሻር ሞክሮ ነበር ።[45]

ፖርታልም አፄ ዮሐንስን ለማግባባት
ያደረገው ሙከራ ሁሉ መክሸፉን የተረዳው
ላቀረበው ድርድር አፄ ዮሐንስ «ይህንን
ሁሉ በምንም ዓይነት አላደርገውም ፤ ከአ
ድሚራል ሂዌት ጋር ባደረግነው ስምምነት
መሠረት ግብጾች ይዘውት የነበረው የቀድ
ሞው የኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ለእኔ እንዲመ
ለስልኝ በእንግሊዝ ጠያቂነት ተስማምተን
ነበር ። አሁን እንደገና ያንኑ ግዛት መልሼ
ለኢጣሊያ እንድለቅ ትጠይቁኛላችሁ ፤ . .
ከእንግዲህ ወዲያ ግን ግዛቴን በምንም ዓይ
ነት ለባዕድ አሳልፌ ለመስጠት ፍላጐትም
ሥልጣንም የለኝም ፤ »[46] የሚል ቁርጠኛ
መልስ በሰጡበት ጊዜ ነበር ። ከዚህም
በስተቀር አፄ ዮሐንስ የ1884ቱን ስም
ምነት እንደገና ከማጽደቅ በቀር ሌላ የሚ
ፈርሙት ምንም ዓይነት ውል እንደሌለ
በመግለጽ ለአገራቸው ነጻነት የሚሰው መ
ሆኑን በማያወላውል ሁኔታ አረጋግጠው
ታል ።

እንግሊዝ አፄ ዮሐንስ ከኢጣሊያ ጋር
እንዲዋዋሉ ያቀረበችው የስምምነት ሐሳብ
በመሠረቱ ኢጣሊያ በብቸኝነት የኢትዮጵ
ያን ግዛት ቀርሳ እንድትወስድና የተጽዕኖ
ክልሏንም እንድታስፋፋ የሚያስችላት መ
ስሉ በአብዛኛው ቢታይም ፥ ስምምነቱ በሁ
ለቱም ዘንድ የሚኖረውን ተፈጻሚነት የመ
ቆጣጠር መብት ለእንግሊዝ ስለሚፈቀድ
ላት በማንኛውም ጊዜ ጣልቃ ለመግባት
አመቺ መንገድ ነበራት ማለት ነው ። ይህ
ም ማለት በኢትዮጵያም ሆነ በኢጣሊያ በ
ኩል ተፈጻሚነቱ ጐድሎ ውዝግብ ቢነሳ
እንግሊዝ ይህን እንደበቂ ምክንያት አድ
ርጋ በመነሳት ጣልቃ ለመግባትና ለመው
ረር ስለሚያስችላት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት
የማድረጓ አጋጣሚ ሰፊ ነበር ለማለት ይቻ
ላል ።

የሆነ ሆኖ በወጥመዱ ውስጥ ኢትዮጵያ
ሳትገባ በመቅረቷ የተሸረበውም ተንኮል
አልያዘም ። ከዚህ በኋላ እንግሊዝ የኢትዮ
ጵያን የፖለቲካ ፤ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ
ሁኔታ በመከታተል እየገመገመችና ጊዜና
ተጨባጭ ሁኔታንም እየጠበቀች በኢትዮ
ጵያ ውስጥ የሚፈጠረውን የመንግሥት ለ
ውጥ ለመጠቀም መሞከሯ አልቀረም ። በ
ተለይም ለዚህ ለድብቅ ዓላማዋ መሳካት ኢ
ጣሊያን ጥሩ መሣሪያ አድርጋ በመጠቀም
በኢትዮጵያ ላይ የተደጋገመ ወረራና ጥቃት
እንዲደርስ አድርጋለች ።

ኢጣሊያ ግንቦት 2 ቀን 1889 የተፈረ
መውን የውጫሌን ውል 17ኛውን አንቀጽ
ፀቅኝ ግዛት ፍላጐቷ እንጻር አጣማ « ኢት
ዮጵያ የእኔ ጥገኛ ናት » ብላ ስታውጅ ፥
ኢትዮጵያም ይህንን በመቃወም የውሉን
ትክክለኛ መንፈስ ለዓለም ሕዝብና መን
ግሥታት አስታወቀች ። ይሁን እንጅ እን
ግሊዝ ይህንን በሚገባ ተረድታ ሳለ ከኢ
ጣሊያ ጋር ሀ/ መጋቢት 24 እና ሚያዝያ
15 ቀን 1891 እና ለ/ ግንቦት 5 ቀን 1894
ባደረገቻቸው ስምምነቶች መላዋ ኢትዮ
ጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ወይም የጥቅም
ክልል እንድትሆን ፤ የዓባይ ምንጭ አካባ
ቢና ሸለቆ ግን በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር
እንዲውል ተዋውላለች ። ከዚህም በቀር
እንግሊዝ በዘይላ ወደብ አካባቢ የኢኮኖ
ሚና የፖለቲካ ሥልጣን ክልል ስለመሠ

ተች እንግሊዝ በሐረርና በአካባቢዋ ላይ የጣልቻ ገብነት መብት እንዲኖራት ኢጣሊያ እንደምትፈቅድ ስምምነቱ ይጠቅሳል።

እነዚህንና ሌሎችንም ሥውር ዓላማዎቿን ተግባራዊ ለማድረግ እንግዝ ለኢጣሊያ የምትሰጠው ድጋፍና ማደፋፈር ቀላል አልነበረም ። በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረኮችም ቢሆን አጋጣሚ እየፈለገች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እውነተኛ የኢምፔሪያሊስት ፍላጐቷን ኢጣሊያን ሽፋን በማድረግ መግለጧ አልቀረም ። በ1894 የአፍሪካ ካርታ በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃጅነትና ስምምነት በኢሄርስሌት አሳታሚነት ታትሞ ሲወጣ «ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ናት» ለማለት በአረንጓዴው ቀለም ካርታዋ ተቀብቶ ወጥቶአል ። ምክንያቱም ያን ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ናቸው የተባሉት ሁሉ ካርታቸው በአረንጓዴ የተቀባ ነበርና ።[47] የዚህ ጽሑፍ ሁለተኛው ክፍል በሚቀጥለው መጽሔት ይቀርባል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Woolf, L.S. *Empire and Commerce in Africa: A Study in Economic Imperialism*, Howard Fertig, New York, 1920, p. 145.
2. Bruce, James, *Travels to Discover the Source of the Nile*... G.G.J. and J. Robinson, Paterin Oster-Row, Edinburgh, MDCCXC.
3. *Ibid.*, Vol. I, pp. 1-8.
4. *Ibid.*, Vol. III, pp. 1-2.
5. Dafton, Henry, *Narrative of a Journey through Abyssinia* 2nd. ed., Chauman and Hall, London, 1867, p. V.
6. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ፤ ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ ፤ አዲስ አበባ ፤ 1965 ፤ 2ኛ እትም ፤ ገጽ 323
7. Salt, Henry, *Voyage to Abyssinia and Travels*... F.C. and J/Rivington, London, 1814, p. 268.
8. *Ibid.*, p. 267.
9. Abir, M., *Ethiopia and the Era of Princes*... 1769-1855 Longmans, London, 1968, pp. 34-35.
10. Hotten, J.C. *Abyssinia and Its People*... Negro University Press, New York, 1868, pp. 69-76.
11. *Ibid.*, p. 76.
12. OP. Cit., Woolf, LS, p. 175.
13. *Ibid.*, p. 176.
14. Jones, A.H.M. and Monroe E, *History of Ethiopia*, Univ. Pr., London, 1935, p. 129.
15. Pankhrust, E. S. *Eritrea on the Eve*, New Times and Ethiopian News "Bks., Woodford, 1962, p. 25.
16. Op. Cit., Jones A.H.M. and Monroe E., p. 130.
17. OP. Cit., Pankhrust, E.S. pp. 25-27.
18. *Ibid.*, p. 28.
19. OP. Cit., Woolf, LS, p. 146.
20. *Ibid.*, p. 144
21. OP. Cit., Pankhrust, E.S. pp. 31-39.
22. *Ibid.*, p. 29.
23. OP. Cit., Woolf ,LS, p. 149.
24. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ አዲስ አበባ ፤ ገጽ 36—37
25. OP. Cit., Pankhrust, E.S. p. 30.
26. OP. Cit. Woolf, LS, pp. 155-156.
27. *Ibid.*, p. 167.
28. *Ibid.*, pp. 199-200.
29. *Ibid.*, p. 203.

Digitized by Google

30. Marcus, H.G. *The Life and Times of Minilik, II; Ethiopia* 1844-1913. Clarendon Pr., Oxford, 1975, p. 201.

31. OP. Cit., Woolf, LS, p. 214.

32. *Ibid.*, p. 214.

33. *Ibid.*, p. 215.

34. *Ibid.*, p. 216.

35. *Ibid.*, p. 174.

36. *Ibid.*, pp. 183-190.

37. *Ibid.*, p. 160.

38. Burns, Emile, *Abyssinia and Italy*, London, 1933, p. 37.

39. OP. Cit., Pankhrust, R.S. pp. 36-37.

40. Wylde, A.B. *Modern Abyssinia*, p. 39.

41. Portal, G.H., *English Mission to Abyssinia*, Warren, Winchester, 1887, p. 8.

42. *Ibid.*, p. 38.

43. *Ibid.*, p. 41.

44. *Ibid.*, p. 75.

45. *Ibid.*, p. 71.

46. *Ibid.*, p. 37.

47. OP. Cit., Woolf, LS, p. 171.

Digitized by Google

አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ

ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

በዘመናችን በዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝብ ዘንድ በጉልህ የሚታየው አንዱ ችግር በአፍሪካ አህጉር በደቡባዊው ጫፍ ተንሰራፍቶ የሚገኘው የጥቂት ነጮች ዘረኛ መንግሥት የዘረጋውና «አፓርታይድ» በመባል የሚታወቀው ኢሰብአዊ ፖሊሲ ነው ፡፡

አብዛኞቹ የአፍሪካ ሕዝቦች ለረጅም ዘመናት ሰብአዊ ክብራቸውንና ብሔራዊ ሕልውናቸውን በቅኝ ገዥዎች ተነጥቀው ከኖሩ በኋላ ባካሄዱት መራራ የአርነት ትግል የብሔራዊ ነፃነታቸውን ተጐናጽፈዋል ፡፡ ይሁንና ለብዙ ዘመናት በደቡብ አፍሪካ ሠራተኛ መደብና ጭቁን ሕዝብ ላይ ተጭኖ የነበረው የቅኝ አገዛዝና የዘረኝነት ፖሊሲ አሁንም የከፋ መልኩን ይዞ ይገኛል ፡፡

የደቡብ አፍሪካ ጥቂት ነጮች መንግሥት ዘረኝነትን ይፋ የፖለቲካ መመሪያው አድርጐ በመነሳት በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ጥቁሮች ፣ ክልሶችና ሕንዶች ላይ ኢሰብአዊ ድርጊት በመፈጸም የዘር አድልዎን ቀንበር ከጫነባቸው ከ30 ዓመታት በላይ ሆኗል ፡፡ በዚህ የጭቆና አገዛዝ ሥር የሚኖሩ ጥቁር አፍሪካውያን ሠርቶ አደሮች ለደቡብ አፍሪካ ባለኢንዱስትሪዎችና አጋሮቻቸው ለሆኑ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ትርፍ ለማስገኘት ፣ የሥራ ኃይላቸውን በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡና አልፎም በነፃ እንዲሠሩ ተገደዋል ፡፡ እነኝህ ጭቁናች ዘረኛውን መንግሥት በየጊዜው በሚያወጣቸው ደንቦች አማካይነት መሠረታዊ የሆኑ ሰብአዊ መብቶቻቸውን ተገፈው በገዛ አገራቸው ተዋርደዋል ፡፡ የግፍ አስተዳደር አንገፍግፏቸው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ በሻርፕቪልና በሰዌቶ እንዳደረገው ዓይነት ጭፍጨፋ ያካሄድባቸዋል ፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአፓርታይድ ፖሊሲ አራማጅ የሆነው የጥቂት ነጮች መንግሥት ያለ ምክንያት የተፈጠረ አይደለም ፡፡ በደ

Digitized by Google

ቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙትን የጥቂት ነጮች አመጣጥና ዛሬ የአፓርታይድ ፖሊሲ ደጋፊ የሆኑ አገሮችን ኢኰኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ስንመለከት ፣ በደቡብ አፍሪካ ሰፍኖ የሚገኘው ዘረኝነት ከቅኝ አገዛዝና ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ ጋር የተያያዘ ክስተት መሆኑን እንገነዘባለን ።

ኢምፔሪያሊስቶች ባልጠበቁት ፍጥነት የአፍሪካ ፣ የላቲን አሜሪካና የእስያ ሕዝቦች ከፍተኛ መሥዋዕትነትን በመክፈል ብሔራዊ ነፃነታቸውን ለመጐናጸፍ በቅተዋል ። አንዳንዶቹም በብሔራዊ ነፃነታቸው ብቻ ሳይገደቡ ጭቆናና ብዝበዛ የሌለበትን ሥርዓት ለመመሥረት በመታገል ላይ ናቸው ። ይህ ሁሉ ተጋድሎ ሲደረግ ቅኝ ገዥዎች መሸነፋቸውን በዝምታ አልተቀበሉትም ። ይልቁንም የነጮች ክምችትና ድርጅት የተጠናከረበትን ደቡብ አፍሪካን የመጨረሻ ምሽጋቸው በማድረግ እጅግ አስከፊ የሆነውን የአፓርታይድን ፖሊሲ በመደገፍ ላይ ናቸው ።

በደቡባዊ አፍሪካ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ለረጅም ዘመናት ሲማቅቁ ከነበሩት አገሮች መካከል ዚምባብዌ ፣ አንጐላና ሞዛምቢክ ዛሬ ብሔራዊ ነፃነታቸውን አግኝተው ለኢኰኖሚና ፖለቲካ ነፃነታቸው በመታገል ላይ ይገኛሉ ። የኢምፔሪያሊስት ምሽግ በሆነችው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኘው ምዝብር ሕዝብም የነዚህን ሕዝቦች ፈለግ በመከተል የአፓርታይድን ፖሊሲ በመዋጋት ፣ ብሎም እስከ መጨረሻ ደምስሶ በአገሪቷ ውስጥ ፍትሕ ፣ ሰላምና እኩልነት እንዲሰፍን ለማድረግ ከዘረኛው ለማ ድረግ መንግሥት ጋራ የከረረ ውጊያ በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

በዚህ ጽሑፍ የአፓርታይድን ፖሊሲ አስከፊ ገጽታዎች ፣ የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች (ትራንስናሽናል ኩባንያዎች) ከደቡብ አፍሪካ ሽብር ፈጣሪ መንግሥት ጋር በመሆን በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ላይ የሚያካሄዱትን ዘረፋና የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል በአጭሩ ለመዳሰስ እንሞክራለን ።

የነጮች በደቡብ አፍሪካ መስፈር

የምዕራባውያን የጭቆና ቀንበር የተጫነው አፍሪካ በርካታ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ፣ የገዥዎች መለዋወጥና የርስ በርስ ጦርነት ሲፈራረቁበት የኖረ አህጉር ነው ። ከዚህም ጋራ በባሪያ ንግድና በሃይማኖት ግጭት ሲሰቃይ ኖሯል ። ሕዝቡ እንደ ሸቀጥ ወደ ሌላ ዓለም እየተጋዘ ሲሸጥና ሲለወጥ ነበር ። የተፈጥሮ ሀብቱና የሥራ ፍሬው ተዘርፏል ። ቀስ በቀስም አንዳንድ ቅኝ ገዥዎች ሥር እየሰደዱ ነዋሪዎች ለመሆን በቅተዋል ። ይህንን ሁሉ ለማድረግ የበቁትም በቀላሉ አይደለም ። ብዙ ሕዝብ ጨርሰዋል ፤ ብዙ ደምም አፍስሰዋል ።

የአውሮፓ ኰሎኒያሊስቶች በአፍሪካ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የምዝበራ መረባቸውን ከዘረጉ ጊዜው ረዘም ያለ ነው ። እነዚህ ተስፋፊዎችና ወራሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሩቅ ምሥራቅ ይወስድ የነበረውን የባሕር መስመር ለመቀየስ ሙከራ ባደረጉ ጊዜ በቅድሚያ ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ ተብሎ በሚጠራው ወደብ በኩል ዘልቀው ለመሄድ የሚያስችለውን የባሕር መንገድ አገኙ ። ይህንኑ ጉዞ ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመሩት ፖርቱጋሎች ነበሩ ። በ15ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ በርተሎሚዮ ዲያዝ ይባል የነበረ ፖርቱጋላዊ መርከበኛ ጉዞውን እንደጀመረ በ1488 * አግረ መንገዱን በደቡብ አፍሪካ ባሕር ዳርቻ መልሕቅ አስጣለ ። ከዚሁ ጊዜ እንስቶ ደቡባዊው የአፍሪካ ክልል ወደ ሩቅ ምሥራቅ ይወስድ ለነበረው

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምሕረቶች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

የባሕር ላይ ጉዞ በፖርቱጋልና በሆላንድ ከበርቴ ነጋዴዎች መያዝ ጀመረ። በጊዜው ምዕራባውያን ከበርቴ ነጋዴዎች ወደ ሩቅ ምሥራቅ በመመላለስ ከፍተኛ የንግድ ግንኙነት በመመሥረት ላይ ስለነበሩ የሥፍራውን ምቹነት በመገንዘብ በየጊዜው እየተሰባሰቡ በአካባቢው መጠናከር ጀመሩ። ከፖርቱጋሎች ቀጥለው ደቾችም ለተመሳሳይ ዓላማ የባሕር ላይ ጉዞ እንደጀመሩ፣ በዚሁ ሥፍራ ደርሰው በአካባቢው ካሉት ሰዎች ጋራ ግጭት ፈጠሩ። ቆይቶም የፖርቱጋል መንግሥት የራሱን ዜጐች በተጠናከረ ሁኔታ በማደራጀት በአካባቢው ያሉትን አገሮች በመውረር በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ጀመረ። ደቾችም በበኩላቸው በተጠናከረው የፖርቱጋል ተስፋፊ ኃይል በመደናገጥ ለመደራጀት ተገደዱ። በዚሁ ወቅት ከፈረንሳይ በሃይማኖት ግጭት ምክንያት የኰበለሉ «ሂዩገኖትስ» ይባሉ የነበሩትም ወደዚሁ ሥፍራ መጥተው እንደ ሌሎቹ ሰፈሩ። ከነዚህ በኋላ በደቡባዊ አፍሪካ ክልል ያውሮፓ ሰፋሪዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መጣ። የአገሪቷ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥና የቦታው ለምነት እንግሊዞችንም በመማረኩ በየጊዜው ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የእንግሊዝ ዜጐች ወደዚሁ ሥፍራ በመምጣት መስፈር ጀመሩ። በ18ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ ዜጐቿ እየበዙ በመሄዳቸው እንግሊዝ ለዘላቂነት ሥፍራውን በቁጥጥሯ ሥር ለማድረግ ቻለች። ለዚህ ዋንኛ መንስኤ የነበረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ላይ የወርቅ፣ የአልማዝና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት በብዛት መገኘትና ለዚሁ ሥራ ርካሽ የሥራ ኃይል መገኘት ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ይህንኑን በመመልከት ለዘረፋው እንዲያመቹ የሰፈሩትን ሰዎች አንድ ላይ በማሰባሰብ በጦር መሣሪያ አጠናክሮ ማስፈሩን ቀጠለ።[1]

የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በደቡብ አፍሪካ ላይ ዓይናቸውን የጣሉበት ዋናው ምክንያት የአገሪቷን ሀብት በመበዝበዝ የአገራቸውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለማቃለል ነበር። በተለይም በኢኮኖሚው መስክ ደቡብ አፍሪካ ለአውሮፓ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ሀብት ማግኛ ሥፍራ፣ የምርት ውጤቶች መሸጫና ርካሽ የሥራ ኃይል የሚገኝበት አካባቢ ነበር። ለምሳሌ፣ ፖርቱጋል በወቅቱ ደርሶባት ከነበረው የኢኮኖሚ ችግር ለመውጣት ቅኝ ግዛቶችዋን በመመዝበር፣ እንግሊዝ የማዕድናት አካባቢን በመከለል የወርቅና የአልማዝ ማዕድናትን በመዝረፍ፣ ደቾችም በበኩላቸው በስንዴ እርሻና ወይን ተከላ ላይ ያተኰሩ ሲሆን ሁሉም እንደየፍላጐታቸው ጥቁር አፍሪካውያን ከሚኖሩበት አካባቢ በመፈንቀል፣ ለም የሆነውን ሥፍራ ይዘው ዝርፊያቸውን ተያያዙት። ይህ ሁሉ ሲደረግ አፍሪካውያን ከፍተኛ ተቃውሞና ውጊያ አካሂደዋል።

ወቅቱ የቅኝ አገዛዝ ዘመን እየተጠናከረ በመሄድ ላይ የነበረበት ጊዜ ስለነበር በአካባቢው ተጽዕኖውን አስፋፍቶ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት በየሥፍራው ተበታትነው የሰፈሩትን ሰዎች ካደራጀ በኋላ በ1910 ላይ የራስ አስተዳደር መብት በመስጠት አገሪቷን (Union of South Africa) የደቡብ አፍሪካ ሕብረት በሚል ስያሜ በይፋ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት እንድትሆን አደረገ።

ደቡብ አፍሪካ (አዛንያ) ቅኝ ግዛት ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ ጥቁር አፍሪካውያን ሠርቶ አደሮች በጭቆናና ቀንበር በመጠመድ ለእርዛት፣ ለረሀብና ለጉስቁልና ተዳርገው፣ በገዛ አገራቸው የበይ ተመልካች ሆነዋል። የሕዝቡ መብት መገፈፍ ያንገፈገፋቸው በርካታ አፍሪካውያን ተቃውሞ በማሰማታቸው በየጊዜው እንዲጨፈጨፉና ካገራቸው ውጭ እንዲሰደዱ ተደርገዋል።

እስከ አፍንጫው ድረስ የታጠቀውን ጠላት በስሜትና በግብታዊነት መጋፈጥ

Digitized by Google

እንደማያዋጣ በመገንዘብ የደቡብ አፍሪካ ታጋዮች የተቀነባበረ ትግል ለማካሄድ መሪ ድርጅት መመሥረት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በ1912 የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስን (ANC) መሠረቱ ። ይኸው ድርጅት ባሁኑ ጊዜ ግብታዊ ከሆነ የፖለቲካ ትግል ተላቆ ሲመዘበር ለኖረው ሕዝብና ሠራተኛ መደብ ወታደራዊና ፖለቲካዊ አመራር በመስጠት ወሳኙን ፍልሚያ ተያይዞታል ።

ነጻነት ፣ እኩልነትና ፍትህ የጠማው ሕዝብ ከተጫነው የግፍ አስተዳደር ለመላቀቅ የሚያካሂደው ትግል ዘረኛውን መንግሥትና ግብረ አበሮቹን ከስጋት ላይ ጥሏቸዋል ። በዚሁ ፍራቻ የተነሣ ዘረኛው መንግሥት በየጊዜው የተለያዩ ድንጋጌዎችን በማውጣት የሕዝቡን የትግል ወላፈን ለማብረድ ሲፍጨረጨርና በሠራተኛው ሕዝብ ላይም ከፍተኛ በደል ሲፈጽም ይታያል ። የነጻነት ትግሉ ዓላማ ደቡብ አፍሪካን ከብዝበዛ ፣ ከጭቆናና ከዘር ልዩነት በማላቀቅ አዲስ ሥርዓት መመሥረት መሆኑን የተገነዘበው ዘረኛው መንግሥት በ1951 ኰሚኒዝምን የማገድ ድንጋጌ (Suppression of Communism Act) ተብሎ የሚታወቀውን ፀረ ኰሚኒዝም ድንጋጌ አውጥቶ የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስንና ፓን አፍሪካን ኰንግሬስ የተባሉትን ነጻ አውጪ ድርጅቶች እንዲዘጉ አደረገ። በነዚሁ ውስጥ አመራር ይሰጡ የነበሩት ታጋዮችንም እያሳደደ ማሠር ጀመረ ። ከነዚሁም መካከል የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኮንግሬስ መሪ የነበረው ታጋዩ ኔልሰን ማንዴላ ሲገኝ እሱም ባሁኑ ጊዜ በሮቢን ደሴት ውስጥ በሚገኝ እሥር ቤት በመማቀቅ ላይ ይገኛል ። የደቡብ አፍሪካ ጭቁን ሕዝብ በሚያካሂደው የፀረ—ዘረኝነት እንቅስቃሴ በዛ ያሉ መሪዎቹን ቢያጣም ለነጻነቱ የሚያደርገው ትግል በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

የአፓርታይድ ፖሊሲ አስፋፊዎች ድርጅት መመሥረት

የእንግሊዝ መንግሥት ደቡብ አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ከያዘ በኋላ በ1910 በክልሉ ሰፍረው የነበሩትን አውሮፓውያን በማሰባሰብ ነጮችን የሚወክል መንግሥት መመሥረቱ ቀደም ሲል ተጠቅሷል ። በኋላም በ1914 በደቡብ አፍሪካ ፓርላማ ሲመሠረት በዚሁ ፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ አውሮፓውያንን በማደራጀት «የአፍሪካነርስ ናሽናሊስት ፓርቲ» (Afrikaners Nationalist Party) የተባለውን መሠረቱ ። የዚሁ ፓርቲ መሥራቾች ካውሮፓ በተለያዩ ጊዜያት ተሰደው በደቡብ አፍሪካ የሰፈሩት ጥቂት ነጮች ብቻ ሲሆኑ ፣ ከነዚህም በዘረኛው መንግሥት መዋቅር ውስጥ በአመራር ላይ የነበሩ ይገኙባቸዋል ። የጥቂት ነጮች መንግሥት የአፍሪካውያንን ተቃውሞና ንቅናቄ ለመቆጣጠር አለመቻሉን እንደተገነዘበ ፣ ጭቆናውን ለማስፋፋትና በአካባቢው የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እንዲቻል « ብሮደር ቦንድ » የሚባለውን ድርጅት መሠረተ ። በኋላም ከብሮደር ቦንድ ጐን ሌላ «ኦሴዋ ብራንድዋግ» ወይንም «ኦክስዋገን ብሮጌድ» በመባል የሚታወቀውን ወታደራዊ ክንፍ መሠረተ ። ይህ ወታደራዊ ክንፍ የአፍሪካውያንን የአርነት ትግል መሪዎች የሚያጠቃ ሃይል እንዲሆን ተደርጐ የተመሠረተ ነው ። ይኸው ወታደራዊ ክንፍ (ኦክስዋገን ብርጌድ) በ፪ኛ የዓለም ጦርነት ወቅት የጀርመን ናዚ ቆሞለት ለነበረው ፋሽስታዊ ድርጊትና የዘረኝነት ዓላማ በደጋፊነት የቆመ ነበር ። የጀርመን ናዚስቶችም ከዚህ ዘረኛ ድርጅት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው ። የቅርብ ግንኙነት ፈጥረው የነበረበትም ዋና ምክንያት በአካባቢው ፀረፋሽዝም እንቅስቃሴ ይነሳል የሚል ፍርሀት ስለነበር ይህንኑ ለመቆጣጠር ታስቦ ነበር ። [2]

Digitized by Google

አክስዋገን ብርጌድ የተመሠረተበትን ዓላማ ከግቡ የሚያደርሰውና ፀረ ሕዝብነቱን በይፋ የሚገልጸው የዚሁ ድርጅት አባል በሆኑ ነጮች አማካይነት ነው ። የጥቂት በዝባዥ አውሮፓውያን ሕልውና የተመሠረተው በዚሁ ድርጅት ላይ ስለሆነ በደቡብ አፍሪካ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ሥልጣን የሚይዝ ማንም አውሮፓዊ የግድ የዚሁ ብርጌድ አባል መሆን አለበት ። አክስዋገን ብርጌድ ዓላማው የአፍሪካነርስ ናሽናልስት ፓርቲ ተብሎ ለሚጠራው የጥቂት ነጮች ፓርቲና የዘረኝነት ፖሊሲ አራማጅ ለሆነው ለደቡብ አፍሪካ ሽብር ፈጣሪ መንግሥት ዘብ መቆም ነው ። የአፓርታይድን ፖሊሲ የቀየሱት ነጮች በሙሉ በዚሁ ድርጅት የታቀፉ ሲሆኑ ፣ እያንዳንዱ የአሴዋ ብራንድዋግ አባልም የአፓርታይድ ፖሊሲ ደጋፊና አራማጅ እንዲሆን ይገደዳል ።

አፓርታይድ ምንድነው ?

አፓርታይድ ማለት በተራ ትርጉሙ መለየት ፣ መከፋፈል ፣ ተለያይቶ መኖር እንደ ማለት ነው ። አፓርታይድ የሚለው ቃል የፖለቲካ ፍች ተሰጥቶት የዘረኛው መንግሥት አስተዳደር መመሪያ ሆኖና በፖሊሲ ደረጃ ታውጆ በጥቁር አፍሪካውያን ላይ ተግባራዊ መሆን የጀመረው ከ1948 አንስቶ ነው ። ለፖሊሲው ተግባራዊነት በወቅቱ የፓርላማ ምርጫ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ፣ በቅስቀሳ ደረጃ በዩኒቨርሲቲ ያስተምሩ የነበሩ አውሮፓውያን «አፓርታይድ» የሚለውን ቃል የፖለቲካ ቅርጽ በመስጠት ማስተጋባት ጀመሩ። በተለይም በሃይማኖት ጉዳይ ከፈረንሣይ የኮበለሉ ሂዩገኖትስና የደች ዜጎች ለዘረኝነት ፖሊሲ መስፋፋት አስተዋጽኦ አድርገዋል። በቅስቀሳው ወቅት «ልዩ ሽግግራዊ ልማት» « ልዩ የኑሮ ዘዴ» ለያንዳንዱ ጉሣ መስጠት አለበት እያሉ ከማስተማራቸውም በላይ የአውሮፓውያን የኑሮ ዘዴ ለአፍሪካውያን (ለጥቁሮች) አይስማማም እያሉ ማስተጋባት ጀመሩ ። እያንዳንዱ ጉሣ የራሱ የሆነ «ሽግግራዊ የልማት ደረጃን» መያዝ እንዳለበት አበክረው ይለፍፉ ነበር ። በነዚህና በተባባሪዎቻቸው አማካይነት የቀለም ልዩነትን በማስፋፋት በነጭና በጥቁር አፍሪካውያን ሠራተኞች መካከል ያለውን የቀለም ልዩነት በተዛባ መልኩ በማስተጋባት ፣ በሠራተኛው መካከል ከፍተኛ መለያየትን ፈጠሩ ።

በማኅበራዊ ኑሮ የአፓርታይድ ፖሊሲ የጥቁር አፍሪካውያን መጨቆኛ መሣሪያ ነው ። ለዚህም በሚያዝያ 1982 በኒውስዊክ መጽሔት ላይ የደቡብ አፍሪካን የዘር ልዩነት ፖሊሲ በማስመልከት የሰፈረውን ጽሑፍ መመልከት ይቻላል ። በጽሑፉ መሠረት ባሁኑ ወቅት ዘረኛው መንግሥት የዘር መዳቢ ቦርድ (Race Classification Board) በሚባለው የዘረኝነት ተቋሙ አማካይነት የአገሪቷን ዜጎች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት (አማካይነት) ከአንዱ ዘር ወደ ሌላ ዘር እንዲለወጡ ያደርጋል ። በአገሪቷ የሚኖሩ ዜጎች የዘር መዳቢውን ቦርድ ሳይጠይቁና ሳያስፈቅዱ ጋብቻን መፈጸም ወይንም ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል ለመሄድ አይችሉም ። ዘረኛው መንግሥትም በዚሁ አማካይነት የአፓርታይድን ምንነት በይፋ እየገለጸ ነው ። ለምሳሌ አንድ ክልስ ክልስነቱን ደብቆ ነጭ እንዲሆን በማመልከቻ ጠይቆ ከተፈቀደለት አንድ አውሮፓዊ የሚያገኘውን ማናቸውንም መብት ያገኛል ። በዚህ ዓይነት ነጭ እንዲሆን ከተፈቀደለት በኋላ ቅድመ አያቶቹ ጥቁር ወይም እስያዊ መሆናቸው ከተጠረጠረ የልደት ሰርቲፊኬቱ እንደገና ከመታየቱም በላይ ፣ የዝርያዎቹ ፀጉር ፣ ቆዳ ፣ የጣት ጥፍርና የፊት አወራረድ ይመረመራል ። « ንጹህ » አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወደ ክልሶች ክልል እንዲሔድ ይገደዳል ። በሌላ አነጋገር አንድ ነጭ ነኝ የሚል ግለሰብ ነጭነቱ በዘር መዳቢው ቦርድ ካልጸደቀ ባው

Digitized by Google

ሮፓዊነቱ ከዘረኛው መንግሥት ያገኘ የነበረውን የ«ነጭነት ክብር» በማጣት የአፓርታይድ አስከፊ ድርጊት ከሚከሰትበት ክልል ውስጥ ይገባል። ይኸው የዘር መዳቢ ቦርድ በ1981 ላይ ቁጥራቸው 794 የሚሆኑ ግለሰቦችን በልዩ ልዩ ቀለም ውስጥ የመደበ ሲሆን ፥ ለ588 ክልሶች ደግሞ ነጭ (አውሮፓውያን) እንዲሆኑ ፈቅዶላቸዋል። (ኒውስዊክ ፥ ሚያዝያ 1982 ፥ ገጽ 35—36)

የአፓርታይድ ፖሊሲ በመናፈሻ ቦታ

የአፓርታይድን ፖሊሲ ካወጡትና ቀንደኛ ፀረ አፍሪካውያን አቋም ከነበራቸው ተስፋፊዎች መካከል በ1948 ተደርጎ በነበረው የፓርላማ ምርጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተመረጠው ዶክተር ዲ.ኤፍ. ማላን ነው። ይኸ ግለሰብ የአፓርታይድን መዋቅር የዘረጋና ፥ የአፍሪካውያንን ሰብአዊ መብት በመግፈፍ ከሚታወቁት አውሮፓውያን መካከል አንዱና ዋንኛው በመሆን የሚታወስ ነው ።[3] የአፓርታይድ ፖሊሲ በደቡብ አፍሪካ በተቀየሰበት ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ የአርነት ትግሎች በመጧጧፍ ላይ የነበሩት ወቅት ስለነበር ፥ በደቡብ አፍሪካም የፀረ አፓርታይድ እንቅስቃሴው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ። የነማላን ቡድንም ይህንኑ ትግል ለማገታትና የጥቁርችን ሰብአዊ መብት ለመግፈፍ ብዙ ፀረ ሕዝብ ድንጋጌዎችን ደንግጎ ነበር ።

በነማላን አገላለጽ አፓርታይድ ማለት አፍሪካውያንን ካውሮፓውያን ማራቅና ፥ መለየት ማለት ሲሆን ፥ በተለይም የቆዳ ጥቁረት በሥልጣኔ ኋላቀር መሆንን ያመለክታል በማለት ያስተጋቡ ነበር ። የአፓርታይድ ፖሊሲ በሥልጣኔና በኑሮ እንዲሁም ሰብአዊ መብትን በሚመለከት ረገድ ጥቁሮችን ከአውሮፓውያን በታች ዝቅ አድርጎ መመልከት ከእያንዳንዱ አውሮፓዊ የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑን በመመሪያ ደረጃ አውጥቷል ። ይህ የዘረኝነት ፖሊሲ በመመሪያ ደረጃ ከወጣበት ከ1948 ጀምሮ ጥቁሮች የፖለቲካ ፥ የኤኰኖሚና ማኅበራዊ ኑሮ መብታቸውን ተገፈው ፥ ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ሥር እንዲኖሩ ተገደዋል ። በዚህ ፖሊሲ መውጣት ከመቶ 87 የሚሆነው የደቡብ አፍሪካ ለም መሬት በአውሮፓውያን ይዞታ ሥር እንዲሆን ሲደረግ ፥ ቁጥራቸው ከ18 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ጥቁር አፍሪካውያን 13% በሆነው እጅግ ጠባብና ለኑሮም አደገኛ በሆነ አካባቢ እንዲታጐሩ ተደርገዋል ።

በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ጥቁሮች የአፓርታይድን ፖሊሲ እንዳይቃወሙ በህግ ከመደንገጉም ሌላ ፥ ተቃውመው ከተገኙ የአውሮፓውያን መብት እንደደፈሩ ተቆጥሮ በህግ ያስቀጣቸዋል ። ይህንን ተቃውሞ ለመቆጣጠር እንዲያመች ዘረኛው መንግሥት በየጊዜው ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ድንጋጌዎችን ቢያወጣም ተቃውሞው ከቁጥጥር ውጭ ሆኖበታል ። ሌላው ቀርቶ ጥቁሮች ያውሮፓውያንን የኑሮ ዘይቤ እንዳይከተሉ ከመከልከላቸውም በላይ የራሳቸውን የአፍሪካውያንን ባህል እንዳያዳብሩ የሚያደርግ መመሪያ ጭምር ወጥቶባቸዋል ። ይህ አውሮፓውያን ባልሆኑ ዜጐች ላይ የሚሠራው ፖሊሲ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ የአፍሪካውያንን የኑሮ ደረጃ እየቀረቀዘና ማኅበራዊ ሕይወታቸውንም እያናጋባቸው ሲሆን ፥ አፓርታይድ ከአመሠራረቱም የአውሮፓውያንን የበላይነት ማስጠበቅያና የጭቆና መሣሪያ እንደሆነ ዓላማው በጉልህ ያስረዳል ። የአፓርታይድ ፖሊሲ መሠረታዊ ዓላማም ፥—

Digitized by Google

1· ነጮችንና ጥቁሮችን በዘርና በቀዩ ልዩነት ለያይቶ ማኖር ፣

2· የጥቁሮችን ከሥፍራ ሥፍራ መዘዋወርና አቀጣጠርን መቆጣጠር በዚህም መሠረት ማንኛውም መሠረቱ ነጭ ያልሆነን ዜጋ የመዘዋወር መብት መገፈፍ ፣

3· «የተለየ ልማት ሥፍራ» እየተባለ በሚታወቀው ዕቅዳቸው መሠፈት ጥቁሮችን በአንድ አካባቢ አስፍሮ የሕዝቡን ብዛት መቆጣጠርን የሚያጠቃልል ነው ።

ለምሳሌ ዘረኛው መንግሥት በ2000 ዓ·ም. ላይ የጥቁሮች ብዛት 21,000,000 ፣ ነጭ 4,500,000፣ ክልስ 4,000,000፣ እስያውያን 1,500,000 ይሆናሉ የሚል ስታትስቲካዊ መረጃ አለኝ በማለት ፣ የጥቁሩን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ ፣ በአንድ አካባቢ አስፍሮ በተላላፊ በሽታዎች እንዲበከሉና እንዲያልቁ ለማድረግ እቅድ አውጥቷል ። በዚህ መንገድ እስከ 2000 ዓ· ም· ድረስ የጥቁሮችን ቁጥር ወደ 6,500,000 ዝቅ ለማድረግ አስቧል ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የአፓርታይድ መሠረታዊ ዓላማዎች ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ጥቁር ሠራተኞችና ሌሎችም መሠረታቸው ነጭ ባልሆኑ ዜጐች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው ። የጥቁር ፣ የክልስ ፣ እንዲሁም የነጮች ሰፈሮች ከመለየታቸውም በላይ በጥቁሩ ሕዝብ ላይ ጭካኔ የተመላበት ኢሰብአዊ ድርጊት እየተፈጸመ ነው ። ባልና ሚስት ልጆችና ቤተሰብ በተለያዩ መንደሮች እንዲኖሩ ሲደረግ ፣ ማንም ጥቁር አፍሪካዊ በማንኛውም ረገድ ከአንድ ነጭ ዜጋ ጋራ እኩል አለመሆኑ በግልጽ ከመደንገጉም በላይ ፣ በየጊዜው በፐሮፓጋንዳ መሣሪያ



በደቡብ አፍሪካ የባቡር ጣቢያ መተላለፊያዎች ሳይቀሩ የቀለም ልዩነት ምልክት አለባቸው

Digitized by Google

ዎች አግካይነት ይለፈፋል ። በሁሁ መሠረት ግንኛውም ነጭ ግለሰብ በአንድ ጥቁር አፍሪካዊ ላይ በኤኰኖሚ ፥ በፖለቲካና በማኅበራዊ ኑሮ የበላይነት አለው ።[4]

የአፓርታይድ ፖሊሲ የሚከሰትባቸው የጭቆና መልኮች

ዘረኛው መንግሥት የአፓርታይድን ፖሊሲ በተለያየ ገጽታው በተግባር ላይ ያውለዋል ። በደቡብ አፍሪካ በተግባር በመዋል ላይ ከሚገኙት የአፓርታይድ ህጐች መካከል ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን ።

የይለፍ ሕግ

በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ከ18,000,000 በላይ የሚሆኑ አፍሪካውያን ፥ 2,000,000 ክልሶች ፥ ከ700,000 በላይ የሚሆኑ ሕንዶችና ከ4,000,000 በላይ የሚሆኑ ነጮች የሚኖሩበት መንደር ተከልሏል ።[5] አውሮፓውያን ያልሆኑ ዜጐች ከሚኖሩበት ክልል ውጭ እንዳይዘዋወሩ ተከልክለዋል ። የጃፓን መንግሥት የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ መንግሥት ከሚረዱት ቀንደኞቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል አንዱ በመሆኑ ዜጐቹ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ካለው የቀለም ልዩነት ነጻ በመሆን « የነጭነት ክብር » (white honrary status) ተሰጥቷቸዋል ።[6]

ማንም ጥቁር ፥ ክልስና እስያዊ (ሕንድና ቻይና ፥) ከተከለለለት ውጭ እንደፈለገ እንዲዘዋወር አይፈቀድለትም ። በተለይም ዕድሜው ከ16 ዓመት በላይ የሆነና አውሮፓዊ ያልሆነ ሁሉ ከመኖሪያው ክልል ውጭ ለመሄድ ቢፈልግ ሥፍራውን ከሚያስተዳድረው ነጭ አስተዳዳሪ የመዘዋወሪያ ወረቀት (የይለፍ ወረቀት) እንዲይዝ ይገደዳል ።[7] ይሁን እንጂ ቁጥራቸው ከ6,000 በላይ የሆኑ በመምህርነት ፥ በሃይማኖት ትምህርት አስፋፊነት ፥ በሐኪምነትና በጸሐፊነት ሥራ የተሰማሩት ጥቁር አፍሪካውያን ሸብር ፈጣሪው መንግሥት በመግሪያነት የሚጠቀምባቸው ስለሆነ የመዘዋወሪያ ወረቀት ይዘው ከመዘዋወር ነፃ ናቸው[8] ።

አንድ አፍሪካዊ ከሚኖርበት ክልል ውጭ ለመዘዋወር ከፈለገ «ፖል ታክስ» ወይም የመዘዋወሪያ ግብር (የኰቴ ግብር) እንዲከፍል ይገደዳል ። ሲዘዋወርም ይህንኑ ወረቀት መያዝ አለበት ። ዕድሜው ከ16 ዓመት በላይ የሆነ ማንም አፍሪካዊ የመዘዋወሪያ ወረቀቱንና የመዘዋወሪያ ግብር የከፈለበትን ይዞ ካልተገኘ እንደ ሕግ ተላላፊ ተቆጥሮ ከመታሠሩም ሌላ ነፃ የጉልበት ሥራ እንዲሠራ ይገደዳል ።

ፖል ታክስን ወደ አፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጣውና ያስፋፋው በነሲስል ሮድ ይመራ የነበረ የሃይማኖት ድርጅት ነበር ። እነዚህ ሃይማኖት አስፋፊዎች ነን ባዮች ኬፕ ኰሎኒ ተብሎ ይጠራ በነበረ አካባቢ ሰፍረው «ሃይማኖትን ማስፋፋት» እንደ ጀመሩ የመጡበት ዋንኛ ዓላማቸው የሆነውን ወርቅን መፈለግ ጀመሩ ። የቁፋሮውን ሥራ የሚያካሂዱበት ገንዘብ ስለአጠራቸው ፥ ይህንኑ ችግር ለማቃለል የሚቻልበትን መንገድ ካጤኑ በኋላ ሕዝቡን የሚቆጣጠሩበት ዘዴ አወጡ ። ባወጡትም ሕግ ውስጥ ማንም አፍሪካዊ ከሥፍራ ሥፍራ ሲዘዋወር የተወሰነ የመዘዋወሪያ ገንዘብ እንዲከፍል ፥ የማይከፍል ሆኖ ከተገኘ ግን እንደ ሕግ ተላላፊ ተቆጥሮ የግዳጅ ሥራ እንዲሠራ ጭምር በመግለጽ መመሪያ አወጡ ። በዚህ መሠረት በቂ ገንዘብ ለመሰብሰብ ከመቻላቸውም በላይ የሚፈልጉትን ርካሽና ነፃ የሥራ ኃይል በፈለጉት መጠን ለማግኘት ቻሉ ። ያሁኑ ሸብር ፈጣሪ መንግሥትም ፖል ታክስን የሚሰበስበውና የአፍሪካውያንን የሥራ ኃይል የሚበዝብ

Digitized by Google

ዘው የቀድሞዎቹ ዘረኞች በጠነሰሱለት የብ·
ዝበዛ ዘዴ መሠረት ነው ።

አንድ ጥቁር አፍሪካዊ ከደቡብ አፍሪካ
ውጭ ለመሄድ ቢፈልግ የመውጫ ፈቃድ
ለማግኘት እንዲችል ከማመልከቻ ጋር 246
ራንድ * ይዞ መቅረብ አለበት ። ይህን አሟ
ልቶ ከወጣ በኋላ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመ
ግባት ይቸገራል ። «ያለፈቃድ» ተመልሶ
ከተገኘ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ እንዲታ
ሠር ከመደረጉም ሌላ አሥራቱን እንደጨ
ረሰ ካገር እንዲወጣ ይገደዳል [9] ። በዚህ ዓይ
ነት ድርጊት የሚቀጡት አፍሪካውያን ቁጥር
ከቀን ወደ ቀን እየበዛ በመሄድ ላይ ነው ።

ከዚህም በተጨማሪ ጥቁር ደቡብ አፍሪ
ካውያንን በአንድ ቦታ አጉር በማስፈር
በጤና መታወክ እየተሰቃዩ እንዲኖሩ ማድ
ረግም የዚሁ የአፓርታይድ ፖሊሲ አንዱ
ገጽታ ነው ። ለምሳሌ የትራንስኬ ሕዝብ
የታጐረበትና ከፍተኛ እልቂት የሚፈጸም
በት በጣም ጠባብና በበሽታ የተበከለ ሥፍራ
በ2ኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ጀርመን ውስጥ
ናዚስቶች የፖለቲካ ሰዎችንና በዘር ልዩ
ነት የተነሳ ይጠሉዋቸው የነበሩትን ጀርመ
ናዊ ያልሆኑ ዜጐችን ከሚያሥሩበት ጥር
ገን ከተባለው መታጐሪያ ጋራ ይመሳሰላል።
ናዚስቶች በዚሁ ዓይነት እስር ቤት ውስጥ
የነበሩ ሰዎችን እያስገደዱ ነፃ የጉልበት
ሥራ እንዲሠሩ ያደርጓቸው እንደነበረ
ሁሉ የደቡብ አፍሪካ ሽብር ፈጣሪ መንግ
ትም በበኩሉ ጥቁር አፍሪካውያን በገዛ
አገራቸው እንዳይዘዋወሩ ካደረጋቸው በኋላ
አንድ ላይ ሰብስቦ ርካሽ የሥራ ኃይል
ማግኛ ምንጭ አድርጓቸዋል ። ከ1948 እስከ
1974 ድረስ የይለፍ ወረቀት ይዘው ባለመ
ገኘታቸው 10,500,000 አፍሪካውያን ታሥ
ረው የግዳጅ ሥራ እንዲሠሩ ተደርገዋል። [10]

በአንድ ግለሰብ የይለፍ ወረቀት ላይ ግለ
ሰቡ በየትኛው ክልል እንደሚኖርና ምን ዓ
ይነት ሥራ ላይ እንደተሰማራ ይጻፍበታል ።



የይለፍ ደብተር በደቡብ አፍሪካ

በዚህ ዓይነት መብቱ የተገደበበት ግለሰብ
በወረቀቱ ላይ ከተጻፈው ክልል ውጭ እን
ዲሄድ አይፈቀድለትም ። የዚህ ሕግ ተግባ
ራዊ ውጤት በርካታ አፍሪካውያንን በነጭ
ካፒታሊስቶች ኢንዱስትሪ አካባቢ እንዲ
ኩለኩሉ ሲያደርግ ሌሎች ደግሞ «ለባ
ንቱ ስታን» በተከለለው አካባቢ እንዲ
ወሰኑ አድርጓቸዋል ። አንድ ሦስተኛ
የሚሆነው የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ በት
ራንስኬ ውስጥ እየተጠበቀ ነው ። ትራን
ስኬ ርካሽ የአፍሪካውያን ጉልበት ማግኛ
ምንጭ በመሆኑ ልጆች ከወላጆቻቸው እየ
ተነጠቁ አነስተኛ በሆነ ምንዳ እንዲሠሩ
የሚገደዱበት ሥፍራ ነው ። በዚሁ ምክን
ያት ለሕፃናት ተንከባካቢ አባት ወይንም
እናት ባለመኖሩ በያመቱ 24,000 ሕፃናት
በምግብ እጦት ፥ በጤና መታወክና በእንክ

* ራንድ የደቡብ አፍሪካ ገንዘብ ሲሆን በአሜሪካ ገንዘብ ሲመነዘር 0.95 ዶላር አንድ ራንድ
ወይንም በኢትዮጵያ ሲመነዘር አንድ ራንድ ብር 1.96 ነው

Digitized by Google

ብካቤ ማጣት ያልቃሉ ። [11] ይህ በዘመናችን እስከፊ ድርጊት የሚታይበት ደቡብ አፍሪካ ፣ ባሁኑ ጊዜ እጅግ በተካረረ የሠራተኛ መደብ ትግል የተወጠረ ሲሆን ፣ ሠራተኛውም ሰብአዊ መብቱንና ነፃነቱን ለማግኘት የተፋፋመ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

የኪራይና የግዳጅ ሥራ ፤

የግዳጅና የኪራይ ሥራ በደቡብ አፍሪካ ክልል ለረጅም ዘመን የቆየ ነው ። ቀደም ብለው በቅኝ ግዛት አስተዳደር ሥር የነበሩና በአሁኑ ጊዜ የነፃነት አየር የሚተነፍሱ የአንጐላ ፣ የሞዛምቢክና የዚምባብዌ ሕዝቦች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፣ ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ላይ በመፈጸም ላይ ያለውን የመከራና የሥቃይ ቀንበር ተሸክመው እንደነበሩ የሚታወስ ነው ።

በደቡብ አፍሪካ አፍሪካውያንን አስገድዶ ያለ ክፍያ ከማሠራቱም በተጨማሪ ሰውን እንደ ዕቃ በመቁጠር ለማዕድን ቁፋሮና ለእርሻ ሥራ በማከራየት ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ከበርቴዎችም ነበሩ ። በጭካኔው ከባሪያ አሳዳሪ ሥልተ ምርት ባልተለየ ሁኔታ ሰብአዊ ክብርን ዝቅ አድርጐ ሰውን እንደ ዕቃ በማከራየትና በኪራዩ ካፒታልን ማደለብ የአፓርታይድ አንዱ አስከፊ ገጽታ ነው።

ለግዳጅ ሥራ አንዱና ዋንኛው ሰበብ የይለፍ ወረቀት ይዞ አለመገኘት ነው ። የይለፍ ወረቀት ይዞ የማይገኘውን ነጭ ያልሆነ ግለሰብ ነፃ የጉልበት ሥራ እንዲሠራ ከመደረጉም ሌላ የደቡብ አፍሪካ ወህኒ ቤቶችም ለካፒታሊስቶች የነፃ ጉልበት ምንጭ ናቸው ። ለምሳሌ ፣ አፓርታይድ በይፋ የዘረኛው መንግሥት የአመራር ፖሊሲ ከሆነ ከ4 ዓመት በኋላ ማለትም በ1952 የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በወህኒ ቤት አከራይነት ከ 1,184,546 ዶላር በላይ ገቢ አግኝቷል ። [12]

በደቡብ አፍሪካ ፣ አፍሪካውያን ለረሃብ ፣ ለበሽታ ፣ ለማይምነት ፣ ለእርዛት ፣ ለኋላቀርነትና ለመሳሰሉት ማኅበራዊ ችግሮች ተጋልጠው እጅግ አሰቃቂ ኑሮ የሚኖሩባት አገር ሆናለች ። በደቡብ አፍሪካ የማዕድን ክምችት ከፍተኛ ነው። ጥቁር አፍሪካውያን እየታፈሱ የግዳጅ ሥራ እንዲሠሩ ከሚገደዱባቸው ሥራዎች መካከል ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘው ይኸው የማዕድን ሥራ ነው ። በአገሪቷ ወርቅን ለገበያ ማምረት የተጀመረው በ1886 አካባቢ ሲሆን ለዘረፋው አመቺ ሥፍራን በመቀየስ በ2 ዓመታት ውስጥ 6,800,000 ፓውንድ ወጭ ተደርጐ በ44 ሥፍራዎች የወርቅ ምርት ሥፍራዎች እንዲዘጋጁ ተደረገ ። ሥራው ከተጀመረ በኋላ ባንድ ዓመት ውስጥ 1,300,000 ፓውንድ ትርፍ ተገኘ ። በወርቅ ማምረት ሥራ የተሰማሩት ሞኖፖሊስቶች በ1890 ላይ በግዳጅ ሥራ በተሰማሩ 100,000 ሠራተኞች አማካይነት 6,000,000 ፓውንድ ዋጋ ያለው ወርቅ አመረቱ ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ አገሪቷ የፋይናንስ ካፒታሊስቶች የዝርፊያ ሜዳ በመሆኗ ፣ ሠርቶ አደሩ ለረሃብና ለጉስቁልና መጋለጥ ጀመረ ።[13]

ባለም ውስጥ ከሚመረቱት ማዕድናት መካከል ደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ ድርሻ አላት ። በ1973 ባለም ውስጥ የተመረቱት ማዕድናት መጠንና ከደቡብ አፍሪካ ተመርተው ለዓለም ገበያ የቀረቡት ማዕድናት ዝርዝር እንደሚከተለው ነበር ።[14]

Digitized by Google

የማዕድናት ዓይነት	ዓለም የተመረተው መጠን	በደቡብ አፍሪካ የተመረተው መጠን	የምርቱ መጠን በ%	ደረጃ
ኒኬል	692,400 ሜትሪክ ቶን	31,626 ሜትሪክ ቶን	2.8	7ኛ
ማንጋኒዝ	9,200,000 ሜትሪክ ቶን	2,963,600 ሜትሪክ ቶን	14.9	2ኛ
ክሮም	3,290,000 ሜትሪክ ቶን	1,078,000 ሜትሪክ ቶን	22.0	1ኛ
ቫናዲየም	19,250 ሜተሪክ ቶን	8,893 ሜትሪክ ቶን	42.4	1ኛ
ወርቅ	1,135,000 ኪሎግራም	898,926 ኪሎግራም	75.4	1ኛ
ፒላቲነም	4,850,000 አውንስ	1,785,000 አውንስ	36.8	1ኛ
የድንጋይ ከሰል	2,206,800,000 ሜት. ቶን	67,925,000 ሜትሪክ ቶን	2.8	8ኛ
አስቤስቶስ	4,490,000 ሜትሪክ ቶን	452,000 ሜትሪክ ቶን	6.7	3ኛ
ዩራኒየም	19,668 ሜትሪክ ቶን	4,080 ሜትሪክ ቶን	13.7	3ኛ
አንቲሞኒ	69,400 ሜትሪክ ቶን	16,757 ሜትሪክ ቶን	22.3	1ኛ
ፍሎርስፓር	4,700,000 ሜትሪክ ቶን	357,324 ሜትሪክ ቶን	4.7	7ኛ

ጥቍር ደቡብ አፍሪካውያን ላባቸውን ያፈሳሉ፤ ነጭ ከበርቴዎች ይዝናናሉ

Digitized by Google

እነኝህ ማዕድናት ከምድረ ከርስ ተፈል
ፍለው ወጥተው ለደቡብ አፍሪካ የገዥ መደ
በችና ለዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች የሀ
ብት ምንጭ ሊሆኑ የቻሉት በጥቁር ደቡብ
አፍሪካውያን ጉልበት ነው። የማዕድናትም
በብዛት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ መገኘት
የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በደቡብ
አፍሪካ ላይ ያለውን ተፅዕኖ እንዲጠናከር
አድርጎታል ።

የምንዳ ልዩነት

የሠራተኛው ብዛት በየጊዜው እያደገና
በዚያው አንፃር ምርት እየጨመረ ቢሄድም
የአውሮፓውያን ከበርቴዎችን ኑሮ ከመገን
የሚሆኑት በአደገኛ ሁናቴ ከመሥራታቸው
የተነሳ ለሞት ተዳርገዋል ። አፍሪካውያን
አደገኛ በሆነ የቁፋሮ ሥራ ሲሰማሩ አውሮ
ፓውያን በተቆጣጣሪነት ይሠራሉ። በተቆ
ጣጣሪነት ሥራ ላይ የተሰማራው ነጭ ዜጋ
የጤና መታወክ ቢደርስበት በሚገባ እንዲ
ታከም ሲደረግ፣ በአንድ አፍሪካዊ ላይ ግን
ማንኛውም ዓይነት አደጋ ቢደርስበት ከነጩ
እኩል የሕክምና እርዳታ አይደረግለትም።
መሬት ውስጥ ገብተው ቁፋሮ በሚያካሂዱ
በት ወቅት ጉድጓድ እየተናደባቸውና በፈ
ንጂ እየተቃጠሉ በዚያው የሚቀሩ ጥቁሮች
ቁጥር እጅግ በርካታ ነው ።



በዚህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ በመሥራት ለሞኖፖሊስቶች ትርፍ የሚያስገኙ የደቡብ አፍሪካ ወዛደሮች

ባት በስተቀር ለጥቁር አፍሪካውያን የተረ
ፋቸው ነገር የለም ። ከ1936—1966 በማ
ዕድን ቁፋሮ ተሰማርተው የነበሩ 19,000
አፍሪካውያን የግዳጅ ሥራ ይሠሩ እንደነ
በረ ሲታወቅ፣ ከነዚሁ መካከል ከመቶ 93

ምንዳ አከፋፈሉም ላይ አድልዎ አለ
በት ። በደቡብ አፍሪካ ያለውን የምንዳ ልዩ
ነት ማለትም ለአፍሪካውያን ፣ ለክልሶች፣
ለእስያውያንና ለነጮች የሚሰጠው ክፍያና
የክፍያውንም ልዩነት ከሚከተሉት ሠንጠ
ረዦች መገንዘብ ይቻላል ።

Digitized by Google

በኢንዱስትሪ ክፍለ ኤኮኖሚ ለሚሠሩ ሠራተኞች በየወሩ የሚከፈል የምንዳ መጠን

/ በራንድ /[15]

ዘሮች	1960		1973		1976	
	የሠራተኛው ብዛት	የምንዳ መጠን በነፍስ ወከፍ	የሠራተኛው ብዛት	የምንዳ መጠን በነፍስ ወከፍ	የሠራተኛው ብዛት	የምንዳ መጠን በነፍስ ወከፍ
አፍሪካውያን	357,000	29.00	645,000	72.00	708,200	126
ክልሶች	125,800	47.58	197,600	103.00	208,500	154
እስያውያን	—	—	68,200	111.00	73,400	183
አውሮፓውያን	208,900	157.50	260,500	388.00	275,400	501

በእርሻ ክፍለ ኤኮኖሚ ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች በያመቱ የሚከፈል የምንዳ መጠን

/ ክፍያው በራንድ ነው /[16]

ዘመን	አውሮፓውያን /በነፍስ ወከፍ/	ክልሶች /በነፍስ ወከፍ/	እስያውያን /በነፍስ ወከፍ/	ጥቁሮች በነፍስ/ ወከፍ/
1963	1311.23	152.09	189.76	72.09
1964	1285.38	154.66	194.24	83.07
1965	1305.76	153.86	245.53	77.50
1969	1727.62	199.03	339.40	94.11
1971	2332.10	244.78	416.81	119.49
1972	2634.82	262.10	526.69	130.59
1973	2930.76	304.48	637.07	152.11
1974	3439.07	346.09	902.70	185.32

Digitized by Google

የይለፍ ወረቀት ይዘው ባለመገኘታቸውና ሽብር ፈጣሪው መንግሥት ባወጣቸው ድንጋጌዎች ባለመመራታቸው ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ አፍሪካውያን በግዳጅ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ። ርካሽ የጉልበት ሥራ ከሚሠራበት ክልል ውጭ ሄደው የሚገኙት ጥቁሮች የግዳጅ ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ። ለምሳሌ በ1948 ባንድ ለወርቅ ቁፋሮ በተከለለ ሥፍራ ውስጥ ቁጥራቸው 380,000የሚሆኑ ጥቁር ሠራተኞችና 21,000 አውሮፓውያን ይሠሩ ነበር ። በዚሁ ተመሳሳይ ሥራ ላይ የተሰማሩ አውሮፓውያን በየወሩ 418 ራንድ ሲከፈላቸው አፍሪካውያን ደግሞ 24 ራንድ ነበር ። ራንድ ይከፈላቸው በ1969 የአንድ አውሮፓዊ ዓመታዊ ገቢ $ 5,838 ሲሆን የአፍሪካውያን ግን $ 528 ነበር ። በደቡብ አፍሪካ መንግሥት የክፍያ ፖሊሲ በሙያና በችሎታ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተ ነው። ይኸም ለመሆኑ የአገሪቷ ዜጎች በሳምንት ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያ በማስመልከት የወጣውን መመሪያ[17] መመልከት ይቻላል ።

አውሮፓውያን -----	70	ፓውንድ
ሕንዶች ---------	27	ፓውንድ
ክልሶች ---------	22	ፓውንድ
ጥቁሮች ---------	13	ፓውንድ

ይህ ክፍያ በርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩትን አይጨምርም። በርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩት አፍሪካውያን በሳምንት 3.23 ፓውንድ የሚከፈላቸው ሲሆን ይህም ባገሪቷ ውስጥ የሚሰጠው የመጨረሻ ዝቅተኛ ክፍያ ነው ።

ወጣቱና የግዳጅ ሥራ

ከጥቁር ወጣቶች መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት በግዳጅ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ዕድል አግኝተውከተማሩ በያመቱ የሚከፍሉት የትምህርት ክፍያ በጣም ከፍተኛ ነው ።. በትምህርት ገበታ ላይ ሲሳተፉም የሚሰጣቸው ትምህርት የተለየ ነው ። የትምህርቱ ልዩነት ከዘረኛው መንግሥት ፖሊሲ የመነጨ ነው ። ለምሳሌ በ1953 ለአፍሪካውያን የሚሰጠውን ትምህርት በሚመለከት በጊዜው ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ሄንሪ ቬርወርድ ለካቢኔ አባሎች መግለጫ በሰጠበት ወቅት ፤

አንድ ጥቁር ዛሬ በማንኛውም ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ በመማሩ በእኩልነት እንደሚኖር ይገምት ይሆናል ። ግን ስሕተተኛ ነው ። በተግባር ላይ የማያውለውን አንድን የባንቱን ወጣት የሚሣብ ትምህርት ማስተማር ዋጋ የለውም ። ስለዚህ ለአገሬው ዜጋ መሰጠት ያለበትን የትምህርት ዓይነት በፖሊሲያችን መቆጣጠር አለብን ፡[18] ብሎ ነበር።

ከዚህ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ለጥቁሮች በተከለሉት ሥፍራዎች የሚሰጠው ትምህርት ዓይነት ጥቁሩን ለነጩ የጉልበት አገልጋይ ለመሆን እስከሚያስችለው ደረጃ ብቻ ነው ።ከዚያ ባሻገር ጥቁሩ በሥራ ላይ የማያውለውን ጠለቅ ያለ ትምህርት መስጠት ለሽብር ፈጣሪው መንግሥት ጠቀሜታ የለውም ።የጥቁሮችን የመማር መብት ለመግታት ሲባልም የትምህርት ቤት መግቢያ ዕድሜ ላይ ተመሳሳይ ተፅዕኖ ይደረጋል ። አንድ ጥቁር ሕፃን ነጩ ሕፃን ት/ቤት ከሚገባበት ዕድሜ በሁለት ዓመት ይዘገያል ። ነጩ ሕፃን በ7 ዓመት መማር ሲጀምር ጥቁሩ በ9 ዓመቱ ይገባል ። ነጩ በተወሰነ ዕድሜ ገብቶ እንዲማር ሲገደድ በጥቁሩ ላይ ግን ምንም ቁጥጥር አይደረግም ። የወላጆቻቸው የኑሮ ደረጃ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በትምህርት ቤት ገብተው ለመማር ከሚመዘገቡት መካከል 25 ከመቶ የሚሆኑት በድኅነት ምክንያት ትምህርታቸውን ከጀመሩ ከአንድ ዓመት በኋላ ለማቋረጥ ይገደዳሉ ። አፍሪካውያን ወጣቶች ከፍተኛ ክፍያ ከፍለው ለመማር ባለመቻላቸው ዘረኛው መንግሥት የኩቴ

Digitized by Google

ግብር (ፖል ታክስ) አልከፈላችሁም እያለ በግዳጅ ሥራ ላይ ያሰማራቸዋል ።

ጥቁሮቹ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በብዛት የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት የሃይማኖት ትምህርት ከመሆኑም በላይ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት በጥቃቅን የእጅ ሥራና በከበርቴዎች እርሻ ላይ ያለ ክፍያ በመሥራት ነው ። በአንድ ነጭ ገበሬ መሬት ላይ ትምህርት ቤት ከተሠራ ግለሰቡ ትምህርት ቢኖረውም ባይኖረውም የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የመሆን መብት አለው ። በዚሁ ሥልጣኑ በመጠቀም በፈለገው ሰዓት ሕፃናትን ከትምህርት ላይ እያስገደደ በመውሰድ ነፃ የጉልበት ሥራ ያሠራቸዋል ።[19]

የደቡብ አፍሪካ ካፒታሊስቶች በተለይም የእርሻ ካፒታሊስቶች በታዳጊ ወጣቶች ላይ ከፍተኛ ግፍ ሲሠሩባቸው ይታያሉ ። ታዳጊ ወጣቶችን በተለይም ዕድሜያቸው ከ 16 ዓመት በታች የሆኑትን ከቤተሰቦቻቸው ጠልፈው በራሳቸው እርሻ ስፍራ ላይ በነፃ ማሠራት የተለመደ ነው ። በአንዳንድ አካባቢ በቀን ከ9 ሰዓት በላይ ያለዕረፍት እያሠሩ የአምሳ ሳንቲም ክፍያ የሚሰጡ ካፒታሊስቶችም አሉ ። ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወጣቶች በተለይም በቤተሰብ የገንዘብ አቅም ማነስ ምክንያት ለመማር አቅቷቸው ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሁሉ ለጋ የወጣትነት ጊዜያቸውን በካፒታሊስቶች የእርሻ ሥፍራ ላይ እንዲያሳልፉ ይገደዳሉ ። የደቡብ አፍሪካ የእርሻ ከበርቴዎች የሸንኮራ አገዳ ተክል ፣ የድንች እርሻ ፣ የዶሮ እና የበግ እርባታዎችን የሚካሄዱት በታዳጊ ወጣቶች ጉልበት ነው ።[20] ይህ የሰውን መብት የሚገፈው የአፓርታይድ አስተዳደር በወጣቶች ላይ የሚፈጽመው ኢሰብአዊ ድርጊት ተወዳዳሪ የሌለው ነው ። በአብዛኛው የተሰማሩት በአትክልት ሥራ ላይ በመሆኑ ሙዝ ፣ ብርቱካን ፣ ወይን በልታችኋል ተብለው የሚገረፉና የሚሰቃዩት ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው ።[21]

የአፓርታይድና የኢምፔሪያሊዝም ግንኙነት

በዚህ የአፍሪካ ክልል የሚገኘው ዘረኛ መንግሥት በአፍሪካውያን ላይ ኢሰብአዊ ድርጊት የሚፈጽመው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በሚሰጠው ድጋፍ ነው ።ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች ቀደም ብለው በዚህች አገር ያፈሰሱት መዋዕለ ንዋይ የሚያስገኝላቸው ትርፍ እንዳይነጥፍ ለማድረግ ይጥራሉ ።

በአንድ ወቅት በእንግሊዝ አገር ውስጥ በሚታተም «ዊክሊ ኦብዘርበር» በሚባለው ጋዜጣ ላይ የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት ባወጣው መግለጫ ላይ «ብሪትንና የምዕራብ ዓለም በአጠቃላይ ፣ ክሮም ፣ ማንጋኒዝ ፣ ቫናዲየም እና ፕላቲንዩምን የመሳሰሉ ዋና ዋና ማዕድናትን በሚመለከት ፣ በደቡብ አፍሪካ ላይ ጥገኛ ናቸው። እነዚህ ማዕድናት የጦር መሣሪያን ሠርቶ ለማውጣት በጣም አስፈላጊ ናቸው ። . . . . የደቡብ አፍሪካ ጠላቶች በሪፓብሊኳ ውስጥ አለመረጋጋትን በማስፈን በምዕራብ ዓለም ውስጥ ትርምስ እንፈጥራለን ብለው ያምናሉ ፤»[22] የሚል አባባል ሠፍሮ ነበር ። ይህ እንግዲህ በደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥትና በኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ያለውን የጥቅም መተሳሰር በሚገባ ከማሳየቱም በላይ ፣ ኢምፔሪያሊስቶች የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ መንግሥት በፈለገው ዓይነት መሣሪያ እስከ አፍጢሙ ድረስ የሚያስታጥቁበትንም ምክንያት ገሃድ ያደርገዋል ።

የኢምፔሪያሊስት አገሮች ከደቡብ አፍሪካ ጋር ያላቸው የኢኮኖሚ ግንኙነት በጣም የጠበቀ ነው ። በደቡብ አፍሪካ ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስትመንት ያላቸው ከ500 በላይ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አሉ ። እነዚህ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ መንግሥት በኢኮኖሚም ሆነ በወታደራዊ ኃይል እንዲጠናከር በማድረግ ላይ ናቸው።

Digitized by Google

ከደቡብ አፍሪካ ጋር የንግድ ግንኙነት ያላቸው አገሮች * (1979)

አገር	ከደቡብ አፍሪካ የሚገዙት (በራንድ)	ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚልኩት (በራንድ)
እንግሊዝ	730,841,693	935,904,559
ዩናይትድ ስቴትስ	1,080,411,021	887,781,586
የጀርመን ፌ. ሬ ፑብሊክ	576,756,282	971,378,811
ፈረንሣይ	264,362,474	388,719,071
ኢጣልያ	252,757,177	178,905,668
እሥራኤል	73,830,163	20,190,412
ጃፓን	685,981,040	579,692,791

ኢምፔሪያሊስቶች ከ1960 ዎቹ ጀምሮ ከዘረኛው መንግሥት ጋራ የጠበቀ የኤኮኖሚና የወታደራዊ ግንኙነት ፈጥረዋል ። ትላልቅ ኩባንያዎቻቸውን በማስገባት የአገሪቷን ጥሬት ሀብ እየበዘበዙ ነው ። የዘረኛውን መንግሥት የመከላከያ ሃይል በዘመናዊ ጦር መሣሪያ ከማጠንከራቸውም በላይ፣ የራሳቸውን ጦር ሠፈር በመመሥረት ሕዝቡ ለነጻነት የሚያደርገውን ትግል ለማጨናገፍ ከፍተኛ ደባ በመፈጸም ላይ ናቸው ።

በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከዘረኛው መንግሥት ጋር ያለው የኤኮኖሚ ግንኙነትና መተሳሰር ከፍተኛ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካን ኩባንያዎች ወደር የሌለው ዘረፋ በማካሄድ ላይ ናቸው ። በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያለው የአሜሪካ ካፒታል የኢንዱስትሪ ካፒታል ብቻ ሳይሆን የባንክ ካፒታልም ቅምር ነው ። ቼዝ ማናሃተን በመባል የሚታወቀው ትልቁ የአሜሪካ ባንክ በ1959 ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከነበረው የእንግሊዝ ስታንዳርድ ባንክ ጋራ በመዋሃድ የፊናንስ ካፒታል የብዝበዛ መረቡን ዘርግቷል ። ይኸው ባንክ ከ1964 እስከ 1968 ባሉት ዓመታት መካከል ብቻ ከ 1 ቢሊዮን እስከ 1.42 ቢሊዮን ድረስ ተንቀሳቃሽ የገንዘብ ካፒታል ነበረው ።[23]

በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ግንባር ቀደም አስተባባሪነት ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የምዕራብ ሞኖፖሊስቶች መዋዕለ ነዋያቸውን ወደ ደቡብ አፍሪካ በማጉረፍ ላይ ናቸው ። በ1980 ወደ ደቡብ አፍሪካ የገባው የውጭ መዋዕለ ንዋይ መጠን 43 ሺህ ሚሊ

* ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎችና ፀረኢምፔርያሊስት ትግሎች ፤ ከኢትዮጵያ የሰላምና የትግል አንድነት ኮሚቴ ዘገባ የተወሰደ ፤ አዲስ አበባ ፣ ሐምሌ 1972 ፣ ገጽ 10

Digitized by Google

ዮን ዶላር ደርሶ ነበር ። ይኸ ኢንቬስትመንት ሲከፋፈል አንድ ሽህ ሁለት መቶ የእንግሊዝ ዋናና ቅርንጫፍ ኩባንያዎች የመጀመሪያውን ደረጃ ፣ 375 የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች የ2ኛውን ፣ 350 የምዕራብ ጀርመን ኩባንያዎች የሶስተኛውን ደረጃ ይዘው ይገኛሉ ። [24]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ባሁኑ ጊዜ ከ500 በላይ የሚሆኑ ሞኖፖሊስቶች በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የደራ ዘረፋ እያካሄዱ ነው ። ከነዚህ መካከል መሠረታቸው የአሜሪካ የሆኑ እንደነ ጀኔራል ሞተርስ ፣ ጀኔራል ኤሌክትሪክ ፣ ፎርድና ሌላም ተመሳሳይ ሞኖፖሊዎች ይገኛሉ ። ከነዚህ ሌላ ከ6000 በላይ የሚሆኑ መለስተኛ የአሜሪካ ኩባንያዎች የዘረፋው ተካፋይ ናቸው። በማዕድን መስክ እንግሊዝና ምዕራብ ጀርመን ቀንደኞቹ ናቸው ። እንግሊዝ በየዓመቱ ለአቶሚክ ኃይል ማስፋፊያ የሚያስፈልጋትን 10,000 ቶን ዩራኒየም የምታገኘው ከዚሁ አገር ነው ። ከማዕድን ፍለጋ ጉንም ኤሶ የተባለው የእንግሊዝ የነዳጅ ኩባንያ 8,500 ስኩዌር ማይልስ ስፋት ያለውን አካባቢ ከልሎ የነዳጅ ዘረፋውን እያጧጧፈ ነው ። ሞቢልና ካልቲክስም ከብሪትሽ ፒትሮሊየምና ሼል ጋራ ሆነው 73 ከመቶ የሚሆነውን የአገሪቷን የነዳጅ ስርጭት በበላይነት ይቆጣጠራሉ ። [25]

ይህንን የመሰለ የተጧጧፈ የተፈጥሮ ሀብት ዘረፋ በማካሄድ ላይ የሚገኙት ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በዚህ ይዞታቸው ሊቆዩ የሚችሉት ዘረኛው መንግሥት እስካለ ድረስ መሆኑን ተገንዝበውታል። ይህንኑ ዘረፋቸውን ለዝንተ ዓለም ለማቆየት በማለትም በደቡብ አፍሪካ የሚካሄደውን የነፃነት ትግል ለማኰላሸት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ። ከዘረኛው መንግሥት ጋር ያላቸው የኢኰኖሚ ግንኙነት በጣም የጠበቀ ከመሆኑም በላይ በወታደራዊ መስክም ከፍተኛ እርዳታ እያደረጉለት ነው ።

ሸብር ፈጣሪው መንግሥት ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በሚያቀብለው የጦር መሣሪያ ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ከዓለም አቀፍ የጦር መሣሪያ አምራች ኩባንያዎች ጋራ በመተባበር በአገሪቷ መሰል ድርጅቶችን በማቋቋም ላይ ነው ። በ1968 ላይ ከ150 ሚሊዮን ዶላር በላይ ካፒታል ያለው የጦር መሣሪያ ማምረቻ ኰርፖሬሽን አቋቁሟል ። ለዚህ ኰርፖሬሽን የኋላ ድጋፍ የሚሰጡ 14 ሞኖፖል ኩባንያዎች ከደቡብ አፍሪካ ሸብር ፈጣሪ መንግሥት ጋራ በመተባበር በደቡብ አፍሪካ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ በማቋቋም ላይ ናቸው ። የአፍሪካ ፈንጅና ኬሚካል ኢንዱስትሪ በሚል ስም የሚታወቀው ኩባንያ በዚህ ትብብር መሠረት በደቡብ አፍሪካ ከተቋቋሙት የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች መካከል አንዱ ነው ።

በእንግሊዝና በፈረንሳይ የተሰሩ ፑማ ሂሊኰፕተሮች

በደቡብ አፍሪካ የፈረንሣይ ፓንሃርድ ብረትለበስ ተሽከርካሪ

Digitized by Google

የጦር መሣሪያ አምራች ድርጅቶች በደቡብ አፍሪካ እየተስፋፉ መምጣታቸውን የቡርዧው ዓለም ጋዜጦች ሳይቀሩ በየጊዜው በሚጽፏቸው ዘገባዎች ላይ እያወጡ ናቸው ። ለንደን ታይምስ የተባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ ጥር 1 ቀን 1969 ባሰፈረው ጽሑፉ ፣ ደፈጣ ተዋጊዎችን እያሰሰ ሊያጠቃ የሚችል ቀላል አይሮፕላን ባሜሪካ ፈቃድ በደቡብ አፍሪካ እየተገጣጠመ መሆኑን ገልጦ ነበር ።

ከዚህም ሌላ በ1969 ሽብር ፈጣሪው መንግሥት 140 የተለያዩ የጥይት ዓይነቶችና ቦምቦችን ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት ከውጭ ኩባንያዎች ጋራ ስምምነት ላይ እንደደረሰ ገልጿል ።[26] ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ የሽብር ፈጣሪው ፖሊሶችና ወታደሮች የሚጠቀሙበት ኤፍ·ኤን የተባለው ጥይት የተሠራው በደቡብ አፍሪካ ሲሆን የዚህም ፓተንት የተገኘው ከኔቶ ነው ።[27]

የኢምፔርያሊስቶች ፖሊሲ ዘረኛው መንግሥት የጦር መሣሪያ ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ሲያመቻች

ኢምፔሪያሊስት አገሮች የዘረኛውን መንግሥት ሕልውና ለማራዘም የሚሞክሩት የጦር መሣሪያ በማቀበልና በደቡብ አፍሪካ የጦር መሣሪያ አምራች ድርጅቶችን በማጠናከር ብቻ አይደለም ። ለረጅም ጊዜና በተለይም ከሻርፕቪል ጭፍጨፋ በኋላ በደቡብ አፍሪካ ሽብር ፈጣሪ መንግሥት ላይ እየተጠናከረ የመጣውን ተቃውሞ ከምንም ባለመቁጠር፣የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መፍትሔ ለማስገኘት የሚያደርጉትን የዲፕሎማሲ ጥረት ሁሉ ለማጨናገፍ መሰሪ የሆነ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም ከደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት ጋራ ያለው ግንኙነት የተጠናከረ ቢሆንም፣ ዘረኛው መንግሥት በደቡብ አፍሪካ የነጻነት ታጋዮች ላይ የሚያካሂደው ጭፍጨፋ ቢባባስም፣ ባሁኑ ጊዜ የደቡብ አፍሪካ ታጋይ ሕዝብ ከ300 ዓመታት በላይ ሲመዘብረው የኖረውን የኢምፔሪያሊዝም የጭቆና አገዛዝና የዘረኝነት ፖሊሲ አራማጅ የሆነውን የጥቂት ነጮች መንግሥት ለመደምሰስና ብዙሀኑን የአገሪቷን ዜጎች የሚወክል ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መንግሥት ለመመሥረት የተጠናከረ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል ። ለዚህም የተቀነባበረ የትጥቅ ትግል ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር በመስጠት ላይ የሚገኘው የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኮንግሬስ ነው ።

የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ትግልና የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኮንግሬስ

የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኮንግሬስ በአሁኑ ወቅት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ለሚካሄደው የአርነት ትግል ተዋጊና ግንባር ቀደም አስተባባሪ ነው። የዚህ ድርጅት አላማ እንደሚያስረዳው ከደቡብ አፍሪካ የኢምፔሪያሊዝምን ሰንኰፍ ነቅሎ መጣልና በአገሪቱ ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎች በሙሉ እኩልነትን በማጎናጸፍ በአንድነት አገራቸውን እንዲገነቡ ማድረግ ነው ።

Digitized by Google

የደቡብ አፍሪካን ሰፊ ሕዝብ የነጻነት ትግል ስንገመግም ሕዝቡ ለጥቂት ነጮች ብዝበዛ ከተዳረገ ጀምሮ ለነጻነቱ ከመታገል የተቆጠበበት ጊዜ እንዳልነበረ ለመረዳት እንችላለን ። ቀንደኞቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የአገሪቷን የተፈጥሮ ሀብት ለመዝረፍ፣ ርካሽ የሰው ጉልበት ለማግኘትና ለወደፊቱም አገሪቷ የሚኖራትን ስትራቴጂካዊነት በመገንዘብ ደቡብ አፍሪካ ላይ ይዞታቸውን በማጠናከር ላይ ናቸው። ለዓላማቸው መሳካት ሽብር ፈጣሪውን የደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች መንግሥት በየደረጃው በጦር መሣሪያ ማጠንከርንና የሕዝቡንም የነጻነት ትግል ማጨናገፍ ያዋጣናል ብለው የተያያዙት የትግል ስልትነው።

የደቡብ አፍሪካን ሕዝብ የነጻነት ትግል ታሪክ ስንመረምር ሕዝቡ ለነጻነቱ መታገል የጀመረው ከአውሮፓ በተለያዩ ጊዜያት ተሰደው በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከተሰባሰቡ በኋላ የራሳቸውን መንግሥት የመሠረቱ አውሮፓውያን ሕዝቡን በገዛ አገሩ መሬት አልባ በማድረግ ሰብአዊ መብቱን መግፈፍ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ። በ1886 የተመሠረተው «እምባምባ ያግ አፍሪካ» የተባለ ውድርጅት ነፃነትን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመጎናፀፍ ሞክር ነበር ። ይህ በ1886 ተመሥርቶ የነበረው እምባምባ ያግ አፍሪካ እና በ1894 በማኀተመ ጋንዲ በደቡብ አፍሪካ ይኖሩ ለነበሩ ሕንዶች ተቋቁሞ የነበረው ናታል ኢንዲያን ኰንግሬስ ያራምዱት የነበረው የትግል ስልት በ20ኛው ምዕተ ዓመት ላይ እንደማይሠራ በመገንዘብ፣ ሌላ መላ ሠርቶ እደሩን የሚያሰባስብና አብዮታዊ አመራር የሚሰጥ ድርጅት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ። ለዚሁ ዓላማ መሳካት የኢንዱስትሪና የንግድ ሠራተኞች ማኅበር የሚባለው ተመሥርቶ በዚሁ ድርጅት አማካይነት ጥቁር አፍሪካውያን የደመወዛቸውን ጣሪያ ለማስወሰንና አንዳንድ መብቶችን ለማግኘት ችለዋል ። ዘረኛው መንግሥት በድርጅቱ ውስጥ የነበሩትን ሠራተኞች አንድነት በመከፋፈል የትግሉን አቅጣጫ ለመቀልበስ ሙከራ አድርጎ ነበር ። ነገር ግን ከብዙ መራራ ትግል በኋላ ተደጎም ብሎ ተመሥርቶ የነበረው የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስ አመራሩን ወስዶ ሕዝባዊ ትግሉን ማቀነባበር ጀመረ ።

የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስ፣ ጥር 8 ቀን 1912 (ከባሱቶላንድ) ሌሶቶ፣ ብቹዋናላንድ (ቦትስዋና)፣ ከርዴሺያ (ዚምባቤ) እና ስዊዝላንድ በተውጣጡ አፍሪካውያን ታጋዮች አማካይነት ብሉምፎንቴን ተብላ በምትጠራው የደቡብ አፍሪካ ከተማ ተመሠረተ ።[28] ይህ ድርጅት እንደተመሠረተ ለዘብተኞች አመራሩን ይዘው ስለነበር ትግሉ ተዳክሞ ነበር ። ይሁን እንጅ ቀስ በቀስ ፀረ አፓርታይድ አቋም ያላቸው ግለሰቦች ኃይላቸውን አስተባብረው ድርጅቱ የተቀነባበረ የትጥቅ ትግል ለማድረግ ወደሚችልበት አቅጣጫ እንዲያመራ አደረጉ።

ዘረኛው መንግሥት የራሱን የመበዝበዣ ተቋሞች ለማጠናከር በየወቅቱ የሚያወጣቸው ሕጎችና ድንጋጌዎች በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት በማጣታቸው የበለጠ ድንጋጤ ላይ ስለጣለው፣ በሕዝቡ ላይ ጭፍጨፋ መካሄዱን ጀመረ ። ይህም ፀረ ሕዝ ብድርጊቱ በ1960 ሻርፕቪል ላይ በፈሰሰው የንጹሐን ሰዎች ደም ይፋ ወጥቷል ።

ዛሬ ስለ ደቡብ አፍሪካ ሁኔታ ለሚከታተል ማናቸውም ሰው ሻርፕቪል ሲባል የሚታወሰው፣ በዚያች ከተማ በዘረኛው መንግሥት የተጨፈጨፉት አፍሪካውያን ናቸው ። በመጋቢት 21 1960 ጥቁር አፍሪካውያን የዘረኛውን መንግሥት ፖሊሲ በመቃወምና በተለይም የይለፍ ሕግ መሰረዝ አለበት ብለው ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። የሻርፕቪልና የላንጋ ከተማ ፖሊሶች በአካባቢያቸው በቆመውና ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደርገው ሕዝብ ላይ የጥይት እሩምታ አዘነቡበት ። የዘረኛው መንግሥት መግለጫ

Digitized by Google

እንደሚያመለክተው በዚህ የተይት ውርጅብኝ በሻርፕቢል 68 አፍሪካውያን ሲሞቱ 272 ቆስለዋል ፤ በላንጋ ከተማ 8 ሲገደሉ 48 ቆስለዋል ። ሰላማዊ ሰልፈኞች ምንም የመከላከያ ትጥቅ አልነበራቸውም ፤ ለመከላከልም የተዘጋጁ አልነበሩም ።

ይህ ጭፍጨፋ የሕዝቡን ቁጣ አገንፍሉት ትምጊው በየቦታው ተዛመተ ። ዘረኛውን መንግሥትም ከፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ከተተው ። ሁኔታውን ለመቆጣጠር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ አሥራ ሁለት ሺህ የሚሆኑ ታጋዮች ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ በእሥር ቤት ታጎሩ ።[29] ትግሉግን በይበልጥ ተቀጣጠለ ። ዘረኛው መንግሥት የማለፊያ ወረቀት ብሎ የሰጣቸውንና የጭቆናቸው አንዱ ምልክት የሆነውን የይለፍ ወረቀት አፍሪካውያን በከተሞች አደባባይ ያቃጥሉ ጀመር ። የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስም ገፊኛው መንግሥት ለወሰደው እርምጃ መልስ የተቃውሞ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ ሕዝቡ እንዲያደርግ ጥሪ አደረገ ። ጥሪው በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ሰልፉም፥ የሥራ ማቆም አድማውም በሰፊው ተካሄደ ። የጥቂት ነጮች መንግሥት በሁኔታው ተደናግጦ ለጊዜው የይለፍ ወረቀት እንዲቀር አደረገ። በወቅቱ ተፋፍሞ የነበረው ትግልም ለ6 ወራት ከቀጠለ በኋላ በረደ ።

የሻርፕቪልና የላንጋ ጭፍጨፋ ለደቡብ አፍሪካ ጭቁን ሕዝብ በተለይም ለአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስ ትልቅ ትምህርት ነበር። ከሻርፕቪል እልቂት በኋላ የሰላማዊ የትግል ስልት ቦታውን ለትጥቅ ትግል ለቀቀ። የተቀነባበረ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ይቻል ዘንድ በታኅሣሥ ወር 1961 ላይ «እምኩንቶ ዌ ሲዚዌ» (የብሔር ጦር) የተባለውን ሕዝባዊ ጦሩን መሥርቶ ፥ በዚሁ አማካይነት በዘረኛው መንግሥት የጦር ሰፈሮችና ፥ በሌሎችም ስትራቴጂያዊ ተቋሞች ላይ የማጥቃት ዘመቻውን ጀመረ ። የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስ ሥር በመስደድ በሠራተኛው መደብ መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቀባይነቱን ማሳደጉን ቀጠለ። ሕዝባዊ ጦሩም በርካታ ታጋዮችን በመመልመል ኃይሉን አጠናከረ ። በገጠሩም ሕዝቡን በማስተማርና በማደራጀት ጠንካራ ፀረ አፓርታይድ ቅስቀሳ እያደረገ ሕዝባዊ ድጋፍ አግኝቶ ከቀን ወደ ቀን በድል ላይ ድልን እየተቀዳጀ መጣ ።

የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስ ወታደራዊ ክንፍ እየተጠናከረ መምጣት የዘረኛው መንግሥት ደጋፊ የሆኑት የእንግሊዝ ፥የምዕራብ ጀርመን ፥ የዩናይትድ ስቴትስ ፥ የፈረንሣይና የመሳሰሉት ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት የሚሰጡትን የፖለቲካ፥ የኤኮኖሚና የወታደራዊ ድጋፍ ይበልጥ እንዲያጠናክሩ አድርጓቸዋል ። የዘረኛው መንግሥት የኑክሌር ኃይል ባለቤት ለመሆን መቃረቡም ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው ። ይሁን እንጂ የመግሪያ ጋጋታና የተቀነባበረ የአድሃሪያን ሤራ ሲመዘበርና ሲረገጥ የኖረን ሕዝብ ትግል ለዘለዓለም አፍኖ ማስቀረት እንደማይችል ታሪክ ህያው ምስክር ነው ። በደቡብ አፍሪካ በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ ትግል እየተፋፋመና እያደገ መምጣት ይኸንኑ ሐቅ ያረጋግጣል ።

የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስ ዘላቂ ነጻነትን ለማግኘት በወታደራዊ ክንፉ አማካይነት ከሚያካሂደው የትጥቅ ትግል ባሻገር የነፃነት ፕሮግራሙን በመንደፍ ሕዝቡን ለመጨረሻ ፍልሚያ በማሰለፍ ላይ ይገኛል። በነጻነት ፕሮግራሙ ውስጥ «ሕዝቡ የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዲኖረው ፤ ደቡብ አፍሪካ በውስጧ ለሚኖሩ ዜጎችዋ ነጭ ፥ ጥቁር ፥ ክልስ ሳትል የጋራ መሆንዋን ፥ ነጻ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች፥ ማንም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን፥ የሕዝቡ ሰብአዊ መብት ስለመከበሩ ወዘተ...»[03] በዝርዝር ተጠቅሷል ። በዚሁ ፕሮግራም መሠረት ዘረኝነትና ጭቆና የሌለበት ዲሞክራሲያዊት ደቡብ አፍሪካን ለመመሥረት

Digitized by Google

በሚደረገው ትግል ሕዝቡ በጀግንነትና በቆራጥነት ከተዋጊው ጦር ጎን ተሰልፎ በመታገል ላይ ይገልኛ ።

ይህ የተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግልና ተቃውሞ እያየለ በመሄዱ ሽብር ፈጣሪው መንግሥት በርካታ ታጋዮችን ወደ እሥር ቤት በማጋዝ ትግሉን ለመግታት በመሞከር ላይ ነው ። ሰብአዊ መብትን በመጠየቃቸው ብቻ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው በርካታ ሰዎች ዛሬ በደቡብ አፍሪካ እስር ቤቶች ውስጥ ታጉረው ይገኛሉ ። በ1973 እና በ 1974 ብቻ የኤ. ኤን. ሲ. ወታደራዊ ክንፍ ባቀነባበረው ጥቃት ዘረኛው መንግሥት ተደናግጦ 625,000 ሰዎችን አሥሯል ። ከነዚህ መካከል 342,000 እሥረኞች የእሥራት ቅጣት የተፈረደባቸው ሲሆኑ 263,000 የሚሆኑት ደግሞ አለፍርድ የታሠሩ መሆናቸውን ታውቋል ።[31] እሥራት ከተፈረደባቸው 342,000 እሥረኞች መካከል 288,000 ጥቁር አፍሪካውያን ፣ 45,000 ክልሶች ፣ 7,000 ነጮች ፣ 1,500 ሕንዶች ሲሆኑ ፣ በዕድሜ ክልልም ከ21—29 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው ። እነዚህ ዘረኛው መንግሥት የሚኖራቸውን ኢሰብአዊ ድርጊቶች የተቃወሙና ለሰብአዊ መብት የቆሙ እንጂ ዘረኛው መንግሥት እንደሚያናፍሰው የሕብ ፀጥታ የነሱ አይደሉም ።

በየጊዜው በማደግ ላይ ያለው የትጥቅና የዲፕሎማሲ ትግል ዘረኛውን መንግሥት አስጊ ሁኔታ ላይ ስለጣለው በየቀኑ የሚታሠረው ሕዝብ ብዛት በ36 በመቶ እያደገ ነው ። የእሥረኞችን ሁኔታ በሚመለከት <u>የአፍሪካ ሬኮርድ</u> የተሰኘው መጽሔት ሲያትት ፤ የአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስ ከተመሠረተ ከአንድ ዓመት በኋላ ማለትም ከ1913 አንስቶ እስከ 1974 ድረስ በሽብር ፈጣሪው መንግሥት ያለአግባብ የታሠሩትን ሰዎች ብዛት[32] ከታች በሠፈረው ቻርት መሠረት ፣ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

ከታች የቀረበው ቻርት እንደሚያስረዳው ዘረኛው መንግሥት የአፍሪካውያንን ተቃውሞ ለመቆጣጠር ከወሰደው እርምጃ አንዱ አፍሪካውያንን ማሰር ነው ። ሆኖም የሰዎች መታሰር የነፃነት ትግሉን አፍኖ ለማስቀረት ፍጹም አልቻለም ። በሶዌቶ በ1976 ተቀጣጥሎ የነበረው ሕዝባዊ ትግል ለዚሁ ቋሚ ምስክር ነው ።

ሶዌቶ ጆሐንስበርግ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ናት። በዚች ከተማ ሰኔ 16 ቀን 1976 ጥቁር አፍሪካውያን ተማሪዎች የዘረኛውን

	1913	1974	ዕድገት በመቶ
የሕዝብ ብዛት	6,000,000	24,924,000	315
እሥረኛ ብዛት	97,000	545,000	461
በየዕለቱ በእስርቤት የሚገኙ እሥረኞች አማካይ ብዛት	14,468	98,851	581
ለእሥር ቤቶች የተደረገ ወጭ /በራንድ/	1,000,000	41,000,000	4,032

Digitized by Google

መንግሥት የትምህርት መመሪያ በመቃወም ሰላማዊ ሠልፍ አደረጉ ። እንቅስቃሴው በጥቁር አፍሪካውያን ይጀመር እንጂ ክልሶች ፣ ሕንዳውያን ፣ ነጭ ተማሪዎች ፣ ሠራተኞችና ሌሎችም የእንቅስቃሴው ደጋፊዎች በሰልፉ ተሳትፈዋል ። በሰኔ ወር የተቀጣጠለው ትግል በነሐሴ ወር በመላው ደቡብ አፍሪካ ተስፋፍቶ ዘረኛውን መንግሥት ብሔራዊ ቀውስ ውስጥ ከተተው። በሰላማዊ ሠልፍ የተጀመረውም የተማሪዎች ትግል የሌሎችን የኅብረተሰቡ ክፍሎች ተሳትፎ ጥያቄዎች በመጨመር በይዘቱና በደረጃ ከፍብሎ ወደ ፖለቲካ ትግል በመለወጡ የነጮችን አገዛዝ ለማስወገድ የሚደረግ ትግል ሆነ ።

በእንቅስቃሴው በመደናገጡና ትግሉን ለማኰላሸት በመቻኰል ዘረኛው መንግሥት አንዳንድ የትምህርት ፖሊሲ ለውጥ እንደሚያደረግ ቢቀባጥርም ተቀባይ አጣ። በሕቡዕ የሚሠራው የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግረስም ገና ከመጀመሪያው የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በመደገፍ በትግሉ ተሳተፈ ። በዚያው አንፃር ዘረኛው መንግሥት ጭፍጨፋውን ተያያዘው ። በዚሁ ጭፍጨፋ ከ 1000 ያላነሱ አፍሪካውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል ። ብዙ ወጣቶችም ይህን የከፋ ጭፍጨፋ ለመቋቋም መሠልጠንና ትጥቅ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በመገንዘብ ወደ ጐረቤት ነፃ አፍሪካ አገሮች ተሰደው በነዚህ አገሮች ውስጥ በአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግረስ መሪነት ወታደራዊ ስልጠና በማግኘት ላይ ናቸው ።

በደቡብ አፍሪካ የሠራተኛው መደብ ትግል

የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ ትግል በአፍሪካ ውስጥ ረጅም ታሪክ ያለው ነው ። የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ ለመደብ ጥቅሙ መቆምና መታገል የጀመረው ሞኖፖሊስቶች የደቡብ አፍሪካን ወርቅና አልማዝ መመዝበር ከጀመሩበት ከ1880ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ጀምሮ ነው ። የሲስል ሮድስ የማዕድን ኩባንያ የደቡብ አፍሪካ ሠራተኞችን በመበዝበዝ ከታወቁት ሞኖፖሊስቶች መካከል የመጀመሪያው ነበር ። « ደ ቢርስ ኰንሶሉዴትድ ማይንስ » (De Beers Consolidated Mines) የተባለው የአልማዝ ሞኖፖል ኩባንያ የሚያካሄድባቸውን ብዝበዛ በመቃወም በኪምበርሊ አካባቢ የሚገኙ የማዕድን ሠራተኞች በ1882 ለከፍተኛ ምንዳና ለተሻለ የሥራ ሁኔታ የሥራ ማቆም አድማ አድርገው ነበር ።

በዓለም ላይ አንጋፋ ከሆኑት የኰምዩኒስት ፓርቲዎች መካከል የደቡብ አፍሪካ ኰምዩኒስት ፓርቲ አንዱ ነው ። የደቡብ አፍሪካ ኰምዩኒስት ፓርቲ የተመሠረተው በ1921[33] መሆኑ ፣ በደቡብ አፍሪካ የሠራተኛው መደብ ትግል ረጅም ታሪክ ያለው ለመሆኑ ቋሚ ምስክር ነው ።

ይህ ፓርቲ በአሁኑ ወቅት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሕጋዊ መድረክ አግኝቶ የሚሠራ ቢሆንም ፣ ሕጋዊ መድረክ ከተነፈገውና በሕቡዕ በመሥራት ላይ ከሚገኘው ከአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግረስ ጋር ግንባር በመመሥረት ፀረ አፓርታይድና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

በአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግረስና በደቡብ አፍሪካ ኰሚኒስት ፓርቲ ድጋፍና አመራር በ1920ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተመሠረተው የኢንዱስትሪና የንግድ ሠራተኞች ማኅበር ፣ በኰሚኒስት ፓርቲውና በአፍካውያን ብሔራዊ ኰንግረስ መካከል ላለው የትግል አንድነት ተግባራዊ መግለጫ ነው ። ቀደም ሲልም እንደተጠቀሰው የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ የሙያ ማኅበር የሆነው የኢንዱስትሪና የንግድ ሠራተኞች ማኅበር ሲመሠረት ከሺህ የማይበልጡ አባላት ነበሩት ፤ በተመሠረተ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ብቻ በውስጡ በነበሩ ኰምኒስ

Digitized by Google

ቶች ብርታት ከ250,000 በላይ አባላት ሊኖራት በቃ ። ጥቍሮች፣ ክለሶችና የእርሻ ሠራተኞች በዚህ ማኅበር ጀርባ በመሰባሰብ ከፍተኛ ትግል ሲያካሄዱ ቆይተዋል ። በ1925 በብሎምፎንቴን የሚገኘው የዚሁ ማኅበር ቅርንጫፍ አባላት ከዘረኛው መንግሥት ፖሊስ ጋር ባደረጉት ግጭት 5 ሰዎች ሲሞቱ ከ60 በላይ ቆስለዋል ። የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ የሙያ ማኅበር የሆነው የኢንዱስትሪና የንግድ ሠራተኞች ማኅበር በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም ። በደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የቻለበትም ምክንያት ከኢኮኖሚ ጥያቄ ባሻገር የፖለቲካ ጥያቄም ይዞ በመነሳቱ ነው ። ይኸ ለመሆኑ በሕገ ማኅበሩ መግቢያ ላይ

የሠራተኞችና የካፒታሊስት አሠሪዎች ጥቅም በተፃራሪነት የቆሙ ናቸው ፤ የመጀመሪያዎቹ የሥራ ኃይላቸውን ሸጠው ከሚያመርቱት ሀብት የተወሰነውን ብቻ ሲያገኙ የኋላኞቹ ደግሞ የሠራተኛውን የሥራ ኃይል በመበዝበዝና የሠራተኞች የሥራ ፍሬ ከሆነው የተወሰነውን በትርፍ መልክ የሚወስዱ በመሆናቸው በሁለቱ መደቦች መካከል ሰላም ሊኖር አይችልም ። ሠራተኞች በኢንዱስትሪ ድርጅታቸው አማካይነት ከካፒታሊስቱ የምርት ማከናወኛዎችን ነጥቀው እራሳቸው በመቆጣጠር ለጥቂቶች የሚውለውን ትርፍ ለሠራተኞች ጥቅም እንዲውል እስካደረጉበት ጊዜ ድረስ ፣ የሥራ ኃይል ውጤት የሆነውን ሀብት በመከፋፈሉ ረገድ በሁለቱ መደቦች መካከል ሁልጊዜም ትግል ይኖራል ... በዚህ ሥርዓት መሠረት የማይሠራ ሁሉ አይበላም . . . [34] የሚል ሠፍሮ ይገኛል ።

የኢንዱስትሪና የንግድ ሠራተኞች ማኅበር በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠርም የመሬት ጥያቄ በማንሳት ገበሬዎችን በብዛት በአባልነት በመመልመል ላይ ነው ። የዚህ ማኅበር ቅርንጫፍ ማኅበራት በአብዛኞቹ የደቡብ አፍሪካ ከተሞች ውስጥ ተቋቁመዋል ። እንዲያውም ቀደም ባለው ጊዜ ከደቡብ አፍሪካ ክልልም ውጭ በናሚቢያ በቀድሞዋ ሮዴሺያ፤ በዛምቢያ፣ በማላዊና በሞዛምቢክ ጭምር ቅርንጫፎች ነበሩት ።

በአሁኑ ወቅት የደቡብ አፍሪካ የሠራተኛ መደብ በአፍሪካውያን ብሔራዊ ኰንግሬስ አመራር የሠራተኞች ማኅበር ኰንግሬስ /SACTU/ የሚል መጠሪያ ባለው የሙያ ማኅበሩ ሥር በመሰባሰብ ከዘረኛው መንግሥት ጋር ቀደም ሲልም ያካሄሂድ የነበረውን ትግል ቀጥሏል ።

በ1980 ይኸው ማኅበር ባቀነባበረው አጠቃላይ የሥራ ማቆም አርምጃ በኢንዱስትሪዎችና በልዩ ልዩ ተቋሞች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ተሳትፈዋል ። የብሔራዊ ልማትና አመራር የተባለው ድርጅት በ1970ና በ1980 ከተደረጉት የሠራተኛ የሥራ ማቆም አድማዎች መካከል የጥቂቶቹን ሁኔታ እንደሚከተለው መዝግቦ ነበር ።

—በ1979 ፣36ጊዜ የሥራ ማቆም አድማ ተደርጉ ከ21,000 ሠራተኞች በላይ ሥራ አቁመዋል ።

—በ1980 መጨረሻ ላይ 61 ጊዜ የሥራ ማቆም አድማ ተደርጎ 95,000 ሠራተኞች ተካፋይ ሆነዋል ።

— በዚሁ ተቃውሞ 19 የሠራተኛ ድርጅቶች ተካፋይ ሲሆኑ የሥራ ማቆም እርምጃዎች መንስኤ የሆኑትም የደመወዝ ጭማሪና የተሻለ ኑሮ ፣ ከሥራ ያለአግባብ አለመባረርን ፣ በሠራተኛው መሪዎች ላይ ጥቃት እንዳይደርስና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሲሆኑ ከዚህም ባሻገር የተግል አንድነት ጥሪንም ያጠቃለሉ ነበሩ ። [35]

ይኸው የሥራ ማቆም አድማ ወደ ትላልቅና መለስተኛ ከተሞች ባጠቃላይም መላው የሠራተኛ መደብ ወደሚገኝበት አካባቢ ተሠራጭቶ የሕዝቡ የነፃነት ስሜት እስተጋብቷል ። የተነሱት ጥያቄዎች አዲስ ባይ

Digitized by Google

ሆኑም ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረጉት
ሥራ ማቆም አድማዎች ዓይነተኛ ጠባይ
በያለበት የተቀጣጠሉ መሆናቸው ፡ ሕዝ
ቡም ለሥራ ማቆም እርምጃው የሰጠው
ድጋፍና ለሠራተኛው የተደረገለት የማቴ
ሪያልና የሞራል ድጉማ ከፍ ማለቱ ነው ።
ይኸም የሕዝቡ ትግል ከመቼውም ጊዜ የበ

የኤ.ኤን.ሲ. የነፃ አውጭ ተዋጊ ጦር አባሎች በሰልፍ ላይ

ለጠ አስተማማኝ ደረጃ ላይ መድረሱን ያመ
ለክታል ።

በአሁኑ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ የሚካሄ
ደው ትግል ሰላማዊና ሰላማዊ ያልሆነ የት
ግል ዘዴን የሚያጠቃልል ነው ። የሠራተ
ኛው መደብና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች
ሕጋዊ መድረኩን በመጠቀም ከሚያካሂ
ዱት ትግል በተጨማሪ በኤ. ኤን. ሲ. የሚ
መራው የትጥቅ ትግል በዘረኛው መንግ
ሥት ላይ የከፈተውን ጦርነት በከፍተኛ
ደረጃ በማፋፋም ላይ ይገኛል ።

የአፍሪካ ብሔራዊ ኰንግሬስ ፕሬዚዳንት
ጓድ ኦሊቨር ታምቦ በቅርቡ የኒው ታይምስ
ተወካይ የትጥቅ ትግሉን በማስመልከት
ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ፡ በአሁኑ
ወቅት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚካሄዱ
ወታደራዊ ጥቃቶች የሚከናወኑት በኤ.
ኤን. ሲ. ወታደራዊ ክንፍ አማካይነት እን
ደሆነ ፡ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ በዘ
ረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት የተመ
ረጡ ስትራቴጂያዊ ኢላማዎች ላይ የሚደ
ረገው ጥቃት እየጨመረ መምጣቱን ፡ ከዚ
ህም አልፎ በተለይ ከ1981 ጀምሮ የኤ. ኤን.
ሲ. ወታደራዊ ክንፍ ከዘረኛው መንግሥት
ወታደሮች ጋር በግንባር እየገጠመ ማጥቃት
መጀመሩንና የነፃነት ተዋጊ ጦሩም ወታደ
ራዊ ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ
መሄዱን ገልጸዋል ።

ሁኔታው እንደዚህ በመሆኑም የኤ. ኤን.
ሲ. ወታደራዊ ክንፍ በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ
ቦታዎችን በአንድ ጊዜ የማጥቃት ችሎታ

Digitized by Google

እስከማግኘት ደርሶአል ። ከትጥቅ ትግሉም ጐን ለጐን ኤ. ኤን. ሲ. በሕዝቡ ውስጥ የፖለቲካ ሥራውን በማጠናከር ላይ ነው ። የሶሻሊስቱ ማኅበረሰብ አባል አገሮች በተለይም ሶቪዬት ኅብረትና መላው ተራማጅ ዓለም ለደቡብ አፍሪካ የነፃነት ትግል የሚሰጡት የፖለቲካ ፣ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ፣ የደቡብ አፍሪካ ተዋጊዎች በማቀናጀት ለሚያካሂዱት የፖለቲካና የትጥቅ ትግል ተጨማሪ ብርታት እየሰጠው ነው ። በመሆኑም የፈለገውን ያህል መሥዋዕትነት ቢጠይቅም ፣ ሐቀኛና ትክክለኛ ዓላማ ይዞ የተነሳው የደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግል በመጨረሻ የድሉ ባለቤት እንደሚሆን አያጠራጥርም ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Neva Makgetla and Ann Seidman, *Outposts of Monopoly Capitalism: Southern Africa in the Changing Global Economy*, Zed Press, London, 1980, p. 61.
2. William J. Pomeroy, *Apartheid Axis: USA and South Africa*, International Publishers, New York, 1977, p. 13.
3. Richard Gibson, *African Liberation Movements: Contemporary Struggles Against* Minority Rule, Oxford University Press, London, 1972, p. 29.
4. Leslie Rubin & Brain Weinstein, *Introduction to African Politics: A Continental Approach*, Praeger Publishers, New York, 1974, p. 107.
5. International Defence and Aid Fund for Southern Africa, *This is Apartheid: A pictorial Introduction*: London, 1978, p. 4.
6. Richard Gibson, Ibid, p. 25.
7. *Ibid.*, p. 20.
8. George Padmore, *Africa: Britain's Third Empire*, Dennis Dobson Ltd. London, 1949, p. 22.
9. Leslie Rubin & Brain Weinstein, Ibid, p. 121.
10. African National Congress, *South Africa is Coming Back*, Inkululeko Publications, London, 1979, p. 9.
11. William J. Pomeroy, Ibid, p. 18.
12. Bernard Makhoseezwe, *The Political Economy of Race and Class In South Africa*, Monthly Review Press, London & New York, 1979, p. 134.
13. A. Lerumo, *Fifty Fighting Years: The South African Communist Party*, 1921-1971, 2nd edition, Inkululeko Publications, London, 1980, p. 23.
14. G. Lanning with M. Mueller, *Africa Undermined: A History of the Mining Companies and the Underdevelopment of Africa*, Penguin Books Ltd, London, 1979, pp. 100-101 and 110-111.
15. Neva Makgetla and Ann Seidman, *Ibid.*, p. 135.
16. *Ibid.*, p. 122.
17. International Defence and Aid Fund for Southern Africa, Ibid, p. 8.
18. William J. Pomeroy, Ibid, p. 19.
19. Patrick Duncan, *South Africa: Rule of Violence*, Methun and Co. Ltd., London, 1964, pp. 125-127.
20. African National Congress, Ibid, p. 21.
21. *Ibid.*, p. 22.
22. Taken from New Times, No. 13, March 1982, p. 17.
23. William J. Pomeroy, Ibid, p. 47.
24. አዲስ ዘመን ፣ ኢ.አ ፣ ሚያዝያ 22 ቀን ፣ 1973 ፣ ገጽ 8
25. Organization of Solidarity of the Peoples of Africa, Asia and Latin America, *Tricontinental*, Number 69-70, Havana, 1980, p. 11.
26. William J. Pomeroy, Ibid, p. 26.
27. *Ibid.*, p. 34.
28. Richard Gibson, Ibid, p. 39.
29. Bernard Makhoseezwe Magubane, Ibid, p. 313.
30. Gwendolen M. Carter and Patrick O'Meara, *Southern Africa; The Continuing* Crisis, Macmillian International College, London, 1980, p. 105.
31. Colin Legum, Africa: *Contemporary Record, Annual Survey and Documents* 1975/76, Africana Publishing Company, New York, 1976, p. B-605.
32. *Ibid.*, p. B-605.
33. A. Lerumo, Ibid, p. 38.
34. *Ibid.*, p. 48.
35. The South African Communist Party, *The African Communist, No.* 85, 2nd Quarter, London, 1981, p. 21.

Digitized by Google

የቅኝ አገዛዝ የመጨረሻዎቹ ቅሪቶች

እ.ኤ.አ. ከ1960ዎቹ ጀምሮ ባለው አጭር ጊዜ ውስጥ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች ባስመዘገቡት ከፍተኛ ድል የተነሳ በዛ ያሉ ቅኝ ግዛቶችን በመያዝ የታወቁ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ሊያንሠራሩ በማይችሉበት አኳኋን ተዳክመዋል ። 10 ሚሊዮን ስኩዌር ኪሎ ሜትር ያህል በሚሆን የቦታ ክልል ላይ የሚኖሩ 140 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕዝቦች የቅኝ አገዛዝ ቀንበርን አሽቀንጥረው ጥለዋል ። በአንድ ወቅት ኃያል የነበረው የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ተንኰታኩቷል ። በፈረንሣይ ፣ በቤልጅግና በሆላንድ የቅኝ ግዛት ቀንበር ሥር የነበሩ ሕዝቦች ነፃነታቸውን ተጐናጽፈዋል ። የመጨረሻውም በቅኝ ግዛቶች ላይ ተመስርቶ የነበረው የፖርቱጋል የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትም (እ- ኤ- አ) በ1975 በሞዛምቢክና በአንጎላ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች ትግል ተሸንፎ ከታሪክ መድረክ ተሰናብቷል ።

ይሁንና አሁንም ቢሆን ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣቱ ሂደት (PROCESS OF DE-COLONIZATION) ጨርሶ አልተከናወነም። አሁን በያዝነው በ1980ዎቹ ዓመታት ውስጥ 0.3 በመቶ የሚሆነው የዓለም ሕዝብና 1 በመቶ የሚሆነው የዓለም ግዛት የተለያየ ስያሜ ቢሰጠውም ገና በቅኝ አገዛዝ ሥር ነው ።

በ1981 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ባወጣው ዲክላሬሽን ላይ ነፃነታቸውን የሚጐናጸፉ ቅኝ ግዛቶች (በትረስትና በራስ አስተዳደር ሥር ያልሆኑ)በሚል ርዕስ ሥር ወደ 20 የሚጠጉ ግዛቶችን አስፍሯል። እነኝህ ወደፊት ነፃነታቸውን የሚቀዳጁና በአሁኑ ጊዜ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉ ግዛቶች ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት ከ6 ሚሊ

አህጉር	ግ ዛ ት	ቅኝ ገዥው አገር	ስፋት በስኩዌር ኪ/ሜትር	የሕዝብ ብዛት
እስያ	ብሩኔ	እንግሊዝ	5,765	190,000
	ምሥራቅ ቲሞር * (የቀድሞው ፖርቹጊዝ ቲሞር)	—	14,925	637,000
አትላንቲክ ውቅያኖስና የካሪቢያን ባሕር	ቤርሙዳ ደሴቶች	እንግሊዝ	53	60,000
	የእንግሊዝ ቨርጂን ደሴቶች	እንግሊዝ	153	12,000
	የአሜሪካ ቨርጂን ደሴቶች	አሜሪካ	344	100,000
	ኬማን ደሴቶች	እንግሊዝ	259	14,000
	ሞንትሴራት	እንግሊዝ	98	12,000
	ፖርቶሪኮ **	አሜሪካ	8,896	3,300,000
	ቅድስት ሂለና ደሴት	እንግሊዝ	122	5,000
	ቅዱስ ክርስቶፈር ንቪስ አንጓየላ ደሴቶች	እንግሊዝ	357	70,000
	ተርክስና ኬኩስ ደሴቶች	እንግሊዝ	430	7,000
→	ፎክላንድ (ማልቪናስ) ደሴቶች	እንግሊዝ	11,961	1,800
አፍሪካ	ምዕራብ ሰሐራ * * * (የቀድሞው የስፓኒሽ ሰሐራ)	264	266,000	140,000
	ናሚቢያ * * * *	ደቡብ አፍሪካ	824,292	12,000,000
አውሮፓ	ጅብራልታር	እንግሊዝ	6	30,000
ፓስፊክና ሕንድ ውቅያኖስ	አሜሪካ ሳሞዋ	አሜሪካ	197	28,000
	ጉአም	አሜሪካ	549	100,000
	ኩኮስ (ኩሊንግ) ደሴቶች	አውስትራሊያ	14	1,000
	ፒቲካይሪን (PITCAIRN)	እንግሊዝ	5	100
	ማይክሮኒሽያ (የፓስፊክ ደሴቶች)	አሜሪካ	1,779	115,000
	ቶኬላው	ኒውዚላንድ	10	1,800

* በሰኔ 1974 ፖርቱጋል የምሥራቅ ቲሞር ሕዝቦችን ነፃነት አወቀች ። በ1979 ኢንዶኔዥያ ...ህን ግዛት እንደ 27ኛው ክፍለ ሀገር በማድረግ አጠቃለው ያዘው ። ይሁንና የምሥራቅ ቲሞር ...ላይ በየዓመቱ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በመቅረብ ላይ ነው ።

* * በ1952 የአሜሪካ መንግሥት ፖርቶሪኮ ከአሜሪካ ጋር በነፃ የተዋሀደ ግዛት ነው በማለት ...ንደ አንድ የአሜሪካ ክፍለ ግዛት (State) አርጐ ቢወስደውም ፤ የተባበሩት መንግሥታት የዲ...ሎናይዜሽን ኮሚቴ ባቀረበው መሠረት የፖርቶሪኮ ሕዝቦች ነፃ መንግሥት የማቋቋም መብታቸው ...ከበር እንዳለበት የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በተደጋጋሚ ወስኗል ።

* * * በ1976 ስፔን በስፓኒሽ ሰሐራ ያለውን የግዛት ጥያቄ ጨርሶ ያነሳ መሆኑን አስታወቀ ። ...ዲያውኑ የሞሮኮ መንግሥት በምዕራብ ሰሐራ ላይ የይገባኛል ጥያቄ በማንሳት ወታደሮቹን ላከ ። ...ሁንና የምዕራብ ሰሐራን የወደፊት ዕድል ለመወሰን በፖሊሳሪዮ ግንባር የሚመራ የአርነት ንቅናቄ ...መካሄድ ላይ ይገኛል ።

* * * * በ1966 የተባበሩት መንግሥትታ ጠቅላላ ጉባኤ የደቡብ አፍሪካን የአስተዳዳሪነት ሥልጣን ...መሻር ናሚቢያን በቀጥታ በተባበሩት መንግሥታት ሥር እንድትተዳደር ቢወስንም ፤ ዘረኛው ...ደቡብ አፍሪካ መንግሥት ይህን ውሳኔ በመጣስ እስከሁን ናሚቢያን ይዞ ይገኛል ። በአሁኑ ጊዜ ...ሚቢያን ከዘረኛው መንግሥት ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ስዋፖ ትግሉን በማፋፋም ላይ ይገኛል ።

Digitized by Google

የን ቀዊት በለቀ ያለ ነው ። በለፈው ገፅ ላይ የቀረበው ቻርት * በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ዲክላሬሽን መሠረት ከቅኝ አገዛዝ ተላቀው ነፃነታቸውን መጐናጸፍ አለባቸው የተባሉ ግዛቶችን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያመለክት ነው ።

እነዚህ ቅኝ ግዛቶች በኦፊሴል በወጣው የተባበሩት መንግሥታት ሊስት ላይ የሠፈሩ ሲሆኑ ፤ ሌሎች በዚህ ሊስት ላይ ያልተጠቀሱ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ ፣ በአሜሪካና በሌሎችም የተደጥ ቅኝ ገዥዎች የተለያየ መጠሪያ የተሰጣቸው ቅኝ ግዛቶች አሉ ። በነዚህ ለጊዜው በተባበሩት መንግሥታት ሊስት ውስጥ ባልገቡ የደሴት ግዛቶች ውስጥ ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል ።

—የዲያጐ ገራሲያ ደሴትና የሻጐስ አርቺፒላጐ ፣ እንዲሁም ሆንግኩንግ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ፤

—ጓዳሉፕ ፣ ማርቲኒክ ፣ የፈረንሣይ ጊያና ፣ የቅዱስ ፒዬሪና ማይኳሎን ደሴቶች፣ ሪዩንየን ፣ አዲሱ ካሌዶንያ፣ የፈረንሣይ ፖሊኒዥያ ፣ ዋሊስና ፉቱና ደሴቶች በፈረንሣይ ኢምፔሪያሊዝም ፤

—በምዕራብ ፓስፊክ ወደ 2ሺህ የሚሆኑ የተበታተኑ ማይክሮኒሺያ በመባል የሚታወቁ የደሴት ግዛቶች በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ፤

—በካሪቢያን ባሕር የሚገኙ ስድስት ደሴቶች በሆላንድ ፤

—በስሜን አፍሪካና በሩቅ ምሥራቅ የሚገኙ ሁለትና ሦስት የሚሆኑ አነስተኛ ግዛቶች በስፔንና በፖርቱጋል ተይዘው ይገኛሉ ።

በአጠቃላይ ኦሽያና እየተባለ በሚታወቀው ስፋት ባለው ቦታ ውስጥ የሚገኙ 15 የሚሆኑ ደሴቶችና አርኪፖላጐዎች በአሜሪካ ፣ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሣይ ፣ በሆላንድና በአንዳንድ ሌሎች ካፒታሊስት አገሮች ተይዘው ይገኛሉ ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የፎክላንድ ደሴቶች ጉዳይም ቀደም ሲል ከሠፈረው ቻርት ላይ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ፤ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ከቅኝ አገዛዝ ሊላቀቁ ይገባል ብሎ ውሳኔ ካስተላለፈባቸው የመጨረሻዎቹ ቅኝ ግዛቶች መካከል ይገኝበታል ።

እንደሚታወቀው እ.አ.አ. ከሚያዝያ ወር 1982 ጀምሮ በፎክላንድ ደሴቶች ምክንያት በእንግሊዝና በአርጀንቲና መካከል ያልታወጀ ጦርነት በመካሔድ ላይ ይገኛል ። ከተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የዲኮሎናይዜሽን ውሳኔ አንጻር በእንግሊዝና በአርጀንቲና መካከል የተነሳውን ግጭት እንዴት እንመለከተዋለን ? ይህን ጥያቄ በቀጥታ ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት ግን ስለፎክላንድ (ማልቪናስ) ደሴቶች ታሪክ የመዘገበውን ሁኔታ መዳሰስ ያስፈልጋል ። * *

የፎክላንድ ደሴቶች አርጀንቲና ማልቪናስ በማለት የምትጠራቸው በደቡብ ምዕራብ አትላንቲክ ከአርጀንቲና ድንበር 480 ኪሎ ሜትር ርቀው የሚገኙ ናቸው ። ፎክላንድ (ማልቪናስ) ሁለት ትላልቅና ሁለት መቶ ትናንሽ ደሴቶችን የሚያጠቃልል 11,961 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውና 1,800 የሚሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት ግዛት ነው ።

የፎክላንድ ደሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኙት የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ኃይሎች ዓለምን እንደቅርጫ መቀራመት በጀመሩበት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ። አርጀንቲና ደሴቶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኙት በ1520

* INTERNATIONAL AFFAIRS, MOSCOW, 1982, No. 3, p. 147.

** News Week, May 10, 1982, pp. 52-53.

Digitized by Google

በስፔኑ መርከበኛ በእሴቱባን ጉሚዝ ነው
ስትል ፤ እንግሊዝ ደግሞ 1592 በእንግሊዙ
የመርከብ ካፒቴን በጆን ዳቪስ ነው ትላ
ለች ። በዚህም ሆነ በዚያ እስከ 19ነኛው
መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የፎክላንድ (ማል
ቪናስ) ደሴቶች ቦይነስአይረስ ይቀመጥ
በነበረው በስፔን ዘውድ ተወካይ ሥር
ሲተዳደሩ ቆይተዋል ። በ19ነኛው መቶ
ክፍለ ዘመን የደቡብ አሜሪካ አገሮች ባካ
ሔዱት የብሔራዊ ነፃነት ትግል በዚያ አህ
ጉር የስፔን ቅኝ ግዛቶች አንድ ባንድ ነፃ
መውጣት ጀመሩ ። አርጀንቲና መጀመሪያ
በስፔን ቅኝ አገዛዝ ሥር ሁና በኋላም ነፃ
ከወጣችበት ከ1820 ጀምሮ በፎክላንድ ደሴ
ቶች ላይ ይኖሩ ለነበሩ ዜጐቿ አገረገዥ
ሹማ እስከ 1833 ድረስ ደሴቶችን የግዛት
ክፍሏ አርጋ ቆይታለች ።

የፎክላንድ ደሴቶች ከእንግሊዝ የ12,000
ኪሎ ሜትር ርቀት ቢኖራቸውም ፣ በ1833
የእንግሊዝ መንግሥት ደሴቶቹን በወታደ
ራዊ ኃይል በመውረር ፣ በወቅቱ በደሴቶቹ
ይኖሩ የነበሩትን የአርጀንቲና ዜጐችና የአ
ርጀንቲናውን አገረገዥ ደሴቶቹን ለቀው
እንዲወጡ ካደረገ በኋላ የፎክላንድ ደሴ
ቶች የእንግሊዝ መንግሥት አካል እን
ዲሆኑ አደረገ ።

ምንም እንኳ እንግሊዝ በፎክላንድ ላይ
ያላትን የባለቤትነት መብት ከስፔን እንደ
ተቀበለች ለማሳመን ብትሞክርም ፣ ከመጀ
መሪያውም ጀምሮ የእንግሊዝ በፎክላንድ
ላይ ያላት የይገባኛል ጥያቄም ሆነ የግዛት
ይዞታ በአርጀንቲና ተቀባይነት አላገኘም ።

በኋላም ራሱ የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ እየ
ተዳከመ መጥቶ ሲፈራርስ ፣ የፎክላንድ(ማ
ልቪናስ) ደሴቶች የተረፉ የእንግሊዝ የቅኝ
አገዛዝ ቅሪቶች ሆነው እስካሁን ቆዩ ። አር
ጀንቲናም ደሴቶቹን በእንግሊዝ ከተነጠቀ
ችበት ጊዜ ጀምሮ እንዲመለሱላት መጉት
ጉቷን አላቋረጠችም ።

የተባበሩት መንግሥታትም የፎክላንድ
ደሴቶች ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ መው
ጣት እንዳለባቸው በማመን ውሳኔ ማስተላ
ለፉ ቀደም ሲል ተጠቅሷል ። በ1965 የተ
ባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የፎክ
ላንድ ደሴቶችን በሚመለከት በአርጀንቲ
ናና በእንግሊዝ መካከል የተነሳው ውዝግብ
በሰላማዊ መንገድ በስምምነት እንዲፈታ
ወሰነ ። በዚህም መሠረት ጉዳዩን በስምም
ነት ለመፍታት ለ15 ዓመታት ያሀል በሁለ
ቱ አገሮች መካከል ውይይት ሲካሔድ ቆየ።

በውይይቱ መድረክ በአንድ ወቅት በደ
ሴቶቹና በአካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሀብ
ት በጋራ ለመጠቀም እስከተቻለ ድረስ የእ
ንግሊዝ መንግሥት በመርህ ደረጃ የፎክላ
ንድ ደሴቶች የአርጀንቲና ግዛት መሆናቸው
ን እንደሚያውቅ ተስማምቶ ስምምነት ላይ
ተደርሶ ነበር ። ይሁንና በ1970ዎቹ አጋማ
ሽ ላይ አንድ ዋና መሥሪያ ቤቱ አሜሪካ ው
ስጥ የሆነ የጅኦፊዚካል ምርምር አድራጊ
ኩባንያ ለእንግሊዝና ለአሜሪካ የዘይት ኩባ
ንያዎች ባደረገው ጥናት፣በደሴቶቹ አካባቢ
በዛ ያለ የዘይት ሀብት ክምችት እንዳለ በመ
ረጋገጡ፣ቀደም ሲል በመርህ ደረጃ ተደርሶ
በት የነበረው ስምምነት በእንግሊዝ ተጣሰ።

ፀሐይ አይጠልቅበትም ይባልለት የነበ
ረው ፣ በቅኝ ግዛቶች የተገነባው የእንግሊዝ
የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ቅኝ ግዛቶቹ ነፃ እየወ
ጡ፣የብዝበዛ መረቡ እየተበጣጠሰ የመጣ ቢ
ሆንም፣ አሁንም ቢሆን አንዳንድ የቀድሞ ቅ
ኝ ግዛቶቹን ሙጥኝ ብሎ በመያዝ ፣ ከታሪክ
ሂደት ጋር በመጋፋት ላይ ይገኛል ። ቀድሞ
ውንም ቢሆን የእንግሊዝ ካፒታሊዝም በዓ
ለም ላይ የበላይነትን ሊቀዳጅ የቻለው በቅ
ኝ ግዛቶቹ ብዝበዛ አማካይነት እንደነበረ
ይታወሳል።አሁንም ቢሆን የእንግሊዝ ኢም
ፔሪያሊዝም የያዛቸውን የተረፉ ቅኝ ግዛ
ቶች ለመልቀቅ የማይፈልገበት ምክንያት
አንዳንዶቹ የተፈጥሮ ሀብት አላቸው ተብሎ
ስለሚገመት (የፎክላንድ ደሴቶች) ይሆንኑ
የተፈጥሮ ሀብት በተለመደው መንገድ ለመ
በዝበዝ ሲሆን፣ ሌሎችን ደግሞ ባላቸው እስ
ትራተጂያዊ አቀማመጥ እንደር ለአሜሪካ

Digitized by Google

ኢምፔሪያሊዝም አሳልፎ በመስጠት ወታደራዊ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ማድረግ ነው። ለዚህም ዲያጐ ገራሲያን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ።

የፎክላንድ (ማልቪናስ) ደሴቶችን ጥያቄ ባጭሩም ቢሆን ለመዳሰስ እንደተሞከረው ፣ በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኩል የታሪክ ሂደት ያለፈበትን ቅኝ አገዛዝ ለማቆየትና የቀድሞ ገናናነቱን ለማስመለስ የሚደረግ ጥረት ሲሆን ፣ በአርጀንቲና በኩል ደግሞ ግዛቷን ለማስመለስ የሚደረግ ትግል ነው። ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ በፎክላንድ (ማልቪናስ) ውዝግብ ላይ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም እንግሊዝን በመደገፍ የወሰደው አቋም ምንን ያመለክታል ?

ቀደም ሲል በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አሜሪካ ፣ ከስፔን ቅኝ አገዛዝ መዳከም በኋላ ሌሎች የአውሮፓ ካፒታሊስት አገሮች በደቡብ አሜሪካ ውስጥ በስፔን እግር እንዳይተኩ «አሜሪካ ለአሜሪካኖች» የሚል መሠረተ ሐሳብ ያዘለው የሞንሮ ዶክትሪን መውጣቱ ይታወሳል ። ይህ ዶክትሪን «የአሜሪካ አህጉሮች ባገኙትና በሚጠብቁት ነፃ ሁኔታ ፣ ከእንግዲህ ወደፊት የማንም የአውሮፓ ኃይል ቅኝ ተገዥ አይሆኑም» የሚል ቢሆንም ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ዶክትሪን በመጠቀም ፣ የደቡብ አሜሪካ አገሮችን «የጓሮ አትክልት ቦታ»በማድረግ ሲበዘብዛቸው ቆየ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በ1948 የሞንሮ ዶክትሪን ውልድ የሆነው የአሜሪካውያን አገሮች ድርጅት (Organization of America States) ተመሠረተ ። ይህ ድርጅት ዓላማው በአሜሪካ አገሮች መካከል የሚነሳውን አለመግባባት በሰላም ለመፍታት ፣ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ የባህልና የማኅበራዊ ግንኙነትን ለማዳበር ወዘተ . . የሚል ነው ። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ድርጅት አማካይነት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከደቡብ አሜሪካ አገሮች ጋር የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የወታደራዊ የጋራ ተራድኦ ውል እንዳለው የታወቀ ነው ።

በዚህ ውል መሠረት በአሁኑ ወቅት በአርጀንቲናና በእንግሊዝ መካከል በተነሳው ጦርነት የአሜሪካ መንግሥት አርጀንቲናን መርዳት ሲገባው ፣ ለእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ወታደራዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ ነው። «አሜሪካ ለአሜሪካኖች» ሲል ቀደም ሲል እራሱ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ያወጣውን መመሪያ በመዘንጋት በአሴንሽን ደሴት ላይ ያለውን የአየር ኃይል ጦር ሠፈር ለእንግሊዝ የባሕር ግብረ ኃይል ግልጋሎት እንዲውል ከማድረጉም በላይ ፣ በሰላይ ሳተላይቶቹ የአርጀንቲናን ወታደራዊ እንቅስቃሴ በመከታተል ወታደራዊ መረጃ ለእንግሊዝ በማቀበል ላይ መሆኑን ኤ. ቢ. ሲ. የተባለው የአሜሪካ የቴሌቢዥን ማሰራጫ ጣቢያ ሳይቀር አስታውቋል ። *

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሲጀመርም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የአሜሪካውያን አገሮችን ድርጅት (O.A.S.) «ኰምኒዝምን ከደቡብ አሜሪካ ለመገደብ» ባለው ዓላማ እንደፈለገ ሊጠቀምበት በበላይነት ያቋቋመው ድርጅት እንደሆነ ነው ። አሁንም ቢሆን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይህን ድርጅት በዚሁ መንፈስ ሊገለገልበት እየከጀለ ከመሆኑም በላይ አሁን በአርጀንቲናና በእንግሊዝ መካከል በተፈጠረው ግጭት ስምምነቱን ባለማክበሩ የተነሳ ፣ የቀሩት የላቲን አሜሪካ መንግሥታት ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያላቸውን የወዳጅነት ስምምነቶችን ሁሉ እንደገና መመርመር የሚገባቸው ወቅት ነው ።

ሌላ በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር አለ ። ይኸውም የአሜሪካን ኢምፔሪያ

---

* New Times, April 1982, No. 16, p. 8.

Digitized by Google

ሊዝም ሁሉንም የዓለም ክፍል የሱ የጥቅም ክልል ብሎ መሰየሙ የተለመደ ቢሆንም ፡ የፎክላንድ ውዝግብን በሚመለከት ግን የሚገርመው ነገር አስታራቂ መስሎ በመግባት አሜሪካ ደሴቶችን ለራሱ መከጀሉ ነው ። በቅርቡ ከዋሽንግተን የወጣ አንድ ጋዜጣዊ መግለጫ*አርጀንቲናና እንግሊዝ ስምምነት ላይ ካልደረሱ በደሴቶቹ ላይ በ«ዓለም አቀፍ የሰላም ኃይል» ሽፋን ፡ በመካከለኛው ምሥራቅ በሲና በረሀ እንዳደረገው ፡ የራሱን የፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር ማስፈር ሌላ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል ሐሳብ ሠንዝሯል። ይህ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አቋም በሚገባ ሲመረመር ግን ይህን ያህል ላያስገርም ይችላል ። ምክንያቱም በፎክላንድ (ማልቪናስ) ደሴቶች አካባቢ ምን ያህል የዘይት ሀብት ክምችት እንዳለ የሚያመለክተው ተጨባጭ መረጃ የገባው የእንግሊዝ የዘይት ኩባንያ በሆነው በብሪትሽ ፔትሮልየም እጅ ብቻ ሳይሆን ፡ በትላልቆቹ የአሜሪካ የዘይት ኩባንያዎች በነኤክሶን፣ ገልፍና ቴክሳኮም እጅ ውስጥ በመሆኑ ነው ።



* Taken from New Times, April 1982, No. 17, p. 1.

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 071 108 935

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google